የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች

የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ

የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት

ዓመታዊ ሪፖርት

ጥራዝ 1

ግንቦት/2009

አዲስ አበባ

ማውጫ

ገጽ

1. መግቢያ 1

2. አዲት በተደረጉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች የተጠቃለለ ሪፖርት /Summery Report/ 4

3. የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች በዘርፍ የተጠቃለለ አዲት ሪፖርት

3.1 የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን 44

3.2 የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች 109

3.3 የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች 132

3.4 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መ/ቤቶች 186

3.5 የልማትና ማህበራዊ አገልግሎት መ/ቤቶች 249

3.6 የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች 318

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የ2008 በጀት ዓመት

ሂሳብ የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት

I. መግቢያ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በኢፌዲሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 101 መሠረት በአዋጅ ቁጥር 982/2008 የሚከተሉት ዓላማዎችን ይዞ እንደገና እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

- የፌዴራል መንግሥት እቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፣
- የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በወጡት ህጎችና ደንቦች መሠረት መሰብሰቡን መጠበቁን እና በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋሉን ማረጋገጥ እና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤት ሪፖርት ማቅረብ፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች እና ድርጅቶች ላይ የፋይናንስ፣ የክዋኔ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ፣ የቁጥጥር ኦዲቶች፣ ልዩ ኦዲቶችና ሌሎች ኦዲቶችን ማካሄድ፣
- አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሳብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
- በሂሳብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሰማሩት የክልልና የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ሙያዊ ዕገዛና ምክር መስጠት፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች ሂሳብ የሚመረመርበት የኦዲት ደረጃ (ስታንዳርድ) ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

ናቸው፡፡

ከላይ የተገለጹትን ዓላማዎች ለማስፈጸም እንዲያስችል የተሰጡት ስልጣንና ተግባራት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችንና ድርጅቶችን ሂሳብ አዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- የፌዴራል መንግሥት መስሪያ መ/ቤቶችና ድርጅቶችን የእንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስርዓት አጠቃቀምና አስተዳደር አዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፣
- የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑን፤ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ አዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
- የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን አዲት ያደርጋል ፤ ያስደርጋል፣
- በፌዴራል መንግሥቱ መ/ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን እንዲሁም ብድርን አዲት ያደርጋል ፤ ያስደርጋል፣
- በዚህ መሰረት ያከናከነውን የአዲት ውጤት እንደነገሩ ሁኔታ ለመ/ቤቱ ወይም ለድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፡፡ የፌዴራል ዋና አዲተሩ ውጤት ወንጀል መፈጸሙን የሚያሳይ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ ያሳውቃል፡፡

ይህንኑ ስልጣን መሰረት በማድረግ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን አዲት ለማከናወን ለፋይናንስና የሀጋዊነት አዲት በእንጌጅሜነት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በ6 የአዲት ዳይሬክቶሬቶች፡- የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች፤የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች፤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፤ የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች፤ የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች እና የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች እና በ2 የክዋኔ አዲት ዳይሬክቶሬቶች፤ እንዲሁም በክልል መንግስታት የተከናወነው የመሰረታዊ አገልገሎቶች ከለላ ድጋፍ (PBS) ተከታታይ አዲት ለማከናወን በ1 የድጋፍና ድጎማ አዲት ዳይሬክቶሬት በመደራጀት የአዲቱ ስራ ተከናውኗል፡፡

አዲቱ የተካሄደው በአብዛኛው የተለመደውን የአልፎ አልፎ ወይም የናሙና አዲት ስልት በመከተል፣ እንዲሁም እንደ አዲቱ አስፈላጊነት የስጋት ደረጃ እና ብዛት ሁኔታ እየታየ በዝርዝር አዲት በማድረግ ነው።

ለአዲቱ መሠረት የሆኑት በዓለም አቀፍ የአዲት ደረጃዎች እና አዲት ተደራጊ የመንግሥት መ/ቤቶች ያቀረቧቸው የሂሳብ መዛግብት እና ሰነዶች እንዲሁም የሂሳብ መግለጫዎችና ማብራሪያዎች ናቸው።

በሪፖርት ውስጥ የተሰጡ አስተያየቶችና የመደምደሚያ ሃሳቦች፣ አዲት የተደረጉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶችን፣ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት በመገምገም ስጋትን ያማከለ አዲት በማድረግ የተገኘውን ውጤት መሠረት በማድረግ ነው።

በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የተከናወነው የአዲት ሥራ እንዳለቀ ከሚመለከታቸው የአዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ኃላፊዎች በአዲት ግኝቶች ላይ የመውጫ ውይይት (Exit Conference) ከመደረጉ ሌላ የአዲት ሪፖርቱ ለእያንዳንዱ አዲት ተደራጊ የፌዴራል መ/ቤትና ተቆጣጣሪ መ/ቤት እየተላከ፣ በአዋጅ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ለሥራ አመራር ሪፖርት መልስ የሰጡትን አዲት ተደራጊ መ/ቤቶችና ድርጅቶችን ምላሽና አስተያየት ያገናዘበ ነው።

መ/ቤታችን በሚከተለው የአዲት ጊዜ አቆጣጠር ከየካቲት 1/2008 እስከ ጥር 30/2009 ዓ.ም (በጊዜያዊነት የተስተካከለ) የ158 የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የፋይናንስና ሕጋዊነት አዲት፣ በመከናወን የአዲት ሪፖርቶቹ፣ አዲት ለተደረጉት መ/ቤቶችና ለሚመለከታቸው አካላት የተላኩ ሲሆን፣ በዚህ ጥራዝ የተጠቃለለ የፋይናንስና ሕጋዊነት አዲት ዋና ዋና ግኝቶች ቀርቧል።

II. <u>አዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና ግኝቶች</u>

አዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተገኙት የጥሬ ገንዘብና ሌሎች የአሰራርና የአፈፃፀም ጉድለቶች በርካታ ሲሆኑ፣ እነዚህ ጉድለቶች በዚሁ ጥራዝ ከገጽ 39 ጀምሮ በየአዲት ተልዕኮ ቡድኖች ስር በተደራጁ የአዲት ተደራጊ መ/ቤቶች አንጻር የታዩት ዋና ዋና ግኝቶችና የተሰጡት ማሻሻያ ሀሳቦች ተጠቃለው ከዚህ በታች ቀርቧል።

1. <u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ ኦዲት</u>

1.1 <u>የጥሬ ገንዘብ ጉድለት</u>

ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ሥርዓት በፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 እና በፌደራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በአዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 144,716.56 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ተገኝቷል።/ዝርዝሩ በአባሪ- 3 ተመልክቷል/

በተጨማሪም በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገውና በቆጠራ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ መካከል የሚታይ ልዩነት በ2 መ/ቤቶች ቆጠራው በብር 2,445,827.16 በመብለጥ የሚታይ ሲሆን፣ በ5 መ/ቤቶች ብር 379,390,668.85 በማነስ የሚታይ መሆኑ ታውቋል። /ዝርዝሩ አባሪ-3/1 ተመልክቷል/

በጉድለት የታየው የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ እንዲተካና የታየው ልዩነትም ተጣርቶ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ክትትል መደረግ እንዳለበት ለየመ/ቤቶቹ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል።

1.2 <u>የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመት የታባቸው መ/ቤቶች</u>

የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ባዘጋጀው የሂሣብ አያያዝ መመሪያ መሠረት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተደረገ መሆኑን፣ የቆጠራውም ውጤት ከመዝገብ (ሌጀር) እና በሂሣብ ማመዘኛው ሪፖርት ላይ ከተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ጋር የሚመሳከር መሆኑንና በባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በተለያዩ መ/ቤቶችና ተጠሪ የሆኑ ቅ/ጽ/ቤቶች በርካታ የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች እንዳሉ ተረጋግጧል። /የመ/ቤቶቹ ዝርዝር አባሪ-4/ሀ-ሰ ተመልክቷል።/

ከሚታዩት ዋና ዋና የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች፣

- በሳጥን ወይም በገንዘብ ያዥ እጅ መያዝ ከሚገባው በላይ በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ወቅት የተገኘ በ3 መ/ቤቶች ብር 913,704.66፣

- የሰበሰቡትን ጥሬ ገንዘብ በወቅቱ ባንክ ወይም ለዋና ገ/ያዥ ያላስገቡ በ4 መ/ቤቶች ብር 2,558,981.76 መገኘቱ፣
- በ8 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 18,892,132.52 በክፍያ መመሪያ ከተወሰነው የገንዘብ መጠን በላይ በጥሬ ገንዘብ ወይም በቼክ ወጪ የተደረገ ሂሳብ የተገኘባቸው፣
- ለተለያዩ ድርጅቶች በባንክ በኩል ክፍያ ለተፈጸመው የባንክ አድቫይስ/ ማስረጃ ከክፍያ ሰነዱ ጋር ሳይያያዝ የተገኘ በ2 መ/ቤቶች ብር 80,073,363.23፣
- የተጣራ ሀብት መደበኛ ያልሆነ ሚዛን የሚያሳይ /ዴቢት/ በ2 መ/ቤቶችና በ4 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 69,939,618.96 መገኘቱና በ1 መ/ቤት ብር 665,031.96 በማነስ የሚያሳይ መሆኑ፣

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሳቦች ላይም ተገቢ ቁጥጥር አለማድረግ ለገንዘብ ጉድለትና ምዝበራ የሚያጋልጥ በመሆኑ፣ የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሣብ ላይ በየወቅቱ ቁጥጥር በማድረግ በመመሪያው መሰረት እንዲተገበር፣ በኦዲት የተገኘው የጥሬ ገንዘብ ጉድለት እንዲተካ፣ በሂሣብ መግለጫ ሪፖርት ላይ የተመለከተው የጥሬ ገንዘብ ሂሣብ ከቆጠራው ጋር በየወቅቱ ሊመሣዘንና ትክክለኛነቱ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል።

2 <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

2.1 <u>በደንቡ መሰረት በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች</u>

ስለመንግሥት ሂሳብ አያያዝ የወጣው ደንብ የደመወዝ ሰነድ ሂሳብ የወሩ ደመወዝ በሚከፈልበት ጊዜ፣ የሥራ ማስኬጃ የሚመለከተው ደግሞ በተለይ የግዢ ሰነድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ እንዲጠናቀቅ ያዛል። ይሁን እንጂ ኦዲት ከተደረጉት መ/ቤቶች ውስጥ በ113 መ/ቤቶች እና በ23 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 5,262,272,848.29 የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሠረት ሳይወራረድ ተገኝቷል። /በዝርዝሩ በአባሪ-6 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ብር	119,432,359.04
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	2,917,783,011.16
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	684,135,065.76
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	1,084,093,170.28
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	224,833,495.66
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	231,995,746.39
ጠ/ድምር	ብር	5,262,272,848.29

ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን፣ የተሰብሳቢ ሂሳቡ ዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን፤ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 134,153,964.72 ፤ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 3,174,764,464.42 ፤ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 372,936,870.76 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 196,565,227.12 ሲሆን፤ ቀሪው ሂሳብ ብር 1,442,462,508.41 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ለመለየት ያልተቻለና ከዚሁ ሂሳብ ውስጥ ብር 375,557,284.38 ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተሰብሳቢ ሂሳብ መሆኑ ታውቆል፡፡

ከውዝፍ ተሰብሳቡ ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ ያዙት የብሔራዊ አደጋ ስጋትና ስራ አመራር ኮሚሽን ብር 2,388,942,192.66፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 720,056,723.48፤ የአ.አ.ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ብር 461,024,828.37፤ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 352,267,320.48፤ የሀገር መከለከያ ሚኒስቴር ብር 172,017,623.31፤ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ብር 122,357,333.28፤ በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴርና በሥሩ ባሉት 7 ተጠሪ ተቋማት ብር 120,806,110.43፤ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ብር 119,048,306.24፤ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ብር 108,320,687.31፤ የትምህርት ሚኒስቴር ብር 82,078,962.89፤ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር እና ሶስት ተጠሪ ተቋማት ብር 57,915,537.72 እና ሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 55,650,002.47 ይገኙበታል፡፡

ይህ የተሰብሳቢ ሂሳብ በደንቡ መሰረት ሳይወራረድ ከዓመት ወደ ዓመት እየተንከባለለ በሂሳብ መግለጫው ላይ የሚታይ ሲሆን፤ በተወሰኑ መ/ቤቶች መሻሻል የሚታይ ቢሆንም የአንዳንዶቹ እየጨመረ የሄደና በአብዛኛው ቀደም ባሉት አዲት ወቅትም ሂሳቡ እንዲወራረድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም፤ ሂሳቡ እንዲወራረድ ያልተደረጉ ናቸው፡፡

በመሆኑም ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳቢን በወቅቱ አለመወራረድ ለመንግሥት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፣ ለረጅም ዓመታት ሳይሰበሰቡ የተገኙት ሂሣቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ፤ ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግሥት መመሪያ መሠረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

2.2 <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ የአሠራር ችግሮች</u>

- ለተሰብሳቢ ሂሳብ ሌጀር ያልተዘገጀ በዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 654,583.29 መገኘቱ ፣
- ከተለመደው የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን የተለየ ክሬዲት ባላንስ (Abnormal balance) የሚታይባቸው በ7 መ/ቤቶች ብር 28,905,615.31 መሆኑ፣
- በወጪ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባው አላግባብ በተሰብሳቢ ሂሳብ የተያዘ በፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ ብር 438,902.91 መገኘቱ፣
- በሁለት መ/ቤቶች ያለአግባብ ከተሰብሳቢ ሂሳብ የተሰረዘ ብር 11,155,949.90 መኖሩ፤

ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ዝርዝራቸው በአባሪ-7 ሀ እስከ መ ተመልክቷል።

በመሆኑም ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት በወቅቱ እንዲወራረዱ /እንዲሰበሰቡ፤ ማስረጃ ያልቀረበላቸውም ሂሳቡ ማስረጃ እንዲቀርብለቸውና ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ ተሰብሳቢ ሂሳቦችም ተጣርተው አስፈላጊው ማስተካከያ እንዲደራግላቸው፤ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ለየመሥሪያ ቤቶቹ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3 የገቢ ሂሳብ

3.1 በገቢ ግብር፤ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ ለመሰብሰብ በሚደነግጉ አዋጆች ደንብና መመሪያዎች መሰረት ሳይሰበሰብ ተገኘ ሂሳብ

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ እንዲሁም በሌሎች ገቢ መሰብሰብን በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት የመንግሥትን ገቢ የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት እና በስሩ ባሉ አስራ አምስት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 1,137,991,342.68፤በሌሎች በ30 መ/ቤቶች ብር 5,920,743.20 በድምሩ ብር 1,143,912,085.88 የገቢ ግብር፣ ቀረጥና ታክስ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ/VAT/፤ ቅድመ ግብር (withholding tax)፤ የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ፤ እና በሌሎች ገቢ መሰብሰብ በሚፈቅዱ አዋጆች መሠረት ያልተሰበሰበ እና በሌሎች 19 መ/ቤቶች ከህንጻ ስራ ተቋራጮችና ዕቃ አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው ያልተሰበሰበ ቅጣት ሂሳብ ብር 226,318,955.97 ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም በተፈራመው የውል ስምምነት መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢና ቅጣት በሶስት መ/ቤቶች ብር 6,157,838.84 እና በሁለት መ/ቤቶች የገንዘብ መጠኑ ያልተገለጸ ገቢ በውሉ መሰረት ያልተሰበሰበ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ- 9 እና 9/1 እና 9/2 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	ብር	137, 991,342.68
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	136,813.59
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	225,013.49
የከፍተኛ ትምህርት ት	"	299,910.67
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	2,923,765.19
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	2,335,240.26
ጠ/ድምር	ብር	1,143,912,085.88

በአዋጁ ደንብና መመሪያው መሠረት ገቢ ካልሰበሰቡት መ/ቤቶች፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን፡- የአዲስ አበባ ቃሊቲ ቅ/ፅ/ቤት ብር 725,157,433.77፣ በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 239,105,787.51 ፣ የምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 55,660,066.90 ፣ አዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት ብር 42,602,011.26 ፣ በኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 20,474,305.24፤ የጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 19,595,253.19 ሲሆን፤ ከሌሎች መ/ቤቶች ደግሞ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ብር 2,334,379.40 እና ከኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ብር 1,512,791.25 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የገቢ ሂሳቡ ሳይሰበሰብ የቀረበት ምክንያት ሲጣራ፣ ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ ላይ ያሳወቁት ሽያጭ በትርፍና ኪሳራ የሂሳብ መግለጫ ላይ ከተመለከተው ሽያጭ ጋር ሲነጻጸር በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የተመለከተው የሚያንስ በመሆኑ ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ፤ ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር Harmonized System Code (H.S.Code) እና Custom Procedure Code (CPC Code) ባለመመደባቸው ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ የመነሻ ዋጋ ለተወሰነላቸው ዕቃዎች በመነሻ ዋጋው መሰረት ያልተስተናገዱ ድርጅቶች መገኘታቸው፣ በትክክለኛው የትራንስፖርት የመጫኛ፣ ማራገፊና ኢንሹራንስና ሌሎች ወጪዎች ለቀረጥ ማስከፈያነት ባለመወሰዱ ምክንያት ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣ በማነፃፀሪያ ዋጋ መሰረት ቀረጥና ታክስ ባለመሰራቱ፣ በንግድ ትርፍ ስሌት ወቅት መቀነስ የሌለባቸው ወጪዎች በመቀነሳቸው ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር፣ በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ በገቡ እቃዎች ላይ በህግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ ያለፈበት ቢሆንም በዋስትና የተያዘው ገንዘብ ለመንግስት ገቢ ያልተደረገ በመሆኑ እና መ/ቤቶች ከሚፈጽሙት ግዢ ላይ ቀንሰው ማስቀረት የሚገባቸው ግብር (Withholding tax)፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ሥራ ግብር ሳይቀንሱ በመቅረታቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች ለወደፊቱ የመንግሥት ገቢ ህግና ደንብ በሚፈቅደው መሠረት መሰብሰብ እንዳለባቸው፣ በተለያዩ ምክንያቶች ያልተሰበሰበውም ገቢ እንዲሰበሰብ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.2 <u>ያልተሰበሰበ ውዝፍ የገቢ ሂሣብ</u>

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶችና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በወጣው ሕግና ደንብ መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፤ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በስር ባሉት ዘጠኝ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች እና በሌሎች 5 መ/ቤቶች ከውዝፍ ግብር፤ ወለድ እና ቅጣት መሰብሰብ የሚገባው በድምሩ ብር 4,009,579,782.80 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ እና በግብር ከፋዮች ለቀረበው ቅሬታ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ ባለመሰጠቱ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤትና በ2 ቅ/ጽ/ቤቶች ያልተሰበሰበ ግብር፤ቀረጥና ታክስ በድምሩ ብር 3,534,374,123.04 በወቅቱ ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 8 እና 8/1 ተመልክቷል/

በተጨማሪም ከሰጡት አገልግሎት ሽያጭ ላይ ውዝፍ ሂሳብ /የዱቤ ሽያጭ ከነወለዱ/ በ4 መ/ቤቶች ብር 758,441,552.94 በወቅቱ /በአባሪ- 8/2/ ያልተሰበሰበ መሆኑ በአዲቱ ተረጋግጧል።

ውዝፍ ገቢ በወቅቱ ካልሰበሰቡ መ/ቤቶች መካከል በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን፣ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 3,568,784,786.96፤ የምራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 221,873,831.48፤የድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ብር 82,614,496.40 ፤የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ብር 53,030,155.76፣ በምስራቅ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 49,103,485.09 እና ባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት ብር 36,468,864.32 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ የዱቤ ሽያጭ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዋና መ/ቤት ብር 621,050,644.38 (ከተወረሱ የኮንትሮባንድ ዕቃዎች ሽያጭ እስከ 8 ዓመታት የቆየ) ይገኝበታል፡፡ የዱቤ ሽያጭን በወቅቱ አለመሰብሰብ፣ ውዝፍ የቤት ኪራይን በወቅቱ አለመሰብሰብ፣ ውሳኔ ወጥቶላቸው በቅሬታ ሰሚ እጅ ያሉ እንዲሁም ቅሬታ ያልቀረበበት እና ቅሬታ ሰሚ ውሳኔ ሰጥቶባቸው ለበርካታ ዓመታት ያልተሰበሰበ ውዝፍ ግብር፤148 በድርጅቶች/ተግልጋዮች/ በመመሪያው መሰረት ቅሬታቸው በወቅቱ ባለመታየቱ ወይም ውሳኔ ባለመሰጠቱ ከ14/01/2007 እስከ 26/04/2009 የቆየ መሆኑ እና በመሳሰሉት የገቢ አሰባሰብ ችግሮች የተነሳ ሳይሰበሰብ የቆየ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል ፡፡

በመሆኑም የሚሰበሰበው ገቢ መንግስት ለሚያከናውናቸው የኢኮኖሚ ልማት፣ ማህበራዊ አገልግሎቶች መስፋፋትና መሠረተ ልማት ዝርጋታ ፕሮጀክቶች ፣ እንዲሁም ለሀገሪቱ የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ መሳካት ወሳኝ ሚና የሚኖረው በመሆኑ፤ ለገቢ አሰባሰቡ ትኩረት ተሰጥቶ የመንግሥት ህግና ደንብ ተከብሮ እንዲሠራ፣ ያልተሰበሰበውም ውዝፍ ገቢ እንዲሰበሰብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.3 <u>ማስረጃ ባለመሟላቱ ምክንያት የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ</u>

የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፣ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን አምስት ቅ/ጽ/ቤቶች እና በ8 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 36,807,405.88 እና በሌሎች 6 መ/ቤቶች በግንዘብ መጠን ያልተገለጸ ማስረጃዎች ባለመሟላታቸው የገቢ ሂሳቡን ትክክለኛነት በአዲት ማረጋገጥ አልተቻለም። /ዝርዝራቸው በአባሪ-10 ተመልክቷል/

ዋና ዋና ምክንያቶቹም የተሰበሰበባቸው 170 ዲክላራሲዮኖች ለአዲት ተጠይቀው ያልቀረቡ በመሆኑ፤በነዚህ ዲክላራሲዮኖች የተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ፤ አግባብ ባለው አካል የጸደቀ የገቢ ታሪፍ/የማስከፈያ ተመን/ ባለመኖሩ ፣ የግብር ማሣወቂያ በፋይሉ ውስጥ ተያይዞ ባለመገኘቱ ምክንያት፣ መግቢያ ደረሰኝ (ማንኛውም እቃ ሲመጣ የሚመዘገብበት) ገቢው ከምን አይነት አገልግሎት እንደተሰበሰበ በአብዛኛው የሚገልጽ ደጋፊ ማስረጃ ከገቢ ደረሰኞቹ ጋር ያልተያያዘ በመሆኑ፤የውስጥ ገቢ ሂሳብ ምዝገባ ባለመካሄዱ እና የውስጥ ገቢ የፋይናንስ እንቅስቃሴን የሚገልጹ አግባብነት ያላቸው የሂሳብ ሪፖርቶች እና መግለጫዎች ባለመዘጋጀታቸው፤ ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የገቢ ማስረጃዎች ባለመቅረባቸው፤ የተሰበሰበውን ገቢ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሳይቻል ቀርቷል፡፡

በሌላም በኩል ዓመታዊ የንግድ ትርፍ ግብር ያለሳወቁ 119 ግብር ከፋዮች ፤የተጨማሪ እሴት ታክስ ያላሳወቁ 27 ግብር ከፋዮች እና ኤክሳይስ ታክስና ተርኦቨር ታክስ ያለሳወቁ 11 ግብር ከፋዮች የተገኙ ሲሆን፤ የሚፈለግባቸው ግብር ምን ያህል እንደሆነም ፤ ስለመክፈላቸው/ስለመሰብሰቡ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስለሆነም ማንኛውም ገቢ ማስረጃ ሳይሟላ በገቢ መመዝገቡ ተገቢ ስላልሆነ፣ የገቢ ማስረጃዎች በትክክል ተደራጅተው እንዲያዙና ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.4 <u>የውስጥ ገቢን ሂሳብ በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ያላካተቱ መ/ቤቶች</u>

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዝግቦና በሂሣብ ሪፖርታቸው ተካቶ ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ11 መ/ቤቶች ብር 196,400,089.47 እና በሌሎች ሁለት መ/ቤቶች በግንዘብ መጠን ያልተገለጸ የሰበሰቡትን የውስጥ ገቢ ባቀረቡት ዓመታዊ የገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝራቸው በአባሪ-11 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	167,457,520.57
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	2,187,238.27
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	14,563,698.31
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	12,191,632.32
በድምር	ብር	196,400,089.47

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የገቢ ሂሳብ በሪፖርት ከማያካትቱ መ/ቤቶች አብዛኞቹ የትምህርት ተቋማት ሲሆኑ፤ ይህ አሰራር በመ/ቤቶች የሚዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ትክክለኛውን የገቢ ሂሳብ እንቅስቃሴ የማያሳይና የመንግስት አጠቃላይ ገቢ ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያሳይ የሚያደርግ ሲሆን፣ ለገቢ ሂሳብ ደረሰኝ አለማዘጋጀት በሂሳቡ ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር በማላላት ገንዘብ እንዲጣፋ ወይም እንዲጎድል መንገድ ይከፍታል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የሚሰበስቧቸውን የገቢ ሂሳብ በሂሳብ መግለጫዎችም በማካተት ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ሪፖርት ሊያደርጉ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.5 <u>የተሰበሰበውን ገቢ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ፈሰስ ያላደረጉ መ/ቤቶች</u>

በመንግሥት ስም የተሰበሰበ ማናቸውም ዓይነት የቀጥታ ገቢ ሂሳብ ወይም ከልዩ ልዩ አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢ በሕግ በተለየ ሁኔታ እንዲሰራበት የተፈቀደ ካልሆነ በስተቀር በበጀት ዓመቱ ውስጥ በየጊዜው ለማዕከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ በፈሰስ /ለሚመለከተው አካል ገቢ የሚደረግ መሆኑም ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ5 መ/ቤቶች ብር 8,250,112.36 ከተለያዩ ገቢዎችና ከሌሎች ተከፋይ ሂሳቦች ላይ ተቀንሶ የቀረውን ሂሳብ ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ወይም ለሚመለከተው አካል ገቢ /ፈሰስ ያልተደረገ ሂሳብ ተገኝቷል። /ዝርዝሩ በአባሪ- 12 ተመልክቷል/

በመሆኑም ገቢ ያልተደረገው ሂሳብ ለሚመለከተው አካል ገቢ/ ፈሰስ መሆን እንዳለበት፤ ለወደፊቱም በሚሰበሰቡት ሂሳቦች ዙሪያ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።።

3.6 <u>በገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች የታዩ ልዩ ልዩ የገቢ አሰባሰብና የአሠራር ድክመቶች</u>

የገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በአዋጅ በተሰጣቸው ስልጣን መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰባቸውንና ተገቢ የሆኑ የቁጥጥር ስርዓት የዘረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የታዩት ዋና ዋና ድክመቶች ቀጥለው ቀርበዋል።።

3.6.1 በገቢዎችና ጉምሩክ ባላስልጣንና ቅ/ጽ/ቤቶች

- በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 መሰረት የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አፈጻጸም ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 118/2008 አንቀጽ 15(1-5) እንዲሁም በብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 591/2008 ክፍል 5 ቁጥር18(2) መሰረት ማንኛውም መንገደኛ ወደ ሀገር ሲገባ የያዘው የውጭ ምንዛሪ የኢትዮጲያ ብሄራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ከተፈቀደው መጠን በላይ ከሆነ ባለስልጣኑ ባዘጋጀው ዲክላራሲዮን ላይ መመዝገብ እንደሚኖርበት እና ተመልሶ ለመውጣት ሲፈልግ ገንዘቡን ያስመዘገበበት ዲክለራሲሆን ካላቀረበ በስተቀር መልሶ ለማውጣት እንደማይችል ይገልጻል።። ይህንኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት፡-

- **በውጭ ዜጎች ባለቤትነት በቀን 22/05/2008 ሊወጣ ሲል በፍተሻ የውጭ ምንዛሬ በዩሮ 211,220.00 እና በዶላር 1,700.0 በወቅቱ ባለው የሀገር ውስጥ ምንዛሬ ሲመነዘር ብር 4,876,186.20 እና 4.336 ኪ.ግ ወርቅ የግለሰቦቹ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሳይኖር እና የገንዘቡ ህጋዊነት በአግባቡ ሳይረጋገጥ ለግለሰቦቹ እንዲመለስ የተደረገ መሆኑን፣**

- **በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀፅ 30 ንዑስ አንቀፅ 2ሀ እና አዋጁን ለማስፈፀም በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀፅ 13 ላይ የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ስለመሆን በሚለው ከንዑስ አንቀፅ 1-4 ድረስ በተዘረዘሩት መሰረት የኢንቨስትመንት የቀረጥ ነፃ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አሰራር ላይ ክትትል እየተደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-**

በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

- **እያንዳንዱ አስመጪ ድርጅት ከቀረጥ ነፃ ዕቃዎችን በሚያስገባበት ወቅት የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ የተጠቀሱትን ዕቃዎች ከቀረጥ ነፃ ለኢንቨስትመንት እንዲገቡ ደብዳቤውን በቀጥታ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የሚጽፍ በመሆኑ እና በዋና መ/ቤት የሚገኘው የኢንቨስትመንት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት አውቆት ክትትል የማይደረግበት መሆኑ፣**
- **አስመጪ ድርጅቶች ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ሲጀምሩ በሚያስገቡበት የጉምሩክ ጣቢያ ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሊያስገባ የተፈቀደለትን የዕቃዎችን ብዛትና ዓይነት ለማወቅ የሚያስችል አሰራር የሌለ መሆኑ፣**
- **ከአንዳንድ የተሰረዙ የኢንቨስትመንት ፍቃዶች እና የህግ ማስከበር ሂደቶች ለመረዳት እንደተቻለው ባለሀብቱ ከቀረጥ ነፃ ያስገባውን ዕቃ ለታለመለት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ስራ በትክክል ስለማዋሉ፣ በስራ ላይ ስለመሆኑ፤መብቱን ያለአግባብ አለመገልገሉን፤ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ፍቃዱ ሲሰረዝ የሚፈለግበትን ቀረጥና ታክስ ለማስከፈል እንዲቻል እና ግዴታዎቹን ሳይወጣ ከሀገር እንዳይወጣ የቅርብ ጊዜ ትክክለኛ አድራሻ በመያዝ ቁጥጥሩን**

ሊያጠናክር የሚችል የተቀናጀ የባለድርሻ አካላት ትክክለኛና ወቅታዊ የሆነ መረጃ የመቀባበል ልምድ እና አሰራር የሌለ መሆኑን፤

- የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በሶስት ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 791,195.26 በተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ ላይ በብልጫ ተቀናሽ ወይም ተመላሽ ተብሎ የተያዘ ሂሳብ መገኘቱ፤
- በገቢ ግብር አዋጅ 286/94 አንቀጽ 66/1/ሀ/ እና በገቢ ግብር ለማስከፈል በወጣው ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ19/1 ና 2 መሰረት የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ቢኖርም ባይኖርም በየዓመቱ ለገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት የሂሳብ እንቅስቃሴውን መረጃ ማቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በአዋጁ እና በደንቡ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡ በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን 6 ቅ/ጽ/ቤቶች፡-
- በገቢ ግብር አዋጅ 286/2002 ክፍል 1 አንቀጽ 38 በተቀመጠው የግብር አስገቢው ስልጣንና ተግባር መሰረት በተከታታይ ኪሳራ የሚያሳውቁ ግብር ከፋዮች ላይ ስለሚደረገው ክትትል ለማጣራት በተሞከረበት ወቅት ፣ የደንበኞች አገልግሎት እንቅስቃሴ አላቸው ብሎ ከያዛቸው ግብር ከፋይ በናሙና ከተመረጡት መካከል፡-

በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ቅ/ጽ/ቤት

- ዶንዲ ኤምፔክስ ሰርቨስ የግብር መለያ ቁጥር /0000388195/ ከ2007 ዓመት ጀምሮ አራት (4) ዓመታት ወደኋላ ተሂዶ ሲታይ ኪሳራ ላይ መሆናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ያቀረቡ በመሆኑ እና የታክስ ህግ ተገዢነት እና የስጋት ቡድን የስራ ሂደት በኩል ስጋት አለባቸው ተብለው ከቀረቡት ዝርዝር ማስረጃ ውስጥ ያልተያዘ መሆኑ፤

የድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

- ጂሮው ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ.ማ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0015445634 ከ2003 እስከ 2007 በጀት ዓመት በንግድ ትርፍ ግብር ዜሮ እያሳወቀ መሆኑ እና በታክስ ህግ ተገዢነት እና የስጋት ቡድን በታክስ ኦዲት እንዲታይ የተመረጠ ቢሆንም ኦዲት ያልተደረገ መሆኑ፤
- መሀመድ አብዱላሂ አክሰዴ የንግድ ስራዎች ኃ.የተ.የግ.ማ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0004978176 ከ2001 እስከ 2007 በጀት ዓመት ድረስ ኪሳራ እያሳወቀ

በመሆኑ የስጋታቸውን ምንጭ በመጥቀስ የስራ ክፍሉ የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች አዲት ወይም ክትትል እንዲደረግባቸው አለመደረጉ ታውቋል፡፡

3.6.2 ሌሎች የገቢ አሰባሰብ ድክመቶች

ገቢ ሰብሳቢ መስሪያ ቤቶች ለሚሰበስቡት ገቢ በሚመለከተው አካል የጸደቀ የገቢ ተመን ያላቸው ለመሆኑና ገቢው በትክክል ለመሰብሰቡ ሲጣራ፣

በጅማ ዩኒቨርሲቲ፤

- በጅማ ሆስፒታል የመድሃኒት ሽያጭ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እና በ2008 በጀት ዓመት በአዲት ሳምፕል በታዩት ብቻ ለAPTS የብር 14,276,899.61 የመድሃኒት ግዥ ከመደበኛ በጀት የተገዛ ሲሆን ከመድሃኒቱ በመልሶ ሽያጭ የተገኘ ገቢ በበጀት ዓመቱ በቀረበ የሂሳብ ሌጀር መሠረት ብር 5,401,390.44 እንደሰበሰበ የተመለከተ ሲሆን ከዚህ የመድሃኒት መልሶ መሸጥ ገቢዎች የተገኘ ብር 28,977,861.37 ሲሆን መድሃኒቱ ከመደበኛ በጀት ግዥ የተፈፀመ በመሆኑ ሂሳቡ ለበጀት መተኪያ ተደርጎ መመለስ ሲገባው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከሆስፒታሉ የውስጥ ገቢ ሂሳብ አካውንት ገንዘቡ ብሎክ ተደርጎ እንዳይወሰድ ለሆስፒታሎች በተፈቀደ የማይዘጋ ሂሳብ አካውንት ቁጥር 1000166208819 ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተቀመጠ መሆኑ፤

በመዳወላቡ ዩኒቨርሲቲ፤

- ከተከታታይ ትምህርት (Extension, Weakened and Summer) እና ከድኅረ-ምረቃ ለሚሰበሰበው ገቢ ከእያንዳንዱ የገቢ ምንጭ የተሰበሰበውን የገንዘብ መጠን ለይቶ የሚያመለክት ተቀጽላ የሂሳብ ቋት (Subsidiary ledger) የሌለ መሆኑ፤
- ዩኒቨርስቲው የውስጥ ገቢ ማመንጫ የሥራ ክፍል በዳይሬክቶሬት ደረጃ ቢኖረውም ከተከታታይ ትምህርት፤ ከድኅረ-ምረቃ፤ ከእርሻ ምርት ሽያጭ፤ የተለያዩ አገልግሎት ከሚሰጡ ሱቆች ኪራይ፤ ከመዝናኛ ክበቦች እና ከሌሎች የተለያዩ ምንጮች የሚሰበሰቡ ገቢዎች በዝርዝር የሚያሳይ መከታተያ የሌለው መሆኑ፤
- በዩኒቨርሲቲው ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ሱቆች፤ መዝናኛ ክበቦች እና የጀበና ቡና አቅራቢዎች በአብዛኛው ውላቸው የተጠናቀቀ /ያልታደሰ/ መሆኑ፤

በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ፤

- **የክፍያ ትዕዛዙ በጥቅለ በክረምት መርሃ- ግብር የድህረ-ምረቃ ተማሪዎችን ያስተማሩበት በሚል ሂሳቡ ከመደበኛ በጀት የተከፈለው ብር 979,976.00 በክረምት የድህረ-ምረቃ ፕሮግራም በትምህርት ሚኒስቴር በኩል የሚላኩትን፣ በሌሎች የመንግስት መ/ቤቶችና በግላቸው ከፍለው የሚማሩ ተማሪዎች በግልጽ ተለይቶ የተያዘ ባለመሆኑ ከመደበኛ በጀት መከፈል የሌለበትን እና ከክረምት ድህረ-ምረቃ ከተሰበሰበው የውስጥ ገቢ መከፈል ያለበትን ሂሳብ ማጣራት ያልተቻለ መሆኑ፤**

በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ፤

- (GIZ) **ለፊጸማቸው የዕቃና አገልግሎት ግዢዎች ሂሳቡ ሲወራረድ በወጪ ሰነዶቹ ላይ የተመለከቱት የተጨማሪ እሴት ታክስ ሂሳቦች** (2%) **በራሱ ስም በታተመ የቅድመ ዊዝ ሆልዲንግ ደረሰኝ መሰብሰቡን ከማመልከቱ በቀር ለሚመለከተው አካል ገቢ ለመደረጉ ሂሳቡ ሲወራረድ ማስረጃ የማይቀርብ መሆኑ፤**
- **የገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት የገቢ ሂሳብ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ብር** 345,009.00 **መገኘቱ፣**
- **በ**6 **መ/ቤቶች ከመንግስት በጀት በተሰሩ ወይም በተዘጋጁ ገቢ ማስገኛዎች ህጋዊ ሥልጣን ባልተሰጠው አካል ገቢ ስለመሰብሰቡና ተጠቅመው ስለመገኘቱ፤**
- **በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን** 3 **ቅ/ጽ/ቤቶች** 10 **ግብር ከፋዮች በተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ ላይ ብር** 791,195.26 **በብልጫ ተቀናሽ ወይም ተመላሽ ተብሎ የተያዘ ሂሳብ መኖሩ፣**
- **በሁለት መ/ቤቶች ስድስት ሰራተኞች የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ ሆነው ግዴታቸውን ባልተወጡ መምህራንን ላይ በገቡት ግዴታ መሰረት ተገቢው እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ/አባሪ-**30 **ይመልቱ/**

በአዲቱ ተረጋግጧል።

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ አሰባሰቡ ደንብና መመሪያ ተጠብቆ እንዲሠራ እንዲሁም ከላይ የተጠቀሱት የገቢ አሰባሰብ፤ አፈፃፀም እና የአሠራር ድክመቶች እንዲታረሙ፣

እንዲሁም በገቢ አሰባሰብ ላይ የሚደረገው የውስጥ ቁጥጥር ሊጠናከር እንደሚገባ በሰጠነው አስተያየት መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ አንዳንዶቹ አዲት ተደራጊ መ/ቤቶች በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል፡፡

3.7 <u>የገቢ ሂሳብ ዕቅድ አፈጻጸም</u>

ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤቶች በዕቅድ የያዙትን ገቢዎች የሰበሰቡ መሆኑን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፡-

ሀ/ የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ፡- ብር 11,771,351,616.51(23%)

ለ/ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ብር 21,287,645.55(18%)

ከዕቅዱ በታች መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም ለመ/ቤቶቹ የገቢ ዕቅድ በጥናት ላይ የተመሰረተ ሆኖ እንዲዘጋጅና በዕቅዱ መሰረት እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

4 <u>የወጪ ሂሳብ</u>

4.1 <u>ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ የተገኘባቸው መ/ቤቶች</u>

በወጪ የተመዘገቡ ክፍያዎች ህጋዊ ማስረጃ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፣ በ15 መ/ቤቶች ብር 36,725,016.96 ማስረጃ ሣይኖረው በወጪ ሂሳብ የተመዘገበና ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 18 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	ብር	2,576,852.24
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	10,885,892.93
የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	"	14,936,002.43
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	6,981,886.20
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	8,326,269.36
በድምር	ብር	<u>36,725,016.96</u>

ማስረጃዎቹ ለኦዲት ባለመቅረባቸው ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ያልተቻለ ወጪ ሂሳብ ከተገኘባቸው፣የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን ብር 12,660,000.00፣ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት ብር 8,179,060.00፣ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,873,851.63፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 4,366,013.47 ፣ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ብር 2,359,106.93 እና የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት ብር 2,276,002.43 ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ተገቢውን ማስረጃ ሳይቀርብ ገንዘብ ወጪ ማድረግ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳርግ ስለሚችል ባለጥቅሞቹ ገንዘቡ የደረሳቸው ለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብ ለወደፊቱም ማስረጃዎች ወዲያውኑ እንዲቀርቡ ቢደረግ ሊያጋጥም የሚችልን ስጋትና አላስፈላጊ ወጪን ለማስቀረት ስለሚያስችል ማንኛውም ወጪ ከመመዝገቡ በፊት ተገቢው ማስረጃ መቅረቡን በማረጋገጥ እንዲመዘገብ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል::

4.2 <u>የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ክፍያ</u>

በወጪ ለተመዘገቡ ሂሳቦች የተሟላ ማስረጃ መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ59 መ/ቤቶች የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 236,452,502.91 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 17 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	430,691.53
ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	1,070,878.00
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	334,587.65
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	56,960,784.04
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	132,739,577.83
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	<u>44,915,983.86</u>
በድምር	ብር	<u>236,452,502.91</u>

ሆኖ ተገኝቷል ።

ባልተሟላ ማስረጃ ወጪን ከመዘገቡት መ/ቤቶች፤ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 47,697,409.60 ፤ የአሶሳ ዩኒቨርስቲ ብር 25,870,747.59፤ የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ብር 21,125,500.00 ፤ የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ብር 20,951,955.77 እና አርሲ ዩኒቨርሲቲ ብር 20,538,683.00 ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፤ ተሟልተው ካልቀረቡት ማስረጃዎች መካከል፣ ከዕቃ አቅራቢው የተሰጠ ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብ፤ በቀረበው የክፍያ ጥያቄ መሠረት የተፈፀመ እንጂ የተከናወነውን ሥራ በሚያሣይ ዝርዝር ማስረጃ ሳይደገፍ፤ የመንግሥት ሰራተኞች የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅፅ አንድ ሳይዘጋጅ፣ ለስልጠና መስተንግዶ ለተከፈለው ሂሳብ መስተንግዶውና ስልጠናው በትክክል ለመሰጠቱ የሰዓት ፊርማ (አቴንዳንስ) በማስረጃነት ያልቀረበ እና በሚመለከታቸው ኃላፊዎች ያልተረጋገጠ ፤ የቀረቡት ተራ ደረሰኞች ማለትም የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር የሌላቸው እና በባንክ በኩል ገንዘቡ ተልኮ ሥራ ላይ መዋሉን ወይም ለተቀባዩ ስለመድረሱ የሚገልጽ ማረጋገጫ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ጐላ ያሉት ናቸው፡፡

ስለሆነም አሠራሩ የመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ደንብ ያልተከተለ በመሆኑ፣ ለወደፊቱ ጥንቃቄ እንዲደረግና ያልተሟላውም ማስረጃ እንዲሟላ በላክነው ሪፖርት ያሳሰብን ሲሆን፣ አብዛኞቹ መ/ቤቶች የቀረበውን አስተያየት መቀበላቸውንና አስፈላጊውን ማስተካከያ እንደሚያደርጉ በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

4.3 ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች

ክፍያዎቹ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሠረት የተፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት አዲት ሲደረግ፣ በ91 መ/ቤቶችና በ3 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 98,768,151.60 ከደንብና መመሪያ ውጭ አላአግባብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ-19 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	4,758,723.09
በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	139,648.20
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	24,677,392.76
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	56,059,377.29
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	4,452,559.33
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	8,680,450.93
በድምር	ብር	98,768,151.60

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከደንብና መመሪያ ውጪ አለአግባብ ከተፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 16,626,212.78፤ ደብረታቦር ዩኒቨርስቲ ብር 13,324,499.96 ፤ ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ ብር 10,149,481.18፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 7,279,127.30፤ ወላይታ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,845,492.87፤ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,544,216.00 እና ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ብር 2,880,610.00 ሲሆኑ፤ ምክንያቶቹም ከሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ መፈጸም ፣ ለሠራተኞች አበልና ደመወዝ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ በመፈጸም፤ ሰራተኞች መስክ ሳይወጡ የውሎ አበል በመክፈል፣ ለውጭ ጉዞ ከወሰዱት የውሎ አበል ሂሳብ በመመሪያው መሰረት መመለስ ሲገባቸው ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ የኃላፊነት አበልና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን ክፍያ መፈጸም ፤ መ/ቤቱን ለቀቁ ሰራተኞች ለበርካታ ወራት የደመወዝ ክፍያ መፈጸምና በሚመለከተው አካል ያልተፈቀደና ግልጽ የሆነ መስፈርት ባሌለው ሁኔታ ለሰራተኞች ማበረታቻ በመክፈልና በመሳሰሉት ምክንያቶች ወጪ የተደረጉ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

ከዚሁ በተጨማሪ በ8 ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብር 7,633,947.38 የስራው ባህሪ በቋሚነት ወይም ቀጠይነት ያለው መሆኑ እየታወቀ በፐብሊክ ሰርቪስና ሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር ያልተፈቀደ የኮንትራት ሠራተኞች በመቅጠር የተፈጸመ ክፍያ እና

በ11 ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደግሞ በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር ብር 58,364,234.32 የተፈጸሙ ክፍያዎች መኖራቸው በአዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ-9/1 እና 9/2 ተመልክቷል/

በመሆኑም አፈጻጸሙ ከመንግሥት ደንብና መመሪያ ውጪ ስለሆነ፣ ማንኛውም ክፍያ የመንግሥት ደንብና መመሪያን የተከተለ እንዲሆንና ያለአግባብ የተከፈለውም ገንዘብ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.4 <u>በብልጫ የተከፈለ ወጪ</u>

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እና ደንብ መሰረት በአግባቡ የተፈጸሙ፤ እንዲሁም መ/ቤቶቹ ላገኙት አገልግሎት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት አዲት ሲደረግ፤ በ18 መ/ቤቶች ለተለያዩ ግንባታና ግዢዎች ብር 19,512,255.86 እና በ25 መ/ቤቶች ለውሎ አበልና ሌሎች ክፍያዎች ብር 10,431,888.97 በጠቅላላው ብር 29,944,144.83 እና በ1መ/ቤት $2,500.00 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-20 ተመልክቷል/

በብልጫ የተከፈለው ሂሳብም በግዢ ሂደት ያለበቂ ምክንያት ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረቡ እያሉ ከፍተኛ ዋጋ ከቀረቡት ድርጅቶች ግዢ በመፈጸም፤ በድጋሚ ወጪ በማድረግ ወይም ከተገቢው ውል ውጭ በመክፈል፣ ከውሎ አበል ተመን በላይ በመክፈል እንዲሁም ለትርፍ ሰዓት፤ ለተለያየ ጥቅማ ጥቅም እና ለመኖሪያ ቤት አበል ከተፈቀደው በላይ በብልጫ የተከፈለ መሆኑ የሚሉት ይገኙበታል፡፡

ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግና በድጋሚ መመዝገብ የመንግስት ሀብት ለብክነት የሚዳርግ ከመሆኑም በላይ ለሙስናም በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች የፋይናንስ ስርዓቱንና የወጡት ደንብና መመሪያዎች ተከትሎ መፈጸም እንደሚገባቸው፤ በብልጫ የተከፈለውም ገንዘብ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ እንዲሆን አስፈላጊ እርምጃ እንዲወሰድ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.5 <u>የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ያልተከተሉ ግዥዎች</u>

የዕቃና አገልግሎት ግዥዎች በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ79 መ/ቤቶችና በ4 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 324,950,102.20 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 21 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	15,802,727.15
ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	774,051.89
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	13,282,333.69
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	98,796,196.46
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	163,811,204.22
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	32,483,588.79
በድምር	ብር	<u>324,950,102.20</u>

ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ካልተከተሉት የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያዎች፡-ያለጨረታ በቀጥታ ግዥ በመፈጸም ብር185,413,357.21፤መስፈርቱ ሳይሟላ በውስን ጨረታ የተገዛ ብር 30,659,951.58 ፤የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ ብር 42,915,658.54 እና ሌሎች የግዥ ሂደት ያልተከተሉ ብር 65,961,134.87 ናቸው፡፡

ከግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ግዥ ከፈጸሙ መ/ቤቶች መካከል፣ ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ብር 69,476,518.45 ፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 24,606,609.47፤የሀዋሳ ዩኒቨርስቲ ብር 22,809,928.86፤ ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ብር 21,294,981.03፤ ጂማ ዩኒቨርሲቲ ብር 11,720,591.17 ፤አዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 11,037,410.63 ፤ አክሱም ዩኒቨርሲቲ ብር 10,105,118.59 ፤ ቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,109,599.15 መቱ ዩኒቨርሲቲ ብር 9,701,853.51 እና አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 8,935,793.76 ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ከዚሁ በተጨማሪ የተገዙት ዕቃዎችና የተሰጠው አገልግሎት በናሙናው መሠረት ገቢ ለመሆኑና አገልግሎት ለመሰጠቱ የቴክኒክ ኮሚቴ/ በባለሙያ ሳይረጋገጥ ክፍያ

የተፈፀመ በ6 መ/ቤቶች የብር 49,599,091.24 መሆኑ ተረጋግጧል። /ዝርዝሩም በአባሪ-21/1 ተመልክቷል፡፡/

ከመንግስት መመሪያ ውጪ ግዥ መፈፀሙ መ/ቤቶቹን ጥራቱን ላልጠበቀ ዕቃ ወይም ግንባታና ለአላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ስለሚችል መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም/ገቢም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መንግሥት ባወጣው የግዥ ደንብና መመሪያ መሠረት መፈጸም እንደሚገባ ያሳሰብን ሲሆን፣ የመንግስትን አዋጅ በማያከብሩ የመ/ቤቶች የስራ ኃላፊዎች ላይም ተገቢው እርምጃ ሊወሳድ ይገባል፡፡

4.6 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተዘጋጀለት</u>

በበጀት ዓመቱ የተገዛ እቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ የተደረገና የንብረት ገቢ ደረሰኝም የተቆጠረለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ14 መ/ቤቶች በብር 21,416,544.15 ተገዙ ተብሎ በወጪ ለተመዘገበ ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ሳይቀርብ ሂሳቡን በወጪ የመዘገቡ መ/ቤቶች እና በ4 መ/ቤቶች ብር 2,674,478.09 ቀረጥ ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ሳይቀረበላቸው ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ-22 እና አባሪ- 22/1 ተመልክቷል/

ገቢ ያልሆነው ንብረት ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	361,180.22
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	10,833,260.25
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	3,199,525.00
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	7,022,578.68
በድምር	ብር	<u>21,416,544.15</u>

ከዚህም ውስጥ ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ብር 6,433,032.76፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ብር 4,743,664.81 ፣ በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,302,552.26 ፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 3,184,000.00 እና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ብር 1,073,235.00 ለግዥ ወጪ ሆኖ የተገዛው ዕቃና የንብረት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ካልተቆረጡት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ፣ ቀረጥ

ተከፍሎባቸው ንብረቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበላቸውም፣ የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ብር 1,496,954.03 እና ወሎ ዩኒቨርሲቲ ብር 918,758.32 ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ለዕቃና ንብረት ግዥ ለወጣው ገንዘብ ዕቃው ገቢ ለመደረጉ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ መመዝገቡ መንግስት ለወጠው ወጪ ተመጣጠኝ አገልግሎት ስለመግኘቱ ማረጋገጥ የማይቻል ሲሆን የተገዛው ንብረት ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በዚህ መልኩ ወጪ ለሆነው ሂሳብ ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲያዘጋጁና ለተከፈለውም የቀረጥ ሂሳብ ምዝገባ ከማከናወናቸው በፊት ቀረጡን የከፈሉላቸው ድርጅቶች ቀረጥ የተከፈለባቸውን ንብረቶች ገቢ ለማድረጋቸው ማረጋገጥ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.7 <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ</u>

በበጀት ዓመቱ በመንግሥት መ/ቤቶች በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ9 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ ኮንትራታዊ አገልግሎቶች ክፍያ በድምሩ ብር 99,645,132.99 በተሰብሳቢ ሂሳብ መመዝገብ ሲገባው በወጪ ተመዘግቦ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 27 ተመልክቷል/

በመሆኑም የመንግሥት ሂሳብ አያያዝ በሚያዘው መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ፣ ቅድሚያ ክፍያው ሥራው ተጠናቆ በቂ ማስረጃ እስከሚቀርብበት ድረስ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲመዘገብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.8 <u>የወጪ የሂሣብ መደብ ሳይጠብቁ የተመዘገቡ ወጪዎች</u>

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/አ/ት/ሚ/ር ነሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣ በ64 መ/ቤቶች ብር 134,338,778.71 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሳይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 25 ተመልክቷል/

ሂሳቡም በዘርፍ ሲጠቃለል፤

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	ብር	56,562,154.04
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	31,381,529.05
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	38,662,041.49
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	7,733,054.13
በድምር	ብር	134,338,778.71

የወጪ ሂሣብ መደብ ሳይጠብቁ ወጪ ከመዘገቡ መ/ቤቶች መካከል የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብር 29,703,434.00 ፣ አክሱም ዩኒቨርሲቲ ብር 22,322,164.80 ፣ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ብር 13,025,029.57 ፣የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንሰቲትዩት ብር 8,879,767.20 ፤ አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ብር 7,296,089.99 እና መቀሌ ዩኒቨርሲቲ ብር 6,582,659.52 ከፍተኛዎቹ ናቸው፡፡

የሂሣብ መደቡን ጠብቆ ወጪ አለመመዝገብ የበጀት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ በመፍጠር ከበጀት በላይ ወይም በታች መጠቀምን ከማስከተሉም በላይ የሂሳብ ሪፖርቱን ትክክለኛነትም ያዛባል፡፡

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.9 <u>የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ</u>

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች በበጀት ዓመቱ ለተገኙ አገልግሎቶች ብቻ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ27 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 106,539,302.53 የበጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ወጪ በ2008 በጀት ዓመት የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ -24 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፤

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	ብር	20,462,380.02
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	5,098,656.18
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	80,650,516.33
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	327,750.00
በድምር	ብር	106,539,302.53

ሲሆን፤ ይህም የበጀት ዓመቱ የበጀት አፈፃፀም በትክክል እንዳይታይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ማዕቀፍ መሰረት በበጀት አመቱ የተገኘ አገልግሎት ወጪው በተገኘበት በጀት ዓመት ሊመዘገብ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.10 በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ ወጪ

የውስጥ ገቢ እንዲሰበስቡና እንዲጠቀሙ የተፈቀደላቸው መ/ቤቶች ከውስጥ ገቢያቸውን ያወጡትን ወጪና ሌሎች ወጪዎች የመደበኛ ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚቀርበው የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳውቁ/ ሁሉም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት የተካተተ/ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ12 መ/ቤቶችና ሁለት ተጠሪ ቅ/ጽ/ቤቶች በድምሩ ብር 176,427,854.32 እና በአንድ ዩኒቨርሲቲ እና አንድ ሆስፒታል በገንዘብ መጠኑ ያልተገለጸ ከውስጥ ገቢ የተከፈለና የሌሎች ወጪ ሂሳብ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ ወይም በወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ-23 ተመልክቷል/

ይህም የዘመኑን የፌዴራል መንግስትን አመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተዛባ ያደርገዋል፤ በተጨማሪም ትክክለኛውን የመ/ቤቶቹን የፋይናንስ አፈጻጸም ላያመለክት ይችላል፡፡

በመሆኑም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 በተደነገገውና በፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሠረት የውስጥ ገቢም ሆነ ወጪ

ለገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ሪፖርት መደረግ እንዳለበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.11 ደንብና መመሪያን ያልተከተሉ የግንባታ ክፍያዎች፤

ከግንባታዎች ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ግንባታዎች በሚያከናወኑ መ/ቤቶች የተፈጸሙ ክፍያዎች በመንግስት የወጡ የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ መሰረት የተከናወኑ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ለተጨማሪ የግንባታ ሥራ ትዕዛዝ የውል ሥምምነት ያልቀረበለትና በአዋጁ መሠረት በዋና ውል ላይ 25% በማስላት ብቻ ተጨማሪ ውል መግባት ሲገባው፣ ሕጉ ከሚፈቅደው በላይ ውል የተገባ በ9 መ/ቤቶች ብር 140,384,732.80 ፤ የተጨማሪ ሥራ ውል ሥምምነት ያልተፈረመ በ3 መ/ቤቶች ብር 66,383,236.25 በድምሩ በብር 206,767,969.05 ተከፍሎ መገኘቱ፤
- ደንብና መመሪያን ያልተከተሉ (የቅድሚያ ክፍያ ዋስትናው ያልታደሰ፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከግንባታ ክፍያው ላይ ያልተቀነሰ መሆኑ፤ ለግንባታው ሥራ የተገዙ የተለያዩ ማቴሪያሎች ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤ የውል ሰነድ እና የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች የሚያሳይ ዝርዝር ሁኔታ ሳይቀርብ እንዲሁም የግንባታ የክፍያ ምስክር ወረቀት ሳይኖር ለGIZ የተከፈለ.....ወ.ዘ.ተ) የግንባታ ክፍያዎች፤ በ5 መ/ቤቶች ብር 37,909,666.37 መፈጸሙ፤
- በተጨማሪም በ20 መ/ቤቶች ብር 133,631,062.49 ከግንባታ ፕሮጀክቶች ጋር የተያያዘ በመጀመሪያ ከተከፈላቸው የቅድሚያ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ ሳይደረግ የቀረ ሂሳብ መኖሩ፤
- በ8 መ/ቤቶች ብር 260,989,864.26 ያለአማካሪ ድርጅት የክፍያ ሠርትፊኬት ትክክለኛነት የማረጋገጥ እና የመሳሰሉት ሥራዎች በግንባታ ጽ/ቤት አማካኝነት የተከናወነ መገኘቱ፤
- በ3 መ/ቤቶች ብር 23,130,699.31 በተከፋይነት ያልተያዘ ፤ በጀት ሳይፈቀደለት የመያዣ ሂሳብ መከፈሉ ተረገግጦል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- አባሪ-20/1 እስከ አባሪ-20/5 ተመልክቷል/

በመሰረቱ ቅድሚያ ክፍያዎች በተሰበሳቢ ሂሳብነት ተይዘው ሥራው መሰራቱ ሲረጋገጥና ተገቢው ማስረጃ ሲሟላ ብቻ በወጪነት መመዝገብ አለበቸው፡፡ የግንባታ ክፍያ በሚከፈሉበት ጊዜም ቀደም ሲል የተከፈለው ቅድሚያ ክፍያ እየተጣራ በሕጉ መሰረት መቀነስ ነበረበት፡፡ተገቢውና ጠንካራ ክትትል ካልተደረገ በቀር በወጪነት የሚመዘገብ ቅድሚያ ክፍያ አገልግሎት ሳይገኝ ባክኖ የመቅረት ዕድሉ እጅግ በጣም ሰፊ ነው፡፡

በመሆኑም የማማከሪ ስራዎችም ገለልተኛና የሙያ ብቃት በተሰጣቸው ባለሙያዎች እንዲከናወን፤ተጨማሪ ውል ሲያስፈልግም ሕጉ በሚፈቅደው ልክ እንዲሆንና በአጠቃላይ የግንባታ ስራዎች በመመሪያው መሰረት እንዲከናወኑ አስፈላጊ ክትትል እንዲደረግ በሪፖርታችን አሳስበናል።

4.12 <u>በባለስልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ</u>

በወጪ ተመዘገቡት ክፍያዎች ስልጣን በተሰጠው ኃላፊ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ9 መ/ቤቶች በኃላፊ ሳይጸድቅ ብር 28,627,001.52 ፤ በ1 መ/ቤት ደግሞ ብር 7,074,728.79 ከተሰጣቸው ውክልና በላይ ወጪ አፅድቀው መገኘቱ እና በሁለት መ/ቤቶች የወጪ ሂሰብን ማዘጋጀት፤ ማረጋገጥና መፍቀድ ተግባራት ተደርቦ በአንድ ሰራተኛ የተከናወነ ክፍያ ብር 230,737.61 መገኘቱ ተረጋግጧል።/ዝርዝሩ በአባሪ-26 እና 26/1 እና አባሪ-26/2 ተመልክቷል/

በዚህም ውስጥ ስለትክክለኝነቱ ወጪውን ባረጋገጠው ኃላፊ ያልተፈረመ፤ በጀት ስለመፈቀዱ የበጀት ሰራተኛ፤ሂሣቡን ባረጋገጠው ሰው ያልተፈረሙና ከተሰጠው ውክልና ባላይ የተፈረመ ሂሳብ ይገኝበታል፡፡

በመሆኑም አሰራሩ ከደንብና መመሪያ ውጭ በመሆኑና ለገንዘብ ብክነት ሊያገልጥ ስለሚችል ሊስተካከል እንደሚገባ አሳስበናል።

4.13 ሌሎች ከወጪ ሂሳብ ጋር የተያያዘ የሚታዩ ችግሮች

4.13.1 የሕንጻና መሠረተ-ልማት ግንባታ አፈጻጸምን በተመለከተ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

- በዩኒቨርሲቲው በርካታ የተለያዩ የፕሮጀክት ሂሳቦች ቢኖሩም የፕሮጀክት ሂሳቦቹ ዝርዝር መረጃ ማለትም የፕሮጀክቱ ስም፣ የፕሮጀክቱ ዓላማ፣ ፕሮጀክቱ የጀመረበት ጊዜ፣ ለሂሳብ ምዝገባው እና ለሪፖርት ዝግጅት የሚጠቀመው የኤሌክትሮኒክስ ምዝገባ ዓይነት፣ በሂሳብ አካውንት ላይ የሚታይ የገንዘብ መጠን ሰኔ 30/2008፣ ወቅታዊ የሂሳብ ሪፖርት እንደሚዘጋጅ፣ የፕሮጀክት ሂሳቡ ኦዲት ለመደረጉ እና ላለመደረጉ ከተደረገ በማን እንደተደረገ የሚገለፅ ማስረጃ እና በህጉ መሰረት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕሮጀክት ሂሳብ እንቅስቃሴ የሚያመለክት ሪፖርት ለማቅረቡ የሚገልፅ ማስረጃ በ2007 በጀት ዓመት ኦዲት እንዲሁም በ2008 በጀት ዓመት ኦዲት ኦዲቱ ከተጀመረ ጀምሮ የተጠየቀ ቢሆንም መረጃው በዩኒቨርሲቲው ያልቀረበ መሆኑ፤

በመቱ ዩኒቨርሲቲ

- በትምህርት ሚኒሰቴር እና በመቱ ዩኒቨርሲቲ መካከል በ2005 ዓ.ም የግንባታ ሥራዎች በዩኒቨርሲቲው ባለቤትነትና ሃላፊነት እንዲካሄድ ከትምህርት ሚኒሰቴር ወደ ዩኒቨርሲቲ ያስረከባቸዉ ስራ ተቋራጮች ርክክብ ሲደረግ ከስራ ተቋራጮች የሚፈለገዉ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣ተከፋይ ሂሳብ እና ዕዳ በትክክል ታውቆ ወደ ዩኒቨርሲቲ ባለመተላለፉ በወቅቱ ዩኒቨርሲቲው ከስራ ተቋራጮች የሚፈለገዉ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣ተከፋይ ሂሳብ እና ዕዳ መዝግቦ ያልያዘ መሆኑና አሁን ያለዉ የህንጻ ተቋራጮች የተሰብሳቢ ፣የተከፋይ እና የመያዣ ሂሳብ የሚያሳየው ዩኒቨርሲተው ግንባታውን ተረክቦ ማስተዳደር ከጀመረበት ጊዜ በኃላ ያለው ሂሳብ ብቻ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- ኒሐም ኢኒተርናሽናል ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የብር 14,699,675.00 ፒፒስ ሲሚንቶ ለማቅረብ ውል የተገባ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው የውሉን ጠቅላላ ዋጋ

*30% (14,699,675.00*30%)= ብር 4,409,902.50 ቅድሚያ ክፍያ መስጠት ሲገባ ብር 14,699,675.00 ሙሉውን ጠቅላላ የውሉን ዋጋ ተሰጥቶ የተገኘ መሆኑ፤

ዲላ ዩኒቨርሲቲ

- ቀደም ሲል ትምህርት ሚኒስቴር ክትትል እየተደረገባቸው የነበሩ እና GIZ በተባለው ድርጅት ተይዘው ሲሰሩ የነበሩ የዩኒቨርሲቲው የህንፃ ግንባታዎች እና የመሰረተ ልማት ግንባታ እንዲሁም የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ፕላንት ግንባታን በተመለከተ ለማወቅ የሚያስችሉ፤ የተደረጉ የሰነድ ርክክቦች፤ ማለትም፤ ለእያንዳንዱ ሥራ ተቋራጭ በቅድሚያ የተከፈለው ጥሬ ገንዘብ፤ ተመላሽ የተደረገው እና ያልተመለሰ ቅድሚያ ክፍያ፤ ለእያንዳንዱ ሥራ ተቋራጭ በዓይነት የተሰጡ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች /Material Advance/ ተመላሽ የተደረገው ገንዘብና እና ያልተመለሰ፤ቀሪ ዕዳ፤እያንዳንዱ ስራ ተቋራጭ ለሚያከናውናቸው ግንባታዎች በመያዣነት ገቢ ያደረገው የመልካም ስራ ዋስትና ገንዘብ እንዲሁም ግንባታ ክፍሉ ከGIZ-IS የተረከባቸው ሰነዶች፤ ለሂሳብ ክፍል ተላልፈው በእያንዳንዱ የህንጻ ስራ ተቋራጭ ስም ሂሳቡ እንዲመዘገብ ስለመደረጉ፤ እንዲሁም ስራው የደረሰበት ደረጃ፤ ያቋረጡ ካሉ በእነሱ ላይ የተወሰደ እርምጃ ካለ፤ ከስራ ተቋራጮቹ የሚፈለገውን የተሰብሳቢ እና የመያዣ ሂሳብ የሚያሳይ ተቀጽላ ሌጀር ካለ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብና እየተደረገ ስላለውም ክትትል ለማወቅ የሚያስችል በቂ ምላሽ የሚሰጥ አካል ባለመገኘቱ የሂሳቡን ሁኔታ ማጣራት አለመቻሉ፤

የጅማ ዩኒቨርሲቲ

- የላብራቶሪና ወርክሾፕ ግንባታ በብር 355,925,389.92 በቀን 07/06/03 ውል የተገባ ሲሆን በፀደቀ የውል ማራዘሚያ እስከ 07/06/05 መጠናቀቅ የነበረበት እስከ ሰኔ 30,2008 ድረስ ያልተጠናቀቀ መሆኑና ከ3 ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ፤
- የሪሰርች ሴንተር እና ኮንፈረንስ ሆቴል ግንባታ በብር 227,919,070.43 በቀን 9/9/2002 ውል የተገባ ሲሆን በፀደቀ የውል ማራዘሚያ እስከ

01/4/2004 መጠናቀቅ የነበረበት እስከ ሰኔ 30,2008 ድረስ ያልተጠናቀቀ መሆኑና ከ4 ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ፤

- የእስታዲየም ግንባታ በብር 144,323,492.00 በቀን 6/8/2007 ውል የተገባ ሲሆን በፀደቀ የውል ማራዘሚያ እስከ 25/1/2008 መጠናቀቅ የነበረበት እስከ ሰኔ 30,2008 ድረስ ያልተጠናቀቀና ስራው ያለበት ደረጃ 23.35% መሆኑ፤
- ዩኒቨርሲቲው በ13/07/2003 ሁለት ቢሮዎች (አንድ ቢሮ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ግቢ ውስጥ እና ግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ ቤተ-መጻህፍት) እና ከዋናው ግቢ ወደ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ የሚያስተላልፍ ድልድይ ለማሰራት ከአፍሮ ፅዮን ኮንስትራክሽን ኃላ.የተ.የግ.ማ ጋር በ48.7 ሚሊዮን ብር ውል የገባ ሲሆን በቢዝነስ እና ኢኮኖሚክስ ግቢ መግንባት የነበረበት ህንፃ ሙሉ በሙሉ ያልተሰራ መሆኑ፤

በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ

- በመከናወን ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ኦዲት ሲደረግ በተገባው ውል መሠረት በወቅቱ ያልተጠናቀቁና አሁንም በመከናወን ላይ ያሉ 4 ፕሮጀክቶች የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ በውሉ በተቀመጠው የማስረከቢያ ቀን መሠረት ግንባታውን አጠናቀው ያላስረከቡ 8 የህንጻ ተቋራጮች መኖራቸው ታውቋል፡፡

በመሆኑም የተጠቀሱት አሰራሮች እንዲስተካከሉ የተጀመሩት ግንባታዎች በጊዜያቸው እንዲጠናቀቁና በውል በተቀመጠው ጊዜ ባለመጠናቀቃቸው የደረሰው የጉዳት ካሳ እንዲጠየቅበት አሳስበናል፡፡

5 <u>የተከፋይ ሂሣብ</u>

5.1 <u>በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሣብ</u>

በገ/ኢ/ት/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ73 መ/ቤቶችና

በስምንት ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 1,880,499,977.09 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 31 ተመልክቷል/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን	ብር	375,652,461.94
የገቢዎችና ጉምሩክ መ/ቤቶች	"	666,574,340.47
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶ	"	77,632,748.48
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	536,771,014.87
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	188,583,502.76
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	35,285,908.57
ድምር	ብር	1,880,499,977.09

በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ተገኝቷል፡፡ የተከፋይ ሂሳቡ በዕድሜ በቆይታ ጊዜው ሲተነተን፣ ከአንድ ወር እስከ አንድ ዓመት ብር 104,587,943.58፣ ከአንድ ዓመት በላይ እስከ አምስት ዓመት ብር 374,727,888.39፣ ከአምስት ዓመት በላይ እስከ አሥር ዓመት ብር 20,043,052.99 እና ከአሥር ዓመት በላይ ብር 23,675,570.61 ሲሆን፣ ቀሪው ሂሳብ ብር 1,357,278,582.92 የቆይታ ጊዜው በግልጽ ለመለየት ያልተቻለ፣ ከዚሁ ሂሳብ ውስጥ በ8 መ/ቤቶችና በ8 ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 833,811,806.31 በቂ ማስረጃ ባለመቅረቡ ለማን እንደሚከፈል፣ መቼ እንደተከሰተ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ተከፋይ ሂሳብ መሆኑ ታውቋል፡፡

በወቅቱ ያልተከፈለ ሂሳብ ከታየባቸው መ/ቤቶች፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብር 419,956,203.21፣በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 342,950,209.55 ፣በአዲስ አበባ ምስራቅ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት ብር 308,074,556.05 ፣የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት ብር 285,468,377.01 ፣ የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ብር 159,561,189.14 ፣ ጎንደር ዩኒቨርስቲ ብር 79,227,247.16፣ የአ.አ. ሳይንስና ቴክ. ዩኒቨርስቲ ብር 39,760,785.78፣ በምዕ/አ/አ/መ/ግ/ከ/ቅ/ጽ/ቤት ብር 35,577,225.60 ፣አዲስ አበባ

ኤርፖርት ብር 26,163,220.64 እና የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ ብር 15,923,663.20 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

በመሆኑም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው ትክክለኛ የመ/ቤቱ ዕዳ መሆኑ እየተጣራ እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

5.2 <u>በተከፋይ ሂሳብ አያያዝ የታዩ ድክመቶች</u>

በዓመቱ መጨረሻ በሂሳብ መግለጫ ላይ የሚታየው የየመ/ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳብ ሚዛን ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

- ያልተመዘገበ የግንባታ የቅድመ ክፍያ ተመላሽ በሁለት መ/ቤቶች ብር 51,470,989.29 እና የመያዣ ተከፋይ ሂሳብ ያልተመዘገበ በ3 መ/ቤቶች ብር 109,539,434.01 መገኘቱ፤
- በተከፋይ ሂሳብ መያዝ ሲገባው በገቢ የተመዘገበ ሂሳብ በመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ብር 6,000,000.00 መገኘቱ፤
- መደበኛ ባልሆነ የሂሳብ ሚዛን (ዴብት) የሚታይ በ3 መ/ቤቶች ብር 20,611,102.35 መኖሩ፣
- ተቀጽላ ሌጀር ያልተዘጋጀላቸው በ2 መ/ቤቶች ብር 1,496,469.73 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-32 ሀ እስከ መ ተመልክቷል/

በዚህ አሰራር የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን የተከፋይ ሂሳብ ሁኔታ እንዳያሳይ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በመሆኑም ምዝገባው ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ጠብቆ መከናወን ያለበት ሲሆን ከላይ የተከሰቱትን ሁኔታዎች በተመለከተ ደግሞ ተገቢውን ማጣራት በማካሄድ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይገባል።

6 የበጀት አጠቃቀም

አዲት በተደረጉት መ/ቤቶች የተፈቀደላቸው በጀትና በሥራ ላይ ያዋሉት ሂሳብ ሲነፃፀር ከበጀት በላይ ወጪ የተደረገና በርካታ ያልተሠራበት በጀት የተገኘ ሲሆን እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

6.1 ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ

የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውን ለማጣራት አዲት ሲደረግ፣ በ52 መ/ቤቶች ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች በደንቡ መሠረት ሳያስፈቅዱ ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ ሥራ ላይ የዋለ ሂሳብ ከመደበኛ በጀት ብር 177,327,518.45 እና ከካፒታል በጀት ብር 92,432,012.04 በድምሩ ብር 269,759,530.49 ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 33 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	5,947,483.52
የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤቶች	"	7,230,416.01
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶ	"	49,404,867.46
የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	195,875,731.29
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች		9,178,686.87
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	2,122,345.34
ጠ/ድምር	ብር	269,759,530.49

ከበጀት በላይ ወጪ ካደረጉ መ/ቤቶች፣ ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 83,491,831.42 ፣ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ ብር 46,964,205.09 ፣ ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ብር 15,798,465.73 ፣ አርሲ ዩኒቨርሲቲ ብር 13,212,410.76፣ ዲላ ዩኒቨርሲቲ ብር 12,013,561.17 እና ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,793,868.48 ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በ5 መ/ቤቶች ብር 24,654,548.49 በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ የተፈፀሙ ከፍያዎች እና በ3 መ/ቤት ለስራው በጀት ስለመኖሩ ሳይረጋገጥ ወይም በሚመለከተው ኃላፊ ሳይፈረም ወጪ የማድረግ አሰራር የሚከተሉ መሆኑ ታውቋል፡፡

በጀት ሳይፈቀድ ወጪ ማድረግ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ የተከለከለ ከመሆኑ በላይ የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክንና በጀት ለማጽደቅ ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ መ/ቤቶቹ የበጀት ዝግጅታቸውም በበቂ ጥናት ላይ ተመስርቶ መዘጋጀት እንዳለበትና አፈጻጸሙ የበጀት አዋጅን ተከትሎ እንዲሆን በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

6.2 <u>ያልተሰራበት በጀት</u>

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት

አዲት ሲደረግ፣ በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% ላይ የሆነውን ብቻ በመውሰድ በ142 መ/ቤቶች መደበኛ በጀት ብር 3,331,577,013.49 እና ካፒታል ብር 1,725,145,215.92 ብር 5,056,722,229.41 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 33 ተመልክቷል፡፡/

ሂሳቡ በዘርፍ ሲጠቃለል፣

የፋይናንስና ኮሙኒኬሽን መ/ቤቶች	ብር	596,704,850.36
የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን	"	754,901,868.91
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች	"	352,069,616.05
የልማትና ማህበራዊ መ/ቤቶች	"	1,000,512,214.44
ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት	"	681,814,885.93
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች	"	<u>1,497,856,757.95</u>
ጠ/ድምር	ብር	<u>5,056,722,229.41</u>

ለልዩ ልዩ የሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት ላይ ሳይሰራበት ከተገኘባቸው መ/ቤቶች፡- በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት እና ቅ/ጽ/ቤቶች ብር 754,901,868.91 ፤ የአ.አ.ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ ብር 424,278,500.86፤ የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር 403,331,824.91፣ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 221,777,718.77፤ትምህርት ሚኒስቴር ብር 215,916,040.78 ፤ የሀገር አቀፍ

የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ ብር 198,236,163.67፤ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ብር 142,012,434.17፣ አዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 128,805,410.23፣ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ብር 115,280,256.32 እና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት ብር 110,230,389.22 ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በጀት ከተፈቀደ በኋላ አለመጠቀም የታቀዱ ሥራዎች ሳይከናወኑ ሊቀሩና መ/ቤቱም ዓላማውን እንዳያሳካ ሊያደርግ ስለሚችል፣ ለወደፊቱ በበጀት ዝግጅትና አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች በሪፖርታችን አሳስበናል።

7 <u>የንብረት አያያዝና አጠባበቅ</u>

7.1 <u>የቋሚ የዕቃና ንብረት አስተዳደር ድክመቶች</u>

መ/ቤቶች የመንግሥትን ንብረት በደንቡ መሠረት መዝግበው ቁጥጥር የሚያደርጉ መሆኑን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ የሚከተሉት የአሰራር ድክመቶች፡ እንደሚገኙ በኦዲታችን ወቅት ተረጋግጧል።/ዝርዝሩ በአባሪ-34/ሀ እስከ አ ተመልክቷል።/

ለቋሚዕቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልሰጡ	38 መ/ቤቶች
ዓመታዊ ቆጠራ ያደረጉ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋረ ትክክለኛነቱን ያላረጋገጡ	39 መ/ቤቶች
የቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ ያላደረጉ	19 መ/ቤቶች
ቋሚና አላቂ ዕቃዎች መዝገብ /እስቶክ ካርድ/ ያላቋቋሙ ወይም የተሟላ ምዝገባ ያላከናወኑ	17 መ/ቤቶች
የስቶክ መቆጣጠሪያ ቢን ካርድ ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	12 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ያለአገልግሎት የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው	28 መ/ቤቶች
አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የተለያዩ ንብረቶች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ሳይወገዱ የተገኙባቸው	72 መ/ቤቶችና 14 ቅ/ጽ/ቤቶች
ተያያዥነት ያላቸው የንብረት አስተዳደር ስራዎች በአንድ ሠራተኛ ብቻ የሚከናወንባቸው	22 መ/ቤቶች
በየስራ ክፍሉ ለተሰጡ የቋሚ እቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (በUser Card) ያላዘጋጁ መ/ቤቶች	10 መ/ቤቶች
በተወረሱና በእንጥልጥል ላይ ያሉ ንብረቶች አያያዝ ችግር የሚታይባቸው:- 243 የተለያዩ ተሽከረካሪዎችና 11 ሞተር ብስክሌቶች	10 ቅ/ጽ/ቤቶች
የለቀቁ ሰራተኞች ሲጠቀሙበት የነበሩ ንብረቶች ወደ ግምጃ ቤት ተመላሽ አለማድረጋቸዉ 26 ላፕቶፕና ሌሎች ዕቃዎች	2 መ/ቤቶች
የንብረት ክፍል ሠራተኞች ሲቀያየሩ ያስረከቡት ንብረት ከወጪ	4 መ/ቤቶች

ቀሪ ትክክለኛነት የማይረጋገጥ መሆኑ፤	
በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ሳይደረጉ ንብረት ክፍል የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙባቸው መ/ቤቶች	1 መ/ቤት
ጊዜው ያለፈበት መድኃኒትና የተለያዩ ኬሚካሎችን በአግባቡ ያላስወገዱ መ/ቤቶች	17 መ/ቤቶችና 2 ቅ/ጽ/ቤቶች

መንግሥት ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች ግዥ በየዓመቱ የሚያወጣው ወጪ ከፍተኛ ቢሆንም በብዙ መ/ቤቶች የሚታየው ንብረት አስተዳደር አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡ በዚህም ምክንያት በእነዚህ መ/ቤቶች የተዘረጋው የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት ደካማ በመሆኑ ዕቃና ንብረት ለምዝበራና ብክነት የመጋለጥ አጋጣሚው ከፍተኛ ነው፡፡ አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ንብረቶች ያለአገልግሎት በየንብረት ክፍሉ ተከማችተው እያለ የተመሳሳይ ንብረቶች ግዥ የሚፈጽሙ መ/ቤቶችም መኖራቸው በአዲታችን ወቅት ታይቷል። እንዲሁም ጊዜ ያለፈባቸውና ሊወገዱ የሚገባ የተለያዩ ለጤና ጎጂ የሆኑ ኬሚካሎች በበርካታ መ/ቤቶች ይገኛሉ፡፡

የእነዚህ የተለያዩ የንብረት አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው በየዘርፍ በንብረት አያያዝና አስተዳደር የታዩ ሌሎች የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ድክመቶች በሚል ተገልጿል ።

በመሆኑም መ/ቤቶቹ የመንግሥትን ንብረት ለምዝበራና ብክነት እንዳይጋለጥ ተገቢውን ምዝገባና ቁጥጥር እንዲያደርጉ፤ አገልግሎት መስጠት የማይችሉትንና ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶችና ኬሚካሎች በመንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረትና በጥንቃቄ እንዲያስወግዱ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>ተሽከርካሪ</u>

የተሽከርካሪ አጠቃቀምና አያያዝን በተመለከተ በፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

ሊብሬ ያልቀረበላቸው	በ27 መ/ቤቶች	170 ተሽከርካሪዎችና 14 ሞተር ብስክሌቶች
በብልሽት ምክንያት የቆሙ	በ32 መ/ቤቶች	453 ተሽከርካሪዎችና 18 ሞተር ብስክሌቶች
የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው፣	በ6 መ/ቤቶች	8 ተሽከርካሪዎች
የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሥም የሆነ	በ8 መ/ቤቶች	182 ተሽከርካሪዎች
የሞተር ቁጥር የሌላቸው	በ2 መ/ቤቶች	8 ተሽከርካሪዎች

የባለቤትነት መታወቂያ ደብተርና በተሽከርካሪ ዎቹ ላይ በተመለከተው የሻንሲ ቁጥር መካከል ልዩነት	በ3 መ/ቤቶች	182 ተሽከርካሪዎችና 2 ብስክሌቶች
የተሽከርካሪ ፋይል የሌላቸው/የማያደረጁ	በ3 መ/ቤቶች	17ተሽከርካሪዎች
የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው የማይሰራ	በ5 መ/ቤቶች	

መኖራቸው ታውቋል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ -35 /ሀ እስከ ሸ ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶቹ በሁኔታው ላይ የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው በመግለጽ በብልሽት ምክንያት ቆመው የሚገኙ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት መስጠት እንዲችሉ፣ የማያገለግሉት ደግሞ በመንግሥት ንብረት አስተዳዳር መመሪያ መሠረት እንዲሸጡ /እንዲወገዱ፣ ሊብሬ የሌላቸው እንዲወጣላቸውና ሰሌዳ የሌላቸው እንዲወጣላቸው አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

8 <u>ባለፈው ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ ስለመሆኑ</u>

ባለፉት በጀት ዓመታት መ/ቤታችን በላካቸው የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣

በ55 መ/ቤቶች እና 19 ቅ/ጽ/ቤቶች/ተጠሪ ጽ/ቤቶች በተለያዩ ነጥቦች ላይ በኦዲት ሪፖርቱ በተገለጸው መሰረት ተገቢውን እርምጃ ያልወሰዱ ሲሆን /ዝርዝሩ በአባሪ-36 ተመልክቷል/ እርምጃ ያልተወሰዱባቸው ነጥቦች በየዘርፉና በየመ/ቤቶቹ ዝርዝር ሪፖርት መጨረሻ ላይ ተመልክቷል፡፡

በመሆኑም በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ አለመወሰዱ አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ እርምጃ እንዲወሰድ ለሁሉም መ/ቤቶች በድጋሚ አሳስበናል።

9 <u>ልዩ ልዩ ፤</u>

9.1 <u>ከውል ውጪ የተፈቀደ ሴሌክትድ ማቴሪያል፤</u>

9.1.1 በእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስቴር የብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል እና የሆለታ የአስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያን የውስጥ ለውስጥ አስፋልትና ለጠጠር መንገድ ለማሰራት ማዕከሉ ከኃቨሪም ኮንስትራክሽን ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ጋር የውል ስምምነት የፈጸመ ሲሆን፣ ድርጅቱ ለመንገድ ሥራው የሚሆን ሴሌክቲቭ ማቴሪያል ከሆለታ የአስኳል

መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ ቆፍሮ ለመጠቀም ይችል ዘንድ እንዲፈቀድለት ሰኔ 2 ቀን 2007 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር HVT/540/07 ማዕከሉን በጠየቀው መሰረት፡-

- ድርጅቱ ሴሌክቲቭ ማቴሪያል የሚጠቀምበት ቦታ ከ1/2 (ግማሽ) ሄክታር እንዳይበልጥ፣
- ለሆለታ አስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ ለሌላ ጊዜ የሚያገለግል ሰሌክትድ ማቴሪያል ድርጅቱ እንዲያዘጋጅና ቦታው ላይ እንዲያደርስ፣
- የግጦሽ ቦታን ሳይጎዳ በአንድ መንገድ እንዲጠቀም፣

የተፈቀደ መሆኑን የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ገልጸዋል፡፡ ሆኖም፡-

- በውል ሥምምነቱ ላይ ከሆለታ አስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ መንገድ ሥራ ለሴሌክቲቭ ማቴሪያል የሚሆን ክፍያ በውሉ ውስጥ የተካተተና ክፍያውም የተፈጸመ ቢሆንም፤ድርጅቱ ሰሌክትድ ማቴሪያሉን ከሆለታ አስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ የተጠቀመ በመሆኑ ገንዘቡ በውል ሥምምነቱ ላይ ለሰሌክትድ ማቴሪያል ተብሎ ከተቀመጠው ላይ ተቀናሽ እንዲሆን ያልተደረገ መሆኑ፤
- ድርጅቱ ሴሌክቲቭ ማቴሪያሉን ከሆለታ ጣቢያ ቆፍሮ እንዲጠቀም ሲፈቀድለት፡-
  - የሚጠቀምበት ቦታ ከ1/2 (ግማሽ) ሄክታር ሳይበልጥ የተፈቀደ ቢሆንም በተባለው መሰረት የተፈጸመ ለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
  - ለሌላ ጊዜ የሚያገለግል ሰሌክትድ ማቴሪያል ድርጅቱ እንዲያዘጋጅና ቦታው ላይ እንዲያደርስ በተባለው መሰረት ድርጅቱ ሰሌክትድ ማቴሪያል አዘጋጅቶ ቦታው ላይ ያላደረሰ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

በመሆኑም የመንገድ ሥራው በውሉ መሰረት ካልተፈጸመ፡-

- ♦ ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤
- ♦ የመንግሥትን ጥቅም የሚያስጠብቅ ስለማይሆን፤

በውል ሥምምነቱ ላይ ከሆለታ አስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ መንገድ ሥራ ለሴሌክቲቭ ማቴሪያል የሚሆን ክፍያ በውሉ ውስጥ የተካተተና ክፍያውም የተፈጸመ ሆኖ ሳለ ድርጅቱ ሰሌክትድ ማቴሪያሉን ከሆለታ አስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ መጠቀሙ አግባብ ስላልሆነ በውል ሥምምነቱ ላይ ለሰሌክትድ ማቴሪያል ተብሎ የተቀመጠው ገንዘብ ተመላሽ እንዲሆን መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

9.2 **<u>ከፍተኛ በሆነ የመተንፈሻ አካል ህመም ምክንያት እየተቀጠፉ የሚገኙ የወተት ላሞችን በተመለከተ፤</u>**

9.2.1 የብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብና ንብረት ኦዲት በተደረገበት ወቅት በሆለታ በሚገኘው አስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ ግንቦት 10 ቀን 2005 ዓ.ም ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ ወጥቶባቸው ከተገዙት 300 የሆሊስቴይን ፍሬዝኮያ ላሞች 84 ብቻ የቀሩ መሆኑ ተገልጸ ለቀረበው ግኝት ማዕከሉ ኮርማዎቹን ለአባለዝር ምርት ለማዋል ወይም ለማስወገድ ከብሄራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት ቴስት የሚያደርግ ኪት ከውጭ አገር በማስገባት ሂደት ላይ እንደሆነ እና ምርመራው ከተጠናቀቀ በኋላ በቅርብ ጊዜ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን በወቅቱ በሰጠው ምላሽ ላይ ተገልጿል፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ኦዲት ወቅትም ለመገንዘብ እንደተቻለው ከ2007 በጀት ዓመት ወደ 2008 በጀት ዓመት በቆጠራ የዞሩ የወተት ላሞች ብዛት 475 ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ 127 ወደ ጣቢያው የገቡት ተደምረው 602 ላሞች የደረሱ ቢሆንም ከነዚህ ውስጥ 179 ላሞች ከፍተኛ በሆነ የመተንፈሻ አካል ህመም ምክንያት በሆነው አይቢአር (IBR) (Infection Bovinerino Tricitits) ቫይረስ መሞታቸውና በህይወት ያሉትም በዚህ መድኃኒት በሌለው ቫይረስ የተጠቁ በመሆኑ የሞሞቻ ጊዜአቸውን እየተጠባበቁ የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም ማዕከሉ የቫይረሱን ስርጭትና ተጋላጭነት ፍተሻ አድርጎ የመፍቴህ አቅጣጫ ካላስቀመጠ፡-

- ✓ ላሞቹን እየፈጀ በሚገኘው ቫይረስ ላይ ተገቢው ጥናት ተደርጎ የመፍትሄ አቅጣጫ እንዲቀመጥ ካልተደረገ በቀሪዎቹ ላሞች ላይም ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል፤
- ✓ ቫይረሱ በቀላሉ ወደ አካባቢው ገበሬዎች ቀንድ ከብቶች ሊዛመት እና ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል፤

ለወተት ላሞቹ አስፈላጊው የጤና ምርምራ ተደርጎላቸው ጤነኞቹ በበሽታው ከተጠቁት እንዲለዩ እንዲደረግ እና ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በቅንጅት አሰፈላጊው እርምጃ በአስቸኳይ እንዲወሰድ አሳስበናል።

9.3 **<u>በአደራ የተቀመጠ የጅማ ዩኒቨርስቲ የግንባታ ንብረቶችን በተመለከተ</u>፤**

9.3.1 ግንቦት 3 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር ጅዩ 92/738 ጅማ ዩኒቨርስቲ በሰበታ ከተማ በብሄዊ እንስሳት ጤና ምርምርና ጥናት ማዕከል አጠገብ ለግንባታ መሬት የተሰጠው መሆኑን ገልጸ በቦታው ላይ ግንባታ ሲጀመር አገልግሎት ላይ የሚውሉ በርካታ አሸዋ፣ ብረትና ጠጠር በማዕከሉ ቅጽር ግቢ ውስጥ በአደራ ለጥቂት ወራት ለማስቀመጥ ፍቃድ የጠየቀና ያስቀመጠ ቢሆንም ንብረቶቹ ከዓመት በላይ ጸሐይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው የሚገኝ መሆኑ ታውቋል።
መሆኑም ንብረቶቹ በቶሎ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ካልተደረጉ ለብልሽት ሊጋለጡ ስለሚችሉ ንብረቶቹ ከዓመት በላይ ጸሐይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው ስለሆኑና ሥራ ላይ ሳይውሉ ለብልሽት ሊዳረጉ ስለሚችሉ በቶሎ ሥራ ላይ ይውሉ ዘንድ ሁኔታውን ለዩኒቨርስቲ ማሳሰብ እንዳለበት አስገንዝበናል።

9.4 **<u>በአካባቢው ህብረተሰብ ላይ የጤና ጠንቅ እያስከተለ የሚገኘውን የማይፈለጉ የህክምና ቁሳቁሶች ቃጠሎን በተመለከተ</u>፤**

9.4.1 በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ከአገልግሎት ወጪ የሆኑ ቀጥለው የተመለከቱት የህክምና ቁሳቁሶች ይገኙበም፡-

- ♦ ሲሪንጅ ከነመርፌው በሴፍቲ ቦክስ፣
- ♦ የተለያዩ አይነት ግላሶች፣
- ♦ ከደም ጋር ንክኪ ያላቸውና ደም የነካቸው ፎጣዎች፣ ጨርቆች፣ ባንዴጆች፣
- ♦ የወንዶች ኬር የተሰራባቸው ማቴሪያሎች፣

የመሳሳሉት በሆስፒታሉ ለህክምና የማይፈለጉ ማንኛውንም ነገሮች በሜዲካል ኮሌጁ ግቢ ውሰጥ እንዲቃጠሉ የሚደረጉ መሆኑ ታውቋል። ይህ ሁኔታ በአካባቢው ህብረተሰብና በሜዲካል ኮሌጁ ሰራተኞች ጤና ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳደረ እና የአካባቢውን ንጹህ አየር እየበከለ መሆኑ በሬዲዮ ፋናም ጭምር አስተያየት የተሰጠበት ጉዳይ ቢሆንም ሁኔታው እስከአሁን እንዲስተካከል ባለመደረጉ ችግሩ መቀጠሉን ለመገንዘብ ተችሏል።

በመሆኑም ሁኔታው በአስቸኳይ እንዲስተካከል ካልተደረገ ሽታው በአካባቢው ህብረተሰብና በሜዲካል ኮሌጁ ሰራተኞች ላይ የጤና ተጽዕኖ ሊያሳድር የአካባቢውን አየርም ሊበክል ስለሚችል ሜዲካል ኮሌጁ የጤና ተጽዕኖ እያሳደረ እና የአካባቢውን ንጹህ አየር እየበከለ ለሚገኘው ቃጠሎ ሌላ መፍቴህ በአስቸኳይ በመፈለግ ህብረተሰቡን ካልተፈለገ ሽታ መታደግ እንዳለበት አሳስበናል።

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
የ2008 በጀት ዓመት የተጠቃለለ የሂሳብ አዲት ሪፖርት

መግቢያ

በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 982/2008 መሰረት በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የ2008 በጀት ዓመት ሂሣብ በተጠቃለለ ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የዋና መ/ቤት፣ የአስራ አምስት ቅ/ጽ/ቤቶችንና የማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

የሪፖርቱ አላማ

የዚህ ሪፖርት አላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙት የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የባለስልጣን መ/ቤቱ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ ለማድረግ ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው የዓለም አቀፍ የመንግስት ኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት የባለስልጣን መ/ቤቱ ባዘጋጃቸው የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ /የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

በዚህም መሰረት የባለስልጣን መ/ቤቱን፣ 16 ቅ/ጽ/ቤቶችን (ማለትም የከፍተኛ ግብር ከፋዮች፣ የመቀሌ፣ የምስራቅ አዲስ አበባ፣ ምዕራብ አዲስ አበባ፣ የሞያሌ፣ የድሬዳዋ፣ የኮምቦልቻ፣ የሀዋሳ፣ የባህር ዳር፣ የአዳማ፣ የጅማ፣ የሞጆ ጉምሩክ፣ የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ፣ የአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ እና የጅግጅጋ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶችንና የዋናው መ/ቤት) እንዲሁም የባለስልጣን መስሪያ ቤቱ የተጠቃለለ የ2008 በጀት አመት የሂሳብ እንቅስቃሴ ኦዲት ተደርጓል፡፡

በኦዲቱም መሰረት የታዩ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች እና የማሻሻያ ሀሳቦች

የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የዋና መ/ቤትና የ15 ቅ/ጽቤቶች እንዲሁም የ2008 በጀት ዓመት የማጠቃለያ ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1. የገቢ ሂሳብን በተመለከተ

1.1 የጉምሩክ ቀረጥና ታክስን በተመለከተ

ሀ) **ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር እና የጉምሩክ የስነ-ስርዓት ኮድ ባለመመደባቸው ምክንያት ብር 339,795.50 ቀረጥና ታክስ ያልተሰበሰበ መሆኑ፡-**

ግኝት

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ምዕራፍ 2 አንቀጽ 102 ንኡስ አንቀጽ 1 መሠረት ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ ማናቸውም ዕቃዎች ላይ የሚከፈል ቀረጥ በጉምሩክ የታሪፍ ደንብ በተወሰነው ምጣኔ መሠረት እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት እቃዎች በሀርሞናይዝድ ሲስተም ታሪፍ አተረጓጎም አጠቃላይ ደንቦች መሰረት መመደባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ዕቃዎች በትክክለኛው የታሪፍ ቁጥር (H.S.code) እና በትክክለኛው የጉምሩክ ስነስርአት (CPC code) ባለመመደባቸው ምክንያት፡-

በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	ብር	82,783.69
በድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	“	11,208.50
በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	“	157,862.35
በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት	“	87,940.00
በድምሩ	ብር	339,795.50

ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡

ስጋት

መንግስት ከገቢ ዕቃዎች መሰብሰብ ያለበትን ቀረጥና ታክስ እንዳይሰበስብ ሊያደርገው ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

እቃዎች በሀርሞናይዝድ ሲስተም ታሪፍ አተረጓጎም አጠቃላይ ደንቦች መሰረት የተመደቡ ለመሆኑ ክትትል በማድረግ እና የፍተሻ ውጤትም በታሪፍና በዋጋ ላይ የሚያመጣው ለውጥ በጥንቃቄ ሊታይ የሚገባው ሲሆን ያልተሰበሰበው ቀረጥና ታክስም ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በኦዲት አስተያየቱ መሰረት ያለውን ቀሪ ሂሳብ የሚሰበስቡ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ለ) <u>የትራንስፖርት እና የኢንሹራንስ ዋጋ በትክክል በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ላይ ባለመካተቱ ና ማስረጃ ባለመቅረቡ ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 1,124,643.99</u>

<u>ግኝት</u>

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ክፍል 4 ምዕራፍ 1 አንቀጽ 89 ንኡስ አንቀጽ 2 መሠረት ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገባ ማናቸውም ዕቃ የቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ የሚሆነው እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ በትክክል ለዕቃው የተከፈለ ጠቅላላ ወጪ መሆን እንዳለበት በሚያዘው መሰረት እንዲሁም በገቢ ዕቃዎች ጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/2008 አንቀፅ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ተጨማሪ ክፍያዎች በተጨባጭ ማስረጃና መረጃ ሊተመኑ ካልቻሉ ዕቃዎቹን እስከ ኢትዮጵያ የጉምሩክ ክልል የመጀመሪያ መግቢያ ድረስ ለማድረስ የተከፈለ የትራንስፖርት ዲክለር ተደርጎ ተቀባይነት ባገኘ የዕቃው ኤፍ ኦ ቢ ዋጋ ላይ 5% ፣ የመጫኛ የማራገፊያና የመንከባከቢያ ወጪዎችና ክፍያዎች ዲክለር በተደረገ የእቃው ኤፍ ኦ ቢ ዋጋ 5% እና የኢንሹራንስ ወጪ ዲክለር ተደርጎ ተቀባይነት ባገኘ የዕቃው ኤፍ ኦ ቢ ዋጋ ላይ 2% በማስላት በቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ ይካተታል በሚለው መሰረት ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፡-

በቃሊቲ አዲስ አበባ ጉምሩክ	ብር	358,529.14
በኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	“	524,087.38
የድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	“	13,957.28
በሞጆ ቅ/ጽ/ቤት፡	“	228,070.19
በድምሩ	ብር	1,124,643.99

ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ መኖሩን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

ለቀረጥ ማስከፈያነት መካተት ያለበት ወጪ በትክክል የማይካተት እና ማስረጃዎች የማይቀርቡ ከሆነ መንግስት ከገቢ ዕቃዎች ሊሰበስብ የሚገባውን ቀረጥ እና ታክስ ሳይሰበስብ ሊቀር ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ዋጋን እና መረጃዎችን በማጣራት ስራ ላይ ያሉ ሰራተኞች መረጃዎችን በተገቢው መንገድ ሊያጣሩ የሚገባ ከመሆኑም በተጨማሪ ያልተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ ከሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ የሚወስዱ መሆን ገልጸዋል፡፡

ሐ) **ዕቃዎች በጊዜያዊነት የሚቆዩበት የጊዜ ገደብ ቢጠናቀቅም ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር233,826,109.48 እንዲሁም ሰነዳቸው ያልተገኘ የዋስትና ሂሳብ ብር 52,972,176.14**

ግኝት

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 ምእራፍ 11 አንቀጽ 73 ንኡስ አንቀጽ ከ1-5 በተገለጸው መሰረት በጊዜያዊነት የገቡ እቃዎች አገር ውስጥ የሚቆዩበት ጊዜ ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ቆይተው የጊዜ ገደቡ ውስጥ ተመልሰው ከአገር መውጣት እንዳለባቸው እና ንኡስ አንቀጽ 6 መሰረት ዕቃው አገር ውስጥ የሚቆይበት ጊዜ ካልተራዘመ በስተቀር በህግ የተወሰነው የመቆያ ጊዜ እንደተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ዕቃው ተመልሶ ከአገር ካልወጣ በዋስትና ያስያዘው ገንዘብ በሙሉ ለመንግስት ገቢ ተደርጎ እቃው ላይ ተገቢው የጉምሩክ ሮርማሊቲ ተከናውኖበት አገር ውስጥ ሊቀር ወይም ሊወጣ ይችላል በሚለው መሰረት ወደ አገር በጊዜያዊነት በሚገቡ እቃዎች ላይ ተገቢው ቁጥጥር የሚደረግ መሆኑን እና በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ተመልሰው ከአገር የሚወጡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	ብር	27,827,561.50
በሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	“	7,731,504.26
የድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	“	2,725,648.81
አዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	“	190,707,282.99
በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት፡	“	4,834,112.12
በድምሩ	ብር	233,826,109.48

ዕቃዎች በጊዜያዊነት የሚቆዩበት የጊዜ ገደብ ቢጠናቀቅም ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ፣ እንዲሁም በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ሰነዳቸው ያልተገኘ የዋስትና ሂሳብ ብር 52,972,176.14 መኖሩን ከየስራ ክፍሉ ከተያዘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

በዋስትና የተያዘዉ ገንዘብ ባለመሰብሰቡ ምክንያት መንግስት ሊያገኘው የሚገባውን ገቢ ሊያሳጣው ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ቅ/ጽቤቱ ያልተሰበሰበውን ገንዘብ እንዲሰበሰብ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡

መ) **ከድህረ እቃ አወጣጥ፣ ከኢንቨስትሜሽን አዲት ሪፖርት እና በደንብ መተላለፍ ውሳኔ መሰረት ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 837,112,120.00 ፣**

ግኝት

በጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ እዳ የክፍያ ጊዜ ስምምነት መመሪያ ቁጥር 69/2004 አንቀጽ 7 ተራ ቁጥር 1 እና 2 መሰረት የቀሪ ቀረጥና ታክስ የውሳኔ ማስታወቂያ የደረሰው ባለ እዳ በ30 ቀናት ውስጥ እዳውን መክፈል ወይም ለመክፈል ከስምምነት መድረስ እንዳለበት ነገር ግን በውሳኔ ማስታወቂያው ላይ ቅሬታ ያለው ባለእዳ ውሳኔው በደረሰው 15 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለባለስልጣኑ ማቅረብ እንደሚችል ይህንን በማይፈጽም ላይ የንብረት መያዝ ስርአት ተፈጻሚ እንደሚሆንበት ይደነግጋል፡፡ በዚሁ መሰረት ቅ/ጽ/ቤቶች ያልተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ እንዲሰበሰብ የሚያደረጉ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	ብር	696,790,059.42
የጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	“	19,539,750.64
የኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	“	19,022,695.59
የድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	“	3,560,680.76

አዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	“	46,984,446.71
ከሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	“	9,338,972.02
ከባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት	“	4,171,944.78
ከአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት	“	37,703,570.08
በድምሩ	ብር	837,112,120.00

የተለያየ እድሜ ያላቸው ከድህረ እቃ አወጣጥ፣ ከኢንቨስትጌሽን ኦዲት ሪፖርት እና በደንብ መተላለፍ ውሳኔ መሰረት ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ መኖሩ ታውቋል፡፡

ስጋት

የገቢ አሰባሰብና ዋስትና ሂሳቦች ቡድን በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ቡድን ውሳኔ መሰረት የቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ ያለባቸውን አስመጪዎች ዝርዝር በመያዝ ዕዳቸውን እንዲከፍሉ የማይከታተል ከሆነ የመንግስት ገቢ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በውሳኔው መሰረት ዕዳቸውን ለመክፈል ፈቃደኛ ባልሆኑ አስመጪዎች ላይ በመመሪያ መሰረት የንብረት መያዝ ስነ-ስርዓቱ ተፈጻሚ እንዲሆን ዝርዝሩን ለንብረት ያዥ ኮሚቴ በማስተላለፍ ያልተሰበሰበው ግብር ከሚመለከታቸው ግብር ከፋዮች ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች በተለያየ ደረጃ እርምጃ እየወሰዱ መሆኑንና አሁንም ክትትል እየተደረገ መሆኑን፣ በተጨማሪም ከቅ/ጽቤቶቹ በድምሩ ብር 748,516,622.1 ባለእዳዎች ለዋናው መ/ቤት አቤቱታ አቅርበው በሂደት ላይ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

ሠ) ለኢንቨስትመንት ከቀረጥ ነጻ ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ ዕቃዎች የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈፃፀም በተመለከተ

ግኝት

በኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2004 አንቀፅ 30 ንዑስ አንቀፅ 2ሀ ላይ ኤጀንሲው እንደ አግባቡ የሚመለከታቸውን የፌዴራል መንግስት ወይም የክልል መንግስታት አስፈፃሚ አካላትን በመወከል ለተሰማሩበት የኢንቨስትመንት ዘርፍ አስፈላጊ የሆኑ

ግብአቶችን ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ የመሆን ማበረታቻ የመፍቀድ እንዲሁም ይህንኑ አዋጅ ለማስፈፀም በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 270/2005 አንቀፅ 13 ላይ የካፒታልና የግንባታ ዕቃዎች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ስለመሆን በሚለው ከንዑስ አንቀፅ 1-4 ድረስ በተዘረዘሩት መሰረት የኢንቨስትመንት የቀረጥ ነፃ የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አሰራር ላይ ክትትል እየተደረገ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

<u>በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>

- እያንዳንዱ አስመጪ ድርጅት ከቀረጥ ነፃ ዕቃዎችን በሚያስገባበት ወቅት የኢንቨስትመንት ኤጀንሲ የተጠቀሱትን ዕቃዎች ከቀረጥ ነፃ ለኢንቨስትመንት እንዲገቡ ደብዳቤውን በቀጥታ ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የሚጽፍ በመሆኑ እና በዋና መ/ቤት የሚገኘው የኢንቨስትመንት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት አውቆት ክትትል የማይደረግበት መሆኑ፣
- አስመጪ ድርጅቶች ዕቃዎችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባት ሲጀምሩ በሚያስገቡበት የጉምሩክ ጣቢያ ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሊያስገባ የተፈቀደለትን የዕቃዎችን ብዛትና ዓይነት ለማወቅ የሚያስችል አሰራር የሌለ መሆኑ፣
- ከአንዳንድ የተሰረዙ የኢንቨስትመንት ፍቃዶች እና የህግ ማስከበር ሂደቶች ለመረዳት እንደተቻለው ባለሀብቱ ከቀረጥ ነፃ ያስገባውን ዕቃ ለታለመለት የኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ስራ በትክክል ስለማዋሉ፣ በስራ ላይ ስለመሆኑ፤መብቱን ያለአግባብ አለመገልገሉን፤ እንዲሁም የኢንቨስትመንት ፍቃዱ ሲሰረዝ የሚፈለግበትን ቀረጥና ታክስ ለማስከፈል እንዲቻል እና ግዴታዎቹን ሳይወጣ ከሀገር እንዳይወጣ የቅርብ ጊዜ ትክክለኛ አድራሻ በመያዝ ቁጥጥሩን ሊያጠናክር የሚችል የተቀናጀ የባለድርሻ አካላት ትክክለኛና ወቅታዊ የሆነ መረጃ የመቀባበል ልምድ እና አሰራር የሌለ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

ከቀረጥ ነፃ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ ተገቢው ክትትል የማይደረግባቸው ከሆነ ወደ አገር የገቡት ዕቃዎች ለታለመለት አላማ እንዳይውል የሚያደርግ እና ለብልሹ አሰራር በር የሚከፍት ሊሆን ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የጉምሩክ ጣቢያ ወይም ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ሊያስገባ የተፈቀደለትን የቀረጥ ነፃ ዕቃዎችን ብዛትና ዓይነት ለማወቅ የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት እና ለታለመለት አላማ መዋሉን ትክክለኛ አድራሻ በመያዝ ቁጥጥሩ በዋና መ/ቤት የሚገኘው የኢንቨስትመንት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት በኩል ክትትል ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

ረ) <u>የጉምሩክ ዋጋ ዝርዝር መግለጫ</u> /VDD/ <u>ላይ የተሞላው መረጃ ከዲክላራሲዮኑ ጋር ተያይዞ ያልቀረበ ስለመሆኑ

<u>ግኝት</u>

በገቢ ዕቃዎች ጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ማስከፈያ ዋጋ አተማመን መመሪያ ቁጥር 111/2008 **አንቀጽ** 24 **ንኡስ አንቀጽ** 1 **መሠረት የጉምሩክ ዋጋ በትክክል ለመወሰን እንዲቻል ዲክላራሲዮን አቅራቢው በአዋጁ አንቀጽ** 10/1 **መሰረት የገቢ እቃዎችን አስፈላጊ መረጃዎችን በመሙላት፣ በማያያዝ እና ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለበት በሚለው መሰረት መሰራቱን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-**

<u>በጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u> ፣

ብዛታቸው 12 **የሆኑና ብር** 7,462,107.95 **ቀረጥና ታክስ የተከፈለባቸው ዲክላራሲዮኖች ላይ በተገለጸው ሙሉ ዝርዝር መግለጫ መሰረት በደጋፊ ሰነድነት መቅረብ ካለባቸው ማስረጃዎች ውስጥ የጉምሩክ ዋጋ ዝርዝር መግለጫ** /VDD/ **ያልቀረበ በመሆኑ በማስረጃው መሰረት ቀረጥና ታክሱ የተከፈለ ስለመሆኑ ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡**

<u>ስጋት</u>

በመመሪያው መሠረት ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ ማናቸውም ዕቃዎች ላይ የጉምሩክ ዋጋ በዝርዝር መግለጫ /VDD/ **ከዲክላራሲዮኑ ጋር ተያይዞ የማይቀርብ ከሆነ ትክክለኛ ቀረጥና ታክሱ ተሰልቶ እንዳይከፈል ሊያደርገው ይችላል፡፡**

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የገቢ እቃዎችን አስፈላጊ መረጃዎችን በመሙላትና ለዋጋ አተማመን መረጃ፣ ማስረጃዎች ሙሉ ዝርዝር በማያያዝና ትክክለኛነታቸውን በማረጋገጥ የጉምሩክ ዋጋ መግለጫ (Valuation details declaration)/VDD/ **ከዲክላራሲዮኑ ጋር ተያይዞ እንዲቀርብ ሊደረግ**

የሚገባ ሲሆን የ12 ዲክላራሲዮኖች በጉምሩክ ዋጋ ዝርዝር መግለጫ /VDD/ መሰረት የተከፈለው ቀረጥና ታክስ ትክክለኛነቱ በውስጥ ኦዲት ተረጋግጦ ሊገለጽልን ይገባል ፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

የጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

በመመሪያው መሰረት ተሞልቶ እንደሚቀርብ መሆኑና ለናሙና የተመረጡ ሰነዶች ቅ/ጽ/ቤታችን የVDD እና የECVS አሰራር ከመጀመሩ በፊት የተሰሩ ስለሆነ የVDD ቅጽ ያልተያያዘው በዚህ ምክንያት በመሆኑ፤በኦዲት አስተያየቱ መሰረት እንደሚሰሩ ገልጸዋል፡፡

ሰ) <u>ሳይፈቀድ የገባ ያገለገለ ልብስ ማጠቢያ /USED LAUNDARY MACHIN /ውሳኔ ሳያገኝ ረዥም ጊዜ ያስቆጠረ መሆኑ</u>

<u>ግኝት</u>

የጉምሩክ ቀሪ ቀረጥና ታክስ ዕዳ የክፍያ ጊዜ ስምምነት መመሪያ ቁጥር 69/2004 አንቀጽ 4(1) መሰረት ለመንግስት መከፈል የነበረበት ቀሪ ቀረጥና ታክስ ከተገኘ የገንዘቡን መጠን የሚገልጽ የውሳኔ ማስታወቂያ ለባለ ዕዳው ወይም ለወኪሉ በጽሑፍ እንዲደርሰው በማድረግ ቀሪ ሂሳቡን መሰብሰብ እንዳለበት በሚያዘው መሰረት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

<u>በጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>

በቀን 24/11/2007 በዲ/የን ቁጥር C-1016/2015 በአቶ ሀሰን መሃመድ አስመጪ ድርጅት ስም ያገለገለ የልብስ ማጠቢያ ማሽን/USED LAUNDARY MACHIN/ በህጉ መሠረት ሳይፈቀድለት ያለ አግባብ ማስገባቱን መስከረም 28/2008 በተጻፈ ደባዳቤ ቁጥር 11.2.7/4266/08 የተገለጸ ቢሆንም፤ ንብረቱ ያለ አግባብ በመግባቱ በህግ አግባብ ጉዳዩ ተቋጭቶ መሰብሰብ ያለበት ቀረጥና ታክስ ሳይሰበሰብ ከአንድ ዓመት በላይ በጽ/ቤቱ መጋዘን የሚገኝ መሆኑ ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

ተገቢው ውሳኔ በወቅቱ እንድሰጥ ክትትል የማይደረግ ከሆነ ጉዳዩ ውሳኔ ባለማግኘቱ የግብር እዳው ሳይሰበሰብ ሊቀር ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠት ውሳኔ እንዲያገኝ ሊያደርግ ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

የጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ዕቃው ዲክለር ከተደረገው ተጨማሪ ዕቃ አለ በሚል ልዩነት የተገኘ ሲሆን እንደ ማንኛውም የንግድ ማጭበርበር ጉዳዩ ለህግ ተላልፎ አስመጪው መጠየቁንና የዘገየበት ዋነኛ ምክንያት ግን አስመጪው በአገር ውስጥ ባለመኖሩ ውሳኔ ሳያገኝ ሊጎተት ችሏል በማለት ገልጸዋል፡፡

ሸ) <u>ከቀረጥ ነፃ ገብተው ለታለመለት አላማ ባለመዋሉ ተይዘው ስለሚገኙ ንብረቶች ግኝት</u>

- አስመጪ ድርጅቶች ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ያስገቧቸውን ዕቃዎች በትክክል ለታለመለት አላማ ባለመዋሉ ተወርሰው በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስር ያሉ ንብረቶች ምዝገባ ተከናውኖላቸው በበቂ ጥበቃ ተቀምጠው ክትትል የሚደረግባቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

<u>በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>

- የተለያየ ዲያሜትር ያላቸው 2,026,260 ኪሎ ግራም ብረቶች በግቢው ውስጥ ለቁጥጥር አመቺ ባልሆነ መልኩ በሜዳ ላይ ተበትነው የሚገኙ መሆኑን፣
- ንብረቶቹ ሲገቡና ሲወጡ በንብረት መዝገብ ላይ ተመዝግበው ቁጥጥር እየተደረገባቸው አለመሆኑን፣
- ንብረቶቹን በኃላፊነት ተረክቦ የሚቆጣጠረው አካል የሌለ መሆኑን በቀረበው ማስረጃ መሰረት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

- የንብረት ተቆጣጣሪ ሳይጠበቅ እና ምዝገባ ሳይደረግባቸው በሜዳ ላይ ተበታትነው የሚገኙ ንብረቶች ለጥፋት፣ ለብልሽት እና ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- **የተወረሱ ንብረቶች ተመዝግበው በንብረት ክፍል በኩል ጥበቃ ሊደረግላቸው የሚገባ ከመሆኑም በተጨማሪ ለቁጥጥር አመቺ በሆነ ቦታ የማስቀመጥ ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፡፡**

ቀ) <u>ለኦዲት ስራ ተፈልገው ለኦዲት ያልቀረቡ ዲክላራሲዮኖች በመኖራቸው የተሰበሰበው ቀረጥና ታክስ ብር 6,810,162.82 ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ</u>፡-

<u>ግኝት</u>

- **በፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት አዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 17/1/ መሰረት የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኦዲተሮች ወይም የፌደራል ዋና ኦዲተር ወኪሎች ለምርመራ ጠቃሚና አሰፈላጊ የሚመስሏቸውን መጻህፍት መዘክሮች፣ መዝገቦች፣ ሰነዶች እና ሌሎች የጽሁፍና የቃል መረጃዎችን ሁሉ ሲጠየቁ የተጠየቀው ግለሰብ፣ ሰራተኛ ወይም ባለስልጣን በትክክልና በተሟላ መልኩ ወዲያውን ማቅረብ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ በባለስልጣን መ/ቤቱ ስር ያሉትን ቅ/ጽ/ቤቶችን ኦዲት ሲደረግ፡-**

በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት፡- በ11 ዲክላራሲዮኖችን የተሰበሰበ ብር 5,509,774.4

በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት፡- በ147 የተሰበሰበ ብር <u>1,300,388.42</u>

በድምሩ <u>ብር 6,810,162.82</u>

የተሰበሰበባቸው 158 ዲክላራሲዮኖች ለኦዲት ተጠይቀው ያልቀረቡ በመሆኑ፤በነዚህ ዲክላራሲዮኖች የተሰበሰበውን ቀረጥና ታክስ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

<u>ስጋት</u>

ለምርመራ የተፈለጉት ሰነዶች በወቅቱ ካልቀረቡ የሂሳባቸውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም በሂሳቡ ላይ ማጭበርበር ተፈጽሞ ሊሆን ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ለኦዲት ያልቀረቡ ፋይሎች በቀላሉ ለማግኘት በሚያስችል መልኩ በአግባቡ ተደራጅተው መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ለኦዲት ሊቀርቡ ያልቻሉ ሰነዶችም ተፈልገው በውስጥ ኦዲት ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ ውጤቱ ሊገለጽልን ይገባል፡፡

በ) **በአስመጪዎች የሚቀርብ አቤቱታ በቅ/ጽ/ቤቶች ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በወቅቱ ውሳኔ ሳያገኝ የቆየ ቀረጥና ታክስ ብር** 6,299,180.07**መኖሩ**

ግኝት

የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል አሰራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 107/2007አንቀጽ 20/1/ሀ-ሐ/ በተዘረዘሩት የጊዜ ገደብ መሰረት ሂደቱን ጠብቆ ቅሬታው ውሳኔ መሰጠት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስር የሚገኙ ተገልጋዮች በድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲትና በፈደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የኦዲት ግኝቶች ላይ የተወሰነባቸውን ሂሳብ በመቃረን የሚያቀርቧቸውን ቅሬታዎች በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ስለመታየታቸውና ወቅቱን ጠብቆ ውሳኔ ስለመሰጠቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት፡ ሶስት ድርጅቶች/ተገልጋዮች/	ብር	411,543.17
በድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የ4 ድርጅቶች	ብር	5,887,636.90
በድምሩ	ብር	6,299,180.07

እዳ ያለባቸው ድርጅቶች ቅሬታቸው በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ወቅቱን ጠብቆ ያልታየላቸው በመሆኑ የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ሊሰበሰብ ያልቻ ለመኖሩ ለማወቅ ተችሏል፡

ስጋት

ጉዳዩ በጊዜ እልባት ካላገኘ መሰብሰብ የሚገባው ገቢ በወቅቱ ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ከላይ በግኝቱ ላይ በተመለከቱት ቅሬታዎች ላይ አፋጣኝ የመፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድ ሆኖ ለወደፊቱ ለአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የሚቀርቡ የቀረጥና ታክስ ቅሬታዎች በተቀመጠላቸው ቀነ ገደብ ውሳኔ በመስጠት ገቢው ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

ተ) **በፍተሻ ተይዞ ያለአግባብ የተለቀቀ የውጭ ምንዛሪ ብር** 4,876,186.20**ና** 4.336 **ኪ.ግ ወርቅ መኖሩን በተመለከተ**

ግኝት

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 መሰረት የጉምሩክ ዲክላራሲዮን አፈጻጸም ለመወሰን በወጣው መመሪያ ቁጥር 118/2008 አንቀጽ 15(1-5) እንዲሁም በብሄራዊ ባንክ ማቋቋሚያ

አዋጅ ቁጥር 591/2008 ክፍል 5 ቁጥር18(2) መሰረት ማንኛውም መንገደኛ ወደ ሀገር ሲገባ የያዘው የውጭ ምንዛሪ የኢትዩጲያ ብሄራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ከተፈቀደው መጠን በላይ ከሆነ ባለስልጣኑ ባዘጋጀው ዲክላራሲዮን ላይ መመዝገብ እንደሚኖርበት እና ተመልሶ ለመውጣት ሲፈልግ ገንዘቡን ያስመዘገበበት ዲክለራሲሆን ካላቀረበ በስተቀር መልሶ ለማውጣት እንደማይችል ይገልጻል፡፡ ይህንኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት፡-

- በውጭ ዜጎች ባለቤትነት በቀን 22/05/2008 የውጭ ምንዛሬ በዩሮ 211,220.00 እና በዶላር 1,700.0 በወቅቱ ባለው የሀገር ውስጥ ምንዛሬ ሲመነዘር ብር 4,876,186.20 እና 4.336 ኪ.ግ ወርቅ ሊወጣ ሲል በፍተሻ የተያዘው የግለሰቦቹ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሳይኖር እና የገንዘቡ ህጋዊነት በአግባቡ ሳይረጋገጥ ለግለሰቦቹ እንዲመለስ የተደረገ መሆኑን፣

<u>ስጋት</u>

በውጭ ዜጎች ባለቤትነት ወደ ሀገር ውስጥ ገባ ተብሎ ተመላሽ የተደረገው የውጭ ምንዛሪና ወርቅ ምናልባት ከሀገር ውስጥ ገበያ የተገኘ ሊሆን ይችላል፡፡ እንደዚሁም ህገ ወጥ የገንዘብ ዝውውርን የሚያበረታታ ሊሆን ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በአዋጅ እና በመመሪያ በተቀመጠው መሰረት መሰራት ይኖርበታል፡፡ እንደዚሁም በቂ ምክንያት እና መረጃ ሳይቀርብ ተመላሽ መደረጉ አግባብ ባለመሆኑ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት፡-

- ስለጉዳዩ ከባለስልጣኑ ጽ/ቤትና ከብሔራዊ ባንክ የተለያዩ መጻጻፊያ ደብደቤዎች የቀረቡና/የታዘዙ፣ በክፍያው ላይ ልዩነት ለተፈጠረው ለዋና ዳይሬክተር ሪፖርት የተደረገበት እና ሌሎችም ሰነዶች የተያያዙ መሆኑን በሰጡት ምላሽ የገለጹ ሲሆን፣ በተጨማሪም በመውጫ ውይይት ጊዜ በተሰጠው ምላሽ የውጭ ምንዛሬ በዶላር 2,360,460.00 በተመለከተ ከባለስልጣኑ ኃላፊዎች በተጻፈ ደብዳቤ ብቻ ሳይሆን ውሳኔው የተላለፈው ከናይጀሪያ ኤምባሲና ከውጭ ጉዳይ ሚ/ር በተጻፈው ደብዳቤ

መሰረት ጉዳዩን በተወሰነ ደረጃ ያየንበት ሁኔታ ያለ በመሆኑ፤ ህግ መጣሱ ትክክል እንዳልሆነ፣ ገንዘቡም የግለሰቡ ስለመሆኑ የማጣራት ስራ ተሰርቶ በተወሰኑ መረጃዎች የውጭ ምንዛሬው የኢትዮጲያ ያለመሆኑን የተጣራ መሆኑ የሀገራችንን ገጽታ ስለሚያበላሽ እና በአየር መንገዳችን ላይ ተጽዕኖ ስለሚፈጥር ተብሎ ምንዛሬው እንዲመለስ የተወሰነ መሆኑን በመውጫ ውይይት ወቅት በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡ በቀን 22/05/2008 የውጭ ምንዛሬ በዩሮ 211,220.00 እና በዶላር 1,700.0 እና 4.336 ከ.ግ ወርቅ በተመለከተ ግን የተገለጸ ሁኔታ የለም ፡፡

<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ከላይ በተገለጸው አዋጅ እና መመሪያ መሰረት ማንኛውም መንገደኛ ወደ ሀገር ሲገባ የያዘውን የውጭ ምንዛሬ በኢትዮጲያ ብሄራዊ ባንክ ከተፈቀደው መጠን በላይ ከሆነ ማስመዝገብ የሚኖርበት በመሆኑ፤ ግለሰቦች ወደ ሀገር ይዘው የገቡት የውጪ ምንዛሬ ከተፈቀደው በላይ በመሆኑና ገንዘቡ ለግለሰቦቹ ተመላሽ የተደረገበት ሁኔታ በኛ አስተያየት በበቂ ማስረጃ ባለመደገፉ ከአዋጁ እና መመሪያው አንጻር ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ምላሻቸውን አልተቀበልነውም፡፡

ቸ) <u>ለዋናው መ/ቤት ቅሬታ አቅርበው በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ያልተሰጠበት አቤቱታ ግኝት</u>

የጉምሩክ ጉዳዮች አቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል አሰራርን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 107/2007አንቀጽ 20/1/ሀ-ሐ/ እና 2/ሀ-ሠ/ በተዘረዘሩት የጊዜ ገደብ መሰረት ሂደቱን ጠብቆ ቅሬታው ውሳኔ መሰጠት እንደለበት ይደነግጋል፡፡ ይሁን እንጂ በባለስልጣን ቅ/መ/ቤቶች ስር የሚገኙ ተገልጋዮች በተለያየ ጊዜ የተወሰነባቸውን ሂሳብ እና የውርስ ሂደት በመቃረን የሚያቀርቧቸውን ቅሬታዎች በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ስለመታየታቸውና ወቅቱን ጠብቆ ውሳኔ ስለመሰጠቱ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፤ 148 ድርጅቶች/ተግልጋዮች/ በመመሪያው መሰረት ቅሬታቸው በወቅቱ ባለመታየቱ ወይም ውሳኔ ባለመሰጠቱ ከ14/01/2007 እስከ 26/04/2009 የቆየ መሆኑ ታውቋል፡፡፤

<u>ስጋት</u>፡-

ጉዳዩ በጊዜ እልባት ካላገኘ መሰብሰብ የሚገባው ገቢ በወቅቱ ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በተገልጋዮች/ድርጅቶች/ ለአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የሚቀርቡ የቀረጥና ታክስ እንዲሁም የውርስ ሂደቶች በቅሬታቸው መሰረት አፋጣኝ የመፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድ በማድረግ በተቀመጠላቸው ቀነ ገደብ ውሳኔ በመስጠት ገቢው ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- 135 አቤቱታዎች የመንግስት ልዩ ውሳኔ የሚጠብቁ በመሆኑ በጽ/ቤቱ የሚሰጣቸው ውሳኔ የለም፡፡ የማጣራት ስራ እያከናወንባቸው አይደለም፤
- ቀሪዎቹ 13 አቤቱታዎች ብቻ በወቅቱ ምላሽ ያልተሰጣቸው ሲሆን ምክንያቱም ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል መረጃ ከቅ/ጽ/ቤቶችና ሌሎች የመረጃ ምንጮች በወቅቱ ባለመድረስ ነው በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

1.2 **<u>የሀገር ውስጥ ገቢ በተመለከተ</u>**

ሀ) <u>ያልተሰበሰበ የአክሰዮን ትርፍ ድርሻ ገቢ ግብር ብር</u> 884,062.13 **<u>መኖሩ</u>**

<u>ግኝት</u>

በየቅ/ፅ/ቤቶች ያሉ ግብር ከፋዮች ሐምሌ 30/2005 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ገ/ኢ/1/2/3 የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ባወጣው የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ክፍፍል ግብር *መመሪያ* አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ 3.4 መሰረት ከ2006 በጀት ጀምሮ ኩባንዮች ያገኙትን ትርፍ ለባለአክሲዮኖች ያከፋፈሉ ወይም የኩባንያውን ካፒታል መዋጮ ለማሳደግ ያዋሉ መሆኑን የሚገልጽ ሪፖርት እና ይህን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ከሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ለገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት እንዲያቀርቡ በሚያዘው መሰረት ማስረጃው መቅረቡን እንዲሁም ከባለስልጣን መ/ቤቱ በቀን 20/12/2005 በደብዳቤ ቁጥር 6.1.0/1776/61 አንቀጽ መ በተገለጸው መሰረት በ 12 ወራት ጊዜ ውስጥ የትርፍ ድርሻውን ለባለ አክሲዮኖች አከፋፍለው ግብር ያልከፈሉ ወይም ለካፒታል ማሳደጊያ ማዋላቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ያላቀረቡ ኩባንያዎች/ባለአክሲዮኖች ያገኙትን የትርፍ ድርሻ ለባለአክሲዮኖቹ እንዳከፋፈሉ ተቆጥሮ ግብሩን መክፈል እንዳለባቸው ስለሚያዝ ቅ/ጽ/ቤቶቹ በዚህ መመሪያ መሰረት እየሰሩ መሆኑ ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፤በመመሪያ መሰረት ያገኙትን ትርፍ የኩባንያውን ካፒታል መዋጮ ያሳደጉ ስለመሆኑ ከሰነዶች ምዝገባና ማረጋገጫ ጽ/ቤት የቀረበ ማስረጃ በፋይላቸው ውስጥ ባለመገኘቱ፤

በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ቅ/ጽ/ቤት ከ4 ግብር ከፋዮች	ብር	259,513.51
በኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	“	262,249.07
በጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት_16 ግብር ከፋዮች	“	77,287.73
በባህር ዳር ቅ/ጽ/ቤት፡-ዘጠኝ (9) ግብር ከፋዮች	“	285,011.82
በድምሩ	ብር	884,062.13

ያልተሰበሰበ የአክስዮን ትርፍ ድርሻ ገቢ ግብር መኖሩ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት

ተሻሽሎ በወጣው መመሪያ መሰረት ግብር ከፋዮች ያገኙትን ትርፍ አክሲዮኑን ለማሳደጊያ ወይም አባላቶቹ ክፍፍል ስለማድረጋቸው የሚገልጽ ማስረጃ ከሚመለከተው አካል ስለማቅረባቸው ክትትል የማይደረግ ከሆነ መንግስት ከትርፍ ገቢ ግብር የሚያገኘውን አስር በመቶ ሊያጣ ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

ቅ/ጽ/ቤቶቹ መመሪያው ባስቀመጠው የአክስዮን ትርፍ ድርሻ ገቢ ግብር የጊዜ ገደብ መሰረት ግብር ከፋዮች ያልከፈሉትን ግብር ወለድ እና ቅጣት ታክሎበት ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ለአብዛኞቹ ድርጅቶች የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ የወጣላቸው ሲሆን፣ ሌሎቹ በቀጣይ የሚታይና መሰብሰብ ያለበት የሚሰበሰብ ይሆናል በማለት ገልጸዋል፡፡

ለ) **ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች በመቀነሳቸው ፣ ያላግባብ የተካካሰ ንግድ ትርፍ በመኖሩ፣ መያዝ ያለበት ገቢ ባለመያዙ እና በእርጅና ቅናሽ ስህተት ምክንያት ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ ግብር ብር** 1,981,696.80 **መኖሩ**

ግኝት

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀፅ 21 ንኡስ አንቀጽ (1) ሀ-ኘ በተገለጸው መሰረት ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች አለመቀነሳቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ

በምስራቅ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	ብር	241,347.55
በኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	“	19,600.40
አዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	“	797,872.80
በባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት	“	17,757.19
በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	“	14,018.12
በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት	“	891,100.74
በድምሩ	ብር	1,981,696.80

ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች በመቀነሳቸው ፣ ያላግባብ የተካካሰ ንግድ ትርፍ በመኖሩ፣ መያዝ ያለበት ገቢ ባለመያዙ እና በእርጅና ቅናሽ ስህተት ምክንያት ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ ግብር መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

<u>ስጋት</u>

ግብር ከፋዮች ሊቀነስ የማይገባቸውን ወጪዎች በመቀነሳቸው፣ ያላግባብ የተካካሰ ንግድ ትርፍ በመኖሩ፣ መያዝ ያለበት ገቢ ባለመያዙ ከግብር ሊገኝ የሚገባውን ገቢ ሊያሳጣው ከመቻሉም ባሻገር ግብር ከፋዮች በትክክል ግብራቸውን እንዳይከፍሉ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሣብ</u>

ቅ/ጽ/ቤቶች ያልተሰበሰበውን የንግድ ትርፍ ግብር ቅጣትና ወለድ ታክሎበት ሊሰበሰብ የሚገባ መሆኑን እና በቀጣይም ይህ አሰራር እንዳይደገም ክትትል ሊያደርጉ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ክትትል እንደሚያደርጉና ከዕርዳታ ጋር ከተያያዘው በስተቀር ያልተሰበሰበውን የንግድ ትርፍ ግብር እንደሚሰበስቡ ገልጸዋል፡፡

መ) 11 <u>ግብር ከፋዮች ወርሃዊ ኤክሳይስ ታክስ እና የተርን ኦቨር ታክስ ስለማሳወቃቸውም ሆነ ታክሳቸውን ስለመክፈላቸው ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ</u>

<u>ግኝት</u>

የኤክሳይዝ ታክስ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 610/2001 አንቀፅ 2ለ ግብር ከፋዩ ታክሱን በሚገባ ለመሰብሰብ አስፈላጊ የሚሆነውን መረጃ የሚያሳይ መግለጫ ከግብር ባለስልጣኑ በሚሰጠው ቅጽ ላይ ሞልቶ በየ30 ቀኑ ለግብር ባለስልጣኑ በግንባር ቀርቦ ወይም ባለስልጣኑ በሚወክለው ሶስተኛ ወገን በኩል ወይም በኤሌክትሮኒክስ የመገናኛ ዘዴ የታክስ ማሳወቂያ በማቅረብ መክፈል የሚገባውን ታክስ ወዲያውኑ ገቢ ማድረግ እንዳለበት እና በተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/2002 አንቀጽ10/ንኡስ አንቀጽ 1/ሀ/ እና 2/ሀ/ መሰረት የተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ ግዴታ የሌለባቸው ግብር ከፋዮች በየወሩ እያንዳንዱ ግብር ከፋዮች በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለታክስ ባለስልጣን የተርን ኦቨር ታክስ ማሳወቂያ በማቅረብ እና የግብር ግዴታቸውን መወጣት እንዳለባቸው በሚደነግገው

እንዲሁም በቁጥር 3.0/146/05 በቀን 05/ሰኔ/2004 በወጣው ሰርኩላር አንቀጽ 2/ንኡስ አንቀጽ2/ መሰረት ንግድ ስራ ፈቃድ አውጥተው ወደ ስራ የተሰማሩ አዳዲስ ግብር ከፋዮች የንግድ ስራ ፈቃድ ካወጡበት ከቀጣዩ ወር ጀምሮ የግብር ግዴታቸውን መወጣት እንዳለባቸው በሚያዘው መሰረት መፈፀሙን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፡-

በድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣

- አራት (4) ግብር ከፋዮች የኤክሳይዝ ታክስ ግብራቸውን ስለማሳወቃቸውም ሆነ ስለመክፈላቸው በግብር ከፋዮቹ ሰነድ ውስጥ ማስረጃ ያልተገኘ መሆኑ፤

በጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣

- 7 ግብር ከፋዮች ከ1 ወር እስከ 1 ዓመት ከ 2 ወር ተርን ኦቨር ታክስ ያላሳወቁ መሆኑ

ታውቋል፡፡

<u>ስጋት</u>

አዋጁ እና በመመሪያው ላይ በተጠቀሰው ቀን ገደብ መሰረት ገቢያወቸውን የማያሳውቁ ከሆነ መንግስት ከታክስ ሊያገኝ የሚገባውን ገቢ ሊያሳጣው ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የኤክሳይስም ሆነ የተርን ኦቨር ታክስ ግብር ከፋዮች በአዋጁ ቀነ ገደብ መሰረት ታክሳቸውን እየከፈሉ መሆኑን ክትትል ሊደረግ የሚገባው ሲሆን ከላይ አላሳወቁም የተባሉት ላይ ቅጣትና ወለድ ታክለውበት እንዲከፍሉ መደረግ ይኖርበታል፡፡

ሠ) <u>በተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ ላይ በብልጫ ብር 791,195.26 ተቀናሽ ወይም ተመላሽ ተብሎ የተያዘ ስለመሆኑ</u>

<u>ግኝት</u>

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/94 አንቀጽ 27/1 እና 2 መሠረት ማንኛውም በግብር ከፋይነት የተመዘገበ ሰው የተመላሽ ገንዘብ ሲኖረው ለግብር አስገቢው ባለስልጣን በብልጫ የተከፈለውን ታክስ ከሚያሳይ የሰነድ ማስረጃ ጋር ማመልከቻ መጻፍ እንዳለበትና ባለስልጣኑም ተመላሽ መደረግ ያለበት መሆኑን አረጋግጦ ተመላሽ የሚሆነውን ገንዘብ ተመላሽ እንደሚያደርግ ይደነግጋል፡፡ በአዋጁ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማጣራት አዲት ሲደረግ፡-

በምስራቅ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት- በ 2 ግብር ከፋዮች	ብር	231,593.71
በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች በ1 ግብር ከፋይ	“	365,849.22
በጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት የ7 ግብር ከፋዮች	“	193,752.33
በድምሩ	ብር	791,195.26

በብልጫ በተመላሽ የተያዘ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት

ተመላሽ የሚደረጉ ሂሳቦች ትኩረት ተሰጥቶበት የሚዞር እና የማይቀናነስ ከሆነ ቅ/ጽ/ቤቱ ያልተገባ ተከፋይ ሂሳብ ክፍያ የሚዳረግ ከመሆኑም በተጨማሪ መንግስትን ላልተገባ ወጪ ሊዳርገው ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ የሚታየው የተመላሽ ሂሳብ ትኩረት ተሰጥቶ ትክክለኛው ሂሳብ መያዝ ያለበት መሆኑን እና በብልጫ የተያዘው ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል፡፡

ረ) የተጨማሪ እሴት ታክስንና እና የንግድ ትርፍ ግብር በወቅቱ የማያሳውቁ ግብር ከፋዮች መኖራቸው

ግኝት

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ 285/1994 ክፍል 7 አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ሀ እና ለ መሰረት እያንዳንዱ በተ.እ.ታ የተመዘገበ ሰው በአንድ የሂሳብ ጊዜ ውስጥ ታክስ የመክፈል ግዴታ ያለበት ቢሆንም ባይሆንም በእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ ሂሳቡን ለባለስልጣኑ ማስታወቅ እና ለእያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ የተሰጠውን የመጨረሻ ታክስ መክፈያ ጊዜ ገደብ ጠብቆ ታክሱን መክፈል እንዳለበት እንዲሁም በገቢ ግብር አዋጅ 286/94 አንቀጽ 66/1/ሀ/ እና በገቢ ግብር ለማስከፈል በወጣው ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ19/1 ና 2 መሰረት የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ቢኖርም ባይኖርም በየዓመቱ ለገቢ ሰብሳቢው መ/ቤት የሂሳብ እንቅስቃሴውን መረጃ ማቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በአዋጁ እና በደንቡ መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ተ.ቁ	ቅርንጫፍ ጽ/ቤት	የተ.እሴት ታክስ ያላሳወቁ ግብር ከፋዮች	ዓመታዊ ንግድ ትርፍ ያላሰወቁ ግብር ከፋዮች
1	በምዕራብአ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	2	8
2	በድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣	11	13
3	በጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፣	9	6
4	በምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች፣		71
5	በኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት		19
6	በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	5	2

በወቅቱ ያላሳወቁ በመሆኑ፣መከፈል የነበረበትን ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም ።።

ስጋት

ግብር ከፋዮች ገቢያቸውን በወቅቱ አሳውቀው ግብራቸውን እንዲከፍሉ ክትትል የማይደረግ ከሆነ መንግስት በወቅቱ ማግኘት የሚገባውን ገቢ እንዳያገኝ ያደርገዋል።። ለብልሹ አሰራርም በር ሊከፍት ይችላል።።

የማሻሻያ እርምጃ

ገቢያቸውን በወቅቱ እና በአግባቡ በማያሳውቁት ላይ በአዋጁ መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድባቸው መደረግ ይኖርበታል።። በግኝቱ የተጠቀሱት ግብር ከፋዮች የገቢ ማስታወቂያቸውን እንዲያቀረቡ በማድረግ ሰነዱ በውስጥ አዲት ተጣርቶ የሚሰበሰብ ገቢ ካለ እንዲሰበሰብ መደረግ ይኖርበታል።።

ሰ) ዓመታዊ ሂሳባቸውን ካሳወቁ ያልተሰበሰበ ገቢ ብር 31,154,339.07 መኖሩ

ግኝት

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 66 እና 86 መሰረት ማንኛውም የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋይ የግብር ዓመቱ በተጠናቀቀ በአራት ወር ጊዜ ውስጥ እንዲሁም የደረጃ "ለ" ግብር ከፋይ የግብር ዓመቱ በተጠናቀቀ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ገቢውን ለግብር አስገቢው ባለስልጣን ማሳወቅ እንዳለበትና የሚፈለግበትንም ግብር ገቢ ማድረግ እንዳለበት ይደነግጋል።። በመሆኑም ግብር ከፋዮች ዓመታዊ ገቢያቸውን አሳውቀው የግብር ግዴታቸውን የተወጡ መሆኑን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፡-

በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች

- **ሁለት ግብር ከፋዮች በድምሩ ብር** 31,154,339.07 **ሂሳባቸውን አሳውቀው ፣ነገር ግን ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብር መኖሩ ታውቋል፡፡**

<u>ስጋት</u>

ግብራቸውን በወቅቱ በማይከፍሉ ግብር ከፋዮች ላይ ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር የማይደረግ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሣብ</u>

እንቅስቃሴ እያደረጉ ያሉትን እና የማያደርጉትን ግብር ከፋዮች በመለየትና ክትትል በማድረግ ግብራቸውን በወቅቱ በማያሳውቁት ላይ ቅጣት እና ወለድ በማካተት ግብራቸውን እንዲከፍሉ ሊደረግ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የምዕራብ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት

- **አንድ ግብር ከፋይ በማእድን ማውጣት ስራ ላይ የተሰማራ ሲሆን ከታክስ ነጻ ነን የሚል ደብዳቤ ከገንዘብ ኢ/ት/ሚኒስቴር በማቅረቡ ሁኔታው በዋናው መ/ቤት ጭምር እየታየ መሆኑን እና እስካሁን ጉዳዩ ያልተቋጨ በሂደት ላይ ሲሆን ፣ድርጅቱ ነሐሴ** 24/2008 **ከህግ አግባብ ውጪ ግብር እንዲከፍል መደረጉ አግባብ አይደለም በሚል ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ደብዳቤ መቅረቡን ፣**

ሸ) <u>በንግድ ትርፍ ማሳወቂያ ላይ የታየው ጠቅላላ ሽያጭ በተጨማሪ እሴት ታክስ ላይ ካሳወቁት ልዩነት በመኖሩ ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ ብር</u> 24,571,487.76 **<u>እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር</u>** 3,240,009.01 **<u>መገኘቱ</u>**

<u>ግኝት</u>

ግብር ከፋዮች በ2007 **በጀት ዓመት በንግድ ትርፍ መግለጫ ላይ ያሳወቁት ጠቅላላ ሽያጭ በተጨማሪ እሴት ታክስ የ**12 **ወር ካሳወቁት ጠቅላላ ሽያጭ ጋር እኩል መሆኑን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፣**

የተጨማሪ እሴት ታክስ	የንግድ ትርፍ ግብር	
ምዕራብ አዲስ አበባ መ/ግ/ጉ/ቅ/ጽ/ቤት	21,746,060.89	409,712.32
ኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	484,922.53	50,450.98
የጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	1,716,961.81	2,182985.31
አዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	133,583.90	217,900.98
በባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት	18,182.18	378,959.42
በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	71,776.45	-
በድምሩ	24,571,487.76	3,240,009.01

ያልተሰበሰበ የንግድ ትርፍ ግብርና ታክስ መኖሩ ታውቋል፡፡

ስጋት

ግብር ከፋዮች ግብራቸውን ካሳወቁ በኋላ ገቢያቸውን በማሳወቂያ ቅጹ ላይ ሙሉ በሙሉ በትክክል እየሞሉ ያሳውቁ መሆኑን ክትትል ና ቁጥጥር ካልተደረገ ነ መንግስት ከግብር ሊያገኝ የሚችለውን ገቢ ሊያሳጣው ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

የማሻሻያ እርምጃ

ያልተሰበሰበው ሂሳብ አፋጣኝ እርምጃ በመውሰድ መሰብሰብ ይኖርበታል፡፡

ቀ) በዜድ ሪፖርት እና በተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ መካከል በታየ የሽያጭ ልዩነት ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 1,958,039.51 **መኖሩ**

ግኝት

ግብር ከፋዮች ባቀረቡት የየወሩ ተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ ላይ የተመለከተው ጠቅላላ ሽያጭ በዓመቱ Z-Report ላይ በታየው ሽያጭ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፡-

ምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	ብር	1,929,272.12
በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	“	28,767.39
በድምሩ	ብር	ብር 1,958,039.51

ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ መኖሩ ታውቋል፡፡

ስጋት

በዕቅዱ መሰረት ይሰበሰባል የተባለውን ግብር ከማሳነሱም በተጨማሪ መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ግብር ሊያሳጣው ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

የስራ ሂደቱ ያልተሰበሰበውን የተጨማሪ እሴት ታክስ ቅጣት እና ወለድ አክሎበት ሊሰበስብ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- በቀጣይ ከድርጅቶች ማስረጃውን በማሰባሰብ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ የሚያወጡ መሆኑን፣

ለ) **የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ከሌላቸው ግብር ከፋዮች ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ብር** 293,890.89**ያልተቀነሰ መሆኑ**

ግኝት

በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 91 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ግብር ከፋይ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ቀንሶ ለሚያስቀረው ሰው/ድርጅት/የግብር ከፋይ መለያ ቁጥሩን ያላቀረበ እንደሆነ ግብር ቀንሶ የሚያስቀረው ሰው/ድርጅት/ከተከፋይ ሂሣብ ላይ ሠላሣ በመቶ(30%) ቀንሶ ገቢ ማድረግ አለበት በሚለው መሰረት ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር አለማቅረባቸው እየታወቀ በአዋጁ መሰረት ከግዥው ላይ 30 በመቶ ተቀናሽ መደረግ ሲገባው 2 ከመቶ ብቻ በመቀነሱ

በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ቅ/ጽ/ቤት	ብር	151,613.99
በጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ_ቅ/ጽ/ቤት	"	114,207.81
በባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት	"	18,549.09
በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	"	9,520.00
በድምሩ	ብር	293,890.89

ያልተሰበሰበ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት

ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ገቢ የሚደረገው ግብር በአዋጁ መሰረት ተግባራዊ ሊሆን ካልቻለ የመንግስት ገንዘብ ላይሰበሰብ ይችላል፡፡በተጨማሪም አሰራሩ ለብልሹ አሰራር በር የሚከፍት ሊሆን ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሣብ</u>

የስራ ሂደቱ በአዋጁ መሰረት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ ያልተከፈለውን ግብር ክትትል በማድረግ ሊሰበስብ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ከድርጅቶቹ በአሁን ሰዓት ማስረጃ ለማሰባሰብ ጥረት እያደረግን መሆኑን እና በቀጣይ ማስረጃ ባላቀረቡት ላይ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ እናወጣለን በማለት ገልጸዋል፡፡

ተ) <u>ኪሳራ በተደጋጋሚ ስለማሳወቅ</u>

<u>ግኝት</u>

የደንበኞች አገልግሎት እንቅስቃሴ አላቸው ብሎ ከያዛቸው ግብር ከፋይ በናሙና ከተመረጡት መካከል፡-

<u>በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ቅ/ጽ/ቤት</u>

- **ዶንዲ ኤምፔክስ ሰርቪስ የግብር መለያ ቁጥር /0000388195/ ከ2007 ዓመት ጀምሮ አራት (4) ዓመታት ወደኋላ ተሂዶ ሲታይ ኪሳራ ላይ መሆናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ ያቀረቡ በመሆኑ እና የታክስ ህግ ተገዢነት እና የስጋት ቡድን የስራ ሂደት በኩል ስጋት አለባቸው ተብለው ከቀረቡት ዝርዝር ማስረጃ ውስጥ ያልተያዘ መሆኑ በኦዲት ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡**

<u>የድሬደዋ ግቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት</u>

- **ጂሮው ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ.ማ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0015445634 ከ2003 እስከ 2007 በጀት ዓመት በንግድ ትርፍ ግብር ዜሮ እያሳወቀ መሆኑ እና በታክስ ህግ ተገዢነት እና የስጋት ቡድን በታክስ ኦዲት እንዲታይ የተመረጠ ቢሆንም ኦዲት ያልተደረገ መሆኑ**
- **መሀመድ አብዱላሂ አክሰዴ የንግድ ስራዎች ኃ.የተ.የግ.ማ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር 0004978176 ከ2001 እስከ 2007 በጀት ዓመት ድረስ ኪሳራ እያሳወቀ በመሆኑ የስጋታቸውን ምንጭ በመጥቀስ የስራ ክፍሉ የሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ኦዲት ወይም ክትትል እንዲደረግባቸው አለመደረጉ ታውቋል፡፡**

ስጋት

ኪሳራ በተደጋጋሚ የሚያሳዩ ድርጅቶች የታክስ ህግ ተገዢነት እና የስጋት ቡድን የስራ ሂደት ስጋታቸው ተለይቶ በታክስ ኦዲት የስራ ሂደት በኩል ኦዲት እንዲደረጉ የማይደረግ ከሆነ ደርጅቶቹ ኦዲት ሳይደረጉ መንግስት ከግብር ሊያገኝ የሚችለውን ገቢ ሊያሳጣው ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

የስራ ክፍሉ በተደጋጋሚ ኪሳራ የሚያሳዩ ድርጅቶችን እንደ አንድ የስጋት ደረጃ በመለየት በታክስ ኦዲት የስራ ሂደት በኩል እንዲታዩ ሊያደርግ ይገባል፡፡

ጎ) **ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀንሶ የቀረውን ግብር (Withholding Tax) የሚያሳይ ማስረጃ ባለመቅረቡ ከንግድ ትርፍ ግብር የተቀነሰውን የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሳብ ብር 5,697,434.17**

ግኝት

ግብር ከፋዮች ግብርን ቀንሶ ገቢ ማድረግ ኃላፊነት ለተሰጠው አካል ሽያጭ በሚያከናውኑበት ሰዓት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ የተደረገባቸውን በዓመቱ የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው የገለፁትን ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የተቀነሰውን (withholding Tax) የሚያሳይ ዝርዝር ማስረጃ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ቅ/ጽ/ቤት

- **ልኡል ኃ/የተ/ የግ.ማ የግብር መለያ ቁጥር /0000007669/ ብር 239,697.88**
- **ሰል አፍሪካ ኢትዮጵያ የግብር መለያ ቁጥር /0039397126/ ብር 4,590,681.00**

በድምሩ ብር 4,830,378.88 የዓመቱን ትርፍና ኪሳራ ሲያሳውቁ አስቀድሞ የተከፈለ (withholding Tax) ተብሎ በትርፍ እና ኪሳራ መግለጫ ላይ የተቀነሰላቸው ቢሆንም ዝርዝር ማስረጃው ባለመቅረቡ ድርጅቶቹ የከፈሉት ስለመሆኑ ማረጋገጥ አለመቻሉ ፤

የጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

አስራ ሁለት (12) ግብር ከፋዮች በድምር ብር 867,055.29 ከንግድ ትርፍ ግብር የተቀነሰላቸው ቢሆንም የሂሳቡን ሁኔታ የሚያሳይ ዝርዝር ማስረጃ በኦዲት ወቅት ሊቀርብ ባለመቻሉ ከንግድ ትርፍ ግብር የተቀሰው ሂሳብን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስጋት

ግብር ከፋዮች በሚያቀርቡት የተከፋይ ሂሳብ ላይ የሚቀነሰውን ቅድመ ግብር ማስረጃ መሰረት ተቀናሽ የማይደረግ ከሆነ የገቢ ግብሩ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ካለማስቻሉም መንግስት ሊያገኝ የሚገባውን ግብር ሊያሳጣው ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በግብር አሰባሰብና ክትትል የሥራ ሂደት በኩል ያልቀረቡት ማስረጃዎች እንዲቀርብ በማድረግና የሂሳቡ ትክክለኛነት በማረጋገጥ ያልተሰበሰበ ግብር ካለ ሊሰበስብ ይገባል፡፡

ነ) ከተከፋይ ሂሳብ ላይ በተቀነስ (Withholding Tax) ስሌት መሰረት በንግድ ትርፍ ግብር ያላሳወቁት ሽያጭ በመኖሩ ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ ግብር ብር 56,369.88 መኖሩ

ግኝት

በ2007 በጀት ዓመት ግብር ከፋዮች በንግድ ትርፍ መግለጫ ላይ ባሳወቁት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ የሚቀነስ (Withholding Tax) ስሌት መሰረት በንግድ ትርፍ እና ኪሳራ መግለጫ ላይ ያሳወቁት ጠቅላላ ሽያጭ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

- ሶስት (3) ግብር ከፋዮች በተከፋይ ተቀናሽ ስሌት መሰረት መሆን የነበረበት ሽያጭ በብር 187,899.61 የሚበልጥ በመሆኑ ባላሳወቁት ሽያጭ ላይ በድምር ብር 56,369.88 ያልተከፈለ የንግድ ትርፍ ግብር መኖሩ ተረጋግጧል ፡፡

ስጋት

ከተከፋይ ተቀናሽ ማስረጃ መሰረት ግብር ከፋዮች የንግድ ትርፍ ግብር ማሳወቂያ ላይ የሚያሳውቁት ጠቅላላ ሽያጭ ትክክለኛነት ተረጋግጦ ግብሩ የማይሰበሰብ ከሆነ መንግስትን ከገቢ ግብር ሊያገኝ የሚገባውን ግብር ሊያጣ ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር የሚከፍት ይሆናል፡፡

የማሻሻያ እርምጃ

የስራ ሂደቱ ያልተሰበሰበ ግብር ወለድ እና ቅጣት ታክሎበት ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

ኘ) ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 10,713.00 መኖሩ

ግኝት

ግብር ከፋዮች ባቀረቡት የ2008 በጀት ዓመት በተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ ላይ የተመለከተው የየወሩ ጠቅላላ ሽያጭ መሰረት ግብሩን እየከፈለ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

የኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	ብር	4,087.53
በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	"	6,625.47
ጠ/ድምር	ብር	10,713.00

ያልተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ መኖሩን ለማየት ተችሏል፡፡

ስጋት

የስራ ሂደቱ ግብር ከፋዮች የተጨማሪ እሴት ታክስ በትክክል እያሳወቀ ክፍያ መፈጸሙን ክትትል በማድረግ ግብሩን የማይሰበስብ ከሆነ የመንግስት ግብር ሊቀር ከመቻሉም በላይ ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

የተጨማሪ እሴት ታክስ ማሳወቂያ ላይ ግብር ከፋዮች ግብራቸውን ሲያሳውቁ ስለትክክለኛነቱ የሚመለከተው የስራ ክፍል አረጋግጦ ግብሩን መሰብሰብ ያለበት ሲሆን አልተሰበሰበም የተባለውንም ግብር ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

ሀ) በገቡት የክፍያ ስምምነት መሰረት የግብር እዳቸውን መክፈል ያልጀመሩ እና ያቋረጡ ግብር ከፋዮች በመኖራቸው ገቢ ያልሆነ የግብር እዳ ብር 14,200,483.24 መኖሩ

ግኝት

የግብርና ታክስ አስተዳደራዊ መቀጫዎች አነሳስ፣ የክፍያ ጊዜ ስምምነት እና የግብር ግዴታን ስለመወጣት በማረጋገጫነት የሚሠጥ የምስክር ወረቀት (ክሊራንስ) አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 55/2003 አንቀጽ 14 መሰረት የክፍያ ማራዘሚያ ጊዜ ውል ስምምነት የገቡ ግብር ከፋዮች ዕዳቸውን በገቡት የውል ስምምነት መሰረት እየከፈሉ እንደሆነ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት በድምሩ ብር 14,200,483.24 ውዝፍ እዳ በስምምነቱ መሰረት ከግብር ከፋዮቹ ያለመሰብሰቡ ታውቋል፡፡

ስጋት

በስምምነታቸው መሰረት የማይከፍሉ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ በታቀደው ጊዜ ውስጥ እንዳይሰበሰብ ከማድረጉም በተጨማሪ ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በተገባው ስምምነት መሰረት ክፍያ በማይፈጽሙ ግብር ከፋይ ድርጅቶች ላይ በመመሪያው መሰረት ወደ ቀጣይ የግብር ውሳኔ እርምጃ በመግባት ያልተሰበሰበው ውዝፍ ግብር እንዲከፈል መደረግ ይኖርበታል፡፡

ከ) <u>በአጠቃላይ ኦዲት፣ ውስን፣ ዴስክ ኦዲት እና በአቤቱታ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የውሳኔ ማስታወቂያ ደርሷቸው ያልተሰበሰበ ግብር ብር</u> 3,988,939,500.18 **<u>መኖሩ</u>**

<u>ግኝት</u>

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 **አንቀጽ** 77/1 **መሰረት በታክስ ኦዲትም ሆነ በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አማካኝነት ውዝፍ የግብር ዕዳ ያለባቸው ግብር ከፋዮች የግብር ዕዳቸውን በ** 30 **ቀናት ውስጥ እንዲከፍሉ ውሳኔ ደርሷቸው ያለባቸውን የግብር እና የታክስ ዕዳ እስካሁን ድረስ ባልከፈሉ ግብር ከፋዮች ላይ ንብረት በመያዝ ያለባቸውን የግብር ዕዳ ለመሸፈን እንዲሆን በአዋጁ መሰረት የንብረት መያዝ እርምጃ እየወሰዱ ስለመሆናቸው ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-**

በኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	**ብር**	1,040,020.38
በድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	"	82,614,496.40
በጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	"	13,202,272.41
በምስራቅ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	"	49,103,485.09
በምዕራብ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	"	221,873,831.48
አዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	"	13,981,868.85
በባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት	"	36,468,864.32
በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት	"	1,869,874.29
በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	"	3,568,784,786.96
ጠ/ድምር	**ብር**	3,988,939,500.18

በአጠቃላይ ኦዲት፣ ውስን፣ ዴስክ ኦዲት እና በአቤቱታ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የውሳኔ ማስታወቂያ ደርሷቸው በተወሰነው ጊዜ ያልተሰበሰበና በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኝ ግብር መኖሩ ታውቋል፡፡

ስጋት

መሰብሰብ ያለበት ገቢ ወቅቱን ጠብቆ ካልተሰበሰበ ከቆይታ ብዛት መሰብሰብ ከማይችልበት ደረጃ ላይ ሊደርስ ከመቻሉም በላይ መንግስት ሊሰበስበው ያቀደውን ገቢ ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል፡

የማሻሻያ ሃሳብ

የዋና መስሪያ ቤቱም ሆነ የቅ/ጽቤቶች ቅሪታ ስሚ አካላት ለጉዳዩ ትኩረት በመስጠትና የስራ ክፍሎቹም የውሳኔ ማስታወቂያ ወቶላቸው በተሰጠው የግብር መክፈያ ቀነ ገደብ መሰረት ግብሩን ለመሰብሰብ የተጀመረውን እርምጃ አጠናክሮ ሊቀጥሉና ገንዘቡንም ሊሰበስብ ይገባል፡፡

ኸ) ለዋናው መ/ቤት ቅሬታ አቅርበው በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ያልተሰጠበት

የብር 2,779,558,320.87 **አቤቱታ**

ግኝት

በአዋጅ ቁጥር 268/2006 አንቀጽ 105 መሰረት አቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር በግብር ከፋዮች መቀጫ እንዲነሳ ወለድ ቀሪ እንዲደረግ ወይም የግብር ግዴታ እንዲሻሻል የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ለመመርመርና ውሳኔ ለመስጠት በሚለው መሰረት የግብር ታክስ ውሳኔ ወጥቶባቸው ግብር እንዲከፍሉ የውሳኔ ማስታወቂያ ከተለያዩ ቅ/ጽ/ቤቶች እንዲደርሳቸው የተደርጉ 57 ግብር ከፋዮች በውሳኔው ባለመስማማት ቅሬታቸውን ለዋናው መ/ቤት አጣሪ ኮሚቴ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ቅሬታቸው በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ወቅቱን ጠብቆ ያልታየላቸው በመሆኑ ከ 18/04/06 እስከ 21/04/09 ጊዜ የቆዩ የብር 2,779,558,320.87 አቤቱታ መኖሩ ታውቋል፡፡ በዚህም ምክንያት ሊሰበሰብ የሚገባው ገቢ ሳይሰበሰብ የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት

ለባለስልጣን መ/ቤቱ የሚቀርቡ ቅሬታቸው በወቅቱ ታይቶ እልባት የማይሰጥ ከሆነ መሰብሰብ የሚገባው ግብርና ታክስ ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በተገልጋዮች/ድርጅቶች/ ለአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የሚቀርቡ የግብርና ታክስ በቅሬታቸው መሰረት አፋጣኝ የመፍትሄ እርምጃ እንዲወሰድ በማድረግ በተቀመጠላቸው ቀነ ገደብ ውሳኔ በመስጠት ገቢው ሊሰበሰብ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ባለሚሚላቱ ቅሬታቸው ያልታየላቸው መኖራቸውን ጨምሮ የተለያዩ ምክንያቶች መኖራችውና የኮሳራ ማሸጋገር ጥናት፤የመሳሰሉትን ጠቅሰው ምልሽ ሰጥተዋል፡፡

0) <u>ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ያላቸው ግብር ከፋዮች ስለ መኖራቸው ፤</u>

<u>ግኝት</u>

በገቢ ግብር አዋጅ 286/1994 አንቀጽ 43 /ሀ/ አንድ ግብር ከፋይ ከአንድ የበለጠ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር መያዝ እንደሌለበት በሚያዘው መሰረት በየቅ/ጽ/ቤቱ ግብር እየከፈሉ ያሉ ግብር ከፋዮች ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እንዳልተሰጣቸው ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

በጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ሁለት ግብር ከፋዮች እያንዳንዳቸው ሁለት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ያላቸው መሆኑ ተረጋግጧል ፡፡

<u>ስጋት</u>

ግብር ከፋዮች ከአንድ በላይ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የሚይዙ ከሆኑ ከድርጅቶች የሚሰበሰበውን ሂሳብ በትክክል ለማወቅ አዳጋች ከማድረጉም በላይ የግብር/ታክስ ማጭበርበር ክፍተት በር ሊከፍት ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በግብር ከፋይ በሰርተፍኬት ላይ የሚታየው የግብር ከፋዮች መለያ ቁጥር ከንግድ ስራ ፈቃድ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን በሚመለከተው አካል ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግበት ይገባል፡፡ ባለፉት አዲቶችም ተመሳሳይ ሁኔታ በመገኘቱ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም፤ እስካሁን ተገቢው እርምጃ ካለመወሰዱም ተመሳሳይ ስህተት አሁንም መገኘቱ ትክክል ሆኖ አላገኘነውም ፡፡

ወ) <u>የታክስ ማዕከል ያልተቀየረላቸው ግብር ከፋዮች መኖራቸው</u>

<u>ግኝት</u>

በቅ/ጽ/ቤቱ ግብራቸውን በመክፈል ላይ ያሉ ግብር ከፋዮች የደንበኞች አገልግሎት በመረጃ ተይዘው ግብራቸውን እየከፈሉ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፤

- በጅማ ቅርንጫፍ በደንበኞች አገልግሎት የተያዙ 221 ግብር ከፋዮች በጋምቤላ የክልሉ ግብር ከፋዮች መሆናቸውና ግብራቸውን አሳውቀው የሚከፍሉት በጋምቤላ የታክስ ማዕከል ሆኖ ሳለ በሲግታክስ መመዝገቢያ ሶፍት ዌር ላይ ግን በፌዴራል ግብር ከፋይነት የጅማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

በቅ/ጽ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት የሚታየው ገቢ በመረጃ ቴክኖሎጂ ዳይሬክቶሬት በቅ/ጽ/ቤቱ ተሰበሰበ ከተባለው ጋር የማይጣጣም ሊያደርገው ከመቻሉም በላይ የተዛባ መረጃ እንዲኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የስራ ክፍሉ በደንበኞች አገልግሎት በቅ/ጽቤቱ ግብር ከፋይ ናቸው ብሎ በያዛቸው መረጃ መሰረት የተሰበሰበው ግብር በሲግታክስ መመዝገቢያ ሶፍት ዌር ላይ ሊታይ የሚገባው በመሆኑ ክትትል ሊያደርግ ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

የጋምቤላ ክልልና የሌሎችን ክልል ግብር ከፋዮች ታክስ ማዕከል ለማስተካከል ከአይቲ ዳይሬክቶሬት ጋር በመነጋገር ለወደፊት ክትትል በማድረግ ችግሩ የሚፈታ ይሆናል በማለት ተግባራዊ እንደሚያደርጉ በስራ አመራር ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

2) <u>የወጪ ሂሳብ</u>

ሀ) <u>የቅድመ ግብር (withholding tax) እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተከፋይ ብር 327,551.57 ከግዢ ላይ ተቀናሽ ሳይደረግ ክፍያው የተፈጸመ መሆኑ</u>

<u>ግኝት</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1994 አንቀጽ 24/2/ሸ/ መሰረት በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ማንኛውም ድርጅቶች ከብር 10,000.00 በላይ እቃ

ግዢ ሲፈጽሙ እና ከብር 500.00 በላይ የአገልግሎት ግዢ ሲፈጽሙ የንግድ ትርፍ ግብር 2 በመቶ ቀንሰው ማስቀረት እንዳለባቸውና በቀን 08/03/2007 ዓ.ም በተላለፈ ሰርኩላር መሰረት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ከሌላቸው ድርጅቶችም ሆነ የግለሰብ ነጋዴዎች ላይ 30% የንግድ ትርፍ ቅድመ ግብር ተቀናሽ መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም በግዥ ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ የአፈጻፀም መመሪያ ቁጥር 27/2002 አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ አንድ መሰረት ማንኛውም ከብር 5,000 በላይ ግዥ የሚፈፅም የመንግስት መ/ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ ቆርጦ በማስቀረት ከወሩ የመጨረሻ ቀን ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለታክስ ባለሥልጣኑ ገቢ ማድረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ ደንብና መመሪያ አንጻር ቅ/ጽ/ቤቶች ስራቸውን እያከናውኑ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት፡- ቅድመ ግብር (withholding tax)	ብር	31,800.00
በባለስልጣኑ ዋና መ/ቤት የተጨማሪ እሴት ታክስ		295,751.57
ጠ/ድምር	ብር	327,551.57

ከግዢ ላይ ቀናሽ ሳይደረግ ክፍያው የተፈጸመ መሆኑታውቋል፡፡

ስጋት

መንግስት ከታክስ ሊሰበስበው ያቀደውን ገቢ በወቅቱ እንዳይሰበሰብ ሊያደርግ ይችላል፡፡ እንዲሁም ወደፊት ሊሰራው ያቀደው እቅድ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድርበት ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ማንኛውም ግዢ በሚፈጽምበት ወቅት በአዋጁ እና በደንቡ መሰረት ተገቢውን የቅድመ ግብር በቅድሚያ እየተቀነሰ ክፍያው ሊከፈል ይገባል፡፡

ለ) መመሪያን ያልተከተለ ግዥ ብር 774,051.89 **መኖሩ**

ግኝት

የፌደራል መንግስት የግዢ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ/2002 በወጣው ክፍል 5 አንቀጽ ቁጥር 25 ንዑስ አንቀጽ 6 እና በአዋጅ 649/2001 አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 2 "ሀ" መሰረት፣ ታህሳስ 12/2008 ተሸሽሎ በወጣው የፌደራል መንግስት የግዥ መመሪያ አንቀጽ 25 (7)ሀ መሰረት፣ በፌዴራል መንግሥት ግዥ አፈጻጸም መመረያ ሰኔ 2002 ዓ.ም አንቀፅ 24 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት፣ በግዢና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ

56/1 መሰረት እና ሰኔ 2002 በወጣው የግዥ አፈጻጸም መመሪያ አንቀጽ 16.7.3.2 ሀ መሰረት በየቅ/ጽ/ቤቱ ግዢዎች የሚፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት በቀጥታ ከ1 ድርጅት ግዥውን የተፈጸመ	ብር	16,840.00
በባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት፡- የጥቃቅን ግዥ ከመመሪያው ውጭ	"	179,423.73
በአ/ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት፡-ከ3 በታች በቀረቡ ተወዳዳሪዎች	"	94,188.15
በጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ደንብን ያልተከተሉ ግዥዎች	"	483600.01
ጠ/ድምር	ብር	774,051.89

የመንግስት መመሪያን ያልተከተለ ግዥ ተገኝቷል፡፡

ስጋት

የመንግስት ገንዘብ አላግባብ እንዲባክን ክፍተት ከመፍጠሩም በላይ ፍትሃዊ የገበያ ውድድር እንዳይኖር ያደርጋል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

በቅ/ጽ/ቤቶች ግዥዎች ሲከናወኑ በግዥ መመሪያው መሠረት የግዢ ሂደታቸውን ተከትሎ መፈጸም ይኖርበታል፡፡አሁንም ተመላሽ መደረግ ያለበት ተመላሽ እንዲሆን ያለአግባብ ግዥ እንዲከናወን ባደረጉ ኃላፊዎችና ሰራተኞች አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡

ሐ) ለሰራተኞች ከተከፈለው የቤት እና የሙያ አበል ላይ ተቀናሽ ያልተደረገ የሥራ ግብር ብር 1,110,514.85 መኖሩ

ግኝት

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 12(1) በመቀጠር የሚገኝ ገቢ ማለት ከመቀጠር በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት የተገኘ ማናቸዉም ክፍያ ወይም ጥቅም ሲሆን በቅድመ ቅጥር የተገኘን ገቢ እና ወደፊት ለመቀጠር አስቀድሞ የሚደረግ ክፍያን እንደሚጨምር ሲደነግግ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 13 እና በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 ከግብር ነፃ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማናቸዉም ክፍያ ወይም ጥቅም ከወር ደምወዝ ጋር እየተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት በአዋጁና በደንቡ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በመሆኑም ይህንኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-ቅ/ጽ/ቤቶቹ ለሰራተኞች የከፈለውን የቤት እና የሙያ አበል በተጠቀሰው አዋጅ ላይ ከግብር ነፃ ያልተደረጉ መሆኑን

እየታወቀ ለመንግስት ገቢ መሆን የነበረበት የስራ ግብር ተቀናሽ ሳይደረግ እንዲከፈላቸው የተደረገ፤

በባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት	ብር	93,215.80
በሞጆ ቅ/ጽ/ቤት	"	34,109.40
በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት	"	83,016.00
በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት	"	64,329.06
በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	"	98,500.02
በጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	"	55,502.55
በምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	"	37,858.75
በምዕራብ አዲስ አበባ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	"	9,555.00
በኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	"	49,841.88
በድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	"	92,114.00
በጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	"	61,092.75
በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	"	106,837.78
በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት	"	324,541.86
ጠ/ድምር	ብር	1,110,514.85

በባለስልጣን መ/ቤቱ ተቀጥረው ከሚሰሩ አቃቢያነ ህግና ሌሎች ሰራተኞች ከተከፈለው የቤት አበል መሰብሰብ የሚገባው የሥራ ግብር ሳይሰበሰብ ቀርቷል፡፡

ስጋት

መንግስት ከሚከፍለው የደመወዝ እና ሌሎች ግብር የሚከፈልባቸው አበሎች ተገቢውን ግብር ተቀንሶ ለሚመለከተው አካል ገቢ የማይደረግ ከሆነ በመንግስት ገቢ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ሊያመጣ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

የሙያ እና የቤት አበል ተከፋይ ሂሳቦች በገቢ ግብር አዋጅ እና ደንብ መሰረት የስራ ግብሩ ተቀናሽ እየተደረገ ለሰራተኞቹ መከፈል ይኖርበታል፡፡ ባለፈው በጀት ዓመትም ተመሳሳይ ስህተት ተፈጽሞ ስለነበር ተመላሽ ካለመደረጉ በተጨማሪ በአሁኑ ስዓትም ሁኔታው መቀጠሉ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ወስለሆነም የባለፈውም ሆነ የዚህ በጀት ዓመት ከሰራተኞቹ ያልተሰበሰበው የስራ ግብር ተሰብስቦ ገቢ መሆን ይኖርበታል፡፡

መ) <u>ሳይፈቀድ በተጨማሪነት የተከፈለ የመዘዋወሪያ አበል ብር 19,200.00 መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ለአቃቢያነ ህግ በደብዳቤ ቁጥር መ240-890/2 **በቀን** 04/07/2007 **ዓ.ም በተላለፈው ሰርኩላር መሰረት ከፈቀደው ጥቅማ ጥቅም ውስጥ የትራንስፖርት አበል ብር** 600 **ብቻ ሲሆን ክፍያው በዚህ መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት፡- ቅ/ጽ/ቤቱ በተጨማሪ ብር** 200.00 **በመክፈል ከተፈቀደው የትራንስፖርት አበል በላይ በየወሩ ብር** 800.00 **እየከፈለ የቆየ በመሆኑ በበጀት ዓመቱ ያለአግባብ የተከፈለ የትራንስፖርት/የመዘዋወሪያ አበል በድምሩ ብር** 19,200.00 **መኖሩ ታውቋል፡፡**

<u>ስጋት</u>

ያልተፈቀደ የመዘዋወሪያ አበል በተጨማሪ የሚከፍል ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ እንዲባክን ያደርጋል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

በሚመለከተው አካል በተፈቀደው መሰረት ብቻ የትራንስፖርት/የመዘዋወሪያ አበሉ ለሰራተኞቹ እንዲከፈል መደረግ ይኖርበታል፡፡ ያለአግባብ የተከፈለው የትራንስፖርት አበል ከሚመለከታቸው ሰራተኞች ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

በመዘዋወሪያ እና በትራንስፖርት አበል መካከል በልዩነት ተከፈለ የተባለዉን ሂሳብ ከ200.00 **ብር ወደ** 600.00 **ብር ስለተቀየረ በመሆኑ ግንዛቤ እንዲወሰድ ሲሉ ምላሻቸውን ሠጥተዋል፡፡**

<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ቅ/ጽ/ቤቱ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ተሸሽሎ በወጣ የትራንፖርት/የመዘዋወሪያ አበል ብር 600.00 **መሰረት አበሉን መክፈል ሲገባው በበጀት አመቱ ለእያንዳንዱ አቃቢያነ ህግ እየተከፈለ ያለው የመዘዋወሪያ አበል ግን ብር** 800.00 **መሆኑ አግባብነት ያለው ክፍያ ሆኖ ስላላገኘነው ምላሹን አልተቀበልነውም፡፡**

ሠ) <u>ያለ አግባብ የተከፈለ የውሎ አበል ሂሳብ ብር</u> 129,648.2 **<u>መኖሩ</u>**

<u>ግኝት</u>

ሀምሌ 2004 **ዓ.ም ተግባራዊ በሆነው የመንግሰት ሠራተኞች የአገር ዉስጥ የቀን ዉሎ አበል ክፍያ አፈፃፀም መመሪያ አንቀፅ** 5/2 **መሠረት ማንኛዉም የመንግስት ሰራተኛ ከመደበኛ የሰራ ቦታው ዉጭ ወደ ሆነ ሌላ የሰራ ቦታ ለሥራ ጉዳይ ሄዶ ዕለቱን መመለስ ካልቻለ እና ከምሽቱ ሁለት ሰዓት በኃላ የሚመለስ ከሆነ የውሎ አበል የሚከፈል መሆኑን ይገልፃል እንዲሁም በአንቀጽ** 9 **አንድ ሰራተኛ ከመደበኛ ቦታው ወደ ሌላ ስፍራ ለስራ ከመላኩ በፊት የውሎ አበል መጠየቂያ ፣መፍቀጃና መክፈያ ቅጾች ለጉዳዩ አግባብ ባለው ሰራተኞች ወይም የስራ ኃላፊዎች እንዲሞላና የስራ መከናወኑን አረጋግጦ ክፍያው እንዲወራረድ ይደረጋል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቶች በዚህ መመሪያ መስረት የዉሎ አበል ክፍያ እየፈጸሙ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ስደረግ፡-**

በሞጆ ቅ/ጽ/ቤት	**ብር**	15,048.00
በጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	"	22,333.40
በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት	"	69,658.50
በምስራቅ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	"	<u>22,608.30</u>
	ጠ/ድምር ብር	<u>129,648.20</u>

ያለ አግባብ የተከፈለ የውሎ አበል ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

<u>ስጋት</u>

የሚከፈሉ የዉሎ አበል ክፍያዎች ትክክለኛነታቸው ተረጋግጦ የማይከፈል ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ ሊባክን ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ሠራተኞቹ ለስልጠናም ሆነ ለሌላ ጉዳይ ወደ ሌላ ስፍራ ሲሄዱ ሙሉ ወጪያቸው ስልጠና በሚሰጠው አካል የሚሸፈን ከሆነ ቅ/ጽ/ቤቱ በድጋሚ የውሎ አበል መክፈል አይገባውም፡፡ ለውሎ ገብ የተከፈለው አበልም ህጉን የተከተለ አይደለም ፡፡ስለሆነም አለአግባብ ለተከፈለው ክፍያም ከሰራተኞቹ ተመላሽ መደረግ ይኖርበታል፡፡

ሠ) <u>የግብር ተመላሽ ሂሳብ ብር 1,070,787.00 ግብር ከፋዩ ስለመቀበሉ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ</u>

<u>ግኝት</u>

በፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 9 ላይ ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች በሚለው ንዑስ አንቀፅ 7 ለተገዛ ዕቃ ወይም አገልግሎት ክፍያ ሲፈፀም በማስረጃነት መቅረብ ያለበት ዋና ደረሰኝ እንደሆነ በሚያዘው መሰረት ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፡-

በድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት በቀን 17/06/08 በBPV 0205320 በሂሳብ መደብ 6419 ለመሀመድ ኢብራሂም የተከፈለ የግብር ተመላሽ ብር 1,070,878.00 ክፍያ ሲፈፀም ተከፋዩ ገንዘቡን ስለመቀበሉ ያቀረበው ማስረጃ ወይም ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>ስጋት</u>

ለግብርና ቀረጥ ተመላሽ የሚፈፀም ክፍያ ማስረጃ የማይያያዝ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ ወጪ እንዲሆን በር ሊከፍት ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የግብር ተመላሽ ክፍያዎች ለግብር ከፋዮች በሚፈጸምበት ወቅት ገንዘብ ተቀባዩ ገንዘቡን ስለመቀበሉ ደረሰኝ መቅረቡ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ አሁንም ማስረጃው እንዲቀርብ መደረግ አለበት፡፡

ረ) <u>ያለአግባብ ተመላሽ የተደረገ ብር 403,137.20 የቅጣት ገቢ በተመለከተ ግኝት</u>

ባለስልጣን መ/ቤቱ የኮምፒውተር ጠረጴዛ ለመግዛት ባወጣው ግልጽ ጨረታ መ/ቤቱ በተዋዋለው ውል መሰረት አሸናፊው (አቅራቢው) ድርጅት ውሉ ላይ በተጠቀሰው የግዜ ገደብ ውስጥ ዕቃውን የማያቀርብ ከሆነ በልዩ ውል ሁኔታዎች ላይ በተቀመጠው መሰረት ለዘገየበት 10 ከመቶ መቀጣት እንዳለበት ተገልጿል፡፡ በዚህ መሰረት ስለመሰራቱ ለማረጋገጥ በተሞከረበት ወቅት አሸናፊው ድርጅት ለዘገየበት በውሉ ላይ በተቀመጠው መሰረት ብር 403,137.20= (4,031,374.90*10%=403,137.20) መቀጣትና ከክፍያው ላይ ተቀንሶ ገቢ መሆን ስገባው ከደርጅቱ ሳይቀነስ /ሳይቀጣ/ ሙሉ ክፍያ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

ስጋት

በውሉ መሰረት ተፈጻሚ ባለመሆኑ መ/ቤቱ ማግኘት ያለበትን ጥቅም ሊያሳጣው ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ያለአግባብ ተመላሽ የሆነው የቅጣት ገቢ ክፍያ መሰብሰብ አለበት፡፡

ሰ) **ያለአግባብ የተከፈለ ብር 10,000.00**

ግኝት

የመንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4//2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 8(2) ላይ እንደተመለከተው ክፍያ ሊፈጸም የሚችለው የመንግስት መ/ቤት ላገኘው ጥቅም ወይም አገልግሎት መሆን እንዳለበት ያዛል፡፡ በዚህ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ስደረግ፡-
በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት

- የመ/ቤቱ ሠራተኛ ለሆኑት የክሊፒ /ቪዲዮ ማሰሪያ ስፖንሰርሽፕ ለማድረግ በሚል ብቻ ለመ/ቤቱ የሚያስገኘው ጥቅም ሳይኖር ወይም ከግምት ውስጥ ሳይገባ ብር 10,000.00 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

ስጋት

ለመ/ቤቱ ጥቅም ለማይሰጡ ጉዳዮች ክፍያ ሊፈጸም ይችላል፡፡ሁኔታውም ለብልሹ አሰራር በር ይከፍታል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

ለመ/ቤቱ የሚያስገኘው ጥቅምም ሆነ የሚሰጠው አገልግሎት የሌለ በመሆኑ ገንዘቡ ለመ/ቤቱ ተመላሽ መደረግ አለበት፡፡

የስራ አመራር ምላሽ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት

- ገንዘቡን የተከፈላቸው ሰራተኛ ከሚያዝያ ወር 2009 ጀምሮ በ20 ወር ተመላሽ ለማድረግ አመልክተው የተፈቀደ መሆኑን ገልጸው ማመልከቻ ኮፒ አቅርበዋል፡፡

3) በጀት

3.1 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት

ግኝት

የፌደራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል 3 አንቀጽ 02/1 ለባለሰልጣን መ/ቤቱ ለበጀት ዓመቱ የተደለደለው የመደበኛ ሆነ የካፒታል በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በ2008 በጀት ዓመት በእያንዳንዱ ዓርእስት ከ10% በላይ ልዩነት ያላቸው በ22 የወጪ ሂሳብ መደቦች ከተደለደለው በጀት በድምሩ ብር 699,785,935.92 (39%) በሥራ ላይ ያልዋለ መደበኛ በጀትና ከተፈቀደው የካፒታል በጀት ውስጥ ከ10% በላይ ልዩነት ያልተጠቀመበትን በጀት የሚያሳዩ የሂሳብ መደቦች ጠቅላላ ድምር ብር 55,115,932.99(33%) ያልተጠቀመበት በጀት መኖሩ ታውቋል፡፡

ስጋት

መ/ቤቱ ስራ ላይ ከሚያውለው በጀት በላይ በስሙ የሚይዝ ከሆነ ለሌሎች የመንግስት መ/ቤቶች ሊያከናውኑ የሚገባቸውን ስራዎች በበጀት እጥረት ምክንያት እንዳያከናውኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

ባለስልጣን መ/ቤቱ በበቂ ጥናት የተመሰረተ አስተማማኝ የበጀት እቅድ በመያዝ በእቅዱ መሰረት ስራ ላይ የሚያውለውን በጀት ክትትል ሊያውል ይገባል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ ለመ/ቤቱ የተፈቀደውና የተስተካከለው ብር 1,779,966,383.73 ሲሆን ከዚህ ውስጥ የተጠቀምነው ወጪ 1,550,776,995.23 ነው ያልተጠቀምነው በጀት 229,189,388.50 ሲሆን ይህም በመቶኛ 13% ነው ፤ ከዚህ ውጪ ከ10% በላይ ያልተጠቀምንባቸው የሒሳብ መደቦች የተለያዩ የግንባታና የግዥ አገልግሎቶች በውላቸው መሰረት ቅድሚያ ክፍያ ተከፍሏቸው ስራው ባለመጠናቀቁ ወደ ወጪ ባለመቀየሩ ነው ፡ ቅርጫፍ ጽ/ቤቶች ሰኔ ላይ በጀታቸውን ጠይቀው ሳይወስዱ በመቅረታቸው እና በበጀት

ዓመቱ ከተቋሙ ከ1400 በላይ ሰራተኞች በመልቀቃቸው መጠቀም ያለባቸው በጀት ባለመጠቀማቸው የተከሰተ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

3.2 ከበጀት በላይ የወጣ

ግኝት

በ2008 በጀት ዓመት የቅርንጫፍ መ/ቤቶች የበጀት ፍላጎት መሰረት ለሁሉም ቅርንጫፍ መ/ቤቶች በተላከው የበጀት ድልድል መሰረት ሥራ ላይ መዋሉን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ ባለስልጣን መ/ቤቱ በተለያዩ ሂሳብ መደብ ከተደለደለለት በጀት በላይ ብር 7,230,416.01 የተጠቀመ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት

በጀት ለማጽደቅም ሆነ የማዘዋወር ስልጣን የተሰጠው አካል ሳይፈቅድ የመንግስት ገንዘብ ስራ ማዋል ላላስፈላጊ ወጪ ሊዳርግ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

ባለስልጣን መ/ቤቱ በበቂ ጥናት የተመሰረተ አስተማማኝ የበጀት እቅድ በመያዝ በእቅዱ መሰረት ስራ ላይ የሚያውለውን በጀት ክትትል ሊያውል ይገባል፡፡

3.3 የገቢ በጀት አፈጻጸም

ግኝቱ

በ2008 በጀት ዓመት የገቢ ሂሳብ ይሰበሰባል ተብሎ በዕቅድ የተያዘው ከተሰበሰበው ጋር ሲነጻጸር፤ በተለያዩ የሂሳብ መደብ በመቶኛ ከ10% በላይ ከዕቅድ በታች ክንውን በ62 የገቢ ሂሳብ መደብ ይሰበሰባል ተብሎ ከታቀደው ብር 51,730,557,891.42 ውስጥ ብር 39,959,206,274.91 የተሰበሰበ ሲሆን ብር 11,771,351,616.51 (23%) ያልተሰበሰበ ገቢ መኖሩ ታውቋል፡፡

ስጋት

በዕቅድና ክትትል ክፍል በኩል በታቀደው መሰረት በቅርጫፍ ጽ/ቤቶች በኩል መሰብሰብ ያለበት ገቢ የማይሰበሰብ ከሆነ መንግስት ሊሰበስብ ባቀደው መሰረት ሳይሰበስብ ሊቀር ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ባለስልጣን መ/ቤቱ የገቢ ዕቅዱን መሰረት በማድረግ ሊሰበሰቡ የሚገባቸውን ገቢዎች ከፍተኛ ትኩረት በመስጠትና ክትትል በማድረግ መሰብሰብ የሚገባው ገቢ ሊሰብስብ ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

- በካፒታል ዕቃዎች ሽያጭ ላይ በተገኘ ትርፍ ላይ የነበረው አፈጻጸም እንቅስቃሴው የታለመለትን ያክል አለመሆን፤
- በአገር ውስጥ የሚመረቱና የሚሰጡ አግልግሎቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የተርን ኦቨር ታክስ ከክፍያ ጋር የሚያሳውቅት ምጣኔ ዝቅተኛ መሆን እና
- የታክስ ህግ ማስከበር ስራዎች ክፍተት መኖር እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ዊዝ ሆልድ ባለበጀት መ/ቤቶች የሰበሰቡትን ታክስ በወቅቱ ለባለስልጣኑ ገቢ አለማድረግ
- እንዲሁም በገቢ አስገቢው ባለስልጣን መ/ቤቱ በኩል የክትትል ክፍተት መኖር ፤
- በኤክሳይስ ታክስ ይሰበሰብባቸዋል የተባሉት ምርቶች እንደታሰበው ያለመመረታቸው እና ግብር ከፋዮችን የሚጠበቅባቸውን የታክሰ መጠን አለማሳወቃቸው መክንያት የተፈጠረ ክፍተት ነው፡፡ በተጨማሪም በጉምሩክ ቀረጥና ታክስ የሚጣለውና የሚሰበሰበው ከውጪ በሚገቡ እቃዎች የታሰበውን ያክል ወደ ሀገር አለመግባታቸው እና የታክስና የጉምሩክ ቅሬታና አቤቱታ አፈታት አዝጋሚ መሆን ሊሰበሰብ ያልቻለ መሆኑን ገልጸዋል፡

3.5 **<u>የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከተደለደለው በጀት በላይ ብር 1,458,099.80 ወጪ መደረጉ፣</u>**

<u>ግኝት</u>

የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 30 ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በወጣው የፌደራል መንግሰት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2 የበጀት ዝውውር ወይም የተጨማሪ በጀት ካልተፈቀደ በስተቀር በሂሳብ መደብ ተለይቶ ከተፈቀደው በጀት በላይ ወጪ መፈጸም እንደማይቻል ተደንግጓል፡፡ ይህ መመሪያ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን ለማጣራት አዲት ሲደረግ፡-

በባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት	ብር	1,133,537.62
በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት	"	52,246.00
በድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	"	272,316.18
ጠ/ድምር	ብር	1,458,099.80

ከዋናው መ/ቤት ለየቅ/ጽ/ቤቶቹ ከተደለደለለት በጀት በላይ ወጪ መደረጉ ታውቋል፡፡

ስጋት

ወጪዎች ያለአግባብ ከዕቅድ በላይ ሊወጡ ይችላሉ በተጨማሪም ለብልሹ አሰራር በር ሊከፍት ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ቅ/ጽ/ቤቶች በየሂሳብ መደቡ የሚያወጧቸውን ወጪዎች በተቻለ መጠን ከተመደበው በጀት አንጻር በማስተካከል ወጪን መፈጸም ይኖርባቸዋል፡፡

4. **የሂሳብ ሪፖርትን በተመለከተ**

4.1 **የ2008 በጀት ዓመት የቅርንጫፍ መ/ቤቶች በሂሳብ መግለጫ የታየው ጠቅላላ ሂሳብ ከተጠቃለለው የሂሳብ መግለጫ ጋር እኩል አለመሆኑ**

ግኝት

በ2008 በጀት ዓመት የገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን መ/ቤት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ያሳወቀው የተጠቃለለ ሂሳብ መግለጫ የቅርንጫፍ መ/ቤቶች ባቀረቡት የሂሳብ መግለጫዎች መሰረት ተጠቃሎ ስለመሆኑ ኦዲት ሲደረግ ፣ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የተላከው የተጠቃለለ ሂሳብ መግለጫ፣

- የገቢ ሂሳብ በብልጫ ብር 26,624.01
- የወጪ ሂሳብ ብር 6,418.40 በማነስ ፣
- የተከፋይ ሂሳብ ብር 9,262,441.19 በመብለጥ እና ብር 20,201,676.93 በማነስ ፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 3,667,382.50 በመብለጥ፡
- የጥሬ ገንዘብ እና ባንክ ሂሳብ ብር 6,699,493.86 ዴቢት እና ብር 7,135.55 ክሬዲት በመብለጥ ፣ እንዲሁም ብር 9,824,997.00 ዴቢት እና ብር 967.52 ክሬዲት በማነስ፣

- የተጣራ ሀብት የሂሳብ መግለጫ ድምር ብር 354,298,760.48 ዴቢት እና ብር 357,862,037.41 ክሬዲት በማነስ የታየ ሲሆን ጠቅላላ ልዩነት በክሬዲት ብር 3,563,276.93 በማነስ
  የሚያሳይ መሆኑ ተረጋግጧል፡

ስጋት

ባለስልጣን መ/ቤቱ ለገ/ኢ/ት/ሚኒስቴር ያቀረበው የተጠቃለለው የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛ የተቋሙን የሂሳብ እንቅስቃሴ ላያሳይ ይችላል፡፡እንዲሁም የተዛባ የመረጃ አያያዝ ክፍተት ሊፈጥር ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሣብ

የባለስልጣን መ/ቤቱ ከየቅርንጫፍ መ/ቤቶች እና በዋናው መ/ቤት በቀረበው የሂሳብ መግለጫዎች መሰረት ትክክለኛ የሂሳብ መደብ በሚያሳይ መልኩ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

4.2) **በቅ/ጽ/ቤቶች የሂሳብ መግለጫ ያልተለመደ ሚዛን የሚያሳዩ የሂሳብ መደቦች በድምሩ ብር 62,254,837.00 መኖሩ**

ግኝት

በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 2/ለ መሰረት የእያንዳንዱ የሂሳብ መደብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን ዴቢትና ክሬዲት ጠብቆ መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት በቅ/ጽ/ቤቶች በተዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ ላይ እያንዳንዱ ሂሳብ መደብ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን የጠበቀ መሆኑ ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

በሞጆ ቅ/ጽ/ቤት፡-

ሰኔ 30/2008 በጉምሩክ ስነስርዓት የስራ ሂደት በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ላይ የዲፖዚት ሂሳብ ሚዛን የተጣራ ሀብት በብር 428,768.51 በዴቢት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑን፣ ይህም ሂሳብ በየዓመቱ የኦዲት አስተያየት እየተሰጠበት ቢሆንም ማስተካከያ ሳይደረግበት አሁንም የተገኘ መሆኑ ታውቋል፣

በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት፡-

በበጀት አመቱ የሂሳብ ማመሣዘኛ ላይ የተጣራ ሀብት በሂሳብ መደብ 5601 የተለመደው ሚዛን ክሬዲት መሆን ሲገባው ብር 189,370.31 ከሂሳብ አያያዝ እና ስርዓት ውጪ ያልተለመደ/ዴቢት ሚዛን የታየ መሆኑ፣

በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት፡-

በባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000026238521 የጥሬ ገንዘብ በሂሳብ መደብ 4101 መደበኛ የሂሳብ ሚዛኑ ዴቢት መሆን ሲገባው ክሬዲት /ያልተለመደ ባላንስ/ሚዛን ብር 1,087.37 የሚያሳይ መሆኑ፣

በኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

የተጣራ ሀብት ብር 21,066,756.38 ያልተለመደ ሚዛን /ዴቢት/ የሚያሳይ መሆኑ ፣ በ2006 በጀት ዓመት በተመሳሳይ በዴቢት ብር 299,806.45 በመታየቱ የአዲት አስተያየት የተሰጠበትና የእርምት እርምጃ ያልተወሰደበት ሲሆን ይህ ሂሳብ በ2008 በጀት ዓመት ጨምሮ የሚታይ መሆኑን፣

በአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት፡-

ሰኔ 30/2008 **በጉምሩክ ስነ-ስርአት** የስራ ሂደት (በገቢ ዋስትና ሂሳብ ቡድን) በኩል በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ላይ፡-

- የተጣራ ሀብት ትክክለኛ ሚዛን ክሬዲት ሆኖ ሳለ ብር 8,968,868.71 ዴቢት ሚዛን ማሳየቱ፤
- ሂሳብ ቁጥር 1962 በባንክ ያለ ገንዘብ (4103) ትክክለኛው ሂሳብ ዴቢት መሆን ሲገባው ብር 897.52 ክሬዲት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ **በገቢ አወሳሰንና አሰባበሰብ** የስራ ሂደት በኩል ሰኔ 30/2008 በተዘጋጀው ሂሳብ መግለጫ ላይ:-

- በባንክ ቁጥር 0160101020200 ብር 5,696.84 እንዲሁም በባንክ ቁጥር 3055 ብር 17,362.43 የተጣራ ሀብት ዴቢት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑን፣
- በባንክ ቁጥር 010019040192 የተጣራ ሀብት ብር 21,434,133.00 ዴብት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት</u>

የተጣራ ሀብት ትክክለኛ ሚዛን ክሬዲት መሆን ሲኖርበት ብር 9,842,089.48 ያልተለመደ ሚዛን/ዴቢት ሚዛን የሚያሳይ መሆኑን፣

ለማወቅ ተችሏል።ይህም ሂሳብ በተጠቃለለው ሂሳብ ባለበት ሁኔታ መመዝገቡ ታውቋል።

<u>ስጋት</u>

እያንዳንዱ የሂሳብ መደብ እንቅስቃሴ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበት ሚዛን ዴቢት እና ክሬዲት ጠብቆ የማይመዘገብ ከሆነ የባለስልጣን መ/ቤቱን የሂሳብ መግለጫ የተሳሳተ ያደርገዋል።

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ከላይ የተገለጸዉ የሂሳብ መደብ በመደበኛ ሁኔታ የሚታወቅበትን ሚዛን ያልጠበቀበት ሁኔታ ተጣርቶ ሊስተካከል ይገባል።

4.3) <u>ያለአግባብ በገቢ ሪፖርት የተካተተ ሂሳብ ብር 10,385,678.63 መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

የገቢ ሂሳቦች እውቅና የሚያገኙ/በገቢነት የሚመዘገቡት ገቢው በተሰበሰበበት ጊዜ ዉስጥ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በሞጆ ቅ/ጽ/ቤት፡-

በበጀት ዓመቱ ሪፖርት ከተደረገ የገቢ ሂሳብ ዉሰጥ ብር 10,385,678.63 ያለአግባብ የገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለትና ሂሳቡ ሳይሰበሰብ ወይም በወቅቱ ገቢ ሳይደረግ በገቢ ሂሳብ የተመዘገበ ሂሳብ በመሆኑ ምክንያት የበጀት ዓመቱ ገቢ በብልጫ ብር 10,385,678.63 የሚያሳይ መሆኑ ታውቋል።

<u>ስጋት</u>

የቀጥታ ገቢ ደረሰኝ የሚቆረጥለት የገቢ ሂሳብ ገቢው ከመሰብሰቡ በፊት ከሆነ በገቢ ደረሰኝ የተመዘገበው ገቢ ሳይሰበሰብ ሊቀር ይችላል።

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ማንኛውም ገቢ በገቢ መመዝገብ የሚኖርበት ገቢው በተሰበሰበበት ሰዓት ወይም ጊዜ መሆን ይኖርበታል። በተጨማሪ የገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለት ያልተሰበሰበው ሂሳብ መሰብሰብ ይኖርበታል።

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

የሞጆ ቅ/ጽ/ቤት፡-

አገልግሎቱ የተሰጠው በደብዳቤ ዋስትና ለመንግስት መሥሪያ ቤቶች በዋና መስሪያ ቤት በተፈቀደ ሁኔታ ቢሆንም ደረሰኙ የተቆረጠው የበጀት ዓመቱ የሚሰበሰብ መሆኑን ታሳቢ የተደረገ ቢሆንም ክፍያው ሳይፈፀም ደረሰኝ መቆረጡ አግባብ አለመሆኑን ይሁን እንጂ በመጋቢት 2009 ገንዘቡ መሰብሰቡን ገልጸዋል፡፡

4.4) **<u>በሳጥን የተቆጠረው እና በባንክ እስቴትመንት ላይ የተገለጸው ሂሳብ በሂሳብ ሪፖርት ላይ ከተገለጸው ጋር የብር 376,117,001.67 ልዩነት የሚያሳይ መሆኑ</u>**

<u>ግኝት</u>

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል 4 መሰረት በመንግስት ስም የተሰበሰበና ቀጥታ ወደ መ/ቤቱ ወይም ለማእከላዊ ግምጃ ቤት ገቢ መደረግ ያለበት የመንግስት ገንዘብ በተሰበሰበበት እለት እንደአግባብነቱ ወደ መስሪያ ቤቱ ወይም የማእከላዊ ግምጃ ቤት የባንክ ሂሳብ ገቢ መደረግ አለበት፡፡ እንደዚሁም በፌዴራል መንግስት የጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 3/2003 ክፍል አራት አንቀጽ 22/ንኡስ አንቀጽ 9 የመንግስት መ/ቤቶች በባንክ ማስተላለፊያ ዘዴ ወደ ባንክ ሂሳባቸው የሚገባውን ገንዘብ በየእለቱ የባንክ ገቢ ደረሰኝ ከባንክ በመሰብሰብ በትክክል በባንክ ሂሳባቸው መመዝገቡን ማረጋገጥ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቶችም በመመሪያዎቹ መሰረት እየሰሩ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት፡-

በቀን 01/11/2008 በውስጥ ኦዲተሮች በተደረገ በጥሬ ገንዘብ፣ በሰነድ እና በሲፒኦ የተገኘ ብር 3,432,281.04 ሲሆን በሰኔ 30/2008 የሂሳብ መግለጫ ላይ በ4101 በጥሬ ገንዘብ ሪፖርት የተደረገው ብር 379,549,282.71 በመሆኑ በልዩነት ብር 376,117,001.67 በብልጫ ሪፖርት የተደረገ መሆኑን፣

በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት፡-

- **በባንክ ሂሳብ ቁጥር** 1000026238537 **በሂሳብ መደብ** 4103 **የሂሳብ ማመሣዘኛ**(Trail balance) **ላይ ብር** 798,636.95 **ሚዛን የሚያሳይ ሲሆን በቀረበው የሰኔ** 30/2008 **ዓ.ም የባንክ ስቴትመንት ላይ ብር** 799,510.58 **የሚያሳይ በመሆኑ ልዩነት ብር** 873.63 **የሚያሳይ መሆኑ እና በተጨማሪም የባንክ ማስታረቂያ ያልተሰራለት መሆኑ፣**
- **በባንክ ሂሳብ ቁጥር** 1000026238521 **በሂሳብ መደብ** 4103 **የሂሳብ ማመሣዘኛ**(Trail balance) **ላይ ብር** 6,616,967.15 **የሚያሳይ ሲሆን ሰኔ** 30/2008 **ዓ.ም የቀረበው የባንክ ማስታረቂያ ላይ ብር** 4,264,587.62 **የሚያሳይ በመሆኑ በሪፖርት ላይ የሚታየው በብር** 2,352,379.53 **ከፍ ያለ በመሆኑ፣**

  በሁለቱም ቅ/ጽ/ቤቶች የቀረበው የሂሳብ መግለጫ ትክክለኛ ስለመሆኑ ማረጋገጫ መስጠት አልተቻለም፡፡

<u>ስጋት</u>

ማንኛውም ወደ ባንክ የሚገባ ገቢ በወቅቱ እየተመዘገበ በየወሩ ከባንክ ማስታረቂያ ጋር እየተመሳከረ ሪፖርት የማይደረግ ከሆነ እና በሳጥን ያለ ጥሬ ገንዘብ ተገቢው ቁጥጥር የማይደረግበት ከሆነ፣ በሪፖርት ላይ የሚገለጸው በባንክ ያለ ገንዘብ እና በሳጥን ያለ ጥሬ ገንዘብ ትክክለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ አስቸጋሪ ይሆናል፣ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል እንዲሁም ሪፖርቱ ተአማኒነት እንዳይኖረው ሊያደርግ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ እርምጃ</u>

በመመሪያው መሰረት የሚሰበሰበውን ገቢ ባንክ ስለመግባቱ እና በሌጀር በወቅቱ ስለመመዝገቡ መረጋገጥ አለበት፡፡ በልዩነት የሚታየው ገንዘብ ላይም አስፈላጊውን ማስተካከያ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

5. <u>ተሰብሳቢ ሂሳብን በተመለከተ</u>

ሀ) <u>በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 33,306,658.64 መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 **መሰረት፡- ለእያንዳንዱ ተሰብሳቢ ሂሳብ የሂሳብ ሌጀር ተሰርቶለት ክትትል በማድረግ የተሰብሳቢ**

ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠርና ሂሳቡም በወቅቱ እንዲወራረድ ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በተጨማሪም የፌዴራል መንግስት የገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 5/2003 አንቀጽ 16/4 መሰረት የውሎ አበልና የመንገሻ ቅድመ ክፍያ ሠራተኛው ስራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት(7) ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ተሰብሳቢ ሂሳቦች ተገቢው የቁጥጥር ስርአት የተዘረጋላቸውና በወቅቱም የሚወራረዱ መሆኑን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፡-

ተ.ቁ	የመ/ቤት/ቅ/ጽ/ቤት/ ስም	የተሰበብሳቢ ሂሳብ	የቆይታው ጊዜ
1	በሞጆ ቅ/ጽ/ቤት	6,271.93	ከ10 ወር እስከ 3 ዓመት
2	በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	32,706.94	ከ 2005 ዓ.ም ጀምሮ
3	በምዕራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	82,026.45	ከ2 ዓመት እስከ 23 ዓመት
4	በኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	4,681.63	ከ 1 ዓመት እስከ 6 ዓመት
5	በ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት	32,923,681.30	ከ6 ወር እስከ 2 ዓመት በላይ
6	በባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት	239,849.14	ከ2006 እስከ 2008 ዓ.ም
7	በከፍተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	17,441.30	ለ 8 ወራት የቆየ
	ድምር	33,306,658.64	

በድምሩ ብር33,306,658.64 በጊዜ ገደቡ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡

ስጋት

ማንኛውም ቅድመ ክፍያዎች በህግ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የማይሰበሰብ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ ያለአግባብ ለብክነት ሊጋለጥ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ ሳይሰበሰብ የቆየው የመንግስት ገንዘብ ከሚመለከታቸው አካላት ሊሰበሰብ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ሳይሰበሰቡ ረጅም ጊዜ የሚያስቆጥሩ ሂሳቦች እንዳይፈጠሩ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የሥራ አመራሩ ምላሽ

በመመሪያው መሰረት እርምጃ እየወሰዱ በሂደት ላይ ያሉ መሆኑንና ለዋናው መ/ቤት የተጠየቀ ሲሆን በቀጣይ በሚሰጠው ውሳኔ የሚሰረዝ መሆኑን ፣ እንዲሁም በቀጣይ አጣርተን የማስተካከያ እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን ገልጸዋል፤

ለ) <u>ማስረጃ የሌለውና ከማን እንደሚሰበሰብ የማይታወቅ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 144,735,887.49 መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማናቸውንም በጥሬ ገንዘብ የተከፈለ የቅድሚያ ክፍያ ሂሳብ በጊዜ ገደቡ የማይወራረድ ከሆነ ሂሳቡ በተሰብሳቢ ሂሳብ መያዝ አለበት በዚህ መሰረት የተሰብሳቢ ሂሳብ በቂ ማስረጃ ሲቀርብበት ብቻ በተሰብሳቢ ሂሳብነት መያዝ ያለበት ሆኖ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት መመሪያው ይገልጻል፡፡ በቅ/ጽ/ቤቶች ከዚህ መመሪያ አንጻር እየተሰራ መሆኑን ለማጣራት አዲት ሲደረግ፡-

በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት	ብር	4,398,290.12
በጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት		667,050.35
በምስራቅ አዲስ አበባ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት		50,455,432.92
በኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት		1,075.41
በድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	"	2,778,859.96
በጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	"	310,553.79
በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት	"	86,124,624.94
ጠ/ድምር	ብር	144,735,887.49

በትክክል ከመቼ ጀምሮ በተሰብሳቢነት እንደተመዘገበ የሚያረጋግጥ ማስረጃ የሌለው ከመሆኑም በተጨማሪ ከማን እንደሚፈለግ ወይም እንደሚሰበሰብ በትክክል የማይታወቅ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም ፡፡

<u>ስጋት</u>

በመመሪያው መሰረት በተሰብሳቢነት ለመዘገባቸው ሂሳቦች ተገቢው መረጃ ባለመኖሩ የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ እርምጃ</u>

በመመሪያው መሰረት በተሰብሳቢነት ለመዘገባቸው ሂሳቦች ተገቢው መረጃ ሊኖረውና አስቀድመው በሌጀር ሊመዘገቡ ስለሚገባ የሂሳቡን ምንነት በማጣራት ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግለት ይገባል፡፡

6. ተከፋይ ሂሳብን በተመለከተ

ሀ) ማስረጃ የሌለው እና ለማን እንደሚከፈል የማይታወቅ ተከፋይ ሂሳብ ብር 636,503,970.25 መኖሩ

ግኝት

የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት የመንግስት መስሪያ ቤቶች ማናቸውንም ወደፊት ክፍያ የሚፈጸምባቸው ሂሳቦች ተከፋይ ሂሳብነታቸውን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ሲቀርብና ስልጣን ባለው አካል ሲፈቀድ ብቻ በተከፋይ ሂሳብነት መያዝ እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ከዚህ አንጻር ቅ/ጽ/ቤቶች በ 2008 በጀት ዓመት ሂሳብ መግለጫቸው ላይ ሪፖርት ላደረጓቸው ተከፋይ ሂሳቦች በቂ ማስረጃና በትክክል የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶቹ እዳ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ተ.ቁ	የመ/ቤት/ቅ/ጽ/ቤት/ ስም	ማስረጃ የሌለው እና ለማን እንደሚከፈል፣የማይተወቅ ሂሳብ
1	በሞጆ ቅ/ጽ/ቤት	16,133.58
2	በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት	26,163,220.64
3	በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት	411,469.09
5	በጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	2,689,271.09
6	በምስራቅ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	305,644,838.75
7	በምዕራብ አ.አ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	35,577,225.60
8	በኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	1,180,495.25
9	በጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	5,267,057.30
10	በ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት	259,554,258.95
	ድምር በብር	36,503,970.25

ማስረጃ የሌለው እና ለማን እንደሚከፈል የማይታወቅ ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡

ስጋት

ማስረጃ የሌላቸው ሂሳብ በተከፋይነት የሚያዙ ከሆነ የመንግስት ገንዘብ አለአግባብ ሊባክን ይችላል፡፡ ለብልሹ አሰራርም በር ይከፍታል፡፡

የማሻሻያ ሀሳብ

በተከፋይ ሂሳብ ለመመዝገብ ሂሳቦቹ ተገቢው ማስረጃ ሊኖረው ስለሚገባ የሂሳቡን ምንነት በማጣራት ተገቢው ማስተካከያ ሊደረግለት ይገባል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች ሂሳቡ በተለያየ ምክንያት ማለትም (በሲስተም በውህደት በክልል ተከፋይና በመሳሰሉት) መከሰቱን ገልጸው ትክክለኛውን ተከፋይ ሂሳብ እንደገና ተፈትሾና ተጣርቶ ሪፖርት የሚያደርጉ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልጸዋል፡፡

ለ) <u>በወቅቱ ያልተወራረደ የተከፋይ ሂሳብ ብር 30,070,370.22</u> <u>መኖሩ</u>

<u>ግኝት</u>

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 አንቀጽ 8 ቁጥር 5 ከ ሀ-ሠ በተዘረዘረው መሰረት በየቅ/ጽ/ቤቱ በሂሳብ መግለጫ ላይ ለታየው ተከፋይ ሂሳቦች የሂሳብ ሌጀር ተሰርቶለት ተገቢው ክትትል እየተደረገባቸው በወቅቱ እንዲወራረዱ የሚደረግ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

ተ.ቁ	የመ/ቤት/ቅጽ/ቤት/ ስም	የተከፋይ ሂሳብ	የቆይታ ጊዜ
1	በኮምቦልቻ ቅ/ጽ/ቤት	95,224.15	ከ24/06 እስከ 30/10/2008
2	በጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት	1,631,310.71	ከአንድ ዓመት በላይ
3	በአዲስ አበባ ምስራቅ መካከለኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ጽ/ቤት	2,429,717.3	ሁለት ዓመት(2)- ዓመት ከአራት(4) ወር
4	የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት	25,914,118.06	ከሁለት ወር እስከ ሁለት ዓመት በላይ የቆየ፣
	ድምር	**30,070,370.22**	

በድምሩ ብር30,070,370.22 በወቅቱና በመመሪያው በተመለከተው የጊዜ ገደብ ያልተወራረዱ ሂሳቦች መኖራቸው ታውቋል፡፡

<u>ስጋት</u>

ተከፋይ ሂሳቦች ትክክለኛነታቸው እየተረጋገጠ ምዝገባ ካልተከናወነ ለብልሹ አሰራር በር ይከፍታል፡፡ መ/ቤቱንም ላልተፈለገ ዕዳ (ክፍያ) ሊዳርጉ ይችላሉ፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ተከፋይ ሂሳቡ በደንብና መመሪያው መሰረት በወቅቱ ለሚመለከታቸው አካላት መከፈል የሚገባ ሲሆን ሂሳቡ የሚከፈለው አካል ማወቅ ያልተቻለውን ሂሳብ ወደ ገቢ በመቀየር ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል፡፡

7. <u>የንብረት አስተዳደርን በተመለከተ</u>

ሀ) <u>የቋሚ እና የአላቂ ዕቃዎች አስተዳደር ቁጥጥር እና ምዝገባ በአግባቡ እየተከናወነ አለመሆኑ</u>

<u>ግኝት</u>

በመንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 58 (1-3) መሰረት የመንግስት ንብረት በሚገባ የክትትል ስርዐት የተዘረጋለት፣ ተገቢውን ጥበቃና እንክብካቤ የተደረገለት መሆኑን እና አገልግሎት የማይሰጥ ሆኖ ሲገኝ በወቅቱ እንዲወገድ የተደረገ መሆኑን እና በአንቀፅ 65 ና ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት ቅ/ጽ ቤቱ የንብረት ቆጠራ አድርጎ ቆጠራው ከንብረት መዝገብ ጋር እንዲመሳከር የሚደረግና ከወጪ ቀሪው የሚረጋገጥ መሆኑን ለማጣራት አዲት ሲደረግ፡-

በሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች፣

- የ2008 በጀት ዓመት የቋሚና የአላቂ ዕቃዎች ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም የቆጠራው ውጤት ከንብረት መቆጣጠሪያ መዝገብ(stock card) ጋር ለማመሳከር ያልተቻለ መሆኑ፣
- በየቅ/ጽ ቤቱ የንብረት ክፍል ውስጥ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ብዛት ያላቸው የኤሌክተወሮኒክስ እቃዎች ምንም ዓይንት ጥገናና እንክብካቤ ሳይደረግላቸው አንዱ በአንዱ ላይ ተደራርበው የሚገኙ መሆናቸው እና የቢሮ እቃዎች ያለአገልግሎት የሚገኙ መሆናቸው፣
- መወገድ የሚገባቸው የተለያዩ እቃዎች ተከማችተው መገኘታቸው
- የዕቃዎቹ መጋዘን ተንቀሳቃሽ ኮንቴነር የሆኑባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች ለዕቃዎቹ ደህንነት ያልተመቸ እና በየቦታው ተበታትኖ የተቀመጡ በመሆናቸው ከሌሎች ኮንቴነሮች ጋር ተቀላቅሎ የመነሳት ዕድላቸው የሰፋ መሆኑን፣

- የአንድ ቅ/ጽ/ቤት ትልቅ ጀነሬተር ለድህንነቱ አመቺ በሆነ ቦታ የተቀመጠ አለመሆኑን እንዲሁም ከንፋስ፣ ፀሐይ እና ዝናብ የሚከላከልለት ምንም ነገር አለመኖሩ በአዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

የተሸከርካሪ ሁኔታ በተመለከተ

በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት፡-

- የሰሌዳ ቁጥር ኮድ-(4) ET 06897 የሆነ ISUZU PICKUP መኪና የማይጠገን እና ሊታደስ የማይችል መሆኑ ቢታወቅም ንብረቱ ሳይወገድ ለረዥም ጊዜ መቆየቱ፣

በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት፡-

- የቅ/ፅ/ቤቱ የሆኑት ሁለት ተሽከርካሪዎች አገልግሎት ሳይሰጡ ተገቢ ጥበቃና እንክብካቤ ሳይደረግላቸው ለዝናብ፣ ለፀሀይ እና ለነፋስ ተጋልጠው የሚገኙ መሆናቸው፣
- ኒሳን (ሰሌዳ ቁጥር 4-16317 ኢት) የሆነች ተሽከርካሪ በመስሪያ ቤቱ ስም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር እና የተሸከርካሪው ህይወት ታሪክ በተሟላ ሁኔታ ያልተያዘላት መሆኑን፤

በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት፡-

- ኮድ 3.-19484 መኪና ከየት እንደመጣች የሚያስረዳ ሰነድ የሌለው መሆኑ፣
- ሁለት ሞተር ሳይክሎች (4-1317 እና 4-1320)በሌብሬ ላየ የተመለከተው የሻንሲ ቁጥር፣ የሞተር ቁጥር እና የመድን ተላላፊ ወረቀት ቁጥር በተሸከርካሪዎቹ ላይ ከሚገኘው የተለያየ መሆኑ፣

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት

- ሁለት መኪኖች የባለቤትነት ማረጋገጫ (ሊብሬ) የሌላቸው መሆኑን፣

ተረጋግጧል፡፡

<u>ስጋት</u>

ቅ/ጽ/ቤቶች የሚያስተዳድሯቸው የቋሚና ስቶክ ንብረቶች ተገቢ ጥበቃ እና እንክብካቤ የማይደረግላቸው ከሆነ እና መወገድ ያለባቸው ዕቃዎች በወቅቱ የማይወገዱ ከሆነ መስጠት

የሚገባቸው አገልግሎት እና ጥቅም ላይሰጡ ይችላሉ፡፡ የመንግስት ንብረት ለጥፋትና ለብክነት በቀላሉ ሊዳረግ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የንብረት ቆጠራ ከንብረት መዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ተመሳክሮ በውጤቱ መሰረት ተገቢው እርምጃ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ንብረቶች ካሉ አስፈላጊው ጥገና ተደርጎላቸው ወደ ስራ የሚገቡበት ሁኔታ ሊመቻች ይገባል፡፡ የማይጠገኑ እና አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ከሆኑም በንብረት አወጋገድ መመሪያ መሠረት መወገድ ይኖርባቸዋል፡፡

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

ሁሉም ቅ/ጽ/ቤቶች የሰው ሃይል እጥረት እና የእቃ ግምጃ ቤት ጥበት መኖሩን በመግለጽ አገልግሎት የማይሰጡ እቃዎች በተመለከተ ለማስወገድ ጥረት እየተደረገ መሆኑን፣ በአጠቃላይ የንብረት አጠባበቅ እና አያያዝ በተመለከተ ለወደፊቱ የማስተካከያ እርምጃ የሚወስዱ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ለ) **<u>የተተዉ፣ የተወረሱ እና ያልተወረሱ በህግ ሂደት ላይ ያሉ ንብረቶች አስተዳደር እና ቁጥጥር በአግባቡ የሚከናወን አለመሆኑ</u>**

<u>ግኝት</u>

በአዋጅ 859/2006 ዓ/ም አንቀጽ 61 እና 62 የተተዉ እና የተወረሱ ዕቃዎች የገበያ ዋጋ ያላቸው ከሆኑ በባለስልጣኑ በሽያጭ እንደሚያስወግዳቸው ወይም በህግ በተደነገገ ክልከላ ወይም ገደብ ምክንያት በጥቅም ላይ ሊዉሉ የማይችሉ ወይም የገበያ ዋጋ የሌላቸው ከሆኑ ባለስልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰኑ ዘዴዎች እንዲወገዱ ያደርጋል ሲል ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት ቅ/ጽ/ቤቶች የተተዉና የተወረሱ ዕቃዎችን አጠባበቅን አያያዝ ሁኔታ ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፡-

በየቅ/ጽ/ቤቱ

- በርካታ የተወረሱ እና የተተዉ የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ኬሚካሎች ፣የሴራሚክስ ማጣበቂያ (water proof adhesive chemical) እና አምፒሊፋየር ባትሪ

እንዲሁም ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ጎማዎች፣ ኮምፒተሮች፣ አዳዲስ አልባሳት እና ሌሎች ዕቃዎች ተከማችተው የሚገኙ መሆናቸው ፣

- በህግ ክርክር ረዥም ጊዜ በማስቆጠራቸው ጉዳያቸው እልባት ሳያገኝ ንብረቶች ለብልሽት እየተዳረጉ የሚገኙ መሆኑ፣
- በውርስ መጋዘን ውስጥ የተወረሱ ንብረቶች መዝገብ ያልተቋቋመላቸው በመሆኑ የንብረቶችን ከወጪ ቀሪ ለማወቅ የማይቻል መሆኑ፣

የተረጋገጠ ሲሆን፣ ከዚህም በተጨማሪ በውርስና ኮንትሮባንድ ምክንያት የተያዙ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ

በባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት፡-

- የተያዙና የተወረሱ ሁለት ሞተር ሳይክ ፣ አንድ ሞተር ሳይክል ባጃጅና 6 ተሽከርካሪዎች ተወርሰው እስካሁን ያልተወገዱ መሆኑን፣
- 18 ተሽከርካሪዎች መጠለያ ስላልተሰራላቸው በቆይታ ብዛት በዝናብና በጸሀይ ለእርጅና እየተዳረጉ መሆኑ፣
- አንድ ኤፍ ኤስ አር በቅ/ጽ/ቤቱ ስር የተገኘ ቢሆንም የንብረቱ ባለቤት የማይታወቅ መሆኑ ፣

በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

- በጊዜያዊነት በመጋዘን ተቀምጠው የሚገኙም ሆኑ በውርስ ተይዘው ባለቤቱ በማስታወቂያ ያልቀረቡና እስከ አንድ ዓመት (1) የቆዩ 39 ተሽከርካሪዎች በገላን መቅረጫ ጣቢያ የሚገኙ መሆኑን እና በመቅረጫ ጣቢያው ውርስ እንዲደረጉ ከገላን ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ደብዳቤ ቢላክም ውርስ ተደርገው በገቢ ያልተያዙ መሆኑ፣

በጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

- በህገወጥ አገባብ ተጠርጥረው የተያዙ ተሽከርካሪዎች በቀረበ ማስረጃ መሰረት 1 ተሽከረካሪ የሰሌዳ ቁጥር ያልተገለጸ፣ 2 ተሽከረካሪ ሻንሲ ቁጥር ያልተገለጸ እና 12 ተሽከርካሪዎች ሞተር ቁጥራቸው ተመዝግቦ ያልተያዙ ወይም ሞተር ቁጥር መኖር አለመኖሩ ያልተገለጸ መሆኑ እና ለአቧራ፣ ለፀሐይ፣ ለዝናብ በተጋለጠ ሜዳ ላይ ያለመጠለያ ለብልሽት ተዳርገው የሚገኙ መሆኑ ፣

በኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

- በሞዴል/265 እንዲሁም ሞዴል/270 የተገለጹ ሶስት (3) ተሽከርካሪዎች የሻንሲ ቁጥሩ እንዲሁም 12 ተሽከርካሪ ሞተር ቁጥራቸው ያልተገለጸ በመሆኑ መኪኖቹን ቅ/ጽ/ቤቱ ሲረከባቸው ተረጋግጦ ስለመሆኑ ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
- ለፀሐይ፣ ለዝናብ እና ለአቧራ ተጋልጠው በሜዳ ላይ ተቀምጠው የሚገኙ የተወረሱ ተሽከርካሪዎች የሚገኙ መሆኑ ፣

በድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

- በመጋዘን ያሉ 88 ተሽከርካሪዎች ሆነ ከመጋዘን ውጪ በሜዳ ላይ የሚገኙ 8 ተሽከርካሪዎች ያሉበት ቦታ የመኖሪያ አካባቢ በመሆኑ የተሽከርካሪዎች አካላት ቢጎድል ወይም ቢጠፋ ቁጥጥር ለማድረግ አመቺ አለመሆኑን ፣
- ለቁጥጥር በማያመች መልኩ ለፀሐይ፣ ለዝናብ እና ለአቧራ ተጋልጠው ሳር በቅሎባቸው መኪና ለመባል የመኪናው የላይ አካል ብቻ ያላቸው የተወረሱ ተሽከርካሪዎች መኖራቸው፣
- መቼና በምን ሁኔታ የማን የሚሉትን ጉዳዮች ለማወቅ የሚያስችል ሰነድ የሌላቸው አራት (4) ተሽከርካሪዎች የሚገኙ መሆኑ
- ተሽከርሪዎች የህግ ውሳኔ ወይም በውርስ ወደ ቅ/ጽ/ቤቱ ገቢ ሲደረጉ የተሽከርካሪው ዋና ዋና ክፍሎች በባለሙያ ተረጋግጦ በማስረጃነት የማይያዝ በመሆኑ የተሽከርካሪው አካል ቢጠፋ ወይም ከጥቅም ውጪ ቢሆን ቀድሞ ከነበረው ጋር ለማመሳከር አመቺ አለመሆኑ፣
- ኮድ 3 ድሬ 01473 ተሽከርካሪ ዳሽ ቦርዱ የሌለው መሆኑ እና ኮድ 3 ኢት 24906 ሲኖትራክ ባትሪ ኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ የሌለው መሆኑ፣
- ኮድ 2 አአ 97277 ላንድ ክሩዘር ተሽከርካሪ በ2003 ቀረጥና ታክስ ባለመክፈል የተያዘ ሲሆን ነገር ግን በህጉ መሰረት ወደ ውርስ መጋዘን ገቢ ተደርጎ ንብረቱን ከብልሽት ለመታደግ አስፈላጊው እርምጃ ባለመወሰዱ ንብረቱ ከጊዜ ብዛት በሜዳ ላይ ለፀሐይ ለዝናብና ለአቧራ ተጋልጦ ለብልሽት ተዳርጎ መገኘቱ፤
- መቼ እንደገባ የማይታወቅ የተተወ አንድ(1) የስካኒያ ሞተር፣ አንድ(1) የመኪና የኋላ አክስል ከነጎማው፣ ለረዥም ጊዜያት በጊዜያዊ የዕቃ ማከማቻ መጋዘን ተቀምጠው የሚገኙና ወደ ውርስ መጋዘን ተዛውረው እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ፣

- የቅ/ጽ/ቤቱ ንብረት የሆነ አንድ(1) ፎርክ ሊፍት በጊዜያዊ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን የሚገኝ መሆኑ እና የቅ/ጽ/ቤቱ ካልሆነ ንብረት ጋር በአንድነት የተቀመጠ ሲሆን ተሽከርካሪው በዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ወቅት ያልተቆጠረ ከመሆኑም በተጨማሪ የቅ/ጽ/ቤቱ የተሽከርካሪዎች ዝርዝር ውስጥ ያልተካተተ መሆኑ ፣

በጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

በጋምቤላ መቆጣጠሪያ ጣቢያ የውርስ መጋዘን ውስጥ

- ብዛታቸው 6 የሆኑ የተለያዩ ላንድ ክሩዘር መኪናዎች እና 3 ሞተር ሳይክል ለአቢራ፣ ለፀሐይ፣ ለዝናብ በተጋለጠ ሜዳ ላይ ያለመጠለያ ለብልሽት ተዳርገው የሚገኙ መሆኑ ፣

በላሬ መቆጣጠሪያ ጣቢያ

- አንድ(1) የጭነት መኪና ሚትሲ ቡሺ እና አንድ(1) ባጃጅ ለፀሐይ፣ ለዝናብ በተጋለጠ ሜዳ ላይ ያለመጠለያ ለብልሽት ተዳርገው የሚገኙ መሆኑ ፣

በአሶሳ መቆጣጠሪያ ጣቢያ

- ከህግ ማስከበር የስራ ሂደት በቀረበልን የመኪኖች ዝርዝር መረጃ መሰረት ሁለት (2) ቦክሰር ሞተር ሳይክል፤ አንድ (1) ቲዮታ ሚኒባስ፤ አንድ (1) ሲውዲ (swedy) ሞተር ሳይክል፤ አንድ (1) ባጃጅ ባለ 3 እግር እና፤ አንድ (1) አይሱዚ የጭነት መኪና ለረጅም ጊዜ ሳይወገዱ የቆዩ መሆኑ ፣

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት

- መ/ቤቱ በፍርድ ቤት ውሳኔ የወረሳቸውን የተለያዩ ተሽከርካሪዎችን ጉዳያቸው ያላለቀ 43 ተሽከርካሪዎች የሚገኙ መሆኑን፣

ለማወቅ ተችሏል።

<u>ስጋት</u>

የተተዉና የተወረሱ ዕቃዎች በወቅቱ የማይወገዱ ከሆኑ ለብልሽትና ላልተፈለገ የዕቀዎች ክምችት ምክንያት ሊሆን ይችላል። እንዲሁም የአከባቢ ብክለት እና የጤና ችግር ሊያስከትሉ ይችላሉ።

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

የተተዉ እና የተወረሱ ዕቃዎች በእቃዎቹ ላይ ብልሽት ሳይደርስባቸው የአወጋገድ ስርዓቱን በጠበቀ መንገድ ወደ ገንዘብ በመለወጥ ቀረጥና ታክሱ እንዲሰበሰብ ማድረግ እና የመጠቀሚያ ጊዜ ያለፈባቸው ዕቃዎችን በአከባቢው ላይ የጤና ጉዳት ሳያደርሱ እንዲወገዱ መደረግ ይኖርባቸዋል፡፡

ሐ) <u>በዱቤ ከተሸጡ የተወረሱ ዕቃዎችን ያልተሰበሰበ ሂሳብ ብር 621,050,644.38 መኖሩን</u>

<u>ግኝት</u>

በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ያሉ ዕቃዎች አወጋገድ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 56/2003 አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀጽ 1፣ በዚህ መመሪያ በተለያዩ አካላት በድርድር የሚሸጡ ዕቃዎችን የሸያጭ ገንዘብ ገዢዎች ዕቃውን በተረከቡ እስከ 45 ቀናት ባለው ጊዜ ውስጥ ባለስልጣኑ በሚያሳውቀው የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ ማድረግ ወይም በባንክ በተረጋገጠ ቼክ ክፍያ መፈጸም አለባቸው ተብሎ ተደንግጓል፡፡ በተጨማሪም በድርድር ለተሸጡ ዕቃዎች በተገለጸው ጊዜ ገንዘቡን ገቢ ያላደረገ ገዢ በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የተገለጸው የጊዜ ገደብ ካለፈበት ቀን ጀምሮ በስራ ላይ ባለው ከፍተኛ ምጣኔ ወለድ ይታሰብበታል ተብሎ በተደነገገው መሰረት እየተሰራ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት

- **ከ2000 እስከ 2008 ድረስ ከቀድሞ ጅንአድ ብቻ ያልተሰበሰበ የዱቤ ሽያጭ ሳይሰበሰብ እስከ 8 ዓመት የቆየ በድምሩ ብር. 471,107,635.76 ወለድ 138,992,799.63 በድምሩ 610,100,435.39 መኖሩን፣**
- **ከ2005 እስከ 2007 ድረስ ከአድስ ፋና ብቻ ያልተሰበሰበ የዱቤ ሽያጭ ሳይሰበሰብ እስከ 4 ዓመት የቆየ ብር 7,964,540.67 ወለድ 2,985,668.32 በድምሩ 10,950,208.99 መኖሩን፣**

ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

በዱቤ ለተሸጡ ዕቃዎች ክትትል እየተደረገ በወቅቱ ገቢው እንዲሰበሰብ የማይደረግ ከሆነ መንግስት ማግኘት የሚገባው ገቢ በወቅቱ እንዳያገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ይህን ጉዳይ በተመለከተ ባለፉት በጀት አመታት የአዲት አስተያየት በተደጋጋሚ አስተያየት የጠሰጠበት ቢሆንም ተግባራዊ አልተደረገም ፡፡አሁንም

- በዱቤ የተሸጡ ዕቃዎችን በአግባቡ መዝግቦ መያዝ ፣
- መመሪያው በሚያዘው መሰረት በወቅቱ ገንዘቡ እንዲሰበሰብ፣
- በህግ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ገንዘቡን ገቢ ከማያደርጉ ገዢዎች ላይ በመመሪያው መሰረት ወለዱ እየታሰበ ገቢው ሊሰበሰብ እንደሚገባ

በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

<u>የሥራ አመራር ምላሽ</u>

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት

ከቀድሞ ጅንአድና አዲስ ፋና ጋር ያለው ውል ከ2007 ግማሽ አመት ጀምሮ የተቋረጠ ሲሆን የሚፈለግባቸውን ዕዳ እና ወለድ ቁጭር ታስቦ እንዲከፍሉ በተደጋጋሚ ተቋሙ ጥረት ቢያደርግም ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ጉዳዩን በህግ አግባብ ለመፍታት እንዲቻል የመጨረሻ ማስጠንቀቂያ በደብዳቤ እንዲገለፅላቸው እና ጉዳዩ በፍ/ቤት የሚታይበት ሁኔታ እየተመቻቸ ይገኛል፡፡

8. **<u>ልዩ ልዩ</u>**

ሀ) <u>የስራ ልምድ የሌለው ሰራተኛ በውስጥ ዝውውር እንዲመደብ የተደረገ መሆኑ</u>

<u>ግኝት</u>

የባለስልጣኑ የውስጥ ዝውውር አፈፃፀም አስመልክቶ ለአንድ ስራተኛ በባለሥልጣኑ መ/ቤት ውስጥ ዝውውር የሚፈጸመው እኩል በሆነ የሥራ ደረጃና ደመወዝ ተመሣሣይ ወደ ሆነ የስራ መደብ ወይም ዝውውር የሚፈፀምበት ክፍት የሆነ ትይዩ የሥራ መደብ ደረጃ መሆኑን ይደነግጋል፡፡ ቅ/ጽ/ቤቶችም በዚህ መመሪያ መሰረት የውስጥ ዝውውሮችን እየፈጸሙ መሆኑን ለማጣራት አዲት ሲደረግ፡-

በመቀሌ ቅ/ጽ/ቤት፡-

በታህሳስ 25/2006 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር ቀ65/EMA-15/3973 **አቶ አማን ገ/ሚካኤል ኪሮስ** ሙሉ የስራ ልምዳቸው በወንጀል ምርመራ ቡድን ከፍተኛ ኦፊሰር ሲሆን በማኔጅመንት

ውሳኔ የያዙት ደሞዝ እና ደረጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ምንም የኦዲተርነት ልምድና ችሎታ ሳይኖራቸው ወደ ውስጥ ኦዲት በከፍተኛ ኦዲተር የስራ መደብ ላይ እንዲመደቡ የተደረገ ቢሆንም የኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን በህዳር 30/2008 ዓ.ም በቁጥር EA - 359/1/08 **የአቶ አማን ገ/ሚካኤል ኪሮስ** ሊያስመድባቸው/ሊያዘዋውራቸው የሚችል በቂ ልምድ የሌላቸው መሆኑን ገልጸ ዝዉወሩን የሰረዘ ቢሆንም ነገር ግን በቅ/ጽ/በቱ የባለሙያው የዝዉዉር ምደባቸው ያለመሰረዙና በተመደቡበት የዉስጥ ኦዲት ቡድን ውስጥ አሁንም እየሰሩ መሆናቸው በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

<u>ስጋት</u>

የባለሙያ ዝውውር በሚከናወንበት ግዜ አግባብነት ያለው የስራ ልምድና የትምህርት ማስረጃ የሌለው ከሆነ ስራተኛን አዘዋውሮ የማስራት አስራር (Job Rotation) ተግባርን ያላገናዘበ ምደባ በስራ ውጤታማነት ላይ ተፅህኖ ይፈጥራል፡፡በዋና መ/ቤት የተወሰኑ ውሳኔዎችን ተግባራዊ አለማድረግ በኃላፊነት ሊያስጠይቅ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ስራተኛው ያለዉን የስራ ልምድና ችሎታ በማገናዘብ ሊሰራበት ወደሚችልበት ተዛማጅ የስራ መደብ ላይ መዛወር ይኖርበታል፡፡ ወደፊትም የሰራተኛ ዝዉዉር ሲፈፀም የስራ መደቡ የሚፈልገዉን የስራ ልምድ እና ችሎታ ያገናዘበ መሆን አለበት፡፡

ለ) <u>የባለፉት አመታት የኦዲት ግኝቶች ላይ የእርምት እርምጃ ያልተወሰደባቸው በተመለከተ</u>

<u>ግኝት</u>

በፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ማቋቋሚያ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 669/2002 አንቀጽ 17(3) መሰረት ተመርማሪ መስሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋናው ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገኙ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አዋጅ አንጻር በየቅ/ጽ/ቤቶች በኦዲት ግኝቶች ላይ የእርምት/የማስተካከያ እርምጃ እየተወሰደ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፡-

በአዲስ አበባ ኤርፖርት ቅ/ጽ/ቤት፡-

- በድህረ እቃ አዲት መሰረት ቀሪ ሒሳብ ብር 14,280,708.54 እንዳለባቸው ከተረጋገጠ ድርጅቶች ገንዘቡ እንዲሰበሰብ የተገለጸ ቢሆንም እስካሁን ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በጊዜያዊነት ወደ ሀገር ውስጥ የገቡ እቃዎች ላይ በጊዜያዊነት የሚቆዩበት የጊዜ ገደብ ቢጠናቀቅም ቀረጥና ታክስ እስካሁን ያልተሰበሰበ ብር 19,236,101.52 መኖሩን፣
- በአቶ ዘመድኩን የጎደለው ብር 163,235.51 እስካሁን ገቢ አለመደረጉ ወይም ለማስከፈል ተገቢው እርምጃ ባለመወሰዱ በ2008 በጀት አመትም በተመሳሳይ ሁኔታ መገኘቱ ፣
- ለአዲት ተጠይቀው ያልቀረቡ 180 ዲክላራሲዮኖች አስካሁን አለመገኘታቸውና ሁኔታው አለመጣራቱ ፣
- በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ብር 2,280,827.11 እንዲወራረድ ማሳሰቢያ የጠሰጠ ቢሆንም ለማወራረድ ምንም እርምጃ አለመወሰዱ ፣

በባህርዳር ቅ/ጽ/ቤት፡-

- **የጉምሩክ ገቢን በተመለከተ**
  - ከአምባሰል የንግድ ስራዎች ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 2,120,323.85 ለመሰብሰብ ምንም እርምጃ አለመወሰዱ ፣
- **የሀገር ውስጥ ገቢን በተመለከተ**
  - እንዲሰበሰብ ወይም ማስረጃ እንዲቀርብለት አስተያየት የተሰጠበት ብር 124,086.36 አለመሰብሰቡ ወይም አስፈላጊው ማስረጃ እንዲቀርብ አለመደረጉ፣
- **በሃብት አስተዳደርን በተመለከተ**
- በሂሳብ መደብ 4203 የሰራተኞች ቅድመ ክፍያ የተመለከተው ብር 7,877.50 እንዲወራረድ ጥረት አለመደረጉ ፣

በሀዋሳ ቅ/ጽ/ቤት፡-

1. የተጨማሪ እሴት ታክስ በየወሩ ያላሳወቁ አራት ድርጅቶች ላይ የእርምት እርምጃ ያለተወሰደባቸው መሆኑ፡-

2. ሀ. በንግድ ትርፍ ሪፖርት እና በተጨማሪ እሴት ታክስ ማስታወቂያ መካከል በታየ ልዩነት ያልተከፈለ የንግድ ትርፍ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ በድምሩ 364,337.37 ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፡፡
3. ዓመታዊ የገቢ ግብር ያላሳወቁ 7 ግብር ከፋዮች ላይ የእርምት እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ፣
4. ንብረቱ ከታገደ ድርጅት(ሲዳማ ቡና ኃ/የተ/የግል ማህበር) ያልተሰበሰበ የግብር እዳ ብር 1,022,255.63 መኖሩ የተገለጸ ቢሆንም እስካሁን እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑን ፣
5. በባንክ ሂሳብ ቁጥር 2078 በሂሳብ መደብ 5026 የሂሳቡ መነሻ ሰነድ /ሂሳቡ ለማን እንደሚከፈል እና ለስንት ጊዜ የቆየ እንደሆነ የማይታወቅ እና ማስረጃ ተጠይቆ ሊቀርብለት ያልቻለ ብር 1,826,510.21 የእርምት እርምጃ ሳይወሰደበት አሁንም በተመሳሳይ ሁኔታ መገኘቱ ፣
6. ተከፋይ በሂሳብ ኮድ 5004 የደመወዝ ተከፋይ ሂሳብ ብር 14,126.93 ከባለፉት አመታት ጀምሮ ሲዞር የመጣ የእርምት እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ
7. ተሰብሳቢ በሂሳብ መደብ 4274 ብር 2490.98 ሳይሰበሰብ ከ 7 ዓመት በላይ የቆየ ቢሆንም እስካሁን ድረስ እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፣

በሞያሌ ቅ/ጽ/ቤት፡-

የእርምት እርምጃ ባለመወሰዱ በድምሩ ብር 439,185.21 ያልተሰበሰበ ሂሳብ መኖሩ ፣

በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

- የትራንስፖርት ወጪና ሌሎች ወጪዎች በትክክል ባለመወሰዳቸውና ደረሰኝ ባለመቅረቡ ምክንያት ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 820,708.78
- ያልተሰበሰበ ቀረጥና ታክስ ብር 24,402,714.42
- ሳይሰበሰብ ረጅም ጊዜ ያስቆጠረና እርምጃ ያልተወሰደበት ቀሪ ሂሳብ ብር 104,603,256.54 ፣ እንዲሰበሰብ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እስካሁን ካለመሰብሰቡም ተጨማሪ በአሁኑ አዲት ወቅት የገንዘብ መጠኑ ጨምሮ ተገኝቷል፡፡

በጅግጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

- **የጉምሩክ ገቢን በተመለከተ**
  - በተለያየ ምክንያት ያልተሰበሰበ ብር 401,501.71 ቀረጥና ጣክስ እንዲሰበሰብ አስተያየት የጠሰጠበት ቢሆንም እስካሁን አለመሰብሰቡ፣
- **የሀብት አስተዳደርን በተመለከተ**
  - የያዥና ጠቋሚ አበል ክፍያ ብር 105,630.10 ተገቢው ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣ተገልጸ ሂሳቡ እንዲሰበሰብ ወይም ማስረጃ እንዲቀርብ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም እስካሁን አለመሰብሰቡና ለወጪውም ማስረጃ አለመቅረቡ ታውቋል፡፡

በምስራቅ አዲስ አበባ መካከለኛ ቅ/ጽ/ቤት

- በ2006 በጀት ዓመት ኦዲት ከተደረገው የገቢ ሂሳቦች ውስጥ የ12 ግብር ከፋዮች በተለያየ የግብር ዓይነቶች ግብራቸውን ያላሳወቁ መሆኑን እና ግብሩ ስለመሰብሰቡ ያልተረጋገጠ መሆኑ፣

የ2007 በጀት ዓመት ኦዲት በተመለከተ

- 8 ግብር ከፋዮች የ2006 በጀት ዓመት ዓመታዊ ግብራቸውን የከፈሉ ስለመሆናቸው ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፡-
- በንግድ ትርፍ ማሳወቂያ ላይ ተመላሽ (Refund) ሂሳብ ብር 329,829.62 በስህተት ሁለት ጊዜ ተቀናሽ በማድረጉ ምክንያት ባላሳወቀው ሽያጭ ብር 329,829.62 ላይ ያልተሰበሰበ ንግድ ትርፍ ግብር ብር 98,948.89 በመኖሩ ግብሩ ያልተሰበሰበ መሆኑ፣

ተገልጸ እርምጃ እንዲወሰድ በስራ አመራሩ ሪፖርት የተገለጸ ቢሆንም ቅ/ጽ/ቤቱ በአስተያየቱ መሰረት እርምጃ አለመውሰዱ፣

በኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

- **የጉምሩክ ገቢን በተመለከተ**

በ2006 እና 2007 የበጀት ዓመት የኦዲት አስተያየት መሰረት በፊዋኦ ፣በድህረ እቃ አወጣጥ ኦዲትና በጊዚያዊነት ዋስትን ከገቡ እቃዎች በድምር ብር 28,134,805.75 እንዲሰበሰብ ወይም ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም በኦዲት አስተያየቱ መሰረት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

❖ **የሀገር ውስጥ ገቢን በተመለከተ**

❖ በ2006ና 2007 በጀት ዓመት የተለያየ የግብር ባለመክፈል የግብር ዕዳ ውሳኔ ማስታወቂያ ደርሷቸው እዳቸውን ባለመክፈላቸው ያልተሰበሰበ ግብር ብር 79,161,855.49

➢ የ2006 በጀት ዓመት ንግድ ትርፍ ግብር ያላሳወቁ ሰባት (7) ግብር ከፋዮች አሳውቀው ስለመክፈላቸው ማስረጃ ያላቀረቡ በመሆኑ እስካሁን ለመሰብሰብ የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ፣

በድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

የጉምሩክ ገቢን በተመለከተ

➢ በድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ቡድን እና በደንብ መተላለፍ ቡድን የቀሪ ቀረጥና ታክስ ውዝፍ እዳ ውሳኔ ደርሷቸው በቅ/ጽ/ቤቱ ሳይሰበሰብ የቆየ ብር 10,905,535.83 መኖሩ፣

የሀገር ውስጥ ገቢን በተመለከተ

➢ በአጠቃላይ ኦዲት እንዲሰበሰብ ውሳኔ ተሰጥቶ ያልተሰበሰበ ግብር ብር 37,801,737.68 መኖሩ

የሀብት አስተዳደርን በተመለከተ

➢ ለክፍያው ተገቢው ማስረጃ ያልቀረበ ብር 493,800.25 መኖሩ

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ዋና መ/ቤት

➢ በስራ ላልተገኙ ሰራተኞች ያለአግባብ የተከፈለ ደመወዝ በድምሩ ብር 412.12 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣

➢ ኤ.ኤም.ቢ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግ.ማ በክፍያ ቁጥር 6 በሰነድ ቁጥር BPV 0007902 ቀን 12/5/2007 የግንባታ ወጪ 6323 ብር 6,409,445.13 መመዝገብ ሲኖርበት ብር 4,328,774.41 በመመዝገቡ በልዩነት በብር 2,080,670.72 በማነስ ተመዝግቦ የተገኘው አስካሁን የሂሳብ ማስተካከያ ያልተሰራለት መሆኑ፣

- የባለስልጣን መ/ቤቱ ንብረት ለመሆናቸው ያልተረጋገጡ ሁለት ተሽከርካሪዎች ለጥገና ተብሎ በድምሩ ብር 232,634.03 የተከፈለው አሁንም ማረጋገጫ ሊቀርብላቸው ያልቻሉ ወይም ግንዘቡ ተመላሽ አለመደረጉ፣
- በባለስልጣን መ/ቤቱ ተቀጥረው ያሉ የዐቃቢ ህግ ባለሙያዎች ከመጋቢት/2007 - ሰኔ/2007 ለ47 ዐቃብያነ ህግ ሰራተኞች ከተከፈለው ደመወዝ መክፈል የነበረባቸው የስራ ግብር በድምሩ ብር 103,993.85 እስካሁን አለመሰብሰቡ በተጨማሪም ተመሳሳይ ስህተት በዚህ በጀት ዓመት ተፈጽሞ መገኘቱ ፣
- ሁለት ተሽከርካሪዎች ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት ከ6 ወር በጥገና ላይ ያሉ ተብሎ የተገለጸ ቢሆንም በአሁኑ ሰዓትም በተመሳሳይ ሁኔታ መገኘታቸው፣

ታውቋል።

<u>ስጋት</u>

ቅ/ጽ/ቤቶች በየአመቱ ሪፖርት ለሚደረጉት የኦዲት ግኝቶች አስፈላጊውን እርምጃ የማይወስዱ ከሆነ በየቅ/ጽ/ቤቱ የሚታዩ የአሰራር ክፍተቶች የማይሰተካከሉና ከጊዜ ወደ ጊዜ ችግሮቹ እየጎሉ ሊመጡ ይችላሉ። በኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ አለመውሰድ በኃላፊነት ሊያስጠይቅ ይችላል።

<u>የማሻሻያ እርምጃ</u>

ቅ/ጽ/ቤቶቹ በግኝቶቹ መሰረት ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ ይኖርባቸዋል። የእርምት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች ላይ የድርጊት መርሃ ግብር በመንደፍ የእርምት እርመጃ ለመውሰድ ክትትል መደረግ ይኖርበታል።

<u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>

በኦዲት ማሻሻያ ሀሰቦቹ መሰረት እርምጃ ለመውሰድ እንቅስቃሴዎች የተደረጉና ክስ ተመስርቶባቸው በክትትል ላይ ያሉ፤ በዋና መ/ቤት አቅርበው በቅሬታ ሂደት፤ የተመዘገበ ሀብት ባለመኖር መሰበብሰበሰ ያለተቻለ የአድራሻ መጥፋት ና የማስረጃዎች እጥረት የመሳሰሉት ያገጠሙ መሆን ገልጸው ክትትሉን እንደሚቀጥሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት

የ2008/2009 የተጠቃለለ የኦዲት ሪፖርት

I. <u>የፋይናንስና ኮሚኒኬሽን መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2008/2009 ዕቅድና ክንውን</u>

1.1 <u>የኦዲት ዕቅድና ክንውን በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና በበጀት አንፃር</u>

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደራጊው መ/ቤት ስም	የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት	በኦዲት የተሸፈነ የተሰተካከለ በጀት		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር	27/01/09	429,560,769	166,748,713	596,309,482.00
2	ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ	12/03/09	94,802,550	289,418,539	384,221,089.00
3	የኢትዮጵያ ብሮድካስት	08/02/09	22,767,305.72	43,447,550.00	66,214,855.72
4	የቤተመንግስት አስተዳደር	11/12/08	165,243,265	383,931,928	549,175,194.00
5	የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	30/01/09	15,703,536	14,828,000	30,531,536.00
6	የህብረት ስራ ኤጀንሲ	05/01/09	31,043,450		31,043,450.00
7	የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ	15/03/09	17,926,874	2,661,238	20,588,112.00
8	የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ	02/13/08	34,506,345		34,506,344.99
9	የብሄራዊ ስነ ልክ ኢንስትቲዩት	12/13/08	28,955,160		28,955,160.00
10	የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ	30/12/08	7,899,140		7,899,140.00
11	የመንግስት የፋይናንስ ድርጅቶች	2/13/08	10,119,850		10,119,850.00
12	ካርታ ስራ ድርጅት	22/03/09	30,885,800	18,000,000.	48,885,800.00
13	ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት	11/01/09	242,219,009	12,000,000.00	254,219,009.00
14	የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት	27/01/09	155,706,778	2,732,999	158,439,777.00
15	ፕሬስ ድርጅት	07/03/09	119,721,240		119,721,240.00
16	ቤተመዛግብትና ቤተመጻህፍት	13/03/09	35,320,692	60,200,000.0	95,520,692.00
17	ብሄራዊ ፕላን ኮሚሽን	19/03/09	42,149,898		42,149,898.00
18	የኢትዮጵያ ብሄራዊ ትያትር ቤት	09/12/08	22,325,000	30,750,000	53,075,000.00
19	ብሄራዊ የስብሰባ ማዕከል	09/12/08	20,634,020.	1,000,000.00	21,634,020.00
20	የኢትዮጵያ ግብርና	19/01/09	24,242,791		24,242,791.00
21	የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ	13/01/09	8,472,950		8,472,950.00
22	የመንግስት ግዥና ንብረት	03/04/09	527,440,878.24		527,440,878.24

ተ.ቁ.	አዲት የተደራጊው መ/ቤት ስም	የሂሳብ ሪፖርት ለአዲት የቀረበበት	በአዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
	ማስወገድ አገልግሎት				
23	የወጣቶችና ስፖርት አካዳሚ	06/01/09	40,351,435	5,000,000	45,351,435.00
24	ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር	23/03/09	73,310,006	28,500,000	101,810,006.00
25	የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ	20/12/09	14,254,630.00		14,254,630.00
26	ቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን	30/2/09	35,152,313	15,136,965	50,289,278.00
27	ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት	20/1/09	35,321,886		35,321,886.00
28	ፌዴሬሽን ም/ቤት	18/01/09	52,681,649	19,000,000	71,681,649.00
29	የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት	11/01/09	49,727,490		49,727,490.00
30	ብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር	29/02/09	8,878,965,053		8,878,965,053.00
31	የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን	06/01/09	443,280,490	200,000,000	643,280,490.00
32	መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ	02/12/08	148,400,902		148,400,902.00
33	የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት	11/12/08	173,102,80		173,102,80
34	የፌዴራል መንግስት የተጠቃለለ ሂሳብ				
	ድምር		11,859,093,155	1,293,355,932	13,152,449,087.95

የተሰጠው የኦዲት አስተያየት

ኦዲት በተደረጉ መ/ቤቶች የተሰጠው ኦዲት አስተያየት ሲተነተን ፤ ሰባት/7/ መ/ቤቶች ነቀፌታ የሌለበት(Clean opinion) ፤ ሃያ ሁለት/ 22/ መ/ቤቶች በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆኖ ጥቂት ስህተቶች በመኖራቸው ነቀፌታ ያለበት (Except for opinion) ፤ ሶስት/3/ መ/ቤቶች የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ /Adverse opinion/ እና አንድ/1/ መ/ቤት ስለሂሳቡ አቋም ለመውሰድ ያልተቻለባቸው መ/ቤቶች(Disclaimer opinion) ናቸው፡፡ /ዝርዝራቸው በአባሪ- 2 ተመልክቷል/

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች

1. ተሰብሳቢ ሂሳብ

1.1 ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ፡-

በፋይናንስ አስተዳደር ደንብ መሰረት ተሰብሳቢ ሂሳቦችን ለመከታተል ተገቢው የቁጥጥር ስርኣት መዘርጋቱንና ሂሳቡም በወቅቱ መወራረዱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤ በ24 መ/ቤቶች ብር 2,917,783,011.64 ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡/ዝርዝሩ በአባሪ- 6 ቀርቧል/

በመሆኑም ውዝፍ ሰነዱን በወቅቱ አለማወራረድ ለመንግስት ገንዘብ መጥፋት በር የሚከፍት ስለሆነ በአስቸኳይ መወራረድ እንዳለበት፤ለረጅም ዓመታት ሳይወራረዱ የተገኙት ሂሳቦች እንዲወራረዱ አስፈላጊው ክትትል እንዲደረግ ፤ሊሰበሰቡ በማይችሉት ላይ በመንግስት መመሪያ መሰረት ከመዝገብ እንዲሰረዙ እንዲደረግ በላክናቸው የስራ አመራር ሪፖርቶች አሳስበናል፡፡

1.2 በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ ልዩ ልዩ የአሠራር ችግሮች

የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር

በፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 3 መሰረት በሰኔ ወር የሚታየው የገቢ፣ የወጪ፣ የተሰብሳቢ፣ የተከፋይና የመሳሰሉት ሒሳቦች መደበኛ የሂሳብ ሚዛናቸውን መጠበቅ እንደሚኖርባቸው ይታወቃል፡፡

ይሁን እንጂ፡-

- በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4201 ተቀጽላ ሌጀር 0002 ብር 14,422.71
- በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4201 ተቀጽላ ሌጀር 0005 108.00

በድምሩ ብር 14,530.71 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን የሚታይ ሲሆን ምክንያቱ ተጣርቶ የሂሳብ ማስተካከያ ሊሰራለት ሲገባ በሪፖርት በመካተቱ የ2008 በጀት ዓመት የተሰብሳቢ ሂሳብ ሚዛን በብር 14,530.71 አላአግባብ ዝቅ ብሎ እንዲታይ የተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስለሆነም ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን ወይም በክሬዲት ወይም ብልጫ የሚታየው ጥሬ ገንዘብ ብልጫው ሊደርስበት የቻለበት ምክንያት ተጣርቶ በብልጫ ወይም በማነስ ሊታይ የቻለበት ምክንያት ተጣርቶ በሚገኘው ውጤት መሰረት እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

<u>የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን</u>

ከ2002-2008 ዓ.ም በዱቤ ካስተላለፈው ማስታወቂያ መሰብሰብ የነበረበት ውዝፍ ሂሳብ ብር 53,030,155.76 እስከ አሁን አለመሰብሰቡ ታውቋል፡፡

<u>የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ</u>

ሰኔ 30/2008 በቀረበው የሂሳብ ሪፖርት በተሰብሳቢ ሂሳብ ርዕስ 4274 ለሌሎች የመያዣ ሂሳቦች ላይ ከሚታየው ብር 466,520.86 ውስጥ ብር 438,902.91 የወጪ ማስረጃ ቀርቦለት በወጪ የተመዘገበ ሲሆን፤ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ አላአግባብ የሂሳብ ማስተካከያ በመሥራት በወጪ የተመዘገበው ተሰርዞ በተሰብሳቢ ሂሳብ የተመዘገበ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት</u>

ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች አገልግሎቶቻቸውን ለማስተዋወቅ እስከ 2008 ዓ.ም ከተላለፈው ማስታወቂያ መሰብሰብ የነበረበት፡-ብር 7,377,298.52 ከደንበኞች ሊሰበሰብ ይገባው የነበረውን ውዝፍ ሂሳብ አለመሰብሰቡ ታውቋል፡፡

ከላይ ለተመለከቱት ግኝቶች፡-

- በውዝፍ የሚገኘው ተሰብሳቢ ሂሳብ በአስቸኳይ እንዲወራረድ፤
- ባልተለመደ የሂሣብ ሚዛን የሚታየው የሂሣብ ማስተካከያ እንዲሠራለት፤
- የዕቃ ግዢ ሠራተኞች ለተለያዩ አገልግሎቶች ማስፈጸሚያ በቅድሚያ የወሰዱት ገንዘብ በደንብና መመሪያ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲያወራርዱ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል እንዲደረግ፤

- በውዝፍ የሚገኘው የዱቤ ሽያጭ ሂሳብ እንዲሰበሰብ ተገቢው የመፍትሄ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባና ለወደፊቱ ድርጅቶቹ የዱቤ ሽያጭ ስርአቱን ሊፈትሹ እንደሚገባ፤
- የወጪ ማስረጃ የቀርበለት ሂሳብ ከተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ ተሰርዞ በወጪ እንዲመዘገብ የስራ አመራሩን አሳስበናል፡፡

2. <u>የገቢ ሂሣብ</u>

<u>የቤተመንግስት አስተዳደር</u>

2.1 <u>ያልተሰበሰበ ገቢ</u>

ታህሳስ 7 2008 በወጣው አዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ በወጣው ጨረታ መሠረት እና ጥር 21/2008 በተፈፀመ የስምምነት ውል ሰነድ መሠረት 592 የደለቡ በሬዎች የአንዱ ዋጋ ብር 14,000.00 በጠቅላላ ብር 8,288,000.00 ለሻግ አስመጪና ላኪ ኢንተርፕራይዝ ለተባለ የግለሰብ ድርጅት የተሸጡ ቢሆንም ገንዘቡ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ስለሆነም ገንዘቡን ባልከፈሉት ግለሰብ ላይ ገንዘቡን እንዲከፍሉ ተገቢው ክትትል እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

<u>የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን</u>፡

<u>በወቅቱ ባንክ ገቢ ያልተደረገ ጥሬ ገንዘብ</u>

በፌዴራል መንግሥት የጥሬ ገንዘብ አሰተዳደር መመሪያ 3/2003 ክፍል 4 አንቀጽ 22 ተራ ቁጥር 5 መሰረት የተሰበሰበ ገቢ በየቀኑ ወደ ባንክ ሂሣብ የገባ መሆኑ ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ በ3 የገቢ ደረሰኞች የተሰበሰበው በድምሩ ብር 26,510.00 ከ1 ወር እስከ 2 ዓመት ባንክ ያልገባ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስለሆነም የዕለቱ ገቢ በቀኑ ወደ ባንክ ገቢ ለመደረጉ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

<u>የወጣቶችና ስፖርት አካዳሚ</u>

<u>በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ ህግ መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ</u>

ለ1 ኃላፊ ከተከፈለው የኃላፊነት አበል ላይ የስራ ግብር ብር 8,856.96 ያልተቀነሰ መሆኑ ታውቋል፡፡

ለ1 ኃላፊ ከሐምሌ 1 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥር 30 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ ብር 615.64 የሕክምና መዋጮ ተቀናሽ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

በመሆኑም ተቀናሽ ያልተደረገው የሥራ ግብር ከደመወዝ ላይ እየተቀነስ ለሚመለከተው አካል ገቢ መደረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

2.2 <u>በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሚታዩ ሌሎች ዋና ዋና የአሠራር ድክመቶች</u>

<u>የቤተመንግሥት አስተዳደር</u>

<u>በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ የገቢ ሂሳብ</u>

- ማንኛውም የገቢና የወጪ ሂሳብ በመንግስት በወጣው የፋይናንስ አስተዳደርና የሂሳብ አወቃቀር ስርዓት መሰረት ተመዝግቦ ሪፖርት እንዲደረግ የታዘዘ ቢሆንም በ2008 በጀት ዓመት ከተለያዩ የመንግስት ተቋማት ለመስተንግዶ አገልግሎት ገቢ የተደረገው ብር 2,187,238.27 የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ የተቆረጠለት ቢሆንም በገቢ ሂሳብ ርዕስ ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባው በተከፋይ ሂሳብ መደብ 5028 በክሬዲት ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም በተገቢው የሂሳብ ርዕስ እንዲመዘገብ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

2.3 <u>የማስከፈያ የዋጋ ተመን ወይም ታሪፍ የሌለው ገቢ</u>

<u>የቤተመንግሥት አስተዳደር</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 ስለፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር ክፍል 4.21.1 የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ለሚያቀርቡት አገልግሎት አዲስ ተመን/ ዋጋ ወይም በነባር ዋጋ ላይ የሚደረግን ለውጥ በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሃሳብ በሚኒስትሩ በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርበው ማስፀደቅ እንደሚኖርባቸው የተደነገገ ቢሆንም ለተለያዩ የመንግስት ተቋማት ከሰጠው የመስተንግዶ አገልግሎት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ብር 2,187,238.27 ገቢ የሰበሰበ ቢሆንም፤ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀ የአገልግሎት አይነቶች ዝርዝር (source of revenues) እና ለእያንዳንዱ አገልግሎት የማስከፈያ የዋጋ ተመን ወይም ታሪፍ (Charge Rates) የሚገልጽ ሰነድ የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የብሔራዊ የሥነ ልክ ኢንስቲትዩት</u>

ኢንስቲትዩቱ ከሚሰጠው ሳይንስና ቴክኖሎጂ አገልግሎት በበጀት ዓመቱ ውስጥ ብር 1,397,944.06 የሰበሰበ ቢሆንም፤ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፀደቀ የቴክኖሎጂ አገልግሎት አይነቶች ዝርዝር (source of revenues) እና ለእያንዳንዱ የቴክኖሎጂ አገልግሎት

የማስከፈያ የዋጋ ተመን ወይም ታሪፍ (Charge Rates) የሚገልጽ ሰነድ የሌለው መሆኑ ታውቋል፡፡

ስለሆነም የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ለሚያቀርቡት አገልግሎት የማስከፈያ የዋጋ ተመን ወይም ታሪፍ እንዲሁም አዲስ ተመን/ ዋጋ ወይም በነባር ዋጋ ላይ የሚደረግን ለውጥ በሚመለከት ያላቸውን የውሳኔ ሃሳብ በሚኒስትሩ በኩል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት አቅርበው ማስፀደቅ እንደሚኖርባቸው አሳስበናል፡፡

<u>የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት</u>

ድርጅቱ በበጀት ዓመቱ ለመሰብሰብ ያቀደውን ገቢ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ2008 በጀት ዓመት ከተለያዩ የገቢ ማስገኛ የስራ ዘርፎች ለመሰብሰብ ከታቀደው ብር 119,721,240.00 ውስጥ መሰብሰብ የተቻለው ብር 98,433,594.45 (82%) በመሆኑ የገቢ እቅዱ ብር 21,287,645.55 በማነስ የሚታይ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ስለሆነም ለወደፊቱ የገቢ ዕቅድና ዝግጅት በጥናትና በመረጃ ተደገፈ መሆን እንዳለበት አሳስበናል፡፡

<u>በተከፋይ ሂሳብ መያዝ ሲገባው በገቢ የተመዘገበ ሂሳብ</u>

<u>የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት</u>

ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አገልግሎት የሚሰጡ 6 ተሽከርካሪዎች መግዣ ብሔራዊ ባንክ ወደ አገልግሎቱ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000003784995 ገቢ የተደረገው ብር 6,000,000.00 ለተሽከርካሪዎች ግዥ ማስፈጸሚያ ተለይቶ የተላከ የአደራ ወይም የመያዣ ሂሳብ በመሆኑ በተከፋይ ሂሳብ መያዝ ሲገባው የገቢ ደረሰኝ ቁጥር 0002807 ገቢ ተቆርጦለት አገልግሎቱ ከተሽከርካሪዎች ሽያጭ ከሚያገኘው ገቢ ጋር ተካቶ በገቢ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

ስለሆነም አላግባብ በገቢ የተያዘው ሂሳብ ማስተካከያ ተሰርቶለት በተከፋይ ሂሳብ እንዲያዝ አሳስበናል፡፡

3. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦችን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

3.1 ምንም ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ

የመ/ቤቱ ስም	የገንዘብ ልክ
የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን፤	12,660,000.00
የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት	2,276,002.43
ድምር	**14,936,002.43**

ስለሆነም ደጋፊ የሂሳብ ሰነዶችና አግባብነት ያላቸው ማስረጃዎች ሊቀርቡ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.2 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

የመ/ቤቱ ስም	የገንዘብ ልክ
የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት	115,837.06
የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር	38,088.33
የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን	24,974.89
የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽቤት	79,375.00
ወጣቶችና ስፖርት አካዳሚ	94,056.45
የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን	3,088.80
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት	75,271.00
ድምር	**430,691.53**

የተሟላ ደጋፊ የክፍያ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ማስረጃ እንዲቀርብ ሆኖ ማስረጃው ከወጪው ጋር እንዲያዝ፤ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ የተመዘገበው ሂሳብም ትክክለኛው የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ እንዲቀርብለት ስራ አመራሩን አሳስበናል፡፡

3.3 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለ አግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች

የመ/ቤቱ ስም	የገንዘብ ልክ
መለስ ዜናዊ ስራአመራር አካዳሚ	2643.00
የኢትዮጵያ ወጣቶችና ስፖርት አካዳሚ	805,336.52
የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር	2,154.60
የፕሬዚዳንት ጽ/ቤት	8,733.40
የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን	1,046.50
የባህልና ቱሪዝም ሚ/ር	403,500.00
የብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻህፍት ኤጀንሲ	62,500.00
የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን	68,000.00
ድምር	**1,353,914.02**

ያላግባብ የተከፈው ገንዘብ ከሚመለከታቸው ላይ ተመላሽ እንዲደረግ፣ ሳይፈቀድ ለተከፈለውም ፈቃድ ሊኖረው እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.4 በመመሪያ መሰረት ያልተከፈለ ውሎ አበል፤

የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያና የሚኒስትሮች ም/ቤት ታህሳስ 27/2003 ዓ.ም ባወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2001 አንቀጽ 10/1/ሀ መሰረት ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ ከመደበኛው ስራው ውጭ ወደ ሌላ የስራ ቦታ ለስራ ጉዳይ ሄዶ ሲመለስ ዕለቱን መመለስ ካልቻለ በስራ ተሰማርቶ ቁርስ፣ ምሳ እና እራት በተመገበባቸው ቦታዎች (ክልል/ዞን/ወረዳ) ከተማ መሰረት ተከፋፍሎ መከፈል እንዳለበት የደነገገ ቢሆንም የሚከተሉት መ/ቤቶች በመመሪያው መሰረት ያልፈጸሙ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	የገንዘብ ልክ
1	የሴቶችና ሕጻናት ጉዳይ ሚኒስቴር	20,865.00
2	የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን	26,428.10
3	የቤተመንግስት አስተዳደር	21,600.90
4	የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ	425,008.05
5	የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር	12,766.50
6	የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር	559,765.00
7	የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን	252,245.50
8	የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት	76,982.82
9	የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ	99,961.95
10	የብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻህፍት ኤጀንሲ	1,694,112.68
11	የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቴአትር	92,663.24
12	የኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል	4258.35
	ድምር	**3,286,658.09**

ስለሆነም አላግባብ ለስልጠናም ሆነ ለውሎ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ ለወደፊቱም በመንግስት ታምኖባቸው በወጡ አዋጆች ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት እንዲፈጸም በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.5 የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች

ተ.ቁ	አዲት ተደራጊው መ/ቤት	የግዥው ዓይነት	ጨረታ ያልወጣለት	ፕሮፎርማ ያልተሰበሰበለት	ጠ/ድምር
1	ወጣቶችና ስፖርት አከዳሚ	የምግብ አቅርቦት	642,281.08		642,281.08
		መስተንግዶና የመኪና ጥገና		188,027.94	188,027.94
2	መለስ ዜናዊ አመራር አካዳሚ	የጽዳት አገልግሎት		220,800.00	220,800.00
3	የቤተመንግስት አስተዳደር	የእንስሳት መኖ		80,868.00	80,868.00
		የማሽን ጥገና		64,768.81	64,768.81
		ለማጓጓዣ ትራንስፖርት		70,408.62	70,408.62
		አላቂ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ		838,302.25	838,302.25
4	የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ጽቤት	መስተንግዶ		473,444.96	473,444.96
5	የመድን ፈንድ አስተዳደር ኤጀንሲ፣	የተሸከርካሪ ጥገና	203,732.35		203,732.35
		ተሸከርካሪ ጥገናና ማስታወቂያ		294,223.94	294,223.94
6	የቅርስ ጥናትና ጥበቃ ባለስልጣን	የአገልግሎት ግዥ	1,099,655.28		1,099,655.28
		መስተንግዶ		831,944.68	831,944.68
7	የብሔራዊ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን፣	መስተንግዶ		36,191.74	36,191.74
8	የባህልና ቱሪዝም ሚ/ር፣	የቢሮ ኪራይ	3,123,385.16		3,123,385.16
		ለአገልግሎት ግዥ		3,298,774.22	3,298,774.22
9	ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን፣	መስተንግዶ		436,994.39	436,994.39
10	የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ	የመስተንግዶ አገልግሎት	235,793.00	11,600.00	247,393.00
11	የመንግስት የፋይናንስ ድርጅቶች ኤጀንሲ	የመስተንግዶ አገልግሎት		267,547.75	267,547.75
12	የብሔራዊ የሥነልክ ኢንስትቲዩት	የመስተንግዶ አገልግሎት		117,440.00	117,440.00
13	በኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን	የመስተንግዶ አገልግሎት		31,533.80	31,533.80
14	ፌደራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ	የአገልግሎት ግዥ	3,235,009.18		3,235,009.18
	ድምር		8,539,856.05	7,262,871.10	15,802,727.15

ስለሆነም ግዥ ሲፈጸም የግዥ ደንብና መመሪያን ተከትሎ መሆን እንደሚኖርበት በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡\

3.6 በብልጫ የተከፈለ ሂሳብ

የመ/ቤቱ ስም	ለግንባታና የተለያዩ ግዥዎች ወጪ	ለውሎ አበል፤ ለደመወዝና ሌሎች ወጪዎች
የብሔራዊ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን		3,744.92
የኢትዮጲያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን፡	2,881.5	
የባህልና ቱሪዝም ሚ/ር		38,131.65
የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ	1,050.00	
የፌዴራል ህብረት ሥራ ኤጀንሲ		11,750.00
የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለሥልጣን	466,500.00	
ድምር	470,431.50	53,626.57

በመሆኑም በብልጫ የተከፈለው ሂሳብ ተመላሽ እንዲደረግ ለወደፊቱም ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳይከሰት ጥንቃቄ መደረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

3.7 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት ሂሳብ

የመ/ቤቱ ስም	የግንዘብ ልክ
የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን	205,698.20
ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት	149,602.79
የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን	5,879.23
ድምር	361,180.22

ስለሆነም የንብረት ገቢ ደረሰኝ ለሌላቸው ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሊሰራላቸውና ገቢ ሊደረጉ እንደሚገባ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.8 ተመላሽ ያልተደረገ የውጭ ሀገር የውሎ አበል

ከቤተ መንግስት አስተዳደር ብር 19,875.00 ፤

ከባህልና ቱሪዝም ሚ/ር ብር 11,111.08

በድምሩ ብር 30,683.08 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስለሆነም መ/ቤቶቹ ከሚመለከታቸው ላይ ተመላሽ እንዲያደርጉ በላክነው ስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

3.9 <u>ከመኖሪያ ቤት አበል፤ ከትርፍ ሰዓት ክፍያ እና ከኃላፊነት አበል ላይ ያልተቀነሰ የሥራ ግብር</u>

የመ/ቤቱ ስም	የገንዘብ ልክ
የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት	121,040.99
የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ	8856.96
የባህልና ቱሪዝም ሚ/ር	6,300.00
ድምር	136,197.95

3.10 <u>ሪፖርት ያልተደረገ የወጪ ሂሳብ</u>

<u>የቤተመንግስት አስተዳደር</u>

- በፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት ቁጥር 6/3 የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች እንዲመዘገቡ ለማድረግ በሚያስችሉ ተለይተው በተዋቀሩት የሂሳብ መለያ ቁጥሮች መሠረት ሂሣባቸውን መመዝገብ እንደአለባቸው የተገለጸ ቢሆንም ብር 1,521,926.47 በተገቢው የወጪ አርዕስት ተመዝግቦ ሪፖርት መደረግ ሲገባው አላግባብ በተከፋይ ሂሳብ ርዕስ 5028 በወጪ (ዴቢት) በመያዙ በበጀት ዓመቱ የወጪ ሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ ታውቋል፡፡

4. <u>የተከፋይ ሂሳብ</u>

4.1 ለባለጥቅሙ ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ

የተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ለሚመለከታቸው መከፈሉና ተያዘውም ተከፋይ ሂሳብ ትክክል ስለመሆኑ አዲት ሲደረግ፤ በ20 መ/ቤቶች ብር 375,652,461.94 በወቅቱ ያልተከፈለ ሂሳብ ተገኝቶል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ- 31 ተመልክቷል/

4.2 <u>በተከፋይ ሂሳብ ዙሪያ የታዩ ዋና ዋና የአሠራር ድክመቶች</u>

የቤተመንግስት አስተዳደር፡

- በፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል ሁለት አንቀፅ 8/5 ለእያንንዱ የተከፋይ ሂሳብ የሂሳብ ሌጀር በመክፈት ክትትል ማድረግ እንደሚገባ የተመለከተ ቢሆንም ከግንባታ ክፍያ ሂሳብ ላይ ተቀናሽ የተደረገ

የመያዣ ሂሳብ ብር 1,471,036.74 ገንዘቡን ያስያዘው የህንፃ ተቋራጭ ስም እና ያከናወነው ግንባታ ወይም የፕሮጀክቱ ዓይነት የሚገልጽ ተቀጽላ ሌጀር የሌለ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስለሆነም የዕዳ ክምችት እንዳይበዛ ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ ለባለጥቅሙ እንዲከፈሉ አሳስበናል፡፡

5. <u>የበጀት አጠቃቀም</u>

5.1 <u>ለየሂሳብ መደቡ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የሆነና ያልተሰራበት በጀት</u>

አዲት ለተደረጉት መሥሪያ ቤቶች በ2008 በጀት ዓመት ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሳብ ሲመዛዘን፡-

በአምስት መሥሪያ ቤቶች ከመደበኛ በጀት ብር 519,9547.71 እና በአንድ መ/ቤት የካፒታል ብር 747,935.81 ከበጀት በላይ የወጣ ሲሆን፤ ከ10% በላይ መደበኛ በጀት በ17 መ/ቤቶች ብር 5,768,429.81፤ በአስራ ሁለት መሥሪያ ቤቶች ከካፒታል ብር 187,608,941.6፤ ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መኖሩ ታውቋል፡፡

/ዝርዝሩ አባሪ- 33 ተያይዟል፡፡/

ስለሆነም የተፈቀደውን በጀት በአግባቡ ስራ ላይ ማዋል እንዲቻል በጥናትና በመረጃ የተደገፈ የበጀት እቅድና ዝግጅት እንዲዘጋጅ ስራ አመራሩን አሳስበናል፡፡

6. <u>የዕቃና ንብረት አስተዳደር</u>

6.1 ለዕቃና ንብረት አስተዳደር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት አዲት ሲደረግ፤

- ለቋሚ ንብረት መዝገብ ያልተቋቋመባቸው …… በ2 መ/ቤቶች
- ለቋሚ ንብረት የመለያ ቁጥር ያልተሰጠ……..በ13 መ/ቤቶች
- የአላቂ ዕቃዎች ምዝገባ ያልተከናወነባቸው…….በ4 መ/ቤቶች
- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያልተካሄደባቸው…….በ7 መ/ቤቶች
- ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያደረጉ ሆነው፣ ከመዝገብ ጋር ያላገነዘቡ……በ4 መ/ቤቶች
- ያልተወገዱ ንብረቶች……. በ16 መ/ቤቶች

መኖሩ ተረጋግጦል፡፡/ዝርዝራቸው በአባሪ-34 ተመልክቷል/

6.2 <u>ሌሎች የንብረት አያያዝ ድክመቶች የታዩባቸው መቤቶች</u>

መለስ ዜናዊ ስራ አመራር አካዳሚ

- የአካዳሚው የንብረት አስተዳደር ሥርዓት የፌዴራል መንግስት ባወጣው የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት እየተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ አዲት

ሲደረግ ፡-አካዳሚው በኦሮሚያ ክልል የፊንፊኔ ዙርያ ልዩ ዞን ሱለልታ ከተማ የሚገኘው የኢህአደግ ጽ/ቤት የተረከባቸው ግንባታቸው የተጠናቀቀና በግንባታ ላይ ያሉ የተለያዩ በቁጥር 16 ሕንፃዎች፤

- ለግንባታ የሚውሉ 33 ዓይነት የተለያዩ የግንባታ ዕቃዎች፤
- የተለያየ መጠን ያላቸው ቀጥሎ የተመለከቱት 4 ትላልቅ የኤሌክትሪክ ጀኔሬተሮች፡-

በአካዳሚው የንብረት ክፍል ሰራተኛ ርክክብ የተፈጸመ ቢሆንም፤ ንብረቶቹ በንብረት ገቢ ደረሰኝ /ሞዴል 19/ ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ በተጨማሪም የኤሌክትሪክ ጀኔሬተሮቹ አገልግሎት ላይ ያልዋሉ መሆናቸውና ተገቢው ጥንቃቄና እንክብካቤ ሳይደረግላቸው ለብልሽት ሊዳረጉ በሚችሉበት ሁኔታ መቀመጣቸው በኦዲት ዳሰሳና ቅኝት ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን

- ሰኔ 2008 የባለስልጣን መ/ቤቱ የቋሚ እና አላቂ ንብረት ቆጠራ የተካሄደ ሲሆን አንድ ላፕቶፕ ኮምፒዩተር፣ አንድ ሲዲኤምኤ፣ አንድ ስትላይት ሀንድ ስኒስ (Stlaight hand snees) እና አንድ መጽሐፍ በቆጠራ ወቅት በጉድለት የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር

- በውስጥ ኦዲት ሪፖርት መሰረት ሰኔ 30 2008 በተከናወነው አመታዊ ቆጠራ 5 ትልቅ ስቲከሮች፣ ሁለት ሊትር የሞተር ዘይት (Quest 2T) እና 1 ኪሎ ግሪስ በማነስ እንዲሁም 34 ፓኬት መካከለኛ አግራፎች እና ብዛታቸው 22 የሆኑ መካከለኛ ስቲከሮች በብልጫ የተገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡
- በቋሚ ንብረት መጋዘንም ሆነ በአላቂ እቃዎች መጋዘን ውስጥ ለተቀመጡ እቃዎች ቢን ካርድ የሚጠቀሙ ቢሆንም ለሁሉም ንብረቶች ቢን ካርድ ባለመኖሩ በምትኩ ነጭ ወረቀት የሚጠቀሙ በመሆኑ በቀላሉ በንፋስ ሊወሰድና ሊጠፋ የሚችል መሆኑ ታውቋል፡፡

የቤተ መንግሥት አስተዳደር

ብሄራዊ ቤተ መንግስት

- ባልደራስ ፈረስ ስፖርት ግቢ ንብረት የመጠበቅ እና ንብረት ገቢና ወጪ የማድረግ ኃላፊነት የፈረስ ስፖርት አሰልጣኝ ከዋና ስራቸው በተጨማሪ ስራውን ደርበው እንዲሰሩ የተደረገ መሆኑ፡
- የተሰራባቸው የገቢ ደረሰኞች ወደ ሰነድ ክፍል ተመላሽ የማይደረጉ መሆኑ አግባብ አለመሆኑን በመጥቀስ በውስጥ ኦዲት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም የማሻሻያ እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፡

በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡

ድሬዳዋ ቤተ መንግስት

- ንብረቶች ገቢና ወጪ የሚደረጉት በቤተ መንግስቱ ኃላፊ መሆኑ፤
- የቤተ መንግስቱ ንብረት ጠባቂና ገንዘብ ያዥ ለሚጠብቁት ንብረት ተመጣጣኝ ዋስትና እንዲያቀርቡ አለመደረጉ፤
- ለቤተ መንግስቱ የሚላኩ የደንብ ልብሶች የአካባቢውን የአየር ጠባይና የሰራተኞቹን ልኬት ያላገናዘበ መሆኑ በሰራተኞች ዘንድ ቅሬታ የፈጠረ መሆኑ፤
- ከዚህም በተጨማሪ ንብረት የሚጠበቅበት ግምጃ ቤት የመግቢያ በር የእንጨት በር በመሆኑ በንብረት ጠባቂው አማካኝነት በሚስማርና በኮምፓልሳቶ የተጠገነና በቀላሉ ሊከፈት የሚችል መሆኑ፤
- በቤተ መንግስቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች እጅግ መስህብነት ያላቸው እና ታሪካዊ የሆኑ የተለያዩ ጌጣጌጦችና ሌሎች እቃዎች ቢኖሩም በሩም ሆነ የበሩ ቁልፍ በማንኛውም ሰው በቀላሉ ሊከፈቱ ስለሚችሉ ንብረቶቹ ለስርቆት የተዳረጉ መሆናቸው፤
- በግቢው ከሚገኙ አራት በሮች መካከል በክልሉ መከላከያ ሰራዊት የሚጠበቁት ሁለት በሮች ቢሆኑም የጥበቃ አባላት ባሉበት በሮች ላይ ሰራተኞች ሲገቡና ሲወጡ ፍተሻ የማይከናወን በመሆኑ የአስተዳደሩ ንብረቶች በቀላሉ ከግቢ ሊወጡ የሚችሉ መሆናቸው፤
- የቤተ መንግስቱን አጥር ተደግፈው የተሰሩ የግለሰብ መኖሪያ ቤቶች፣ የንግድ ድርጅቶች፣ የመንግስት ተቋማት ያሉ ሲሆን በነዚህ አካባቢ የቤተ መንግስት ጥበቃ ያልተመደበ መሆኑ፤

- በቤተ መንግስቱ የመጀመሪያ በር አካባቢ የሚገኝ የግንብ አጥር እጅግ ከመሰነጣጠቁም በላይ ለመውደቅ የተቃረበ መሆኑ፤ በድንገት ወድቆ ሰው ላይ አደጋ የማድረሱ ሁኔታ እጅግ የሰፋ መሆኑ፤
  በአዲት ወቅት ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

<u>መልካሳ ቤተ መንግስት</u>

- በግቢ ውስጥ በቂ ውሃ አቅርቦት አለመኖሩ እና ጀኔሬተር የሌለ መሆኑ፤
- የግቢው አጥር አስተማማኝና ጠንካራ በሆነ መልኩ ባለመታጠሩ ምክንያት በአካባቢው የሚኖሩ የተለያዩ ሰዎችና እንስሳቶች ወደ ቅጥር ግቢው በቀላሉ የሚገቡ መሆናቸው፤
- ለወተት ላሞች እና ጥጆች በቂ የመኖ አቅርቦት ባለመኖሩ ምክንያት ከብቶቹ እጅግ የተጎሳቆሉ እና የከሱ መሆናቸው፤
- ለአንበሳ ለምግብነት የተገዙ የቀንድ ከብቶች ወጪ ሲደረጉ የንብረት ወጪ ደረሰኝ የማይቆረጥላቸው መሆኑ፣
- ለአንበሳ ምግብ ፍጆታ የሚውሉ የቀንድ ከብቶች ለምግብነት እንዲውሉ ሲደረግ በዋናው ቤተ መንግስትና በመልካሳ ቤተ መንግስት መካከል የሚደረግ የርክክብ ማስረጃ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

<u>ቆቃ ቤተ መንግስት</u>

- ቀደም ባሉት አመታት ቆቃ ቤተ መንግስት ባለው ሰፊ የእርሻ ማሳ ላይ ልዩ ልዩ አትክልት እና ፍራፍሬዎች እንዲሁም ሰብሎችን ያመርት እንደነበረ ቢገለጽም በአሁን ሰዓት በማሳው ላይ ምንም አይነት ልማት የሌለና ገቢ እያስገኘ አለመሆኑ፤
- ለመስኖ ልማት አስፈላጊ የሆነው የውሃ መሳቢያ ፓምፕም አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑ፤
- የተሠራባቸው የግቢ ደረሰኞች ወደ ብሄራዊ ቤተ መንግስት ተመላሽ የማይደረጉ መሆኑ፣
- በቤተ መንግስቱ የተለያዩ የስራ መደቦች በአንድ ሰው ያለ አግባብ እንዲሰራ የሚደረግና ሰራተኞች ከፍተኛ የስራ ጫና ያለባቸው መሆኑ ለምሳሌ የአትክልትና ፍራፍሬ ንብረት ቁጥጥር ስርጭት ባለሙያ የግንዘብ ያዥነትንም ስራ ደርበው

የሚሰሩ መሆናቸው፤ እንዲሁም የአትክልትና ፍራፍሬና ሰብል ባለሙያ የሂሳብ ሰራተኝነትን እና የንብረት አስተዳደርን ደርበው የሚሰሩ መሆናቸው፤

- በግቢው ቅጥር ውስጥ ፕሪንተር፣ ፎቶ ኮፒ ማሽን፣ ፋክስ ማሽን ባለመኖሩ ምክንያት እነዚህን አገልግሎት ለማግኘት ከግቢው ቅጥር ውጭ ወደ አዳማ ከተማ ለመሄድ ስለሚገደዱ ሚስጥራዊ የሆኑ የቤተመንግስት ሰነዶች የያዙትን ሚስጥር ለመጠበቅ የማያስችል አሰራር መኖሩ ታውቋል፡፡

የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስትቲዩት

- ንብረት የመጠበቅ ኃላፊነት እና የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኝ (ሞ/19 እና ሞ/22) የማዘጋጀት ስራ በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን፤
- የኤሌክትሪካል እና የመካኒካል መማሪያ ማሽኖች መጠቀሚያ ካርድ ያልተከፈተላቸው እና ኮንቴነሮች በአግባቡ ካለመቀመጣቸው በተጨማሪ ውኃ ወደ ውስጥ የሚያፈሱ፤
- ከጃይካ(ከጃፓን ተራድዖ ድርጅት) በዕርዳታ የተገኙ ንብረቶች ርክክብ እና ቆጠራ ያልተጠናቀቀ ከመሆኑ በተጨማሪ የቆርቆሮ መጋዘኑ የፈረሰ በመሆኑ ዝናብና ፀሐይ ስለሚያስገባ በውስጡ የሚገኙት ንብረቶች ለብልሽት የተጋለጡ መሆኑ በአዲቱ ወቅት ለማየት ተችሏል፡፡

የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን

- ሰኔ 2008 የባለስልጣን መ/ቤቱ የቋሚ እና አላቂ ንብረት ቆጠራ የተካሄደ ሲሆን አንድ ላፕቶፕ ኮምፒዩተር፣ አንድ ሲዲኤምኤ፣ አንድ ስትላይት ሀንድ ስኒስ (Stlaight hand snees) እና አንድ መጽሐፍ በቆጠራ ወቅት በጉድለት የተገኘ መሆኑ ታውቋል፡፡

የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ

- **በአዲስ አበባ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት** የአላቂ እና የቋሚ ዕቃን በኃላፊነት የመጠበቅና የንብረት ገቢና ወጪ ሂሳብ የመመዝገብ ስራ በተጨማሪም የተሸከርካሪ መኪናዎች እንቅስቃሴ የመከታተል ሥራ በአንድ የሰው ሀይል ወይም የንብረት ክፍል ሰራተኛ (Store Keeper) ብቻ የሚከናወን መሆኑ ታውቋል፡፡

የብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ

- በቤተ መፅሀፍት ውስጥ የሚገኙ የወጪና የአገር ውስጥ መፅሀፎች፡-
- በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ የመፅሀፍት ቆጠራ የማይደረግ መሆኑ፣

- ቤተመፅሀፍት ዉስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች ሲቀጠሩም ሆነ ኤጀንሲውን ሲለቁ የመፅሀፍት ርክክብ የማይደረግ መሆኑ፣
- በኤጀንሲው ቤተመጻሕፍት ውስጥ አናሎግ ካሜራ የሚገኝ ቢሆንም ድጅታል ካሜራ የማይጠቀም በመሆኑ በቤተመጻህፍት ውስጥ ያሉ የተጠቃሚዎችን እንቅስቃሴ በተፈለገው ሁኔታ ለመቆጣጠር አመቺ ያለ መሆኑ፤

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት

- ለስራ ማከናወኛ በተለያየ ጊዜ በየክፍሉ የሚገኙ ሰራተኞች ወጪ ያደረጉዋቸዉ ቋሚ ንብረት የሆኑ 8 ዲጅታል ወክማን ቴፕ፤ 5 ወክማን በጠቅላላ ብር 29,470.34 የሚያወጡ ንብረቶች የጠፉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

የኢትዮጵያ ጨረራ መከላከያ ባለስልጣን

ባለስልጣኑ ከሴባስቶፖል ሲኒማ ከገዛቸው 250 የስብሰባ አዳራሽ ወንበሮች ውስጥ ብር 546,500 የሚያወጡ በቁጥር 100 ወንበሮች በአዲቱ ወቅት በባለስልጣኑ መ/ቤት ያልተገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

ስለሆነም የጠፉ ንብረቶች እንዲተኩ ተከታታይነት ያላቸው ስራዎች በተለያዩ ሰራተኞች እንዲከናወኑ የንብረት ምዝገባ እንዲከናወን ለቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር እንዲሰጥ፤ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ጊዜውን ጠብቆ እንዲከናወን፤የቆጠራ ውጤቱ ከመዝገብ ጋር በማመሳከር ትክክለኛነቱ እንዲረጋገጥ ለንብረቶች ተገቢው እንክብካቤና አካላዊ ጥበቃ እንዲደረግ በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

6.3 <u>የተሸከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም</u>

ተ ቁ	የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ስም	የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር/ሊብሬ/የሌላቸው	በብልሽት ምክንያት የቆሙ ተሽከርካሪዎች	የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው	የተሸከርካሪ ፋይል የሌላቸው	ሞተር ቁጥር የሌለው
1	የወጣቶችና ስፖርት አካዳሚ	5				
2	የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር		2			
3	የኢትዮጵያ ብሮድ ካስቲንግ ኮርፖሬሽን		13 : ከ3 ዓመት-6 ወር የቆየ		✓	
4	የመንግሥት ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት	1 ተሽከርካሪ				ሰሌዳ ቁ.4-19780

ተ ቁ	የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ስም	የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር/ሊብሬ/የሌላቸው	በብልሽት ምክንያት የቆሙ ተሽከርካሪዎች	የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው	የተሽከርካሪ ፋይል የሌላቸው	ሞተር ቁጥር የሌለው
	ቤት					
5	ብሔራዊ አደጋ ስጋትና ስራ አመራር ኮሚሽን		147፤ለረጅም ጊዜያት የቆሙ			
6	የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስትቲዩት	የውኃ መቆፈርያ ማሽን የተሸከመ ሪግ	ሁለት ተሽከርካሪዎች			
7	የፊዴራል ሕብረት ሥራ ኤጀንሲ	4				
8	የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ		18 ተሽከርካሪዎችና አንድ ጄኔሬተር			
9	የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር		9 ተሽከርካሪዎች			
10	የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት		6 መኪናዎች			

የፊዴራል ሕብረት ሥራ ኤጀንሲ

የሁለት ተሽከርካሪዎች ሊብሬ በሌላ መ/ቤት ስም የተመዘገበ

የቤተ መንግሥት አስተዳደር

- በቤተ መንግሰት ጋራዥ/በመኪና ማቆሚያ ውስጥ በተለያየ ጊዜ በልዩ ልዩ ሁኔታ ለቤተ መንግስቱ የተሰጡ/የተላለፉ አዳዲስ የተለያዩ ሞዴል ያላቸው የእንግዳ መቀበያ ተሽከርካሪዎች ቢኖሩም አገልግሎት ሳይሰጡ ለረጅም ጊዜ የቆሙ መሆናቸው ታውቋል፡፡

ስለሆነም ከጥቅም ውጭ የሆኑ ተሽከርካሪዎች በመመሪያው መሰረት እንዲወገዱ አገልግለት ሊሰጡ የሚችሉት ተጠግነው ስራ ላይ እንዲውሉ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው ሊብሬ እንዲዘጋጅላቸው በላክነው የስራ አመራር ሪፖርት አሳስበናል፡፡

7. ባለፉት ዓመታት ኦዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ጉዳዮች

<u>የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ሚኒስቴር</u>

- ከዓመት ፈቃድ ክፍያ ላይ ያልተከፈለ የስራ ግብር ብር 2,963.91 እንዲሰበሰብ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ገንዘቡ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

- ልዩ ልዩ ላፕቶፖችና ፕሪንተሮች፣ LCD ፕሮጀክተሮች፣ የቢሮ ዕቃዎች፣ የመኪና መለዋወጫዎችና ጎማዎች፣ ብረታ ብረቶች፣ ጊዜ ያለፈባቸው ህትመቶች፣ ልዩ ልዩ ዋንጫዎችና በሴት ምስል የተሰሩ የሽልማት ዕቃዎች እና ልዩ ልዩ ቁሳቁሶች ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ወይም መወገድ ያለባቸው ተለይተው አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም እርምጃ አለመወሰዱ፤

<u>የፌዴራል ሕብረት ሥራ ኤጀንሲ</u>

- ለተጣታፊ በብልጫ የተከፈለ ብር 1,120.00 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣
- አምስት እስክሪን ኮምፒዩተሮች ፣ አስራ ሶስት ሞኒተሮች፣ አራት ሳምሶናይቶች፣ አንድ የመኪና መስታወት፣ አንድ ቴሌቭዥን ከነስታንዱ፣ ሁለት ትልቅ እና አራት ትንንሽ እስፒከሮች፣ አንድ ክሪክ እና ፕሮጀክተር እንዲወገዱ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም በአገለገሉ ንብረቶች ማስቀመጫ መጋዘን ውስጥ የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ</u>

- በደሴ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ለመስተንግዶ ወጪ ሆኖ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 612496 የተከፈለው ብር 73,109.64 ወጪ የተደረገበት የባንክ ወጪ ማስመስከሪያ እና ደጋፊ የወጪ ማስረጃዎች በወቅቱ ባለመቅረቡ ማስረጃ እንዲቀርብ ቢጠየቅም ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የቤተ መንግሥት አስተዳደር</u>

- በጉድለት የሚታይ ጥሬ ገንዘብ ብር 27,025.73 እንዲተካ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ገንዘቡ አልተተካም፡፡
- በሂሳብ ምዝገባ ማዘጋጃ ቁጥር 445817 በ6255 የሂሳብ መደብ ብር 57,103.16፣ በሂሳብ ምዝገባ ማዘጋጃ(JV) ቁጥር 445814 በ6314 የሂሳብ መደብ ብር 155,932.89 በድምሩ ብር 213,036.35 የሂሳብ ማስተካከያ በሚሰራበት ወቅት የትኛውን ሂሳብ ለማስተካከል እንደሆነ ማጠቃቀሻ (መነሻ ሰነድ) የሌለው በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ስለማይቻል የሂሳብ ማስተካከያ የተሰራበት ምክንያት እንዲጠቀስ እና አጣቃሽ ቁጥር እንዲሰጥ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ ባለመወሰዱ በዘመኑ አዲትም ተመሳሳይ ስህተቶች መገኘታቸው፤
- በዋናው ቤተ መንግስት አስተዳደር ለሚገኙት ለውድ ጌጣጌጦቹና ቅርሳቅርሶቹ ለእያንዳንዳቸው የታሪክ ማህደር በመክፈት በትክክልና በተሟላ ሁኔታ በቅርስ ጥበቃ አዋጅ ቁጥር 209/92 ወይም በፌዴራል መንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ

ቁጥር 9/2003 ክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ንኡስ አንቀጽ 1.ሀ እና ረ መሰረት ተመዝግበው በየዓመቱ ቆጠራ እየተደረገ በውጤቱ መሰረት እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ ማሳሰቢያ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ አልተወሰደም ፡፡

- በዋናው ቤተ መንግስት አስተዳደር የሚገኙት ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉት ተሽከርካሪዎች ተለይተው ተጠግነው ለአገልግሎት እንዲበቁ፣ በቅርስነት ሊጠበቁ የሚገባቸው ተሽከርካሪዎች በባለሙያ እንዲለዩ እና ሊወገዱ የሚገባቸው ተሽከርካሪዎች ደግሞ በመመሪያው መሰረት እንዲወገዱ እና በተጨማሪም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸውን ተሽከርካሪዎች በተመለከተ ሊወጣላቸው ለሚችሉት እንዲወጣላቸው ሊወጣላቸው ለማይችሉት ደግሞ እንዲለዩ የአዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ተግባራዊ አለመደረጉ ታውቋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የባህል ማዕከል

- ብር 9,000.00 ከቀን ውሎ አበል በተጨማሪ ለቁርስ የተከፈለ ለአንድ ተሳታፊ ከውሎ አበል በተጨማሪ ለአልጋ የተከፈለ ብር 150.00 ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

የብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ

- ቤተመጻሕፍት እያመሹ ለሚሰሩ ሰራተኞች የትራንስፖርት አበል እንዲከፈል የሚመለከተው አካል ሳይጠየቅና ሳይፈቀድ ብር 294,975.90 ክፍያ መፈጸሙ አግባብ ባለመሆኑ ገንዘቡ እንዲመለስ ባለፉት በጀት ዓመታቶች የአዲት ማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ገንዘቡ ለመንግስት ካዝና ተመላሽ አልተደረገም፡፡
- ሠራተኞች ለመስክ ስራ ጉዳይ ከመሄዳቸው በፊት መሞላት የሚገባው የውሎ አበል መጠየቂያ፣ መፍቀጃ፣ መክፈያና ሲመለሱ የቀን ውሎ አበል ክፍያ መቆጣጠሪያና የሥራ ክንውን መመዝገቢያ ቅጽ ሳይሞላ ብር 34,450 ከክልል ለስልጠና ለመጡ ተሳታፊዎች (ለእያንዳንዳቸው ብር 200) መክፈሉና መቀሌ ለተደረገው የመጽሀፍ አውደራእይ ላይ ለተሳተፉ ለመስተንግዶ ብር 95,908.37 በጥሬ ገንዘብ ክፍያ መፈጸሙ እና ለ71 ተሳታፊዎች ብር 14,200.00 ከሙሉ ቀን ውሎ አበል በተጨማሪ ለአልጋ ተከፍሎ በመገኘቱ በውስጥ ኦዲት ተረጋግጦ በብልጫ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግ እና የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም እርምጃ አልተወሰደም፡፡

<u>የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን</u>

- በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 0284470 በቀን 23/03/07 የኮርፖሬሽኑ ሰራተኞች በመንግስት ፖሊሲዎች ላይ ስልጠና ለተካፈሉ ሰልጣኞች የምሳ አበል በሚል በድምሩ ብር 305,650.00 ያላግባብ የተከፈለ በመሆኑ ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ የኦዲት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ገንዘቡ ተመላሽ አልተደረገም፡፡
- የዉሎ አበል ክፍያ ሰኔ /2004 በወጣዉ የመንግስት ሰራተኞች የቀን ዉሎ አበል መመሪያ ውጭ ከመደበኛ የስራ ሰዓት ዉጭ በትርፍ ሰዓታቸዉ ለሰሩ ለኮርፖሬሽኑ ሰራተኞች ተብሎ ብር 562,764.15 የዉሎ አበል ክፍያ መፈጸሙ አግባብ አለመሆኑና ክፍያውን ለመፈጸም ከሚመለከተው አካል ፍቃድ ሊኖር እንደሚገባ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ ባለመወሰዱ በዘመኑ ኦዲትም ተመሳሳይ ስህተቶች ሊገኙ ችሏል፡፡
- ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ምርትና አገልግሎቶቻቸዉን ለማስተዋወቅ በገቡት ዉል መሰረት የሚያስከፍለዉ ክፍያ የድርጅቱ ዋንኛዉ የገቢ ምንጭ ሲሆን ከ 2002-2007 ዓ/ም መሰብሰብ የነበረበት ዉዝፍ ሂሳብ በድምሩ ብር 27,609,130.31 መኖሩ ታዉቋል፡፡

<u>ባህልና ቱሪዝም ሚ/ር</u>

- በመደበኛ የስራ ቦታ ለተሰሩ ስራዎች ለውሎ አበል የተከፈለ በድምሩ ብር 152,000.15 ለትርፍ ሰዓት ስራ ለተፈጸመ ክፍያ ብር 199,174.75 በመ/ቤቱ በተዘጋጀው የኦዲት መርሃ ግብር ላይ እርምጃ እንደተወሰደ ቢገለጽም እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ ታውቋል፡፡
- እንዲወገዱ አስተያየት የተሰጠባቸው ንብረቶች አለመወገዳቸው ለማየት ተችሏል፡፡

<u>የኢትዮጵያ ወጣቶች ስፖርት አካዳሚ</u>

- የቢ.ፒ.አር. ጥናት ላቀረቡ የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኞች ማበረታቻ ተብሎ ብር 120,000.00 እንዲሁም የምርምር ጥናት ጽሁፍ ላቀረቡ ብር 57,914.00 በድምሩ ብር 177,914.00 አላግባብ የተከፈለ በመሆኑ ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም እርምጃ አልተወሰደም፡፡
- ለምግብ አቅርቦት ክፍያ ሲፈጸም ከቀረበው ማስረጃ በላይ በድምሩ ብር 5,264.00 በብልጫ በመከፈሉ አስተያየት የተሰጠ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ኦዲቱ እስከ ተጠናቀቀበት

ጊዜ ድረስ ብር 1,581.00 ተመላሽ ተደረገ ሲሆን ቀሪው ብር 3683.00 ተመላሽ አልተደረገም፡፡

- በተለያዩ ጊዜያቶች ከሞኤንኮ የተፈጸሙ የመለዋወጫና የጥገና አገልግሎት ግዥ ብር 68,406.56 የወጣ ሲሆን ለተገዙት መለዋወጫ ዕቃዎችም የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ያልቀረበላቸው በመሆኑ ለተገዙት የመለዋወጫ ዕቃዎች የንብረት ገቢ ደረሰኝ እንዲቀርብለት አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም እርምጃ አልተወሰደም፡፡
- የቦርዱ የውሳኔ ሀሳብ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ቀርቦ ሳይጸድቅ ብር 552,500.00 የኪስ ገንዘብ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ ሲሆን በዚህ በጀት ዓመትም ተመሳሳይ ሁኔታ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- ከ2006 በጀት ዓመት ወደ 2007 በጀት ዓመት የዞረ ብር 259,489.94 በሂሳብ ማመሣከሪያ ሪፖርት ላይ በ4107 የሂሳብ ኮድ በክሬዲት የሚታይ ሲሆን፣ የሂሳቡ ምንነት የማይታወቅና የሰነድ ማስረጃ ሊቀርብለት አልቻለም፡፡

ስለሆነም በኦዲት ግኝቶች ላይ እርምጃ አለመውሰድ ተጠያቂነትን የሚያስከትል በመሆኑ ለግኝቶቹ መርሃግብር በመቅረጽ ተገቢው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች መሥሪያ ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት
የ2008 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ
መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት

1. **የኦዲት ዳይሬክቶሬቱ ዕቅድና ክንውን፣**

የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት፡-

- በየቡድኑ ያሉትን ድክመቶችን እና ጥንካሬዎችን በመለየት የተሰጣቸውን ሥራ በወቅቱ እንዲያከናውኑ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ፣
- የዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን በመጠቀም ጥራቱን የጠበቀ ኦዲት እንዲከናወን በማድረግ፣
- ጥራቱን የጠበቀ የኦዲት ሪፖርት እንዲወጣ ጥረት በማድረግ እና
- የህዝብን ሀብትና ንብረት በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ እንዲውል የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት

ለመ/ቤታችን አስተዋጽዖ የሚያደርግ ነው። የዳይሬክቶሬቱ መሠረታዊ ዓላማው፡-

- በዳይሬክቶሬቱ ኦዲት የሚደረጉ መ/ቤቶችን የኦዲት ሽፋን 100% ማድረስ፣
- ዳይሬክቶሬቱ በሀገሪቱ የክህሎት አቅምን በመገንባት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያደርጉትን*
  - 11 ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትንና
  - 25 የተለያዩ መ/ቤቶችን ኦዲት ያደርጋል፡፡
- የዓለም አቀፍ የመንግሥት ኦዲት ደረጃዎችን የተከተለ እና ጥራቱን የተጠበቀ የኦዲት አገልግሎት መስጠት፣

የሚሉት ናቸው፡፡

በዚሁ መሠረት የተጠቀሱትን መ/ቤቶች እና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ሂሳብ ኦዲት ተደርገው የተሰጠቸው የኦዲት አስተያየት፡-

- አጥጋቢ ሆኖ ጥቂት ስህተት በመኖራቸው ነቀፌታ ያለበት 20 መ/ቤቶች
- የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ 15 መ/ቤቶች
- አቋም ለመውሰድ ያልተቻለበት የ1 መ/ቤት

ሂሳብ ናቸው፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 2 ተመልክቷል

1.1 **<u>የኦዲት ዕቅድና ክንውን በኦዲት ተደራጊ መ/ቤቶች ብዛትና በበጀት አንፃር፣</u>**

ተ.ቁ.	ኦዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በኦዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	የትምህርት ስትራቴጂ ማዕ..	18/12/09	23,696,005.50	12,994,400.00	36,690,405.50
2	የፋይ/ደህንነት መረጃ ማዕ.	25/12/09	17,023,680.00	-----	17,023,680.00
3	የኢት.ልማት ምርምር ኢን.	10/12/09	5,866,670.00	-----	5,866,670.00
4	የሆቴልና ቱሪዝምሥራ ማሰልጠኛ ኢ/ት.	06/01/09	52,186,305.34	1,710,000.00	53,896,305.34
5	የፍትህና የሕግ ሥርአት ምርምር ኢንስቲትዩት	25/01/09	10,433,520.00	------	10,433,520.00
6	አሶሳ ዩኒቨርስቲ	10/04/09	136,643,483.00	245,718,300.00	382,361,783.00
7	ወልቂጤ ዩኒቨርስቲ	15/02/09	268,378,496.15	403,502,183.34	671,880,679.49
8	ዋቸሞ ዩኒቨርስቲ	19/03/09	220,462,011.04	403,161,148.96	623,623,160.00
9	ሳይንስና ቴክ.ሚ/ር.	26/03/09	92,596,252.66	123,476,936.28	216,073,188.94
10	ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ	19/05/09	224,351,000.00	382,183,592.57	606,534,592.57
11	የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚ/ር	15/05/09	95,458,980.00	73,147,969.00	168,606,949.00
12	የኢ.አ.ሳይንስና ቴክ. ዩኒ.	18/04/09	296,472,748.79	561,863,451.21	858,336,200.00
13	የመገናኛና ኢን/ን ቴክ.ሚ/ር	26/01/09	65,717,400.00	219,586,000.00	285,303,400.00

ተ. ቁ.	አዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	የሂሳብ ሪፖርት ለአዲት የቀረበበት ቀን	በአዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
14	የኢትዮጵያ የብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት	07/04/09	50,023,779.97	-	50,023,779.97
15	የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	10/12/08	43,192,370.00	67,564,200.00	110,756,570.00
16	የሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ	15/03/09	380,659,413.38	-	380,659,413.38
17	የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን	02/13/08	33,516,300.00	-	33,516,300.00
18	የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት	02/02/09	26,215,426.84	-	26,215,426.84
19	የምግብ መጠጥና ፋርማ/ል ኢንዱስትሪ ልማት ኢ..	13/01/09	26,016,670.00	-	26,016,670.00
20	የብሔ. የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆ/ና ማጥፊያ ኢ..	12/03/09	65,000,000.00	-	65,000,000.00
21	የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	27/12/08	24,249,786.35	35,000,000.00	59,249,786.35
22	የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል	26/01/09	27,995,210.00	15,451,531.09	43,446,741.09
23	የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ	25/01/09	192,181,400.00	140,000,000.00	332,181,400.00
24	የመቱ ዩንቨርስቲ	27/01/09	190,644,034.00	426,601,557.73	617,245,591.73
25	የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የሥ/ና ማ.	12/12/08	16,657,052.18	-	16,657,052.18
26	አዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ	19/01/09	525,667,680.00	503,300,000.00	1,028,967,680.00
27	አዴግራት ዩኒቨርሲቲ	19/12/08	280,808,796.00	497,000,000.59	777,808,796.59
28	ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ	12/01/09	214,899,800.00	350,000,000.00	564,899,800.00
29	ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ	25/02/09	215,512,316.00	507,716,855.53	723,229,171.53
30	የእንስሳት መድኃኒትና	30/01/09	43,679,450.00	--------	43,679,450.00

ተ.ቁ.	አዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	የሂሳብ ሪፖርት ለአዲት የቀረበበት ቀን	በአዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
	መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን				
31	ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት	10/04/09	127,147,140.00	127,000,000.00	254,147,140.00
32	የኢትዮጵያ የአካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት	24/01/09	35,773,104.00	26,820,640.00	62,593,744.00
33	የኢትዮጵያ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	24/12/09	39,154,340.00	120,000,000.00	159,154,340.00
34	ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ	19/3/09	42,803,764.32	93,753,360.00	136,557,124.32
35	የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚ/ር	17/04/09	34,475,820.00	------	34,475,820.00
36	የአካባቢ፣የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚ/ር	09/05/09	55,648,920.75	------	55,648,920.75
ጠቅላላ ድምር			4,201,209,126.27	5,337,553,126.30	9,538,921,252.57

1.2 መርሀ-ግብር የተጠየቁና ምላሽ የሰጡ፣

ተቁ	የአዲት ተደራጊው መ/ቤት	ደብዳቤ/ፎርም የተላከላቸው፡	መርሀ-ግብር በማዘጋጀት ምላሽ የሰጡ	ምላሽ ያልሰጡ
1	36 መ/ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች	ለሁሉም	የእንስሳት መድ/ት/ና መኖ አስተ/ና ቁጥጥር ባለሥልጣን	30 መ/ቤቶችና ዩኒቨርስቲዎች ምላሽ አልሰጡም
2			የሆቴልና ቱ/ም ሥራ መ/ኛ ማዕ.	
3			የጨርቃ ጨርቅ ኢ/ሪ ልማት ኢ/ት	
4			የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ	
5			የቴክ/ና ሙያ ት/ት ሥ/ና ኤጀንሲ	
6			ደብር ታቦር ዩኒቨርስቲ	

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች፣

1. የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሣብ፣

1.1 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣

- በአዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ብር 144,716.56 ከግዥ ሠራተኞችና ከገ/ያገሮች የሚፈልግ ገንዘብ ገቢ አለመደረጉን፣

የማሻሻያ ሀሳብ፣

በእዳ የሚፈለገውም የመንግስት ገንዘብ ከሚመለከታቸው ሰራተኞች ተመላሽ መሆን አለበት ለወደፊቱም የመንግሥትን ገንዘብ ከጥፋትና ከጉድለት ለመከላከል እንዲቻል ተቋሙ በጥሬ ገንዘብ አስተዳደር ላይ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

1.2 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ አያያዝ ድክመቶች፣

- **የትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል** የሳጥንና የባንክ ሂሳብ ወጪ በጀት ስለመኖሩ በቅድሚያ ሳይረጋገጥ እንዲሁም በወጪ ማስመስከሪያ ላይ በሚመለከተው ኃላፊ ሳይፈረም ብር 2,292,102.58 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
- **የወልቂጤ ዩኒቨርስቲ** ለተለያዩ ድርጅቶች በባንክ ክፍያ ተፈጽሞ ለተገኘው የባንክ አድቫይስ ማስረጃ ከክፍያ ሰነዱ ጋር ሳይያያዝ ብር 8,944,593.24 ተከፍሎ ተገኝቷል፡
- **የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ** ከሚሰበስባቸው የመደበኛ ገቢ ሂሳብ ውስጥ ብር 24,826.52 ወደ ባንክ ገቢ የተደረገው ከሰባት ቀን እስከ አንድ ወር ዘግይቶ ለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- **የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ** በሳጥን ወይም በገንዘብ ያዥ መያዝ የሚገባው እስከ ብር 100,000.00 ቢሆንም ነገር ግን ዩኒቨርሲቲ በሰኔ 30/2008 ይዞ የተገኘው ብር 307,862.25 መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- **የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ** በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ 5 ‹‹በበጀት ዓመቱ ውስጥ የሚከፈሉ የክፍያ መጠናቸው ከብር 50,000.00 በላይ የሆኑ ወጪዎች መከፈል ያለባቸው ወደ ባለመብቱ ባንክ ሂሳብ መተላላፍ እንዳለበት›› መመሪያው ቢያመለክትም በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ(JV) ቁጥር 767551 ብር 226,576.00 ለውጪ መምህራን

የትራንስፖርት ክፍያ ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ የባንክ ሂሳብ በማስተላለፍ ክፍያ መፈጸም ሲገባው ክፍያው ከሳጥን የተፈጸመ መሆኑ፣

- **<u>የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር</u>**
  - ጥሬ ገንዘብ በመ/ቤቱ ገንዘብ ያገሮች እጅ ላልተወሰነ ቀናት እንዲቆይ የሚደረግ እና የመነሻ ሂሳብ በአግባቡ እየተመዘገበ የማይያዝ መሆኑ፣
  - ብር 13,600.00 በቼክ መከፈል ሲገባው በጥሬ ገንዘብ ወጪ መደረጉን፣
  - ብር 402,964.21 በባንክ ሂሳብ ቁጥር በማስተላለፍ ክፍያ መፈጸም ሲገባው በገንዘብ ያዥ በኩል መከፈሉን፣
- **በጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት** በሂሳብ መደብ 4104 በሌተር አፍ ክሬዲት የባንክ ሂሳብ የሚታየው ብር 71,128,769.99 ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑን፣
- **በወልዲያ ዩኒቨርሲቲ** በድምሩ ብር 115,095.38 ከተቋሙ ካዝና ወጪ ሆኖ በጥሬ ገንዘብ መከፈሉ፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ የወጣውን መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ በአግባቡ እንዲጠበቅ እና ሥራ ላይ እንዲውል ቁጥጥር ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው አሳስበናል።

2. <u>የተሰብሳቢ ሂሳብ፣</u>

2.1 <u>ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሣብ፣</u>

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመንገሻ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ እንዲሁም በመመሪያው ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል። ይሁንና በሃያ አራት መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው ብር 684,135,065.76 ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ መኖሩ የታወቀ ሲሆን፣ የተሰብሳቢ ሂሳቡ የዕድሜ ቆይታ ቀጥሎ ቀርቧል። /ዝርዝሩ በአባሪ- 6 ቀርቧል/

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ያልተሰበሰቡት ሂሳቦች እንዲሰበሰቡ፣ ሊሰበሰቡ የማይችሉ ከሆነ ግን በመመሪያው መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ መደረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

2.2 <u>በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ ልዩ ልዩ የአሠራር ችግሮች፣</u>

- **የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ** በሂሳብ መደብ 4201(የቅድሚያ ክፍያ) ብዛታቸው በቁጥር 71 የሚሆኑ ተቀጽላ ቋቶች/ሌጀሮች/ ሚዛኑን ያልጠበቀ ተሰብሳቢ በድምሩ ብር 160,393.64 በክሬዲት ሚዛን(ባላንስ) ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- **የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ** በተለያዩ የሂሳብ መደቦች በድምሩ ብር 3,249,470.48 በተሰብሳቢ ተይዞ መገኘቱንና ዝርዝር መረጃ ባለመቅረቡ የቆይታ ግዜውን ለማወቅ አለመቻሉን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የተቀጽላ ቋቶቹ ክሬዲት የሚያሳዩበት ምክንያት በማጣራት የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ እንደሚገባው፣ እንዲሁም ዝርዝር ማስረጃ ያልቀረበውን በሚመለከት ሂሳቡ የተያዘበት ግዜ እና ተሰብሳቢው የሚፈለግበት አካል ተለይቶ ሪፖርት እንዲቀርብ እና እንደየቆይታው ሂሳቡ የሚወራረድበት ሁኔታ እንዲመቻች የሥራ አመራሩ ክትትል ማድረግ እንደሚጠበቅበት አሳስበናል፡፡

3. <u>የገቢ ሂሣብ</u>፣

3.1 <u>ያልተሰበሰበ ውዝፍ ገቢ፣</u>

- **የወልቂጤ ዩኒቨርስቲ** ከሚያዝያ 2007 ዓ/ም እስከ ሰኔ 2008 ዓ/ም በግቢው ውስጥ ከሚገኙ የተለያዩ አገልግሎት ከሚሰጡ ድርጅቶች ጋር ውል በመግባት የቤት ኪራይ ገቢ የሚያገኝ ቢሆንም፣ በአጠቃላይ ብር 266,043.54 ከድርጅቶቹ ሳይሰበስብ ተገኝቷል፡፡
- **የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ** ግቢ ውስጥ አገልግሎት ከሚሰጡ ድርጅቶች ጋር በተገባው ውል መሰረት ከድርጅቶቹ የሚጠበቀውን የቤት ኪራይ ከ12/04/08 እስከ 30/10/08 ዓ.ም ወይም የ 6 ወር ከ 19 ቀን ብር 15,917.00 በበጀት ዓመቱ ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

- **የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት** ለተማሪዎች ክፍል ቁም ሳጥኖች ለመግዛት በተገባው ውል መሠረት አቅራቢው በወቅቱ ገቢ ባለማድረጉ ላዘገየበት መክፈል የሚገባው የጉዳት ካሣ ብር 167,256.00 ገቢ አለመደረጉን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- የተለያዩ አገልግሎት እየሰጡ ያሉ ድርጅቶችም በውላቸው መሰረት በወቅቱ የቤት ኪራይ እየከፈሉ እንዲጠቀሙ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንደሚኖርበት፣
- ያልተሰበሰበው ሂሳብ እንዲከፍሉ በማድረግ ለወደፊቱም ገቢው በወቅቱ ሊሰበሰብ እንደሚገባ፣ እንዲሁመም ገቢ መደረግ የሚገባው የጉዳት ካሣም ከአቅራቢው ገቢ እንዲደረግ ክትትል መደረግ እንደሚኖርበት፣

አሳስበናል፡፡

3.2 <u>በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ ህግ መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ፣</u>

የገቢ ሂሳብ በገቢ አዋጅ ደንብና መመሪያዎች መሰረት መሰበብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፣ በ9 መ/ቤቶች የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 98,734.48፤ የቅድሚያ ግብር ብር 34,284.11 **እና** የስራ ግብር ብር 91,994.90 በድምሩ ብር 211,668.49 ያልተሰበሰበ መኖሩ ተረጋግጦል፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ማንኛውም የግብርና የቀረጥ ሂሳብ በመሰብሰብ ለግብር ሰብሳቢው ባለስልጣን ገቢ መደረግ አንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

3.3 <u>በገቢ ሂሣብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ የገቢ ሂሳብ፣</u>

- **የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ** ከውስጥ ገቢ ምንጮች የሰበሰበውን ብር 7,122,765.96 ዓመታዊ ሪፖርት የማይዘጋጅና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት የማይደረግ በመሆኑ የገቢውን ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- **የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ** በ2008 በጀት ዓመት ከመደበኛ ሂሳብ የሰበሰባቸውን ገቢዎች ውስጥ በድምሩ ብር 563,416.10 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑን፡፡

- **የአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ** ብር 6,877,516.25 በውስጥ ገቢ ሂሳብ በገቢ መያዝ የሚገባው በተከፋይ ተመዝግቦ የሚታይና በሂሳብ ሪፖርት ያልተካተተ መሆኑ፣
- **የዓዲግራት ዩኒቨርስቲ** በበጀት ዓመቱ ከዩኒቨርሲቲው የተለያዩ አገልግሎት መስጫ ድርጅቶች ኪራይ የተሰበሰበው ገቢ እና ወጪ የተደረገው የገንዘብ መጠን የማይታወቅ እና ተገቢው ምዝገባ እየተከናወነ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- የፋይናንስ መመሪያው ተጠብቆ መሰራት ስላለበት በገቢ መያዝ ያለበት የገቢ ሂሳብ በመመሪያው መሰረት እንዲመዘገብና በሪፖርት እንዲካተት ተደርጎ ሪፖርትለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር መቅረብ ሊቀርብ እንደሚገባ፣ አሳስበናል፡፡

3.4 **<u>ለሚመለከተው አካል ፈሰሰ ያልተደረገ ገቢ</u>**፣

- **የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ፣** ከመደበኛ ተማሪዎች የሰበሰበው የመመዝገቢያ ክፍያ በድምሩ ብር 1,140,950.00 ገቢ ወደ መደበኛው ሂሳብ ገቢ ተደርጎ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ፈሰስ መደረግ ሲገባው ወደ ውስጥ ገቢ ሂሳብ ገቢ የሚያደረግ ለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- **የእንሰሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን፣** በመድሃኒትና መኖ ጥራት ምርመራ ማዕከል በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በባንክ ሂሳብ የታየው ከወጪ ቀሪ ብር 1,273,307.92 ወደ ማዕከላዊ ግምጃ ቤት ፈሰስ አለመደረጉ፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- ወደ ውስጥ ገቢ ሂሳብ ገቢ ሊደረጉ የሚገባቸው ገቢዎች ዩኒቨርሲቲው ከመደበኛ ሥራው ውጭ ገቢ ለማመንጨት ፕሮግራሞችን ነድፎ የሚያመነጨው ገቢ ብቻ መሆን የሚገባው ሲሆን፣ መደበኛ ሥራውን በሚሰራበት ጊዜ የሚሰበስበው ማንኛውም መደበኛ ገቢ ተገቢው ምዝገባ እየተደረገለት መደበኛ ሂሳብ ውስጥ ገቢ በማድረግ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ፈሰስ ሊደረግ እንደሚገባ፣
- በባንክ የታየው የጥሬ ገንዘብ ለሚመለከተው አካል ፈሰስ እንዲደረግ እና በፈሰስ ሂሳብ ሪፖርት እንዲገለፅ መደረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱም ፈሰስ መደረግ

የሚገባው ገንዘብ ፈሰስ እንዲደረግ ተገቢው ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት፣

አሳስበናል፡፡

3.5 <u>ማስረጃ ባለመሟላቱ የገቢውን ትክክልኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ፣</u>

- **የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት** ብር 5,361,976.42 ከማታና ከተከታታይ ትምህርት የተሰበሰበው ገቢ በሚመለከተው አካል ባልጸደቀ የገቢ ተመን ተሰብስቦ ተገኝቷል፡፡
- **የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ፣**
  - ለእያንዳንዱ ትምህርት በክሬዲት የተተመነ የማስከፈያ ዋጋ ተመን /ታሪፍ/ በቦርድ የጸደቀ ሰነድ ሳይኖር ዩኒቨርሲቲው ከማታ እና ከርቀት ተማሪዎች ገቢ የሚሰበስብ መሆኑን፣ እንዲሁም ከመመዝገቢያ፣ ከትምህርት ማስረጃ ክፍያ፣ ከጊዜያዊ ሰርተፍኬት፣ ከስቱደንት ኮሚ፣ ከዲግሪ/ዲፕሎማ ማሰሪያ እና ከተለያዩ ቅጣቶች ወዘተ የሚሰበሰብ ገቢ በቦርድ ተመኑ /ታሪፉ/ ሳይወጣለት የሚሰበስብ መሆኑ፣
  - በባንክ በኩል የገባ ተበሎ የገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት በድምሩ ብር 345,009.00 የገቢው ዓይነት፣ ገቢው ከማን እንደተገኘ፣ የገቢው ምክንያት እና የማስከፈያ ተመን/ታሪፍ ባለመታወቁ የገቢውን ትክክለኝነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- **የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣**
  - የመገናኛ (አይ.ሲ.ቲ.) ዕቃዎች ቴክኒክ ብቃት ማረጋገጫ በድምሩ በዶላር 1,080.00 ወይም በብር 23,396.24 ለተሰበሰበው የገቢ ሂሳብ የገቢ ተመን የሌለው መሆኑ፣
  - ዶላር 744 (ብር15,539.13) ለተሰበሰበው ገቢ ምንጩን ለማወቅ ያልተቻለ መሆኑ፣
- **መቱ ዩኒቨርስቲ፣**
  - <u>የውስጥ ገቢ ሂሳብ ምዝገባ አለመካሄድና ሪፖርት አለመደረግ፣</u>

    የዩኒቨርቲዉ የውስጥ ገቢ የባንክ ሂሳብ በባንክ ስቴትመንቱ መሰረት መጋቢት 30/2008 ብር 5,730,362.09 የሚታይ ቢሆንም የውስጥ ገቢ ሂሳብ ምዝገባ ባለመካሄዱ እና የውስጥ ገቢ የፋይናንስ እንቅስቃሴን

የሚገልጹ አግባብነት ያላቸው የሂሳብ ሪፖርቶች እና መግለጫዎች ባለመዘጋጀታቸው የዩኒቨርሲቲውን የውስጥ ገቢ ሂሳብ በዝርዝር አዲት በማድረግ ትክክለኝነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣

- **በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት** ብር 104,376.80 ገቢ የተደረገባቸው የገቢ ደረሰኞች ለአዲቱ ባለመቅረባቸው የገቢውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉ፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- የተቋሙ የገቢ ማስገኛ ምንጮች ዓይነት እና ለእያንዳንዱ የገቢ ማስገኛ ምንጭ የማስከፈያ ዋጋ ተመን /ታሪፍ/ በዝርዝር የሚገልጽና በሚመለከተው አካል የጸደቀ ሠነድ ተዘጋጅቶ በጥንቃቄ እንዲጠበቅ ማድረግ እንደሚኖርበት፣
- የገቢ ደረሰኝ ተፈላጊውን መረጃ አሟልቶ እንዲይዙ አግባብነት ያላቸው ደጋፊ ሰነዶች አባሪ በማድረግ ከገቢ ደረሰኝ ቅጠል ጋር እንዲያያዙ መደረግ እንዳለበትና ለወደፊቱም የእርምት እርምጃ በመውሰድ አስፈላጊው ጥንቃቄ ሊደረግ እንደሚገባ፣
- ዩኒቨርሲቲዉ ምን ያህል ገቢ እንደሰበሰበ፣ ምን ያህል ከውስጥ ገቢ ወጪ አድርጎ እንደተጠቀመ እና የውስጥ ገቢ ሂሳብ ከወጪ ቀሪ ምን ያህል እንደሆነ የሚያሳይ ትክክለኛ ምዝገባ ተካሂዶ ተገቢው የሂሳብ መግለጫዎች ተካተው የሂሳብ ሪፖርት መዘጋጀት እንደሚኖርበት፣
- የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንዲቻል ተገቢው ማስረጃ ለአዲቱ ሊቀርብ እንደሚገባ፣

አሳስበናል፡፡

3.6 **<u>በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሚታዩ ሌሎች ዋና ዋና የአሠራር ድክመቶች፣</u>**

የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ የሚሰበስባቸው የመደበኛ ገቢ ሂሳብ ውስጥ ብር 24,826.52 ወደ ባንክ ገቢ የተደረገው ከሰባት ቀን እስከ አንድ ወር ዘግይቶ መሆኑ፣

የደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ:-

- ገቢ የመሰብሰብ ሥልጣን ባልተሰጠው በተማሪዎች ህብረት ገቢ ተሰብስቦ መገኘቱ፣
- በተማሪዎች ህብረት ሥም በተዘጋጀ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ገቢ እንዲሰበሰብ መደረጉ፣

- በበጀት ዓመቱ ከተሰበሰበው የውስጥ ገቢ ብር 936,204.00 በመደበኛ በጀት የባንክ ሂሳብ ገቢ መደረጉን፣

የዓዲግራት ዩኒቨርስቲ:-

- በዩኒቨርስቲው ተገቢው የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት ያልተዘረጋ እና በሚመለከተው አካል የጸደቀ የዋጋ ተመን ያልወጣለት በመሆኑ የገቢውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉን፣
- የዩኒቨርስቲው የኪራይ ገቢ ህጋዊ ሥልጣን ባልተሰጠው በተማሪዎች ህብረት እየተሰበሰበ ህብረቱ እየተጠቀመበት የሚገኝ መሆኑን፣
- የዩኒቨርስቲው የውስጥ ገቢ -ተቀጽላ ቋት ያልተዘጋጀላቸው በመሆኑ ከወጪ ቀሪውን ለማረጋገጥ አለመቻሉን፣

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የመ/ቤቱ የገንዘብ ፍሰት ዕቅድ ሲዘጋጅ የሚሰበሰበው ገቢ በዕቅድ እንዲያዝ የማይደረግ መሆኑን፣

ወልዲያ ዩኒቨርስቲ ከውስጥ ገቢ የተሰበሰበ ብር 730,973.15 በመደበኛ በጀት የባንክ ሂሳብ ገቢ ተደርጎ ተገኝቷል።

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- የሚሰበስበውን ገቢ በመመሪያው መሰረት ወደ ባንክ ገቢ ማድረግ እንደሚኖርበትት ገቢ ለመደረጉም ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ፣
- በተማሪዎች ህብረት የሚሰብሰውን ገቢ በማስቆም በዩኒቨርሲተው ገንዘብ የመሰብሰብ ሥልጣን በተሰጠው ሠራተኛ እንዲሰበሰብ ማድረግ እንደሚገባና ገቢው በህጋዊ የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ መሰብሰብ እንደሚኖርበት፣
- ከውስጥ ገቢ አርዕስቶች የተሰበሰበው ገንዘብ በተገቢው የውስጥ ገቢ የሂሳብ መደብ እንዲያዝ እና ለዚሁ በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ገቢ እንዲሆን ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ እንደሚኖርበት፣
- መ/ቤቱ አገልግሎት በመስጠት የሚያገኘውን ገቢ በዕቅድ በመያዝ እና ከተሰበሰበው ገቢ ጋር በማመሳከር የዕቅድ ክንውን ግምገማ ማድረግ እንደሚኖርበት፣

አሳስበናል።

4. የወጪ ሂሳብ፣

4.1 የተሚላ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሣብ፣

ተ.ቁ.	የመ/ቤቱ ስም	ደረሰኝ ያልቀረበ	ዝርዝር ማስረጃ ያልቀረበ	በዱቤ ሽያጭ የተወራረደ	ድምር
1	የአሶሳ ዩኒቨርስቲ	384,314.60	311,165.44	25,175,267.55	25,870,747.59
2	የወልቂጤ ዩኒቨርስቲ	---	104,376.00	-----	104,376.00
3	የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ	158,335.15	2,133,435.99	----	2,291,771.14
4	የሳይ/ና ቴክ. ሚ/ር	15,122,682.55	1,535,922.26	----	16,658,604.81
5	የሙቱ ዩኒቨርስቲ	744,084.80	---	---	744,084.80
6	የሳ/ና ቴክ.መረጃ ማ.	1,321,493.92	----	----	1,321,493.92
7	የብሔ. ቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆ/ና ማጥ.ኢንስቲትዩት	16,294.77	---	---	16,294.77
8	የሀገር አቀ. የትም.ምዘ/ና ፈ/ች ኤ	---	195,139.46	----	195,139.46
9	የኢ.ት.ካይዘን ኢ.ን/ት	----	16,350.00	---	16,350.00
10	የወልቂጤ ዩኒቨርስቲ	----	75,240.00	----	75,240.00
11	የደ.ታቦር ዩኒቨርስቲ	360,500.00	----	----	360,500.00
12	የቴክ/ና ሙ.ያ ት.ም/ና ሥ/ና ኢ.ን/ት	531,216.50	----	---	531,216.50
13	የቴክ/ና ሙ.ያ ት.ም/ና ሥ/ና ኤጀንሲ	65,104.00	269,992.63	---	335,096.63
14	የአካ.የደ/ና የኤር ን/ት ለውጥ ሚኒስቴር	20,521.52	249,765.91	----	270,287.43
15	አዳማ ሳ/ና ቴክ.ዩኒ.	5,211,949.32	----	2,709,600.20	7,921,549.53
16	ወልዲያ ዩኒቨርስቲ	---	---	227,556.47	227,556.47
	ጠቅላላ ድምር	23,936,497.13	4,891,387.69	28,112,424.22	56,940,309.04

የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ገንዘቡ በስማቸው ወጪ የተደረገ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች ማስረጃዎቹን እንዲያቀርቡ ወይም ገንዘቡን ተመላሽ እንዲያደርጉ መደረግ እንዳለበትና ለወደፊቱም ለክፍያዎች ትክክለኛ ደጋፊ የክፍያ ደረሰኝ ሳይቀርብላቸው ሂሳቡ እንዳይወራረድና እንዳይመዘገብ ክትትል መደረግ እንዳለበት፣
- መስተንግዶው የሚመለከታቸው ሰዎች ስም ዝርዝር እና አገልግሎቱን ስለማግኘታቸው የሚያሳይ የሰዓት ፊርማ በማቅረብ ክፍያዎች ከመፈፀማቸው በፊት ለማን እና እንዴት እንደተከፈለ የሚያሳይ የተሚላ የሰነድ ማስረጃ መኖሩን በማረጋገጥ እንዲከፈል ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንደሚኖርበት፣

- ለወደፊት እንደዚህ ዓይነት ስህተት እንዳይፈጸም ተቋሙ ማንኛውም ክፍያ ሲያከናውን መሟላት ያለባቸው ማስረጃዎች እንዲሟሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርግ እንደሚገባ፣

አሳስበናል፡፡

4.2 <u>ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለ አግባብ የተፈፀሙ ክፍያዎች፣</u>

ወጪ ተደርገው የተመዘገቡት ሂሳኖች ደንብና መመሪያዎችን የተከተሉ ለመሆናቸው ኦዲት ሲደረግ፤ በ22 መ/ቤቶች ብር 24,677,392.80 ከመመሪያን ያልተከተሉ አላአግባብ የተከፈለ ሲሆን፤ አግባብ የተከፈለ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም በመክፈል፤ ሳያስፈቅዱ የትርፍ ሳዓት ክፍያ በመፈጸም፤የውሎ አበል ደንብ ያልተከተለ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- ማንኛውም ክፍያ ደንብና መመርያዎችን መሰረት ባደረገ መልኩ መከናወን እንደአለበት፡ ከመመሪያ ውጭ የተፈጸሙ የትርፍ ሰዓት ክፍያዎች ተመላሽ ሆኖ ወደ መንግስት ካዝና ገቢ መሆን እንደአለበትና ለወደፊቱም የክፍያዎች መጠን በሚመለከተው አካል በማስፈቀድ ተግባራዊ መደረግ እንደሚኖርበት፣
- ያለአግባብ ከደንብና መመሪያ ውጭ የምግብ አበል ክፍያ፣ የኃላፊነት አበል እና ሌሎችም ጥቅማ ጥቅሞች እየተከፈለ ያለው በአስቸኳይ እንዲቆም እና አለአግባብ የተከፈለውም ከሰራተኞች ገንዘቡ ተመላሽ ሊደረግ እንደሚገባ፣
- ለመደበኛ የመማር ማስተማር ተግባራት አገልግሎት ሊውል የሚችለውን የውስጥ ገቢ አለአግባብ ወጪ ማድረጉ መመሪያን ያልተከተለ ሀኖ በመገኘቱ ገንዘቡ ተመላሽ ተደርጎ ዩኒቨርሲቲው በመመሪያው መሠረት ለሚፈፅማቸው ተግባራት ማዋል እንደሚኖርበትና ባልተፈቀደ በጀት አለአግባብ ከመደበኛ በጀት ለአክሲዮን ግዥ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ መደረግ እንደሚኖርበት፡

አሳስበናል፡፡

4.3 <u>የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች፣</u>

የዕቃና አገልግሎት ግዥዎች በመንግሥት ደንብና መመሪያ መሠረት የተፈጸመ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በ27 መ/ቤቶች ብር 98,796,196.46 የመንግሥትን የግዢ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ያልተከተለ ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 21 ተመልክቷል፡፡/

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- **ማንኛውም ግዥ ሲፈጸም አዋጅን፣ ደንብንና መመርያዎችን መሰረት በማድረግ የመንግስትን ጥቅም በሚያስጠብቅ መልክ መከናወን እንደአለበትና ጨረታውን ካለሸነፉት ድርጅቶች ግዥ እነዲፈፀም የተደረገበትን ሁኔታ ማጣራት ተደርጎ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባና ለወደፊቱም መሰል ስህተት እንዳይከሰት ጥንቃቄ መወሰድ እንደሚኖርበት፣**

አሳስበናል፡፡

4.4 <u>በናሙናው መሠረት ለመግባቱና አገልግሎት ለመሰጠቱ የቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ የተፈፀመ የግዥ ክፍያዎች፣</u>

- **የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ለፈጸመው ግዥ በናሙናው መሠረት ለመግባቱና አገልግሎት ለመሰጠቱ በቴክኒክ ኮሚቴ ሳይረጋገጥ ብር** 7,579,153.41 **ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡**
- **የወልቂጤ ዩኒቨርስቲ ለፈጸመው ግዥ ማንኛውም በመንግስት በጀት የሚተዳደር የመንግስት ተቋም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች የፅሁፍ ማረጋገጫ መቅረብ ሲገባው ዩኒቨርሲቲው በድምሩ ብር** 257,415.84 **አገልግሎቱን የሚያገኙት ግለሰቦች ስም ዝርዝርና የጽሁፍ ማስረጃ በግልፅ ባልተቀመጠበት ሁኔታ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን ተረጋግጧል፡፡**
- **የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር መ/ቤት በአጠቃላይ ብር** 2,508,853.81 **ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከተለያዩ አቅራቢ ድርጅቶች የገዛቸውን ዕቃዎች በናሙናው መሰረት ገቢ ስለመሆናቸው የቴክኒክ ኮሚቴ ያረጋገጠበት ማስረጃ ከክፍያ ሰነዱ ጋር ያልቀረበ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡**
- **የቡሌ ሆራ የኒቨርሲቲ ዕቃው ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች የጽሑፍ ማረጋገጫ ሳይቀርብ በድምሩ ብር** 193,024.36 **ክፍያ ፈጽሞ ተገኝቷል፡፡**

<u>የማሻሻያ ሀሰብ፣</u>

- **ማናቸውም ግዥ ሲያከናውን በናሙናው መሰረት መግባቱን አገልግሎት በአግባቡ መሰጠቱን በቴክኒክ ኮሚቴ መረጋገጥ እንዳለበት ሆኖ ለተገለፁት**

ዕቃዎች የናሙና ማረጋገጫ ያልቀረበበት ተጣርቶ የእርምት እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.5 <u>በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ ክፍያ፣</u>

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	የገንዘብ መጠን	የወጪው ምክንየት በአጭሩ
1	የትምህርት ስት/ጂ ማዕከል	251,321.00	የቢሮ ኪራይ
2	ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ	1,900,595.12	መምህራን የትርፍ ሰዓት ክፈያ
3	የኢት. ሲቪል ሰርቪስ ዩኒ/ቲ	10,339.65	ለመስተንግዶ የወጣ
4	መቱ ዩኒቨርስቲ	473,339.65	ለህትመትና ለመምህራን የተከፈለ
5	የመገ/ና ኢን/ን ቴክ. ሚ/ር	29,040.50	የአገልግሎትና ዕቃ ግዥ
6	የሀገር አቀፍ የት. ም/ና ፈ/ች ኤ	85,137.38	የአገልግሎት ግዥ
7	የአካ.ደንና የአ. ን/ት ለውጥ ሚኒስቴር	68,580..66	የኮምፑዩተር ግዥ
8	አዲግራት ዩኒቨርስቲ	17,644,026.06	የእቃና አገልግሎት ግዥ
ጠቅላላ ድምር		<u>20,462,380.02</u>	

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- የበጀት ዓመቱ ወጪ በበጀት ዓመቱ ክፍያ ተፈፅሞ እንዲመዘገብ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እና የ2008 በጀት ዓመት የተመደበለትን የበጀት አጠቃቀም አሉታዊ ተፅዕኖ የሚፈጥር በመሆኑም ለወደፊቱ ጥንቃቄ መደረግ እንደሚኖርበት፣

አሳስበናል፡፡

4.6 <u>በብልጫ የተከፈለ፣</u>

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	ለግንባታና የተለያዩ ግዥዎች ወጪ	ለውሎ አበል፤ ለደመወዝና ሌሎች ወጪዎች
1	ዋቸሞ ዩኒቨርስቲ	---	59,971.92
2	መቱ ዩኒቨርስቲ	960,901.10	60,000.00
3	የኢት.ብዝሃ ሕይወት ኢንስቲትዩት		8,553.91
4	የፍትህ አ/ት ባለ/ች የሥ/ና ማዕከል		261.00
5	የብሔ.ቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢን.		352.00
6	የመ/ኛና ኢን/ን ቴክ.ሚ/ር		3,661.94

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	ለግንባታና የተለያዩ ግዥዎች ወጪ	ለውሎ አበል፤ ለደመወዝና ሌሎች ወጪዎች
7	የቴክ/ና ሙያ ትም/ና ሥ/ና ኤጀንሲ		2,994.33
8	የአካ.ደንና አየር ንብብት ለውጥ ሚ/ር (የኮምፑዩተርና የህንፃ ኪራይ)	1,253,870.01	
9	ደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ		251,920.00
ጠቅላላ ድምር		2,214,771.11	387,715.10

የማሻሻያ ሀሳብ፤

- በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ወቅታዊ የገቢያ ዋጋ ኢንዴክስ ሳይኖር የዋጋ ማስተካከያ ተደርጎ የተከፈለው አለአግባብ መሆኑ ታዉቆ በብልጫ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ ሊደረግ እንደሚገባና ለወደፊቱም የዋጋ ማስተካከያ ሲያደርግ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ወቅታዊ የገቢያ ዋጋ መረጃን መሰረት በማድረግ ሊሆን ይገባል፡፡ ከግለሰቦቹ ገንዘቡን ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱ ማንኛውም ወጪ በትክክል ስለመሰላቱ ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንደሚኖርበትና ያልተሰራበት ደመወዝ ፣ ለውሎ አበልና ለአልጋ ክፍያ በብልጫ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ ሊደረግ እንደሚገባ፣አሳስበናል፡፡

4.7 **በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ ወጪዎች፤**

የወጪ ሂሣቦች የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ኑሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው ደንብ መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፣በ19 መ/ቤቶች ብር 31,381,529.05 የወጪ ሂሣብ መደባቸውን ሳይጠብቁ ተመዝግበው ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-25 ተመልክቷል/

በመሆኑም ሂሣቦቹ በተገቢው የወጪ ሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡና ለወደፊትም ተመሣሣይ የአሠራር ግድፈት እንዳይፈፀም ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.8 **በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ የተያዘ ሂሳብ፤**

- **የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት** መጠናቸው ብር 210,622.50 የሆኑ ቼኮች የዕቃ ግዥ ሠራተኞች በመጀመሪያ ሂሳቡ በተሰብሳቢ ሳይመዘገብ

የወጪ ማስረጃ ባመጡበት ጊዜ ከወጪ ማስመስከሪያው ጋር በማያያዝ ወጪው የሚመዘገብ መሆኑ፣

- **የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር** የተለያዩ የምርምር ሥራዎችን ለማሰራት ከተለያዩ ተቋማትና ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ውል በመግባት እያሠራ ሲሆን፣ በውሉ መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ለተመራማሪ ተቋማት ሲከፍል በቅድሚያ ክፍያ መመዝገብ ሲገባው፣ በአጠቃላይ ብር 31,644,188.65 አገልግሎቱ ሳይገኝ ሙሉ በሙሉ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- **የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል** የክላውድ ዳታ ሴንተር ግንባታ ለማካሄድ Huawei International Co.Limited ከተሰኘ የቻይና ኩባንያ ጋር ከተዋዋለው ውስጥ ማዕከሉ USD 700,000.00 በብር 15,925,278.41 ሌተር ኦፍ ክሬዲት (LC) የተከፈተበት ሂሳብ በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ ተይዞ የተገኘ መሆኑ፣
- **የእንሰሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን** ለማዕከሉ የላቦራቶሪ መገልገያ መሣሪያዎች፣ ኬሚካሎችና ሌሎች ግብዓቶችን ለመግዛት በጨረታ አሸናፊ ለሆነው አቅራቢ ብር 11,610,351.95 በቅድሚያ የተከፈለ ሲሆን ክፍያው በሂሳብ መደብ 4253 በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ ተይዞ መገኘቱን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የሂሳብ አያያዝና አወቃቀር ስርዓት መሰረት ባደረገ አሰራር ተግባራዊ ሊደረግ እንደሚገባና ወጪ ሳይሆኑ በወጪ የተመዘገቡ ሂሳቦች ማስተካካያ ሊሰራለት እንደሚገባ፣
- የቅድሚያ ክፍያ ሂሳቦች የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት እንዲመዘገብ በማድረግ ለወደፊቱም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንደሚኖርበት፣

አሳስበናል፡፡

4.9 **<u>የተለያዩ የመሰረተ ልማት ግንባታ ወጪዎችን በተመለከተ</u>፣**

4.9.1 **<u>በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ቅድሚያ ክፍያ</u>፣**

- **የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ** ለውሃ መስመር ዝርጋታ ፕሮጀክት ለስራ ተቋራጩ በቅድሚያ የተከፈለው ብር 3,450,317.45 በቅድሚያ ክፍያ መመዝገብ ሲገባው በቀጥታ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- **በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ** የግቢ አጥር ለማሰራት ውል ከተገባው ብር 5,051,028.15 30% የቅድሚያ ክፍያ ብር 1,515,308.45 የተከፈለ ሲሆን ሂሳቡ በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፣

<u>የማሸሻያ ሀሳብ</u>፣

- **የቅድሚያ ክፍያ ሂሳቦች የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት እንዲመዘገብ በማድረግ ለወደፊቱም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንደሚኖርበት፣**

አሳስበናል፡፡

4.9.4 **<u>ሌሎች ከግንባታዎች ጋር የተያየዙ ችግሮች</u>፣**

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	በገንዘብ መጠን	የወጪው ምክንያት
1	አሶሳ ዩኒቨርስቲ	8,809,188.08	የጉዳት ካሳ(ቅጣት) ያለመከፈሉ
2	ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ	1,244,415.82	« «
3	መቱ ዩኒቨርስቲ	37,841,348.48	« «
ጠቅላላ ድምር		<u>47894952.38</u>	

የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ፡-

- ገለልተኛ አማካሪ መሃንዲስ ሣይቀጥር የዩኒቨርሲቲው የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት በሚሰጠው የክፍያ የምስክር ወረቀት ብቻ በድምሩ ብር 8,028,122.88 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑን፣
- ከተለያዩ የስራ ተቋራጮች በገባው የውል የገንዘብ መጠናቸው በድምር ብር 28,420,771.30 ለግንባታ ስራ ውል ቢገባም ነገር ግን በተለያዩ ምክንያት ከዩኒቨርሲቲው ጋር የነበረው ውል በመቋረጡ የተወሰደው ቅድሚያ ክፍያ

በድምሩ ብር 4,261,142.06 ለዩኒቨርሲቲው ተመላሽ ያልተደረና እንዲሁም በውሉ መሰረት ያልተቀጡ መሆኑን፣

- ከአንድ የስራ ተቋራጭ የውል መጠን ብር 15,777,590.75 ከዩኒቨርሲቲው ጋር የነበረው ውል የተቋረጠ ቢሆንም፣ ምንም እንኳን የወሰደው ቅድሚያ ክፍያ ቢመልስም በውሉ መሰረት ያልተቀጣ መሆኑን፣

የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ

- ለተከናወነው የግንባታ ሥራ ከአማካሪ መሃንዲስ በሚሰጥ የክፍያ የምስክር ወረቀት መከናወን የሚገባውን የማማከር ስራ በጠቅላላ የውል ዋጋ ብር 20,385,583.59 ያላቸው እና በድምሩ ብር 5,883,019.82 የክፍያ ሰርተፊኬት ትክክለኛነት በአማካሪ ድርጅት ሳይረጋገጥ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ብር 2,359,106.93 በችሮታ ጊዜ የተመዘገበ የግንባታ ወጪ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ የተመዘገበ ዋና ሰነድ (ኦሪጅናል) ለኦዲት ስራ ተጠይቆ ማቅራብ ስላልተቻለ የወጪውን ትክክለኝነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣

መቱ ዩንቨርስቲ፡-

- የሶስተኛ ምእራፍ 1ኛ ዙር እና የሶስተኛ ምእራፍ 2ኛ ዙር ግንባታዎች መጠናቀቅ ከነበረባቸው ከ126 እስከ 450 ቀናት የዘገዩ መሆኑ፣
- ሳይጠናቀቁ ከዘገዩ የኮንስትራክሽንና የመሠረተ ልማት ግንባታዎች ላይ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ መሆን የነበረበት የዋናው ውል 1/1000ኛ የጉዳት ካሳ በድምሩ ብር 37,841,348.48 ለዩኒቨርሲቲው ገቢ አለመደረጉ ተረጋግጧል፡፡
- በትምህርት ሚኒሰቴር እና በመቱ ዩኒቨርሲቲ መካከል በ2005 ዓ.ም የግንባታ ሥራዎች በዩኒቨርሲቲው ባለቤትነትና ሃላፊነት እንዲካሄድ ከትምህርት ሚኒሰቴር ወደ ዩኒቨርሲቲ ያስረከባቸዉ ስራ ተቋራጮች ርክክብ ሲደረግ ከስራ ተቋራጮች የሚፈለገዉ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣ተከፋይ ሂሳብ እና ዕዳ በትክክል ታውቆ ወደ ዩኒቨርሲቲ ባለመተላለፉ በወቅቱ ዩኒቨርሲቲው ከስራ ተቋራጮች የሚፈለገዉ ተሰብሳቢ ሂሳብ፣ተከፋይ ሂሳብ እና ዕዳ መዝግቦ ያልያዘ መሆኑና አሁን ያለዉ የህንጻ ተቋራጮች የተሰብሳቢ ፣የተከፋይ እና

የመያዣ ሂሳብ የሚያሳየው ዩኒቨርሲተው ግንባታውን ተረክቦ ማስተዳደር ከጀመረበት ጊዜ በኃላ ያለው ሂሳብ ብቻ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

- ኒሐም ኢኒተርናሽናል ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር የብር 14,699,675.00 ፒፒስ ሲሚንቶ ለማቅረብ ውል የተገባ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው የውሉን ጠቅላላ ዋጋ *30% (14,699,675.00*30%)= ብር 4,409,902.50 ቅድሚያ ክፍያ መስጠት ሲገባ ብር 14,699,675.00 ሙሉውን ጠቅላላ የውሉን ዋጋ ተሰጥቶ የተገኘ መሆኑ፤

በአዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፡-

- የክፍያ ሰነዶችና የምስክር ወረቀቶች በዩኒቨርሲቲው የግንባታ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ስራ አስኪያጅ እንዲፀድቁ በማድረግ ብር 103,950,823.27 መከፈሉን፣
- ለተጨማሪ የግንባታ ሥራዎች መከፈል ከሚገባው በላይ በድምሩ ብር 28,906,495.29 ተከፍሎ መገኘቱን፣
- ዩኒቨርሲቲው ባልተጠናቀቁ የግንባታ ስራዎች ተጨማሪ ውል ሳይገባ ከውሉ በላይ በብልጫ በድምሩ ብር 39,536,072.57 ክፍያ ፈጽሞ መገኘቱን፣

በደብረ ታቦር ዩኒቨርስቲ፡-

- በተቋሙ የግንባታ ጽ/ቤት መሀንዲስ እና በሀ/ሥ/ተቋራጮች በተዘጋጁ የክፍያ ሰርተፍኬቶች በድምሩ ብር 46,274,890.74 ለተለያዩ ተቋራጮች እንዲከፈል መደረጉን፣
- ማዕከላዊ የቤተ መፅሐፍት ለማስገንባት ዩኒቨርሲቲው በገባው ውል ብር 17,728,617.38 ላይ ተጨማሪ ውል የዋና ውሉን 25% ብር 4,432,154.35 መሆን ሲገባው፣ በብር 8,721,849.94 ውል በመፈፀሙ ብር 4,289,695.59 እንዲሁም በአዲስ ዘመን ሆስፒታል ሳይት አንድ በዋና ውል ብር 6,946,195.97 ላይ ተጨማሪ ውል የዋና ውል 25% ብር 1,736,549 መሆን ሲገባው፣ በብር 2,031,588.41 ውል በመግባቱ ብር 295,039.42 በድምሩ ብር 4,584,735.01 ከአዋጁ ውጭ በብልጫ ውል መግባቱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ የስፖርት ፋሲሊቲ ለማሰራት በገባው በቀድሞ ውለታ ያልተካተቱ ስራዎችን ለማሰራት በአዋጁ መሠረት በዋና ውል ብር 6,568,585.15 ላይ 25% በማስላት ለብር 1,642,146.29 ብቻ ተጨማሪ ውል መግባት ሲገባው፣ በብር 26,596,784.85 አዲስ ውል በመግባቱ ከአዋጁ ውጭ በብልጫ የብር 24,954,638.56 ውል ገብቶ መገኘቱ፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>፣

- በወጣው የመንግሥት አዋጅ፣ ደንብ እና መመሪያ መሠረት የግንባታ ሥራዎችን እንዲከናወኑ በማድረግ የህዝብ ሀብት ለብክነት እንዳይጋለጥ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ፣
- ግንባታዎቹን በውሉ መሰረት በወቅቱ ባላጠናቀቁ ኮንትራክተሮች ላይም በመመሪያውና በውሉ መሠረት ተገቢውን እርምጃ መውሰድ እና ለወደፊቱ እንዲህ አይነት ክስተቶች እንዳይፈጠሩ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ፣
- በህንጻ ስራ ተቋራጮች ላይ ግንባታው ወደ ዩኒቨርሲቲው ሳይተላለፍ በፊት የነበረውን የተሰብሳቢ፣ የተከፋይ እና የመያዣ ሂሳብ ሰነድ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመነጋገር ርክክብ ተከናውኖ ከስራ ተቋራጮች የሚፈለገው ዕዳ በትክክል ታውቆ ከስራ ተቋራጮች ያልተቀነሰ ተሰብሳቢ/ዕዳ መሰብሰብ እንደሚኖርበት፣
- ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሳይገኝ የማማከር አገልግሎት መሰጠት እንደማይኖርበትና ለወደፊቱም መሰል ስህተቶች እንዳይከሰቱ የእርምት እርምጃ መወሰድ እንደሚኖርበት፣
- የተጨማሪ ስራ /supplementary orders/ በመመሪያው ከተቀመጠው 30 በመቶ በላይ ተጠቅሞ መገኘቱ አግባብ ባለመሆኑ ለምን ከመንግስት የግዢ ደንብና መመሪያ ውጭ ሊፈጸም እንደቻለ ተጣርቶ ሪፖርት ሊቀርብ እንደሚገባ፣
- ከውሉ በላይ ለተፈጸመው ክፍያ ተጨማሪ የስራ ውለታ ወይም የለውጥ የሥራ ትእዛዝ /Supplementary & Variation Orders/ የተሟላ ማስረጃ ሊቀርብ እንደሚገባ፣ ካልሆነም ክፍያው አግባብ ስላልሆነ ገንዘቡ ተመላሽ ሊሆን እንደሚገባ፣

አሳስበናል፡፡

4.10 <u>**የወጪውን ትክክለኛነት ማጣራት ያልተቻለ ሂሳብ፣**</u>

- **የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት** ብር 1,496,954.03 ለቀረጥ የተከፈለ ቢሆንም ዕቃዎቹ ስለመግባታቸው የሚያረጋግጡ ተገቢው ማስረጃ ሊቀርብ ባለመቻሉ ማረጋገጫ መስጠት አልተቻለም፡፡
- **የዋቸሞ ዩኒቨርስቲ** ብር 347,726.00 የውሎ አበል ክፍያ ዩኒቨርሲቲው በራሱ በቀረፀው የውሎ አበል ክፍያ ማወራረጃ ቅጽ ሂሳቡ እንዲወራረድ መደረጉና ሠራተኛው ለጉዞ የተነሳበት እና የደረሰበት ሰዓትና ቀን እንዲሁም ለሥራ የቆየባቸው ቦታዎች ባለመገለፃቸው የተነሳ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- **በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት** በድምሩ ብር 8,179,060.00 የተከፈለባቸው የወጪ ማስረጃዎች ለኦዲት ባለመቅረባቸው የክፍያውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

<u>**የማሻሻያ ሀሳብ፣**</u>

- ማናቸውም የመንግስት ገንዘብ ወጪ ሆኖ ለዕቃም ሆነ ለአገልግሎት ክፍያ ሲከናወን ተገቢው ማስረጃ መቅረብ እንዳለበትና የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ያልቀረበለት ክፍያ ደረሰኝ ቀርቦ ከወጪ ሰነዱ ጋር መያያዝ አለ ዕቃውም ገቢ ለመሆኑ የንብረት ደረሰኝ ሊቆረጥ እንደሚገባ፣
- ዩኒቨርሲቲው የውሎ አበል ክፍያ ሲፈጽም በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር የውሎ አበል ክፍያን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንዲቻል ዝርዝር መረጃ በቅፁ ላይ እንዲገለፅ እና በተገቢው የማወራረጃ ቅጽ እንዲወራረድ ጥብቅ ክትትል እና ቁጥጥር መደረጉደሚኖርበት፣
- የተሰበሰበውን ገቢ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንዲቻል ተገቢው ማስረጃ ለኦዲቱ መቅረብ እንዳለበት፣

አሳስበናል፡፡

4.11 <u>**የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበበት ወጪ ሂሳብ፣**</u>

ተ.ቁ	የመ/ቤቱ ስም	በገንዘብ መጠን	የወጪው ምክንያት
1	የሳ/ና ቴክ.ሚኒስቴር	4,743,664.81	የተለያዩ ዕቃዎች የተገዛበት
2	የሳ/ና ቴክ. መረጃ ማዕ.	690,947.96	ኮምፒዩተር የተገዛበት
3	የአካ. ደንና አ.ን. ለውጥ ሚኒስቴር	22,860.22	« «

4	የቴክ/ና ሙያ ት/ና ሥ.ኤ	1,073,235.00	ምንጣፍ የተገዛበት
5	አዳማ ሳ/ና ቴክ. ዩኒቨ.	4,302,552.26	የውሃ ማጠራቀሚያ ጋን የተገዛበት
ጠቅላላ ድምር		10,833,260.25	

የማሻሻያ ሀሳብ፣

- ወደ መስሪያ ቤቱ ዕቃ መጋዘን ንብረቱ ገቢ ሳይሆን የሚከናወን ክፍያ አግባብነት ስለለሌው ገቢ ሳይሆን ለተከፈለው ክፋያ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለት ከወጪ ሰነዱ ጋር መያያዝ እንደአለበትና ለወደፊትም የዕቃ ግዥ ክፍያ ሲፈጸም በንብረት ገቢ ደረሰኝ ዕቃው ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ስለመደረጉ ተጣርቶ መከፈል እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

5. የተከፋይ ሂሳብ፣

5.1 ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ / በቆይታ ጊዜው ይተንተን/፣

በገ/አ/ል/ሚ/ር መመሪያ መሠረት በበጀት ዓመቱ በተከፋይ ሂሣብ የተያዙት ሂሣቦች በተገቢው ጊዜ ውስጥ መከፈላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በ21 መ/ቤቶች ብር 77,632,748.48 በወቅቱ ያልተከፈለ ተከፋይ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 31 ተመልክቷል/

በመሆኑም መ/ቤቶች በወቅቱ ያልተከፈለውን ተከፋይ ሂሳብ ለሚመለከተው አካል የፋይናንስ ሕጉን ተከትለው እንዲከፍሉ አሳስበናል፡፡

5.2 በተከፋይ ሂሳብ ዙሪያ የታዩ ዋና ዋና የአሠራር ድክመቶች፣

- **በደብረታቦር ዩኒቨርሲቲ** በዕቅድና በተከፋይነት ያልተያዘ እና በጀት ያልተፈቀደለት የመያዣ ሂሳብ በድምሩ ብር 2,524,444.26 በሂሳብ መደብ 6323 በወጪ ተይዞ ለተለያዩ የህንፃ ተቋራጮች ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
- **በወልዲያ ዩኒቨርሲቲ** በዕቅድና በተከፋይ ያልተያዘ እና በጀት ያልተፈቀደለት የመያዣ ሂሳብ በድምሩ ብር 947,988.21 በሂሳብ መደብ 6323 በወጪ ተይዞ ለተለያዩ የህንፃ ተቋራጮች ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ፡-

- በተለያዩ የሂሳብ መደቦች በድምሩ ብር 8,870,339.63 በተከፋይ ተይዞ መገኘቱንና በተከፋይ የተያዘበትን ቀንና ዓ.ም፣ የሚከፈልበትን ግዜ እና

የሚከፈለውን ባለመብት ድርጅት ወይም ግለሰብ የሚገልፅ ዝርዝር መረጃ ባለመቅረቡ ሂሳቡ ለሚመለከተው አካል ሳይከፈል ለምን ያህል ግዜ እንደቆየ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

- ለብየዳ የደህንነት መጠበቂያ መነጽር ተገዛበት ክፍያ ሲፈፀም ፤የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 11,775.00 እና የዊዝ ሆልዲንግ ክፍያ ብር1,570.00 በድምሩ ብር 13,345.00 ተቀናሽ ለመደረጉ ማስረጃ ቢቀርብም በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ በተከፋይ ሳይመዘገብ መገኘቱ፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ክፍያው የመንግስትን የክፍያ መመሪያ ያልተከተለ በመሆኑ በሥራ አመራሩ ክትትል ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ እንንሚገባና ለወደፊቱም በጀት ያልተፈቀደላቸው ክፍያዎች እንዳይፈፀሙ ተገቢው ቁጥጥር መደረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

6. **<u>የበጀት አጠቃቀም፤</u>**

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት አዲት ሲደረግ፣

- በ12 መ/ቤቶች የመደበኛ በጀት ብር 44,402,009.14 እና ካፒታል ብር 5,002,858.32 በድምሩ ብር 49,404,867.46 ከበጀት በላይ ወጪ የሆነ፤
- በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% ላይ የሆነውን ብቻ በመውሰድ በ36 መ/ቤቶች መደበኛ በጀት ብር 899,209,302.76 እና ካፒታል ብር 598,647,455.19 በድምሩ ብር 1,497,856,757.95 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩም በአባሪ- 33 ተመልክቷል፡፡/

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- መ/ቤቶቹ ለወደፊቱ በበጀት ዕቅድ ዝግጅት እና አጠቃቀም ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲሁም ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንደሚኖርበት፣
- መ/ቤቶቹ በተጨባጭ ሊሰራ ካቀደው ተግባር ጋር የዓመቱን የበጀት አጠቃቀምን በመገምገም የሚጠየቀው በጀት መረጃን መሠረት በማድረግ በበቂ ምክንያት በጥናት ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባል፡፡

7. <u>የዕቃና ንብረት አስተዳደር፣</u>

7.1 <u>ለዕቃና ንብረት አስተዳደር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት፣</u>

7.1.1 <u>ለቋሚ ንብረት መዝገብ ያልተቋቋመባቸው /ያልተመዘገቡ/ መቤቶች፣</u>

- **በዋችሞ ዩኒቨርስቲ፡-** አልፎ አልፎ የምግብ ቤት ዕቃዎች ስቶክ ካርድ ያልተከፈተላቸው መሆኑ፣
- **የብሔራዊ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት፡-** የቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች እንዲሁም ለነዳጅ ኩፖን መዝገብ ወይም እስቶክ ካርድ ያልተዘጋጀና ንብረቶች ሙሉ በሙሉ ያልተመዘገቡ መሆኑ፣
- **የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የሥልጠና ማዕከል፡-** የአላቂና ቋሚ ዕቃዎች መዝገብ (ስቶክ ካርድ) ያልተቋቋመ መሆኑ፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የመ/ቤቱ ሥራ አመራር የቁጥጥር ድክመቶችና የአሰራር ክፍተቶች ላይ አፋጣኝ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

7.1.2 <u>የአላቂ ዕቃዎች ምዝገባ ያልተከናወነባቸው መቤቶች,</u>

- **የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚ/ር** ምንም ዓይነት የቢን ካርድ እና የስቶክ ካርድ መዝገብ ለአላቂ ዕቃ የማይጠቀም መሆኑን፣
- **የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት** በንብረት ክፍል የነዳጅ ኩፖንና የሞባይል ካርድ የንብረት ገቢና ወጪ ደረሰኞች በስቶክ ካርድና በቢን ካርድ የማይመዘገቡ መሆኑ፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የንብረት አስተዳደር አዋጁ በሚያዘው መሠረት በንብረት ገቢና ወጪ ሰነዶች ላይ የተመለከቱት በስቶክ ካርድና በቢን ካርዱ ለመመዝገባቸው ጥብቅ ክትትል ቁጥጥር መደረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

7.1.3 <u>ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያደረጉ ሆነው፣ ከመዝገብ ጋር ያላገነዘቡ መቤቶች፣</u>

- **የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ** በ2008 በጀት ዓመት በኮሚቴ የንብረት ቆጠራ ተደርጎ ከምዝገባ ጋር የማመሳከርና የማመዛዘን ሥራ ያልተሰራ መሆኑን፣
- **የሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ** የተቆጠሩት ቋሚ ዕቃዎች ከስቶክ ካርድና ከተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ

ካርድ (User Card) ከተመለከተው ጋር የማስታረቅና የማመሳከር ሥራ ያልተሰራ መሆኑ፣

- **የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል** ማዕከሉ በ2008 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ ያደረገ ቢሆንም፣ በቆጠራ የተገኘውና በስቶክ ካርድ ላይ የተመለከተው የእያንዳንዱ ቋሚ ዕቃ ከወጪ ቀሪ ጋር ተመዛዝኖ ትክክለኛነቱ የማይረጋገጥ መሆኑና ቋሚ ዕቃዎቹ ሙሉ በሙሉ መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- **በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት** በበጀት ዓመቱ የንብረት ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ከዕቃ መዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር እንዲመሳከር አለመደረጉን፣
- **የእካባቢና የደን ምርምር ኢንስቲትዩት** በበጀት ዓመቱ በሰራተኞች እጅ ያሉ የቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ከመነሻ መዝገብ ጋር እንዲመሳከር አለመደረጉን፣
- **የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር** በግምጃ ቤት የሚገኙ ንብረቶች ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ያልተገናዘበ እና በዓይነታቸው ተለይተው ያልተቀመጡ መሆኑን፣

7.1.4 <u>ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያልተካሄደባቸው መቤቶች፣</u>

- **የብሔራዊ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት** 2008 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ የቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ እና አገልግሎት ለሚሰጡ ቋሚ ዕቃዎች አብዛኛው መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- **የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የሥልጠና ማዕከል** ዓመታዊ የቋሚ ንብረት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ እና የቋሚ ዕቃ መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፣
- **የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን** በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ የቋሚዕቃዎች ቆጠራ ያልተከናወነ መሆኑ፣
- **የመቱ ዩኒቨርስቲ** በ2008 በጀት ዓመት የቋሚ ንብረት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ እና ለቋሚ ንብረቶች መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፣
- **የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር** በ2008 በጀት ዓመት ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ በዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ያለው ብቻ የተደረገ ቢሆንም፣

በሠራተኞች ወይም በየቢሮው የሚገኙ ቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ ያልተከናወነ መሆኑ እና ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ያልተሠጠ መሆኑ፣

- **የአካባቢ፤የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር** በሰራተኞች እጅ የሚገኙ ቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ ያልተደገረና በየክፍሉ የሚገኙ ንብረቶች መለያ ቁጥር /ታግ/ ያልተሰጣቸው መሆኑን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

- የንብረት አስተዳደሩ መንግስት ባወጣው የንብረት አጠቃቀም፣ አጠባበቅና አያያዝ መመሪያ መሠረት እንዲስተካከልና እንዲፈፀም ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር ማደረግ እንደሚኖርበት፣
- በቆጠራ የተገኘውና በስቶክ ካርድ የተመለከተው የእያንዳንዱ ቋሚ ዕቃ ከወጪ ቀሪ ጋር ተመዛዝኖ ትክክለኛነቱ መታወቅ እንደሚኖርበት፣
- ለቋሚ ዕቃዎች ተከታታይ መለያ ቁጥር ሙሉ በሙሉ ሊሠጣቸው እንደሚገባ፣

አሳስበናል፡፡.

7.1.5 **<u>ሌሎች የንብረት አያያዝ ድክመቶች የታዩባቸው መቤቶች፣</u>**

በትምህርት ስትራቴጂ ማዕከል ሠራተኞች በተለያየ ምክንያት ማዕከሉን ሲለቁ ወደ ቋሚ ግምጃ ቤት አሮጌ ኤሌክትሮንስ እቃዎች ሲመለሱ እቃዎቹ እስከነሙሉ እቃቸዉ ስለመመለሳቸው በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያ(ICT) የማይረጋገጥ መሆኑ በኦዲት ተገኝቷል።

በፋይናንስ ደህንነት መረጃ ማዕከል፡-

- የማዕከሉ ቋሚ ንብረት የተሟላ መለያ ቁጥር አለመሰጠቱን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡
- በማዕከሉ የሚገኙ ያገለገሉ ቋሚ ንብረቶች በወቀቱ የማይወገዱ መሆኑን በኦዲት ተረጋግጧል፡፡

በሆቴልና ቱሪዝምሥራ ማሰልጠኛ ኢ/ት. መወገድ የሚገባቸው ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ሳይወገዱ መገኘቱ፣

በአሶሳ ዩኒቨርስቲ:-

- መወገድ ያለባቸው በርካታ የተለያዩ ንብረቶች ያልተወገዱ መሆኑ፣

- በቁጥር 69 አዲስ የተማሪ መኝታ (አልጋ) ሜዳ ላይ ተበታትኖ ዝናብና ፀሐይ እየተፈራረቀበት መሆኑ፣
- ተጠግነው አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ በርካታ የተለያዩ ንብረቶች ጥገና ያልተደረገላቸውና አገልግሎት እንዲሰጡ ያልተደረገ መሆኑ፣
- በተጠቃሚዎች እጅ ያሉት ላፕቶፖች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፤

በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የዩኒቨርስቲው የንብረት አስተዳደር ሲታይ በንብረት ደንብና መመሪያ መሠረት በአግባቡ ዕቃዎች ያልተያዙና ያልተወገዱ መሆኑን፣

በዋቸሞ ዩኒቨርስቲ:-

- የምግብ ቤት ዕቃዎች በሞዴል 19 እና በሞዴል 22 ገቢና ወጪ የሚደረገው በአንድ ሠራተኛ መሆኑ፣
- Flash/ፍላሽ/ የአገልግሎት ዘመኑ ከአንድ ዓመት በላይ ቢሆንም ብዛታቸው ከ 481 በላይ ፍላሾች በአላቂ ንብረት መዝገብ ተመዝግበው ለሠራተኞች የተሰጡ መሆኑ፣
- የምግብ ቤት ዳቦ ማሽን እና ማቀዝቀዣዎች ያለ አገልግሎት ከሶስት(3) ዓመት በላይ የተቀመጡ መሆናቸው፣
- የአላቂ ንብረት ግምጃ ቤት ጣሪያ የሚያፈስ መሆኑ፣

በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚ/ር:-

- በአላቂ እና በቋሚ ንብረት ክፍል የንብረት ገቢ (ሞ/19) እና ወጪ (ሞ/22) ደረሰኝ በአንድ ግለሰብ እጅ ብቻ እንደሚገኝ እና የንብረት መዝጋቢ ባለመኖሩ በአንድ ሠራተኛ የሚከናወን መሆኑ፣
- በሚንስቴር መ/ቤቱ መዋቅር መሠረት የቋሚና የአላቂ ንብረት ክፍል የተለያየ ሰው መሆን ሲገባው ሁለቱም በአንድ ሰው የሚሰራ መሆኑን፣

ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ:-

- በዩኒቨርስቲ በንብረት አስተዳደር መመሪያ መሰረት የተናጠል ዋጋቸው 1000 በላይ የሆኑ ተለያዩ እቃዎች በቋሚ ንብረት መመዝገብ ሲገባቸው እንደአላቂ ንብረት በአላቂ ንብረት ሞዴል 19 ገቢ እና በአላቂ ንብረት ሞዴል 22 ወጪ ሆኖ ለሠራተኞች የተሰጡ መሆኑ።

- በዩኒቨርሲቲው ለቋሚ ዕቃ ንብረት በክፊል መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑን፣

የፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚ/ር ሚ/ር መ/ቤቱ መወገድ ያለባቸው የተለያየ ዓይነት ዕቃዎችና ከቀድሞ አቅም ግንባታ ሚኒስቴር የመጡ የተለያዩ ንብረቶች መወገድ ሲገባቸው ያልተወገዱ መሆኑን፣

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ፡-

- በሀይድሮሊክ ህንፃ ክፍል ውስጥ በርካታ ዕቃዎች በመሬት ላይ ተደራርበው ንፅህና በሌለው ክፍል ውስጥ ያለ መደርደሪያ መቀመጣቸው እና ቢን ካርድ የማይንጠለጠልባቸው መሆኑ፣
- መስራት እየቻሉ ከአንድ ዓመት በላይ ተጠቃሚዎች ሳያወጧቸው የተቀመጡ ንብረቶች የተገኙ መሆኑን፡፡
- በርካታ አዳዲስ የላይብረሪ ጠረጴዛ በላይብረሪው በራፍና ዙሪያ ውጪ ተቀምጠው ለፀሐይና ለዝናብ እየተጋለጡ መሆኑ፣
- መስራት እየቻሉ ከሶስትና ከአራት ዓመት በላይ ተጠቃሚዎች ሳያወጧቸው የተቀመጡ አላቂ ንብረቶች የሚገኙ መሆኑ፣
- በሃይድሮሊክ ህንፃ በአንድ ክፍል ውስጥ መስራት እየቻሉ ተመላሽ ተደርገው ከማይሰሩ ዕቃዎች ጋር ተደባልቀው መቀመጣቸው እና ቢን ካርድ የማይንጠለጠልባቸው መሆኑ፣
- መወገድ የሚገባቸው በርካታ የመኪና ጎማዎች ከዓመት በላይ መቀመጣቸውን በአዲት ወቅት ለማረጋገጥ ችለናል፡፡

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ፡-

- በቋሚ ንብረት ክፍል ውስጥ የንብረት መጠበቅ፣ የሞደል 19 እና 22 የመመዝገብ በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑን፣ ተረጋግጧል፡፡
- የቋሚ ንብረት ክፍል ውስጥ ሁለት ንብረት ያዥ /የሚያስተዳድሩት/ ሰራተኞች የሚቆጣጠሩት ውስጥ የማይሰሩ ንብረቶች አንድ ክፍል ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው በቂ የንብረት መጋዘን ባለመኖሩ በርከት ያሉ ንብረቶች መሬት ላይ እና በአንድ ላይ ተደራርበው የሚገኙ መሆኑ፣

- የአላቂ ንብረት ክፍል ጥበት የተነሳ በቋሚ ንብረት ክፍል እና በአላቂ ንብረት ክፍል የጋራ ኮሪደር ውስጥ ብዛታቸዉ 132 ፔርሙሶች በካርቶን የተቀመጡ መሆኑ፣
- በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ የተለያዩ መኪናዎች መለዋወጫዎች ካለ አገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣
- በቴክኒክ ክፍል አካባቢ የተለያዩ ዕቃዎች ሳይወገዱ ተከማችተው የተገኙ መሆኑ፣

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት መወገድ የሚገባቸው የተለያዩ ቶነሮች፣ ማሽነሪዎች፣ ጠረጴዛ፣ ወንበሮች፣ የተሸከርካሪ መለዋወጫዎች፣ አንድ ሞተር ተሸከርካሪ፣ ሳይወገዱ መገኘቱ፣

የምግብ መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት

- የቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ ሪፖርት ለኦዲት ያልቀረበ መሆኑ፣
- በንብረት ክፍሉ ውስጥ የሚወገዱ ናቸው ተብለው የተቀመጡ የተለያዩ ዕቃዎች ሳይወገዱ መገኘታቸው፣

የብሔራዊ የቆላ ዝንብና ገንዲ በሽታ መቆጣጠሪያና ማጥፊያ ኢንስቲትዩት፡-

- በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) እንዲሁም በንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 22) ላይ አልፎ አልፎ የዕቃዎቹ ዋጋ የማይገለጽ መሆኑ፣
- የተሰባበሩ ቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች የሚገኙ መሆኑ እና እስከ አሁን ድረስ በመመሪያው መሰረት ሳይወገዱ የተገኙ መሆኑ፣
- የንብረት ክፍል ሠራተኛ አንድ በመሆኑ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ተገዝተው በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ገቢ እንዲሁም በንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 22) ወጪ የሚደረጉት በዚሁ ሰራተኛ መሆኑ

የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የሥልጠና ማዕከል፡-

- በተጠቃሚዎች እጅ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (UC) ያልተቋቋመ መሆኑ፣
- በቢን ካርድ ላይ ያለዉ ከወጪ ቀሪ ሚዛን እና በንብረት ክፍል ውስጥ የተገኘው ዕቃ ከወጪ ቀሪ እኩል አለመሆኑን፣
- ብዛታቸው የማይታወቅ የሚወገዱ ንብረቶች ሳይወገዱ የቆዩ መሆኑ፣

- በሞ/19 እና በሞ/22 ንብረት ገቢና ወጪ የማድረግ ሥራ እና ንብረትን የመጠበቅ ሥራ በአንድ ሠራተኛ የሚከናወን መሆኑ፣

የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፡-

- የፕሮጀክት ንብረት በሞዴል 19 ገቢ እና በሞዴል 22 ወጪ ሲደረግ፣ እንዲሁም ምዝገባው የሚከናወነው ከመደበኛው ገቢና ወጪ ጋር በአንድነት ተቀላቅሎ መሆኑ፣
- በየቢሮው ያሉ ቋሚ ዕቃዎች መቆጣጠሪያ ካርድ (UC) ያልተቋቋመ መሆኑ፣
- ቢን ካርድ እና ስቶክ ካርድ ቢኖርም፣ ቢን ካርዱ እና ስቶክ ካርዱ በወቅቱ የማይመዘገብ መሆኑን፣
- በ2008 በጀት ዓመትም የተለያዩ የሚወገዱ ዕቃዎች የሚገኙ መሆኑ፣

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን፡-

- የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች አገልግሎት የማይሰጡ ቴፕሪኮርደር፣ ድምጽ መቅረጫና የመሳሰሉት የሀይለክስ ፍሪሲዮን ዲስክ፣ የመኪና ባትሪ ባጠቃላይ 110 ዓይነት ዕቃዎችና የተለያየ ብዛት ያለው ዕቃ መኖሩ፣
- ከቢሮ የተመለሱ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች አገልግሎት የማይሰጡ ኮምፒውተር፣ ስክሪን እና ሌሎች 28 ዓይነት ዕቃዎችና የተለያየ ብዛት ያለው ዕቃ መኖሩ፣
- ባትሪዎች 7 ዓይነት ዕቃዎችና የተለያየ ብዛት ያለው ዕቃ መኖሩ፣
- እንጨትና ችፑድ 9 ዓይነት ዕቃዎችና የተለያዩ ብዛት ያለው ዕቃ መኖሩ፣
- ሲንክ፣ መሰታወትና ሌሎች 10 ዓይነት ዕቃዎችና የተለያየ ብዛት ያለው ዕቃ መኖሩ እና የተለያዩ የኃላፊ ስም የእንግሊዝኛና የአማርኛ ቲተር 12 ዓይነት መኖሩ፣

በአጠቃላይ ንብረቶቹ ለመንግስት ግዥና ንብረት ማሰወገድ አገልግሎት በ02/11/2005 የቀረበ ቢሆንም፣እስከአሁን ንብረቶቹ ሳይወገዱ ተገኝተዋል፡፡ በተጨማሪም በ2007 አዲት ወቅት አሰተያየት የተሰጠ ቢሆንም እርምጃ ሳይወሰድ መገኘቱ፣

- የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል/19 እና የንብረት ወጪ ደረሰኝ ሞዴል/22 የማዘጋጀትና የዕቃ ግምጃ ቤትን በኃላፊነት የመጠበቅ ሥራ በአንድ ሠራተኛ የሚሰራ መሆኑ፣

የሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ፡-

- በተጠቃሚዎች እጅ ላይ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) በሁለት ቅጅ ተዘጋጅቶ አንዱ ለተጠቃሚው ሌላው በንብረት ክፍል እንዲያዝ መመሪያው ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ የመሥሪያ ቤቱ ንብረት ክፍል በተሟላ ሁኔታ የሚሰራበት አለመሆኑ፣
- የቋሚ ዕቃዎች ቆጠራ ሲካሄድ በቆጠራ ሰንጠረዡ ላይ የተቆጠሩት ቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥራቸው በአብዛኛው ያልተገለጸ በመሆኑ በየቢሮው ተቆጠሩ የተባሉትን ቋሚ ዕቃዎች ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
- የተሸከርካሪ መለዋወጫ ዕቃዎች፣ የኮምፒውተር እና ሌሎች በርካታ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ሊወገዱ የሚገባቸው ዕቃዎች ስለመኖራቸው ተረጋግጧል፡፡
- የቋሚ ዕቃ እና የአላቂ ዕቃ ንብረት ክፍል (ግምጃ ቤት) የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሞዴል/19 እና የንብረት ወጪ ደረሰኝ ሞዴል/22 የሚዘጋጀውና የሚመዘገበው በሁለቱም ንብረት ክፍል ለየእራሱ አንድ አንድ ሰው በመመደብ በአላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኛ እና በቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኛ ብቻ የሚሰራ መሆኑ፣

መቱ ዩኒቨርስቲ፡-

- በዩኒቨርሲቲው በቂ የንብረት መጋዘን ባለመኖሩ በርከት ያሉ ንብረቶች መሬት ላይ ተደራርቦ የተቀመጡና የተቀናጀ አስራር የሌለ መሆኑ፡
- በቋሚ እና አላቂ ንብረት ክፍል ዉስጥ ስቶክ ካርድ በአግባቡ በመመዝገብ የንብረት ቁጥጥር የማይደረግ መሆኑን፣
- በቋሚ ንብረት ክፍል ዉስጥ ቢን ካርድ ላይ አልፎ አልፎ የሚመዘገብ ቢሆንም ከንብረት ከወጪ ቀሪ ጋር ሲናበብ ልዩነት የሚያሳይ መሆኑና ለበርካታ ንብረቶች ቢን ካርድ ያልተቋቋመ መሆኑን፡

- በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ ለንብረቶቹ ቢን ካርድ ያልተቋቋመላቸው መሆኑ፣
- በቋሚ እና በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኙት እቃዎች በዓይነት፣በባህሪይና በሚሰጡት አገልግሎት ተለይተው በሥርዓት ያልተቀመጡ መሆኑ፣
- በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ ብዛታቸው 224 የላብራቶሪ ጠረጴዛዎች አለአግባብ ከተገዙበት አላማ ዉጪ እንደ ዕቃ መደርደሪያነት ጥቅም ላይ በመዋላቸው ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፣
- ከንብረት ክፍል ንብረቶች ወጪ ሲደረጉ አብዛኛዎቹ ንብረቶች በሞዴል 22 ላይ የእያንዳንዱ ዋጋ እና ጠቅላላ ዋጋ የማይመዘገብ መሆኑን፣
- በተማሪዎች ክሊኒክ አካባቢ ያለው በአሮጌ ዕቃ መመለሻ ክፍል ውስጥ የማያገለግሉ እቃዎች ሳይወገዱ የሚገኙ መሆኑ፣
- የቋሚ ንብረት መጋዘን ውስጥ የተለያዩ እቃዎች እና አንድ ካረቶን መስታውቶች ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣
- የቋሚ ንብረት መጋዘን ውስጥ መወገድ የሚገባቸው ጊዜ ያለፈባቸዉ ኬሚካሎች የሚገኙ መሆኑ፣
- የቋሚ ንብረት መጋዘን አካባቢ እና የተማሪዎች ምግብ አዳራሽ አካባቢ ብዛታቸው የማይታወቁ የፌሮ ብረት ቁርጥራጮች መሬት ላይ ተጥለው የዛጉና ለበለጠ ብልሽት የተጋለጡ መሆኑ፣
- በቀርሳ የሚገኘው የቋሚ ንብረት መጋዘን ውስጥ የተለያዩ ዕቀዎች ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣ እንዲሁም በግቢ ውስጥ ብዛታቸው የማይታወቅ ወንበሮች በግለሰቦች አለአግባብ እየተጠቀሙበት በመሆኑ ለብልሽት የተጋለጡ መሆኑ፣
- የቋሚ ንብረት መጋዘን ውስጥ የሚሰሩና የማይሰሩ ወንበሮች አንድ ላይ የሚገኙ መሆኑ፣
- በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ የማይሰሩ የኮምፑዩተር ዕቃዎች የሚገኙ መሆኑ፣

- በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ ብዛት ያላቸው ዕቃዎች ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣
- ብዛት ያላቸውየውሃና የቢሮ ዕቃ መለዋወጫዎች ከ2004 ዓ.ም ጀምረው ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣

<u>የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃ ግምጃ ቤት፣</u>

- አንድ የዳቦ መጋገሪያ ማሽን፣ አንድ የዳቦ ማቡኪያ ማሽንና ሦስት የስጋ መፍጫ፣ አንድ የድንች መላጫ፣ ስድስት ፍሪጆች በ2005 በጀት ጀምሮ ካለ ስራ የተቀመጡ መሆኑ፣
- የእህል መጋዘኑ አካባቢ ብዛት ያላቸው የዘይት ጀረኪናዎች ሳይወገዱ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ።።

<u>የተማሪዎች ክሊንክ፣</u>

- የመድሀኒት መጠበቂያ(ስቶር) ክፍል ውስጥ ብዛት ያለቸው መጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈባቸው መድሀኒቶች ሳይወገዱ የሚገኙ መሆኑ፣

የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት የሚወገዱ የተለያዩ ንብረቶች ማለት

የተሸከርካሪ መለዋወጫ፣ የተሸከሪካሪ ጎማዎች፣ ከመናዳሪዎች፣ ፓልፖችና ባትሪዎች፣ኮምፒዩተሮች ተያያዥነት ያላቸው የኤሌትሮኒክስ ዕቃዎች እና ቶነሮች ከተከማቹ ከ3-5 ዓመት የሆናቸው ሲሆን ንብረቶቹን በአካል ለማየት ተሞክሮ የአቀማመጥ ችግርና የመጋዘን ጥበት በመኖሩ ያልተቻለ መሆኑ፣

የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት፡-

- በ2008 በጀት ዓመት ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ቆጠራ በስቶክ ወይም በዕቃ መጋዘን ውስጥ እንዲሁም በሠራተኛው ወይም በየቢሮው የሚገኘው የቋሚ ዕቃ ቆጠራ የተከናወነ ቢሆንም የቆጠራውን ሥራ በማጠናቀቅ ለበላይ ኃላፊዎች የቆጠራ ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑ እና ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር በተሟላ ሁኔታ ተሰጥቶ ያላለቀ መሆኑ፣
- አገልግሎት የማይሰጡ ኮምፒዩተሮችና በርካታ የተለያዩ ንብረቶች እንዲወገዱ ለመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የተጻፈ ቢሆንም እስከአሁን ሳይወገዱ የሚገኙ መሆኑ፣ እንዲሁም የንብረት

ክፍሉ ጣሪያ ክፍት በመሆኑ ንብረቱ ለስርቆትና ለብልሽት የተጋለጠ መሆኑ እና በ2007 አዲት ሪፖርት የታየ ቢሆንም ምንም ዓይነት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል ንብረት የሚጠበቀው ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ተገዝተው በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ገቢ እንዲሁም በንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 22) ወጪ የሚደረጉት በአንድ ሠራተኛ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

- በእንሰሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፤ቋሚ ዕቃዎች በመ/ቤቱ ሰራተኞች እጅ የሚገኙ መሆኑን የሚገልፅ ዝርዝር መግለጫ አለመኖሩን፣
- በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት በ2007 በጀት ዓመት የተገዛ 2,000 በርሜል ሬንጅ ከአንድ ዓመት በላይ ጥቅም ላይ ሳይውል መገኘቱን፣

በአዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ:-

- ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ ገቢ የተደረጉ ከለር ሞኒተሮችና የውሃ ማሞቂያዎች ያለ አገልግሎት እንዲቀመጡ መደረጉን፣
- በአለም አቀፍ ጨረታ የተገዙ ብዛት ያላቸው የቅየሳ መሳሪያዎች በንብረት ክፍል ውስጥ ያለ አገልግሎት ከ 2 ዓመት በላይ የተቀመጡ መሆናቸውን፣
- አዲስ የተሰሩ የብረትና የእንጨት ምርቶች በዩንቨርስቲው ንብረት ክፍል ገቢ ተደርገው የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦላቸው እንደንብረት የማይመዘገቡ መሆኑን፣
- የእንጨት ማሽኖችና የተለያዩ መሣሪያዎች ከሁለት አመት በላይ አገልግሎት ሳይሰጡ የተቀመጡ መሆኑና በተጨማሪም ሁለት ማሽኖች ሞተራቸው ከወሰጡ ተፈትቶ የወጣና የሌለ መሆኑን፣

በሠራተኛና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፦

- የተለያዩ ህትመቶች በተደጋጋሚ እንዲታተሙ መደረጉንና አገልግሎት ሳይሰጡ በመ/ቤቱ ቢሮዎች መተላለፊያ(ኮሪደሮች) ላይ እንዲቀመጡ መደረጉን፣
- ለሚኒስትር ዴኤታዋ እና ለቤተሰባቸው የተመደቡትን የሰሌዳ ቁጥር 4-16876 እና 4-01568 የሚ/ር መ/ቤቱን ተሽከርካሪዎች የመ/ቤቱ ሠራተኛ ያልሆኑ ግለሰብ በስማቸው ፈርመው እንዲረከቡ በማድረግ በሸፌርነት እንዲሠሩ መደረጉን፣

ደብረ ታቦር ዩኒቨርሲቲ፦

- በተማሪዎች ክሊኒክ የአገልግሎት ግዜያቸው ያለፈ የተለያዩ መድሀኒቶች የሚገኙ መሆኑ,
- በተማሪዎች ምግብ ማብሰያ ቤት ውስጥ 2 የእቃ ማጠቢያ እና የተለያዩ ምጣዶች ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤
- ሊወገዱ የሚገባቸው ምጣዶች ፣በእጅ የሚሰሩ ምድጃዎች ፣ ወንበሮች ከግምጃ ቤት ውጪ ተጥለው ለበለጠ ብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፤
- በቋሚ ንብረት ክፍል ውስጥ አሮጌ ያገለገሉ ንብረቶች፤ የመኪና ጎማዎችና ወንበሮች ከአዳዲስ ንብረቶች ጋር አንድ ላይ እንዲቀመጡ መደረጉን፤
- በርካታ ቁጥር ያላቸው ለህንጻ መስሪያ የሚያገለግሉ ብረቶች ያለአገልግሎት እንዲቀመጡ መደረጉን፤

በወልዲያ ዩኒቨርሲቲ፦

- በተማሪዎች ክሊኒክ የአገልግሎት ግዜያቸው ያለፈ ብር 13,048.60 የሚገመቱ መድሀኒቶች የሚገኙ መሆኑ,
- በተማሪዎች ክሊኒክ ዉስጥ በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ መደኃኒቶች በመድኃኒት ማስቀመጫ ላይ መቀመጥ ሲገባቸው መሬት ላይ እንዲቀመጡ መደረጉን,
- በተማሪዎች ምግብ ማብሰያ ቤት የተለያዩ ዕቃዎች ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ,

- በቋሚ ንብረት ክፍል አሮጌ ያገለገሉ ንብረቶች፤ የመኪና ጎማዎችና ወንበሮች ከአዳዲስ ንብረቶች ጋር አንድ ላይ እንዲቀመጡ መደረጉን፣
- የቋሚ ንብረት እና ለተማሪዎች የምግብ አገልግሎት የሚውል ጤፍ ከቋሚ ንብረት ጋር በአንድ ክፍል ውስጥ በተለያዩ ሰራተኞች የሚጠበቅ መሆኑ፣
- በአንድ ንብረት ክፍል ውስጥ የተለያዩ ንብረቶች በ3 ባለሙያዎች እንዲጠበቁ መደረጉን፣

በዓዲግራት ዩኒቨርስቲ፡-

- ብዛት ያላቸው የአይሲቲ ዕቃዎች ከንብረት ክፍል ውጪ ያለ አገልግሎት የተቀመጡ መሆናቸውን፣
- ጊዜያቸው ያለፈ ብዛት ያላቸው መድሃኒቶች ከ2 ዓመት በላይ ሳይወገዱ በክሊኒኩ እንዲቀመጡ መደረጉን፣
- ብዛት ያላቸው የተሸከርካሪ ጎማዎች፣ የምግብ ማብሰያ ዕቃዎች፣ የተበላሹ የኤሌክትሪክ ምጣዶች፣ እና ሌሎችም የተለያዩ ዕቃዎች ሳይወገዱ በተማሪዎች ምግብ ቤት አካባቢ ተከማችተው የተቀመጡ መሆናቸውን፣
- አሮጌ (ተመላሽ) የተሸከርካሪ የመለዋወጫ ዕቃዎች ወደ መጋዘን እንዲመለሱ የማይደረግ መሆኑን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

- ያልተወገዱ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች በደንቡ መሠረት እልባት እንደዲያገኙ ማድረግ ይገባል፡፡ ንብረቶች ለብክነት እንዳይዳረጉ የቁጥጥሩን ሥራ ማጠናከርና ያለአግባብ የተቀመጡ ንብረቶች ጥቅም ላይ ሊውሉ እንደሚገባ፣
- ንብረት የሚጠበቀው፤ ቋሚና አላቂ ዕቃዎች ተገዝተው በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19 ገቢ ፤ እንዲሁም በንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞዴል 22) ወጪ የሚያደርግ ሰራተኛ አንድ መሆኑ የመንግሥት ንብረት አጠባበቅ ላይ አስተማማኝ ስለማይሆን መለየት እንደሚገባው፣
- በሌሎቹም የንብረት አያያዝና አጠባበቅ ላይ የእርምት እርምጃ መወሰድ እንዳለበት፣

አሳስበናል፡፡

7.1.6 <u>የገቢ ደረሰኝና ሌሎች የሕትመቶች አያያዝ ችግሮች የሚታዩባቸው መ/ቤቶች፣</u>

- ቡሌ ሆራ ዩኒቨርስቲ ገቢ የተሰበሰበበት የግንዘብ መቀበያ ደረሰኞች በሞዴል 42 ተመዝግቦ ለሰነድ ያዥ ሰራተኛ ርክክብ የማይደረግ መሆኑን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- ክፍያዎች ከመፈጸማቸው በፊት ከክፍያው ጋር ተያያዥነት ያለቸው አላሪ ማስረጃዎች የተሟሉ መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚኖርበት፣
- የቁጥጥር አደረጃጀቱ በፋይናንስ መመሪያ መሠረት የክፍሉን ሥራ እንዲያከናወኑ ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰራተኞች በአግባቡ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማድረግ እንደሚኖርበት፣

አሳስበናል፡፡

7.2 <u>የተሸከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም፣</u>

7.2.1 <u>ሊብሬ ያልቀረበላቸው፣</u>

- **በፍትህና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት** የሠሌዳ ቁጥር 4-23036 እና 4-230374 መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌላቸው መሆኑ፣
- **የአሶሳ ዩኒቨርስቲ** ኢት ኮድ 4-20298፣ ኢት 4-20299፣ ኢት 4-19997፣ ኢት 4-18520፣ ኢት 4-20259 ፣ኢት 4-18531፣ ኢት 4-17012፣ እና ኢት 4-19998፣ መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌላቸዉ መሆኑን፣
- **መቱ ዩንቨርስቲ** የሰሌዳ ቁጥር 416993 ኢት፣ 4-16934 ኢት እና 4-19648 ኢት የተሸከርካሪዎች የባለቤትነት ማረጋገጫ መታወቂያ ደብተር ለኦዲት ስራ ሊቀርብ ስላልቻለ የተሸከርካሪዎቹ ባለቤትነት የዩንቨርስቲው ለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው መኪናዎች ከሚመለከተው አካል የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር እንዲሰጣቸው ጥረት ማደረግ ይጠበቅበታል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር እያላቸው ለኦዲት ስራ ያልቀረበ ምክኒያቱ ተገልጸ ከወዲሁ ለኦዲት ስራ እንዲያቀርብ ጥረት ማድረግ እንደሚኖርበት አሳስበናል፡፡

7.2.2 **<u>የተሽከርካሪ ፋይል የሌላቸው፣</u>**

- **የሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ** ለተሽከርካሪ መኪናዎች በየስማቸው የጥገና መጠየቂያ እና የመሳሰሉት ፋይል የተከፈተላቸው ቢሆንም፣ የተጠቀሙበት የነዳጅ ፍጆታን በየወሩ የሚያሳይ ቅጽ በፋይል የተያዘ ሳይሆን በአንድ ላይ በፖስታ ውስጥ የተቀመጠ መሆኑ ባለፈው የኦዲት ወቅት አስተያየት የተሰጠበትና አሁንም እርምጃ ሳይወሰድበት የተገኘ መሆኑ፣
- **የዓዲግራት ዩኒቨርስቲ የዩኒቨርስቲው** ተሽከርካሪዎች የህይወት ታሪክ ያልተሞላ እና በተሽከርካሪው ፋይል ውስጥ እንዲቀመጥ ያልተደረገ መሆኑ፤

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በመመሪያው መሰረት ተሽከርካሪዎች በየሥማቸው የጥገና መጠየቂ እና የነዳጅ ፍጆታ በየወሩ የሚያሳይ ቅጽ በየፋይላቸው ሊያዝ እንደሚገባ አሳስበናል።።

7.2.3 **<u>የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው የማይሰራ፣</u>**

- **በፍትህና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት** የሠሌዳ ቁጥር 4-00832 እና 4-02805 የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው የማይሰራ መሆኑ፣
- **በዓዲግራት ዩኒቨርስቲ**
  - አንድ ተሽከርካሪ በአንድ ሊትር ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደሚጓዝ የሚያሳይ የተሽከርካሪ የነዳጅ ልኬት መረጃ አለመኖሩን፣
  - 3 ተሽከርካሪዎች የኪሎ ሜትር መቆጣጠሪያ ጌጃቸው የማይሰራ ሆኖ መገኘቱን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- አንድ ተሽከርካሪ በአንድ ሊትር ምን ያህል ኪሎ ሜትር እንደሚጓዝ የሚያሳይ በባለሙያ የተደገፈ ትክክለኛ የተሽከርካሪ የነዳጅ ልኬት መረጃ እንዲኖረው ከሚመለከተው መ/ቤት ጋር በመመካከር ተግባራዊ ማድረግ እንደሚኖርበት፣

- የነዳጅ መቆጣጠሪያቸው የማይሰራ መኪኖች እንዲሰሩ መደረግ እንደሚኖርበት፣

አሳስበናል፡፡

7.2.4 <u>በብልሽት ምክንያቶች የቆሙና በወቅቱ ያልተጠገኑ ተሽከርካሪዎች፣</u>

- **በእንሰሳት መድኃኒትና መኖ አስተዳደር ቁጥጥር ባለሥልጣን** 2 ተሽከርካሪዎች በመበላሸታቸውና በወቅቱ እንዲጠገኑ ባለመደረጋቸው አገልግሎት ሳይሰጡ እንዲቆሙ መደረጉን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

ተሽከርካሪዎች በደንቡ መሠረት መያዝ ማስተዳደር እንደሚገባቸው አስገንዝበናል፡፡

8. <u>ባለፉት ዓመታት አዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ፣</u>

በኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት፡-

- የኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች ለትምህርት ወደ ተለያዩ ሀገራት ሲሄዱ ከኢንስቲትዩቱ በገቡት ውል መሰረት ወደ ሥራ ገበታቸው ተመልሰው ኢንስቲትዩቱን የመገልገል ግዴታውን ባይወጡ እያንዳንዳቸው የሚፈለግባቸውን ገንዘብ ለኢንስቲትዩቱ መክፈል እንደሚጠበቅባቸው በውሉ ቢገለፅም በድምሩ ብር 352,002.67 እና USD 151,058.65 ገቢ አለመደረጉን በኦዲት ለመረዳት ተችሏል፡
- አዲስ እና ያገለገሉ ቋሚ ዕቃዎች በአንድ ላይ እንዲቀመጡ መደረጉንና የማያገለግሉ ጠረቤዛ እና ወንበሮች ከንብረት ክፍል ውጪ በተላያዩ ቦታዎች ተቀምጠው መገኘታቸውን ተረጋግጠዋል፡
- **በፍትህና የሕግ ሥርዓት ምርምር ኢንስቲትዩት** ከሐምሌ 9/2005 ጀምሮ ሳይወራረድ የቆየ በሂሳብ መደብ 4201 ብር 1,646.60 መገኘቱ፣

በአሶሳ ዩኒቨርስቲ፡-

- የዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት ኮሚቴ በተሰጠው ውሳኔ ለ3 የግዥ አጽዳቂ ኮሚቴ አባላት ማበረታቻ ለእያንዳንዱ አባል ብር 5,000.00 በድምሩ ብር 15,000.00 አላግባብ ከፍሎ ተገኝቷል፣
- ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በስህተት በብልጫ ተከፍሎ ተመላሽ መደረግ የነበረበት ብር 17,072.14 መገኘቱ፣

- ብር 41,790.70 የዩኒቨርሲቲው የፕሮጀክት ጽ/ቤት ገንዘብ ያዥ የሚያንቀሳቀሱት የጥሬ ገንዘብ ከወጪ ቀሪ በማነስ የተገኘ መሆኑ፤
- በድምሩ ብር 1,687.47 ከተከፋይ ላይ የሚቀነስ ታክስ ከተለያዩ ክፍያዎች ላይ ተቀናሽ ያልተደረገ በመሆኑ፣

በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ፡-

- ዩኒቨርሲቲው ክፍያ ሲፈፅም ለወልቂጤ ንግድ ባንክ ለባለመብቱ በባንክ ሂሳብ እንዲተላላፍ ደብዳቤ የሚጽፍ ቢሆንም ክፍያ በባንክ መተላለፉን የሚገልጽ የባንክ አድቫይስ ማስረጃ ሙሉ በሙሉ ከክፍያ ሰነዱ ጋር የማይያያዝ መሆኑን፣
- ዩኒቨርሲቲው የተቋቋመበትን ዓላማ ለማስፈጸም ዕቅዶችና ዝርዝር የዕለት ተዕለት ተግባራት በማከናወን ሂደት የሚከሰቱ ችግሮችና የተጋላጭነት ደረጃ ለመለየት የስጋት ምንጮች ዳሰሳ በማካሄድ የስጋት አስተዳደር ፖሊሲ ማዘጋጀት ያለበት ቢሆንም ይህን በተመለከተ በዩኒቨርሲቲው የተሰራ ስራ አለመኖሩን፣

በዋቸሞ ዩኒቨርስቲ፡-

- ዩኒቨርሲቲው በማኔጅመንት ቃለ ጉባኤ ለ2006 ዓ.ም የተማሪዎች ቅበላ ዝግጅት ላይ የሰሩ በማለት ከአንድ ዓመት በኋላ ከበጀት ዓመቱ ውጭ ለእያንዳንዳቸው ብር 5000.00 ሂሳብ ለ12 መምህራኖች በድምሩ ብር 60,000.00 አላግባብ ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ፣
- የዩኒቨርሰቲው ማናጅመንት ካውንስል በስሩ ለሚገኙ ለ10 መምህራን የሃድያ ቋንቋ ስርዓተ ትምህርት የቀረጻ ስራ ስለሰሩ የማትጊያ ክፍያ በሚል ብር 100,000.00 ያለአግባብ ከፍሎ ተገኝቷል፡፡ በድምሩ ብር 160,000.00 ለማበረታቻ እና ለማትጊያ በሚል ያላግባብ ከደንብና መመሪያ ውጭ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል።
- ኮረሚ ኮንስትራክሽን ለሚገነባው ሁለት ዶርሚታሪ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ921 ቀናት ወይም ከ2 ዓመት ከ6 ወር በላይ የዘገዩ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ የግንባታ ዋጋ ብር 15,885,319.28 በመሆኑ

በማዘግየቱ ሊቀጣ የሚገባው/ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 15,885,319.28 *921*1/1000=14,630,379.06 ሲሆን ነገር ግን ቅጣቱ ከውሉ 10% መብለጥ ስለሌበት 15,885,319.28 *10% = ብር 1,588,531.93 ሊከፍል ይገባል።

- አስቴር መንግስቱ ጠ/ህ/ተቋራጭ እና ውኃ ነክ ስራዎች ለሚገነባው ኢንፍራስትራክቸር ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ730 ቀናት ወይም ከ2 ዓመት በላይ የዘገዩ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ የግንባታ ዋጋ ብር 76,662,576.76 በመሆኑ በማዘግየቱ ሊቀጣ የሚገባው /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 76,662,576.76 *730*1/1000=55,963,681.03 ሲሆን ነገር ግን ቅጣቱ ከውሉ 10% መብለጥ ስለሌበት 76,662,576.76 *10% = ብር 7,666,257.67 ሊከፍል ይገባል።
- ለሚገነባው ኢንፍራስትራክቸር ፌዝ 2 በተገባ ውል ከሰኔ 22/2005 እስከ ሰኔ 21/2006 በ365 ቀናት ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ሲሆን መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ440 ቀናት ወይም ከ1ዓመት ከ2 ወር በላይ የዘገዩ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ የግንባታ ዋጋ ብር 93,314,107.58 በመሆኑ በማዘግየቱ ሊቀጣ የሚገባው /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 93,314,107.58 *440*1/1000=41,058,203.34 ሲሆን ነገር ግን ቅጣቱ ከውሉ 10% መብለጥ ስለሌበት 93,314,107.58 *10% = ብር 9,331,410.76 ሊከፍል ይገባል።
- አስቴር መንግስቱ ጠ/ህ/ተቋራጭ እና ውኃ ነክ ስራዎች ለሚገነባው ትሪትመንት ፕላንት በተገባ ውል መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ05 ቀናት የዘገዩ ሲሆን፤የፕሮጀክቶቹ የግንባታ ዋጋ ብር 138,768,353.91 በመሆኑ በማዘግየቱ ሊቀጣ የሚገባው /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 138,768,353.91 * 05 * 1/1000 = 693,841.77 ሊከፍል ይገባል።
- ጌታቸው አባተ ጠ/ህ/ተቋራጭ ለሚገነባው ሶስት ዶርሚተሪ በተገባ ውል ከሰኔ 29/2006 እስከ ሚያዝያ 29/2007 በ240 ቀናት ይጠናቀቃል ተብሎ ውለታ የተገባ ሲሆን፤ መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ61 ቀናት የዘገዩ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ የግንባታ ዋጋ

ብር 30,557,364.10 በመሆኑ በማዘግየቱ ሊቀጣ የሚገባው /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/30,557,364.10 *61 *1/1000 = 1,863,999.20 ሊከፍል ይገባል።

- ተሰማ መለሰ ጠ/ህ/ተቋራጭ ለሚገነባው ሶስት ዶርሚተሪ በተገባ ውል መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ61 ቀናት የዘገዩ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ የግንባታ ዋጋ ብር 30,557,364.10 በመሆኑ በማዘግየቱ ሊቀጣ የሚገባው /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 30,557,364.10 * 61 * 1/1000 = 1,863,999.20 ሊከፍል ይገባል።
- ታዴዎስ ማስረሻ ጠ/ህ/ተቋራጭ ለሚገነባው አራት ሴሚናር ግንባታ በተገባ ውል መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ61 ቀናት የዘገዩ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ የግንባታ ዋጋ ብር 32,437,806.50 በመሆኑ በማዘግየቱ ሊቀጣ የሚገባው /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 32,437,806.50 * 61 * 1/1000 = 1,978,706.20 ሊከፍል ይገባል።
- አስቴር መንግስቱ ጠ/ህ/ተቋራጭ እና ውኃ ነክ ስራዎች ለሚገነባው 1 ሴንትራል ላይብረሪ፣ 1አዲዮ ማክስ፣ 2 ዳይኒግ ሆል እና 1 ኪችን ግንባታ በተገባ ውል መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ274 ቀናት የዘገዩ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ የግንባታ ዋጋ ብር 51,768,127.71 በመሆኑ በማዘግየቱ ሊቀጣ የሚገባው 51,768,127.71 *274*1/1000=14,184,466.99 ሲሆን ነገር ግን ቅጣቱ ከውሉ 10% መብለጥ ስለሌበት 51,768,127.71 *10% = ብር 5,176,812.77 ሊከፍል ይገባል።
- ጉጄ ጉሌ ጠ/ህ/ተቋራጭ ለሚገነባው ሁለት ዶርሚተሪ ግንባታ በተገባ ውል መጠናቀቅ ከነበረባቸው የውለታ ጊዜ ከ298 ቀናት የዘገዩ ሲሆን የፕሮጀክቶቹ የግንባታ ዋጋ ብር 24,694,259.19 በመሆኑ በማዘግየቱ ሊቀጣ የሚገባው /ሊኩዴሽን ዳሜጅ/ 24,694,259.19 * 298 * 1/1000 = 7,358,889.24 ሲሆን ነገር ግን ቅጣቱ ከውሉ 10% መብለጥ ስለሌበት 24,694,259.19 *10% = ብር 2,469,425.92 ሊከፍል ይገባል።

በቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ፡-

- ከተከታታይ እና የርቀት ትምህርት ፕሮግራም በሥራ አመራር ውሳኔ ከፕሬዝዳንቱ ጀምሮ በየደረጃው ላሉት የዩኒቨርስቲው ኃላፊዎች በየወሩ የማስተባበሪያ አበል በሚል ከብር 500 እስከ 450 እንዲከፈል የተወሰነ ሲሆን፣ በሐምሌ/06 ብር 5,950.00፣ ከደንብና መመሪያ ውጭ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- የቡሌ ሆራ ዩኒቨርሲቲ ለግንባታ ሥራ ተቋራጮች በገቡት ውል መሠረት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ አጠናቀው ባለማስረከባቸው ግንባታዎችን ላጓተቱበት የጉዳት ካሳ /liquidation Damage/ ብር 32,565,719.50 መሰብሰብ ያለበት የቅጣት ሂሳብ ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ፡-

- ዩኒቨርሲቲው ብር 27,355,417.24 የተሰብሳቢ ሂሳቦች ላለፉት ሁለት ዓመታት የአዲት አስተያየት የተሰጠባቸው ሲሆን እስካሁን እልባት ያለገኙ መሆኑ፡፡
- ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ አቅራቢዎች ጋር የውል ስምምነት በማድረግ የዕቃዎች ግዥ የፈጸመ ሲሆን ንብረቶቹ በውሉ መሰረት ለዩኒቨርስቲው በወቅቱ ገቢ ባለመደረጋቸው ለዘገዩበት በመመሪያው መሰረት አቅራቢዎች ሊከፍሉ የሚገባቸው የጉዳት ካሳ በድምሩ ብር 1,081,913.24 ገቢ አለመደረጉ፤
- ግንባታዎች የስራ ደረጃና የሰነድ ርክክብ ሲደረግ ፡-

✓ ለእያንዳንዱ ሥራ ተቋራጭ በቅድሚ የተከፈለ ጥሬ ገንዘብ፤ ከተቋራጩ ተመላሽ የተደረገውና በተሰብሳቢ ተይዘው የሚገኘው ቅድሚ ክፍያ የማጣራት ስራ አለመሰራቱ፡፡

- ✓ ለእያንዳንዱ ሥራ ተቋራጭ የተሰጡ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ዓይነት፣ ብዛትና ዋጋ በተመለከተ የማጣራት ስራ አለመሰራቱ፣

- **የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት** ከሐምሌ 2006 እስከ ሰኔ 2007 ዓ.ም ለቀጥታ ስልክ በውስጥ መመሪያ ከተቀመጠላቸው ተመን በላይ በድምሩ ብር 12,927.78 ተከፍሎ ለተገኘው ከሚመለከታቸው ሠራተኞች ደመወዝ ላይ ብር 7,630.08 ተቀናሽ ተደርጎ ገቢ የተደረገ ሲሆን፣ ቀሪው ብር 5,297.70 ተመላሽ አለመደረጉ ተረጋግጧል፡፡
- **የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር** የ2007 የኦዲት ሪፖርት ግኝት ላይ ሠራተኞች ያልሰሩበት የደመወዝ ሂሳብ ብር 12,225.60 በብልጫ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ ሳይደረግ የተገኘ መሆኑ፣
- **የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወትኢንስቲትዩት** የ2006 እና የ2007 በጀት ዓመት አዲት ግኝቶች እርምጃ ሳይወሰድባቸው የተገኙ መሆኑ፣

መቱ ዩኒቨርስቲ፡-

- ▪ ብር826,511.00 ኮንትራክተሮች የገንዘብ እጥረት ስላጋጠማቸው በሚል ብድር ተሰጥቶ መገኘቱ እና ለመውሰዳቸው ከድርጅቶቹ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ፣
- ብር 3,568,559,99 መቀነስ ከሚገባው የሲሚንቶ ዋጋ በታች በመቀነሱ ከኮንትራክተሮች በዕዳ የሚፈለግ ሲሆን፣ ብር 962,557.36 ደግሞ ከኮንትራክተሮች ላይ መቀነስ የሚገባው የሲሚንቶ ዕዳ ሳይቀነስ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
    - ብር 23,210.00 የግንባታ ሥራ የሚያከናውኑ ኮንትራክተሮች አፈር በመድፋታቸው እና አፈሩን ለማስነሳት በሚል ተከፍሎ መገኘቱ፣

- ብር 968,150.35 ንብረቱ ወጪ የሆነበት ሞዴል 22 ማስረጃው ከሰነድ ጋር ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣

ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት፣

- በ2007 በጀት ዓመት ብር 70,332,928.12 እና በ2008 በጀት ዓመትም ብር 71,128,769.99 በሂሳብ ማመሣከሻ /Trial Balance/ በሂሳብ መደብ 4104 መገኘቱንና ዝርዝር ማስረጃ አለመቅረቡን፣
- ለስልክ አገልግሎት ክፍያ ከተፈቀደው ተመን በላይ ብር 2,554.58 ተከፍሎ በመገኘቱ ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ቢሰጥም ገቢ አለመደረጉን፣

በዓዲግራት ዩኒቨርስቲ፡-

- አቅራቢዎች ዕቃዎችን በወቅቱ ገቢ ባለማድረጋቸው ላዘገዩበት ለዩኒቨርሲቲው ገቢ ማድረግ የሚገባቸው በድምሩ ብር 1,480,454.64 የጉዳት ካሣ ለዩኒቨርስቲው ገቢ አለመደረጉን በተመለከተ ከድርጅቶቹ ገቢ ተደርጎ ሪፖርት እንዲቀርብ አስተያየት ቢሰጥም ዩኒቨርሲቲው እርምጃ ባለመውሰዱ ገንዘቡ ገቢ አለመደረጉን፣
- ከ2006 ለ2007 በጀት ዓመት ከዞረ የውስጥ ገቢ ተከፋይ ሂሳብ ውስጥ፣ በሂሳብ መደብ 5055 ብር 20,800.00፤ እንዲሁም በሂሳብ መደብ 5051 ብር 19,932.30 በድምሩ ብር 40,732.30 ከ2006 በጀት ዓመት ለ2007 በጀት ዓመት የዞረ ተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር የሌለው እና በ2007 በጀት ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ያልታየበት መሆኑን፣
- በመክፈቻ ሂሳብ /Opening balance/ ላይ በሂሳብ መደብ 5028 የሚታይ ብር 142,567.25 ተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር የሌለው እና በ2007 በጀት ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ ያልታየበት መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው ለሚያስገነባው የተማሪዎች መመገቢያ ህንፃ ከመኮንን ገ/ኪዳን የህንፃ ሥራ ተቋራጭ ጋር በገባው ውል

መሠረት ግንባታው በወቅቱ ባለመጠናቀቁ ላዘገየበት ብር 112,586.76 የጉዳት ካሳ ገቢ አለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት የተገለፀ ቢሆንም የሥራ አመራሩ ገንዘቡ ገቢ እንዲደረግ ተገቢውን እርምጃ አለመውሰዱን፣

- ዩኒቨርሲቲውን ለለቀቁ 12 ሠራተኞች በድምሩ ብር 13,038.60 ላልሰሩባቸው ወራት እና ቀናት አለአግባብ ደመወዝ መከፈሉንና ከሠራተኞቹ ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ተመላሽ አለመደረጉን በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

በአዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ፡--

- የዩኒቨርሲቲው የፑል ማጫወቻ የሁለት ወራት ኪራይ በድምሩ ብር 34,734.00 ገቢ አለመደረጉን፣
- ትምህርታቸውን ያቋረጡ ወይም ያራዘሙ መምህራን ማስረጃ ሳያቀርቡ አለአግባብ የተከፈላቸው በድምሩ ብር 727,526.00 ተመላሽ አለመደረጉን፣

የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኢንስቲትዩት አቅራቢዎች በገቡት ውል መሰረት እቃዎችን ባለማቅረባቸው መክፈል የሚገባቸው የጉዳት ካሣ ብር 275,366.51 ገቢ አለመደረጉ፣

ወልዲያ ዩኒቨርሲቲ፡-

- ከመደበኛ አበል በተጨማሪ ከዉስጥ ገቢ ለአልጋ እየተደጎመ እንዲከፈል በመደረጉ በድምሩ ብር 81,000.00 ከመመሪያ ውጪ አለአግባብ ተከፍሎ መገኘቱን፣
- በማታ ትምህርት መርሃ ግብር ለተሳተፉ የአስተዳደር ሰራተኞች የሚመለከተው አካል ሳይፈቅድ ከመመሪያ ውጭ ብር 37,410.00 የትርፍ ሰዓት ተከፍሎ መገኘቱን፣
- በቋሚ እና በአላቂ ዕቃ ንብረት ክፍል ውስጥ ሞዴል 19 እና ሞዴል 22 የመሥራት እንዲሁም ንብረት የመያዝ ሥራ በአንድ ሰው የሚከናወን መሆኑ፣

- በተማሪዎች የምግብ ቤት ውስጥ የተለያዩ የምግብ ቤት ዕቃዎች፣ ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑን፣
- ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ አገልግሎት ላይ ያልዋለ የዳቦ መጋገሪያ ማሽን አገልግሎት ሳይሰጥ እንዲቀመጥ መደረጉን፣

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱ ዩኒቨርሲቲዎችና ሌሎች መ/ቤቶች የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እንዲቀረፉ ብሎም ግልጸኝነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን የተቋማቱ ሥራ አመራር በአዲት በሚሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሠረት የእርምት እርምጃ በመውሰድ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

9 **<u>ልዩ ልዩ፣</u>**

- **የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የሥልጠና ማዕከል** ማዕከሉ፣ ለ12 ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች የመኖሪያ ቤት በነጻ የሰጣቸው ሲሆን፣ ለሠራተኞቹ የመኖሪያ ቤት እንዲሰጣቸው ከሚመለከተው አካል የተፈቀደበት ለአዲት እንዲቀርብ ተጠይቆ ያልቀረበ እና ሠራተኞቹ የሚጠቀሙት የመብራት እና የውሀ ፍጆታ ቤቱን ከተረከቡት ጊዜ ጀምሮ ከመ/ቤቱ በጀት የሚሸፈን መሆኑን ተረጋግጧል፡፡

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ፡-

- 2008 በጀት ዓመት ከውስጥ ገቢ ለመሰብሰብ የታቀደው የገንዘብ መጠን ወይም የገቢ መሰረተ ግምት፣ የሚሰጠው አገልግሎት ዓይነትና አገልግሎቱን በመስጠት ሊገኝ የሚችለው የገንዘብ መጠን በዝርዝር የሚገልጽ የገቢ ዕቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑን፣ የገቢ እቅድ ከክንውን ጋር በማነጻጸር ለመገምገም እንዲሁም የተሰበሰበው ገንዘብ መሰብሰብ በሚገባው መጠን የተሰበሰበ መሆኑን ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፣
- እስከ 2008 በጀት ዓመት መጨረሻ በዩኒቨርሲቲው ለትምህርት ሄደው በውለ መሰረት ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ወደስራ ያልተመለሱ 3 መምህራን መኖራቸውና ዩኒቨርሲቲው በውለ መሰረት እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ፣

የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል በልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች በተፈቀደው መዋቅር መሰረት የሚያስፈልገው የሰው ኃይል ብዛት 278 ሲሆን በአሁኑ ወቅት በሥራ ላይ ያለው የሰለጠነ የሰው ኃይል ብዛት 109 መሆኑ ታውቋል፤በመሆኑም በቀሪው 169 (61%) ክፍት የሥራ መደቦች ላይ ሠራተኛ ያልተቀጠረ መሆኑ፣

የቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ኢንሰቲትዩቱ ከተፈቀደለት 184 የሥራ መደቦች ውስጥ በሰው ኃይል የተሞላው 144 ሲሆን፣ 40(21%) የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው፣

የብረታ ብረት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት 107 (42%) ክፍት የሥራ መደቦች ላይ ሠራተኛ ያልተቀጠረ መሆኑ፣

የምግብ መጠጥና ፋርማሲዩቲካል ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት 473 (80.85%) ክፍት የሥራ መደቦች ላይ ሠራተኛ ያልተቀጠረ መሆኑ፣

የፍትህ አካላት ባለሙያዎች የሥልጠና ማዕከል መሥሪያ ቤቱ በመዋቅር ከተፈቀደለት 231 ውስጥ 80 የሰራ መደቦች በሰው ኃይል የተያዙና ቀሪው 151 (65%) የሥራ መደቦች ሠራተኞች ያልተቀጠሩባቸው (ክፍት) ሆነው መገኘታቸው፣

የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴ፡-

- በድምሩ ብር 939,139.99 የቀረበው የወጪ ማስረጃ ለየትኛው የስልክ አገልግሎት እንደተከፈለ ሳይገለጽ በጥቅል ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም በየወሩ ለ4GB የኢቲዮ ቴልኮም የክፍያ ታሪፍ ምን ያህል እንደሆነ የሚገልጽ ማስረጃ ያልተያያዘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- በድምሩ ብር 7,074,728.79 ከገደብ በላይ ተፈርሞ ክፍያው የተፈፀመ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- ሐምሌ/2007፣ ህዳር፣ ታህሳስ፣ ግንቦት እና ሰኔ/2008 ለሚኒስቴሩ ሰራተኞች ለፋይናንስም ይሁን ለሰው ሀብት አስተዳደር ከሚመለከተው የስራ ክፍል በሥራ ላይ መገኘታቸውን የሚያረጋግጥ(Duty report) ሳይቀርብ ብር 3,867,188.16 ተከፈሎ የተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- ሚኒስቴሩ ከተፈቀደለት 360 የስራ መደቦች ውስጥ በሰው ኃይል የተሞላው 285 ሲሆን፣ 75 (20.83%) የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው፣

የኢትዮጵያ ምርት ገበያ ባለሥልጣን፡-

- ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ የሚጠቀምባቸው የመደበኛ ስልክ ቁጥር ዝርዝር የሚገለጽበት የአገልግሎት መጠየቂያ ደረሰኝ ሳይቀርብ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ብቻ በማቅረብ ብር 551,108.51 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡
- ባለስልጣን መ/ቤቱ ለሕግ ባለሙያ ሰራተኞች በተለያየ የሕግ ጉዳዮች ላይ ለማሰልጠን ለፍትህ አካላት ባለሙያ የስልጠና ማዕከል ለ14 ሠልጣኞች ከህዳር 17/2008 እስከ ህዳር 25/2008 ዓ.ም ድረስ ለ8 ቀናት ብር 20,475.00 ለስልጠና መስተንግዶ ለተከፈለው ሂሳብ መስተንግዶውና ስልጠናው በትክክል ለመሰጠቱ የሰዓት ፊርማ (አቴንዳንስ) በማስረጃነት ያልቀረበ እና በሚመለከታቸው ኃላፊዎች ያልተረጋገጠ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- ባለሥልጣን መ/ቤቱ በኃላፊነቱ ሥር ያሉትን ተሽከርካሪዎች ብዛት፣ ዓይነት፣ የሚገኙበትን ሁኔታና የመሳሰሉትን መረጃዎች በማጠናከር የበጀት ዓመቱ እንደተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ሪፖርት ያላቀረበ መሆኑ፣
- የቀጥታ ስልክ መስመር ለቁጥጥር እንዲያመች በየሥራ ክፍሉ የሚጠቀሙበት የስልክ ሂሳብ ልክ (ተመን) ያልወጣለት መሆኑ፣
- ባለስልጣኑ ከተፈቀደለት 161 የሥራ መደቦች ውስጥ በሰው ኃይል የተሞላው 124 በመሆኑ 37(22.98%) የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው፣
- የስልጣን ውክልና ገደብ በጽሁፍ ሳይሰጥ በግዥና ፋይናንስ ንብረት የሥራ ሂደት ዳይሬክተር እና በከፍተኛ የሂሳብ ሠራተኛ (አካውንታንት) ወጪ እየተፈቀደ መሆኑ፣

የሀገር አቀፍ የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች ኤጀንሲ፡-

- ኤጀንሲው ለሥራ አገልግሎት የሚውል የቀጥታ ስልክ መሰመር በየሥራ ክፍሉ ለቁጥጥር እንዲያመች የሚጠቀሙበት የስልክ መጠን (ተመን) ያልወጣለት መሆኑ፣

- አንዳንድ የአላቂ ዕቃዎች በዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ከወጪ ቀሪ እያላቸው ተደጋጋሚ ግዥ መፈጸሙ ይህም በ2008 በጀት ዓመት አዲት ወቅት የተጠየቀውን በሙሉ መግዛት እንጂ በ2007 አዲት አስተያየት የተሰጠበት ንብረት ክፍል ያለውን ዕቃ በማቀናነስ የተሰራ አለመሆኑ፣

የመቱ ዩኒቨርስቲ፡-

- ለጥቃቅን ወጪዎች መሸፈኛ የሚከፈለው ወጪ እስከ ብር 2000,00 ብቻ መሆን እንዳለበት በመመሪያ የተፈቀደ ቢሆንም በተለያዩ የወጪ ቫውቸሮች በድምሩ ብር 11,959.00 ከመ/ቤቱ ካዝና ወጪ ሆኖ የተከፈለ መሆኑ፣
- ዩኒቨርሲቲው ገዝቶ ለስራ ተቋራጮች የሚያቀርበው የሲሚንቶ እና የብረት አቅርቦቶች /Material Delivered / ዋጋ መጠን በየክፍያ ሰርተፊኬቱ ቢቀነስም በእያንዳንዱ ስራ ተቋራጭ ስም ሌጀር ተከፍቶለት ምን ያህል ወጪ አድርጎ እንደወሰደ እና ምን ያህል ከወሰደ ዉስጥ እንደተቀነሰ የሚያሳይ ምዘገባ የማይከናወን በመሆኑ ስራ ተቋራጩ በዕቃ ወጪ ማድረጊያ ሞ/22 ወጪ ያደረገው ግን በክፍያ ሰርተፊኬት ላይ ያልተቀነሰውን መጠን በቀላሉ ማግኘት ያልተቻለ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡
- ለትምህርት ሄደው በቀነ ገደብ ያልተመለሱ 3 መምህራን መኖራቸውና ዩኒቨርሲቲው እርምጃ ያልወሰደ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

- **የኢትዮጵያ ካይዘን ኢንስቲትዩት** ኢንስቲትዩቱ ከተፈቀደለት የትምህርት ዘርፍ የሥራ መደቦች 219 ውስጥ በሰው ኃይል የተሞላው የሥራ መደብ 120 ሲሆን፣ ክፍት የሥራ መደቦቹ 99 (45%) ሆነው መገኘታቸው፣
- **የኢትዮጵያ ብዝሀ ህይወት ኢንስቲትዩት፡-**
  - ጥቅምት፣ ታህሳስ፣ የካቲት፣ ሚያዚያ እና ሰኔ/2008 ለኢንስቲትዩቱ ሠራተኞች የወር ደመወዝ ክፍያ ሲፈፀም ለሰው ሀብት አስተዳደር ከሚመለከተው የስራ ክፍል ሠራተኞች በሥራ ላይ መገኘታቸውን የሚያረጋግጥ (Duty report) ሳይቀርብ ብር 14,677,321.13 ተከፍሎ የተገኘ መሆኑ፣

- ብር 5,736,407.47 በጀት ስለመኖሩ በበጀት ኃላፊ ያልተፈረመ መሆኑ፣
- የደመወዝ መክፈያ (Payroll) እና የደመወዝ ማጠቃለያ (Payroll) ላይ ያዘጋጀው፣ያረጋገጠውና ያፀደቀው የሚለዉ የማይዘጋጅና የማይፈርም እንዲሁም የአበል ክፍያ በጥቅል መሆኑ፣
- ለ47 ሠራተኞች በአሻም አፍሪክ ሆቴል ለተደረገላቸው መስተንግዶ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን የሰለጠኑት ሠራተኞች የስም ዝርዝር እና የሰዓት ፊርማ ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፣
- ኃላፊዎች በወጪ ላይ ለሚፈርሙበት የፊርማ ገደብ ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑና በተጨማሪም የበጀትና ፕላን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በወጪ ሂሳብ ላይ እየፈረሙ ይገኛሉ በመሆኑም የውክልና ደብዳቤ ተጠይቆ ለኦዲት ሊቀርብ ያልቻለ መሆኑ፣
- የወጪ ደረሰኞች እና Transaction Register(TR) አመዘጋገብ ላይ የብር 11,620.00 መጠን ልዩነት የታዬ መሆኑ፣
- ኢኒስቲትዩቱ ከተፈቀደለት 772 የስራ መደቦች ውስጥ በሰው ኃይል የተሞላው 552 ሲሆን 220(28.50%) የሥራ መደቦች ክፍት መሆናቸው፤

የእካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር፡-

- ሚ/ር መ/ቤቱ በጠቅላላ የተፈቀደለት 511 ሠራተኞች ሲሆኑ በአሁኑ ወቅት 211 ሠራተኞች ብቻ የሚገኙ በመሆኑ 300 (58.7%) ክፍት የስራ መደብ መኖሩ፡
- መ/ቤቱ በውክልና ሰራተኞችን አዛውሮ የሚያሰራ ቢሆንም ዕቅድና በጀት ዝግጅት ክትትልና ግምገማ ዳሬክቶሬት፣ ፋይናንስ ግዥ ዳሬክቶሬት ፣የግዥ ቡድን ፣ንብረት አስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ዋና የስራ ክፍሎች ውክልና እንኳን ሳይሰጥባቸው ክፍት ሆነው መገኘታቸው፤

<u>የማሻሻያ ሀሳብ፣</u>

- ለሥራ አገልግሎት የሚውል የቀጥታ ስልክ መሰመር በየክፍሉ የሚጠቀሙበትን የስልክ ክፍያ መጠን (ተመን) በማውጣት ከተፈቀደላቸው በላይ ሲሆን ከሚመለከተው ሰራተኛ ተመላሽ የሚያደረግበትን የቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት እንደሚኖርበት፣
- የስጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ በየጊዜው ቢደርግ በውስጥ ቁጥጥር ስርዓት

ድክመት የተነሳ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች ለይቶ ቅድመ ጥንቃቄ ለመወሰድ የሚኖረውን ጥቅም ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የሥጋት ተጋላጭነት ዳሰሳ እንዲደረግ የበኩሉን አሰተዋጽኦ ማድረግ እንደሚጠበቅ፣

- በመመሪያው መሠረት ተቋሞች የተሰጣቸውን ኃላፊነት በአግባቡ ለመወጣት ያስችላቸው ዘንድ ክፍት የሥራ መደቦችን በቅጥርና በእድገት እንዲያሟሉ ማድረግ እንደሚኖርባቸው፣
- ሠራተኞች ተከታታይ የስራ አፈፃፀም ምዘና በማካሄድ የሰራተኞችን ጠንካራና ደካማ ጎኖች በመለየት ቀጣዩ የስራ አፈፃፀማቸው እንዲሻሻል በማድረግ ውጤታማ እንዲሆኑ ማድረግ እንደሚኖርበት፣
- መምህራን ከሥልጠና ተመልሰው አገልግሎት እንዲሰጡና አገልግሎት ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ ተቋሙ ያወጣውን ወጪ እንዲመልሱ ማድረግ እንደሚኖርበት፣
- የፌደራል መንግሥት ሠራተኞች የፌደራል መንግሥት ሠራተኞች የዋስትና አሰጣጥ ሥርዓት መመሪያ መሰረት ዋስትና የሚያስፈልጋቸው ሠራተኞች ዋስትና ወይም ተያዥ ሊያቀርቡ እንደሚገባ፣
- ሌሎች ግድፈቶችም ደንብና መመሪያን በጠበቀ መልኩ የእርምት እርምጃ መወሰድ እንደሚገባ፣

አሳስበናል፡፡

10. <u>ልዩ አዲት፣</u>

1. በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ትእዛዝ መሠረት **የተገጣጣሚ ሕንፃ አካላት ማምረቻ ድርጅት** ከ2001 እስከ 2003 በጀት ዓመት የንብረት ሂሳብ ልዩ ኦዲት ተደርጎ ለጠያቂው ፍርድ ቤት ሪፖርቱ ተልኳል፡፡
2. በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ትእዛዝ መሠረት **በፌዴራል ትራንስፖርት ሚኒስቴር የትራንስፖርት ባለሥልጣን የዕለት ገንዘብ ሰብሳቢ** የነበሩት ከግንቦት/2006 ዓ.ም. እስከ ህዳር/2007 ዓ.ም. ድረስ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ ለጠያቂው ፍርድ ቤት ሪፖርቱ ተልኳል፡፡
3. የብሔራዊ የትግራይ ክልላዊ ምክር ቤት አፈ ጉባዔ በቀረበ ጥያቄ **የክልሉን ዋና ኦዲተር ጽ/ቤት** የ2008 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ተደርጎ ሪፖርቱ ተልኳል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት ዳይሬክቶሬት
የ2008 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ
መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት

መንግሥት ባወጣቸው የፋይናንስ ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያዎችና ሥርዓቶች መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም የመንግሥት ንብረቶች በሚገባ መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2008 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ 23 ዩኒቨርስቲዎችና 3 መ/ቤቶች በዕቅድ መያዙ ይታወቃል፡፡

በዕቅድ የተያዙት መሥሪያ ቤቶች በሙሉ የኦዲት ሥራቸው ተጠናቋል ፡፡

ኦዲት ለተደረጉ መሥሪያ ቤቶች በሙሉ የመውጫ ስብሰባ ተደርጎ ረቂቅ የሥራ አመራር ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን፣ መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሣብ መሠረት የወሰዱትን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው መሥሪያ ቤቶቹ የሰጡትን ምላሾች መሰረት በማድረግ የኦዲት አስተያየቱን የያዘ የኦዲት ሪፖርት እና የመጨረሻው የሥራ አመራር ሪፖርት እንዲላክላቸው ተደርጓል፡፡

1. የኦዲት ዳይሬክቶሬቱ ዕቅድና ክንውን

1.1. ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ለማድረግ በዕቅድ የያዛቸውን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ 23 ዩኒቨርስቲዎችና 3 መሥሪያ ቤቶች የኦዲት ሥራ አጠናቋል፡፡ ይህም የዕቅዱን 100% የሸፈነ ነው፡፡

1.2. በኦዲት ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶችን ዝርዝር፣ በ2008 በጀት ዓመት የተፈቀደላቸውን የመደበኛና የካፒታል በጀት እና የበጀት ዓመቱን ሂሳብ የዘጉበትን ጊዜ የሚያሳይ ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

በአዲቱ የተሸፈነው በጀትና የሂሳብ ሪፖርት የቀረበበት ቀን

ተ.ቁ	አዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	የሂሳብ ሪፖርት ለአዲት የቀረበበት	በአዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	ትምህርት ሚኒስቴር	03/05/09	837,946,231.28	1,857,607.568.77	2,695,553,800.05
2	አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ		1,266,379,888.36	1,196,780,568.38	2,463,160,456.74
3	መቀሌ ዩኒቨርሲቲ	08/03/09	903,036,291.70	1,097,690.074.35	2,000,726,366.05
4	ጅማ ዩኒቨርሲቲ	30/01/09	948,711,500.00	1,028,851,160.15	1,977,562,660.15
5	ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ	17/02/09	813,008,882.00	1,003,383,741.51	1,816,392,623.00
6	ጎንደር ዩኒቨርሲቲ	30/01/09	875,831,849.01	746,048,073.09	1,621,879,922.00
7	ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ	19/03/09	768,307,122.46	757,900,000.00	1,526,207,122.46
8	ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ	15/04/09	646,840,099.19	802,220,980.89	1,449,061,080.08
9	አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	05/02/09	524,305,047.89	710,809,700.00	1,235,114,747.89
10	ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ	13/01/09	332,110,110.50	573,798,526.40	907,908,636.90
11	አምቦ ዩኒቨርሲቲ	01/02/09	443,886,895.00	444,999,910.97	888,886,005.00
12	ዲላ ዩኒቨርሲቲ	20/03/09	430,414,421.91	450,504,850.00	880,919,271.91
13	ወላይታ ዩኒቨርሲቲ	18/01/09	351,601,619.00	476,529,339.28	828,130,958.29
14	ወልጋ ዩኒቨርሲቲ	13/03/09	352,352,215.50	438,452,550.00	790,804,765.50
15	አክሱም ዩኒቨርሲቲ	2/2/09	342,406,370.00	344,500,000.00	686,906,370.00
16	ወሎ ዩኒቨርሲቲ	30/10/08	413,863,876.66	242,241,331.86	656,105,208.52
17	ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ	20/01/09	313,862,090.26	318,292,255.15	632,154,345.41
18	ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ	06/01/09	319,797,689.50	311,500,000.00	631,297,689.50
19	ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	15/02/09	293,954,700.00	267,000,000.00	560,954,700.00
20	ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ	15/02/09	268,989,450.58	256,122,305.98	525,111,756.56
21	ሠመራ ዩኒቨርሲቲ	15/02/09	246,888,047.76	272,445,949.38	519,333,997.14
22	መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ	20/12/08	252,052,429.78	253,849,722.98	505,902,152.76
23	አርሲ ዩኒቨርሲቲ	20/01/09	289,589,747.02	55,864,132.80	345,453,879.82
24	ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ	16/01/09	64,658,907.21	250,000,000	314,658,907.21

ተ.ቁ	አዲት የተደረገው መ/ቤት ስም	የሂሳብ ሪፖርት ለአዲት የቀረበበት	በአዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
25	የፖ/ሊሲ ጥ/ና ምርምር ማዕ	20/02/09	46,369,943.76	-	46,369,943.76
26	የከፍተኛ ትም/ ጥራትና አግባብነት ኤጀንሲ	25/12/08	13,972,174.68	----	13,972,174.68
	ድምር		12,361,137,601.01	11,202,095,098.82	26,520,529,541.38

1.3 የተሰጠው የአዲት አስተያየት

በዳይሬክቶሬቱ አዲት ለተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የአዲት ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን፣ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው አጥጋቢ ባለመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ የአዲት አስተያየት የተሰጣቸው 21 መ/ቤቶች፣ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሆኖ በመገኘቱ ነቀፌታ ያለበት የአዲት አስተያየት ለ5 መ/ቤቶች ናቸው።/ ዝርዝሩ በአባሪ-2 ተመልክቷል።

ዋና ዋና የአዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች

በዳይሬክቶሬቱ የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው አዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የአዲ ግኝቶትችና የማሻሻያ ሐሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል፡

1. **የሳጥን እና የመክፈቻ ሂሳብ፣**

1.1.1 **ግኝት፣**

የአዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ ከባለፈው በጀት ዓመት የዞረ ማለትም ቋሚ ሂሳቦች እንደ የባንክ እና ጥሬ ገንዘብ ሂሳብ፣ የተሰብሳቢ ሂሳብ፣ የተከፋይ ሂሳብ፣ የተጣራ ሃብት እና የመሳሰሉት በ2008 በጀት ዓመት መክፈቻ ሂሳብ እንደመነሻ ሂሳብ ተደርጎ ዩኒቨርሲቲው ለመጠቀሙ እና የሂሳብ ምዝገባው ላይ ለማካተቱ አዲት ሲደረግ፡

የ2006 በጀት ዓመት የመጨረሻ ሂሳብ ወደ 2007 በጀት ዓመት የመክፈቻ ሂሳብ አዲት ያልተደረገ በመሆኑ የ2007 በጀት ዓመት የመጨረሻ ሂሳብ ወደ 2008 በጀት ዓመት መክፍቻ ሂሳብ ተብሎ የዞረው ሂሳብ ትክክለኝነቱን ለማረጋገጥ አልተቻለም።

1.1.2 የማሻሻያ ሃሳብ፣

ለ2006 በጀት ዓመት የመጨረሻ ሂሳብ ወደ 2007 በጀት ዓመት እንደ መነሻ ሂሳብ ተጠቅሞ እና የሂሳብ ምዝገባ ተድርጎ ባለመነሳቱ የሂሳብ ሪፖርቱ ትክክለኛ ገፅታውን እንዳያሳይ የሚያደርግ በመሆኑ ሂሳቡን በሚገባ መዝግቦ ከሚመለከተው መ/ቤት ጋር በመነጋገር የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

1.2 የጥሬ ገንዘብና ባንክ ሂሣብ፤

1.2.1 ግኝት፣

የአዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቱ በተለያየ ጊዜ የተለያየ ገቢዎች ሲሰበስብ በአዲት ናሙና በተመረጡት ብቻ በአማካኝ ከ5 ቀን እስከ 10 ቀን ድረስ አዘግይቶ ብር 2,507,645.24 ወደ ባንክ የገባ መሆኑ በአዲቱ ተረጋግጧል፡፡

1.2.2 የማሻሻያ ሃሳብ፣

በኢንስቲትዩቱ በየዕለቱ የሚሰበሰብ ገቢ በተሰበሰበበት ቀን ወደ ባንክ ገቢ የሚደረግበትን አሰራር ሊዘረጋ ይገባል ማኔጅመንቱም ጥብቅ የሆነ ክትትል ማድረግ አለበት፡፡

1.3.1 ግኝት

1. ብር 50,000.00 በላይ ለሆኑ ግዢዎች በባንክ ማስተላለፍ የክፍያ ዘዴ ወይም በተከፋዩ ድርጅት ስም በተዘጋጀ ቼክ ለዕቃ አቅራቢዎች እና አገልግሎት ሰጪዎች ክፍያ መፈፀም ሲገባው፤
    - በመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ ብር 1,518,122.88
    - በአርሲ ዩኒቨርሲቲ ብር 10,093,038.14
    - በሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ብር 4,076,786.01 በድምር ብር 15,687,947.03

   በቀጥታ በባለመብቱ የባንክ ሂሳብ ገቢ ማደረግ ወይም በቼክ መክፈል ሲገባ ከመመሪያ ውጪ በጥሬ ገንዘብ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በገንዘብ ያገሮች እጅ ተገኝቶ የተቆጠረው ጥሬ ገንዘብና በሂሣብ ሚዛን ሪፖርት የተደረገው ሲነጻጸር፣በቆጠራ የተገኘው በአራት ዩኒቨርስቲዎች

ብር 3,273,667.18 በማነስ ሲታይ በሁለት ዩኒቨርስቲዎች ብር 2,445,827.16 በቆጠራ የተገኘው በመብለጥ እንዲሁም በአንድ ዩኒቨርስቲ ከ2007 በጀት ዓመት የዞረ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 123,599.27 የኦዲቱ ሥራ እስከተጠናቀቀበት (27/5/2009) ጊዜ ድረስ ያልተተካ መሆኑ ታውቋል፡፡

/ዝርዝሩም በአባሪ- 3/2 ቀርቧል፡፡/

2. **<u>ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ</u>፤**

በሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 3 አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 2 ካዝና ውስጥ መገኘት ያለበት የጥሬ ገንዘብ መጠን በልዩ ሁኔታ ካልተፈቀደ በስተቀር ከብር 100,000.00 መብለጥ እንደሌለበት የተመለከተ ቢሆንም በሐምሌ 1/2008 በውስጥ ኦዲት የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ወቅት ብር 455,878.41 በገንዘብ ያገኖች እጅ ተገኝቷል፡፡

3. **<u>አምቦ ዩኒቨርስቲ</u>**

- ዩኒቨርሲቲው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሳያስፈቅድ በተማሪዎች ህብረት ስም በተከፈተ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አምቦ ቅርጫፍ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000015171786 ከቤቶች ክራይ፣ ከጀበና ቡና አገልግሎት እና ከፑልና ጆቴኒ አገልግሎት የሚያገኛቸውን ገቢ በራሱ በተከፈተ የሂሳብ ቁጥር ገቢ የሚያደርግ መሆኑ፤
- የአምቦ ዩኒቨርሲቲ የመዝናኛ ክበብ የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ እና የገንዘብ ወጪ ማዘዣ በጅማ ዩኒቨርሲቲ አምቦ ኮሌጅ የተማሪዎች መዝናኛ ክበብ ስም በታተመው የክፍያ ቫውቸሮች እየሰራ መሆኑ፤

1.3.2 ማሻሻያ ሀሳብ፤

- ለወደፊቱ በሂሳብ መዝጊያና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት የሂሳብ ሌጀሮች ተገቢውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው ሳይረጋገጥ ሪፖርት እንዳይቀርብ የተገለጹት ልዩነቶችም ተጣርተው ተገቢውን እርምጃ እንዲወሰድ
- ክፍያዎች በፋይናንስ ደንብና መመሪያው መሠረት እንዲፈጸሙ ማድረግ ይገባል፡፡
- የጥሬ ገንዘብ ቆጠራ በሚደረግበት ወቅት በገንዘብ ያገኖች እጅ በቆጠራ የተገኘው የጥሬ ገንዘብና ሰነድ ሂሳብ ከጥሬ ገንዘብ የሌጀር ሚዛን ጋር እንዲመሳከር አሳስበናል፡፡

2 ተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1 በደንቡ መሰረት ያልተሰበሰበ ወይም ያልተወራረደ ሂሳብ፤

2.1.1 ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ እንዲሁም በመመሪያው ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁንና በሃያ ስድስት መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው ብር 1,084,093,170.38 ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ መኖሩ የታወቀ ሲሆን፣

/ዝርዝሩ በአባሪ- 6 ቀርቧል፡፡/

ከላይ ከተገለጸው ተሰብሳቢ ሂሳብ ውስጥ፣

1. **አዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ**

- በዋናው ግቢ

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ብር 679,376,980.06 ተሰብሳቢ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን በዝርዝር ሲታይ፤ ከዚህ ውስጥ፡-

- ብር 64,685,325.49 ተሰብሳቢ ሂሳብ ለሠራተኞች ቅድሚያ ክፍያ፣ለግዥ ሠራተኞች ቅድመ ክፍያ፣ በመንግስት መ/ቤቶች ውስጥ ሌሌች የቅድሚያ ክፍያዎች ተሰብሳቢ ሂሳብ ተብሎ የተያዘ፣
- ብር 597,506,410.76 ተሰብሳቢ ሂሳብ ለአቅራቢዎች ቅድመ ክፍያ፣ ለኮንትራክተሮች ቅድመ ክፍያ ተብሎ የተያዘ፣
- ብር 17,185,243.81 ልዩ ልዩ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተብሎ የተያዘ፣

ቢሆንም ለሂሳቡ ተገቢ የሆነ ተቀፅላ የሂሳብ ሌጅር ያልተቋቋመ መሆኑ ተሰብሳቢ ሂሳቡ የሚፈለግባቸው ግለሰቦች፣ በእያንዳንዱ ግለሰብ የሚፈለገው ገንዘብ መጠን፣ ገንዘቡ ወጪ የሆነበት ቀን፣ወር እና ዓ.ም፣ ሂሳቡ መወራረድ ያለበት ጊዜ የሚገልጽ ማስረጃ የሌለ እና ሂሳቡ ያልተወራረደ በመሆኑ በአጠቃላይ የተሰብሳቢ ሂሳብ ትክክለኛነት በኦዲቱ ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

➢ በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቱ

- በጠቅላላው ብር 40,682,445.86 ከ1 ወር በላይ እስከ 5 ዓመት የቆየና በወቅቱ ሂሳቡ ያልተወራረደና ለረጅም ጊዜ ያልተሰበሰበ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡

➢ በተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ

- በድምሩ ብር 39,412.282.88 2008 በጀት ዓመት መጨረሻ መወራረድ ሲገባው ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ የታወቀ ሲሆን፡-

2. ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ

- በ4202 ሂሳብ መደብ ብር 36,644.28 ከቀድሞ ገንዘብ ያዥ የሚፈለግ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ጉዳዩ በፍርድ ቤት ውሳኔ አግኝቶ ከባለዕዳው ዋስ ገቢ እየተደረገ የነበረ ቢሆንም ከሚያዝያ/08 ጀምሮ ከዋሱ ያልተቀነሰ መሆኑ፤
- ድርጅቱ በዋጋ ማወዳደሪያ ከጠየቀው ብር 426,915.78 ውስጥ 50% ብር 213,457.89 በቅድሚያ ሲከፍል ለክፍያው የባንክ ዋስትና ያልቀረበ መሆኑ፤
- በ4251 የሂሳብ መደብ ከሚታየው ለተቋራጮች ቅድመ ክፍያ ተብሎ ሪፖርት ከተደረገው ውስጥ ብር 3,196,621.28 ለህግ አገልግሎት ተመርቶ ማስረጃ በማሰባሰብ በሚል ክስ ሳይመሰረትበት የቆየ ሂሳብ መሆኑ፤
- በ4253 ሂሳብ መደብ በአቅራቢዎች ቅድሚያ ክፍያ የተመለከተው ብር 80,000.00 ለአዲስ አበባ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በቅድሚያ የተሰጠ ሲሆን የተሰጠበት ምክንያት የሚያመለክት ማረጋገጫ ያልቀረበለት ከመሆኑ በተጨማሪ የውለታ ሠነድ የሌለው መሆኑ፤
- በ4272 ሂሳብ መደብ በክብ ጎ/ሥራ ማህበር ስም የተመለከተው ብር 38,107.00 የተሰጠበት ምክንያት የሚያመለክት ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፤

3. ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ

- በ4203 ሂሳብ መደብ ለሠራተኞች ለነዳጅ፤ ለውሎ አበል፤ ለመጓጓዣና ለሌሎች የተለያዩ ወጪዎች በቅድሚያ ከተከፈለው ብር ውስጥ፤
- ብር 2,854,021.04 በዋናው ካምፓስ በጊዜ ገደቡ ሳይወራረድ ለ7 ዓመት የቆየ መሆኑ፤

- ብር 465,326.08 በተቋሙ በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ከሚገኙ ሠራተኞች የሚፈለግ ከ1-7 ዓመት (ከ1999 - 2008) ሳይወራረድ የሚገኝ መሆኑ፤
- ብር 122,479.67 ከውጭ ዜጎች የሚፈለግ ሣይወራረድ ከ1-7 ዓመት (ከ1999 - 2008) የቆየ መሆኑ፤
- በ4211 ሂሳብ መደብ በግዢ ቅድሚያ ክፍያ ከተመለከተው ውስጥ በዋናው ካምፓስ ለግዢ ሠራተኞች በቅድሚያ ተሰጥቶ ብር 191,650.30 ከ4 ዓመት በላይ የቆየ መሆኑ፤
- በ4253 ሂሳብ መደብ ለአቅራቢዎች የቅድሚያ ክፍያ ከተመለከተው ውስጥ ብር 4,152,510.40 በዋናው ካምፓስ ለተለያዩ አቅራቢዎችና አገልግሎት ሰጪዎች
- በቅድሚያ ተሰጥቶ በጊዜ ገደቡ ሳይወራረድ ከ7 ዓመት በላይ የቆየ መሆኑ፤
- ብር 526,092.57 በተቋሙ በተለያዩ የሥራ ክፍሎች ከሚገኙ ሠራተኞች የሚፈለግ ከ1-7 ዓመት (ከ1999 - 2008) ሳይወራረድ የሚገኝ መሆኑ፤
- ብር 503,074.78 በመ/ቤቶችና ድርጅቶች ስም የተያዘ ከ1-8 ዓመት የቆየና ከተጠቀሰው ሂሳብ ውስጥ ብር 200,000.00 በኢትዮጵያ ኦሎምፒክ ኮሚቴ ስም የተያዘ (በ2001 ወጪ የሆነ) የሚገኝ መሆኑ፤

4. ትምህርት ሚኒስቴር የታየው ብር 82,078,962.89 ከ 1 ዓመት እስከ 13 ዓመት ሳይወራረድና ሣይሰበሰብ የቆየ መሆኑ ፤
5. ወላይታ ዩኒቨርሲቲ ብር 11,626,060.69 ከ1 ዓመት እስከ 4 ዓመት ሳይወራረድና ሣይሰበሰብ የቆየ፤
6. አምቦ ዩኒቨርሲቲ ከ1 ዓመት እስከ 14 ዓመት ሳይወራረድና ሣይሰበሰብ የቆየ
7. ወለጋ ዩኒቨርሲቲብር 184,575.63 በሂሳብ መደብ 4202 ከ 3 ገንዘብ ያገኙ የሚፈለግ ከ 3 ዓመት እስከ 6 ዓመት ምንም አይነት እቅስቃሴ ሳይደረግበት የቆየ ሲሆን ቀሪው ብር 19,248.42 ደግሞ በጊዜ ገደቡ ያልተወራረደ መሆኑ፤
8. ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ ከ1 ዓመት እስከ 10 ዓመት ሳይወራረድና ሣይሰበሰብ የቆየ፤
9. ዲላ ዩኒቨርሲቲ ከ1 ዓመት እስከ 14 ዓመት ሳይወራረድና ሣይሰበሰብ የቆየ፤
10. አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ ከ1 እስከ 5 ዓመት ሳይወራረድና ሣይሰበሰብ የቆየ መሆኑ ፤

2.1.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ከዓመት ወደ ዓመት ሳይወራረዱ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ የሚታዩ ከሆነ የሂሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡት ከመቻላቸውም በላይ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነትና ለጥፋት ሊዳረግ የሚችል ስለሆነ መሥሪያ ቤቶቹ በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች እንዲወራረዱ፤ መሰብሰብ የማይችሉትን ደግሞ አጣርተው አስፈላጊውን እርምጃ መወሰድ እንዳለባቸው በተደጋጋሚ አሳስበናል፡፡

2.2 <u>መደበኛ ሚዛናቸውን ያልጠበቁና ተቀጽላ ሌጀር የሌላቸው ተሰብሳቢ ሂሳቦች፤</u>

2.2.1 <u>ግኝት</u>

በተሰብሳቢ ተቀጽላ ሌጀሮች (Subsidery ledger) ላይ የተመለከቱት ዝርዝር ሂሳቦች ውጤት ከአጠቃላይ ሌጀሩና (General Ledger) በሂሳብ መግለጫው ጋር ከተመለከተው ሂሳብ ሚዛን ጋር ተመሳሳይ መሆናቸውን እና ተሰብሳቢ ሂሳቦቹም መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. <u>በአዲስአበባ ዩኒቨርሲቲ</u>

   ዋናው ግቢ በተሰብሳቢ ሂሳብ /ለሰራተኞች ቅድሚያ ክፍያ/ ብር 370,980.65 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ክሬዲት) ተመዝግቦ መገኘቱ በኦዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

2. <u>በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ፡-</u>

   በዋናው ግቢ በተሰብሳቢ ሂሳብ መደብ 4211 በተቀጽላ ሌጀር ኮድ 001 ብር 306,943.12 እንዲሁም በተቀጽላ ሌጀር ኮድ 002 ብር 36,196.08 በድምሩ ብር 343,139.20 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ክሬዲት) ተመዝግቦ መገኘቱ፤

3. <u>በዲላ ዩኒቨርሲቲ</u>

   በተለያዩ የተሰብሳቢ ሂሳብ መደቦች ላይ ብር 654,583.29 የሂሳብ ሪፖርቱ ላይ የሚታይ ቢሆንም ለመከታተል የሚያስችል ተቀጽላ ሌጀር የሌለው መሆኑ፤

4. <u>በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ</u>

   በ4203 ሂሳብ መደብ ለሠራተኞች ቅድሚያ ክፍያ ከተመለከተው ብር 4,813.06 ውስጥ ብር 2,702.44 መቼ ወጪ እንደሆነና ከእነማን እንደሚፈለግ ለማወቅ የሚያስችል ማስረጃ የሌለው መሆኑ፤ታውቋል፡፡

2.2.2 የማሻሻያ ሃሳብ

- ባልተለመደ የሂሣብ ሚዛን የሚታየው የሂሣብ ማስተካከያ እንዲሠራለት፤
- ተቀጽላ ሌጀር የሌላቸው እንዲዘጋጅላቸውና
- በውዝፍ የሚገኘው ተሰብሳቢ ሂሳብ በአስቸኳይ እንዲወራረድ፣
- የዕቃ ግዢ ሠራተኞች ለተለያዩ አገልግሎቶች ማስፈጸሚያ በቅድሚያ የወሰዱት ገንዘብ በደንብና መመሪያ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ እዲያወራርዱ ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

3 የገቢ ሂሳብ

3.1.1 ያልተሰበሰበ የገቢ ሂሣብ

3.1.2 ግኝት.

1. **በውለታው መሠረት መሰብሰብ ሲገባው ያልተሰበሰበ ገቢ**

ተ.ቁ	አዲት ተደራጊው መ/ቤት	የግኝቱ መግለጫ	የገንዘቡ ልክ
1	ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ	በኦሮሚያ ጤና ቢሮ ስፖንሰርነት ከሚማሩ ተማሪዎች እስከ ሰኔ 30/2008 በውለታው መሠረት መሰብሰብ ሲገባው ያልተሰበሰበ ብር 2,705,894.00 የተገኘ መሆኑ፤	2,705,894.00
		የውል ግዴታውን ካልፈጸመ አንድ መምህር ብር 111,168.00 ግንቦት 9/2006 ለተቋሙ እንዲከፍል የተወሰነ ሲሆን እስካሁን ገንዘቡ ከባለጉዳዩ ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፤	111,168.00
2	ዲላ ዩኒቨርሲቲ	ለትምህርት ወደተለያዩ ሀገራት ከሄዱ ሰራተኞች የውል ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው	142,740.00
3	ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ	ወጪ ትምህርታቸውን ተምረው ሲጨርሱ በውላቸው መሰረት ያልተመለሱትን እና የተለያዩ አገልግሎቶችና ተመላሽ ገንዘቦችን በወቅቱ ገቢ ባለማድረጋቸው በዩኒቨርሲቲው የህግ አገልግሎት ዳይሬክቶሬት ክስ የተመሰረተበትና በፍርድ ቤት ውሳኔ ብር 3,642,125.20 ለዩኒቨርሲው የተወሰነለት ቢሆንም ብር 449,902.86 ብቻ ገቢ የሆነና ቀሪው ብር 3,192,222.34 ገቢ ያልተደረገ መሆኑ፣	3,192,222.34
		ድምር	**6,152,024.34**

- ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ በኦሮሚያ ጤና ቢሮ ስፖንሰርነት ከሚማሩ ተማሪዎች እስከ ሰኔ 30/2008 በውለታው መሠረት መሰብሰብ ሲገባው ብር 2,705,894.00 ያልተሰበሰበ መሆኑ፣
- ከባህርዳር ዩኒቨርሲቲ ፣ ከዲላ ዩኒቨርሲቲና ከሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ለትምህርት ወደተለያዩ ሀገራት ከሄዱ ሰራተኞች የውል ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው መክፈል የሚገባቸውን በድምሩ ብር 365,076.00 ያልከፈሉ በመሆኑ በጠቅላላው ብር 6,152,024.34 ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

2. **ያልተሰበሰበ የጉዳት ካሳ፤**

ከሶስት ዕቃ አቅራቢዎችና ከአስራ ሶስት ሕንጻ ተቋራጮች በድምሩ ብር 133,028,402.77 በገቡት ውል መሰረት ባለመፈጸማቸው፣ ህንፃዎች በውላቸው ላይ በተገለፀው የጊዜ ገደብ ባለመጠናቀቃቸው ላደረሱት የጉዳት ካሳ፣ ተሰብስቦ ገቢ አለመደረጉን፡ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ-9/1 ቀርቧል/ በመሆኑም ባለው ውል ስምምነት መሰረት ተፈጸሚ እንዲደረግ ለየመ/ቤቶቹና ለዩኒቨርሲቲዎቹ የጉዳት ካሳው እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

3. **ያልተሰበሰበ ሥራ ግብር፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና ቅድመ ግብር፤**

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 ዓ.ም አንቀጽ 53 እንዲሁም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 78/1994 ዓ.ም አንቀጽ 24 ተራ ቁጥር 1 እና 2 በግዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 27/2002 አንቀጽ 4 ቁጥር 1 ማንኛውም ወኪል በሚፈፅመው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ለአቅራቢው መክፈል የነበረበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሶ በማስቀረት ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ እንዲያደርግ በተደነገገው መሠረት ተግባራዊ መደረጉን እንዲሁም ለህንፃ ተቋራጭ የሚፈጸመው ክፍያ በውሉና በህጉ መሰረት የተፈጸመ መሆኑን እና ተገቢው ምዝገባም የሚከናወን መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ ከክፍያው ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 76,749.71 እንዲሁም የቅድሚያ ታክስ /withholding / የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር ድርጅቱ ስለሌለው ከሚከፈለው ሂሳብ ላይ 30 ፐርሰንት /ሰላሳ በመቶ/ በማከል ብር 153,499.42 በድምሩ ብር 230,249.13 ተቀናሽ መሆን ያለበት ታክስ ያልተቀነሰ እና ለሚመለከተው ግብር ሰብሳቢ መ/ቤት ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ
- መቀሌ ዩኒቨርሲቲ 31,304.35 የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 3,503.00 ቅድመ ገቢ ግብር ታክስ ሳይቀነስ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
- አምቦ ዩኒቨርሲቲ 30% መቀነስ ሲገባው 2% ብቻ የተቀነሰ በመሆኑ ያልተቀነሰ የቅድመ ግብር ከፍያ 17,278.80 መገኘቱ
- ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ በድምሩ ብር 17,575.39 የስራ ግብር ከተጠቃሚዎቹ መቀነስ ሲገባው ከውስጥ ገቢ በመሸፈን ክፍያ መፈፀሙ፤ ተረጋግጧል፡፡

4. በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሚታዩ ሌሎች ዋና ዋና የአሠራር ድክመቶች

በጅማ ዩኒቨርሲቲ፤

በጅማ ሆስፒታል የመድሃኒት ሽያጭ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ እና በ2008 በጀት ዓመት በኡዲት ሳምፕል በታዩት ብቻ ለAPTS የብር 14,276,899.61 የመድሃኒት ግዥ ከመደበኛ በጀት የተገዛ ሲሆን ከመድሃኒቱ በመልሶ ሽያጭ የተገኘ ገቢ በበጀት ዓመቱ በቀረበ የሂሳብ ሌጀር መሠረት ብር 5,401,390.44 እንደሰበሰበ የተመለከተ ሲሆን ከዚህ የመድሃኒት መልሶ መሸጥ ገቢዎች የተገኘ ብር 28,977,861.37 ሲሆን መድሃኒቱ ከመደበኛ በጀት ግዥ የተፈፀመ በመሆኑ ሂሳቡ ለበጀት መተኪያ ተደርጎ መመለስ ሲገባው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከሆስፒታሉ የውስጥ ገቢ ሂሳብ አካውንት ገንዘቡ ብሎክ ተደርጎ እንዳይወሰድ ለሆስፒታሎች በተፈቀደ የማይዘጋ ሂሳብ አካውንት ቁጥር 1000166208819 ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተቀመጠ መሆኑ

በመዳወላቡ ዩኒቨርሲቲ፤

- ከተከታታይ ትምህርት (Extension, Weakened and Summer) እና ከድኅረ-ምረቃ ለሚሰበሰበው ገቢ ከእያንዳንዱ የገቢ ምንጭ የተሰበሰበውን የገንዘብ መጠን ለይቶ የሚያመለክት ተቀጽላ የሂሳብ ቋት (Subsidiary ledger) የሌለ መሆኑ፤
- ዩኒቨርስቲው የውስጥ ገቢ ማመንጫ የሥራ ክፍል በዳይሬክቶሬት ደረጃ ቢኖረውም ከተከታታይ ትምህርት፤ ከድኅረ-ምረቃ፤ ከእርሻ ምርት ሽያጭ፤ የተለያዩ አገልግሎት ከሚሰጡ ሱቆች ኪራይ፤ ከመዝናኛ ክበቦች እና ከሌሎች የተለያዩ ምንጮች የሚሰበሰቡ ገቢዎች በዝርዝር የሚያሳይ መከታተያ የሌለው መሆኑ፤
- በዩኒቨርሲቲው ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ሱቆች፤ መዝናኛ ክበቦች እና የጀበና ቡና አቅራቢዎች በአብዛኛው ውላቸው የተጠናቀቀ /ያልታደሰ/ መሆኑ፤

በሐረማያ ዩኒቨርሲቲ፤

ተከራዮች በገቡት ውለታ መጠን ወርሃዊ ክፍያውን የማይፈጽሙ መሆኑ፤ (ለምሳሌ፡- ከኢንተርፕራይዝ በቀረበው መረጃ መሠረት ልዩ ምግብ ቤት በየወሩ ብር 3,573.90 ሂሳብ መክፈል ሲገባው የ5 ወራት ብር 2,859.00 ሂሳብ በመክፈሉ በየወሩ ብር 714.90 ያልተከፈለ፤ ራሄል ኢርኮ በተመሳሳይ በየወሩ ብር 2,708.80 መክፈል ሲገባት ለ2 ወራት ብር 1,708.80 በመክፈሏ ብር 2,000.00 ያልተከፈለ፤ ቆንጂት ጌታቸው የሴቶች የውበት ሳሎን በየወሩ ብር 822.00 መክፈል ሲገባት የጥቅምትና የህዳር/08 ብር 702.00 ሂሳብ በመክፈሉ ብር 240.00 (120*2) ያልተከፈለ (ያልተሰበሰበ) እና ሌሎችም በተመሳሳይ መልኩ የሚገኙ መሆኑ)፤

በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ፤

የክፍያ ትዕዛዙ በጥቅሉ በክረምት መርሃ- ግብር የድህረ-ምረቃ ተማሪዎችን ያስተማሩበት በሚል ሂሳቡ ከመደበኛ በጀት የተከፈለው ብር 979,976.00 በክረምት የድህረ-ምረቃ ፕሮግራም በትምህርት ሚኒስቴር በኩል የሚላኩትን፣ በሌሎች የመንግስት መ/ቤቶችና በግላቸው ከፍለው የሚማሩ ተማሪዎች በግልጽ ተለይቶ የተያዘ ባለመሆኑ ከመደበኛ በጀት መክፈል የሌለበትን እና ከክረምት ድህረ-ምረቃ ከተሰበሰበው የውስጥ ገቢ መክፈል ያለበትን ሂሳብ ማጣራት ያልተቻለ መሆኑ፤

በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ፤

- ከመምህራን የተሰበሰበ የቤት ኪራይ ገቢ ብር 392,987.11 የመደበኛ ሂሳብ ገቢ ሆኖ ሳለ አላግባብ በውስጥ ገቢ የተመዘገበና ለሚመለከተው አካል ፈሰስ ያልተደረገ መሆኑ፤
- (GIZ) ለፈጸማቸው የዕቃና አገልግሎት ግዢዎች ሂሳቡ ሲወራረድ በወጪ ሰነዶቹ ላይ የተመለከቱት የተጨማሪ እሴት ታክስ ሂሳቦች (2%) በራሱ ስም በታተመ የቅድመ ዊዝ ሆልዲንግ ደረሰኝ መሰብሰቡን ከማመልከቱ በቀር ለሚመለከተው አካል ገቢ ለመደረጉ ሂሳቡ ሲወራረድ ማስረጃ የማይቀርብ መሆኑ፤

3.1.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- መድሃኒት በመደበኛ በጀት እየተገዛ ከሽያጭ የሚገኘው ገቢ በሙሉ ወደ ውስጥ ገቢ የሚገባ ከሆነና አሰራሩም በዚህ ከቀጠለ የመንግስት በጀት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር ይችላል፡፡ በመሆኑም ከመደበኛ በጀት

ተገዝቶ በመልሶ መሸጥ የተገኘው ገቢ ሙሉ በሙሉ የሆስፒታሉ ገቢ ባለመሆኑ የማይዘጋ ሂሳብ አካውንት የገባው ገንዘብ ለመንግስት ፈሰስ ተደርጎ ሪፖርት ሊቀርብ እንደሚገባ ገልጸናል፡፡

- ዩኒቨርሲቲው ተቀናሽ ያላደረገውን የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የቅድመ ታክስ /withholding/ ከድርጅቱ ተመላሽ እንዲደረግ በማድረግ ለሚመለከተው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ፈሰስ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ለወደፊቱ በኢትጵያ ነዋሪ ባልሆነ ሰው ወይም ድርጅት በሚሰጡ አገልግሎቶች ከሚመለከተው አካል (ከግ/ኢ/ል/ሚኒሰቴር ወይም ከኢ/ግ/ጉ/ባለስልጣን) ታክሱ በገዥው አካል ተቀንሶ መያዝ የለበትም ተብሎ በጹሑፍ እስካልተገለጸ ድረስ በመመሪያው መሰረት ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የቅድመ ታክስ / withholding / ከሚከፈልበት ግብይት ላይ ተገቢውን ታክስ ከክፍያው ላይ ተቀናሽ በማድረግ ለሚመለከተው ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት ፈሰስ ማድረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡
- ከላይ የተመለከተውን ቅጣት አቅራቢዎቹ እንዲከፍሉ ለወደፊቱም አቅራቢዎች በገቡት ውል መሠረት ዕቃውን ወይም አገልግሎቱን ካላቀረቡ በመመሪያው መሠረት መክፈል ያለባቸውን የጉዳት ካሳ በህግ መጠየቅ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡
- ከእያንዳንዱ የገቢ ምንጭ የተሰበሰበውን የገንዘብ መጠን ለይቶ የሚያመለክት ተቀጽላ የሂሳብ ቋት (Subsidiary ledger) እንዲዘጋጅና
- በገቢ ግብር አዋጁ፣ ደንብና በተላለፈው መመሪያ መሰረት ያልተቀነሰው የገቢ ግብር ተቀንሶ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4. የወጪ ሂሳብ

4.1 የግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈፀሙ ግዥዎች፡

4.1.1 ግኝት

የፌዴራል መንግሥት ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣዉ የእቃና የአገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት እንዲሁም የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሕ/አ/2/59 በተጻፈ ደብዳቤ ሰኔ 2002 ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል ባስተላለፈው እና ከታኅሳስ 12 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ በሆነው የግዥ መመሪያ መሰረት በጨረታ መገዛት ለሚገባቸው ግዥዎች ጨረታ መውጣቱን፤ የዋጋ ማወዳደሪያ ተሰብስቦ ሊገዙ ለሚገባቸው ግዥዎች የዋጋ ማወዳደሪያ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በስምንት ዩኒቨርስቲዎች ጨረታ ሳይወጣ በብር 102,542,855.24 የቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
2. በሶስት ዩኒቨርስቲዎች ግልጽ ጨረታ ሳይወጣና የዉሱን ጫራታ መስፈርቱ ሳይሟላ በብር 9,705,233.86 በውስን ጨረታ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
3. በሶስት መሥሪያ ቤቶች ጨረታ ሳይወጣ በብር 6,404,521.85 በዋጋ ማወዳደሪያ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
4. በስድስት ዩኒቨርስቲዎች የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ በብር 27,110,508,79 የቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
5. በአስር ዩኒቨርሲቲዎች ተከፋፍሎ በዋጋ ማወዳደሪያ ብር 23,540,438.10 ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
6. በአራት ዩኒቨርስቲዎች በብር 912,168.23 ከጨረታው አሸናፊ ውጭ ፤ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበ አቅራቢ፣ የታደሰ የንግድ ፈቃድና የአቅራቢነት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ካላቀርቡ አቅራቢዎች ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

በ18 መ/ቤቶች በድምሩ በብር 163,811,204.22 የግዥ አዋጅ፤ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ግዥዎች ተፈጽመው ተገኝተዋል፡፡/ዝርዝሩም በአባሪ-21 ቀርቦል/

4.1.2 የማሻሻያ ሃሳብ፣

- ዩኒቨርስቲዎቹ ማቀድ እስከተቻለ ድረስ በጥቅል ወይም በጅምላ ሊገዙ የሚችሉ እቃዎችን በግልጽ ጨረታ የግዥ ዘዴ እንዲፈጽም
- በዋጋ ማቅረቢያ በተደጋጋሚ ለሚፈጽማቸው ግዥዎች በግዥ ስራ ክፍሉ የገበያ ጥናት በማድረግ እንዲሁም በኤጀንሲው ድረ-ገጽ የሚወጣውን ወቅታዊ ዝርዝር ዋጋ ጋር በማመሳከር ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገቢያ ዋጋ መሆኑን ከተረጋገጠ በኃላ ከተሳተፉት አቅራቢዎች ውስጥ አሸናፊ ሆኖ የተመረጠው ያቀረበው ዋጋ ጋር ተመሳክሮ ዋጋው የተጋነነ መሆኑን እና አለመሆኑን በማረጋገጥ ግዥውን መፈጸም እንዳለባቸው
- የተወሰኑ አቅራቢዎች ብቻ በተደጋጋሚ መጋበዝ ለብልሹ አሰራር መንገድ የሚከፍት በመሆኑ አቅራቢዎች እኩል የመወዳደር እድል እንዲኖራቸው በዙር ሁሉም ሊሳተፉ የሚችሉበት አሰራር መዘርጋት እና ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ለወደፊቱ የዚህ አይነት አሰራር እንዳይከሰት ጥብቅ ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበትና የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትለው ግዥዎችን መፈጸም ያለባቸው መሆኑን አሳስበናል፡፡

4.2 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ፣

4.2.1 ግኝት

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ (የክፍያ ደረሰኝ ሳይቀርብ፣ በተራ ፋክቱር፣ በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ፣ በባንክ የተላከው ገንዘብ ስለመድረሱ ማረጋገጫ ሳይቀርብ፣ ለሥልጠና ክፍያ Attendance sheet የሌለው፣ የዕቃዎች ጥራት በቴክኒክ ኮሚቴ ወይም በሚመለከተው ባለሙያ የዕሁፍ ማረጋገጫ ሳይቀርብ፣....) በ21 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 132,739,577.83 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ-17 ቀርቧል፡፡/

- ከላይ ከተመለከተው ሂሳብ በጅማ ዩኒቨርስቲ ከመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የመድሃኒት ግዥ ተፈጽሞ በወጪ ለተመዘገበው ብር 16,195,279.28

የቀረበው የክፍያ ማስረጃ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ መሆኑ፤ ከተገለጹት ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

- በዩኒቨርስቲው ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ዕቃዉ ወይም አገልግሎቱ በትክክል በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር/Specification/ መሠረት መቅረቡን ወይም አገልግሎት መሰጠቱን ከሚመለከታቸዉ ባለሙያዎች የፅሁፍ ማረጋገጫ ሳይቀርብ በጠቅላላው ድምር ጅማ ዩኒቨርስቲ ብር 18,521,960.82፤ አርሲ ዩኒቨርስቲ ብር 20,538,683.00 ክፍያ የፈጸሙ መሆኑ፣

4.2.2 የማሻሻያ ሃሳብ፤

- ዕቃዉ ወይም አገልግሎቱ በትክክል ለመቅረቡ ወይም ለመሰጠቱ የዕቃዉ ወይም አገልግሎቱ በተፈላጊ ባህሪያት ዝርዝር/Specification/ መሠረት መቅረቡን ወይም አገልግሎት መሰጠቱን፣ ከሚመለከታቸዉ ባለሙያዎች የፅሁፍ ማረጋገጫ ሊቀርብ ይገባል፡፡ማረጋገጫውም ተጠያቂነትን በሚያስከትል መልኩ እንዲቀመጥ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር እርምጃ መውሰድ እንዳለበት፣
- አቅራቢዎቹ ህጋዊ ኦርጂናል ደረሰኝ እንዲያመጡ ማድረግ እንዳለባቸውና፣
- ከደንብና ከመመሪያ ውጪ ክፍያ መፈጸም የመንግሥት ገንዘብ አግባብ ላልሆነ ወጪ ሊጋለጥ እና የመንግስት በጀት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል በጻፍነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.3 ከደንብና መመሪያ ውጭ የተፈጸሙ ክፍያዎች፤

4.3.1 ግኝት

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ ከፋይናንስ ደንብና መመሪያ ውጭ (በዩኒቨርሲቲዎች ቦርድ ውሳኔ መሰረት የሃላፊነት አበል፤ መኖሪያ ቤት ላገኙ የአካዳሚክ ባለሙያዎች አላግባብ የተከፈለ የቤት አበል፤ የተለያዩ ሥራዎች ላከናወኑ ሠራተኞች የማትጊያ ክፍያ፤ ለተለያዩ የኮሚቴ አባላት ለአካዳሚክ ባለሙያዎች ከተፈቀደው የትርፍ ሰዓት ክፍያ ተመን በላይ የተከፈለ፤ ለመደበኛ ተማሪዎች የሚውሉ የተለያዩ የምግብ ግብዓቶችና የሞተር ሳይክል ግዥ ከውስጥ ገቢ ክፍያው የተፈጸመ መሆኑ፣ የፐብሊክ ሰርቪስ ሚ/ር ሳይጠየቅና ሳይፈቀድ ለትርፍ ሰዓት ሥራ የተከፈለ፤ አላግባብ የተፈጸመ የካሣ ክፍያ፤ በመንግስት ከተፈቀደው የውሎ አበል ተመን በላይ የተከፈለ፤ የተፈቀደ በጀት ሳይኖር የተፈጸመ ክፍያ

....) በ20 መ/ቤቶች በድምሩ ብር 56,059,377.29 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 19 ቀርቧል፡፡/

4.3.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ፣</u>

በአዲት ናሙና ከወደቁት ውጪ በሌሎችም ወጪዎች ክፍያው ሊኖር ስለሚችል ከመደበኛ በጀትም ሆነ ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ክፍያው የተፈጸመው ፀንቶ በሚሠራባቸው አዋጅ፣ ደንብ እና መመርያ መሠረት መፈጸም ስላለበት ያለአግባብ ከደንብና መመሪያ ውጭ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ መደረግ ያለበት መሆኑን የገለጽን፣ሲሆን መመሪያውን ተከትለው ክፍያዎችን መፈጸም ያለባቸው መሆኑን አሳስበናል፡፡

4.2 በፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ያልተፈቀደ የኮንትራት ሠራተኞች ቅጥር፡

4.2.1 ግኝት

ተ.ቁ	አዲት ተደራጊው መ/ቤት	የግኝቱ መግለጫ	የገንዘቡ ልክ
1	አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ	በዋናው ግቢ ብር 322,022.22 በተፈጥሮና ኮምፒቲሽናል ሳይንስ ኮሌጅ ብር 716,175.00 በድምሩ ብር ብር 1,038,197.22 በ2008 በጀት ዓመት የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ ዘላቂነት ባለዉ የሥራ መደብ ላይ ለተቀጠሩ የኮንትራት ሰራተኞች ክፍያ የፈፀመ መሆኑ፤	1,038,197.22
2	መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ	የኮንትራት ቅጥሩ በፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒሰቴር ሳይፈቀድ በቢድሬ፣ ሀረዋና ሮቤ የምርምር ጣቢያዎች እና በግብርና ጣቢያዎች ላይ ለሚሰሩ የኮንትራት /ጊዜያዊ/ ሰራተኞች ምንዳ በበጀት ዓመቱ ብር 1,690,988.21 የተከፈለ መሆኑ፤	1,690,988.21
3	ጅማ ዩኒቨርሲቲ	**በግብርናና እንስሳት ሕክምና ኮሌጅ** በ2008 በጀት ዓመት የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሳይፈቅድ ዘላቂነት ባለዉ የሥራ መደብ ላይ ለተቀጠሩ የኮንትራት ሰራተኞች ምንዳ ብር 483,929.00 ክፍያ የፈፀመ መሆኑ፤	483,929.00
4	አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ	ዘላቂነት ባላቸውና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በተመደበ የስራ መደብ ላይ በቋሚነት ቀጥሮ ማሰራት ሲገባው በቀን ሰራተኝነት በ3ቱ ካምፓሶች በድምሩ ብር 1,649,905.58 ተከፍሎ መገኘቱ፤	1,649,905.58
5	ዲላ ዩኒቨርሲቲ	ዘላቂነት ባላቸው ክፍት የስራ ቦታዎች ላይ ተመሳሳይ ስም ላላቸው የቀን እና የኮንትራት ሠራተኞች እንዲሁም በመደበኛ ሰዓት ማከናወን በሚቻልባቸው ስራዎች ላይ ብር 1,259,300.25 የትርፍ ሰዓት ክፍያ መፈፀሙ፤	1,259,300.25
6	ሀዋሣ ዩኒቨርሲቲ	በተከታታይ አንድ ዓይነት ስም ላላቸው የቀን ሠራተኞች በኮንትራት/በጊዜያዊነት/ ለተቀጠሩ ሠራተኞች ብር 534,016.12 መከፈሉ፤	534,016.12
7	ወላይታ ዩኒቨርሲቲ	ዘላቂነት ባላቸው የስራ ቦታዎች ላይ ለቀን ሠራተኞች ብር 264,240.00 የተከፈለ መሆኑ፤	264,240.00
8	ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ	ለሞዴል ት/ቤት እና በተለያዩ የአስተዳደር ሥራ ዘርፎች ላይ ጊዜያዊ /ኮንትራት/ ቅጥር የተፈፀመ ሲሆን በበጀት ዓመቱ የኮንትራት ሰራተኞች ምንዳ በሚል በናሙና በታዩት 5 ወራቶች ብር 713,371.00 ክፍያ የተፈፀመ መሆኑ በአዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡	713,371.00
		ድምር	**7,633,947.38**

4.4.2 <u>የማሻሻያ ሀሳብ</u>

ዘላቂነት ባለውና በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በተመደበ የስራ መደብ ላይ ሰራተኞችን በቀን ሰራተኝነት ቀጥሮ ማሰራት አግባብነት የሌለው በመሆኑ የስራ መደቦቹ በቋሚ ሰራተኞች በውስጥ ደረጃ እድገት ወይም በውጭ ቅጥር ማስታወቂያ በማውጣት ሰራተኞቹ ሊመደቡ/ሊቀጠሩ/እንደሚገባ በቀን ሰራተኝነት እየተከፈለ ያለው ክፍያም እንዲቆም፡፡ ለወደፊቱ እጅግ አስፈላጊ ለሆነና ለአጭር ጊዜ ብቻ የኮንትራት/ጊዜያዊ ቅጥር መፈጸም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ጥያቄውን በቅድሚያ ለሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር በማሳወቅ ተቀባይነት ሲያገኝ ተፈጻሚ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.3 <u>የክፍያ ተመን ሳይኖር የተፈጸሙ ክፍያዎች</u>፤

4.3.1 <u>ግኝት</u>

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ በመንግስት የተፈቀደ የክፍያ መመሪያና የክፍያ ተመን ሳይኖር (ተመራማሪዎች ጥናት ላቀረቡበት፤ለድህረ ምረቃ (Msc and Phd) ተማሪዎች ፈተና ለፈተኑበት/ለገመገሙበት (Internal and External Examiner/Session) እና የማማከር አገልግሎት ለሰጡበት (Supervision) በጥቅሉ የHonorarium ክፍያ ከሚመለከተው አካል የጸደቀ የክፍያ ተመን ሳይኖረው በአስተዳደር ካውንስል በተወሰነው ተመን መሰረት፤ የመመረቂያ ጽሑፍ ለሚያማክሩ አማካሪ መምህራን፤ ፈተና ለማረም፣ አሳይንመንት ለማረም፣ ፈተና ለማዘጋጀት፣ ፈተና ሱፐርቫይዝ ለማድረግ፣ ለሞጁል ዝግጅት እና ለሞጁል ኤዲተር፤ ለተመራቂ ተማሪዎች የመመረቂያ ጽሁፍ የሚያዘጋጁበት የፋይናንስ ድጋፍ፤ የተማሪዎች የመመረቂያ ፅሁፍ ለገመገሙበት፤ ሞጁል ላዘጋጁ፣ የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን ላስተማሩ፣ ፈተና ለፈተኑ እና ላማከሩ፤ ለሐኪሞች ለማበረታቻ /ቶፕ አፕ/፤ ...ወ.ዘ.ተ) በድምሩ ብር 58,364,234.64 ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በአባሪ- 19/ ቀርቧል፡፡/

4.3.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፤

በመማር ማስተማር ሂደት የመምህራን የትርፍ ሰዓት ክፍያ ማስፈፀሚያ ተመን ውስን በመሆኑና ሁሉንም የመማር ማስተማር ክንዋኔዎች የተማሪ ምርምር ስራን ማማከር፤ ፈተና ማውጣት፤ ፈተናና አሳይመንት ማረም፤ ሞጁል ማዘጋጀትና ኤዲት ማድረግ፤

የክትትል ስራ መስራትና ለመሳሰሉት በመንግስት የወጣ ተመን ባለመኖሩ ወይንም ባለመካተቱ ክፍያው በአብዛኛው ዩኒቨርስቲዎች የአከፋፈል ስርዓቱና የክፍያ መጠኑ የተለያየ በመሆኑ ለዩኒቨርቲው ተገቢነት ካለው ለትምህርት ሚኒስቴርም ሆነ ለሚመለከተው የመንግስት አካል በማቅረብ ሲፈቀድ ብቻ ሊከፈል ይገባል፡፡ ክፍያዎች በደንብና መመሪያ መሠረት እንዲፈጸሙ ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ ለዩኒቨርስቲዎች ስራ አመራሮች አሳስበናል፡፡

4.3.3 <u>የዕቃ ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት</u>

የመንግስት በጀት ወጪ ሆነው የተገዙት ዕቃዎች ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ስለመደረጋቸው አዲት ሲደረግ፡-

- **ዲላ ዩኒቨርሲቲ፡-** ለተማሪዎች የምግብ አገልግሎት የሚውል ጤፍ በብር 2,120,000.00፤ ከአትዮጵያ አትክልትና ፍራፍሬ ገበያ አክሰሲዮን ማህበር በብር 1,064,000.00 ለተገዛው ማርማላት የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠለት መሆኑ፤
- **ጎንደር ዩኒቨርሲቲ፡-በአፄ ቴዎድሮስ ግቢ** ለጃን ተከል ማተሚያ ቤት ለተከፈለ ብር 15,525.00 የህትመት ወጪቶቹ ገቢ ለመሆናቸው ሞ/19 የሌለ መሆኑ፤-

በድምሩ ብር 3,199,525.00 የተገዘው ንብረት ገቢ ስለመሆኑ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ ተውቋል፡፡

4.6.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ዩኒቨርሲቲዎቹ በማንኛውም በግዥ የሚረከቧቸውን ንብረቶች ጥራታቸውና የተፈለገው ዕቃ ስለመቅረቡ በባለሙያ በማረጋገጥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ ተቆርጦለት በንብረት ገቢ ደረሰኙ መሰረት ክፍያ ሊፈጸም እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.7 <u>በብልጫ የተከፈለ</u>፤

4.7.1 <u>ግኝት</u>

1. የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ ለደመወዝ፤ ለውሎ አበልና ትራንስፖርት፤ ለግንባታ ሥራዎች ፣ ለተለያዩ የዕቃ ግዢ፣ የአገልግሎት ክፍያዎችና በማቀፍ ግዥ መገዛት ያለባቸው እቃዎች ፕሮፎርማ ብልጫ በመክፈል ግዥ በድምሩ ብር 14,649,929.68 በብልጫ ተከፍሎ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ፡-

ተ.ቁ	አዲት ተደራጊው መ/ቤት	ለውሎ አበልና ትራንስፖርት	ከተመን በላይ ለትርፍ ሰዓት ክፍያ	በብልጫ የተከፈለ ደመወዝ	ለግንባታ ሥራዎች	ለዕቃና አገልግሎት ግዢዎች
1	ጅማ ዩኒቨርሲቲ	270,938.00	4,440,825.59	948,546.05		
2	ዲላ ዩኒቨርሲቲ				4,446,005.03	
3	አርባምንጭ ዩኒቨርሲቲ		1,591,040.00	21,858.00		
4	አክሱም ዩኒቨርሲቲ		1,401,929.48			203,665.00
5	መቀሌ ዩኒቨርሲቲ	44,896.15	343,356.25			
6	ሀዋሣ ዩኒቨርሲቲ			170,100.00		
7	ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ		159,502.44	6,934.00		
8	ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ					126,373.24
9	ወሎ ዩኒቨርሲቲ					76,947.12
10	አምቦ ዩኒቨርሲቲ	28,415.34				
11	ወለጋ ዩኒቨርሲቲ					6,299.99
12	ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ			246,996.00		
13	ወላይታ ዩኒቨርሲቲ			7,286.00		
14	አ.አ ዩኒቨርሲቲ			55,886.00		52,130.00
	ድምር	344,249.49	7,936,653.76	1,457,606.05	4,446,005.03	465,415.35

2. በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢኒስቲትዩት መንግሥት ካወጣዉ የዉጪ ሀገር መምህራን የደመወዝ መጠን በላይ በብልጫ በድምሩ $2,500.00 ተከፍሏቸው ተገኝቷል፡፡

4.7.2 ማሻሻያ ሀሳብ፤

- በብልጫ የተፈጸመው ክፍያ ከሚመለከታቸው ተመላሽ እንዲደረግና ለወደፊቱ ክፍያዎች በጥንቃቄ እንዲፈጸሙ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡
- የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎ በማቀፍ እንዲገዙ ውል የገባባቸው እቃዎች በውሉ መሰረት ሊገዛ ይገባል፡፡በተጨማሪም አላግባብ ግዥዉን የፈጸሙት አካላት ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ተወስዶ ሪፖርት ሊቀርብ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.8 በትክክለኛው ሂሣብ መደብ ያልተመዘገበ፤

4.8.1 ግኝት

የገ/ኢ/ት/ሚ/ር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት ሂሳቦች በተገቢው የሒሳብ መደብ የተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፤ በትክክለኛው ሂሣብ መደብ ያልተመዘገበ በ12 መ/ቤቶች ብር 56,562,154.04 ተገኝቷል። /ዝርዝሩ አባሪ-25 ተመልክቶል።/

4.8.2 የማሻሻያ ሃሳብ

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ማንኛውም ሂሳብ በትክክለኛ የሂሳብ መደብ (ኮድ) ለመመዝገቡ መረጋገጥ እንዳለበትና ለሂሳቡም ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል።

4.9 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ ሂሣብ፤

4.9.1 ግኝት፤

1. **በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ**

   - ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቱ

     በድምሩ ብር 51,862,573.51 የዉስጥ ገቢና የፕሮጀክት ሰኔ 30 2008 ዓ.ም የሂሳብ ሪፖርት የሚያሳይ ሲሆን የውስጥ ገቢ ሂሳብ ወጪ በበጀት ለማስፈቀዱ የሚገልፅ ማስረጃ ሳይኖር ከውስጥ ገቢ ብር 43,763,202.61 ወጪ ተደርጎ የተገኘ መሆኑ፤ለፕሮጀክት ሂሳብና የዉስጥ ገቢ ሂሳብ የሂሳብ ሪፖርት ተለያይቶ የማይዘጋጅ መሆኑ፤ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት የማይደረግ መሆኑ እና የፕሮጀክት ሂሳቦች አዲት ያልተደረጉ መሆኑ በአዲቱ ተረጋግጧል።

2. **በጅማ ዩኒቨርሲቲ፤**

   - የግብርናና እንስሳት ሕክምና ኮሌጅ የውስጥ ገቢና የፕሮጀክት ሂሣብ የሂሣብ ምዝገባ በነጠላ ሂሳብ አመዘጋገብ (single entry) የተከናወነ መሆኑና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ 22,995,253.74 ከወጪ ቀሪ የሚገኝ መሆኑ፤

- **የስፔሻላይዝድ ሆስፒታል** የውስጥ ገቢ እና ፕራይቬትዊንግ የ2008 በጀት ዓመት ሪፖርት በመንግስት የሂሳብ ሪፖርት ማቅረቢያ ይዘት መሠረት ያልተዘጋጀ መሆኑ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡ የሂሳብ ሪፖርት ተዘጋጅቶ ያልተጠናቀቀ መሆኑ እና የሂሣብ ሪፖርት ለገንዘብና ኢ/ል/ሚኒስቴር ያልተላከ መሆኑ፤

3. **በሠመራ ዩኒቨርሲቲ** በበጀት ዓመቱ ከውስጥ ገቢ የተሰበሰበው ብር 4,764,331.45 እና ከውስጥ ገቢ ወጪ የተደረገው ብር 3,472,185.76 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡

4. **በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ** በእርዳታ የተገኘ የፕሮጀክት ሂሳብ ብር 2,460,717.53 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡
5. **በዲላ ዩኒቨርሲቲ** በማነስ ሪፖርት የተደረገ የውስጥ ገቢ ብር 2,833,280.20 ተገኝቷል፡፡
6. **ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ** በእርዳታ የተገኘ የፕሮጀክት ሂሳብ ብር 3,727,432.08 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡
7. **በሀዋሣ ዩኒቨርሲቲ** ከውስጥ ገቢ የተሰበሰበ ብር 104,269,903.33 እና ከውስጥ ገቢ ወጪ የተደረገ ብር 89,971,051.94 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡
8. **በወላይታ ዩኒቨርሲቲ**
   - ብር 1,394,071.76 ያልተመዘገበና በሂሣብ ሪፖርት ያልተካተተ የወጪ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡
   - በማነስ ሪፖርት የተደረገ ብር 69,419.05 የወጪ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

4.9.2 <u>**የማሻሻያ ሃሳብ**</u>፣

የሂሳብ ሪፖርት ከመዘጋጀቱ በፊት የአጠቃላይና የተቀጽላ ሌጀር ሚዛን ትክክለኛነቱ መረጋገጥ አለበት ፡፡በመሆኑም የሂሳብ ምዝገባዎች ከሂሳብ እንቅስቃሴ ወደ ሌጀር እንዲሁም ወደ ሂሳብ ሪፖርት በትክክል በማስተላለፍ የሂሳብ ሪፖርቱ እንዲዘጋጅ፣

ኦዲት ያልተደረጉ ፕሮጀክቶች ኦዲት ተደርገዉ ሪፖርት መቅረብ እንዳለበትና የውስጥ ገቢ ወጪ በጀት በሚመለከተው አካል ብቻ ሲፈቀድ ወጪ መደረግ

እንደሚገባ ሥራ አመራሮች ሂሣቦቹ በአግባቡ እንዲመዘገቡና የሂሣብ ሪፖርት በወቅቱ እየተዘጋጀለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሪፖርት እንዲቀርብ በጥብቅ አሳስበናል፡፡

4.10 ከመመሪያ ወጭ የተፈጸመ የደመወዝ ክፍያ፤

4.10.1 ግኝት

ተ.ቁ	አዲት ተደራጊው መ/ቤት	የግኝቱ መግለጫ	የገንዘቡ ልክ
1	ጅማ ዩኒቨርሲቲ	በግብርናና እንስሳት ሕክምና ኮሌጅ ኮሌጁን ለቀው ለሄዱ ሁለት ግለሰቦች ለዶ/ር ካባ ኡርጌሳ የወር ደመወዝ ብር 10,790.00 በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር 129,480.00 እና ለዶ/ር ሰለሞን ሞገስ የወር ደመወዝ ብር 9,486.00 የቤት አበል ብር 1,000.00 በበጀት ዓመቱ በድምሩ ብር 125,832.00፤ በጠቅላላው ብር 255,312.00 አላግባብ የተከፈለ መሆኑ፤	255,312.00
2	ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	በዩኒቨርሲቲው እና በውጭ ሀገር መምህራን መካከል በተገባው ውል መሰረት መምህራኑ በየ2 ዓመቱ የሚታደስ ውል ከዩኒቨርሲቲው ጋር የገቡ መሆኑና የክፍያ አፈፃፀሙም ለመጀመሪያው ዓመት እስከ ነሀሴ እንደሚከፈል እና ለሚቀጥሉት ክፍያዎች ግን ለትምህርት ዘመኑ ይህም እስከ ሰኔ 30 እንደሆነ ውሉ የሚገልፅ ቢሆንም ዩኒቨርሲቲው ከውል ውጭ የሀምሌ እና የነሀሴ ወር በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 36414 ብር 986,554.86፣ በ36417 ብር 382,230.94 እና በ33436 ብር 933,525.58 በድምሩ ብር 2,302,311.38 አላግባብ የከፈለ መሆኑ በአዲቱ ተረጋግጧል፡፡	2,302,311.38
3	ትምህርት ሚኒስቴር	በጡረታ ለተገለሉ አንድ ሠራተኛ የጥቅምት እና የህዳር ወር 2008 ዓ.ም ደመወዝ በድምሩ ብር 2,364.00 ያለአግባብ ተከፍሎ መገኘቱ፤	2,364.00
4	ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ	ዩኒቨርሲቲውን ለለቀቁ 4 ሠራተኞች ብር 2,642.23 እንዲሁም 6 ሠራተኞች አገልግሎት የሚሰጡት ለሠራተኞች የመዝናኛ ክበብ ሆኖ ሳለ በበጀት ዓመቱ ብቻ ብር 132,552.00 ከመደበኛ በጀት ላይ የደመወዝ ክፍያ የተፈፀመ በመሆኑ በድምሩ ብር 135,194.23 አላግባብ መከፈሉ፤	135,194.23
		ድምር	2,695,181.61

4.10.2 የማሻሻያ ሃሳብ፤

አላግባብ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ እንዲደረግና ለወደፊቱ መመሪያው ተጠብቆ እንዲሰራ የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.11 በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ፤

4.11.1 ግኝት

የበጀት ዓመቱ ሂሳብ በበጀት ዓመቱ የሚመዘገብ መሆኑን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ በአንድ መሥሪያ ቤትና በአስራ ሶስት ዩኒቨርሲቲዎች ብር 80,650,516.33 የ2007 በጀት ዓመት የወጪ ሂሳቦች በ2008 በጀት ዓመት በወጪ ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡/ዝርዝራቸውም በአባሪ-24 ቀርቧል፡፡/

4.11.2 የማሻሻያ ሃሳብ

የበጀት ዓመቱ ወጪ በበጀት ዓመቱ እንዲመዘገብ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.12. የወጪውንና የፕሮጀክት ሂሳብ ትክክለኛነት ማጣራት ያልተቻለ ሂሳብ፤

4.12.1 ግኝት

ተ.ቁ	አዲት ተደራጊው መ/ቤት	የግኝቱ መግለጫ	የገንዘቡ ልክ
1	አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ	በዩኒቨርሲቲው በርካታ የተለያዩ የፕሮጀክት ሂሳቦች ቢኖሩም የፕሮጀክት ሂሳቦቹ ዝርዝር መረጃ ማለትም የፕሮጀክቱ ስም፣ የፕሮጀክቱ ዓላማ፣ ፕሮጀክቱ የጀመረበት ጊዜ፣ ለሂሳብ ምዝገባው እና ለሪፖርት ዝግጅት የሚጠቀመው የኤሌክትሮኒክስ ምዝገባ ዓይነት፣ በሂሳብ አካውንት ላይ የሚታይ የገንዘብ መጠን ሰኔ 30,2008፣ ወቅታዊ የሂሳብ ሪፖርት እንደሚዘጋጅ፣ የፕሮጀክት ሂሳቡ አዲት ለመደረጉ እና ላለመደረጉ ከተደረገ በማን እንደተደረገ የሚገለፅ ማስረጃ እና በህጉ መሰረት ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የፕሮጀክት ሂሳብ እንቅስቃሴ የሚያመለክት ሪፖርት ለማቅረቡ የሚገልፅ ማስረጃ በ2007 በጀት ዓመት አዲት እንዲሁም በ2008 በጀት ዓመት አዲት አዲቱ ከተጀመረ ጀምሮ የተጠየቀ ቢሆንም መረጃው በዩኒቨርሲቲው ያልቀረበ መሆኑ በአዲቱ ተረጋግጧል፡፡	

2	**ጎንደር ዩኒቨርሲቲ**	**በአጄ ፋሲል ግቢ** የክህሎት ማሳደጊያ ስልጠና ለሰጡ መምህራንና አስተባባሪዎች በሚል ለስልጠና ብር 67,200.00 የተከፈላቸዉ ቢሆንም አሰልጣኞቹ ስልጠናዉን ለማን እንደሰጡና የተሳታፊዎች ብዛትና የሰአት ፊርማ እንዲሁም ስልጠናዉ የወሰደዉን አጠቃላይ የቀን ብዛት የሚገልፅ ምንም አይነት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤ **ማራኪ ግቢ** ለመስተንግዶ ለተከፈለው ክፍያ ብር 40,834.57 ግብጥዉ እንዲከናወን የፈቀደዉ አካል፣ የተጋባገሮች ማንነትና ብዛት እንዲሁም ስለመሳተፋቸዉ የሚያሳይ የሰአት ፊርማ ባለመቅረቡ የክፍያዉን ህጋዊነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣ በአጠቃላይ ድምር ብር 108,034.57 **በ2ቱ ግቢዎች** ለወጣው ወጪ የተሟላ ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አልተቻለም።።	108,034.57
3	**ወሎ ዩኒቨርሲቲ**	ከውጭ ለገቡ የተለያዩ ዕቃዎች ለጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ማስፈፀሚያ ለቀረጥ ብር 918,758.32 የተከፈለ ቢሆንም ከውጭ ሀገር ገባ የተባለው ዕቃ ወደ ንብረት ክፍል ገቢ ለመሆኑ ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኝነት ማረጋገጥ አለመቻሉ፣	918,758.32
4	**ዲላ ዩኒቨርሲቲ**	• በናሙና ከተመረጡት ሰነዶች ውስጥ ብር 6,873,851.63 የያዙ 16 የክፍያ ቫውቸሮች ለኦዲት ያልቀረቡ በመሆኑ የተመዘገበው ሂሳብ ለታለመለት ዓላማ ለመዋሉ ለማረጋገጥ አለመቻሉ	6,873,851.63
		• ቀደም ሲል ትምህርት ሚኒስቴር ክትትል እየተደረገባቸው የነበሩ እና GIZ በተባለው ድርጅት ተይዘው ሲሰሩ የነበሩ የዩኒቨርሲቲው የህንፃ ግንባታዎች እና የመሰረተ ልማት ግንባታ እንዲሁም የፍሳሽ ቆሻሻ ማጣሪያ ፕላንት ግንባታን በተመለከተ ለማወቅ የሚያስችሉ፣ የተደረጉ የሰነድ ርክክቦች፣ ማለትም፣ ለእያንዳንዱ ሥራ ተቋራጭ በቅድሚያ የተከፈለው ጥሬ ገንዘብ፣ ተመላሽ የተደረገው እና ያልተመለሰ ቅድሚያ ክፍያ፣ ለእያንዳንዱ ሥራ ተቋራጭ በዓይነት የተሰጡ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች /Material Advance/ ተመላሽ የተደረገው ገንዘብና እና ያልተመለሰ፣ቀሪ ዕዳ፣እያንዳንዱ ስራ ተቋራጭ ለሚያከናውናቸው ግንባታዎች በመያዣነት ገቢ ያደረገው የመልካም ስራ ዋስትና ገንዘብ እንዲሁም ግንባታ ክፍሉ ከGIZ-IS የተረከባቸው ሰነዶቹ ለሂሳብ ክፍል ተላልፈው በእያንዳንዱ የህንጻ ስራ ተቋራጭ ስም ሂሳቡ እንዲመዘገብ ስለመደረጉ፣ እንዲሁም ስራው የደረሰበት ደረጃ፣ ያቋረጡ ካለ በእነሱ ላይ የተወሰደ እርምጃ ካለ፣ ከስራ ተቋራጮቹ የሚፈለገውን የተሰብሳቢ እና የመያዣ ሂሳብ የሚያሳይ ተቀጽላ ሌጀር ካለ እንዲቀርብ ተጠይቆ ሊቀርብና እየተደረገ ስላለውም ክትትል ለማወቅ የሚያስችል በቂ ምላሽ የሚሰጥ አካል ባለመገኘቱ የሂሳቡን ሁኔታ ማጣራት አለመቻሉ፣	
		ድምር	7,900,644.52

4.12.2 የማሻሻያ ሃሳብ

- ያልቀረቡት ሰነዶች በአስቸኳይ እንዲቀርቡና ሂሳቡ እንዲጣራ አሳስበናል፡፡
- ዩኒቨርሲቲው ለፕሮጀክት ሂሳቦች ከላይ በተገለፀው መሰረት ተገቢ የሆነ ወቅታዊ የሂሳብ ሪፖርት ማዘጋጀት እና ኦዲት ማስደረግ፣ በመመሪያው መሰረት ለሚመለከተው መ/ቤት ማሳወቅ እና ለፕሮጀክት እና ለእያንዳንዱ ሂሳብ ቁጥር የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.13. የመሰረተ ልማት ግንባታ ወጪዎችን በተመለከተ፤

4.13.1 ከሥራ ተቋራጮች የሚፈለግ ያልተወራረደ ቅድሚያ ክፍያ፤

4.13.1.1 ግኝት

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ የግንባታ ሥራዎችን አጠናቀው ያስረከቡና ሥራውን ያቋረጡ ሥራ ተቋራጮች ተመላሽ ያላደረጉት የቅድሚያ ክፍያና የማቴሪያል ሂሣብ ብር 108,122,653.73 ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ፡-

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	የገንዘቡ ልክ
1	ጅማ ዩኒቨርሲቲ	63,077,064.58
2	ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	18,553,183.46
3	ወላይታ ዩኒቨርሲቲ	8,109,588.59
4	ወለጋ ዩኒቨርሲቲ	5,723,497.11
5	መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ	4,099,492.48
6	ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ	3,360,928.55
7	ወሎ ዩኒቨርሲቲ	3,104,883.51
8	ደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ	1,678,252.92
9	አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ	415,762.53
	ድምር	108,122,653.73

4.13.1.2 **የማሻሻያ ሃሳብ**

ከተቋራጮቹ የሚፈለገው የመንግሥት ገንዘብ ተመላሽ እንዲሆን የዩኒቨርሲቲው ሥራ አመራር አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ እንዳለበት ለወደፊቱም በግንባታ ክፍያ አፈጻጸምና አመዘጋገብ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.13.2 ደንብና መመሪያን ያልተከተሉ የግንባታ ክፍያዎች

4.13.2.1 ግኝት

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ ደንብና መመሪያን ያልተከተሉ (የቅድሚያ ክፍያ ዋስትናው ያልታደሰ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከግንባታ ክፍያው ላይ ያልተቀነሰ መሆኑ፣ ለግንባታው ሥራ የተገዙ የተለያዩ ማቴሪያሎች ለረጅም ጊዜ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣ የውል ሰነድ እና የሥራ ተቋራጮች እና አማካሪዎች የሚያሳይ ዝርዝር ሁኔታ ሳይቀርብ ...ወ.ዘ.ተ) ብር 37,909,666.37 የግንባታ ክፍያ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ፡-

ተ.ቁ	ኦዲት ተደራጊው መ/ቤት	የገንዘቡ ልክ
1	ጅማ ዩኒቨርሲቲ	4,439,379.50
2	ዲላ ዩኒቨርሲቲ	13,182,000.00
3	ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ	14,964,325.86
4	መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ	4,204,448.10
5	ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ	1,119,512.91
	ድምር	37,909,666.37

1.1.1. የክፍያ የምስክር ወረቀቶች የማማከር ፈቃድ ሣይኖረው በዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ዕ/ቤት ፀድቆ ስለመገኘቱ፤

የወጪ ሂሣብ ኦዲት ሲደረግ ደንብና መመሪያን ያልተከተሉ (የክፍያ የምስክር ወረቀቶች የማማከር ፈቃድ ሣይኖረው በዩኒቨርሲቲዎች ግንባታ ፕሮጀክት ዕ/ቤት ፀድቆ መገኘቱ ...ወ.ዘ.ተ) ብር 71,898,368.99 የግንባታ ክፍያ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ፡-

ተ.ቁ	አዲት ተደራጊው መ/ቤት	የገንዘቡ ልክ
1	ጅማ ዩኒቨርሲቲ	31,773,279.69
2	አክሱም ዩኒቨርሲቲ	9,268,656.24
3	ዲላ ዩኒቨርሲቲ	30,856,433.06
	ድምር	71,898,368.99

1.1.2. <u>መመሪያው ከሚፈቅደው በላይ የተለዋጭ እና ተጨማሪ ሥራ ትዕዛዝ አላግባብ የተሠጠ፤</u>

የወጪ ሂሣብ አዲት ሲደረግ ደንብና መመሪያን ያልተከተሉ (ከውለታው በላይ የተፈፀመ ክፍያ፤ መመሪያው ከሚፈቅደው በላይ የተለዋጭ እና ተጨማሪ ሥራ ትዕዛዝ አላግባብ የተሠጠ መሆኑ፤ ...ወ.ዘ.ተ) ብር 81,938,863.94 የግንባታ ክፍያ ተገኝቷል፡፡ ዝርዝሩ፡-

ተ.ቁ	አዲት ተደራጊው መ/ቤት	የገንዘቡ ልክ
1	ጅማ ዩኒቨርሲቲ	29,809,754.34
2	ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ	26,374,222.23
3	ወሎ ዩኒቨርሲቲ	20,210,185.76
4	ጎንደር ዩኒቨርሲቲ	5,544,701.61
	ድምር	81,938,863.94

4.13.3 <u>በአግባቡ ያልተመዘገቡ የግንባታ ክፍያዎች፤</u>

<u>4.13.3.1 ግኝት</u>

1. በሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ፤
   - ለሥራ ተቋራጮች የተከፈለ ቅድመ ክፍያ በዋናው ግቢ ብር 33,043,565.81 እና በቴፒ ግቢ ብር 1,119,617.02 በድምሩ ብር 34,163,182.83 በተሰብሳቢነት መያዝ ሲገባው በቀጥታ በወጪነት ተመዝግቦና ሪፖርት ተደርጎ መገኘቱ፤
   - የተለያዩ ግንባታዎች ክፍያ ሲፈፅም የቅድመ ክፍያ ተመላሽ በዋናው ግቢ ብር 17,326,177.40 እና በቴፒ ካምፓስ ብር 267,184.29 በድምሩ ብር 17,593,361.69 በክፍያ የምስክር ወረቀት ላይ እንደተቀነሰ የሚታይ ቢሆንም ተቀናሽ ሂሳቡ ያልተመዘገበ መሆኑ፤

2. **በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤**የተለያዩ ግንባታዎች ክፍያ ሲፈፅም የቅድመ ክፍያ ተመላሽ በዋናው ግቢ ብር 33,877,627.60 በክፍያ የምስክር ወረቀት ላይ እንደተቀነሰ የሚታይ ቢሆንም ተቀናሽ ሂሳቡ ያልተመዘገበ መሆኑ፤

3. **በጅማ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ** በበጀት ዓመቱ ብር 34,119,221.50 የግንባታ መያዣ ተከፋይ ሂሳብ በተዘጋጀዉ የክፍያ ምስክር ወረቀት ላይ ከክፍያ ላይ የተቀነሰ ቢሆንም ተመዝግቦ በሂሳብ ሪፖርት ላይ መታየት ሲኖርበት ያልተመዘገበና በሂሳብ ሪፖርት ላይ ያልተካተተ መሆኑ፤

4.13.3.2<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በሂሳብ አቀናነሱ እና በአመዘጋገቡ ላይ በታዩት ስሕተቶች ምክንያት፡-

- የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያመለክት ምክንያት ሊሆኑ ስለሚችሉ፤
- ሊቀነስ የሚገባው ገንዘብ ሳይቀነስ ሊቀር ስለሚችል፤
- መከፈል የሌለበት ገንዘብ ሊከፈል ስለሚችል፤
- ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤

ለታዩት ስህተቶች ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራ፤ መሰብሰብ ያለበት ሂሳብ እንዲሰበሰብ፤ መመዝገብ ያለበት ሂሳብ እንዲመዘገብ፤ ለወደፊቱም በግዥና በግንባታ ክፍያ አፈጻጸምና አመዘጋገብ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.13.4 <u>የሕንጻና መሠረተ-ልማት ግንባታ አፈጻጸምን በተመለከተ፤</u>

4.13.5.1 ግኝት

1. **በመደወላቡ ዩኒቨርሲቲ** በውለ በተቀመጠው የማስረከቢያ ቀን መሠረት ግንባታውን አጠናቀው ያላስረከቡ 8 የህንጻ ተቋራጮች መኖራቸው ታውቋል፡፡
2. **በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ** በመከናወን ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ኦዲት ሲደረግ በተገባው ውል መሠረት በወቅቱ ያልተጠናቀቁና አሁንም በመከናወን ላይ ያሉ 4 ፕሮጀክቶች የሚገኙ መሆኑ ታውቋል፡፡
3. **የጅማ ዩኒቨርሲቲ** የሕንፃና መሠረተ-ልማት ግንባታ ሥራዎች አፈጻጸም ኦዲት ሲደረግ፤ • የላብራቶሪና ወርክሾፕ ግንባታ በብር 355,925,389.92 በቀን 07/06/03 ውል የተገባ ሲሆን በፀደቀ የውል ማራዘሚያ እስከ 07/06/05 መጠናቀቅ የነበረበት እስከ ሰኔ 30,2008 ድረስ ያልተጠናቀቀ መሆኑና ከ3 ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ፤ • የሪሰርች ሴንተር እና ኮንፈረንስ ሆቴል ግንባታ በብር 227,919,070.43 በቀን 9/9/2002 ውል የተገባ ሲሆን በፀደቀ የውል ማራዘሚያ እስከ 01/4/2004 መጠናቀቅ የነበረበት እስከ ሰኔ 30,2008 ድረስ ያልተጠናቀቀ መሆኑና ከ4 ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ፤ • የእስታዲየም ግንባታ በብር 144,323,492.00 በቀን 6/8/2007 ውል የተገባ ሲሆን በፀደቀ የውል ማራዘሚያ እስከ 25/1/2008 መጠናቀቅ የነበረበት እስከ ሰኔ 30,2008 ድረስ ያልተጠናቀቀና ስራው ያለበት ደረጃ 23.35% መሆኑ፤ • ዩኒቨርሲቲው በ13/07/2003 ሁለት ቢሮዎች (አንድ ቢሮ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ግቢ ውስጥ እና ግብርናና እንስሳት ህክምና ኮሌጅ ቤተ-መጻህፍት) እና ከዋናው ግቢ ወደ ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ የሚያስተላልፍ ድልድይ ለማሰራት ከአፍሮ ፅዮን ኮንስትራክሽን ኃላ.የተ.የግ.ማ ጋር በ48.7 ሚሊዮን ብር ውል የገባ ሲሆን በቢዝነስ እና ኢኮኖሚክስ ግቢ መገንባት የነበረበት ህንፃ ሙሉ በሙሉ ያልተሰራ መሆኑ፤ ታውቋል፡፡

4.13.5.2 **<u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>**

የግንባታ ሥራዎች በታቀደው መሠረት እንዲከናወኑ በየጊዜው ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

5. **<u>በጀት</u>**

4.2 **<u>የበጀት አጠቃቀም፤</u>**

5.1.1 **<u>ግኝት</u>**

አዲት ለተደረጉት መሥሪያ ቤቶች በ2008 **በጀት ዓመት ለመደበኛ እና ለካፒታል በጀት ለየፕሮግራሞቹ የተፈቀደው እና በሥራ ላይ የዋለው ሂሳብ ሲመዛዘን፡-**

ከመደበኛና ካፒታል በጀት ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የተደረገ በ16 **መ/ቤቶች ብር** 195,875,731.29 **እና ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት በ**24 **መ/ቤቶች ብር** 681,814,885.93 **ተገኝቷል፡፡**

/ዝርዝሩ በአባሪ- 33 **ተመልክቷል፡፡/**

5.1.2 **<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>**

- **ዩኒቨርስቲዎቹ በዕቅድና በፕሮግራም ላይ የተመሠረተ በጀት ሊይዙ እንደሚገባ፤ የበጀት ዕጥረት ካጋጠማቸውም በበጀት ሕጉ መሰረት የበጀት ዝውውር መጠየቅ እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡**
- **ዩኒቨርስቲዎቹየተፈቀደላቸውን በጀት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይችሉ ዘንድ በዕቅድና በፕሮግራም ላይ የተመሠረተ በጀት ሊይዙ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡**

5.1.1 **<u>ግኝት</u>**

የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ሊፈፀም ወይም ወጪ ሊደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ ነው ሆኖም የአዲስ አበባ ዩኒቨርሰቲ በከፍተኛ ትምህርት ማቋቋሚያ አዋጅ ላይ የገቢ ማመንጫ ማቋቋም እንደሚችል በተገለፀው መሰረት ዩኒቨርሰቲው በገቢው ለማቋቋም ያሰበውን የገቢ ማመንጫ/ ኢንተርፕራይዝ/ የመነሻ ካፒታል ሰጥቶ የተቋቋመ ሲሆን በተጨማሪ በ2008 **በጀት ዓመት የተፈቀደ በጀት ሳይኖር በቀን** 29/10/08 **በበጀት ዓመት ማጠናቀቂያ በባንክ ወጪ ማሰመሰከሪያ ቁጥር** 0007674 **ከሚመለከተው**

አካል ፍቃድ ሳይገኝ ከውስጥ ገቢ ሂሳብ ወደ ኢንርፕራይዝ የባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000071386485 ለኢንተርፕራይዙ ለካፒታል ትርፍ ለማስደግ በሚል ብር 10,000,000.00 ገቢ የተደረገ መሆኑን በአዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

5.1.2 <u>የተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ ፣</u>

ዩኒቨርሰቲው ለካፒታል ትርፍ ለማስደግ ተብሎ ለኢንተርፕራይዙ ከውስጥ ገቢ የተሰጠው ድጋፍ የመንግስት ገንዘብ ክፍያ ሊፈፀም ወይም ወጪ ሊደረግ የሚችለው የተፈቀደ በጀት ሲኖር ብቻ በመሆኑ ህገዊነት እንደሌለው ታምኖ ገንዘብ ወደ መንግስት ካዝና ተመላሽ ሆኖ ሪፖርት ሊቀርብ ይገባል ፡፡

6 <u>ተከፋይ ሂሳብ</u>፤

6.1 <u>ግኝት</u>

የተከፋይ ሂሳብ አዲት ሲደረግ በወቅቲ ያልተወራረደ ከዚህ በታች በሰንጠረዡ የተመለከተው ውዝፍ የተከፋይ ሂሣብ ተገኝቷል፡፡

ተ.ቁ	አዲት ተደራጊው መ/ቤት	የውዝፍ ተከፋይ ሂሳቡ ልክ	መግለጫ
1	አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ	419,956,203.21	ከተገለጸው ውዝፍ ሂሳብ ውስጥ ብር 276,119,045.50 የተከፋይ ሂሳቡ ሳይከፈል የቆየበት ቀን፣ወር፣ ዓ.ም ተቀፅላ የሂሳብ ሌጀር የሚገልፅ ማስረጃ የሌለ በመሆኑ፤
2	አርሲ ዩኒቨርሲቲ	131,795.70	በጤና ካምፓስ ከቅድሚያ ክፍያ ታክስ የተሰበሰበው ብር 64,661.13፤ በጤና ካምፓስ እና በግብርና ካምፓስ ከተጨማሪ ዕሴት ታክስ የተሰበሰበው ብር 67,134.57 በድምሩ ብር 131,795.70 የታክስና ግብር ተከፋይ ለሚመለከተው አካል ገቢ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡
3	ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ	599,688.95	በሰኔ 30/2008 በተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት በ5002 ሂሳብ መደብ (ልዩ ልዩ ተከፋይ) ከተመለከተው ውስጥ ብር 599,688.95 ለተጠቃሚዎቹ ሳይከፈል ከ1-9 ዓመት (1999 - 2007) በተቋሙ ተይዞ የሚገኝ መሆኑና ከተጠቀሰውም ከፍተኛው ብር 428,425.11(71%) ለሐረሪ ክልል መንግስት የሚከፈል በሚል የተያዘ ከ8 ዓመት በላይ ለተጠቃሚው ሳይከፈል በዕዳነት ተይዞ ተገኝቷል፡፡
4	አክሱም ዩኒቨርሲቲ	2,577,599.96	በድምሩ ብር 1,869,494.95 ከነተቀጽላ ሌጀሩ ከ2007 በጀት ዓመት ለ2008 በጀት ዓመት የዞረ ተከፋይ ሂሳብ በ2008 በጀት ዓመት ምንም እንቅስቃሴ ያልታየበትና ባለበት ሁኔታ ለ2009 በጀት ዓመት መተላለፉ እና ሌላ ብር 708,105.01 ተከፋይ ሂሳብ ደግሞ በወቅቱ አለመወራረዱ፣
5	ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ	682,877.12	በበጀት ዓመቱ መጨረሻ መወራረድ ሲገባዉ ያልተወራረደና ከ2001 እስከ 2008 በጀት ዓመት የቆየ በድምሩ ብር 682,877.12 ተከፋይ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን ይህም በሂሳብ መደብ 5005 የተያዘ የ2008 በጀት ዓመት ብር 2,289.49 እና በሂሳብ መደብ 5052 ከ2001-2008 በጀት ዓመት የተያዘ ብር

ተ.ቁ	አዲት ተደራጊው መ/ቤት	የውዝፍ ተከፋይ ሂሳቡ ልክ	መግለጫ
			680,587.63 መሆኑ፣
6	ጎንደር ዩኒቨርሲቲ	79,227,247.16	ብር 79,227,247.16 ተከፋይ ሂሳብ እስከ 2008 በጀት ዓመት መጨረሻ መወራረድ ሲገባ ያልተወራረደ መሆኑ፣
7	ወሎ ዩኒቨርሲቲ	8,182,107.28	የበጀት ዓመቱ ተከፋይ ሂሳብ አዲት ሲደረግ፣ በድምሩ ብር 8,182,107.28 እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ መወራረድ የነበረበት ተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ሳይወራረድ የተገኘ ሲሆን ይህም፣ • በልዩ ልዩ ተከፋይ ሂሳቦች /sundry creditors 5002/ የተያዘ ከችሮታ ጊዜ ተከፋይ ውጭ ሌሎች ክፍያዎች ብር 4,221,444.35 ሲሆን ክፍያው ተከፍሎ መወራረድ ያለበት ሂሳብ ቢሆንም እስካአሁን ያልተወራረደ መሆኑ፣ • ዩኒቨርሲቲዉ ከተለያዩ ድርጅቶች ከአገልግሎትም እና ከግዥ ክፍያ የሰበሰበውና በየወሩ ለግብር ሰብሳቢው መስሪያ ቤት ፈሰስ መደረግ ሲገባ በወቅቱ ፈሰስ ያልተደረገ የተጨማሪ እሴት ታክስ /5059 value add tax/ ብር 3,110,804.21 መሆኑ፣ ተረጋግጧል፡፡
8	ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ	1,538,594.02	በድምሩ ብር 1,538,594.02 ተከፋይ ሂሳቦች እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ መወራረድ ሲገባቸው አለመወራረዳቸው፣
9	አርባ ምንጭ ዩኒ.	1,710,612.35	
10	ዲላ ዩኒቨርሲቲ	12,784,647.46	ለ8 ዓመታት የቆየ
11	ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ	8,265,722.85	ከ5 ወር እስከ 10 ዓመት የቆየ
12	ደብረ ብርሃን ዩኒ.	519,590.80	ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት የቆየ
13	ወለጋ ዩኒቨርሲቲ	506,268.97	
14	መቀሌ ዩኒቨርሲቲ	88,059.04	በአጠቃላይ ድምር ብር 88,059.04 ተከፋይ ሂሳብ በመመሪያው መሠረት በወቅቱ ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡
ድምር		536,771,014.87	

6.2 <u>ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን የተመዘገበ ተከፋይ ሂሳብ፣</u>

6.2.1 <u>ግኝት</u>

የገቢና የወጪ ሂሳቦች የሚያዙትና የሚመዘገቡት የገ/ኢ/ል/ሚ/ር ኑሐሴ 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በዋናው ግቢ ተከፋይ ሂሳብ ብር 10,486,750.90 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን (ዴቢት) ተመዝግቦ መገኘቱ በአዲት ወቅት ተረጋግጧል፡፡

6.2.2.**የማሻሻያ ሃሳብ፣**

- **የተከፋይ ሂሳብ አያያዝ እና አመዘጋገብ በመመሪያው መሠረት ተግባራዊ እንዲደረግ እና በሪፖርት ዝግጅት ወቅት የሂሳብ ሌጀሮች ትክክለኛውን የሂሳብ ሚዛን ማሳየታቸው እንዲረጋገጥ ክትትል እና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት፣**
- **የተከፋይ ሂሣቦች በወቅቱ እንዲወራረዱ በየጊዜው ተገቢ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ እንደሚገባ በላክነው ሪፖርት አሳስበናል።።**

7. **የዕቃና ንብረት አስተዳደር፤**

7.1. ለዕቃና ንብረት አስተዳደር የተዘረጉ የውስጥ ቁጥጥር ስርዓት፤

7.1.1 ግኝት

የዩኒቨርሲቲው የንብረት አያያዝ፣ አጠባበቅና አጠቃቀም በፌዴራል መንግሥት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፣

አርሲ ዩኒቨርሲቲ፣ ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲና መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ በስቶክ ካርድ እና ቢን ካርድ የተሟላ ምዝገባ ያልተከናወነ መሆኑ፤

- **ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ፣ጅማ ዩኒቨርሲቲና የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ በተለያዩ የሥራ ክፍሎች /ቢሮዎች/፣ በተማሪዎች ዶርምና በመማሪያ ክፍሎች ወጪ የተደረጉ የተለያዩ ቋሚ ንብረቶች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፤**
- **ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ፣ጅማ ዩኒቨርሲቲ የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ በተለያዩ የሥራ ክፍሎች /ቢሮዎች/፣ በተማሪዎች ዶርምና በመማሪያ ክፍሎች ወጪ የተደረጉ የተለያዩ ቋሚ ንብረቶች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣**
- **መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲእያንዳንዱ ሰራተኛ በስሙ ከንብረት ክፍል የተረከበው ዕቃ በተጠቃሚዎች መዝገብ /User card/ ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ**
- **አርሲ ዩኒቨርሲቲ 28 ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ 1 ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ 1 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው መሆኑ፤**

- **አርሲ ዩኒቨርሲቲ** 5. **ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ** 4 **ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ** 1 **ተሽከርካሪዎች በከባድ ብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑና፤ዲላ ዩኒቨርሲቲ** 25 **ሀዋሣ ዩኒቨርሲቲ** 19
- ***መደወላቡ ዩኒቨርሲቲ***
  - **የቋሚም ሆነ የአላቂ ዕቃዎች ንብረት ምዝገባ የተቋረጠ በመሆኑ፤**
  - **በተለያዩ የሥራ ክፍሎች /ቢሮዎች/፤በተማሪዎች ዶርምና በመማሪያ ክፍሎች ወጪ የተደረጉ የተለያዩ ቋሚ ንብረቶች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፤**
  - **ብዛት ያላቸው ዴስክ ቶፕ ኮምፒውተሮች፤ ፕሪንተሮች፤ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፤ ቴሌቪዥኖች፤ ወንበሮች እና ሌሎች የተለያዩ ንብረቶች ተጠግነው ወደ አገልግሎት እስኪመለሱ ድረስ ለበለጠ ብልሽት በሚዳርግ መልኩ በተበታተነ ሁኔታ ወለል ላይ የተቀመጡ መሆኑ፤**
  - **እያንዳንዱ ሰራተኛ በስሙ ከንብረት ክፍል የተረከበው ዕቃ በተጠቃሚዎች መዝገብ /User card/ ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፤**

በአላቂ ግምጃ ቤት አንዳንድ ዕቃዎች (የስቴፕለር ሽቦ፤ መዶሻ፤ ገጀራ....) ቢን ካርድ የሌላቸው መሆኑ፤አገልግሎት ላይ መዋል የሚችሉ ብዛታቸው 10 የሚሆን ስታፋ ብረት (ጥቅልል ብረት) እና ብዛታቸው የማይታወቅ ፌሮ ብረት ለስርቆት እና ለዝገት (ለብልሽት) በተጋለጠ ሁኔታ መሬት ላይ ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ፤

አርሲ ዩኒቨርሲቲ

<u>ቋሚና አላቂ ግምጃ ቤትን በተመለከተ፤</u>

- **በሆስፒታል እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የቋሚና አላቂ ስቶር ክፍል ተመድበው የሚሰሩ ሰራተኞች ንብረት የመያዝ፤ በሞዴል 19 ገቢ የማደረግና በሞዴል 22 ንብረት ወጪ የማድረግ ሃላፊነቶችን በተደራቢነት የሚሰሩ መሆኑ፤**
- **ለቋሚና አላቂ ዕቃዎች የገቢና ወጪ መከታተያ (ስቶክ ካርድ) ያልተዘጋጀ መሆኑ፤**
- **በናሙና ከታዩት በዕርዳታ የተገኙ ዕቃዎች መካከል ላብ ቼይር ብዛት 10፤ ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተር ብዛት 140፤ ላፕ ቶፕ ብዛት 2 እና ኤፒሲ ሰርጀሪ**

ብዛት 142፤ የዕቃዎቹ ዋጋ ሳይታወቅ በሞዴል 19 ቁጥር 63652 እና 63651 ገቢ የተደረጉ መሆኑ፤

- ንብረት (የቋሚና አላቂ) የሚያንቀሳቅሱ (የሚይዙ) ሠራተኞች በተለያየ ምክንያት የሥራ ክፍል ሲቀይሩ ወይም ተቋሙን ሲለቁ ማስረከብ በሚገባቸው ልክ ለማስረከባቸው በኡዲት የማይረጋገጥ መሆኑ፤

<u>የመድሃኒት ግምጃ ቤትን በተመለከተ (ጤና ሳይንስ ካምፓስ)</u>

- ከዋናው የመድኃኒት ስቶር መድኃኒት ወጪ ሆኖ ወደ መድኃኒት ማደያ (Dispensary room) የገባው መድሃኒት፤ ለመውጣቱ /ለመሰራጨቱ/ ማረጋገጫ የፕሪስክሪፕሽን ወረቀት ቢኖርም በስቶክ ካርድ እና ቢን ካርድ ምዝገባ የማይከናወን ከመሆኑም በተጨማሪ መድኃኒቱ ተሰራጭቶ ሥራ ላይ የዋለው መድኃኒት ምን ያህል እንደ ተሰራጨ በአይነት እና በግንዘብ መጠን ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ሪፖረት የማይደረግ መሆኑ፤

- በሆስፒታሉ ቅጥር ግቢ ውስጥ በሚገኝ አንድ ኮንቴይነር ውስጥ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈ መቼ እንደተቀመጡ፤ ዓይነታቸውና ብዛታቸው የማይታወቅ ከፍተኛ መጠን ያላቸው መድኃኒት የሚገኝ መሆኑበሆስፒታሉ በዋና `መድሃኒት ስቶር ክፍል ተመድቦ የሚሰራ ሰራተኛ ንብረት የመያዝ፤ ገቢና ወጪ የማድረግ ሃላፊነቶችን በተደራቢነት የሚሰራ መሆኑ፤

ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ

- ብዛት ያላቸው የግንባታ ብረቶች በዩኒቨርሲቲው ግቢ ዉስጥ በተለያየ ቦታ ላይ ተከማችተዉ ለብልሽት ተጋልጠው የሚገኙ መሆኑ፤

- መወገድ ያለባቸው በርካታ የተለያዩ ወንበሮች፣ ጠረጴዛዎች፤ አሮጌ ቆርቆሮዎች፣ የተለያዩ ብረታ ብረቶች፣ የውሃ ፕላስቲኮች፣ የአጥር ሽቦዎች፣ የፍሳሽ ማስወገጃ ትቦዎች፣ አሮጌ ጎማዎች እና ፓኔሎች የሚገኙ መሆኑ፤

ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ

- ቋሚ ዕቃ ወጪ ላደረጉ ሠራተኞች የተጠቃሚ ካርድ/user card/ ያልተዘጋጀ መሆኑ፤

- ለቋሚ ዕቃዎች በተሟላ ሁኔታ መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፤
- በስቶክ ካርድ እና ቢን ካርድ የተሟላ ምዝገባ ያልተከናወነ መሆኑ፤
- የዕቃ ግዥ ከመፈፀሙ በፊት በንብረት ክፍል ለመኖሩና ላለመኖሩ/out of stock/ የሚረጋገጥበት አሰራር የሌለ መሆኑ፣
- በመግንባት ላይ ያለ ህንፃ ውስጥ በሚሰራው ሴንትራል ላይብረሪ በሞ/19 ገቢ የተደረጉ በርካታ አርምቼር፣ የቤተ-መፅሀፍት ጠረጴዛዎች እና የኮምፒውተር ጠረጴዛዎች ተገቢ ጥበቃ በሌለው ክፍት በሆነ ቤት ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፤
- በቋሚ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ አገልግሎት መስጠት የሚችሉትና የማይችሉት ተለይተው ያልተቀመጡ መሆኑ፤
- በንብረት ክፍል ገቢ ከተደረጉ ጀምሮ አገልግሎት ያልሰጡ ንብረቶች መኖራቸው (ለምሳሌ፡- 6 ሶኒ ቴፕሪከርደሮች፣ 12 ታይፕራይተሮች)፤
- በዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ምግብ ቤት የምግብ ማዘጋጃ ክፍል ውስጥ ከትምህርት ሚኒስቴር የመጡ ትልልቅ ስቶቮች፣ የወጥ ድስቶች፣ የዕቃ ማጠቢያ፣ የስጋ መፍጫ፣ ቤት መሰል ሶስት ፍሪጆች እና የመሳሰሉት ወደ ዩኒቨርሲቲው በ2004/05 የገቡ ቢሆንም ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤ በአዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ

<u>የዋናው ግቢ ቋሚ ንብረት</u>፤

- ቋሚ ንብረቶች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፤
- በ2005 በአቅራቢዎች ለናሙና የቀረቡ ብዛታቸው በትክክል ያልታወቀ ባለመደገፊያ ወንበሮች፤ በመመሪያው መሰረት ከ6 ወራት በላይ ያስቆጠሩ ቢሆንም ገቢ ያልተደረጉ መሆኑ፤
- የተለያዩ አሮጌ የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች በአንድ ትልቅ ግምጃ ቤት ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

<u>የዋናው ግቢ አላቂ ዕቃ</u>፤

- ለአላቂ ዕቃ ገቢና ወጪ መከታተያ ስቶክ ካርድ ቢኖርም ምዝገባው ከወጪ ቀሪ መነሻ ያላደረገ መሆኑ፤

- የገቢና የወጪ መከታተያ ስቶክ ካርዶች በቆጠራ ኮሚቴም ሆነ በውስጥ አዲት የማይዘጉ መሆኑ፤

<u>የዋናው ግቢ የመለዋወጫ ዕቃዎች፤</u>

- የመለዋወጫ ዕቃ ገቢና ወጪ መከታተያ ስቶክ ካርድ ቢኖርም ምዝገባው ከወጪ ቀሪ መነሻ ያላደረገ ከመሆኑም በተጨማሪ የተሟላ ምዝገባ የሌለ መሆኑ፤

<u>የጤና ሳይንስ ኮሌጅና የህይወት ፋና ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ቋሚና አላቂ ንብረት፤</u>

- በሆስፒታል የቋሚ፤ በጤና ሳይንስ ኮሌጅ ደግሞ የቋሚና አላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኞች ንብረት የመያዝና የማደል ሥራዎች ከሚያከናውኑት በተጨማሪ የንብረት ወጪ ደረሰኝ (ሞ/22) የማዘጋጀት ሥራዎች በተደራቢነት የሚሰሩ መሆኑ፤
- በሆስፒታል አላቂ ዕቃ፤ በጤና ሳይንስ ኮሌጅ ደግሞ የቋሚና አላቂ ንብረት ገቢ እና ወጪ መከታተያ (ስቶክ ካርድ) የተጀመረ ቢሆንም ምዝገባው የተሟላ አለመሆኑ፤
- በሆስፒታል በዕርዳታ የተገኙ የህክምና ዕቃዎች ዋጋቸው ሳይታወቅ ገቢ የሚደረጉ መሆኑ፤
- በጤና ሳይንስ ኮሌጅ የጤና ተማሪዎች መለማመጃ የህክምናና ላቦራቶር መሳሪያዎች ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤ (በ2007 የተገዙ Rectangular Laboratory Bench፤ Storage cabinet with Drawers፤ Fume hude Equipment Supply and installation የሚገኙ መሆኑ)፤
- የሆስፒታል እና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የ2008 በጀት ዓመት መጨረሻ የቋሚ ንብረቶች ቆጠራ ለሚመለከተው የሥራ ክፍል ኃላፊ ሪፖርት ያልተደረገ መሆኑ፤

<u>የጤና ሳይንስ ኮሌጅና ሕይወት ፋና ሆስፒታል መድኃኒት አያያዝና አጠባበቅ፤</u>

- ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ መ/ቤቶችና ድርጅቶች በዕርዳታ የተገኙ መድኃኒቶችና ህክምና የህክምና መገልገያዎች ዋጋቸው ሣይታወቅ ገቢ የሚደረጉ መሆኑ፤
- ድረጊስት በፈረቃ ሲቀያየሩ በተናጠል ወይም በጋራ ሊጠየቁበት የሚያስችል አሠራር የሌለ መሆኑ፤

- በኬዝ ቲም አስተባባሪዎች ለመድኃኒት ማደያዎች መድኃኒት ወጪ ከተደረገው ቀሪው ሪፖርት የሚደረግ ቢሆንም በሥራ ላይ የዋለው በትክክል ለታለመለት ዓላማ ለመዋሉ የሚረጋገጥበት አሠራር የሌለ መሆኑ፤
- በየፋርማሲዎች የኬዝ ቲም አስተባባሪዎች ከዋናው መድኃኒት ግምጃ ቤት ለመድኃኒት ማደያዎች (Dispensary room) ወጪ ያደረጉት መድኃኒት ከመድኃኒት አዳዮቹ (ድረጊስቶች) ጋር ርክክብ ካለመኖሩ በተጨማሪ መድኃኒቱን ወጪ ያደረጉት አስተባባሪዎች በተረኝነት እየሰሩ መድኃኒት የሚያድሉ መሆኑ፤
- የሆስፒታሉ የዋናው መድኃኒት ግምጃ ቤት ባለሙያዎች በየዓመቱ ሲቀያየሩ ርክክብ የሚፈፀም ቢሆንም ማስረከብ በሚገባቸው ልክ ለማስረከባቸው ትክክለኛነቱ የማይረጋገጥ መሆኑ፤ (ከ2007 ጀምሮ አሁን ያሉት 3ኛ ተረካቢ ወይም ተቀያሪ መሆናቸው)፤
- የህክምና ቋሚ ንብረት ኃላፊው በኃላፊነት ያልተረከቧቸው የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈ በርካታ መድኃኒቶች በግምጃ ቤቱ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤
- በጤና ሳይንስ ኮሌጅ በተማሪዎች መታከሚያ (ምርመራ ክፍል) ውስጥ የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያለፈ ዓይነታቸው እና ብዛታቸው የማይታወቅ በካርቶን የተቀመጡ መድሃኒቶች የሚገኙ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል።

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

<u>የዋናው ግቢ፤</u>

- የቋሚ ንብረት መመዝገቢያ ካርድ ያልተዘጋጀና ምዝገባ የማይከናወን መሆኑ፣
- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የአላቂና ቋሚ ንብረቶች ቆጠራ የተደረገ ቢሆንም የቆጠራ ውጤቱ በመዝገብ ከተመለከተው ከወጪቀሪ ጋር ያልተመሳከረ መሆኑ፤
- ለህንፃዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጠ እና ተመዝግበዉ ያልተያዙ መሆኑ፣
- ንብረት ክፍል ገቢ ተመላሽ የሚደረጉ ንብረቶች አዲስ ተገዝተዉ ከሚገቡ ንብረቶች ተለይተው ያልተጠበቁ መሆኑ፤
- የተለያዩ ፒቢሲዎች ለግንባታ ሥራ ከንብረት ክፍል ወጪ ተደርገዉ ያለአገልግሎት ሊሰባበሩ እና ሊሰረቁ በሚችሉበት ሁኔታ የተቀመጡ መሆኑ፤

- በደረሰኝ ቁጥር 841321 በቀን 06/03/2008 ከአልታ ኮምፒዩተር በብር 9,940,289.50 የተገዙ የኦል ኢን ዋን ዴስክቶፕ ኮምፒዩተሮች ከዋናዉ ንብረት ክፍል የአይሲቲ ንብረት ክፍል ሰራተኛ ወጪ ያደረጉ ሲሆን ለኮምፒዩተሮቹ ማስቀመጫ የሚሆን ቦታ ስለሌላቸዉ ንብረቶቹ በሌላ ግለሰብ እጅ ያለምንም ርክክብ የሚገኙ መሆኑ እና የተቀመጡበት ክፍል መስኮቶቹ መስታወት እና ፍርግርግ የሌላቸው በመሆኑ ንብረት ለማስቀመጥ ምቹ ባልሆነ ሁኔታ በአግባቡ ካለመቀመጡም በተጨማሪ ከአንድ ዓመት በላይ ያለምንም አገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤
- ከትምህርት ሚኒስቴር የመጡ ሁለት ሰንሎንግ አውቶቡስ እና ታታ አውቶቡስ ስራ ላይ ሳይውሉ ከሁለት እስከ ሶስት ዓመት ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ጎን ቆመዉ የሚገኙ መሆኑ፤
- የሚወገዱ የተለያዩ ዕቃዎች ያልተወገዱ መሆኑ፤
- በተጠቃሚዎች እጅ የሚገኙ ቋሚ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (UC) ላይ የዕቃዎቹ ዋጋ እና የተጠቃሚዉ ፊርማ የሌለ መሆኑ፤

የቴክኖሎጂ ኢንስቲትት፤

- የዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊው የዕቃ ገቢ ደረሰኝ /ሞደል 19/ የሚያዘጋጅ መሆኑ፣
- በዕቃ ግምጃ ቤቱ ቢንና ስቶክ ካርድ ያለ ቢሆንም ምዝገባ በወቅቱ የማይከናወን መሆኑ፣
- ከኢንስቲትዩቱ ቋሚ ዕቃ ለወሰዱ ሠራተኞች የቋሚ ዕቃ መቆጣጠሪያ ካርድ ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፤

የግብርናና እንስሳት ሕክምና ኮሌጅ፤

- ሁለት የውሃ ፓምፕ ማሽን ከአስር ዓመት በላይ በኮሌጁ በመቀመጡ ለብልሽት እየተዳረገ መሆኑ የሚገኝ መሆኑ፤
- በኮሌጁ የሚገኙ ሁለት ላንድሮቨር እና ዲፎርዲ ሳይወገዱ ዝናብና ፀሐይ እየተፈራረቀባቸው ለበለጠ ብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፤

የጅማ ዩኒቨርሲቲ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፤

- የንብረት ገቢ ደረሰኝ የማዘጋጀት እና ንብረት የመጠበቅ (የዕቃ ግምጃ ቤት ኃላፊነት) ሥራዎች በአንድ ሠራተኛ የሚከናወኑ መሆኑ፣
- በንብረት ክፍል ቢን ካርድ ያለ ቢሆንም በአግባቡ እና ወቅቱን በጠበቀ መልኩ የማይቀናነስ መሆኑ፤
- ከሶስት ዓመት በላይ ያለአገልግሎት የተቀመጡ በርከት ያሉ የሴት ጫማና አልባሳት በንብረት ክፍል የሚገኙ መሆኑ፤

የሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲ ኮሌጅ፤

- በንብረት ክፍል የንብረት ጸሃፊ ያልተመደበ መሆኑ፤
- የፎቶ ኮፒ ማሽኖች ከንብረት ክፍል ውጪ ተገቢው ጥንቃቄ ሳይደረግላቸው የተቀመጡ መሆኑ፣
- አዳዲስ ፕሮጀክተሮች ከሦስት አመት በላይ ያለአገልግሎት በንብረት ክፍል ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

የትምህርትና ስነ-ባህሪ ኮሌጅ፤

- በኮሌጁ ንብረት የሚያቀናንስ የስቶክ ኮንትሮል ባለሙያ የሌለ መሆኑ፣
- 205 አዳዲስ ዩፒኤሶች /UPS/ ከዋናው ስቶር በ2007 ዓ.ም የመጡ በኮሌጁ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤
- በ2007 ከዋናው ስቶር ወደ ኮሌጁ የተላኩ ብዛት 2005 ፈሳሽ ሳሙናዎች ከቋሚ እቃዎች ጋር የተቀመጡ ሲሆን አንዳንድ ፈሳሽ ሳሙናዎች በራሳቸው ጊዜ ፈንድተው እየፈሰሱ መሆኑ፤

የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ፤

- የኮሌጁ መዝገብ ቤትና ንብረት ክፍል በአንድ ቢሮ(ክፍል) ሥራቸውን የሚያከናውኑ መሆኑ፤
- በግምጃ ቤቱ የዕቃ ገቢና ወጪ መቆጣጠሪያ ስቶክ ካርድ ስራ ላይ ያልዋለ (የሌለ) መሆኑ፤
- አንድ አዲስ ማባዣ ማሽን ያለአገልግሎት ግምጃ ቤት ውስጥ የሚገኝ መሆኑ፤

የሕግና አስተዳደር ኮሌጅ፤

- ከሁለት ዓመት በፊት ንብረት ክፍል ገቢ የተደረጉ 168 UPS እና 4 ስካነር ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣
- ንብረት የመጠበቅና የንብረት ዐሐፊነት ሥራዎች በአንድ ሠራተኛ የሚከናወን መሆኑ፤

የከፍተኛ ትምህርት አግባብነትና ጥራት ኤጀንሲ

- መወገድ የሚገባቸው በርካታ የፕሪንተር ቶነሮች (cartridges) የሚገኙ መሆኑ፤
- የሚወገዱ በቁጥር 63 የመኪና ጎማዎች የሚገኙ መሆኑ፤
- የሚወገዱ ልዩ ልዩ ጠረጴዛዎች፣ ወንበሮች፣ ሽልፍና ልዩ ልዩ የመኪና መለዋወጫ እቃዎች የሚገኙ መሆኑ፤
- ለቋሚ እቃዎች መለያ ቁጥር ያልተሰጠ መሆኑ፤

ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ

ዋናው ግቢ

- በጣም ብዛት ያለቸው የማይሰሩና አገልግሎት የማይሰጡ ዕቃዎች ሳይወገዱ ለረጅም ጊዜ ከሌሎች አገልግሎት ከሚሰጡ ንብረቶች ጋር ተቀላቅለው መቀመጣቸው፣

ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ

- መወገድ ያለባቸው እቃዎች ለብዙ ጊዜ ሳይወገዱ በንብረት ክፍል ውስጥ ከሌሎች አገልግሎት ከሚሰጡ እቃዎች ጋር ተቀምጠው መገኘታቸው፣
- በ2008 በጀት ዓመታዊ አንዳንድ የንበረት ቆጠራና በቢን ካርድ ሚዛን መካከል ልዩነት መኖሩ (ምሳሌ መስተዋት በቆጠራ 77 የተገኘ ሲሆን በቢን ካርድ የተመለከተ ሚዛን 87 በመሆኑ በማነስ 10 የሚታይ መሆኑ)፣

ግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ

- ብዛት ያላቸው መወገድ ያለባቸው እቃዎች ለብዙ ጊዜ ሳይወገዱ በንብረት ክፍል ውስጥ ከሌሎች አገልግሎት ከሚሰጡ እቃዎች ጋር የተቀመጡ መሆኑ፣

ህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ

- የቋሚ ዕቃዎች ምዝገባ ያልተደረገና መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው መሆኑ፣

ይባብ ግቢ

- የስቶር ጥበት በመኖሩ አላቂና ቋሚ እቃዎች በአንድ ክፍል ተቀላቅለው መቀመጣቸው፣

ባህር ዳር ቴክኖሎጅ ኢንስቲትዩት

- በተቋሙ የሚገኙ የትምህርት ክፍሎች ንብረት ክፍል የንረት ግቢ እና ወጪ ደረሰኞችን (ሞ/19 እና ሞ/22) የማይጠቀሙ መሆኑ፣

የኢትዮጵያ ቴክስታይልና ፋሽን ዲዛይን ኢንስቲትዩት

- የንብረት ክፍል ቆርቆሮ በቆርቆሮ የተሰራ በመሆኑ ንብረቶች በቀላሉ ለዘረፋ የተጋለጡ መሆኑ፡
- በንብረቶች የተናጠል መመዝገቢያ ካርድ ላይ የንብረቶች ዋጋ የማይጠቀስ መሆኑ፣

ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲ

<u>ዋናው ግቢ</u>፤

- መወገድ ያለባቸው 391 አሮጌ ጎማዎች፣ 53 የተሸከርካሪ ባትሪዎች በንብረት ክፍል ተከማችተው መቀመጣቸው፣
- በቁጥር የማይታወቅ ብዛት ያለው የአርማታ ብረት መስክ ላይ ወድቆ ሳር የበቀለበት እና ወደ አፈርነት እየተቀየረ መሆኑ፣
- አንድ የቋሚ ዕቃ መጋዝን /ስቶር/ ቆርቆሮ በቆርቆሮ የተሰራ በመሆኑ በውስጡ የሚገኙ ንብረቶች በቀላሉ ለዘረፋ የተጋለጡና በውስጡ ከሚገኙ ንብረቶች 14 ቴሌቪዥኖች መሬት ላይ በመቀመጣቸው ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፣
- ለዋናው ንብረት ክፍል /ስቶር/ መስኮት ግሪል /ፍርግርግ/ ባለመሰራቱ ንብረቶች በቀላሉ ለዘረፋ የተጋለጡ መሆኑ፣
- የሚሰሩና የማይሰሩ የተለያዩ የምግብ ቤት ዕቃዎች በጊዜዊ የዕቃ ማስቀመጫ መጋዘን ውስጥ ተሰብስበው የተቀመጡ መሆኑ፣

ቡሬ ካምፓስ፤

- በቋሚነት የተዘጋጀ የንብረት ክፍል የሌለ በመሆኑ ሁኔታው ለንብረት አስተዳደር ችግር የፈጠረ መሆኑ፤
- የንብረት መዛግብቶችን ሥራ የማከናወን እና ንብረት የመያዝ ሥራ በአንድ ሰው የሚከናወን መሆኑ፣
- በቋሚም ሆነ በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ ቢን ካርድ የማይጠቀሙ መሆኑ፣
- የዕቃ መደርደሪያ ሼልፍ ባለመኖሩና ዕቃዎች መሬት ላይ በመቀመጣቸው ዕቃዎቹ በቀላሉ ለብልሽት እተጋለጡ መሆኑ፣
- በቁጥር ከ400 በላይ የሚሆኑ አሮጌ ፍራሾች በአንድ ክፍል ውስጥ በወለል ላይ የተቀመጡ በመሆኑ ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፣

የተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃ ግምጃ ቤት፤

- የተማሪዎች ምግብ ቤት ንብረት ክፍል ቆርቆሮ በቆርቆሮ የተሰራ በመሆኑ በቀላሉ ለዝርፊያ የተጋለጠ መሆኑ፤
- በቦታ ጥበት ምክንያት የተለያዩ የምግብ ግብዓቶች በአንድ ቦታ የተቀመጡና በቀላሉ ለብልሽት እየተጋለጡ ሆኖ መሆኑ፣
- በምግብ ማብሰያ ህንጻ ውስጥ ብዛት ያላቸው አሮጌ ጀሪካኖች ተሰብስበው የተቀመጡ በመሆኑ አካባቢያዊ ብክለት ሊፈጥሩ የሚችሉ መሆኑ፤
- በቡሬ ካምፓስ የተማሪዎች ምግብ ቤት ሞ/19 እና 22 እንዲሁም ንብረት ክፍል በአንድ ሰራተኛ እየተከናወነ መሆኑ፣

የተማሪዎች ክሊኒክ፤

- የመድሐኒት ማስቀመጫ ሼልፍ ትክክለኛ የመድሐኒት ማስቀመጫ ባለመሆኑ መድሐኒቶች በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ መሆኑ፣
- በክሊኒኩ ሞ/19 እና 22 እንዲሁም የመድሐኒት ክፍል ስራ በአንድ ሰራተኛ እየተከናወነ መሆኑ፤
- የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፉ የተለያዩ መድሐኒቶች ሳይወገዱ ተለይተው ለብዙ ጊዜ የተቀመጡ መሆኑ፤

- ለተማሪዎች ክሊኒክ አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ ፍሪጅ፤ ማይክርስኮፕ እና ፎቶ ሜትር እንዲገዙ ከ2 ዓመት በፊት ጀምሮ ቢጠየቅም ግዥ ባለመከናወኑ በአገልግሎት አሰጣጡ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ እያሳደረ መሆኑ፣ ታውቋል።።

ጎንደር ዩኒቨርሲቲ

<u>ሆስፒታል እና ጤና ሳይንሰ ኮሌጅ</u>፣

- በሆስፒታል አላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ ያለው የሰው ሃይል አደረጃጀት ሲታይ ክፍሉ እስቶክ ካርድ መዝገቢ፣ ዳታ ኢንኮደር፣ እስቶክ ኮንትሮለር የሌለው መሆኑ፣
- በርካታ የውሃ ማጠራቀሚያ ሮቶዎች፣ በረኪናዎች እና ሌሎች ብረታ ብረቶች በአላቂ እስቶር ውስጥ ለብልሽት ተደርገው ተከምረው እንዳሉ፣

<u>ዋና ግቢ ስፔር ፓርት ስቶር</u>፤

- በስቶሩ ውስጥ መወገድ ያለባቸዉ አሮጌ መለዋወጫዎች በብዛት ተከማችተዉ እንደሚገኝ፣
- አገልግሎት ሳይሰጡ ለረዥም አመታት በስቶር ዉስጥ ተከማችተዉ የሚገኙ መለዋወጫዎች መኖራቸውን፣
- ከተሽከርካሪ ጥገና በኋላ የተቀየረ አሮጌ የመለዋወጫ እቃ ተሟልቶ ወደ ስቶር ተመላሽ የማይደረግ መሆኑ፣

ወሎ ዩኒቨርሲቲ

የደሴ ግቢ የአላቂ ንብረት ክፍል፤

- የሚወገዱ ንብረቶች በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፣
- የፕሪንተር ቀለም ከሁለት አመት በላይ አገልግሎት ላይ ሳይውል በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ የሚገኝ መሆኑ፣
- ለጽዳት አገልግሎት የሚውሉ ከ700 በላይ የእጅ ጓንቶች ያለአገልግሎት በአላቂ ንብረት ክፍል ውስጥ እንደሚገኙ፣

የደሴ ግቢ የኬሚካልና የላብራቶሪ እስቶር፤

- መድሐኒቶች፣ የላብራቶሪ ዕቃዎች፣ የዲፈረንሻልና የካምቢዮ ዘይት ተቀላቅለው በአንድ ክፍል ወስጥ ጎን ለጎን ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፣

- የእስቶሩ ጣራ ክፍት በመሆኑ በቀላሉ ለስርቆት የተጋለጠ መሆኑ፣

የኮምቦልቻ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት የተማሪዎች ምግብ ቤት፤

- በትምህርት ሚ/ር አማካኝነት የመጡና አገልግሎት የማይሰጡ አራት በባዮ ጋዝ የሚሠሩ ባለ 4 መቀመጫ እስቶቮች፣ ሦስት በባዮ ጋዝ የሚሰሩ የምግብ ማብሰያ ድስቶች፣ 12 ባለ አንድ መቀመጫ በባዮ ጋዝ ሊሰሩ የሚችሉ እስቶቮች፣ ሦስት በኤሌክትሪክ የሚሰሩ የምግብ ማብሰያ ድስቶች፣ ስድስት በኤሌክትሪክ የሚሰሩ እስቶቮች፣ 12 የምግብ መግፊያ ድሮዌሮች፣ አንድ የሊጥ ማቡኪያ፣ አንድ ዳቦ መጋገሪያ ማሽን ለብልሽት ተዳርገው የተቀመጡ መሆኑ፣

የደሴ ግቢ የተማሪዎች ምግብ ቤት፤

- በባዮ ጋዝ ሊሰሩ የሚችሉ እስቶቮች፣ በኃይል እጥረት ሦስት በኤሌክትሪክ የሚሰሩ የምግብ ማብሰያ ድስቶች እና ስድስት በኤሌክትሪክ የሚሰሩ እስቶቮች ለብልሽት ተዳርገው መቀመጣቸው፣

ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ

<u>በዕቃ ግምጃ ቤት</u>

- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የአላቂና የቋሚ ንብረቶች ከወጪ ቀሪ ቆጠራ (Inventory) ያልተደረገ መሆኑ፤
- በንብረት መጠበቂያ መጋዘኖች ውስጥ የሚገኙት ዕቃዎች በሥርዓት ያልተቀመጡ መሆኑ፣
- በንብረት ስቶር ዉስጥ የንብረት መከታተያና መቆጣጠሪያ መዝገብ (ስቶክ ካርድ እና ቢን ካርድ) ያልተቋቋመ መሆኑ፤

<u>በተማሪዎች ክሊኒክ</u>

- መድሃኒቶች መከታተያና መቆጣጠሪያ መዝገብ (እስቶክ ካርድ እና ቢን ካርድ) ያልተቋቋመ መሆኑ፤
- በተማሪዎች ክሊኒክ ሚኒ-ስቶር ክፍል ውስጥ የተወሰነ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸዉ መድሃኒቶች ሳይወገዱ ተከማችተዉ የተቀመጡ መሆኑ፣
- በበጀት አመቱ መጨረሻ የመድሃኒት ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፤

አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ

- በሁሉም ካምፓሶች የቋሚ እቃ ቆጠራ ቢደረግ በሰራተኛ እጅ ያለው ንብረት ያልተቆጠረ መሆኑ፤
- በሁሉም ካምፓሶች በርካታ የተበላሹና አገልግሎት የማይሰጡ የተለያዩ እቃዎች መኖራቸው፤
- በውድ ዋጋ የተገዙ የተለያዩ አዳዲስ የመረጃና ኮምዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ /አይሲቲ/ እቃዎች ከዋና ግቢ ንብረት ክፍል ወጪ ሆነው ወደ ክፍሉ ሚኒ ንብረት ክፍል ሲገቡ በእቃ ገቢ ማድረጊያ ደረሰኝ ወይም ሞደል 19 ገቢ የማይደረግ መሆኑ
- ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የተበላሸ 176 ኩንታል አተር እና ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ የተበላሸ 17 ኩንታል ምስር ክክ ምንም አይነት የመፍትሄ እርምጃ ሳይወሰድባቸው በስቶር ውስጥ የተቀመጡ መሆኑ፣
- በብልሽት ምክንያት አገልግሎት ሳይሰጡ ለበርካታ አመታት በተማሪዎች የምግብ ማብሰያ ቦታ የተቀመጡ ስቶቮች፣ ቦይለሮች፣ የሊጥ ማቡኪያ፣ በጣም ትልቅ /ቄርሃውስ/ ፍሪጆች እና አገልግሎት የሰጡ ከ4000 በላይ የመመገቢያ ሳህኖች ያለመፍትሄ የተቀመጡ መሆኑ፣
- ከዋናው የመድኃኒት ስቶር መድኃኒት ወጪ ሆኖ ወደ ተማሪዎች ክሊኒክ በየካምፓስ መድሃኒት ስርጭት /እደላ/ ክፍል የገባው መድሃኒት ለመውጣቱ /ለመሰራጨቱ/ ከዋናው ግቢ የተማሪዎች ክኒሊክ በስተቀር በሁሉም ካምፓሶች መድሃኒት ስርጭት /እደላ/ ክፍል የመደኃኒት ቆጠራ ያልተደረገ እና በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ምን ያህል መድሃኒት እንደቀረ የማይታወቅ መሆኑ፤

አምቦ ዩኒቨርሲቲ

- በቋሚ እቃ ግምጃ ቤት፤ በተማሪዎች ምግብ ቤት ውሰጥ በርካታ ንብረቶችና ኬሚካሎች ሳይወገዱ ለብዙ ዓመታት ተከማችተው የተቀመጡ መሆኑ፤

ዲላ ዩኒቨርሲቲ

- የተለያዩ ህንፃዎች እንደቋሚ ንብረት በተለየ መዝገብ ላይ መመዝገብ ሲገባ በ2008 በጀት ዓመት እና ከዚያ በፊት ባሉት ዓመታት ርክክብ የተፈፀመባቸውና

ዩኒቨርስቲው የሚገለገልባቸው ሕንጻዎች እንዲሁም የጋራ መኖሪያ ቤቶች ያልተመዘገቡ መሆኑ፣

- ስራቸውን በፈቃዳቸው ለቀው የመልቀቂያ ደብዳቤ ባልወሰዱ የቀድሞ የዩኒቨርሲቲው የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች እጅ የሚገኙ 1 አፕል ፓድ፣ 1 አፕል ማርክ ቡክ፣ 15 ላፕ ቶፕና 2 ተደራራቢ አልጋዎች ተመላሽ ያልተደረጉ መሆኑ እና ባልመለሱ የስራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች ላይ ምንም ዓይነት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤
- የዩኒቨርሲቲው የስብሰባ አዳራሽ የእድሳት ስራው ተጠናቋል ተብሎ ርክክቡ ከተፈፀመ በኋላ ኮርኒሱ በመገነጣጠል ላይ ያለ መሆኑ፤ -የውኃ ፍሳሽ ማስተላለፊያ ቱቦዎች መገነጣጠላቸው፣የተገጠሙት የእንጨት በሮች በምስጥ የተበሉ መሆናቸውን እንዲሁም ከአዳራሹ ጋር አብሮ ተያይዞ የተገነባው የሠራተኞች መዝናኛ ክበብ ጣራ የሚያፈስ መሆኑ፤
- ከ1989 ዓ.ም ጀምሮ የአገልግሎት ዘመናቸው ያበቃ ለኬሚስትሪ እና ባዮሎጂ ትምህርት ክፍል ላብራቶሪ የሚያገለግሉ ኬሚካሎች እና መዳኒቶች ሳይወገዱ ለረጅም ጊዜ ተከማችተው መቆየታቸው፤

ሀዋሣ ዩኒቨርሲቲ

- በዋና ግቢ፣በወንዶ ገነት ደንና ተፈጥጥሮ ሀብት ኮሌጅ፣በወንዶ ገነት ደንና ተፈጥጥሮ ሀብት ኮሌጅ በርካታ እቃዎች ያለ አገልግሎት በመጋዘን ውስጥ መቀመጣቸው፤
- የተለያዩ ህንፃዎች እንደቋሚ ንብረት በተለየ መዝገብ ላይ መመዝገብ ሲገባ በ2008 በጀት ዓመት እና ከዚያ በፊት ባሉት የበጀት ዓመታት ርክክብ የተፈፀመባቸው ዩኒቨርስቲው የሚገለገልባቸው ሕንጻዎች እንዲሁም የጋራ መኖሪያ ቤቶች ያልተመዘገቡ መሆኑ፣

ደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ

- ለቢሮዎች፣ ለተማሪዎች ዶርምና ለመማሪያ ክፍሎች፣ ላይብረሪዎች፣ በየላብራቶሩ የሚገኙ የተለያዩ የላብራቶር መሳሪያዎችና ወንበሮች (ባለ 3 እግር) እና ሌሎች ለተለያዩ የሥራ ክፍሎች ለአገልግሎት መስጫ ወጪ የተደረጉ ቋሚ ንብረቶች የተሟላ መለያ ቁጥር ያልተሰጣቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ቁጥር

የተሰጣቸውም ቢሆን ቁጥሩ እየለቀቀ በስማቸው ላወጡአቸው ንብረቶች ራሳቸው ቁጥር የሚሰጡበት ሁኔታ መኖሩ፤

- በርካታ የተለያዩ አሮጌ ዕቃዎች በግምጃ ቤቱ ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ

- አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል የማተሚያ ማሽኖች ከነሙሉ አክሰሰሪዎቹ ጋር ቢኖሩም ተገቢውን አገልግሎት እየሰጠ አለመሆኑና በብልሽት ምክንያት አገልግሎት ሳይሰጥ ከ4 ዓመት በላይ የተቀመጠ የፎቶ ኮፒ ማሽን፣ ከ3 ዓመት በላይ የተቀመጡ 3 የማባዣ ማሽኖች በማባዣ ክፍሉ ውስጥ መኖራቸው፣
- በቋሚ፣ በመኪና መለዋወጫ ፣ የጽዳት እና የግንባታ እቃዎች ንብረት ክፍል ስቶክ ካርድ ስራ ላይ የዋለ ቢሆንም በየቀኑ እየተመዘገበ ከወጪ ቀሪ የማይገናዘብ መሆኑ ፣
- በዋናው ግቢ በርካታ የተማሪዎች የምግብ ጥሬ እቃና የማብሰያ እቃዎች ሳይወገዱ የተቀመጡ መሆኑ፤
- ከዋናው የምግብ ግብዓቶች ንብረት ክፍል የምግብ ጥሬ እቃ ወጪ ሆኖ ወደ ንኡስ የምግብ ጥሬ እቃ ንብረት ክፍል/ሚኒ ስቶር/ ሲገባ ገቢው በንብረት ገቢ ማድረጊያ ደረሰኝ /ሞ-19/ እንዲሁም ወጪ ሲሆን በንብረት ወጪ ማድረጊያ ደረሰኝ /ሞ/-22/ ወጪ የማይደረግ መሆኑ፣

መቀሌ ዩኒቨርሲቲ

- ርክክብ የተፈፀመባቸው ዩኒቨርስቲው የሚገለገልባቸው ሕንጻዎች እንዲሁም የጋራ መኖሪያ ቤቶች ያልተመዘገቡ መሆኑ፣ **የሀይደር ሪፈራል ሆስፒታል የንብረት መጋዘን፡-**
- የቋሚ እና አላቂ ዕቃዎች በአንድ መጋዘን መቀመጣቸው፣
- ብዛት ያላቸው በእርዳታ የገቡ መድኃኒቶችና የህክምና መሳሪያዎች ለአብነት 2.5 ኪ.ግ 56 ኦክስጅን፣ 3.21 ኪ.ግ $N_2O_2CO_2$ የሚባል በቁጥር 3፣ ዲስፈንክሽን ስቴርላይዜሽን የሚባል መሳሪያ፣ ዲኮስታር የሚባል መሳሪያ፣ በቁጥር 50 ብለድ ትራንስፈር ዲቫይስ የሚባሉ መሳሪያዎች፣ የህክምና ክፍል ለቀዶ ጥገና

አገልግሎት የሚውል መብራት፣ ለህክምና አገልግሎት የሚውል ፊሪጅ፣ የተለያዩ ለህፃናት ለደብተር መያዣነት አገልግሎት የሚውሉ ቦርሳዎችና ደብተሮች እንዲሁም የተለያዩ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያለፈና አገልግሎት የሚሰጡ መድኃኒቶች እና ሌሎችም የህክምና ዕቃዎችና መሳሪያዎች ሞዴል 19 ያልተቆረጠላቸውና ቢን ካርድ ሳይዘጋጅላቸው ከሌሎች ንብረቶች ጋር አብረው መቀመጣቸው፡

- **በጤና ሳይንስ ኮሌጅ**
  - በቋሚ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ መቀመጥ ያለባቸው 33 ላፕቶፖች በአላቂ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ መኖራቸው፣

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ዋናው ግቢ-

- የምግብ ጥሬ ዕቃዎች ንብረት መዝጋቢና ንብረት ጠባቂ ያልተለየ መሆኑ፤
- ተማሪዎች ለተግባር ልምምድ በተለያዩ ተቋሞች በሚሄዱበት ጊዜ ከትምህርት ክፍሉ ወይም ከተማሪዎች አገልግሎት ዲን ለተግባር ልምምድ ሲሄዱ ለምግብ ቤት ኃላፊ የሚያሳዉቁ ቢሆንም ወጥነት ባለዉ ሁኔታ መረጃ የማይተላለፍ መሆኑ፣
- ከዋናዉ የምግብ የምግብ ጥሬ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ስድስት ኩንታል የነቀዘ አተር ክክ ያልተወገደ መሆኑ፤በአዲት ቅኝት ወቅት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡
- ያልተወገዱ ልዩ ልዩ ንብረቶችን ለማስወገድ መርሃ ግብር ወትዶ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል ፡፡
- የምግብ ጥሬ ዕቃዎችን ንብረት መዝጋቢና ንብረት ጠባቂ ያልተለየ፤

8. <u>የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም</u>፤

የተሽከርካሪ አያያዝና አጠቃቀም ኦዲት ሲደረግ

8.1 **መዳወላቡ ዩኒቨርሲቲ**

ዩኒቨርሲቲው ካሉት 40 ተሽከርካሪዎች ውስጥ 28 ተሽከርካሪዎች የተገዙበት (በስጦታ የተሰጡበት) ዋጋ የማይታወቅ መሆኑ፤

8.2 አርሲ ዩኒቨርሲቲ

- ✓ 28 ተሽከርካሪዎች የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው መሆኑ፤
- ✓ የ7 ተሽከርካሪዎች የሻንሲ እና የሞተር ቁጥር የማይታወቅ መሆኑ፤
- ✓ 5 ተሽከርካሪዎች በከባድ ብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑና፤
- ✓ ዩኒቨርስቲው በመመሪያው መሰረት ተሽከርካሪዎቹ በአንድ ወጥ የመለያ ኮድ (ኢት) እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ ሲገባው 10 ተሽከርካሪዎች በኦሮ እና 2 ተሽከርካሪዎች ደግሞ በአሰ የሚንቀሳቀሱ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

8.3 ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ

- ✓ 1 ተሽከርካሪ (ሚኒባስ ኢት 4-20774) የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌለው መሆኑ፤
- ✓ 2 ተሽከርካሪዎች (ኒሳን ፒክአፕ ኢት 4-12998 እና ኢት 4-14195) ጌጃቸው የማይሰራ መሆኑ፤

ተሽከርካሪዎች (ኢት 4-12315፤ 4-17622፤ 4-14962፤ 4-17623) በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ተረጋግጧል፡፡

8.4 ድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ

- ✓ 1 ተሽከርካሪ (ሚኒባስ ኢት 4-20917) የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር (ሊብሬ) የሌለው መሆኑ፤
- ✓ 1 ተሽከርካሪ (ሚኒባስ ኢት 4-15563) እና 1 ሞተር ሳይክል (ኢት 4-0109) በብልሽት ምክንያት አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑ፤

8.5 ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ

- ✓ 4 ተሽከርካሪዎች የሠሌዳ ቁጥር የሌላቸው መሆኑ፤
- ✓ 14 ተሽከርካሪዎች የውጭ ጋራዥ የገቡ ሲሆን 4ቱ ከ6 ወራት እስከ 2 ዓመት የቆዩ መሆኑ፤
- ✓ የተቋሙ ተሽከርካሪዎች የተሟላ የህይወት ታሪክ ማህደር የሌላቸው መሆኑ፤
- ✓ ተሽከርካሪዎች በተቋሙ ጋራዥና በውጭ ለጥገና ሲገቡና ተጠግነው ሲወጡ የተሟላ ማስረጃ (መረካከቢያ) የሌለ መሆኑ፤
- ✓ አሮጌ ተመላሽ የመለዋወጫ ዕቃዎች መረካከቢያ የሌለ መሆኑ፤

- ✓ የመለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኛ ከግንቦት 1/2005 ጀምሮ ወደ ሌላ ሥራ ሲመደቡ በእጃቸው ያለው ንብረት እስካሁን ርክክብ ያልተፈፀመ መሆኑ፤
- ✓ በግቢ ውስጥ ለጥገና የቆሙና ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ ተሽከርካሪዎች መጠለያ የሌላቸው በመሆኑ ለበለጠ ብልሽት በሚዳርግ መልኩ ፀሐይና ዝናብ የሚፈራረቅባቸው መሆኑ፤

አክሱም ዩኒቨርሲቲ

- ✓ ስለዩኒቨርሲቲው ተሽከርካሪዎች ነዳጅ፣ ቅባትና ዘይት ፍጆታ አጠቃቀምም ሆነ በዩኒቨርሲቲው ሥር ስላሉት ተሽከርካሪዎች መረጃ በመመሪያው በተቀመጠው መሠረት ለሚመለከታቸው አካላት ሪፖርት የማይቀርብ መሆኑ፣

ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ

- ✓ **በዩኒቨርሲቲው አስተዳደር /ማዕከል/** 7 ተሽከርካሪዎች የኪ/ሜትር ጌጁ የማይሰራ መሆኑ፣
- ✓ **በኢትዮጵያ ቴክስታይል እና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት** አንድ ሚኒባስ ተሽከርካሪ በብልሽት ምክንያት ለብዙ ጊዜ የቆመና ሜዳላይ በመውደቁ ለበለጠ ብልሽ እየተዳረገ መሆኑ፣
- ✓ በአስተዳደር /ማዕከል/ 21፣ በባህር ዳር ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት 6 እና በኢትዮጵያ ቴክስታይል እና ፋሽን ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት 2፣ ባጠቃላይ 29 ተሽከርካሪዎች ክትትል ተደርጎ ቋሚ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ቁጥር/ሌብሬ/ ሊወጣላቸው ሲገባ ከ1 ዓመት በላይ በጊዜዊ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የቆዩ መሆኑ፣ በተጨማሪም ከነዚህ ተሽከርካሪ መኪናዎች ውስጥ፣
    - ➢ ኢት 4-18478 እና ኢት 4-18479 የሆኑ ተሽከርካሪ መኪናዎች በተሰጣቸው ጊዜያዊ የባለቤትነት ደብተር ላይ የሞተር ቁጥርና የቻንሲ ቁጥር የተቀያየሩ ሲሆን ከሚመለከተው አካል ጋር ተነጋግሮ ጉዳዩ እንዲስተካከል ያልተደረገ መሆኑ፣
    - ➢ በአስተዳደር /ማዕከል/ ኢት 4-18479 ሚኒባስ በወቅቱ ተጠግኖ መውጣት ሲገባ ከ1 ዓመት በላይ በሞኤንኮ ጋራዥ ውስጥ የቆመ መሆኑ፣
- ✓ የዩኒቨርሲቲው ተሽከርካሪዎች ለጥገና ወደ ጋራጅ ሲገቡ ውል የማይያዝ በመሆኑ እና መቼ እንደሚወጡ የጊዜ ገደብ በውል ስለሌለ ተሽርካሪዎች ለብዙ ጊዜ በጋራዥ ውስጥ

ቢዘገዩ ወይም በጋራዥ ውስጥ በተሸከርካሪዎች ላይ ችግር ቢፈጠር ውል ያልተገባ በመሆኑ በወቅቱ እንዳይጠገኑ ከማድረጉም በተጨማሪ በህግ ለመጠየቅ የማይቻል ሆኖ መገኘቱ፣

ጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ

- ✓ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-08711 መርቸዲስ አውቶቡስ እና የሰሌዳ ቁጥር ኢት 4-05683 ኤኔትሬ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ፍጆታ መከታተያ የኪ/ሜ ቆጣሪ ጌጅ የማይሰራ መሆኑ እና ተሽከርካሪዎቹ የሄዱበት ኪ/ሜ ተገምቶ ነዳጅ የሚሞላላቸው መሆኑ፣

አርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ

- የሰሌዳ ቁጥር 4-01269 አይሺኮ መ/አውቶቢስ፣4-20767 ታታ አውቶቢስ፤ 4-17648 ሚኒ ባስ፤ 4-13989 አውቶሞቢል፤ 4-19898 አምቡላንስ፤ 4-14609 ቱርቦ ባስ፤ 4-21823 ኮስትር ባስ እና 4-1013 ያማሃ ሞተር ሳይክል የባለቤትነት መታወቂያ /ሊብሬ/ ደብተር የሌላቸው መሆኑ፣
- በጥገና ክፍሉ ዘመናዊ የተሽከርካሪ መጠገኛ ማሽኖች ቢኖሩም በጥቂት መለዋወጫ እቃዎች ችግር እና በባለሙያ እጥረት ሙሉ በሙሉ ወደ አገልግሎት ያልገቡ መሆኑ፣

በጥገና ክፍል ግቢ ውስጥ ያለምንም አገልግሎት ለረጅም ጊዜ ለፀሃይና ለዝናብ ተጋልጠው በብልሽት የቆሙ ግሬደር፤ ሩሎ፤ ዳምፐር፤ ስካቨተር እንዲሁም 2 የኤሌክትሪክ ኃይል የሚያመነጩ ጄኔሬተሮች፤ ለእርሻ አገልግሎት የሚውል የውሃ ጄኔሬተር እና በጥገና ክፍል ውስጥ 9 የሚሆኑ አዳዲስ የሶላር ዕቃዎች የሚገኙ መሆኑ፤

ዲላ ዩኒቨርሲቲ

- ✓ በቀላል እና ከባድ ብልሽት ምክንያት 25 ተሽከርካሪዎች አገልግሎት እየሰጡ አለመሆኑ፤

ሀዋሣ ዩኒቨርሲቲ

ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ የኮሌጁ ተሽከርካሪዎች ለብዙ አመታት ፀሐይና ዝናብ እየመታቸው ሳይወገዱ ያለ ምንም አገልግሎት የተቀምጡ 16 መኪኖች የዩኒቨርሲቲው የግብርና ኮሌጅ ቅጥር ጊቢ ውስጥ የሚገኙ 19 የተለያዩ ተሽከርካሪዎች ሳይወገዱ ለረጅም ጊዜ ያለ አገልግሎት መቀመጣቸው፤

ትምህርት ሚኒስቴር

የባለቤትነት መታወቂያ ካርድ የሌለውና ታርጋ ያልተሰጠው አዲስ ተሽከርካሪ የመለዋወጫ እቃ የለም በሚል ከአምስት አመት በላይ አፍሪካ ሌክስ ጋራዥ ውስጥ ቆሞ የሚገኝ መሆኑ፤

መቀሌ ዩኒቨርሲቲ

የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ከሌላቸው ተሽከርካሪ መኪናዎች ውስጥ 3ቱ የሰሌዳ ቁጥራቸው ወደ መንግሥት ተሽከርካሪ መኪና ኮድ (ኮድ 4) ያልተቀየረና በኮድ 5 ያለ መሆኑ፣ ታውቋል፡፡

9. **<u>ባለፉት ዓመታት አዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ</u>፤**

9.1 **ጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲ**

<u>2007 በጀት ዓመት አዲት የተገኙ ግኝቶች</u>፤

- **በእጅ በእጅ ሽያጭ ፋክቱር የተወራረደው ብር** 1,788,526.00 **የቫት ደረሰኝ እንዲቀርብለት ያልተደረገ መሆኑ፤**
- **ተቋሙን ለለቀቁ ሠራተኞች አላግባብ የተከፈለው ብር** 17,563.86 **ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤**

9.2 **ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ**

<u>በ2004 በጀት ዓመት አዲት የተገኙ ግኝቶች</u>፤

- **ከኮንስትራክሽን ድርጅቶች የሚፈለግ የሲሚንቶ ብድር ብር** 2,245,974.10 **ተቀንሶ ክፍያ እንዲፈፀም የኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት የገለፀ ቢሆንም የፋይናንስ ክፍሉ ሳይቀንስ ክፍያ መፈፀሙ፤**
- **ዩኒቨርሲቲው በገቡት ውል መሰረት የግንባታ ስራቸውን ያላጠናቀቁ የሥራ ተቋራጮች የጉዳት ካሳ ብር** 17,320,938.60 **እንዲከፍሉ ያላደረገ መሆኑ፤**

<u>በ2007 በጀት ዓመት አዲት የተገኙ ግኝቶች</u>፤

- **የክፍያ ማስረጃ ያልቀረበለት ብር** 62,628.53 **ገንዘቡ ወደ ባንክ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤**
- **ብር** 141,472.14 **የደመወዝ ብድር በተሰብሳቢ ሂሳብ አለመያዙ፤**

በገቡት ውል መሰረት አቅራቢዎች ባለመፈፀማቸው ብር 311,878.79 የጉዳት ካሳ እንዲከፍሉ ያልተደረገ መሆኑ፤

9.3 ጅማ ዩኒቨርሲቲ

በ2006 በጀት ዓመት አዲት የተገኙ ግኝቶች፤

- ለህብረተሰብ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ እስፔሻሊስቶች በየወሩ 58 ሰዓት የስራ ክብደት እና ማበረታቻ በሚል ከመመሪያ ውጪ የተከፈለው ብር 3,683,558.00 ተመላሽ ያልተደረገና አሰራሩ ያልተቋረጠ መሆኑ፤
- የኮሚቴ አባላት የጨረታ ዶክመንት ያዘጋጁበት በሚል ብር 225,281.77 እና የሪፈራል ሆስፒታል ሠራተኞች የቁሳቁስ ግዥ በርካታ ውስብስብ ስራዎች በእረፍት ጊዜያቸውና የበዓላት ቀንን ጨምሮ ለሰሩበት በሚል ብር 34,879.16፤ በድምሩ ብር 260,160.93 አላግባብ የተከፈለው ገንዘብ ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

በ2007 በጀት ዓመት አዲት የተገኙ ግኝቶች፤

- በዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ በወጪ ለተመዘገበው ብር 17,107,718.00 የክፍያ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ፤
- ዕቃው ገቢ መደረጉን የሚገልጽ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ሳይቀርብለት በወጪ ለተመዘገበው ብር 3,169,680.00 የዕቃ ገቢ ደረሰኝ (ሞ/19) ያልቀረበ መሆኑ፤
- ዩኒቨርሲቲው ከተለያዩ የህንፃ ሥራ ተቋራጮች ጋር 1,508,271,870.04 ዋጋ ያላቸዉ በቁጥር 9 የመኖሪያና መኖሪያ ያልሆኑ ህንፃዎች ግንባታ ለማከናወን ውል የገባ ሲሆን ግንባታዎቹ ከ45 እስከ 1301 ቀናት የዘገዩ ቢሆንም ተቋራጮቹ ላዘገዩበት ቀናት በገቡት ውል መሰረት ብር 147,652,432.00 ቅጣት መክፈል ሲገባቸው ያልከፈሉ መሆኑ፤
- ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 30/10/2007 ዓ.ም ድረስ በተለያዩ ጊዜ ለትምህርት ወደ ውጪ ሀገር ተልከው ካልተመለሱ ሰራተኞች እና መ/ቤቱን በተለያየ ምክንያት ከለቀቁ ሰራተኞች ያልተሰበሰበ ብር 368,999.14 ገቢ መደረጉን የሚገልጽ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

9.4 አክሱም ዩኒቨርሲቲ

በ2007 በጀት ዓመት አዲት የተገኙ ግኝቶች፤

- የትርፍ ሰአት ላስተማሩት የህክምና ዘርፍ ረዳት ፕሮፌሰሮች በክሬዲት አወር (credit hours) ብር 120.00 መከፈል ሲገባ ብር 400.00 በመከፈሉ ከተፈቀደው መጠን በላይ በድምሩ ብር 77,840.00 ያለአግባብ በብልጫ መከፈሉ፣
- በዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች ተረጋግጦ በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ገቢ የተደረገ በቁጥር አንድ ሳውንድ ፕሩፍ ጀኔሬተር ብር 4,499,700.00 የተከፈለበት ቢሆንም ሌሎች የዩኒቨርሲቲው ባለሙያዎች እንደገና በረጋገጡት መሰረት ዕቃው በውሉ ላይ በተገለጸው ዝርዝር (specification) መሰረት አለመሆኑ ስለተረጋገጠ ዩኒቨርስቲው ለከፈለው ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም ማግኘቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፣
- ግንባታዎችን ውል ከገቡበት የማጠናቀቂያ ጊዜ በላይ ካዘገዩ ኮንትራክተሮች መሰብሰብ የነበረበት ብር 21,163,962.31 የጉዳት ካሳ አለመሰብሰቡ፣

9.5 ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ

በ2007 በጀት ዓመት አዲት የተገኙ ግኝቶች፤

- በበጀት ዓመቱ መጨረሻ በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ ብር 11,217.53 በማነስ የታየ መሆኑ፣
- ብር 747,574.31 የተጨማሪ እሴት ታክስ ያለአግባብ ለገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ተከፍሎ መገኘቱ፣

ሶስት የዩኒቨርሲቲው ሰራተኞች የኮምፒውተርና የቢሮ መገልገያዎችን ሳያስረክቡ የለቀቁ መሆኑ፣ በሚሉ የ2007 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

9.6 ጎንደር ዩኒቨርሲቲ

በ2006 በጀት ዓመት አዲት የተገኙ ግኝቶች፤

- አለአግባብ የተከፈለ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ብር 310,320.0 ተመላሽ መሆን ሲገባው ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፣

- ለICT እና ምህንድስና ባለሙያ ሰራተኞች ማትጊያ መመሪያው ከሚፈቅደው ውጪ ከተመን በላይ በድምሩ ብር 94,000 ክፍያ የተፈፀመ እና መመለስ የሚገባው ገንዘብ ተመላሽ አለመደረጉ፣
- ከዩኒቨርሰቲው የውስጥ ገቢ ለመምህራን ከደንብና መመሪያ ውጭ የተፈከለ የቤት አበልና የኃላፊነት አበል ክፍያ ብር 1,234,064.35 ተመለሻ መሆን ሲገባው ተመላሻ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ለተለያዩ የኮሚቴ አባላት ለእያንዳንዳቸው ብር 5,000.00 እንዲሁም ለሁለት የኮሚቴ አባላት ለእያንዳንዳቸው ብር 2,500.00፣ በድምሩ ብር 35,000.00፣ ለንብረት አስወጋጅ ኮሚቴ አባላት ብር 29,100.00፣ በጠቅላላው ብር 64,100.00 ያለአግባብ የተከፈለ የማበረታቻ ክፍያ ተመላሽ መሆን ሲገባ ተመላሽ አለመደረጉ፣
- በ4201 በተሰብሳቢ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀር 0048 የተመዘገበው ሂሳብ ብር 1,957,491.28 ከ1998 ጀምሮ ከስምንት አመት በላይ በመክፍቻ ሂሳብ /Opening balance/ የሚታይ መሆኑ፣ ሂሳቡ እንዲሰረዝ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጥያቄ መቅረቡና ሂሳቡን የማስመለስ ስራ እየተከናወነ ቢሆንም አሁንም የማስተካከያ እርምጃው በከፊል የሚቀር መሆኑ፣በ4273 የሂሳብ መደብ ብር 1,511,994.10 በተቀጽላ ሌጀር 0009 በመክፈቻ ሂሳብ /Opening balance/ ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን ወይም ክሬዲት የሚታይ ከመሆኑም በላይ የእቃ ግዥ ሰራተኞች ሂሳባቸውን አዲት ሳያስደርጉ ከዩኒቨርሲቲው የለቀቁ መሆኑን እና በተሰብሳቢ ሂሳብ የሚታይባቸውን ሂሳብ የማስመለስ ስራ እየተከናወነ ቢሆንም አሁንም የማስተካከያ እርምጃው በከፊል የሚቀር መሆኑ፣
- በ4273 የሂሳብ መደብ በመክፍቻ ሂሳብ /Opening balance/ በተለያዩ ተቀጽላ ሌጀሮች የተያዘ በድምሩ ብር 5,755,686.35 ምንም አይነት እንቅስቃሴ የሌለው መሆኑ፣ በ2008 በጀት ዓመትም ሂሳቡ በተሰብሳቢ ተይዞ መገኘቱን፤

<u>በ2007 በጀት ዓመት አዲት የተገኙ ግኝቶች፤</u>

- ዩኒቨርሰቲው ለገቢ ማመንጫነት ያቋቋማቸው ጃንተከል ማተሚያ እና ብሩህ ሆቴል ልዩ ልዩ ስራ መተዳደሪያ ደንቦችና መመሪያዎች በቦርድ መጽደቅ ቢገባም ያልፀደቀ መሆኑ፣

- በሆስፒታል ተፈላጊውን የሥራ ልምድ ሳያሟሉ ተመድበው ስለሚሰሩ ሠራተኞች የማስተካከያ እርምጃ መወሰድ ቢገባም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

9.7 ወሎ ዩኒቨርሲቲ

<u>በ2006 በጀት ዓመት ኦዲት የተገኙ ግኝቶች፤</u>

- በደሴ ካምፓስ በተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 914,211.82 ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን ዩኒቨርሲቲው በግል የውጪ ኦዲተሮች ሂሳቡን ለማጥራት ሂደት ላይ መሆኑ አንድ እርምጃ ቢሆንም ሂሰቡ ተጣርቶ የማስተካከያ እርምጃ ያልተሰራለት መሆኑ፤
- በኮምቦልቻ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ 4101-0003 ተቀጽላ ሌጀር ብር 300,886.74 ያልተለመደ የሂሳብ ሚዛን ወይም ክሬዲት ዩኒቨርሲቲው በግል የውጪ ኦዲተር ሂሳቡን ለማጥራት ሂደት ላይ ቢሆንም ሂሰቡ ተጣርቶ የማስተካከያ እርምጃ ያልተሰራለት መሆኑ፤
- በደሴ ካምፓስ በጀት ዓመቱ መጨረሻ በገንዘብ ያዞች እጅ በቆጠራ የተገኘው የጥሬ ገንዘብና ሰነድ ድምር ብር 37,695.00 ሲሆን በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት ከተደረገው በእጅ ያለ ጥሬ ገንዘብ ብር 365,128.34 ጋር ሲነጻጸር በሪፖርት የተመለከተው በእጅ ያለ ጥሬ ገንዘብ በብልጫ ብር 327,433.34 ዩኒቨርሲቲው በውጪ የግል ኦዲተር ሂሳቡን ለማጥራት በሂደት ላይ መሆኑ አንድ እርምጃ ቢሆንም ሂሰቡ ተጣርቶ የማስተካከያ እርምጃ ያልተሰራለት መሆኑ፤
- ብር 518,963.60 ለደሴ ሪፈራል ሆስፒታል ሃኪሞች እና ለደሴ ዩንቨርሲቲ መምህራን ክሊኒካል አሎዋንስ በሚል አላግባብ የተከፈላቸዉ ዩኒቨርሲቲው ክፍያው እንዲቆም ማስደረጉ አንድ እርምጃ ቢሆንም አለአግባብ የተከፈለው ክፍያ ተመላሽ ያልሆነ መሆኑ፤
- በደሴ ካምፓስ የዋጋ ኤንዴክስ ከሚሰጠው አካል ወቅታዊ መረጃ ሳይቀርብ አማካሪ መሐንዲሱ ባቀረበው የዋጋ ኢንዴክስ መረጃ መሰረት ብቻ ብር 414,966.48 ፋል ትሬዲንግ ጠቅላላ ስራ ተቋራጭ የዋጋ ማስተካከያ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ ማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፣

በ2007 በጀት ዓመት አዲት የተገኙ ግኝቶች፤

- በደሴ ግቢ በጥሬ ገንዘብ ቆጠራ የተገኘዉ ብር 597.10 ሲሆን በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገዉ ብር 293,393.51 በመሆኑ ብር 292,796.41 በብልጫ ሪፖርት መደረጉ፣ እንዲሁም በኮምቦልቻ ካምፓስ በጥሬ ገንዘብ የተቆጠረዉ ብር 4,071.00 ሲሆን በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት የተደረገዉ ብር 161,048.96 በመሆኑ ብር 156,977.18 በብልጫ ሪፖርት መደረጉ፣ በጠቅላላ ድምር 449,773.59 በብልጫ ሪፖርት የተደረገበት ተገቢው የማስተካከያ ማሰረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- በደሴ ካመፓስ በ4101 ብር 816,686.04 በተቀፅላ ሌጀር የተገኘው ገንዘብ የገንዘብ ያዥ ስም ተጣርቶ ያልቀረበ መሆኑ፣
- በዩኒቨርሲቲው በሁለቱም ግቢ ለለቀቁ ሠራተኞች ከተከፈልና ተመላሽ መደረግ ካለበት ደመወዝ ብር 36,419.87 ውስጥ ብር 2,275.68 ብቻ ተመላሽ መደረጉ፣
- በምግብ ግብዓት ላይ የዋጋ ማስተካከያ ለመደረጉ ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር የውል ስምምነት ሳይደረግ እና በወቅቱ በምርቶቹ ላይ የዋጋ ጭማሪ ለመደረጉ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ሳይቀርብ በድምሩ ብር 41,805.50 በብልጫ ተከፍሎ መገኘቱን፤
- ከኦይል ሊቪያ እና ከቶታል ነዳጅ ማደያዎች ለተገዛው ነደጅ ክፍያ ሲፈጸም በቅድመ ክፍያ ተይዞ እያንዳንዱ መኪና የተጠቀመበት የነዳጅ መጠን ሲረጋገጥ በወጪ መመዝገብ ሲገባው ለተሸከርካሪዎች ነዳጅ በትክክል ለመሞላቱ ተገቢው ማስረጃ ሳይቀርብ በድምሩ ብር 4,646,850.00 በወጪ ተይዞ መገኘቱ፤
- የአዳራሽ ወንበሮች ለተሰሩበት ለጳጉሜ ኢንዱስትሪያል ኮሜርሻል ኃ/የተ/የግ/ማህበር ብር 342,902.40 በሚመለከተው ኃላፊ ሳይፈቀድ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑን፤

ዩኒቨርስቲው ከGIZ-IS የግንባታ ሥራዎች አስፈፃሚ ድርጅት ከተረከባቸው ያልተጠናቀቁ ግንባታዎች መካከል፤ ከኦርቢት ኢንጅነሪንግ፤ ከፋል ጀነራል ትሬዲንግ እና ከተለያዩ የኮብልስቶን ማህበራት የሰነድ ርክክብ ሲደረግ፣ ለእያንዳንዱ ሥራ ተቋራጭ በቅድሚያ የተከፈለው ጥሬ ገንዘብ፤ በተሰብሳቢ ተይዞ የሚገኘው ቅድሚያ ክፍያ፤ ለእያንዳንዱ ሥራ ተቋራጭ በቅድሚያ የተሰጡ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ዓይነት፤ ብዛት እና ዋጋ፤ ከተቋራጮች በገንዘብ ተመላሽ የተደረገ የዕቃዎች ዋጋ፤ ያልተከፈለ ቀሪ ዕዳ፤ እንዲሁም እያንዳንዱ ስራ ተቋራጭ ለሚያከናውናቸው ግንባታዎች በመያዣነት ገቢ ያደረገው የመልካም ስራ ዋስትና

ገንዘብ በእያንዳንዱ ስራ ተቋራጭ ስም እንዲመዘገቡ ባለመደረጉ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አለመቻሉን፤ ይህ ግኝት በ2007 በጀት ዓመት አዲት የማሻሻያ ሀሳብ ተሰጥቶበት የነበረ ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑ፣

9.8 ዲላ ዩኒቨርሲቲ

<u>የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ አዲት ግኝቶች፤</u>

- ጤና ሳይንስ ኮሌጅ እና ሪፈራል ሆስፒታል እና በዋናው ግቢ ለአስተዳደር ሰራተኞች ማለትም ለፋይናንስ፣ ለሰዉ ሃብት ልማት፣ ለጥበቃ ሰራተኞች፣ ለሬጅስትራር እና ለመሳሰሉት በየወሩ ክፍያ እንደሚፈፀም የታወቀ ሲሆን በጠቅላላው ድምር ብር 919,473.07 ያለአግባብ ሚኒስተር መስሪያ ቤቱ ለመፍቀዱ ማስረጃ ሳይኖር የተከፈለው ትርፍ ሰዓት ክፍያ ተመላሽ ያልሆነ መሆኑ፤
- በናሙና ከተመረጡት የወጪ ሰነዶች ውስጥ ብር 2,054,486.48 የሆኑ የወጪ ሂሳብ ሰነዶች ለአዲት ባለመቅረባቸው በወጪ የተመዘገበው ሂሳብ ለታለመለት ዓላማ ለመዋሉ ለማረጋገጥ ያለመቻሉን፤
- ብር 694,006.65 በየወሩ ለመስሪያ ቤቱ የስራ አመራር አባለት በማኔጅመንት ውሳኔ ከደንብና መመሪያ ውጪ የተከታታይ ትምህርት እና TDP ማበረታቻ የተከፍለ ክፍያ ተመላሽ ያለመሆኑ፤
- በጤና ሳይንስ ኮሌጅ ሪፈራል ሆስፒታል የተረኝነት አበል በሚል በየወሩ ከብር 3,333.00 እስከ 4,000.00 ከደንብና መመሪያ ውጪ የተከፈለው ብር 1,309,953.00 ተመላሽ ያለመሆኑ፤
- በስራ ገበታቸው ሰይገኙ የመምህራን እና ለአስተዳደደር ሰራተኞች ድምር ብር 65,283.13 የተከፈለ እና ከአንድ ወር በላይ ደመወዝ የተከፈላቸው ብር 11,388.00 ተመላሽ ያለመሆኑ፤
- በዩነቨርሰቲው ከደንብና መመሪያ ወጪ የተከፈል የተረኝነት አበል ብር 2,066,015.67 ተመላሽ ያለመሆኑ፤
- ዩኒቨርሲቲው ለተለያዩ የምግብ ግብዓቶች ከቃሊቲ ምግብ አ/ማ የተከፈለ፣ ከሎሜ አዳማ የግ/ህ/ስ/ማ ዩኒየን እና ለለምለም የዳቦ መጋገሪያ ለተከፈለው ብር 9,103,756.20 የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ያልቀረበ መሆኑ፤

- ለለአሮር ጉዞ፣ ለዉይይት እና ለስልጠና ተገቢው ማስረጃ ሳይቀረብ ለተከፈለ ውሎ አበል ብር 568,090.00 ተመላሽ ያለመሆኑ፤
- ከተለያዩ ዩኒቨርሰቲው ሠራኞች ከደመወዝ እና ጥቅማጥቅም ክፍያ መቀነሰ የነበረበት የስራ ግብር ብር 84,689.13 ተቀነሶ ለሚመለከተው አካል ገቢ ያለመደረጉ፤

<u>የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ አዲት ግኝቶች</u>

- ብር 29,654,748.63 የገንዘብ መቀበያ ደረሰኝ፣ የሽያጭ ደረሰኝ እና ህጋዊ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ መገኘቱ፣
- ብር 16,735,379.14 የዋጋ ማስተካከያ፣ የለውጥ ሥራ እና የተጨማሪ ሥራ በሚል በነባር ፕሮጀክት በትምህርት ሚ/ር እና በኤም.ኤች.ኢንጂነሪነግ አማካኝነት ቀሪው በዩኒቨርሰቲው ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያ ተፈጽሞ መገኘቱ፣
- ብር 16,142,260.00 የሚያወጣ ዩኒቨርስቲው ለማሕበራት በብድር ለሰጠው ጤፍ ከሚከፈላቸው የእነጀራ ዋጋ ተቀንሶ ገቢ ለመደረጉ ማስረጃ ባለመቅረቡ ስለትክክለኝነቱ ማረጋገጥ አለመቻሉን፣
- ብር 3,798,720.53 በሥራ አመራር ካውንስል ውሰኔ ለተለያዩ የኮሚቴ አባሎች፣ ኃላፊዎች እና ሌሎች የአስተዳደር ሠራተኞች ማበረታቻና የትራንስፖርት አበል በሚል ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ መገኘቱ፣
- ብር 3,709,426.53 የተከፈለ እና የወጪ ሰነዶች ለክልሉ ትምህርት ቢሮ እንደተላከና ሰነዱን ማቅረብ እንደማይቻል ስለተነገረን የወጪውን ትክክለኝነት ማረጋገጥ አለመቻሉን፣
- ብር 1,947,778.29 ዩኒቨርሰቲው ከአቅራቢዎችና ከተቋራጮች የሰበሰበውን ታክስ ለሚመለከተው አካል ገቢ ሳያደርግ መገኘቱ፣
- ብር 1,396,665.35 ለመፈተንና ለማማከር ለመጡ መምህራን፣ የዓመት እረፍታቸውን በደመወዝ በመቀየር እና የዋጋ ተማኞች በሚል በሥራ አመራር ውሳኔ ባልተፈቀደ በጀት እና ከደንብና መመሪያ ውጭ ተከፍሎ መገኘቱ፣
- ብር 756,859.84 ዝቅተኛ ዋጋ ከአቀረበ ድርጅት ባለመግዛቱ በልዩነት ተከፍሎ መገኘቱ፣

ብር 109,782.5 ከዕቃ አቅራቢዎች መስብሰብ ያለበት የቅጣት ሂሳብ ሳይሰበሰብ መገኘቱ፣

9.9 ሀዋሣ ዩኒቨርሲቲ

<u>የ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ አዲት ግኝቶች፤</u>

- ብር 97,384,001.29 ከውስጥ ገቢ ሂሳብ የተሰበሰ ለግንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈስስ መደረግ የነበረት ሂሳብ ፈሰስ አለመደረጉ፤
- በኃላፊነት ላይ ላለ የአስተዳደር ሠራተኞች፣ ለቴክኒክ ኢንስቲትዩት አለአግባብ የተከፈለ የቤት አበል እና ጥቅማ ጥቅም ብር 1,622,360.46 ተመላሽ አለመሆኑ፤

<u>የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብ አዲት ግኝቶች</u>

- ለመምህራን ከተከፈለው የትርፍ ሰዓት ክፍያ የሥራ ግብር መቀነስ ቢኖርበትም ዩኒቨርስቲው በራሱ ብር 169,941.00 ታክስ ሸፍኖ መገኘቱ፤
- ዩኒቨርስቲው የኮሌጅ ኃላፊዎች ውስጥ ለሚገኙ የአስተዳደር ሠራተኞች በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ፈቃድ ሳይገኝ የቤት አበል በጤና ሳይንስ እና ሪፈራል ሆስፒታል ብር 53,601.75 እና በወንዶ ገነት ኮሌጅ ብር 15,300.00 በድምሩ ብር 68,901.75 የቤት አበል መከፈሉ፤

ከመምህራን ከሚከፈላቸው መቀነስ የነበረበት የሥራ ግብር ብር 237,596.85 በዩኒቨርሰቲው መሸፈኑ፤

9.10 ወላይታ ዩኒቨርሲቲ

<u>በ2007 የአዲት ግኝት ላይ የተገኙ፤</u>

- ለጤና ሣይንስ ኮሌጅ የህክምና ባለሙያዎች፣ የትምህርትና የአስተዳደር ስራን በማስተባበርና በመስራት ለተሳተፉ ሰራተኞች እና ኃላፊዎች በድምሩ ብር 1,618,689.46 ለማበረታቻ (ቶፕ አፕ) እና የማስተባበር ስራ ለሰሩበት በሚል ያላግባብ ከደንብና መመሪያ ውጪ የተከፈለ ክፍያ፣
- ለትምህርት በመንግሥት ወደ ውጭ ሃገር የተላኩ ሠራተኞች ሙሉ ደመወዛቸው በመከፈሉ በድምሩ ብር 93,117.00 ከመመሪያ ውጭ አላግባብ በብልጫ የተከፈለ፣
- በዩኒቨርሲቲው የመንግስት የጋራ መኖርያ ቤት ለተሰጣቸው መምህራን በየደረጃው ከሚገባቸው የቤት አበል ላይ ለመኖሪያነት የተሰጣቸው ቤት ዋጋ ግምት ተቀንሶ ልዩነቱ በጥሬ ገንዘብ አላግባብ በድምሩ ብር 126,500.00 የተከፈላቸው መሆኑ፣

በውሉ መሠረት ሳይጠናቀቁ ከዘገዩ ሌሎች ግንባታዎች ለዩኒቨርሲቲው ገቢ መሆን የነበረበት በድምሩ ብር 15,329,482.39 የጉዳት ካሳ ለዩኒቨርሲቲው ገቢ አለመደረጉ፤

በልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት

የ2008 በጀት ዓመት ሂሳባቸው ኦዲት የተደረጉ

መሥሪያ ቤቶች የተጠቃለለ ሪፖርት

መንግሥት ባወጣቸው የፋይናንስ ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያዎችና ሥርዓቶች መሠረት የመንግሥት ገቢ በአግባቡ መሰብሰቡንና የተፈቀደው በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን እንዲሁም የመንግሥት ንብረቶች በሚገባ መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ የልማትና ማኅበራዊ መሥሪያ ቤቶች ኦዲት ዳይሬክቶሬት የ2008 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ለማድረግ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ የ33 መሥሪያ ቤቶችንና ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ፣ ለእንስሳትና ዓሣ ሀብት፣ ለጤና ጥበቃና ለከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ተጠሪ የሆኑ 12 መሥሪያ ቤቶችን በዕቅድ መያዙ ይታወቃል፡፡

በዕቅድ የተያዙት ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ መሥሪያ ቤቶች በሙሉ የኦዲት ሥራቸው የተጠናቀቀ ሲሆን፣ ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆነው የሚዛንና የገዋኔ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጆች የኦዲት ሥራ ግን በሰው ኃይልና በጊዜ እጥረት ምክንያት ሳይከናወን ቀርቷል፡፡

ኦዲት ለተደረጉ መሥሪያ ቤቶቹ በሙሉ የሥራ አመራር ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን፣ መሥሪያ ቤቶቹ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሣብ መሠረት የወሰዱትን እርምጃ እንዲገልጹ ተጠይቀው ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ መሥሪያ ቤቶች በሙሉ ምላሽ የሰጡ ሲሆን፣ ለእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆነው የምግብ ዋስትና ዳይሬክቶሬት እና ለእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር ተጠሪ የሆነው የብሄራዊ እንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ማዕከል ምላሽ አልሰጡም፡፡ መሥሪያ ቤቶቹ የሰጡትን ምላሾች መሰረት በማድረግ በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር፣ በእንስሳትና ዓሣ ሀብት ሚኒስቴር፣ በጤና ጥበቃና በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ሥር ሂሳባቸው ለተጠቃለሉ አሥር ተጠሪ መሥሪያ ቤቶች የመጨረሻው የሥራ አመራር ሪፖርት ብቻ፤ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሂሳብ አቅራቢ ለሆኑት ሰላሳ ሶስት መሥሪያ ቤቶች ደግሞ የኦዲት አስተያየቱን የያዘ የኦዲት ሪፖርት እና የመጨረሻው የሥራ አመራር ሪፖርት እንዲላክላቸው ተደርጓል፡፡

I. <u>የኦዲት ዳይሬክቶሬቱ ዕቅድና ክንውን</u>

2.1. ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት ለማድረግ በዕቅድ የያዛቸውን ሂሳብ አቅራቢ የሆኑ የሰላሳ ሶስት መሥሪያ ቤቶችን የኦዲት ሥራ አጠናቋል፡፡ ይህም የዕቅዱን 100% የሸፈነ መሆኑን መግንዘብ ይቻላል፡፡

2.2. በኦዲት ዳይሬክቶሬቱ በበጀት ዓመቱ ኦዲት የተደረጉ መሥሪያ ቤቶችን ዝርዝር፣ በ2008 በጀት ዓመት የተፈቀደላቸውን የመደበኛና የካፒታል በጀት እና የበጀት ዓመቱን ሂሳብ የዘጉበትን ጊዜ የሚያሳይ ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ስም	የተፈቀደ በጀት			
		ሒሳብ የዘጉበት ቀን	ለመደበኛ በጀት	ለካፒታል በጀት	ድምር
1	የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር	ጥር 2009	6,257,156,942.48	661,283,310.53	6,918,440,253.01
1.1	የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስ ጽ/ ቤት	-	-	-	-
1.2	የምግብ ዋስትና ዳይሬክቶሬት	-	-	-	-
1.3	የአላጌ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ	-	-	-	-
1.4	የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ	-	-	-	-
1.5	የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ	-	-	-	-
1.6	የቡና ጥራት ምርመራና ሰርተፊኬሽን ማዕከል	-	-	-	-
2	የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር	ጥቅምት 2009	85,702,100.51	2,190,248,062.51	2,275,950,163.02
2.1	የገፈርሳ የአዕምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል	-	-	-	-
3	የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር	ጥቅምት 2009	658,580,849.04	5,960,117,642.17	6,618,698,491.21
4	የኢትዮጵያ ምግብ ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን	ነሐሴ 2008	88,203,170.00	10,763,110.00	98,966,280.00
5	የብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ	መስከረም 2009	56,097,329.92	58,650,000.00	114,747,329.92
	የሚዞር ድምር		7,145,740,391.95	8,881,062,125.21	16,026,802,517.16

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ስም	የተፈቀደ በጀት			
		ሒሳብ የዘጉበት ቀን	ለመደበኛ በጀት	ለካፒታል በጀት	ድምር
	የዞረ ድምር		7,145,740,391.95	8,881,062,125.21	16,026,802,517.16
6	የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር	ጎዳር 19/2009	116,847,134.55	70,360,120.00	187,207,254.55
6.1	የፌዴራል የተቀናጀ የከተማ መሬት መረጃ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት	-	-	-	-
6.2	የፌዴራል መንግሥት ሕንጻዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት	-	-	-	-
7	የማዕድን፣ ነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር	ጥቅምት 2009	41,379,314.00	38,888,400.00	80,267,714.00
8	የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት	መስከረም 2009	9,292,000.00	50,000,000.00	59,292,000.00
9	የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት	ነሐሴ 2008	29,267,612.91	12,028,800.00	41,296,412.91
10	የትራንስፖርት ሚኒስቴር	መስከረም 2009	32,681,337.85		32,681,337.85
11	የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	መስከረም 2009	66,929,771.63	90,034,000.00	156,963,771.63
12	የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት	ነሐሴ 2008	52,609,670.00	18,485,000.00	71,094,670.00
13	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	መስከረም 2009	56,275,802.50	5,938,220.00	62,214,022.50
14	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን	ጥቅምት 2009	57,073,766.40	84,000,000.00	141,073,766.40
15	የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ	መስከረም 2009	39,923,428.38		39,923,428.38
16	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	መስከረም 2009	93,098,650.00	7,896,120.00	100,994,770.00
17	የስትራቴጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ	ነሐሴ 2008	40,114,581.00		40,114,581.00
18	የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር	መስከረም 2009	517,135,515.67	85,945,500.00	603,081,015.67
19	የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን	መስከረም 2009	22,806,800.00		22,806,800.00
20	የብሔራዊ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፈንድ አስተዳደር ጽህፈት ቤት	ነሐሴ 2008	1,629,200.00		1,629,200.00
21	የመንገድ ፈንድ ጽሕፈት ቤት	መስከረም 2009	6,945,910.00		6,945,910.00
22	የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን	መስከረም 2009	9,149,240.00	3,000,120.00	12,149,360.00
23	የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን	ጥቅምት 2009	25,172,700.00	28,080,000.00	53,252,700.00
	የሚዞር ድምር		8,364,072,826.84	9,375,718,405.21	17,739,791,232.05

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ስም	የተፈቀደ በጀት			
		ሒሳብ ዘጉበትቀን	ለመደበኛ በጀት	ለካፒታል በጀት	ድምር
	የዞረ ድምር		8,364,072,826.84	9,375,718,405.21	17,739,791,232.05
24	የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን	ጥቅምት 2009	55,315,250.00	68,950,860.00	124,266,110.00
25	የኢትዮጵያ ጤና መድኅን ኤጀንሲ	ኅዳር 2009	140,567,480.00		140,567,480.00
26	የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል	ነሐሴ 2008	48,951,807.72	75,038,000.00	123,989,807.72
27	የአለርት ማዕከል	መስከረም 2009	89,473,126.99	37,253,888.57	126,727,015.56
28	የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ	መስከረም 2009	82,354,411.00	800,256,917.00	882,611,328.00
29	የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን	ጥቅምት 2009	12,410,000.00	23,980,000.00	36,390,000.00
30	የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስቴር	ጥር 2009	297,981,240.31	138,441,856.23	436,423,096.54
30.1	የብሔራዊ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል	-	-	-	-
30.2	የብሄራዊ እንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ማዕከል	-	-	-	-
31	የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር	ነሐሴ 2008	46,432,823.74		46,432,823.74
32	የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት	ታህሳስ 2009	51,493,755.97		51,493,755.97
33	የብሄራዊ ደም ባንክ አገልግሎት	ሐምሌ 2009	45,018,199.20		45,018,199.20
	ጠቅላላ ድምር		9,234,070,921.77	10,519,639,927.01	19,753,710,848.78

II. <u>የተሰጠው የኦዲት አስተያየት</u>

በዳይሬክቶሬቱ ኦዲት ለተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የኦዲት ሪፖርት የተላከላቸው ሲሆን፣ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው አጥጋቢ ያልሆነ የኦዲት አስተያየት ለ8 መሥሪያ ቤቶች፤ የፋይናንስ አስተዳደር ሥርዓታቸው ከጥቂት ጉድለቶች ወይም ስህተቶች በስተቀር በአጠቃላይ ሲታይ አጥጋቢ ሆኖ በመገኘቱ ነቀፌታ ያለበት

የኦዲት አስተያየት ለ16 መሥሪያ ቤቶች፣ ነቀፌታ የሌለበት የኦዲት አስተያየት ደግሞ ለ9 መሥሪያ ቤቶች ተሰጥቷቸዋል። /ዝርዝሩ በአባሪ- 2 ተመልክቷል።/

III. ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች

በዳይሬክቶሬቱ የ2008 በጀት ዓመት ሂሣባቸው ኦዲት በተደረጉ መሥሪያ ቤቶች የተገኙ ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሐሳቦች እንደሚከተለው ቀርቧል።

1. የገቢ ሂሳብ

1.1 በውስጥ ገቢ አሰባሰብ ላይ የታዩ የአሰራር ክፍተቶች፤

1.1.1 ግኝት

1. የብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ በበጀት ዓመቱ ለስቪል አቪዬሽን ባለሥልጣን የአየር ትንቢያ መረጃ አገልግሎት ለሰጠበት ብር 1,671,858.93 ገቢ የሰበሰበ ቢሆንም ለገቢው በሚመለከተው አካል የጸደቀ ታሪፍ ባለመኖሩ ምክንያት ገቢው በታሪፉ መሰረት ስለመሰብሰቡ ለማረጋገጥ ያልተቻለ ሲሆን፣ ስለሁኔታው በ2006 እና በ2007 በጀት ዓመት ኦዲት ወቅት አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም የማሰተካከያ አርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤
2. የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ታህሳስ 23 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር በጠ2/6/64 የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ባስተላለፈው መመሪያ ቁጥር 39/2006 መሰረት ከግል ህክምና አገልግሎቱ የሰበሰበውን የሆስፒታሉን ድርሻ በበጀት አሲይዞ በመመሪያው በተፈቀደው አግባብ መጠቀም ሲገባው በጀት ሳያሲዝ ብር 102,568.07 ሲቲስካን ላይ ለተሰማሩ ባለሙያዎች በገቢ የሂሳብ ኮድ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ የፈጸመ መሆኑ፣
3. በእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስቴር የኳራንቲን ማቢያዎቹ ባንክ ገቢ ባደረጉበት የባንክ አድቫይስ መሰረት የገቢ ደረሰኝ በማዘጋጀት ብቻ በገቢ የመዘገበ ከመሆኑም በተጨማሪ ገቢው ከምን አይነት አገልግሎት

እንደተሰበሰበ በአብዛኛው የሚገልጽ ደጋፊ ማስረጃ ከግቢ ደረሰኞቹ ጋር ያልተያያዘ በመሆኑ የግቢውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤

4. የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ከግንባታና ከግንባታ መሳሪያዎች ጋር የተያያዙ ግቢዎችን (ምዝገባ፣ የብቃት ማረጋገጫ እና የመሳሰሉት) የሚሰበስብ ቢሆንም ለሚሰበስበው ገቢ በሚመለከተው የመንግሥት አካል የጸደቀ የገቢ ታሪፉ ያልቀረበ መሆኑ፤

5. የብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል የወተት ምርቱን ለማስረከብ ሐምሌ 23 ቀን 2006 ዓ.ም ከኤ. ቢ.ኤም ኃላፊነቱ የግል ማህበር ጋር ባደረገው የውል ስምምነት መሠረት ማህበሩ የተረከበው የጥሬ ወተት ሽያጭ ክፍያ በየ15 ቀኑ በማዕከሉ የባንክ ሂሳብ ገቢ ማድረግ እንዳለበት እና ያለበትን እዳ በወቅቱ ባይከፍል ላቆየበት በባንክ ወለድ መሰረት ለማዕከሉ መክፈል እንዳለበት የተመለከተ ቢሆንም ድርጅቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2007 ዓ.ም በብር 306,381.18 የተረከበውን የወተት ሽያጭ ጥቅምት 30 ቀን 2008 ዓ.ም ገቢ ያደረገ ቢሆንም ድርጅቱ ገቢውን ላዘገየበት ወለድ እንዲከፍል ያልተደረገ መሆኑ፤

6. የዱር እንሰሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን በአዋሽ ብሄራዊ ፓርክ የሚገኘውን የከረዩን ሎጅና በባሌ ብሄራዊ ፓርክ የሚገኘውን የዲንሾ ሎጅ ኪራይ ከአዲአማት ኢትዮጵያ አስጎብኚና የጉዞ ወኪል ጋር በተፈራረመው የውል ስምምነት መሠረት ውል ተቀባይ እስከ አሁን ለባለስልጣን መሥሪያ ቤቱ ምንም አይነት ክፍያ የፈጸመ አለመሆኑና ሎጁ በአሁኑ ሰዓት በምን አይነት ሁኔታ ላይ እንዳለ ለአዲት የቀረበ መረጃ አለመኖሩ እንዲሁም ለተከራያቸው ሁለቱም ሎጆች በውሉ መሠረት ዋስትና ስለመግባቱ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤

7. በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 አንቀጽ 30 ተራ ቁጥር 2(ሀ) መሰረት የፌዴራልና የክልል መንግሥታት እንዲሁም የከተማ መስተዳድሮች የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከግብር ነጻ መሆናቸው ተደንግጓል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/1999 አንቀጽ 24 መሰረት በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች፣

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ የግል ድርጅቶች እና መንግሥታው ያልሆኑ ድርጅቶች የአገልግሎትና የእቃ ግዥ ሲፈጽሙ 2% የንግድ ትርፍ ግብር ቀንሰው እንደሚያስቀሩ ተመልክቷል፡፡ ሆኖም የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጁ ለሆራ የምግብ ኮምፕሌክስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከሸጠው የስንዴ ምርት ሽያጭ ብር 11,500,769.50 ላይ ድርጅቱ ብር 230,015.39 የቅድሚያ ግብር (ዊዝሆልዲንግ) ቆርጦ ያስቀረ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

1.1.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- ✓ ያለታሪፍ ለሚሰበሰበው ገቢ ታሪፍ እንዲወጣለትና በሚመለከተው አካል እንዲጸድቅ መደረግ እንዳለበት፤
- ✓ በገቢ ሂሳብ ኮድ የወጪ ክፍያ መፈጸም ተገቢነት ያለው አሰራር ስላልሆነ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ታህሳስ 23 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር በጠ2/6/64 ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት የውስጥ ገቢውን ለመጠቀም በቅድሚያ በጀት በመያዝ ክፍያውንም በተገቢው የወጪ ርዕስ መፈጸም እንዳለበት፤
- ✓ የገቢ ሂሳቦቹ የገቢ ምንጭ በዝርዝር እንዲገለጽ እየተደረገ ትክክለኛነታቸው መረጋገጥ እንዳለበት፤
- ✓ የብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል የወተት ሽያጭ ገቢው ለዘገየበት በውሉ መሰረት ወለዱን እንዲሰበስብ፤ ለወደፊቱም የወተት ሽያጭ ገቢው በውሉ መሰረት ለመሰብሰቡ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንዳለበት፤
- ✓ የዱር እንሰሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን አስጎብኚ የጉዞ ወኪሉ በገባው የውል ስምምነት መሰረት ባለመፈጸሙ መንግሥት ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም እንዳያገኝ ስለሚያደርግ ሁኔታውን በመከታተል ወቅታዊ እርምጃ መውሰድ እንዳለበት፤

- ✓ የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ግዥውን የፈጸመው ድርጅት ህጉ ከሚፈቅደው አግባብ ወጪ ቀንሶ ያስቀረውን ገንዘብ ተመላሽ አስደርጎ ፈስስ ማድረግ እንዳለበት፤

አሳስበናል፡፡

4 ተሰብሳቢ ሂሳብ

3.1 በደንቡ መሰረት ያልተሰበሰበ ወይም ያልተወራረደ ሂሳብ፤

3.1.1 ግኝት

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ለውሎ አበልና ለመጓጓዣ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ከተመለሰ በኋላ በሰባት ቀናት ውስጥ እንዲሁም በመመሪያው ቁጥር 5/2003 መሰረት ደግሞ ለግዥ የተሰጠ ቅድሚያ ክፍያ በሰባት ቀናት ውስጥ መወራረድ እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁንና በሃያ አንድ መሥሪያ ቤቶች እና በዘጠኝ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው ብር 224,833,495.66 ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ ያልተወራረደ (ያልተሰበሰበ) ሂሳብ መኖሩ የታወቀ ሲሆን፣ የተሰብሳቢ ሂሳቡ የዕድሜ ቆይታ በዚሁ ጽሁፍ በአባሪ- 1 እና ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር በአባሪ- 6 ቀርቧል፡፡

3.1.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ከዓመት ወደ ዓመት ሳይወራረዱ በሂሳብ መግለጫዎቹ ላይ የሚታዩ ከሆነ የሂሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡት ከመቻላቸውም በላይ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነትና ለጥፋት ሊዳረግ የሚችል ስለሆነ መሥሪያ ቤቶቹ በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት የቅድሚያ ክፍያ ሒሳቦች እንዲወራረዱ፣ መሰብሰብ የማይችሉትን ደግሞ አጣርተው አስፈላጊውን እርምጃ መወሰድ እንዳለባቸው በተደጋጋሚ አሳስበናል፡፡

2.2 መደበኛ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ ተሰብሳቢ ሂሳቦች፤

2.2.1 ግኝት

በተሰብሳቢ ተቀጽላ ሌጀሮች (Subsidery ledger) ላይ የተመለከቱት ዝርዝር ሂሳቦች ውጤት ከአጠቃላይ ሌጀሩና (General Ledger) በሂሳብ መግለጫው ጋር ከተመለከተው ሂሳብ ሚዛን ጋር ተመሳሳይ መሆናቸውን እና ተሰብሳቢ ሂሳቦቹም መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሶስት መሥሪያ ቤቶችና በሁለት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ከ2007 በጀት ዓመት ወደ 2008 በጀት ዓመት በተሰብሳቢ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች ላይ በተለያየ ሂሳብ መደቦች የዞሩት ከወጪ ቀሪ ሂሳቦች መነሻ ሚዛን (Beginning Balance) ብር 28,016,571.11 ክሬዲት ሚዛን የሚያሳዩ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝሩ በዚሁ ጽሁፍ አባሪ -3 እና ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር በአባሪ- 7ለ ተያይዟል፡፡

2.2.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ወይም የክሬዲት ሚዛናቸውን የጠበቁ ለመሆኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበትና፤ የሂሳቡም ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3. ተከፋይ ሒሳብ

3.1 ለረጅም ዓመታት በተከፋይ ተይዞ የሚገኝ ሂሳብ፤

3.1.1 ግኝት

በተከፋይ ሒሳብ መግለጫዎቹ ላይ የተመለከቱት ሒሳቦች በተገቢው ማስረጃ የተደገፉ መሆኑንና ለሚመለከተው አካል በተገባው ውልና በህግ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ የሚከፈሉ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በስምንት መሥሪያ ቤቶች እና በስድስት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች በጠቅላላው በጠቅላላው ብር 35,285,908.57 ከ1994 ዓ.ም ጀምሮ በተከፋይ ሂሳብ ተይዞ የሚገኝ ሲሆን፣ የተከፋይ ሂሳቡ የዕድሜ ቆይታ ተተንትኖ በዚሁ ጽሁፍ በአባሪ- 2 እና ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር በአባሪ- 31 ቀርቧል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

የተከፋይ ሂሳቡ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው አርምጃ ካልተወሰደ የሂሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡ ስለሚችሉ መሥሪያ ቤቶቹ የተከፋይ ሂሳቦቹን ሁኔታ በማጣራት አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ እንዲወስዱ በተደጋጋሚ በተደረጉ ኦዲቶች አሳስበናል፡፡

3.2 መደበኛ የሂሳብ ሚዛኑን ያልጠበቀ ተከፋይ ሂሳብ፤

3.2.1 ግኝት

በተከፋይ ተቀጽላ ሌጀሮች (Subsidery ledger) ላይ የተመለከቱት ዝርዝር ሂሳቦች ውጤት ከአጠቃላይ ሌጀሩና (General Ledger) በሂሳብ መግለጫው ጋር ከተመለከተው ሂሳብ ሚዛን ጋር ተመሳሳይ መሆናቸውን እና ተከፋይ ሂሳቦቹም መደበኛ ሚዛናቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሁለት መሥሪያ ቤቶች ከ2007 በጀት ዓመት ወደ 2008 በጀት ዓመት በተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች ላይ የዞሩት ከወጪ ቀሪ ሂሳቦች መነሻ ሚዛን (Beginning Balance) ብር 10,124,351.45 ዴቢት ሚዛን የሚያሳዩ መሆኑ ታውቋል፡፡ በዚሁ ጽሁፍ በአባሪ- 2 እና ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር በአባሪ-32 ቀርቧል፡፡

3.2.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ሂሳቦች መደበኛ የዴቢት ወይም የክሬዲት ሚዛናቸውን የጠበቁ ለመሆኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበትና፤ የሂሳቡም ሁኔታ ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4. የወጪ ሂሳብ

4.1 ጨረታ ሳይወጣ የተፈጸመ ግዥ፤

4.1.1 ግኝት

የፌዴራል መንግሥት ሰኔ 2002 ዓ.ም ባወጣዉ የእቃና የአገልግሎት ግዥ መመሪያ መሰረት እንዲሁም የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ታህሳስ 14 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ሕ/አ/2/59 በተጻፈ ደብዳቤ ሰኔ 2002

ዓ.ም የወጣዉን የእቃና የአገልግሎት ግዥ አንዳንድ አንቀጾችን ለማሻሻል ባስተላለፈው እና ከታኅሳስ 12 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ በሆነው የግዥ መመሪያ መሰረት በጨረታ መገዛት ለሚገባቸው ግዥዎች ጨረታ መውጣቱን፤ የዋጋ ማወዳደሪያ ተሰብስቦ ሊገዙ ለሚገባቸው ግዥዎች የዋጋ ማወዳደሪያ መሰብሰቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- ✓ በአንድ መሥሪያ ቤት ግልጽ ጨረታ ሳይወጣ በብር 1,139,622.13 በውስን ጨረታ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
- ✓ በአራት መሥሪያ ቤቶች ጨረታ ሳይወጣ በብር 5,970,981.28 የቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
- ✓ በሁለት መሥሪያ ቤቶችና በአንድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ጨረታ ሳይወጣ በብር 5,385,659.05 በዋጋ ማወዳደሪያ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤
- ✓ በአምስት መሥሪያ ቤቶች የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ በብር 786,071.23 የቀጥታ ግዥ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡ በዚሁ ጽሁፍ በአባሪ- 4 እና ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር በአባሪ-21 ቀርቧል፡፡

4.1.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ግዥዎች የግዥ መመሪያውን ተከትለው የማይፈጸሙ ከሆነ፡-

- ♦ በግዢ አፈጻጸም ረገድ ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም እንዳያስገኝ፤ ቁጠባን የአፈጻጸም ብቃትን እና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ እንዳይቻል የሚያደርግ በመሆኑ፤ በጀትን በቁጠባ መጠቀም እንዳይቻል የሚያደርግ መሆኑ፤ ተጠያቂነትን የሚስከትል በመሆኑ፤

መሥሪያ ቤቶች የግዥ አዋጁንና መመሪያውን ተከትለው ግዥዎችን መፈጸም ያለባቸው መሆኑን አሳስበናል፡፡

4.2 በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ፤

4.2.1 ግኝት

የገ/አ/ት/ሚ/ር ግንቦት 1999 ዓ.ም ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት ሂሳቦች በተገቢው የሒሳብ መደብ የተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ በሃያ መሥሪያ ቤቶችና በስድስት ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ብር 38,662,041.49 መመዝገብ ባለባቸው የሂሳብ መደቦች ሳይመዘገቡ ተገኝቷል፡፡ በዚሁ ጽሁፍ በአባሪ- 5 እና ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር በአባሪ- 25 ቀርቧል፡፡

4.2.2 የማሻሻያ ሃሳብ

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ማንኛውም ሂሳብ በትክክለኛ የሂሳብ መደብ (ኮድ) ለመመዝገቡ መረጋገጥ እንዳለበትና ለሂሳቡም ተገቢው ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.3 በጀት ዓመቱን ያልጠበቀ የወጪ ሂሳብ፤

4.3.1 ግኝት

የበጀት ዓመቱ ሂሳብ በበጀት ዓመቱ የሚመዘገብ መሆኑን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ በሰባት መሥሪያ ቤቶች ብር 5,098,656.18 የ2007 በጀት ዓመት የወጪ ሂሳቦች በ2008 በጀት ዓመት በወጪ ተመዝግበው ተገኝተዋል፡፡

ዝርዝራቸው በዚሁ ጽሁፍ በአባሪ-5 እና ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር በአባሪ-24 ቀርቧል፡፡

4.3.2 የማሻሻያ ሃሳብ

የበጀት ዓመቱ ወጪ በበጀት ዓመቱ እንዲመዘገብ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.4 <u>አለአግባብ የተፈጸመ የውሎ አበልና የመሳሰሉት ክፍያ፤</u>

4.4.1 <u>ግኝት</u>

የውሎ አበል ክፍያ የፐብሊክ ሰርቪስ ሚኒስቴር ሰኔ 2004 ዓ.ም ባወጣው የመንግሥት ሰራተኞች የአገር ውስጥ የቀን ውሎ አበል ክፍያ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት እንዲሁም ከኢትዮጵያ ወጪ ለሚሄዱ የበላይ ኃላፊዎች፣ ከፍተኛ ኃላፊዎች፣ ኃላፊዎችና ሰራተኞች የሚከፈለው የውሎ አበል የሚኒስትሮች ምክር ቤት መስከረም 8 ቀን 2002 ዓ.ም ያወጣውንና የግ/ኢ/ት/ሚ/ር መስከረም 25 ቀን 2002 ዓ.ም በቁጥር 1/54/9 ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ፡-

1. በሰባት መሥሪያ ቤቶችና በአንድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት 928,831.90 ከአገር ውስጥ የውሎ አበል መመሪያ ውጭ ክፍያ የተፈጸመ፤

፡ ለዝርዝሩ በዚሁ ጽሁፍ በአባሪ- 6 እና ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር በአባሪ-19 ቀርቧል፡፡

2. በሁለት መሥሪያ ቤቶች ብር 294,130.02 የውጭ ሐገር የውሎ አበል መመሪያውን ሳይከተል ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን፣ ዝርዝራቸውም፡-
   - 1.1 በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ብር 283,626.26፤
   - 2.2 በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር 10,503.76፤

   ናቸው፡፡

4.4.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ደንብና መመሪያን ሳይከተል የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ፣ ለወደፊቱም የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሐገር የውሎ አበል ክፍያዎች የወጡትን መመሪያዎች ተከትለው መፈጸም እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.5 አለአግባብ የተፈጸመ ክፍያ፤

4.5.1 ግኝት

በበጀት ዓመቱ የተፈጸሙ ክፍያዎች በሚመለከተው አካል የተፈቀዱ እና ለክፍያውም በጀት የተያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድና ለክፍያው ተብሎ የተያዘ በጀት ሳይኖር ለሶስት የሥራ አመራር አባላት ለአሸከሪካሪ ስልጠና ተብሎ ብር 11,430.21 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
2. በቡና ጥራት ምርመራና ሰርተፊኬሽን ማዕከል በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድና ለክፍያው ተብሎ የተያዘ በጀት ሳይኖር ለሰራተኞች ለህክምና አገልግሎትና ለመድኃኒት ግዥ በሚል በበጀት ዓመቱ ብር 90,838.05 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡
3. በሚመለከተው አካል የማበረታቻ ክፍያ እንዲፈጸም ሳይወሰን እንዲሁም ለክፍያው ተብሎ የተፈቀደ በጀት ሳይኖር በሶስት መሥሪያ ቤቶች ብር 720,625.35 የማበረታቻ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ ሲሆን፣ ዝርዝራቸውም፡-
   1.1 በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ 500,000.00፤
   1.2 በአለርት ማዕከል 191,925.35፤
   1.3 በማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር ብር 28,700.00 ፤ ናቸው፡፡

4.5.2 የማሻሻያ ሃሳብ

በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድና ለክፍያው ተብሎ የተያዘ በጀት ሳይኖር ክፍያ መፈጸሙ አግባብ ባለመሆኑ ክፍያው በአስቸኳይ እንዲቆም፤ የተፈጸመውም ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.6 በመመሪያ ከተፈቀደው በላይ የተፈጸመ ክፍያ፤

4.6.1 ግኝት

በበጀት ዓመቱ የተፈጸሙ ክፍያዎች በሚመለከተው አካል የተፈቀዱ እና ክፍያውም በመመሪያው መሰረት የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

- የቀድሞው የሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ሰኔ 10 ቀን 2004 ዓ.ም በቁጥር ሲስሚ30/ጠ13/40/880 ባስተላለፈው ሰርኩላር በተለያዩ ተቋማት በሥራ ባህሪያቸው የተነሳ ለጤና ጠንቆች ተጋላጭ በሆኑ የስራ መደቦች ላይ መደበኛ ሥራ ለሚያከናውኑ ሰራተኞች የሚፈጸመው የወተት አበል ክፍያ ከሐምሌ 1 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ ከብር 30 ወደ ብር 80 ከፍ እንዲል በወሰነው መሰረት ክፍያ የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ በሁለት መሥሪያ ቤቶችና በአንድ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ብር 207,702.88 በመመሪያ ከተፈቀደው በላይ የወተት ግዥና ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን፣ ዝርዝራቸውም፡-

  1.1. በኢትዮጵያ ምግብ፣ መድኃኒት፣ ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን
  137,699.38፤

  1.2. በቡና ጥራት ምርመራና ሰርተፊኬሽን ማዕከል ብር 54,043.50፤

  1.3. በማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር ብር 15,960.00,፤

  ናቸው፡፡

- የጠቅላይ ሚኒሰቴር ጽህፈት ቤት የከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎችን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞች ለመወሰን ጥቅምት 19 ቀን 1997 ዓ.ም በቁጥር ጠ80-አጠ/3/02/15 ባወጣው መመሪያ መሰረት ለከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች ቤተሰቦች ለሚመደቡ ተሽከርካሪዎች ፍጆታ የሚውል 100 ሊትር ቤንዚን መፈቀዱ ተመልክቷል፡፡ ነገር ግን የትራንስፖርት ሚኒስቴር ከመስከረም 2008 ጀምሮ ለኃላፊዎች ቤተሰቦች በወር 130 ሊትር ቤንዚን ተግባራዊ በማድረጉ በመመሪያ ከተፈቀደው የነዳጅ ፍጆታ በላይ ለ600 ሊትር ቤንዚን ብር 9,966.00 ወጪ ያደረገ መሆኑ ታዉቋል፡፡

4.6.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በመመሪያ ከተፈቀደው በላይ ክፍያ መፈጸም ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ከመሆኑም በተጨማሪም ተጠያቂነትን የሚያስከትል በመሆኑ ከመመሪያው በላይ የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም ክፍያዎች መመሪያውን ትከትለው እንዲፈጸሙ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.7 <u>ከልዩ ልዩ የጥቅማጥቅም ክፍያዎች ላይ ሥራ ግብር ያልተቀነሰ ስለመሆኑ፤</u>

4.7.1 <u>ግኝት</u>

በገቢ አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 13 እና በገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 3 ከግብር ነጻ ከተደረጉ ገቢዎች በስተቀር ማናቸውም ክፍያ ወይም ጥቅም (ለምሳሌ የቤት አበል፣ ቦነስ፣ የዓመት ፍቃድ ክፍያ፣ የአገልግሎት ካሳ ....ወዘተ ከወር ደመወዝ ጋር እተደመረ ግብር እንደሚከፈልበት በአዋጁና በደንቡ በግልጽ የተመለከተ መሆኑን በመግለጽ ነሐሴ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በቁጥር 1አውግ-54 በተጻፈ ደብዳቤ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ባሳወቀው መሠረት መፈጸሙን ለማጣራት አዲት ሲደረግ በሶስት መሥሪያ ቤቶችና በአንድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ብር 1,842,053.71 ከቤትና ከኃላፊነት አበል፣ ከልጆች የትምህርት ቤት ክፍያና ከመሳሰሉት ላይ ሥራ ግብር ተቀናሽ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝራቸውም፡- በአባሪ-9 ለ ተመልክቷል፡፡

4.7.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በገቢ ግብር አዋጁ፣ ደንብና በተላለፈው መመሪያ መሰረት ያልተቀነሰው የገቢ ግብር ተቀንሶ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም እንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ሲያጋጥም ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.8 ሳይፈቀድ የተፈጸመ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ፤

4.8.1 ግኝት

በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች አዋጅ ቁጥር 515/99 አንቀጽ 34/2 መሰረት ከሐምሌ 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረግ የትርፍ ሰዓት ሥራ አከፋፈል መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን ሰኔ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ30/ጠ13/36/8/3 በተጻፈ ደብዳቤ ያሳወቀ ቢሆንም፤ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ እንደገና ጳጉሜ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በቁጥር መ30/13/37/820 በተጻፈ ደብዳቤ የትርፍ ሰዓት ክፍያው ተግባራዊ ሳይደረግ እንዲቆይ ማሳወቁ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ በፐብሊክ ሰርቪስ እና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር ሳይፈቀድ በዘጠኝ መሥሪያ ቤቶች ብር 2,049,393.91 የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ ተውቆል፡፡ /ለዝርዝሩ በዚሁ ጽሁፍ በአባሪ- 6 እና ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር በአባሪ-19 ቀርቧል፡፡

4.8.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ለትርፍ ሠዓት የተፈጸመው ክፍያ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለወደፊቱም በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዳይፈጸም ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.9 በመመሪያው መሰረት ያልተቀነሰ የህክምና ክፍያ፤

4.9.1 ግኝት

ከሚኒስትሮች ምክር ቤት ሚያዝያ 16 ቀን 2004 ዓ.ም በቁጥር መ30-899/4 የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችን የሚመሩ ዋና እና ምክትል ዋና ዳይሬክተሮች የሚያገኙትን ጥቅማ ጥቅሞች አሰጣጥ በተመለከተ በተላለፈው መመሪያ መሰረት ቤተሰቦቻቸው በጦር ኃይሎች ሆስፒታል የነጻ ህክምና አገልግሎት ማግኘት እንደሚችሉ ከወር ደሞዝቸው ላይ 1% የህክምና መዋጮ መቀነስ እንዳለበት እንዲሁም ለሚኒስትሮችና ለሚኒስትር ዴኤታዎች በምክር ቤት የተፈቀደበትን መመሪያ ጠቅሶ የግ/ኢ/ል/ሚ/ር ታኅሳስ 4 ቀን 1998 ዓ.ም ባስተላለፈው ደብዳቤ ቁጥር በጠ1/6/76

ከደመወዛቸው ከደመወዛቸው ላይ በየወሩ 2% የህክምና መቀነስ እንዳለበት መመሪያ ተላልፏል፡፡ ሆኖም ከሐምሌ በመመሪያው መሰረት መቀነሱ ሲጣራ በሁለት መሥሪያ ቤቶች ብር 5,487.28 የህክምና መዋጮ ያልተቀነሰ መሆኑ ታውቋል፡፡ ዝርዝራቸውም ፡-

1. ከኮንስትራክሽን ሚኒስቴር ብር 3,254.20 ፤
2. ከኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ብር 2,333.08፤

ናቸው፡፡

4.9.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በመመሪያ መሰረት ያልተቀነሰው የህክምና ክፍያ እንዲቀነስ፤ ለወደፊቱም በተላለፈው መመሪያ መሰረት እንዲፈጸም ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.10 <u>አለአግባብ የተፈጸመ የትራንስፖርት ክፍያ፤</u>

4.10.1 <u>ግኝት</u>

የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒት ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን የፈጸማቸው የትራንስፖርት ክፍያዎች መመሪያን የተከተለ መሆናቸውን እና አግባብነታቸውን ለማረጋገጥ በናሙና ኦዲት ሲደረግ ለመሥሪያ ቤቱ ሰራተኞች በስነ-ምግባር ዳይሬክቶሬት በኩል ከጥቅምት 15 አስከ 30 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ ለአስራ አምስት ቀን በሰርቪላንስ /በኢንተለጀንስ ጽንስ ሃሳብ ዙርያ በተሰጠዉ ስልጠና ለተሳተፉ ለ46 ሰልጣኞች ለትራንስፖርት አበል በቀን 30 ብር ሂሳብ ለሃያ ቀን ብር 27,600.00 የተከፈለ ሲሆን፣ ሥልጠናው ከተጠናቀቀ በኋላ የአምስት ቀን ብር 6,900.00 በተጨማሪ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታወቋል፡፡

4.10.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ክፍያዎች ደንብና መመሪያን ተከትለው ካልተፈጸሙ ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ ወጪ መሆን ምክንያት ሊሆኑ እና ክፍያውንም ተዓማኒነት ሊያሳጡት ስለሚችሉ አለአግባብ የተከፈለው ክፍያ ተመላሽ እንዲሆን፤

ለወደፊቱም የትራንስፖርት ክፍያ መንግሥት ያወጣውን የክፍያ መመሪያ ተከትሎና ሊከፈል የሚገባው ብቻ ለመክፈሉ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.11 ከግዥና ከግንባታ ክፍያዎች ላይ ያልተቀነሰ እና ተቀንሶ ያልተመዘገበ ሂሳብ፤

4.11.1 ግኝት

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/1994 ዓ.ም አንቀጽ 53 እንዲሁም በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 78/1994 ዓ.ም አንቀጽ 24 ተራ ቁጥር 1 እና 2 በግዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ አፈጻጸም የወጣ መመሪያ ቁጥር 27/2002 አንቀጽ 4 ቁጥር 1 ማንኛውም ወኪል በሚፈፅመው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ለአቅራቢው መክፈል የነበረበትን የተጨማሪ እሴት ታክስ ቀንሶ በማስቀረት ለታክስ ባለስልጣኑ ገቢ እንዲያደርግ በተደነገገው መሠረት ተግባራዊ መደረጉን እንዲሁም ለህንፃ ተቋራጭ የሚፈጸመው ክፍያ በውሉና በህጉ መሰረት የተፈጸመ መሆኑን እና ተገቢው ምዝገባም የሚከናወን መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በሶስት መሥሪያ ቤቶችና በሶስት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ብር 1,057,840.62 የተጨማሪ ዕሴት ታክስ ተቀናሽ ያልተደረገ ሲሆን፡-
   1.1. በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የገፈርሳ የአዕምሮ ሕመማን ማገገሚያ ማዕከል ብር 620,324.37፤
   1.2. በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ብር 266,573.54፤
   1.3. በብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ብር 127,814.95፤

   በዋንኛነት ይጠቀሳሉ፡፡

2. በሶስት መሥሪያ ቤቶችና በአንድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ብር 12,884.04 የቅድሚያ ግብር ተቀናሽ ያልተደረገ ሲሆን ዝርዝራቸውም፡-
   2.1.በአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን ብር 4,977.83 ፤
   2.2.በብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ብር 4,156.91 ፤

2.3.በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል ብር 2,772.62 ፤

2.4. በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የገፈርሳ የአዕምሮ ሕመማን ማገገሚያ ማዕከል ብር 976.68፤ ናቸው፡፡

3. በአራት መሥሪያ ቤቶችና በአንድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ብር 17,903,826.48 ተመላሽ ያልተደረገ የቅድሚያ ክፍያ የተገኘ ሲሆን፣ ከቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል ደግሞ ተቀንሶ ያልተመዘገበ የቅድሚያ ክፍያ ብር 163,823.20 መኖሩ ታውቋል፡፡ተመላሽ ካልተደረገው የቅድሚያ ክፍያ ውስጥ፡-

3.1. በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል ብር 16,046,156.16፤

3.2. በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ብር 1,398,669.27፤

3.3.በብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ብር 451,926.00፤

በዋንኛነት ይጠቀሳሉ፡፡

4. በሶስት መሥሪያ ቤቶች ብር 34,881.31 ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ ሲሆን፣ በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ደግሞ ተቀንሶ ያልተመዘገበ ብር 633,083.09 የመያዣ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡ ተቀናሽ ያልተደረገው የመያዣ ሂሳብ ዝርዝራቸውም፡-

4.1. በብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ብር 23,309.90፤

4.2. በአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን ብር 11,571.41፤

4.3.በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ብር 3,347.91፤

ናቸው፡፡

5. በሁለት መሥሪያ ቤቶች እና በአንድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ብር 3,692,696.57 ያልተመዘገበ የግንባታ ወጪ ሂሳብ የተገኘ ሲሆን፣ በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን ደግሞ ብር 19,400.00 ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ መኖሩ ታውቋል፡፡ ያልተመዘገቡ የግንባታ ሂሳቦች ዝርዝራቸውም፡-

5.1. በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል ብር 1,828,442.35፤

5.2. በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በአላጌ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ብር 1,333,093.65፤

5.3.በብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ ብር 531,160.57፤

ናቸው፡፡

ዝርዝሩ በዚሁ ጽሁፍ በአባሪ- 6 እና ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር በአባሪ - 9 ቀርቧል፡፡

4.11.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በሂሳብ አቀናነሱ እና በአመዘጋገቡ ላይ በታዩት ስሕተቶች ምክንያት፡-

- የሂሳብ መግለጫው ትክክለኛውን ገጽታ እንዳያመለክት ምክንያት ሊሆኑ ስለሚችሉ፤
- ሊቀነስ የሚገባው ገንዘብ ሳይቀነስ ሊቀር ስለሚችል፤
- መከፈል የሌለበት ገንዘብ ሊከፈል ስለሚችል፤
- ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤

ለታዩት ስህተቶች ተገቢው ማስተካከያ እንዲሰራ፤ መሰብሰብ ያለበት ሂሳብ እንዲሰበሰብ፤ መመዝገብ ያለበት ሂሳብ እንዲመዘገብ፤ ለወደፊቱም በግዥና በግንባታ ክፍያ አፈጻጸምና አመዘጋገብ ላይ ተገቢው ጥንቃቄ እንዲደረግ አሳስበናል፡፡

4.12 <u>በውል ስምምነት መሰረት ያልተፈጸመ ክፍያ</u>፤

4.12.1 <u>ግኝት</u>

የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል ከሳንታ ማሪያ ኮንስትራክሽን እና ታይም ኢንጂነሪንግና ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ ማህበር ጋር የካቲት 17 ቀን 2006 ዓ.ም በቁጥር ጴ2294/40/1/06 ባደረገው የኤሌክትሪክ ፍጆታ ወጪ የመጋራት ውል ስምምነት መሠረት ድርጅቶቹ ተመላሽ ማድረግ የነበረባቸውን ሂሳብ ብር 73,988.84 ተመላሽ ያላደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡ ቀደም ሲል በተደረገው ኦዲት ወቅትም በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ሆስፒታሉ ተገቢውን እርምጃ እየወሰደ አለመሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

4.12.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በውል ሥምምነቱ መሰረት ያለመፈጸም የመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ስለሚችል ሆስፒታሉ ከውል ተቀባዮች ላይ ተገቢውን ገንዘብ ሰብስቦ ለመንግሥት ካዝና ገቢ ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.13 <u>ከሥራ ከለቀቁ በኋላ የተፈጸመ የደመወዝ ክፍያ</u>

<u>እና ለክፍያው ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ</u>፤

4.13.1 <u>ግኝት</u>

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መመሪያ መሰረት በጀት ዓመቱ የተከፈለውን የደመወዝ ሂሳብ ክፍያ አግባብነት፣ የምዝገባውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በናሙና አዲት ሲደረግ፡-

1. በስድስት መሥሪያ ቤቶች እና በአንድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ከሥራ ከለቀቁና ወደ ሌላ መሥሪያ ቤት ከተዛወሩ በኋላ ለሰራተኞቹ ብር 111,813.76 ደመወዝ የተከፈለ ሲሆን አለአግባብ ከተፈጸመው ክፍያ ውስጥ፡-
   1.1. በውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር 73,781.15፤
   1.2. በኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ብር 23,555.64፤
   1.3. በኢትዮጵያ ሥራ አመራር ፕሮጀክት ኮንስትራክሽን ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት ብር 8,711.63፤
   1.4.በቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ብር 5,886.30 ፤
   በዋንኛነት ይጠቀሳሉ፡፡ ለዝርዝሩ አባሪ 6 ተያይዟል፡፡
2. በእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስቴር ለተፈጸመው የደመወዝ ክፍያ ብር 1,736,915.40 ክፍያው የተፈጸመበት ፔይሮል ሊቀርብለት ያልቻለ መሆኑ፤

3. በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል በወጪ ለተመዘገቡና ላልተከፈሉ የደመወዝ ሂሳቦች ብር 353,421.65 ተገቢው የሂሳብ ማስተካከያ እንዲሰራላቸው ያልተደረገ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

4.13.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

አለአግባብ የተከፈለው ደመወዝ ተመላሽ እንዲደረግ፤ ማስረጃ ላልቀረበለት የደመወዝ ክፍያ ሂሳብ ማስረጃ እንዲቀርብለት፤ በወጪ ተመዝግበው የማስተካከያ ምዝገባ ላልተሰራላቸው ሂሳቦች ማስተካከያ እንዲሰራላቸው፤ ለወደፊቱም እንዲህ ዓይነቱ ክፍያ እንዳይፈጸም ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.14 <u>ተገቢው ማስረጃ ያልቀረበለት የወጪ ሂሳብ</u>፤

4.14.1 <u>ግኝት</u>

በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ብብር ሚኒስቴር የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሰረት ለወጪ ሂሳቦች ተገቢው ማስረጃ ቀርቦላቸው የተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር ሰኔ 20 ቀን 2005 ዓ.ም ወደ ዉጭ የሚላኩ የሆርቲካልቸር ምርቶች ትራንስፖርት ወጪ ድጎማን በተመለከተ ባወጣው መመሪያ ቁጥር 36/2005 እና የዚህን መመሪያ የቆይታ ጊዜ ለማራዘም ጳጉሜ 5 ቀን 2007 ዓ.ም እንዲሁም መስከረም 5 ቀን 2008 ዓ.ም በወጡት መመሪያዎች መሰረት በባህር ዳር እና መቀሌ ለሚገኙ አበባ፣ አትክልት፣ ፍራፍሬና ኸርብስ አምራች ድርጅቶች ለአዲስ አበባ ቅርብ ከሆኑ አምራች ድርጅቶች ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ከማምረቻ ቦታቸው እስከ አዲስ አበባ ኤርፖርት በየብስ ትራንስፖርት የሚጓጓዘውን የአበባ ምርት ማጓጓዣ ወጪ ሙሉ በሙሉ በመንግሥት እንደሚሸፈን ያመለክታል፡፡ በዚሁ መሰረት ኤጀንሲው ለሚሸፍነው ክፍያ በፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት የቀረቡት የክፍያ ሰነዶች ኦርጅናል ሰነድ መሆናቸዉን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከባህርዳር ወደ አዲስ

አበባ በየብስ ትራንስፖርት ለተጓጓዙ የኤክስፖርት ሆርቲካልቸር ምርቶች ለትራንስፖርት የድጎማ ሂሳብ ብር 3,093,359.00 ክፍያ ሲፈጸም በኦርጁናል ደጋፊ የሂሳብ ሰነድ መወራረድ ሲገባቸው በኮፒ ሰነድ የተወራረዱ መሆኑ፤

2. የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር ሰኔ 29 ቀን 2004 ዓ.ም በቁጥር ሲሰሚ/30/ጠ13/40/883 ባወጣው የውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ መሰረት አንቀጽ 9 (1, 2 እና 3) መሰረት በአገር ውስጥ ለሚፈጸም የመስክ ጉዞ በቅድሚያ የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅጽ ተሞልቶ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲያዝ ከተደረገ በኋላ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ሲመለስ ደግሞ የውሎ አበል ክፍያ ማወራረጃ ቅጽ እንዲሚላ ተደርጎ ሂሳቡ እንዲወራረድ የሚደረግ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በአራት መሥሪያ ቤቶች ብር 334,587.65 የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅጽ ያልተሞላ ሲሆን፣
በዚህም ምክንያት የክፍያውን አግባብነትና ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ መሆኑ፤ዝርዝራቸውም፡- በአባሪ-17 ተመልክቷል፡፡

3. የፌዴራል መንግሥት የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 መሰረት ለወጪ ሒሳቦች ተገቢው የወጪ ማስረጃ የቀረበላቸው ስለመሆኑ ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ከግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት ለበቆጂ ግብርና ቴ/ሙ/ት/ሥ ኮሌጅ ከ1996 ዓ.ም በፊት ጀምሮ ለስራ ማስኬጃ ተልኮ በተሰብሳቢ ሂሳብ የተያዘው ሂሳብ በአጣሪ ኮሚቴ ተጣርቶ ብር 522,939.00 የ2008 በጀት አመት አካል ሆኖ በወጪ የተመዘገበ ቢሆንም በወጪ እንዲመዘገቡ ከተደረጉት ሂሳቦች ውስጥ ለብር 13,388.99 ምንም አይነት የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

4.14.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- በፎቶ ኮፒ የሚወራረዱ ሂሳቦች ኦርጅናል ሰነዶቻቸዉ ሌላ ቦታ በድጋሚ ክፍያ ሊፈጸምባቸው እና ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤
- ክፍያውን ተዓማኒነት ሊያሳጣው ስለሚችል፤
- ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤
- የመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ ወጪ እንዲሆን ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤
- ለክፍያዎች የወጪ ማስረጃ የማይቀርብላቸው ከሆነ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ስለማይቻል፤

የፎቶ ኮፒ የሂሳብ ማስረጃ ቀርቦላቸዉ የተወራረዱ ሂሳቦች በሙሉ ኦርጅናል ማስረጃቸዉ እንዲቀርብላቸው፤ ለአገር ውስጥ ለመስክ ጉዞ ለሚፈጸም የውሎ አበል ክፍያ በውሎ አበል አከፋፈል መመሪያ ጋር ተያይዞ በቀረበው የማወራረጃ ቅጽ መሰረት የውሎ አበል መጠየቂያና መፍቀጃ ቅጽ ተሞልቶ በተሰብሳቢ ሂሳብ እንዲያዝ ከተደረገ በኋላ ሰራተኛው ሥራውን አጠናቆ ሲመለስ ደግሞ የውሎ አበል ክፍያ ማወራረጃ ቅጽ እንዲሟላ ተደርጎና መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች ከተሟሉ በኋላ ሂሳቡ እንዲወራረድ፤ የወጪ ማስረጃ ላልቀረበለት ሂሳብ ተገቢው ማስረጃ እንዲቀርብለት፤ ማስረጃ ሊቀርብለት ካልቻለ ግን ገንዘቡ ተመላሽ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

4.15 <u>ማስረጃ ያልቀረበለት የትርፍ ሰዓት</u>

<u>እና የምግብ አበል ክፍያ</u>፤

4.15.1 <u>ግኝት</u>

የውሃ፣ መስኖና አሌክትሪክ ሚኒስቴር ለከሰም ግድብና መስኖ ግንባታ የክፍያ ሰርተፍኬት ቁጥር 46 እና 50 ቀርቦ ክፍያ ሲፈጽም ከግንባታው ወጪ በተጨማሪ የትርፍ ሰዓት ክፍያና የምግብ አበል (Allowance) ብር 826,547.85 ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ ታውቋል። ሆኖም፡-

- ክፍያው በውል ስምምነቱ ውስጥ የሌለ ሲሆን በክፍያ ሰርተፍኬቱ ውስጥ ተካቶ የቀረበ መሆኑ፣
- ክፍያው እንዲፈጸም በሚመለከተው አካል የተወሰነ ለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
- የወጪ ሂሳቡን ትክለኛነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

ታውቋል።።

4.15.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- በደመወዝ በግንባታ የውል ስምምነት ውስጥ ያልተካተቱ ክፍያዎችን መፈጸም ተገቢነት የሌለውና ተጠያቂነትን ሊያሥከትል ስለሚችል፤
- ለትርፍ ሰዓት ክፍያና ለምግብ አበል ተብሎ ለተፈጸመው ክፍያ ማስረጃ ካልቀረበ የወጪ ሒሳቡን አግባብነትና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሰለማያስችል፤
- የመንግሥት ግንዘብ ያላግባብ ሊባክን ስለሚችል፤

ክፍያው እንዲፈጸም በሚመለከተው አካል የተወሰነ ለመሆኑ ማስረጃ እንዲቀርብ፤ በተጨማሪም ለክፍያው የሚያስፈልጉ ማስረጃዎች ሊቀርቡ እንደሚገባ፤ ለወደፊቱም የግንባታ ወጪዎች ምዝገባም ሆነ ክፍያው በውሉ መሰረት የተፈጸመ መሆኑ ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበናል።።

4.16 <u>የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይ ካልሆኑ</u>

<u>አቅራቢዎች የተፈጸመ ግዥ፤</u>

4.16.1 <u>ግኝት</u>

በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በግዥው ተይዞ ስለሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ የወጣውን መመሪያ እንደገና ለማሻሻል በወጣ መመሪያ አንቀጽ 5/1 መሠረት ከብር 50,000.00 በላይ ዋጋ ያለው የእቃ ወይም የአገልግሎት ግዥ መፈጸም የሚቻለው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች የተፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሁለት መሥሪያ ቤቶች በብር 919,838.70 የተፈጸሙ ግዥዎች ለተጨማሪ

እሴት ታክስ ከተመዘገቡ ታክስ ከፋዮች ያልተፈጸመ መሆኑ የታወቀ ሲሆን፣ ዝርዝራቸውም፡-

1. በኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ብር 109,439.00፤
2. በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን ብር 810,399.70፤

4.16.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

መመሪያን ተከትሎ ግዥን ያለመፈጸሙ ምክንያት መንግሥት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ሊያገኝ የሚገባው ገቢ ሊቀንስ ስለሚችል መሥሪያ ቤቶቹ በመመሪያው መሠረት ከብር 50,000.00 በላይ የሆኑ የእቃና የአገልግሎት ግዥዎችን የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ ከሆኑ አቅራቢዎች መፈጸም እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

4.17 <u>ከውል ውጪ የተፈጸመ ክፍያና ለክፍያው ህጋዊ ደረሰኝ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ</u>፤

4.17.1 <u>ግኝት</u>

በፌዴራል መንግሥት የግንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 መሰረት ግዥዎች በውል ሥምምነቱ መሰረት የተፈጸሙ እና ለክፍያውም ተገቢው የክፍያ ደረሰኝ የቀረበላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ በናሙና አዲት ሲደረግ ጥቅምት 30 ቀን 2008 ዓ.ም በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 711708 በከሰም ተንዳኦ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት በከሰም ሳይት አካባቢ ባሉት አርብቶ አደሮች ላይ የተከሰተውን የመጠጥ ውሃ እጥረት ለመቅረፍ አፋጣኝ የውሃ ቦቴ አቅርቦት ከሰኔ 4 ቀን 2006 ዓ.ም እስከ ነሐሴ 30 ቀን 2007 ዓ.ም ድረስ የውሃ እደላ ለተደረገበት ክፍያ የውሃ፣ መስኖና አሌክትሪክ ሚኒስቴር ብር 1,182,600.00 በወጪ መዝግቦ ለአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን ሲልክ፡-

- በውል ስምምነቱ መሰረት የመኪና ኪራዩ ዋጋ ነዳጅን ጨምሮ በቀን ብር 2,000.00 ሆኖ ሳለ ለነዳጅ ብር 281,784.00 ተጨማሪ ክፍያ ተፈጽሞ የተገኘ መሆኑ፤

- ክፍያው ለባለመብቱ ለመፈጸሙ ህጋዊ ማስረጃ ሳይቀርብለት በወጪ እንዲመዘገብ የተደረገ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

4.17.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- ከውል ስምምነት ውጪ ክፍያ መፈጸም የመንግሥት ገንዘብ አላግባብ እንዲወጣ ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤
- ህጋዊ ደረሰኝ ካልቀረበ የክፍያውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንዳይቻል ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤

ከውሉ ውጭ አላግባብ የተፈጸመው ክፍያ ብር 281,784.00 ተመላሽ እንዲደረግ፤ ለክፍያው ህጋዊ ደረሰኝ እንዲቀርብለት አሳስበናል፡፡

4.18 <u>ለተጨማሪ የግንባታ ሥራ ትዕዛዝ የውል ሥምምነት ያልቀረበለት ስለመሆኑ፤</u>

4.18.1 <u>ግኝት</u>

ሰኔ 2002 በወጣው የግዥ መመሪያ በወጣው መመሪያ አንቀጽ 25 መሰረት ከአንድ አቅራቢ ላይ ግዥ ለመፈጸም በአዋጁ አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 1 "መ" እና "ሠ" መሰረት የሚፈጸም ግዥ በዓይነት እና በዋጋ አንድ የሆኑ ዕቃዎችን፣ አገልግሎቶችን፣ የግንባታ ዘርፍ ሥራዎችን እና የምክር አገልግሎቶችን ቀደም ሲል እነዚህን ካቀረበ ተጫራች መግዛት ጠቃሚ መሆኑ ሲታመንበት በአቅራቢው ፍቃደኝነት ላይ በመመሥረትና በመመሪያው ላይ የተቀመጡትን አሰራሮች በመከተል ተጨማሪ ግዥ ለመፈጸም ይቻላል፡፡ ሆኖም በግዥ መመሪያው አንቀጽ 25(11) በአዋጁ አንቀጽ 51(1ሰ) እና 51(2) መሰረት ካልሆነ በስተቀር የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ከአንድ አቅራቢ ለሚፈጽመው ግዥ የውል ሥምምነት መፈረም እንዳለበት የተመለከተ ቢሆንም የሳንታማሪያ ኮንስትራክሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል ለሚያከናውነው ግንባታ በቀረበው የክፍያ ሰርተፊኬት ቁጥር 3 እና 4 ላይ ለለውጥ ሥራ ትዕዛዝ የተጨማሪ ዕሴት ታክስን ጨምሮ ለተፈጸመው ተጨማሪ ክፍያ ብር

26,483,318.00 የተጨማሪ ሥራ ውል ሥምምነት ያልተፈረመ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.18.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በግዥ መመሪያው አንቀጽ 25(11) መሰረት የለውጥ ሥራ ትዕዛዝ ተብሎ በተጨማሪነት ለተፈጸመው ክፍያ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ የውል ሥምምነት ካልተፈራረመ ክፍያው ተገቢነት ላይኖረው ስለሚችል በተጨማሪነት ለተፈጸመው ክፍያ በግዥው መመሪያው መሰረት ተጨማሪ ውል መፈረም እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.19 <u>እጅግ የተጋነነ የማማከር አገልግሎት ክፍያ እና</u>

<u>ለተጨማሪው ክፍያው ውል ያልተፈረመ ስለመሆኑ፤</u>

4.19.1 <u>ግኝት</u>

የስትራተጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ ለማማከር አገልግሎት የፈጸመው ግዥና ክፍያ በግዥ መመሪያውና በተገባው ውል መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ኤጀንሲው በወረታ ከተማ በሚገኘው መጋዘን ውስጥ ለሚያሰራው የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ የማማከር አገልግሎት ግዥ ከአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት የመንገድና ህንፃ ዲዛይን ግንባታና ቁጥጥር ሥራዎች ድርጅት ጋር ውል የፈጸመ ሲሆን፣ በውሉ ስምምነት መሰረት ክፍያ የሚጀምረው የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታውን ለማከናወን በጨረታ አሸናፊ ከሚሆነው ድርጅት ጋር የሚፈጸመው የውል ጊዜ መነሻ ይሆናል ይላል፡፡ ሆኖም የወረታ መጋዘን ቅ/ጽ/ቤት የኤሌክትሪክ መስመር ዝርጋታ ለመስራት ውል የገባው የአማራ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ስምምነቱን እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 30 ቀን 2015 ጀምሮ የተዋዋለ ሲሆን፣ በውሉ መሰረት የማማከር አገልግሎት ሥራውን ለመስራት በወር ብር 33,076.88 እየተከፈለው ሥራው በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ እንደሚጠናቀቅ ተገልጿል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአጠቃላይ የውሉ ከፍል ተራ ቁጥር 14(1) ላይ አጠቃላይ የውሉ ሁኔታዎች ሥምምነት ማስተካከያ (ለውጥ) ሲደረግ የጽሁፍ ሥምምነት መፈረም እንዳለበት

ተመልክቷል፡፡ ሆኖም ኤጀንሲው ለአማካሪ ድርጅቱ ከጥቅምት 16/2008 ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2008 ዓ.ም ድረስ ባለው ጊዜ የአስራ አንድ ወራት ክፍያ ብር 363,845.68 የፈጸመና ለተጨማሪ ጊዜው ምንም አይነት ውል ሳይፈጸም ክፍያ የፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

4.19.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የማማከር አገልግሎት ግዥው በዕቅድና በተገቢው ጥናት ያልተደገፈ በመሆኑ እና በሁለት ወራት መጠናቀቅ ለነበረበት ሥራ አሥራ አንድ ወር ሙሉ ክፍያ መፈጸሙ መንግሥት ላልተገባ ለተጨማሪ ወጪ የዳረገ ስለሆነ ኤጀንሲው እንዲህ ዓይነቱ ሥራ ሲፈጽም በእቅድና በጥናት ላይ ተመስርቶ ሥራውን ማከናወን እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4.20 <u>በጀት እስኪፈቀድ ድረስ ተብሎ ከተጣራ</u>

<u>ሐብት ላይ እንዲቀነስ የተደረገ ክፍያ</u>፤

4.20.1 <u>ግኝት</u>

የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር ፔትሮናንስ ኩባንያ ሊሚትድ የተባለው የቻይና ኩባንያ በመሠረተበት ክስ ላይ በአለም አቀፍ ፍርድ ቤት ለመከራከር ልምድ ያለው አማካሪ በመቅጠር ክርክር ላይ መሆኑንና ለዚሁ አገልግሎት የሚውል ተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ እንደሚያስፈልግ በመጥቀስ የግ/ኢ/ት/ሚኒስቴርን ሰኔ 8/2007 ዓ.ም በቁጥር 8.T/2/15 በተጻፈ ደብዳቤ በጠየቀው መሠረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሰኔ 10 ቀን 2008 ዓ.ም በቁጥር ክሃ002/7/82 በተጻፈ ደብዳቤ በሰጠው ምላሽ በፔትሮሊየም ስምምነት መሠረት ከሚሰበሰበው የመሬት ኪራይና የፊርማ ጉርሻ ሂሳብ ላይ ክፍያ መፈጸም እንደሚቻል ፈቅዷል፡፡ በዚሁ መሰረት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አስፈላጊውን የምንዛሪ ሂደት ጨርሶ በ6251 የሂሳብ መደብ የወጪ ሂሳብን እንዲሁም በሂሳብ መደብ 4103 የባንክ ሂሳብን ክሬዲት በማድረግ ብር 10,121,169.44 በወጪ ከመዘገበ በኋላ እንደገና ምዝገባውን በመቀየር የተጣራ ሐብት (Net Asset Equity) ዴቢት እንዲሁም የወጪ ሂሳብን ክሬዲት በማድረግ ምዝገባ ያከናወነው መሆኑ ታውቋል፡፡ ሆኖም የክፍውን

እና የተሰራውን ማስተካከያ አግባብነት ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ ደንብ ቁጥር 190/2002 ክፍል አምስት አንቀጽ 28(2) "ገቢውን ያገኘው መሥሪያ ቤት በገቢው መጠቀም ካልተፈቀደለት በስተቀር በመንግሥት ንብረት በመገልገል ወይም የመንግሥት ንብረት በማስወገድ የተገኘ ማናቸውም ገቢ በተጠቃለለው ፈንድ ውስጥ ገቢ መደረግ እንዳለበት" የተደነገገ ሲሆን፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ባወጣው የፌዴራል መንግሥት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 አንቀጽ 10(2) መሰረት ደግሞ " ሚኒስቴሩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቱ ያቀረበውን የተጨማሪ በጀት ጥያቄ በመገምገም አስፈላጊነቱን ሲያምንበት እና ከመጠባበቂያ በጀት ወይም በሌላ አማራጭ የማይሸፈን ሆኖ ሲያገኘው የተጨማሪ በጀት ጥያቄ በማዘጋጀት ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እንደሚያቀርብ " መመሪያ ወጥቷል። ነገር ግን መሥሪያ ቤቱ መስከረም 27 ቀን 2009 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር መ1/13/1/2 ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ለክፍያው በጀት እንዲያዝለት በመጠየቅ የተጣራ ሐብት (የሂሳብ መደብ 5601) ዴቢት የወጪ ሂሳብን ክሬዲት በማድረግ ክፍያው ከተጣራ ሃብት ላይ እንዲቀነስ ተደርጓል። ሆኖም ለሂሳቡ በጀት እስኪያዝለት ድረስ ወጪውን ማውጣት ከተፈለገ በተሰብሳቢ ሒሳብ ተይዞ በጀቱ ሲፈቀድ በወጪ እንዲያዝ ሊደረግ ሲገባ ወጪው በቀጥታ ከተጣራ ሐብት ላይ እንዲቀነስ የተደረገ መሆኑ ታውቋል።

4.20.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የሂሳብ መግለጫዎቹ ትክክለኛ የበጀት ዓመቱን ሂሳብ እንዳያመለክት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል የወጪ ሂሳቡ በትክክለኛው የሂሳብ መደብ እንዲመዘገብ በማድረግ የሂሳብ ሪፖርቱ ትክክለኛውን ገጽታ እንዲያሳይ መደረግ እንዳለበት አሳስበናል።

5. በጀት

5.1 ከበጀት በላይ የወጣናሥራ ላይ ያልዋለ የመደበኛና የካፒታል በጀት፤

5.1.1 ግኝት

መ/ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብ መሠረት ሥራ ላይ ማዋላቸውና በጀታቸውንም በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ ከበጀት በላይ ወጪ የሆነ በ12 መ/ቤቶች ከመደበኛ በጀት ብር 7,624,306.43 ፣ ከፒታል ብር 1,554,380.44 በድምሩ ብር 9,178,686.87 ሲሆን ፣በየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት ከ10% ላይ የሆነውን ብቻ በመውሰድ በ33 መ/ቤቶች መደበኛ በጀት ብር 553,850,153.77 እና ካፒታል ብር 446,662,060.67 በድምሩ ብር 1,000,512,214.44 ያልተሰራበት በጀት ተገኝቷል፡፡ /ዝርዝሩ በዚሁ ጽሁፍ በአባሪ-7 እና ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር በአባሪ-33 ቀርቧ፡፡/

5.1.2 የማሻሻያ ሃሳብ

መሥሪያ ቤቶች የተፈቀደላቸውን በጀት በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ይችሉ ዘንድ በዕቅድና በፕሮግራም ላይ የተመሠረተ በጀት ሊይዙ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

6. ንብረት

6.1 የመሥሪያ ቤቶች የንብረት አስተዳደር መንግሥት የንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 እና በተጨማሪም ይህንኑ ለማስፈፀም በወጣው የመንግሥት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚፈጸም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት የአሰራር ክፍተቶች ታይተዋል፡፡ ይኸውም፡-

/በዚህ ጽሁፍ አባሪ-8 እና ከሌሎች መ/ቤቶች ጋር በአባሪ-34 ተመልክቷል/

6.1.2 የማሻሻያ ሃሳብ

የአሰራር ክፍተቶቹ የመንግሥት ንብረቶችን ለብክነትና ለብልሽት የሚያጋልጡ በመሆኑ እና ለንብረት ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆኑ ስለሚችሉ

የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠቃቀም መመሪያ መሠረት መስተካከል እና መፈጸም እንዳለበት አሳስበናል፡፡

6.2 የመሥሪያ ቤቶች የንብረት አያያዝ አጠቃቀምና አወጋገድ ሥርዓት መንግሥት ያወጣውን መመሪያ ተከትሎ የሚፈጸም መሆኑ ሲጣራ በዋንኛነት የታዩት ክፍተቶች ቀጥለው ቀርበዋል፡፡

6.2.1 <u>ግኝት</u>

1. <u>በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በገፈርሳ የአዕምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል</u>፤

2.1 በመድኃኒት ግምጃ ቤት በርካታ የህክምና መገልገያ መሳሪያዎች ያለምንም አገልግሎት ሳይሰጡ ከአንድ ዓመት በላይ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

1.2 በአላቂ እቃዎች ግምጃ ቤት በወቅቱ ጥቅም ላይ ባለመዋላቸው ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ በርካታ ሲሚንቶዎች የሚገኙ መሆኑ፤

2. በኢትዮጵያሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ 26 ላፕቶፖች፣ 40 ዴስክቶፕ ኮምፒዩተሮች፣ አንድ ፕሪንተር በዕቃ መጋዘን ውስጥ ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

3. <u>በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ</u>፤

3.1 በመደበኛ መድኃኒት እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ በብዛት አይጦች ከመኖራቸው የተነሳ መድኃኒቱ ለብልሽት እየተዳረገ ከመሆኑም በተጨማሪ ንጽህናው ያልተጠበቀ በመሆኑ ከፍተኛ ሽታ ያለው መሆኑ፤

3.2 በሽያጭ ፋርማሲ መድኃኒት እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ጊዜያቸው ያለፉባቸው መድኃኒቶች አገልግሎ ከሚሰጡት መድኃኒቶች ጋር ተደባልቀው የሚገኙ መሆኑ፤

3.3 በርካታ አገልግሎት የማይሰጡ የህክምና ቋሚ ዕቃዎች የሚገኙ መሆኑ፤

4. በኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የኬሚካልና የምርምር ዕቃዎች የሚቀመጡበት 38 ግምጃ ቤት ያሉት ሲሆን፣ በናሙና ከታዩት በ22 ግምጃ ቤቶች ውስጥ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተከስተዋል፡-

4.1 የ22ቱም ግምጃ ቤቶች ጠባቂ አንድ ሰው ብቻ መሆኑ፤

4.2 የኬሚካልና የምርምር መገልገያዎቹ እስቶር ኃላፊ ወደ እስቶር ሲገቡ የሚለብሱት ከሚካሎቹን መቋቋም የሚችል የጥንቃቄ ልብስ የሌላቸው መሆኑ፤

4.3 በግምጃ ቤቱ ውስጥ ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ የተቀመጡ አደገኛ ኬሚካሎች ሳይወገዱ ለረጅም ጊዜ የቆዩ ከመሆናቸው በተጨማሪ መጋዘኑ ከህንጻው ሥር (Under Ground) ሲሆን፣ የውሃና የሽንት ቤት ፍሳሽ በውስጡ አቋርጦ የሚያልፍ በመሆኑ ኬሚካሎች ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ፤

4.4 በግምጃ ቤቱ ውስጥ የተበላሹና አገልግሎት የሚሰጡ ኬሚካሎችና ለምርምር የሚያገለግሉ መሣሪያዎች በግምጃ ቤት ውስጥ በአንድ ላይ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

በ2006 በጀት ዓመት አዲት ወቅትም ስለሁኔታው ተገልጸ አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም እርምጃ ሳይወሰድ የተገኘ መሆኑ፤

5. በኢትዮጵያ ምግብ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን በውጭ ምንዛሪ የተገዙ በርካታ መጽሐፍቶች ለብልሽት በተጋለጠ መልኩ በካርቶንና በማዳበሪያ የተቀመጡ ሲሆን፣ በተጨማሪም ጠረጴዛ፣ ወንበር ኮምፒዩተር፣ የግርግዳ ሰዓት፣ ዲቨዲ፣ ፍሬም ዲዛይን ባለመስታወት ከአንድ ዓመት በላይ ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፤

6. በብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ አገልግሎት የማይሰጡ ኮምፒውተሮች፣ ኤርኮንድሽነር፣ ፎቶ ኮፒ ማሽን ፣ የተለያዩ የሚቲዎሮሎጂ ዕቃዎች እና የተለያዩ የብረታ ብረት ዕቃዎችና የመሳሰሉት ሳይወገዱ በዕቃ ግምጃ ቤቱ የሚገኙ ሲሆን፣ ስለሁኔታው በ2007 በጀት ዓመት አዲት ወቅትም አሰተያየት የተሰጠበት ቢሆንም የማሰተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

7. <u>የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር</u>፤

7.1. በስቴሽነሪ ዕቃ ግምጃ ቤት አገልግሎት የማይሰጡ ፕሮጀክተር፣ ስካነር ፣ ኮምፒዊተር ፣ ካሜራ ፣ የተለያዩ ሞደሞች፣ ሌንስ ፕሮጀክተር፣ ፋክስ፣ አይረን ፓይፕ፣ ሜትር፣ የፕሪንተር እና የፋክስ ቶነሮች ካኖን 5570/670 ካኖን 1015-6310 ሳይወገዱ የሚገኙ መሆኑ፤

7.2 ከቀድሞው ኢነርጂ ባለሥልጣን የመጡ በርካታ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች ጥቅም ላይ ሳይውሉ በመለዋወጫ ስቶር ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤

7.3 አሚቼ በሚገኘው መጋዘንና ጋራዥ አገልግሎት የማይሰጡ ሊዝ ማሽን የብረት ቅርጽ ማውጫ ማሽን፣ ጥቅልና በየቦታው የተከማቹ የተጠቀለሉ የአርማታ ብረቶች እንዲሁም ለረጅም ዓመታት ለጸሐይና ለዝናብ የተጋለጡ ኬሚካል የያዙ እሽግ ብረት በርሜሎች የሚገኙ መሆኑ፤

8. <u>የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር</u>፤

8.1. በካዛንችስ አላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት የታይፕ ወረቀቶች ብዛት 76፣ የታይፕ ሪቫን ብዛት 7፣ ፊሊፕ ቻርት ብዛት 100፣ Epson የፕሪንተር ሪቫን 7754 ብዛት 104፣ IBM Ribbon ብዛት 12፣ Cannon Cartridge Film Ribbon ብዛት 19፣ ፎቶ ኮፒ ቶነር 2030 ብዛት 3፣ የፓርከር መቀያየሪያ ብዛት 27 እና ሌሎችም አገልግሎት የማይሰጡ የጽህፈት ዕቃዎች ከ2002 ዓ.ም. ጀምሮ ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

8.2 በሳሪስ እና በቃሊቲ አላቂ ዕቃ ግምጃ ቤቶች አገልግሎት ላይ የማይውሉ በርካታ የተለያዩ ሕትመቶች የሚገኙ መሆኑ፤

8.3 በሳሪስ ማዕከላዊ የመለዋወጫ ዕቃ ግምጃ ቤት የተለያዩ አገልግሎት የማይሰጡ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች የሚገኝ መሆኑ፤

8.4 <u>በሳሪስ ቁጥር ሁለት ማዕከላዊ የከባድና ቀላል ዕቃዎች ግምጃ ቤት</u>፤

- የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች፣ የህንጻ መሳሪያዎች፣ የቧንቧ ዕቃዎች፣ ጎማዎች፣ አካፍና ዶማ፣ የአሳ መያዣ ክር እና 14 ተሽከርካሪ ወንበሮች አስሩ ሳይገጣጠሙ፣ ፍሪጆች አገልግሎት ላይ ሳይወሉ የሚገኙ መሆኑ፤
- በኮንቴነሩ ውስጥ የሚገኙና ኮንቴነሩ ቢከፈት ለጤና ላይ ጎጂ የሆኑ ኬሚካል፣ የደረቁ ማዳበሪያዎች፣ የጓሮ አትክልት ዘር፣ ኮንዲዩት (ለሕንጻ ሥራ የሚያገለግል)፣ የምግብ ዘይት፣ የቅባት እህሎች፤ በኮንቴር ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤
- በግቢው ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ ብዛት ያላቸው የተለያዩ ጎማዎች፣ ብረታ ብረቶች፣ የተጠቀለለ ሽቦ እና የሚወገዱ መኪናዎች ጸሀይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው የሚገኙ መሆኑ፤

8.5 <u>የፅዋትና የአዝርዕት ኬሚካሎች ዕቃ ግምጃ ቤት</u>፤

- አንድ ከቆርቆሮ የተሰራ መጋዘን ከአንድ በኩል ጣራው የተገነጠለ፣ የግቢው አጥሩ የወደቀና ውሃና መብራት የሌለው ሲሆን፣ ቁልፉም በንብረት ሰራተኛው እጅ የማይገኝ በመሆኑ በውስጡ ያለውን ንብረት ለማየት ያልተቻለ መሆኑ፤
- በግቢው ውስጥ ከቆርቆሮ የተሰሩ በርሜሎች ጸሀይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው የሚገኝና በተለያዩ መጋዘን ውስጥ

ተመላሽ የተደረጉ የተለያዩ ፍራሾች፣ ጄሪካኖችና የውሃ መቅጃ ባልዲዎች ያለአገልግሎት የሚገኙ መሆኑ፤

8.6 <u>በሳሪስ ዕቃ ግምጃ ቤት፤</u>

አሮጌ ፕላስቲክ የፊልድ ድንኳኖች፣ የድንኳን ጠረጴዛና ወንበሮች፣ መደርደሪያዎች፣ ኬሚካል መርጫ መሳሪያ የሚያገለግል፣ ኦክሲጂን 4 እና የላብራቶሪ ዕቃዎች (ለምሳሌ ከ1991 ዓ.ም ጅምሮ የሚገኝ Rate tender ብዛት 207፣ ከ2002 ዓ.ም ጀምሮ የሚገኝ Filter Paper ብዛት 32 Pack፣ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ የሚገኝ Xylene Bottle ብዛት 78፣ ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የሚገኝ Pyrex Flu ብዛት 432 ፣ Round Filter ብዛት 40፣ Killing Jar Large ብዛት 15) ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

8.7 <u>በቃሊቲ ዕቃ ግምጃ ቤት፤</u>

በተለያዩ ግምጃ ቤት ለጤና እና ለአካባቢው አስጊ የሆኑ የሚወገዱ ኬሚካሎች፣ ባትሪ ድንጋይ፣ ባለ 25 ሊትር በርሜሎች፣ የተሰባበሩ የቢሮ ዕቃዎች፣ ወንበር፣ ሼልፍ፣ ጠረጴዛ፣ የባኞና የሽንት ቤት ዕቃዎች፣ ፍሪጅ፣ የፈረስ ኮርቻ የለስላሳ ጠርሙሶች፣ ከቀርከሃ የተሰሩ ትንንሽ ሙቀጫዎች፣ የተሰባበሩ የጋራጅ ዕቃዎችና አንድ ኮንቴነር ጣራ የሌለው በውስጡ የአይጥ ወጥመድ፣ የፎቶ ኪፒ ማሽን፣ የተለያዩ ብረታ ብረቶች የሚገኙ መሆኑ፤

8.8 <u>በቃሊቲ የተመላሽ ዕቃ ግምጃ ቤት፤</u>

በርካታ የመንገድ አልጋዎች፣ ፍራሾችና ትራሶች፣ የተለያዩ የላብራቶሪ ማሽኖች፣ መጋረጃዎች፣ ድንኳኖች ከነካስማው፣ የቡና ጥራት መቅመሻ ዕቃ፣ ፋይሊንግ ካቢኔት፣ የቢሮ ጠረጴዛና ወንበሮች፣ ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ ኮምፒውተሮች፣ ስሊፒንግ ባግ፣ ፍሪጆች እና 10 የካርታ ማተሚያ፣ በተለያዩ መጋዘኖች የሚገኙና በግቢው ውስጥ ሜዳ ላይ እና ጥግ ጥጉን ወድቀው የሚታዩ የጤፍ መዝሪያ ባለ 2 ሌቨል (Level) ብዛት 204 እና ባለ 3 ሌቨል

(Level) ብዛት 329፣ 4 ፍሪጆች፣ 4 የእሳት ማጥፊያ 4፣ የውሃ ማሞቂያ 2 እና በተጨማሪም በርካታ በነዳጅ የሚሰሩ ማረሻ፣ ማለስለሻና ያለምንም አገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

በአብዛኛዎቹ ላይ ባለፉት በጀት ዓመታት አዲት ወቅትም ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠባቸው ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

9. **<u>በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በአላጌ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ፤</u>**

9.1 በቴክኒክ እቃ ግምጃ ቤት ያሉ በርካታ ብረታ ብረቶች እንዲወገዱ ያልተደረገ መሆኑ፤

9.2 የኮሌጁ ቁራ ለረጅም ጊዜ የኤሌትሪክ ሲስተሙ ስለተበላሸ አገልግሎት የማይሰጥ መሆኑ፤

9.3 በማረጃው ቁራ ውስጥ የሚገኙ 3 ዲፕ ፍሪጅዎች (የጥሬ ስጋ ማስቀመጫ ትልቁ ፍሪጅ፣ የበሰለ (የተቀቀለ) ስጋ ማስመጫ መካከለኛ ፍሪጅ እና የቢራ ማስቀመጫ ፍሪጅ)፣ የእሳማ ስጋ እና ቅመማቅመሞች ማደባለቂያ ማሽን፣ በውሃ የሚሰራ የሞርቴዴላ ማሸጊያ ማሽን እና በእንፋሎት ማንኛውንም ስጋ የሚቀቅል ማሽን ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ሳይሰጡ የሚገኙ መሆኑ፤

9.4 በማረጃው ቁራ እስቶር ውስጥ 24 የፕላስቲክና 10 ትልልቅ የስጋ ማስቀመጫ ሳህኖች፣ ጥቅም ላይ ያልዋለ 1 ቬንትሌተር እና 2 ኮንፕረሰር፣ የቢለዋ መቀቀያ ማሽን፣ ከቦታ ቦታ የስጋ መውሰጃ ፍሪጅ፣ የተለያዩ መለዋወጫ ያዎች እና ከማሽኑ ጋር የመጡ 12 ኬሚካሎች እና የልብስ ማጠቢያ ማሽን ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ሳይሰጡ የሚገኙ መሆኑ፤

9.5 የወተት ማለቢያ ማሽኖች ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ሳይሰጡ የተገኙ መሆኑ፤

9.6 ኢንኩቤተር እና ገሪ የሚባል ማሽን ከ1994 ጀምሮ ለኮሌጁ አገልግሎት ሳይሰጥ የተገኘ መሆኑ፤

9.7 አገልግሎት መስጠት የሚችል በርካታ ችጥዶች አገልገሎት ሳይሰጡ ለረጅም አመት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

9.8 ተቀቅሎ በስራ ላይ ሊውል የሚችል እጅግ በጣም ብዙ ያልተቀቀለ የሸክላ ጡብ ግድግዳ በሌለው መጋዘን ውስጥ ተከማችቶ የተገኘ መሆኑ፤

9.9 21 የጨፍ መዝሪያ ማሽን ዝናብና ጸሀይ እየተፈራረቀበት የሚገኝ መሆኑ፤

9.10 ከ1995 ጀምሮ ጥቅም ላይ ያልዋለ የኬሚካል እና የላብራቶሪ መገልገያ እቃዎች የሚገኙ መሆኑ፤

9.11 አብጃታ ካምፓስ በሚገኘው የተመላሽ እቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ኮሌጁ ህጻናት አምባ ከነበረበት ወቅት ጀምሮ የነበሩ በርካታ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ለምሳሌ ያህል የተለያዩ ሞዴል ብስክሌቶች ብዛት 26 ከ30 በላይ የሚሆኑ አሮጌ ጎማዎች፣ የፕላስቲክ ማስመሪያ 496፣ የጫማ ብሩሽ 236፣ ታይፕራይተር 17፣ የማባዣ ማሽን 5 ፣ ፕላስቲክ ዝርግ ሰሃን 139፣ ሹካ 587 ፣ማንኪያ 114፣ የተለያዩ ብረት ድስቶች 18 የህጻናት አልጋ 110 ሳይወገዱ ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

በአብዛኛዎቹ ላይ ቀደም ሲል በተደረገው ኦዲት ወቅት ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየየት የተሰጠ ቢሆንም ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

10. <u>በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ፤</u>

10.1 በቋሚና አላቂ ዕቃ ግምጃ ቤት ጊዜ ያለፈባቸውና አገልግሎት የማይሰጡ ሊወገዱ የሚገባቸው 9ሺ ካርዶች፣ 13 ጥራዝ ሜሞ ፣ 66 ጥራዝ ፒአር እና 12 ኤልሲዲ ፕሮጀክተሮች የሚገኙ መሆኑ፤

10.2 በተማሪዎች የምግብ ጥሬ ዕቃዎች ግምጃ ቤት ለተማሪዎች ቀለብ ተብሎ ከተገዛው የምግብ ጥሬ ዕቃ ላይ ሐምሌ 20 ቀን 2007 ዓ.ም 15 ኩንታል የዳቦ ዱቄት፣ 5 ኩንታል ክክ ሽሮ፣ 5

ኩንታል ጥሬ ክክ እና 3 ኩንታል ጨው ለኮሌጁ ሠራተኞች ካፍቴሪያ በብድር ተሰጥቶ ሳይመለስ ከዓመት በላይ ያለፈው መሆኑ፤

10.3 በመለዋወጫ ግምጃ ቤት ኮሌጁ የማይተቀምባቸው 2 የበቆሎና 2 የሩዝ መፈልፈያ ማሽኖች ያለአገልግሎት ለረጅም ጊዜ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

10.4 **<u>በአሳሳ መጋዘን ግቢ</u>፤**

- ✓ በርካታ አሮጌ ጎማዎች የተለያዩ ብረታ ብረቶች ተከማችተው የሚገኙ ከመሆኑም በላይ ምንም መጠለያ ስለሌላቸው ለፀሐይና ለዝናብ ተጋልጠው የሚገኙ መሆኑ፤
- ✓ አገልግሎት የማይሰጡ ሊወገዱ የሚገባቸው የተለያዩ ኬሚካሎች የሚገኙ መሆኑ፤

10.5 በኮሌጁ ክሊኒክ በርካታ የህክምና ዕቃዎች ቢኖሩም በሰለጠነ የሰው ኃይል እጥረት ምክንያት ያለአገልግሎት ታሽጎባቸው የሚገኙ መሆኑ፤

10.6 በአገለገሉ ዕቃዎች (ሳልቫጅ)ግምጃ ቤት ሊወገዱ የሚገባቸው በርካታ አሮጌ ጎማዎች፣ 6 የውሃ ማሞቂያዎች፣ 28 ታይፕራይተሮች፣ 4 የፋክስ ማሽን፣ 14 የባኞ ቤት ሲንክ፣ 8 የመኪና ባትሪዎች፣ 22 የላስቲክ በርሜሎች፣ እና ሌሎችም ቁሳቁሶች ተከማችተው የሚገኙ መሆኑ፤

በ2006 በጀት ዓመት ሂሳብ አዲት ወቅት በተወሰኑት ላይ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤

11. <u>በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ</u>፤

11.1 በርካታ አሮጌ ወይም አገልግሎት መስጠት የማይችል የመኪና መለዋወጫዎች ሳይወገዱ በአሮጌ የመኪና መለዋወጫ እስቶር ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤

11.2 9,960 እስቶክ ካርድ ምንም አገልግሎት ሳይሰጡ ከ2003 በጀት ዓመት ጀምሮ በእስቶር ውስጥ ያለ መሆኑ፤

11.3 በርካታ ደረሰኞች ያለምንም አገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

11.4 አገልግሎት የማይሰጡ ሃያ ስድስት (26) ፍሪጆች፣ አንድ የውሃ ሞተር ፓምፕ፣ ሁለት ጄነሬተሮች፣ ወንበሮች፣ በርካታ ኮምፒዩተሮች፣ ታይፕ ራይተር፣ ፕሪንተሮች እንዲሁም የፎቶ ኮፒ ማሽኖች በስቶር ውስጥ ያለአገልግለት የሚገኝ መሆኑ፤

11.5 አገልግሎት የማይሰጡ ከሰማኒያ በላይ የሚሆኑ ጎማዎች የሚገኙ መሆኑ፤

11.6 የኮሊጁ ላይብረሪ እየፈራረሰ መሆኑ፤

12 <u>በብሄራዊ እንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ማዕከል</u>፤

12.1 ከግንቦት 2006 ዓ.ም ጀምሮ አስራ አንድ የፎቶ ኮፒ ቀለሞች የአንዱ ዋጋ ብር 672.75 ጠቅላላ ዋጋቸው ብር 7,400.25 የሆኑ ያለአገልግለት በስቶር ውስጥ የሚገኙ መሆኑ፤

12.2 ከ1990 ዓ.ም ጀምሮ የገቡ በርካታ ኬሚካሎች የተበላሹና የአገልግሎት ዘመናቸውን የጨረሱ (ሰልፈሪክ አሲድ መሬት ላይ ፈሶ) በስቶር ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ ከመሆናቸውም በላይ በሰራተኞች ላይ የጤና ችግር እያስከተሉ የሚገኙ መሆኑ፤

12.3 በርካታ ተመላሽ የተደረጉ የመኪና መለዋወጫዎች ወደ 40 የሚሆኑ ዴስክቶፕ ኮምፒዩተሮች 6 ላፕቶፕ እንዲሁም ሌሎች በርካታ ኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ያለአገልግሎት በስቶር ውስጥ ተቀምጠው የሚገኝ መሆኑ፤

12.4 በግንባታ ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ 5 ላሜራ ብረት፣ 33 ዶማ እንዲሁም የተለያዩ ብረታ ብረቶች (ለምሳሌ ያህል Steel fencing stand ብዛቱ 1,011) ለረጅም አመታት ያለአገልግሎት በስቶር ውስጥ ተቀምጠው የሚገኝ መሆኑ፤

13 በኢትዮጵያ ዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን ፤

13.1 በዋናው መሥሪያ ቤት፤

- ህገወጥ የዱር እንስሳት ውጤቶች ማስቀመጫ መጋዘን ሰራተኛ ጳጉሜ 3 ቀን 2007 ዓ.ም ጀምሮ ከስራቸው የለቀቁ እና መጋዘኑ የታሸገ ሲሆን ለሁለት ዓመት ያህል ምንም ዓይነት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤
- ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በተከራየው የክብር እቃ ማስቀመጫ ሳጥን የሚገኙ የኢትዮጲያ ግዛት የሚል የወርቅና የብር ሳንቲሞች እንዲሁም የተለያዩ የከበሩ እቃዎች ከሚያዝያ 2000 ጀምሮ የንብረት ቆጠራ ያልተደረገላቸው ከመሆኑም በተጨማሪ ንብረቱን በወቅቱ የተረከቡት ሰራተኛ ከንብረት ክፍል የለቀቁና አሁን ላሉት የንብረት ሰራተኞች ጋር ርክክብ ያልተደረገ እና የሳጥኑ ቁልፍ የጠፋ በመሆኑ የከበሩ እቃዎቹ አሁን ያሉበት ሁኔታ የማይታወቅ መሆኑ፤

13.2 በጋምቤላ ብሄራዊ ፓርክ፤

- ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ የመኪና ጎማዎች፣ ላፕቶፕ ኤችፒ፣ ኮምፒተሮች፣ ጄነሬተር፣ ፍሪጅ፣ ስሊንደር፣ ኮንካቲቪ፣ ፕሪንተርና ጂፒኤስ የሚገኙ መሆኑ፤
- በእቃ ግምጃ ቤቱ የሚገኙ አላቂና ቋሚ እቃዎች በበርሜል ከተሞሉ እንደ ቤንዚን ካሉ በቀላሉ ሊቀጣጠሉ ከሚችሉት ጋር በአንድ ላይ ተቀምጠው የተገኙ መሆኑ፤

13.3 በአቢጃታ ሻላ ብሄራዊ ፓርክ፤

- ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ የመኪና ጎማዎች፣ ጠመንጃዎች፣ ፕሪንተር፣ ባይናኩላሮች፣ ፍሪጅ፣ ሲሊንደር፣ የተሰባበሩ ብረቶች፣ የሽቦ አልጋዎች፣ በርሜሎች፣ የመኪና ባትሪዎች፣ ተሸከርካሪ ወንበሮች፣ ለረዥም ጊዜ አገልግሎት ሳይሰጥ

የተቀመጡ የመኪና መለዋወጫዎች፣ ታይፕ ራይተር እና ሌሎችም በርካታ አሮጌ እቃዎች የሚገኙ መሆኑ፤

- ከአብያታ ሻላ ብሄራዊ ፓርኩ ወደ ገራይሌ ብሄራዊ ፓርክ የተዛወሩ ሰራተኛ የፓርኩ ንብረት የሆነውን ላፕቶፕ ኮምፒውተር እና ሌሎች ንብረቶችን ሳያስረክቡ የተዛወሩ መሆኑ፤

14 <u>በብሄራዊ ደም ባንክ አገልግሎት</u>፤

በርካታ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች (16 ኮምፒተሮች፣ 5 ፕሪንተር ፣ 3 ፎቶ ኮፒ ማሽን ፣ 4 center feug ፣ 2 center feug ፍርጅ ፣ 3 ዲፕ ፍርጅ ፣ 3 Incubator (ማሞቂያ)፣ 2 Dry Oven ፣ 1 Outoclave ፣ 224 ሶዲየም ክሎራይድ ፣ 1 Newamatic ከፍተኛ አደጋ ሊያስከትል የሚችል ኬሚካል ፣ በርካታ የተሰባበሩ ወንበሮች እና ጠረጴዛ፣ 112 UPS ፣ 27 የሰው ሚዛን እና የመሳሰሉት) በእቃ ግምጃ ቤት የሚገኙ መሆኑ፤

15 <u>በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር</u>፤

15.1 በዋናው መሥሪያ ቤት ዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ የመኪና መለዋወጫ አዲስና አሮጌ ጎማዎች ፣ ኮምፒውተሮች፣ የተለያዩ የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች ፣ አሮጌ የስልክ ቀፎዎች፣ አሮጌ ላፕቶፖች ፣ አዲስና አሮጌ የእንግዳ ወንበሮች፣ የቢሮ ጠረጴዛዎች አዳዲስ የኃላፊ ወንበሮች፣ ካሜራዎች ያለአገልግሎት ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

15.2 በሳሪስ መጋዘን ውስጥ የሚገኙት በርካታ የሚወገዱ ዕቃዎች ለምሳሌ ጋዜጦች፣ ጎማዎች፣ ጠረጴዛዎች፣ ጣውላዎች፣ ወንበሮች፣ ሲዲዎች፣ የኤሌክትሪክ ገመዶች፣ የመኪና መለዋወጫዎች፣ ውሃ ማጣሪያዎች እና የመሳሰሉት ሳይወገዱ ለበርካታ ዓመታት በመጋዘኑ ውሰጥ ተቀምጠው የሚገኙ መሆኑ፤

15.3 ከዋናው መሥሪያ ቤት ግቢ ውጭ በኮንቴነር የተቀመጡ የመኪና መለዋወጫዎች፣ ጎማዎች እና የተለያዩ የሚወገዱ ዕቃዎች የሚገኙ መሆኑ፤

16 <u>የፌዴራል የተቀናጀ የከተማ መሬት መረጃ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት</u>፤

አገልግሎት የማይሰጡ አስራ አንድ ተሽከርካሪ ወንበር፣ ስድስት ጠረጴዛ፣ የተለያዩ የስልክ ቀፎዎች፣ ዩፒኤስ፣ ኮምፒተር፣ ሃያ ሁለት የመኪና ጎማ የመሳሰሉት በዕቃ ግምጃ ቤት ውስጥ ሳይወገዱ የተገኙ መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

6.2.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

በንብረት አስተዳደሩ ላይ የታዩት ክፍተቶች ፡-

- ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም ምክንያት ሊሆኑ ስለሚችሉ፤
- ንብረቶቹ ለብክነትና ለከፋ ለብልሽት ሊጋለጡ ስለሚችሉ፤
- የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው ንብረቶች በወቅቱ ጥቅም ላይ የማይውሉ ከሆነ ለመንግሥት ገንዘብ ያለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆኑ ስለሚችሉ፤

የንብረት አያያዙ እና አጠቃቀሙ መንግሥት ባወጣው መመሪያ መሠረት እንዲስተካከል እና እንዲፈጸም ተገቢው ሥራ መሰራት እንዳለበት አሳስበናል፡፡

6.3 የመሥሪያ ቤቶች የተሽከርካሪ ሥምሪት፣ አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ በፌዴራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት መፈጸሙን ለማረጋገጥ አዲት ሲደረግ፤

6.3.1 <u>ግኝት</u>

1. <u>ሊቢሬ ያልቀረበላቸው (የሌላቸው) ተሽከርካሪዎች</u>፤

✓ በአምስት መሥሪያ ቤቶችና በአንድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ለ37 የተለያዩ ዓይነት መኪኖች፣

- ✓ በሶስት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ለ11 ሞተር ብስክሌቶች፣
- ✓ በአንድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ለ1 ትራክተር፣

2. <u>በብልሽት ምክንያት ለረጅም ጊዜያት የቆሙ ተሽከርካሪዎች</u>፤

- ✓ በስምንት መሥሪያ ቤቶችና በአምስት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች 144 የተለያዩ ዓይነት መኪኖች፣
- ✓ በሁለት መሥሪያ ቤቶችና በአንድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች 16 ሞተር ብስክሌቶች፣
- ✓ በአንድ መሥሪያ ቤት 1 ሎቤድ ተሳቢ፣
- ✓ በአንድ መሥሪያ ቤት 1 ፎርክሊፍት፣
- ✓ በአንድ መሥሪያ ቤት 2 ትራክተሮች፣

3. <u>ሊቢሪያቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሥም የሆኑ</u>፤

- ✓ በስድስት መሥሪያ ቤቶችና በአንድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት 180 የተለያዩ ዓይነት መኪኖች፣

4. <u>የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው</u>፤

- ✓ በሶስት መሥሪያ ቤቶችና በአንድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት 6 መኪኖች፣
- ✓ በአንድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት 1 ትራክተር፣

ናቸው። ለዝርዝሩ አባሪ 8 እና አባሪ -35 ተያይዟል።

6.3.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

- ✓ በወጣው የተሽከርካሪዎች መመሪያ መሰረት ያለመፈጸም በውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ ላይ ክፍተት ሊፈጥር ስለሚችል፣
- ✓ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተራቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶች የሆኑ እንዲሁም የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸውን ተሽከርካሪዎች የመሥሪያ ቤቶቹ ንብረቶች ናቸው ብሎ ለመቀበል ሊያስቸግር ስለሚችል፣
- ✓ ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የሚችሉ ተሽከርካሪዎች ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ካልተደረገ፤ አገልግሎት መስጠት የማይችሉት

ደግሞ እንዲወገዱ ካልተደረገ ለከፋ ብልሽት ሊዳረጉና ዋጋቸው ሊቀንስ ስለሚችል፣

መሥሪያ ቤቶቹ በተሽከርካሪዎቹ አያያዝ፣ አጠባበቅና አወጋገድ ላይ የታዩትን ክፍተቶች በመመሪያው መሰረት ማስተካከል እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

7. እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፉት በጀት ዓመታት ግኝቶች፤

7.1 የፌዴራል ዋና ኦዲተር ያለፉት በጀት ዓመታት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት መሥሪያ ቤቶች ተገቢውን እርምጃ የወሰዱ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

7.1.1 ግኝት

1. በስድስት መሥሪያ ቤቶችና በአንድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት መመሪያን ሳይከተሉ የፈጸሙት የውሎ አበል ክፍያ ብር 727,379.31 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
2. በሶስት መሥሪያ ቤቶች ሰራተኞች ከሥራ ከለቀቁ በኋላ የተከፈለው ደመወዝ ብር 21,678.37 ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤
3. በሶስት መሥሪያ ቤቶች ሚኒስትሮች ምክር ቤት ባወጣው መመሪያ መሰረት ከደመወዝ ላይ ያልተቀነሰው የሕክምና መዋጮ ብር 11,461.32 ገቢ እንዲሆን ያልተደረገ መሆኑ፤
4. በአራት መሥሪያ ቤቶችና በአንድ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት ሂሳብ ብር 4,180,693.38 በዚህ በጀት ዓመት ኦዲት ወቅትም ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፤

ታውቋል፡፡

7.1.2 የማሻሻያ ሃሳብ

መሥሪያ ቤቱ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት የማስተካከያ እርምጃ የማይወሰድ ከሆነ፡-

- ለአዲት ሪፖርት የሰጡት ግምት አንስተኛ መሆኑን ሊያመለክት ስለሚችል፤
- ለውስጥ ቁጥጥር ሥርዓቱ መዳከም እንዲሁም ለመንግሥት ገንዘብ እና ንብረት መባከን እና አለ አግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤

በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ፤ ለወደፊቱም በአዲት ሪፖርት በሚሰጡት የማሻሻያ ሃሳቦች መሰረት እርምጃ ለመወሰዱ ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር መደረግ እንዳለበት በድጋሚ አሳስበናል፡፡

8. ልዩ ልዩ ፤

8.1 ከውል ውጪ የተፈቀደ ሴሌክትድ ማቴሪያል፤

8.1.1 ግኝት

በእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስቴር የብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል እና የሆለታ የአስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያን የውስጥ ለውስጥ አስፋልትና ለጠጠር መንገድ ለማሰራት ማዕከሉ ከኃቨሪም ኮንስትራክሽን ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ ጋር የውል ስምምነት የፈጸመ ሲሆን፣ ድርጅቱ ለመንገድ ሥራው የሚሆን ሴሌክቲቭ ማቴሪያል ከሆለታ የአስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ ቆፍሮ ለመጠቀም ይችል ዘንድ እንዲፈቀድለት ሰኔ 2 ቀን 2007 ዓ.ም በደብዳቤ ቁጥር HVT/540/07 ማዕከሉን በጠየቀው መሰረት፡-

- ድርጅቱ ሴሌክቲቭ ማቴሪያል የሚጠቀምበት ቦታ ከ1/2 (ግማሽ) ሄክታር እንዳይበልጥ፣
- ለሆለታ አስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ ለሌላ ጊዜ የሚያገለግል ሰሌክትድ ማቴሪያል ድርጅቱ እንዲያዘጋጅና ቦታው ላይ እንዲያደርስ፣
- የግጦሽ ቦታን ሳይጎዳ በአንድ መንገድ እንዲጠቀም፣

የተፈቀደ መሆኑን የማዕከሉ ዋና ዳይሬክተር ገልጸዋል፡፡ ሆኖም፡-

1. በውል ሥምምነቱ ላይ ከሆለታ አስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ መንገድ ሥራ ለሴሌክቲቭ ማቴሪያል የሚሆን ክፍያ በውሉ ውስጥ የተካተተና ክፍያውም የተፈጸመ ቢሆንም ድርጅቱ ሰሌክትድ ማቴሪያሉን ከሆለታ አስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ የተጠቀመ በመሆኑ ገንዘቡ በውል ሥምምነቱ ላይ ለሰሌክትድ ማቴሪያል ተብሎ ከተቀመጠው ላይ ተቀናሽ እንዲሆን ያልተደረገ መሆኑ፤

2. ድርጅቱ ሴሌክቲቭ ማቴሪያሉን ከሆለታ ጣቢያ ቆፍሮ እንዲጠቀም ሲፈቀድለት፡-

   2.1. የሚጠቀምበት ቦታ ከ1/2 (ግማሽ) ሄክታር ሳይበልጥ የተፈቀደ ቢሆንም በተባለው መሰረት የተፈጸመ ለመሆኑ ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣

   2.2. ለሌላ ጊዜ የሚያገለግል ሰሌክትድ ማቴሪያል ድርጅቱ እንዲያዘጋጅና ቦታው ላይ እንዲያደርስ በተባለው መሰረት ድርጅቱ ሰሌክትድ ማቴሪያል አዘጋጅቶ ቦታው ላይ ያላደረሰ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

8.1.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

የመንገድ ሥራው በውሉ መሰረት ካልተፈጸመ፡-

- ለመንግሥት ገንዘብ አለአግባብ መውጣት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል፤
- የመንግሥትን ጥቅም የሚያስጠብቅ ስለማይሆን፤

በውል ሥምምነቱ ላይ ከሆለታ አስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ መንገድ ሥራ ለሴሌክቲቭ ማቴሪያል የሚሆን ክፍያ በውሉ ውስጥ የተካተተና ክፍያውም የተፈጸመ ሆኖ ሳለ ድርጅቱ ሰሌክትድ ማቴሪያሉን ከሆለታ አስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ መጠቀሙ አግባብ ስላልሆነ በውል ሥምምነቱ ላይ ለሰሌክትድ ማቴሪያል ተብሎ የተቀመጠው ገንዘብ ተመላሽ እንዲሆን መደረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

8.2 ከፍተኛ በሆነ የመተንፈሻ አካል ህመም ምክንያት እየተቀጠፉ የሚገኙ የወተት ላሞችን በተመለከተ፤

8.2.1 ግኝት

የብሔራዊ ሰው ሰራሽ እንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል የ2007 በጀት ዓመት ሂሳብና ንብረት ኦዲት በተደረገበት ወቅት በሆለታ በሚገኘው አስኳል መንጋና ዝርያ ማሻሻያ ጣቢያ ግንቦት 10 ቀን 2005 ዓ.ም ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪ ወጥቶባቸው ከተገዙት 300 የሆሊስቴይን ፍሬዢያ ላሞች 84 ብቻ የቀሩ መሆኑ ተገልጸ ለቀረበው ግኝት ማዕከሉ ኮርማዎቹን ለአባለዝር ምርት ለማዋል ወይም ለማስወገድ ከብሄራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት ቴስት የሚያደርግ ኪት ከውጭ አገር በማስገባት ሂደት ላይ እንደሆነ እና ምርመራው ከተጠናቀቀ በኋላ በቅርብ ጊዜ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን በወቅቱ በሰጠው ምላሽ ላይ ተገልጿል። ነገር ግን በአሁኑ ኦዲት ወቅትም ለመገንዘብ እንደተቻለው ከ2007 በጀት ዓመት ወደ 2008 በጀት ዓመት በቆጠራ የዞሩ የወተት ላሞች ብዛት 475 ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ 127 ወደ ጣቢያው የገቡት ተደምረው 602 ላሞች የደረሱ ቢሆንም ከነዚህ ውስጥ 179 ላሞች ከፍተኛ በሆነ የመተንፈሻ አካል ህመም ምክንያት በሆነው አይቢአር (IBR) (Infection Bovinerino Tricitits) ቫይረስ መሞታቸውና በህይወት ያሉትም በዚህ መድኃኒት በሌለው ቫይረስ የተጠቁ በመሆኑ የሞሞቻ ጊዜአቸውን እየተጠባበቁ የሚገኙ መሆኑ ታውቋል።

8.2.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ማዕከሉ የቫይረሱን ስርጭትና ተጋላጭነት ፍተሻ አድርጎ የመፍቴህ አቅጣጫ ካላስቀመጠ፡-

- ✓ ላሞቹን እየፈጀ በሚገኘው ቫይረስ ላይ ተገቢው ጥናት ተደርጎ የመፍትሄ አቅጣጫ እንዲቀመጥ ካልተደረገ በቀሪዎቹ ላሞች ላይም ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል፤
- ✓ ቫይረሱ በቀላሉ ወደ አካባቢው ገበሬዎች ቀንድ ከብቶች ሊዛመት እና ጉዳት ሊያስከትል ስለሚችል፤

ለወተት ላሞቹ አስፈላጊው የጤና ምርምራ ተደርጎላቸው ጤነኞቹ በበሽታው ከተጠቁት እንዲለዩ እንዲደረግ እና ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በቅንጅት አሰፈላጊው እርምጃ በአስቸኳይ እንዲወሰድ አሳስበናል፡፡

8.3 በአደራ የተቀመጠ የጅማ ዩኒቨርስቲ የግንባታ ንብረቶችን በተመለከተ፤

8.3.1 ግኝት

ግንቦት 3 ቀን 2007 ዓ.ም በቁጥር ጅዩ 92/738 ጅማ ዩኒቨርስቲ በሰበታ ከተማ በብሄዊ እንስሳት ጤና ምርምርና ጥናት ማዕከል አጠገብ ለግንባታ መሬት የተሰጠው መሆኑን ገልጸ በቦታው ላይ ግንባታ ሲጀመር አገልግሎት ላይ የሚውሉ በርካታ አሸዋ፣ ብረትና ጠጠር በማዕከሉ ቅጽር ግቢ ውስጥ በአደራ ለጥቂት ወራት ለማስቀመጥ ፍቃድ የጠየቀና ያስቀመጠ ቢሆንም ንብረቶቹ ከዓመት በላይ ጸሐይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው የሚገኝ መሆኑ ታውቋል፡፡

8.3.2 የማሻሻያ ሃሳብ

ንብረቶቹ በቶሎ አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ካልተደረጉ ለብልሽት ሊጋለጡ ስለሚችሉ ንብረቶቹ ከዓመት በላይ ጸሐይና ዝናብ እየተፈራረቀባቸው ስለሆኑና ሥራ ላይ ሳይውሉ ለብልሽት ሊዳረጉ ስለሚችሉ በቶሎ ሥራ ላይ ይውሉ ዘንድ ሁኔታውን ለዩኒቨርስቲ ማሳሰብ እንዳለበት አስገንዝበናል፡፡ \

8.4 በአካባቢው ህብረተሰብ ላይ የጤና ጠንቅ እያስከተለ የሚገኘውን የማይፈለጉ የህክምና ቁሳቁሶች ቃጠሎን በተመለከተ፤

8.4.1 ግኝት

በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ ከአገልግሎት ወጪ የሆኑ ቀጥለው የተመለከቱት የህክምና ቁሳቁሶች ይገኙበታል፡-

- ሲሪንጅ ከነመርፌው በሴፍቲ ቦክስ፣
- የተለያዩ አይነት ግላሶች፣

- ከደም ጋር ንክኪ ያላቸውና ደም የነካቸው ፎጣዎች፣ ጨርቆች፣ ባንዴጆች፣
- የወንዶች ኬር የተሰራባቸው ማቴሪያሎች፣

የመሳሳሉት በሆስፒታሉ ለህክምና የማይፈለጉ ማንኛውንም ነገሮች በሜዲካል ኮሌጁ ግቢ ውሰጥ እንዲቃጠሉ የሚደረጉ መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህ ሁኔታ በአካባቢው ህብረተሰብና በሜዲካል ኮሌጁ ሰራተኞች ጤና ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳደረ እና የአካባቢውን ንጹህ አየር እየበከለ መሆኑ በሬዲዮ ፋናም ጭምር አስተያየት የተሰጠበት ጉዳይ ቢሆንም ሁኔታው እስከአሁን እንዲስተካከል ባለመደረጉ ችግሩ መቀጠሉን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

8.4.2 <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ሁኔታው በአስቸኳይ እንዲስተካከል ካልተደረገ ሽታው በአካባቢው ህብረተሰብና በሜዲካል ኮሌጁ ሰራተኞች ላይ የጤና ተጽዕኖ ሊያሳድር የአካባቢውን አየርም ሊበክል ስለሚችል ሜዲካል ኮሌጁ የጤና ተጽዕኖ እያሳደረ እና የአካባቢውን ንጹህ አየር እየበከለ ለሚገኘው ቃጠሎ ሌላ መፍቴህ በአስቸኳይ በመፈለግ ህብረተሰቡን ካልተፈለገ ሽታ መታደግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

አባሪ. 1

በደንቡና በመመሪያው መሰረት ያልተሰበሰበ (ያልተወራረደ) ሂሳብ የዕድሜ ቆይታ ጊዜን የሚያሳይ ዝርዝር

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	የተሰብሳቢ ሂሳቡ የዕድሜ ቆይታ ጊዜ				ድምር
		ከ1 ወር እስከ አንድ ዓመት	ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት	ከ5 ዓመት እስከ 10 ዓመት ድረስ	ከ10 ዓመት በላይ	
1	በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴርና በሥሩ ባሉት ተጠሪ ተቋማት	4,713,596.96	33,389,997.80	3,231,292.76	79,471,222.91	120,806,110.43
1.1	በሚኒ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ	4,713,596.96	32,722,135.82	3,180,052.68	5,045,514.41	45,015,828.31
1.2	በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠ ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት				74,418,923.60	74,418,923.60
1.3	በአላጌ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትነ ስልጠና ኮሌጅ	305,199.39	503,030.45	48,820.08		857,049.92
1.4	በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ	318,264.61	36,548.19			354,812.80
1.5	በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ	5,981.56	32,141.96		6,784.90	44,908.42
1.6	የምግብ ዋስትና ዳይሬክቶሬት	16,026.00	96,141.38			112,167.38
1.7	የቡና ጥራት ምርመራና ሰርተፊኬሽን ማዕከል			2,420.00		2,420.00
2	የአለርት ማዕከል			2,987.21		2,987.21
3	የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር		87,885.65			87,885.65
4	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን	2,940,325.62	2,116,006.39			5,056,332.01
5	የኢትዮጵያ ጤና መድህን ኤጀንሲ	22,093.12				22,093.12
6	የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር		91,354.95	4,322,362.78	138,869.82	4,552,587.55
7	የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል		1,758.00	3,677.98	51,946.28	57,382.26
	የሚዞር ድምር	7,676,015.70	35,687,002.79	7,560,320.73	79,662,039.01	130,585,378.23

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	የተሰብሳቢ ሂሳቡ የዕድሜ ቆይታ ጊዜ				ድምር
		ከ1 ወር እስከ አንድ ዓመት	ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት	ከ5 ዓመት እስከ 10 ዓመት ድረስ	ከ10 ዓመት በላይ	
		7,676,015.70	35,687,002.79	7,560,320.73	79,662,039.01	130,585,378.23
8	የውኃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር	1,172,060.00		15,039.32	10,234,724.81	11,421,824.13
9	የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን	70,395.19	44,548.60			114,943.79
10	የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ		15,196.41			15,196.41
11	የማዕድን ነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር	2,101,702.71	104,930.15		2,064,364.36	4,270,997.22
12	የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ				51,546.22	51,546.22
13	የኢትዮጲያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን	257,693.25	80,593.03	17,097.98		355,384.26
14	የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን		401,944.53			401,944.53
15	የከተማ ልማትና ቤቶች ሚ/ር እና ተጠሪ ተቋማት		7,445,963.83	50,175,457.57	294,116.32	57,915,537.72
15.1	በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ		7,286,722.09		294,116.32	7,580,838.41
15.2	የፌዴራል የተቀናጀ የከተማ መሬት መረጃ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት		159,241.74			159,241.74
15.3	የፌዴራል መንግሥት ሕንጻዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት			50,175,457.57		50,175,457.57
16	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ			14,389,992.92	1,115,104.57	15,505,097.49
17	የእስትራቴጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ			2,509.00		2,509.00
18	የብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ	582,924.36		1,252,187.24	1,041,249.87	2,876,361.47
	የሚዞር ድምር	11,860,791.21	43,780,179.34	73,412,604.76	94,463,145.16	223,516,720.47

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	የተሰብሳቢ ሂሳቡ የዕድሜ ቆይታ ጊዜ				ድምር
		ከ1 ወር እስከ አንድ ዓመት	ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት	ከ5 ዓመት እስከ 10 ዓመት ድረስ	ከ10 ዓመት በላይ	
	ድምር	11,860,791.21	43,780,179.34	73,412,604.76	94,463,145.16	223,516,720.47
19	የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን	6,882.91	82,827.62			89,710.53
20	የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት	1,701.76	1,106,523.02			1,108,224.78
20.1	በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ		153,832.21			153,832.21
20.2	የብሄራዊ እንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ማዕከል	1,701.76	952,690.81			954,392.57
21	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	118,839.88				118,839.88
	ጠቅላላ ድምር	11,988,215.76	44,969,529.98	73,412,604.76	94,463,145.16	224,833,495.66

አባሪ. 2

ያልተከፈሉ ሂሳቦችን የዕድሜ ቆይታ ጊዜን የሚያሳይ ዝርዝር

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	የተከፋይ ሂሳቡ የዕድሜ ቆይታ ጊዜ				ድምር
		ከ1 ወር እስከ አንድ ዓመት	ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት	ከ5 ዓመት እስከ 10 ዓመት ድረስ	ከ10 ዓመት በላይ	
	በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር እና በተጠሪ ተቋማት	909,406.27	1,980,444.44	1,551,410.32	22,826,603.35	27,267,864.38
1.1	በሚኒ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ	889,383.13	1,772,142.72	1,263,078.70	169,176.90	4,093,781.45
1.2	በግብርናቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት				22,657,426.45	22,657,426.45
1.3	በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ	3,115.94	75,688.82			78,804.76

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	የተከፋይ ሂሳቡ የዕድሜ ቆይታ ጊዜ				ድምር
		ከ1 ወር እስከ አንድ ዓመት	ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት	ከ5 ዓመት እስከ 10 ዓመት ድረስ	ከ10 ዓመት በላይ	
1.4	በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ		34,888.90			34,888.90
1.5	በምግብ ዋስትና ዳይሬክቶሬት	16,907.20	25,840.66			42,747.86
1.6	የቡና ጥራት ምርመራና ሰርተፊኬሽን ማዕከል		71,883.34	288,331.62		360,214.96
2	የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር			130,486.51		130,486.51
3	የብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ			2,021,288.09	739,750.87	2,761,038.96
4	የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር እና ተጠሪ ተቋማት	9,954.21	4,818,444.28			4,828,398.49
4.1	በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ	9,954.21	3,903,491.68			3,913,445.89
4.2	የፌዴራል መንግሥት ሕንጻዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት		914,952.60			914,952.60
	የሚዞር ድምር	919,360.48	6,798,888.72	3,703,184.92	23,566,354.22	34,987,788.34

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	የተከፋይ ሂሳቡ የዕድሜ ቆይታ ጊዜ				ድምር
		ከ1 ወር እስከ አንድ ዓመት	ከ1 ዓመት እስከ 5 ዓመት	ከ5 ዓመት እስከ) ዓመት ድረስ	ከ10 ዓመት በላይ	
	ድምር	919,360.48	6,798,888.72	3,703,184.92	23,566,354.22	34,987,788.34
5	የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን		113,086.68			113,086.68
6	የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ		14,529.26			14,529.26
7	የእስትራቴጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ		44,836.76			44,836.76
8	የኢትዮጵያ ጤና መድህን ኤጀንሲ	88,668.65	36,998.88			125,667.53
	ጠቅላላ ድምር	1,008,029.13	7,008,340.30	3,703,184.92	23,566,354.22	35,285,908.57

አባሪ. 3

መደበኛ የመነሻ የሂሳብ ሚዛናቸውን ያልጠበቁ የተሰብሳቢና የተከፋይ ሂሳብ ተቀጽላ ሌጀሮች፤

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ክሬዲት ሚዛን የሚያሣይ የተሰብሳቢ ሂሳብ ሂሳብ	ዴቢት ሚዛን የሚያሣይ የተከፋይ ሂሳብ ሂሳብ
1	በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴርና በሥሩ ባሉት ተጠሪ ተቋማት	25,689,234.28	2,808,333.82
1.1	በሚኒ በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ	5,375,867.32	2,808,333.82
1.2	በግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት	20,310,979.18	
1.3	በአጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ	2,387.78	
2	የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን	838,504.17	
3	የብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ	1,488,832.66	7,316,017.63
	ጠቅላላ ድምር	28,016,571.11	10,124,351.45

አባሪ. 4

የግዥ መመሪያውን ሳይከተል የተፈጸሙ ግዥዎች ዝርዝር

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	የተፈጸመው ግዥ	ግልጽ ጨረታ ሳይወጣ			የዋጋ ማወዳደሪያ ሳይሰበሰብ የተፈጸመ ግዥ
			በውስን ጨረታ የተፈጸመ ግዥ	በቀጥታ የተፈጸመ ግዥ	በዋጋማወዳደሪያ የተፈጸመ ግዥ	
1	የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን	የሞተር ሳይክልና የውሃ ጥልቀት መለኪያ መሳሪያ ግዢ	1,139,622.13			
2	የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር	ለመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ		351,158.02		
3	የኢትዮጵያ የምግብ የመድኃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለሥልጣን	ለመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ		2250,494.69		
		ለመጋረጃ ግዥ			370,797.18	
		ለመስተንግዶ አገልግሎትና ለሰራተኞች የደንብ ልብስ (ዩኒፎርም) ግዥ				238,249.77
4	የስምጥ ሸለቆ ሀይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን	ለመስተንግዶ አገልግሎትና ትራንስፖርት አገልግሎት ግዥ				144,840.04
5	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	ለጣውላ ግዥ				132,000.00
6	የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት	የላፕቶፕ ኮምፒውተር ግዥ				37,117.17
7	የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እና የገፈርሳ የአእምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል	ለመስተንግዶ አገልግሎት እና የተለያዩ የህክምና መገልገያ እቃዎች ግዥ			5,014,861.87	
8	የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ	የማማከር ሥራ አገልግሎት ግዥ		2,649,261.36		
		ለተለያዩ አልባሳትና የመስተንግዶ አገልግሎት ግዥ		720,067.21		
		የዕቃና የአገልግሎት ግዥዎች				233,864.25
	ጠቅላላ ድምር		1,139,622.13	5,970,981.28	5,385,659.05	786,071.23

አባሪ. 5

የሒሳብ መደቡን እና በጀት ዓመቱን ሳይጠብቅ የተመዘገበ የወጪ ሂሳብ ዝርዝር

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	የተፈጸመው ግዥ	በጀት ዓመቱን ሳይጠብቅ ተመዘገበ ወጪ	ትግቢው የሂሳብ መደብ ልተመዘገበ ወጪ
1	የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር	ለተለያዩ ግዥዎችና አገልግሎቶች የተፈጸመ ክፍያ		24,874.46
2	የትራንስፖርት ሚኒስቴር	ለማስታወቂያ ሥራና ለቦርሳ ግዥ		464,999.70
3	የአለርት ማዕከል	ለተለያዩ አገልግሎቶች የተፈጸመ ክፍያ		12,335.00
4	የስትራተጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ	ለማማከር አገልግሎት የተፈጸመ ክፍያ		198,461.28
5	የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን	ለጉልበት አገልግሎትና ለፕሮጀክተር ግዥ		26,214.16
6	የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት	ለተለያዩ አገልግሎቶች የተፈጸመ ከፍያ	75,490.97	15,827.16
7	የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል	ለተለያዩ የጥገና ሥራና ለዲዩቲ የተከፈለ	554,246.44	
		ለሰንደቅ ዓላማና መለዮ ግዥ እንዲሁም ለተለያዩ አገልግሎቶች የተፈጸመ ክፍያ		153,294.62
8	የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	ለግንባታ ቅድሚያ ክፍያ፣ ለማስታወቂያና ለአሸዋ ግዥ		29,703,434.00
9	የምግብ፣ የመድኃኒት ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለስልጣን	ለወተት አበልና ለትርፍ ሰዓት የተፈጸመ ክፍያ		89,342.28
10	የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር	ለውሎ አበል ለነዳጅና ለጠረጴዛ መግዣ ወጪ የተደረገ	112,308.71	
		ለተለያዩ አገልግሎቶች የተፈጸመ ክፍያ		610,970.00
11	የስምጥ ሸለቆ ሀይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን	ለጥናትና ምርምር ሥራ ፣ በኖክ ካርድ ለነዳጅ ግዥ፣ ለድንጋይ እንዲሁም ለደን ዘርና ችግኝ መግዣ የወጣ		732,029.00
12	የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን	ለተለያዩ ዕቃዎች ግዥ ወጪ የተደረገ		1,977,682.03
13	የብሄራዊ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፈንድ ጽህፈት ቤት	ለሙያ አገልግሎት የተፈጸመ ክፍያ		5,635.00
	የሚዞር ድምር		742,046.12	34,015,098.69

ተራ ቁጥ	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	የተፈጸመው ግዥ	በጀት ዓመቱን ሳይጠብቅ የተመዘገበ ወጪ	በተገቢው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ ወጪ
	የዞረ ድምር		742,046.12	34,015,098.69
14	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	ለተለያዩ አገልግሎቶችና ግዥዎች የተፈጸመ ክፍያ		250,231.04
15	የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት	ለውሎ አበል፣ለትራንስፖርትና ለመሳሰሉት የተፈጸመ ክፍያ		73,549.33
16	የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር	ለመኪና እጥበት፣ ለጉልበት ዋጋና ለፕሪንተር ግዥ የተከፈለ		36,122.50
		ለተለያዩ አገልግሎቶች የተፈጸመ ክፍያ	4,356,610.06	
17	የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚ/ር እና የብሔራዊ የእንሰሳትና ጤና ምርመራና ጥናት ማዕከል	ለአዳራሽ ግንባታ ለማማከር ሥራ ፣ ለትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ፣ ለፎቶ ኮፒ ማሽንና ለፕሪንተር ግዥ እና ለመሳሰሉት		1,862,854.31
18	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	ለሰራተኞች ደመወዝና ብሮሸርና ባነር ለታተመበት የተፈጸመ ክፍያ		183,134.49
19	የኢትዮጵያ ጤና መድህን ኤጀንሲ በአራት ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች	ለተለያዩ አገልግሎቶች የተፈጸመ ክፍያ		431,262.77
20	የብሄራዊ ደም ባንክ አገልግሎት	ለተለያዩ አገልግሎቶችና ግዥዎች የተፈጸመ ክፍያ		1,783,060.46
21	የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር	የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ		6,508.16
22	በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የገፈርሳ የአእምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል	ለተለያዩ አገልግሎቶች የተፈጸመ ክፍያ		20,219.74
	ጠቅላላ ድምር		5,098,656.18	38,662,041.49

አባሪ. 6

መመሪያን ሳይከተሉ የተፈጸሙ ክፍያዎች ዝርዝር፤

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ሳይፈቀድ የተፈጸመ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ	ከመመሪያው ውጭእና *መስክ ሳይወጡ የተፈጸመ የውሎ አበል ክፍያ	ከግዥ ላይ እና ከግንባታ ክፍያዎች ላይ ያልተቀነሰ እና ተቀንሶ ያልተመዘገበ				ያልተመዘበ የግንባታ ወጪ	ከሥራ ላቀቁ በኋላ የተከፈለ ደመወዝ
				የተጨማሪ ዕሴት ታክስ	የቅድሚያ ግብር	ያልተቀነሰ የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ * ተቀንሶ ያልተመዘገበ	ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ * ተቀንሶ ያልተመዘገበ		
1.	በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የገፈርሳ የአዕምሮ ሕመማን ማገገሚያ ማዕከል			620,324.37	976.68				1,916.00
2.	በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የአላጌ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ		* 29,678.00	25,444.35				1,333,093.65	
3.	በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ			266,573.54					
4.	በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ					1,398,669.27	* 633,083.09		
5.	የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስቴር	80,541.76	159,610.25						
6.	የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል				2,772.62	16,046,156.16 * 163,823.20		1,828,442.35	
7.	የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር	6,508.16							
8.	የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን			17,683.41	4,977.83	7,075.05	11,571.41		
	የሚዞር ድምር	87,049.92	189,288.25	930,025.67	8,727.13	17,615,723.68	644,654.50	3,161,536.00	1,916.00

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ሳይፈቀድ የተፈጸመ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ	መመሪያው ውጭ እና *መስክ ሳይወጡ የተፈጸመ የውሎአበል ክፍያ	ከግዥ ላይ እና ከግንባታ ክፍያዎች ላይ ያልተቀነሰ እና ተቀንሶ ያልተመዘገበ				ያልተመዘገበ የግንባታ ወጪ	ከሥራ ከለቀቁ በኋላ የተከፈለ ደመወዝ
				የተጨማሪ ዕሴት ታክስ	የቅድሚያ ግብር	ያልተቀነሰ የቅድሚያ ክፍያተመላሽ * ተቀንሶ ያልተመዘገበ	ያልተቀነሰ የመያዣ ሂሳብ ተቀንሶ ያልተመዘገበ		
	ድምር	87,049.92	189,288.25	930,025.67	8,727.13	17,615,723.68	644,654.50	3,161,536.00	1,916.00
9.	የቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ			5,399.54		5,994.06	3,347.91		5,886.30
10.	የብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ	139,399.73		127,814.95	4,156.91	451,926.00	23,309.90	531,160.57	
11.	ኮዮጵያ ሥጋና ወተት ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት		26,082.25						
12.	የስትራቴጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ		30,100.00						
13.	የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት	1,224.67							
14.	የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	117,062.20	354,853.50						2,413.35
15.	የኢትዮጵያ የምግብ፣ የመድኃኒት ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን	1,597,191.14							
16.	የብሄራዊ ደም ባንክ አገልግሎት		54,538.00						
	የሚዞር ድምር	1,941,927.66	654,862.00	1,057,840.62	12,884.04	18,067,649.68	671,312.31	3,692,696.57	4,329.35

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ሳይፈቀድ የተፈጸመ የትርፍ ሰዓት ሥራ ክፍያ	ከመመሪያው ውጭ እና *መስክ ሳይወጡ የተፈጸመ የውሎ አበል ክፍያ	ከግዥ ላይ እና ከግንባታ ክፍያዎች ይ ያልተቀነሰ እና ተቀንሶያልተመዘገበ				ያልተመዘገበ የግንባታ እና ሌሎች ወጪዎች	ከሥራ ከለቀቁ በኋላ የተከፈለ ደመወዝ
				የተጨማሪ ዕሴትታክስ	የቅድሚያ ግብር	ያልተቀነሰ የቅድሚያ ክፍያ ተመላሽ * ተቀንሶ ያልተመዘገበ	ያልተቀነሰ የመያዣሂሳብ * ተቀንሶ ያልተመዘገበ		
	ድምር	1,941,927.66	654,862.00	1,057,840.62	12,884.04	18,067,649.68	671,312.31	3,692,696.57	4,329.35
17.	የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥ ጋዝ ሚኒስቴር	41,397.35	113,500.00						
18.	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	56,492.90	146,200.00						
19.	የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት	9,580.00	14,269.90						8,711.63
20.	የኢትዮጵያ ሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት								23,555.64
21.	የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር								73,781.15
22.	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር								1,435.99
	ጠቅላላ ድምር	2,049,397.91	928,831.90	1,057,840.62	12,884.04	18,067,649.68	671,312.31	3,692,696.57	111,813.76

አባሪ .7

ያልተሰራበትን እና ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ ወጪ የተደረገውን የሚያሳይ ዝርዝር

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ያልተሰራበት በጀት		ለየሒሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ	
		ከመደበኛ በጀት	ከካፒታል በጀት	ከመደበኛ በጀት	ከካፒታል በጀት
1	በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴርና በተጠሪ ተቋማቱ	63,371,293.90	31,847,775.62	1,389.86	
1.1	በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ	26,495,595.46	11,089,538.93		
1.2	የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት	2,754,106.33			
1.3	የአላጌ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ	* 8,113,170.97	11,355,270.82		
1.4	የአርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ	* 7,621,602.02	4,211,294.71		
1.5	የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ	* 16,869,513.48	5,191,671.16		
1.6	የቡና ጥራት ምርመራ ማዕከል	1,517,305.64		1,389.86	
2	በጤና ጥበቃ ሚኒስቴርና በተጠሪ ተቋሙ	5,721,417.62	1,414,253.81	224,379.23	
2.1	በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ	5,122,592.65	1,414,253.81	224,379.23	
2.2	የገፈርሳ የአዕምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል	598,824.97			
3	የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር	239,927,046.96	163,404,777.95		
4	የኢትዮጵያ ምግብ ፣ መድኃኒትና ጤና ክብካቤና ቁጥጥር ባለሥልጣን	9,964,783.40	3,953,042.53	1,488,388.52	93,000.00
5	የብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ	6,306,745.13	6,265,069.28	725,469.28	
6	የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር በተጠሪ ተቋማቱ	42,160,617.51	60,928,934.79	14,154.60	
6.1	በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ	40,557,331.14	32,354,519.88	14,154.60	
6.2	የፌዴራል የተቀናጀ የከተማ መሬት መረጃ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት	1,603,286.37	11,754,880.91		
6.3	የፌዴራል መንግሥት ሕንጻዎች ግንባታ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት		16,819,534.00		
7	የማዕድን ነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር	6,971,709.78	13,200,285.00		
	የሚዞር ድምር	374,423,614.30	281,014,138.98	2,453,781.49	93,000.00

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ያልተሰራበት በጀት		ለየሂሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ	
		ከመደበኛ በጀት	ከካፒታል በጀት	ከመደበኛ በጀት	ከካፒታል በጀት
	የዞረ ድምር	374,423,614.30	281,014,138.98	2,453,781.49	93,000.00
8	የውሃ ልማት ፈንድ ጽህፈት ቤት	2,415,719.15			
9	የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዮት	6,120,454.08	10,624,528.77		
10	የትራንስፖርት ሚኒስቴር	5,013,989.58			
11	የአማኑኤል የአዕምሮ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል	1,263,124.77	23,949,493.82		
12	የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት	4,161,655.27	12,140,923.59		
13	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	6,776,674.86		245,958.14	
14	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን	4,394,454.06	15,881,685.27		
15	የሆርቲካልቸር ልማት ኤጀንሲ	7,765,125.63	42,089,690.00		
16	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	11,921,928.13 * 22,453,419.85	4,744,861.03		
17	የስትራተጂክ መጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ	327,015.30			
18	የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር	525,702.87			
19	የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን	9,845,435.31			
20	የብሔራዊ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፈንድ አስ/ር ጽ/ ቤት	726,321.47			
21	የመንገድ ፈንድ ጽሕፈት ቤት	228,547.55			
22	የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለሥልጣን	499,309.79	116,278.55		
23	የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን	1,156,357.75	419,474.08		
24	የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን	2,439,411.80	16,759,701.70		658,093.03
25	የኢትዮጵያ ጤና መድኅን ኤጀንሲ	27,582,962.86		277,345.23	
	የሚዞር ድምር	**490,041,224.38**	**407,740,775.79**	**2,977,084.86**	**751,093.03**

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ያልተሰራበት በጀት		ለየሒሳብ ኮዶቹ ከተደለደለው በጀት በላይ የወጣ	
		ከመደበኛ በጀት	ከካፒታል በጀት	ከመደበኛ በጀት	ከካፒታል በጀት
	የዞረ ድምር	490,041,224.38	407,740,775.79	2,977,084.86	751,093.03
26	የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል	327,937.11		10,647.30	
27	የአለርት ማዕከል	170,821.46	9,599,979.58	9,265.00	
28	የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ	3,402,347.47		3,342,494.95	289,174.25
29	የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን	1,347,615.76	3,585,094.07		
30	የእንስሳትና ዓሣ ሀብት ልማት ሚኒስቴር ተጠሪ ተቋማቱ	15,683,028.32	25,736,211.23	1,284,814.32	514,113.16
30.1	በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ	5,541,510.17	25,080,398.43	1,272,704.40	514,113.16
30.2	የብሔራዊ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል	2,403,837.25 * 742,383.20		12,109.92	
30.3	የብሄራዊ እንስሳት ጤና ምርመራ ማዕከል	6,995,297.70	655,812.80		
31	የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር	15,119,883.54			
32	የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት	23,148,608.41			
33	የብሄራዊ ደም ባንክ አገልግሎት	4,608,687.32			
	ጠቅላላ ድምር	553,850,153.77	446,662,060.67	7,624,306.43	1,554,380.44

* ከውስጥ ገቢ የተረፈውን በጀት የሚያሳይ ነው፡፡

አባሪ. 8

በንብረት አስተዳደር ላይ የታዩ ክፍተቶች

ተ. ቁ	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያደረጉ እና ከመዝገብ ጋር ያላገናዘቡ	ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር መለ በሙለ ወይም *በከፊል ያልተሰጠ	እስቶክ የመያዝ ፣ የመረከብና ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ	ሊቢሬ ያልቀረበላቸው (የሌላቸው) ተሽከርካሪዎች	በብልሽት ምክንያት የቆሙ ተሽከርካሪዎች	ሊቢሬያቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሥም የሆነ ተሽከርካሪዎች	የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው ተሽከርካሪዎች
1.	የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን	✓	✓	✓				
2.	የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር	✓			9 መኪኖች			
3.	የኢትዮጵያ ሆርቲካልቸራል ልማት ኤጀንሲ	✓		✓	3 መኪኖች		3 መኪኖች	
4.	የማዕድን፣ነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ሚ/ር	✓	✓			1ሎቤድ ተሳቢ		
5.	የስምጥ ሸለቆ ሐይቆች ተፋሰስ ባለሥልጣን	✓						
6.	የብሔራዊ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ፈንድ አስተዳደር ጽህፈት ቤት	✓						
7.	የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ሰርቬይ	✓	✓*					
8.	የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር	✓		✓		31 መኪኖች 1ፎርክ ሊፍት		1 መኪና
9.	በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚ/ር የአጋርፋ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ	✓			2ሞተርሳይክል	7 መኪኖች		
10.	በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚ/ር የአላጌ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኮሌጅ	✓	✓*			5 መኪኖች 8 ሞተሮች		

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያደረጉ እና ከመዝገብ ጋር ያላገናዘቡ	ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር መለ በሙለ ወይም *በከፊል ያልተሰጠ	እስቶክ የመያዝ ፣ የመረከብና ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ	ሊቢራ ያልቀረበላቸው (የሌላቸው) ተሽከርካሪዎች	በብልሽት ምክንያት የቆሙ ተሽከርካሪዎች	ሊቢራያቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሥም የሆኑ ተሽከርካሪዎች	የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው ተሽከርካሪዎች
1	በእንስሳትና ዓሳ ሀ/ ል/ት ሚ/ር የብሄራዊ እንስሳት ጤና ምርመራና ጥናት ማዕከል					1 መኪና	20 መኪኖች	
2	የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት		✓ *					
3	የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል		✓ *	በምግብ ዕቃዎች ግምጃ ቤት				
4	የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር		✓	✓	8 መኪኖች	27 መኪኖች	47 መኪኖች	
5	የብሄራዊ ደም ባንክ አገልግሎት		✓	✓	1 መኪና			
6	የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር		✓ *			23 መኪኖች	73 መኪኖች	
7	የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል			✓		4 መኪኖች		
8	የኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ማኔጅመንት ኢንስቲትዩት			✓		2 መኪኖች		
9	የኢትዮጵያ ጤና መድኅን ኤጀንሲ			✓				
10	በከ/ ል/ ቤቶች ሚ/ር የፌዴራል መንግሥት ሕ/ግንባታ ጽ/ ቤት			✓				
11	የኮንስትራክሽን ሚኒስቴር				16 መኪኖች			
12	በእርሻና ተ/ ሀ/ ሚ/ር የእርዳይታ ግብርና ቴክኒክና ሙያ ት/ት ሥ/ ኮሌጅ				2 ሞተር ሳይክል 1 ትራክተር			1 ትራክተር

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያደረጉ እና ከመዝገብ ጋር ያላገናዘቡ	ለቋሚ ዕቃዎች መለያ ቁጥር መለ በሙለ ወይም *በከፊል ያልተሰጠ	እስቶክ የመያዝ ፣ የመረከብና ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች በአንድ ሰራተኛ የሚከናወን መሆኑ	ሊቢሬ ያልቀረበላቸው (የሌላቸው) ተሽከርካሪዎች	በብልሽት ምክንያት የቆሙ ተሽከርካሪዎች	ሊቢሬያቸው በሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሥም የሆኑ ተሽከርካሪዎች	የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው ተሽከርካሪዎች
1	በእንስሳትና ዓሳ ሀብት ልማት ሚኒስቴር የብሄራዊ ሰው ሰራሽ የእንስሳት ማራቢያ ዘዴ ማዕከል				1 መኪና 8 ሞተር ሳይክል			
2	በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የገፈርሳ የአዕምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል					1 መኪና		1 መኪና
3	የኢትዮጵያ ሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት					2 መኪኖች	1 መኪና	1 መኪና
4	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን					36 መኪኖች 6 ሞተሮች 2 ትራክተሮች		3 መኪኖች
5	የአባይ ተፋሰስ ባለሥልጣን					3 መኪኖች 2 ሞተሮች	12 መኪኖች	
6	በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የቡና ጥራት ምርመራና ሰርተፊኬሽን ማዕከል					1 መኪና		
7	የአዋሽ ተፋሰስ ባለሥልጣን						24 መኪኖች	

አባሪ. 9

እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፉት በጀት ዓመታት አዲት ግኝቶች

ተራ ቁጥር	የመሥሪያ ቤቱ ሥም	ተመላሽ ያልተደረገ የውሎ አበልና የመሳሰሉት ክፍያዎች	ከሥራ ከለቀቁ በኋላ የተከፈለ ደመወዝ	ያልተሰበሰበ የህክምና መዋጮ	የወጪ ማስረጃ ያልቀረበለት
1	በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የገፈርሳ የአዕምሮ ሕሙማን ማገገሚያ ማዕከል	38,024.87			
2	የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት	5,152.50			568,008.94
3	የቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል	7,261.25			81,545.00
4	የማዕድን፣ ነዳጅና ተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር	176,645.00	15,442.17	5,138.25	
5	የውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚኒስቴር	207,467.00	3,658.10	2,337.60	
6	የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር	281,733.33			
7	የዱር እንስሳት ልማትና ጥበቃ ባለሥልጣን	11,095.36	2,578.10		3,223.36
8	የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር			3,985.47	
9	የኢትዮጵያሥጋና ወተት ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዮት				3,323,351.08
10	በእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ሥልጠና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽህፈት ቤት				204,565.00
	ጠቅላላ ድምር	727,379.31	21,678.37	11,461.32	4,180,693.38

የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች አዲት ዳይሬክቶሬት የ2008 በጀት አመት አዲት የተጠቃለለ ዓመታዊ ሪፖርት

ዋና ዋና የኦዲት ግኝቶች እንደሚከተለው ቀርቧል

1. የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ

1.1 የጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሳብ

ጥሬ ገንዘብ

1.1 በጥሬ ገንዘብ ጉድለት

- **የቀድሞ ጥቃቅንና አነስተኛ ኤጀንሲ ኢንተርፕራይዝ**

  የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ..... ብር 107,529.71

  ከአንድ ዓመት በላይ ሳይተካ ተገኝቷል፡፡

የገንዘብ ጉድለቱ እንዲተካ አስፈላጊውን እርምጃ መወሰድ እንዳለበት ለወደፊቱ የዚህ አይነት ክፍተት እንዳይፈጠር በጥሬ ገንዘብ ላይ ጥብቅ የሆነ ቁጥጥርና ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

ለጥቃቅን ወጪዎች መሸፈኛ በካዝና ውስጥ እንዲያዝ ከተፈቀደው በላይ የተገኘ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ፤

ማዕከላዊ ዕዝ ጠቅላይ መምሪያ

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ትብብር ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር ክ/ሂመ39/7/19 በቀን 30/07/2007 አዲስ ባሻሻለው መመሪያ መሠረት የመንግስት መ/ቤቶች ለጥቃቅን ወጪዎች መሸፈኛ በካዝና እንዲይዙ የሚፈቅደዉ የገንዘብ መጠን ከብር 100,000 ያልበለጠ መሆን እንዳለበት ይገልጻል፡፡ ነገር ግን በጠቅላይ መምሪያው ሐምሌ 1 ቀን 2008 ዓ.ም ብር 2,433,990.90 በካዝና ውስጥ በቆጠራ ተገኝቷል፡፡

ማዕከላዊ ዕዝ ጠቅላይ መምሪያ ለተላከለት የሥራ አመራር ሪፖርት በሰጠው መልስ በካዝና ሀምሌ 01/2008 ዓ.ም ከተቆጠረው ብር 2,433,990.90 ውስጥ ብር 1,768,167.27 የሠራዊት ደመወዝና ቀለብ መሆኑንና ሠራዊቱ ካለው አቀማመጥ አንፃር ከሰኔ 30 በፊት ደመወዙንና ቀለቡን መክፈል ስልላልተቻለ ደመወዙ በሰኔ መጨረሻ ስለመጣ ወደ ካዝና መጥቶ ሊቆጠር

መቻሉንና የውስጥ ኦዲተር ሀምሌ 1 ቀን 2008 ዓ.ም. በቆጠራ ያረጋገጠ መሆኑን፣ በሂሳብ መደብ 6417 ብር 226,461.15 የአገልግሎት ማበረታቻ ክፍያ በፔሮል ተሰርቶ ከላይ በተገለጸው ምክንያት ካለው የሠራዊት አቀማመጥ በወቅቱ መክፈል ባለመቻሉ በሳጥን እንዲቆጠር መደረጉን፣ በሂሳብ መደብ 5054 ብር 403,497.66 ከመከላከያ ገቢዎች ዳይሬክቶሬት ለሚስጥራዊ ስራ ክፍያ የሚፈፀምበት እና በሐምሌ ወር 2008 ዓ.ም.፣ በነሐሴ ወር 2008 ዓ.ም. እና በመስከረም ወር 2009 ዓ.ም. ለሚመለከታቸው የተከፈለ፣ በሂሳብ መደብ 5059 የተጨማሪ እሴት ታክስ ብር 10,381.82 መሆኑንና ወደ ገቢዎች ጉምሩክና በሐምሌ ወር 2008 ዓ.ም. ገቢ የተደረገ፣በሂሳብ መደብ 5052 የፍርድ ቤት ማስያዣዎች ብር 25,483.00 ከሠራዊቱ በፍርድ ቤት ውሳኔ ከደመወዛቸው ላይ ተቀናሽ ተደርጎ በሳጥን የተገኘና ለቤተሰባቸውለቤተሰባቸው በሐምሌ ወር 2008 ዓ.ም. ለባለመብቶች የተከፈለ ገንዘብ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በካዝና ውስጥ የተገኘው ጥሬ ገንዘብ ከላይ ለተገለጹት ክፍያዎች የሚውል ለመሆኑ ዝርዝር ማስረጃው ባለመቅረቡ በወቅቱ ከሠራዊት ደሞዝ ተከፋይ ላይ ምን ያህሉ እንዳልተከፈለ እንዲሁም መያዣ ሂሳቦቹ ለማን የሚከፈሉ እንደነበር በዝርዝር ያልተገለጸ በመሆኑ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ በመሆኑም ሂሳቡ በውስጥ ኦዲት በኩል ተጣርቶ ሊቀርብ እንደሚገባና ለወደፊቱም በጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያ መሰረት ሊሰራ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

1.2 <u>በጥሬ ገንዘብና የባንክ ሂሣብ አያያዝ ድክመቶች</u>

<u>በፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር</u>

- በገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በደብዳቤ ቁጥር ክሂ39/7/9 በቀን 30/7/07 አዲስ ተሻሽሎ የወጣው የጥቃቅን ወጪዎች መሸፈኛ መመሪያ የመንግስት መ/ቤቶች በሳጥን የሚይዙት የገንዘብ መጠን ከብር 100,000 ያልበለጠ መሆን እንዳለበት ይገልጻል ፡፡ ነገር ግን መ/ቤቱ መመሪያውን በመጣስ በአንድ ጊዜ ብር 150,000 ከባንክ ወጪ አድርጎ ወደ ሳጥን ማስገባቱ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡በጥሬ ገንዘብ አስተዳደር መመሪያው ላይ ከተመለከተው የገንዘብ መጠን በላይ በካዝና እንዳያድር ጥብቅ ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

- የሳጥንና የተጣራ ሀብት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሰኔ 30 /2007 መጨረሻ የሳጥን ከወጪ ቀሪ ብር 85,991.85 ዴቢት ሲሆን የ2008 በጀት ዓመት የሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ መነሻ ሆኖ የተወሰደው ብር 172,363.05 ዴቢት ሆኖ ተገኝቷል፡፡በዚህም ምክንያት መነሻ ሚዛኑ በብር 86,371.20 በልጦ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም የተጣራ ሀብት በ2007 በጀት ዓመት መጨረሻ ብር 1,044,908.27 ክሬዲት ሲሆን በ2008 በጀት ዓመት መጀመሪያ ወይም ሐምሌ 1ቀን 2007 መነሻ ሆኖ የተመዘገበው ብር 379,876.31 ክሬዲት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የተጣራ ሀብት መነሻ በብር 665,031.96 አንሶ ተገኝቷል፡፡

  የልዩነቱ መንስኤ ተጣርቶ ለሂሳቡ ማስተካከያ ሊሰራለት እንደሚገባ በሪፖርታችን ገልጸናል፡፡

1.4. <u>የባንክ ሂሳብ</u>

<u>የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ</u>

- በባንክ ሌጀር ሳይመዘገብ የተገኘ የአደራ ሂሳብ ብር 751,819.90 ተገኝቷል፡፡

  ሂሳቡ በሪፖርቱ እንዲካተትና የተስተካከለው ሪፖርት ለገ/ኢ/ት/ል/ሚ/ር እንዲላክ፣ ለመ/ቤታችንም በግልባጭ እንዲያውቀው እንዲደረግ በሪፖርታችን ያሳሰብን ሲሆን ኦዲት ተደራጊዎቹ የኦዲት ሪፖርት ከተላከ በኋላ በላኩት የድረጊት መርሃ ግብር መሠረት ምዝገባውን በማስተካከል ሪፖርት ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ታህሳስ 14 ቀን 2009 ዓ.ም በደ.ቀ. ሠማ/4/6661 ሸኝነት እንደላኩ ገልጸዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ የቋሚ ሂሳቦች ተቀጽላ ሌጀር ቁጥሮች ትክክለኛ ያልሆነ ሚዛን የታየባቸውን በሌሎች ተቀጽላ ሌጀሮች ትክክለኛ ሚዘን የሚያሳዩትን የሂሳብ ሚዛን በመውሰድ ወደ ኮንትሮል ሌጀር ማስተላላፉ ከሂሳብ አሰራር ውጭ መሆኑን የተጣራ ሀብት ትክክለኛ ያልሆነ ሚዛን የታየባቸውን ምክንያት በማጣራት ወደ ሚቀጥለው በጀት ዓመት በትክክል ማለፋቸውን ሊያረጋግጥ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡ እንዲሁም በመመሪያው መሠረት ገንዘቡ በተሰበሰበ ዕለት ወይም በማግስቱ ባንክ ገቢ እንዲሆን ክትትል መደረግ እንደሚኖርበት እንዲሁም የአደራ ሽያጭ ብር ወደ ባንክ ሂሳብ መደቡ ‹‹D›› ገቢ ማድረግና የአገልግሎት ገቢውን (commission) ወደ ባንክ ሂሳብ መደቡ ‹‹B›› ገቢ መደረግ እንደሚኖርበት በሪፖርታችን አሳስበናል፡

2. ተሰብሳቢ ሂሳብ

2.1 በወቅቱ ያልተወራረደ የሰነድ ሂሳብ

በተሰብሳቢ የተመዘገቡት ሂሳቦች በትክክለኛ ማስረጃዎች መደገፋቸውንና በወቅቱ መሰብሰባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በድምሩ 21,611,766.23 በደንቡ መሠረት ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

ከፍተኛው በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር የተገኘው ሲሆን ይህም በሂሳቦቹ ላይ በማስረጃ ሊደገፍና አስፈላጊውን ማጣራት ተደርጎ ሂሳቡ እንዲሰበሰብ ተገቢ የሆነ ጥረትና ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል ፡፡

የመ/ቤቱ ስም	ከ1 ወር እስከ 1 ዓመት	ከ1 -5 ዓመት	ከ5-10 ዓመት	ከ10 ዓመት በላይ
ንግድ ሚኒስቴር		1,242,482.58		
የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮምሽን	48,827.16			
ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ		11,859.00		
የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት			684,593.35	
የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት	63,173.21			
በፌዴራል ፖሊስ የአስተዳደር ልማት ዘርፍ	210,819.97			
በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት				43,426.47
የበጎ አድራጎት ድረጅቶችና ማህበራት		24,259.74		
ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	7464.15			13,479,052.01
ብሄራዊ አክሪዲቴሽን ጽ/ቤት	580,316.45	0.00		
የፌዴራል ማረሚያ	3,808,719.64	0.00		

ቤቶች አስተዳደር				
የፌዴራልና የአርብቶአደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር	28,169.39	0.00		164,997.48
የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ	0.00	1,200,357.20		
የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም	5,148.43	8,100.00		
ድምር	4,752,638.40	2,487,058.52	684,593.35	13,687,475.96

2.2 በተሰብሳቢ ተዝግቦ የተገኘ እና ማስረጃ ባለመቅረቡ ትክክለኛነቱ ያልተረጋገጠ

- መከለከያ ሚኒስቴር ብር 172,017,623.31
- የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብር 38,366,356.85

<u>በተሰብሳቢ ሂሳብ ላይ የታዩ ልዩ ልዩ የአሠራር ችግሮች</u>

<u>ያለ አግባብ የተሰረዘ ተሰብሳቢ ሂሳብ</u>

- የሀገር መከላከያ ሚኒቴር አለአግባብ የተሰረዘ ተሰብሳቢ ብር 11,134,824.23
- ጠቅላይ ፍ/ቤት የ2007 ዓ.ም ማስረጃ ሳይቀርብ ከሪፖርት የተሰረዘ ብር <u>21,125.67</u>

ድምር <u>11,155,949.90</u>

ተገኝቷል፡፡

ከፍተኛው የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ሲሆን ሂሳቡ ወደነበረበት ተመልሶ ተሰብሳቢው በተሰብሳቢነት ተከፋዩም በተከፋይ እንዲመዘገብ እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባና ሂሳቦቹን ከመዝገብ ለመሰረዝ መመሪያውን ተከትሎ ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር ሊቀርብ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

<u>መከላከያ ሚኒሰቴር</u>

- በሂሳብ መደብ 4202 ብር 243,487.77 የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ከተያዘው ውስጥ በሎጀስቲክስ ዋና መምሪያው ብር 200,187.27 ከ10 ከዓመት በላይ ሳይተካ የቆየ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ሲሆን በፍ/ቤት ውሳኔ ቢያገኝም መ/ቤቱ ገንዘቡን ሊያስመልስ አልቻለም፡፡ እልባት ሳያገኝ ብዙ ዓመታት ያስቆጠረ በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶት ክትትሉ እንዲጠናከር እንዲሰበሰብ አሳስበናል፡፡

3. የገቢ ሂሳብ

3.1 ለሚመለከተው አካል ፈሰሰ ያልተደረገ ገቢ

- የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ..... ብር 5,442,867.33

በየወሩ ፈሰስ መሆን ሲገባው ፈሰስ ያልሆነ ተገኝቷል፡፡ ገቢዎች በሕጉ መሠረት በወቅቱ ለገ/ኢ/ት/ቢ/ር ፈሰስ መደረግ ሲገባቸው የበጀት ዓመቱ መጨረሻ ድረስ ማስቀመጥ እንደማይገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

በገቢ ግብር ቀረጥና የታክስ ሕግ መሠረት ያልተሰበሰበ ገቢ

- **የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት**

ከቤት አበል ላይ የገቢ ግብር ..... ብር 2,334,379.40

የገቢ ግብር ስለማስከፈል በወጣው ደንብ መሰረት የቤት አበል ክፍያን ከደመወዝ ጋር በመደመር ከሚገኝ ገቢ ሶስቱም ፍርድ ቤቶች ከዳኞችና ከሠራተኞች ላይ ያልተቀነሰውን የገቢ ግብር በመቀነስ ለሚመለከተው አካል ገቢ እንዲያደርጉ በቀጣይም በደንቡ መሠረት የገቢ ግብሩ ሊቀነስ እንደሚገባ እንዲሁም የተጨማሪ እሴት እና የተከፋይ ሂሳብ ያልተቀነሰ በታክስ ሕግ መሠረት መቀነስ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

3.2 በገቢ ሂሳብ ሪፖርት ውስጥ ያልተካተተ የገቢ ሂሳብ፤

በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ገቢ በትክክል ተመዘግቦና በሂሳብ ሪፖርት ተካቶ ለገ/ኢ/ት/ሚ/ር መቅረቡን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በሀገር መከላከያ ሚኒስቴር

- በሎጀስቲክስ ዋና መምሪያ የትራንስፖርት መምሪያው ከልዩ ልዩ አገልግሎት የሰበሰበው ገቢ በፌዴራል መንግሥት ሂሳብ አወቃቀር መሠረት በገቢ ሂሳብ መደብ መዝግቦ ሪፖርት ያደረገ መሆኑ ሲጣራ፣ ትራንስፖርት መምሪያው የሰበሰበውን ገቢ ብር 11,685,878.06 በ5054 በተከፋይ ሂሳብ መደብ መዝግቦ ሪፖርት ያደረገ መሆኑና ዋና መምሪያውም በዚሁ አርዕስት እንደመዘገበ ታውቋል፡፡ በዚህ ምክንያት የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት የተገኘው ገቢ በገቢ ሂሳብ መደብ ሳይመዘገብና በሪፖርት ሳይገለጽ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም በአደራ የተመዘገበ ይህንኑ ገቢ ለሎጅስቲክስ ዋና መምሪያ በዚሁ የሂሳብ መደብ 5054 ሌሎች መያዣዎች በማለት እንደመዘገበ ተውቋል፡፡ በዚህም ምክንያት የትራንስፖርት አገልግሎት በመስጠት የተገኘው ገቢ በገቢ ሂሳብ መደብ ሳይመዘገብና በሪፖርትም ሳይገለጽ

ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የሰበሰበውን ገቢ የትራንስፖርት አገልግሎት ወደ መከላከያ ገቢዎች ዳይሬክቶሬት ገቢ መደረጉ አግባብ ባለመሆኑ ከመንግስት በጀት በዚህ አገልግሎት ለተገኘው ገቢ ወጪ የሆነው ሂሳብ ተቀናሽ ተደርጎ ለገ/ኢ/ል/ሚ/ር ፈሰስ ሊሆን እንደሚገባበ,ና ለተገኘው የውስጥ ገቢም የአጠቃቀም መመሪያ ሊኖረዉ እንደሚገባ አሳስበናል::

<u>በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር</u>

- አስተዳደሩ በበጀት ዓመቱ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች የሰበሰበውን ብር 505,754.26 ምዝገባውም ሳይከናወንና በሂሳብ ሪፖርት ውስጥ ሳይካተት ተገኝቷል፡፡ በገቢ ሂሳብ አመዘጋገብ ላይ ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

3.3 <u>በገቢ አሰባሰብ ዙሪያ የሚታዩ ሌሎች ዋና ዋና የአሠራር ድክመቶች፤</u>

<u>በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ</u>

- የኤጀንሲው (የመንግስትን)ጥቅም በሚነካ መልኩ የሚመለከተውን አካል ሳይፈቅድ ሶስት የተለያዩ ቅጾችን በማሳተም (የመኪና ሽያጭ ውል፣ የመኖርያ ቤት ሽያጭ ወይም በሌላ በማናቸውም መንገድ በሚያስተላልፍ ባለጉዳዮች እና የባለጉዳይ ማስረጃ መጠየቂያ ማመልከቻ ቅጽ) በመሸጥ ከአገልግሎቱ የሰበሰበው ገቢ በኤጀንሲው በኩል ተሰብስቦ ለመንግስት ገቢ መደረግ ሲገባው ያለአግባብ የኤጀንሲው ሶሻል ማህበር እንዲሰበስብና እንዲጠቀምበት ተደርጎ ተገኝቷል፡፡

<u>የፌዴራል ጥቃቅን እና አነስተኛ</u>

- በድምር ብር 560,193.91 የአደራ ሽያጭ ብር ወደ ባንክ ሂሳብ መደቡ ‹‹D›› ገቢ ማደረግ ሲገባ ወደ ባንክ ሂሳብ መደብ ‹‹B›› ገቢ አድርጎ ተገኝቷል፡፡ በመመሪያው መሠረት ገንዘቡ በተሰበሰበ ዕለት ወይም በማግስቱ ባንክ ገቢ እንዲሆን ክትትል መደረግ እንደሚኖርበት እንዲሁም የአደራ ሽያጭ ብር ወደ ባንክ ሂሳብ መደቡ ‹‹D›› ገቢ ማድረግና የአገልግሎት ገቢውን (commission) ወደ ባንክ ሂሳብ መደቡ ‹‹B›› ገቢ መደረግ እንደሚኖርበት በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>መከላከያ ሚኒስቴር</u>

በሎጅስቲክስ ዋና መምሪያ የትራንስፖርት መምሪያ ተሽከርካሪ ተከራይ ድርጅቶች ሊከፍሉ የሚገባቸው የገንዘብ መጠን ለመወሰን የትራንስፖርት ዋና የስራ ሂደቱ የሚጠቀምበት በኪራይ ዉሉ ላይ የገንዘቡ መጠን የማይገለጽ መሆኑና የኪራይ ታሪፉ ደግሞ በሚመለከተው

አካል በመመሪያ የፀደቀ ወይንም ራሱ ያወጣው ታሪፍ የሌለው ሲሆን ክፍያ የሚጠይቀው በብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን /ብኢኮ/ በሚያወጣዉ ወቅታዊ የጭነት ታሪፍ መሰረት መሆኑ ታዉቋል፡፡ መምሪያው ለሚሰጠው የትራንስፖርት ኪራይ አገልግሎት የተጠና ታሪፍ ባለመኖሩ ስምምነቱ የመንግስትን ጥቅም የማያሰጠብቅ ባለመሆኑ የተጠና ታሪፍ ሊኖረውና በተጠቀሰው ታሪፍ ክፍያ መፈጸሙ ክትትል ይደረግ ዘንድ በውሉ ላይ የገንዘቡ መጠን መጠቀስ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

4. <u>የወጪ ሂሳብ</u>

4.1 <u>ምንም ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ፤</u>

የፌዴራልና የአርብቶአደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር	ብር	84,784.01
የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት	"	112,534.74
የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተር ፕራይዞች ኤጀንሲ	"	91,200.00
ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር	"	4,290,398.47
ጠ/ድምር	ብር	4,578,917.22

የተከፈሉ ሂሳቦች በወጪ ከመመዝገባቸው በፊት በተገቢው የወጪ ማስረጃ የተደገፉ ለመሆኑ ሊረጋገጥ እንደሚገባ ለተጠቀሱት ወጪዎች ማስረጃ ሊቀርብለት ወይም ከሚመለከተው ሰራተኛ ወይም ኃላፊ ገንዘቡ ተመላሽ ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.2 የተሟላ የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ ሂሳብ

ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ	ብር	106,956.00
የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት	"	19,164,997.67
የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት	"	1,786,958.10
የኢትዮጵያ የደረጃዎኤጀንሲ	"	161,500.00
የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን	"	21,125,500.00
ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የተላከበባንክ ለመላኩ ዴቢት አድቫይስ ያልቀረበለት		
የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	"	10,875.00
የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን	"	606,995.14
የቀድሞው ጥቃቅንና አነስተኛ ኤጀንሲ	"	356,093.61
የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት	"	1,334,085.83
ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር	"	262,022.51
ጠ/ድምር	ብር	44,915,983.86

ከፍተኛው የብሔራዊ መረጃና ደህንንት አገልግሎት ሲሆን የተከፈለውን ወጪ ከማስረጃው ጋር አገናዝቦ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሳብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ሥራ አመራሩ በሰጠው ምላሽ ክፍያው በተለያየ የሀገራችን ክፍሎች ላሉ ስደተኞች ከውጭ በእርዳታ ለሚመጣ ምግብና መድሃኒት የመሳሰለው ከቀረጥ ነጻ እንዲገባ ግንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚ/ር በደብዳቤ ቢያሳውቅም እስከ ቅርብ ጊዜ ሳይተገበር ቀርቶ ከመስከረም ወር 2009 ዓ.ም. ለገባ እቃ ከቀረጥ ነጻ እየገባ እንደሚገኝ ገልጿል፡፡በመሆኑም የጉምሩክ ቀረጥ ሂሳብ ክፍያ ወጪዎች ሆነው ሊመዘገቡ የሚችሉት የቀረጥ ክፍያ የዕቃ ማሳወቂያ ቅጽ /ድክላራሲዮን/፣ የዕቃውን ዝርዝር እና ዋጋ የያዘ ኢንቮይስ፣ የዕቃው መጫኛ መረጃ /ፓኪንግ ሊስት /እና እቃው ንብረቱ ገቢ ለመሆኑ ሞዴል 19(የዕቃ ወይም የንብረት ገቢ ደረሰኝ) የተመዘገበበት ማስረጃው በመመሪያው መሰረት በዝርዝር ቀርቦ በውስጥ ኦዲቱ የሂሳቡ ትክክለኛነት ሊረጋጥ እንደሚገባ፤ በዋናው መ/ቤት በኩል ለተፈጸመ የማዕከል ግዥ ከዋናው መ/ቤት ክፍያው መፈጸሙን ድርሻው ምን ያህል እንደሆነ ንብረቱን ሲረከብ የጠቅላላው ግዥ የአቅራቢዎች የግንዘብ መቀበያ ደረሰኝ በኮፒ ተደርጎ በማምጣትና ከሰነዱ ጋር ሊያያዝና ሊቀርብ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.3 ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ያለአግባብ የተፈጸሙ ክፍያዎች፤

የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	ብር	3,919,224.90
የፌዴራልና የአርብቶአደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር	"	2,191,329.78
የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	"	18,040.00
የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን	"	198,724.95
የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት	"	1,636,493.00
በጎ አደራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ	"	110,976.50
የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኤጀንሲ	"	68,468.16
ኢንቨስትመንት	"	137,500.00
የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤት	"	61,902.77
ውጭ ጉዳይ	"	337,790.87
ጠ/ድምር	ብር	8,680,450.93

ከዚህ ውስጥ ከፍተኛው የአገልግሎት ክፍያ የተከናወነው በፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር ለሠራተኞች ካፊቴሪያና ለመኪና ማቆሚያ ለማሰራት ከብረታ ብረት ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን የብረታ ብረት ፋብሪኬሽን ኢንዱስትሪ ጋር ውል ተዋውሎ ሥራው

ሳይጀመር ሙሉ ክፍያ የተፈጸመ፣ የፌዴራልና አርብቶአደር ልማት ሚኒስቴር የቀን ውሎ አበል ተከፍሎ እያለ በድጋሚ ለሆቴል የተከፈለና ደመወዝ ይገኙበታል፡፡ በግዥ ሕጉ መሠረት ቅድሚያ ክፍያ 30% መከፈል ሲገባው ሙሉ በሙሉ መከፈሉ መ/ቤቱን የሚያስተዳድረውን ገንዘብ ኃላፊነትን ባላገናዘበ መንገድ ወጪ ማድረግ በመሆኑ መ/ቤቱ ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ እንደሚገባ፤ እንዲሁም ከደንብና መመሪያ ውጭ አላግባብ ተከፍሎ የተገኘውን ደንብና መመሪያ ተከብሮ መሠራት እንዳለበት በሪፖርታችን ገልጸናል፡፡

4.4 <u>የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ የተፈጸመ ግዥ</u>

በበጀት ዓመቱ የተፈጸመው ግዢ በመንግሥት የግዢ ደንብና መመሪያ መሠረት መሆኑን ለማጣራት አዲት ሲደረግ፤

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር	ብር	24,606,609.47
ንግድ ሚኒስቴር	"	135,147.60
የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት	"	541,201.88
የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ	"	443,800.00
ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ	"	10,000.00
የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሪዲቴሽን ጽ/ቤት	"	339,876.00
የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ	"	140,344.05
የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	"	4,165,488.90
የፌዴራልና የአርብቶአደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር	"	1,685,752.98
የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን	"	29,978.44
የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ	"	363,659.53
የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽ/ቤት	"	<u>21,750.00</u>
ጠ/ድምር	ብር	<u>32,483,608.85</u>

የግዥ አዋጅ ደንብና መመሪያ ሳይከተሉ ግዥተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ ከዚህ ከፍተኛው የሀገር መከላከያ ሚኒቴር ሲሆን ከዚህ ውስጥ ግዥዎች በግዥ ህጉ መሰረት ፍትሃዊ የሆነ ውድድር ሊደረግና ለመንግስት ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያስገኝ በሚችል መልኩ መፈፀም እንዳለባቸው አሳስበናል፡፡

ተ.ቁ.	የመ/ቤቱ ስም	ያለጨረታ የተገዛ	በውስን ጨረታ የተገዛ	በቀጥታ ግዥ	ያለዋጋ ማወዳደሪያ የተገዛ	ሌሎች	ድምር
1	መከላከያ ሚኒቴር	23,663,465.29			816,079.93	127,044.25	
2	በብሄራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት				541,201.88		
3	ንግድ ሚኒሰቴር				135,147.6		
4	የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ				443,800.00		
5	ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ				10,000.00		
7	የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት				29,978.44		
8	የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ				363,659.5		
9	የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽ.ቤት				21,750.00		
10	የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሪዲቴሽን ጽ/ቤት	310,306.00		29,570.00		0.00	339,876.00
11	የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ	140,344.05		0.00			140,344.05
12	የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	3,919,224.90		0.00		246,264.00	4,165,488.90
13	የፌዴራልና የአርብቶአደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር	0.00		1,615,752.98		70,000.00	1,685,752.98
ድምር		28,033,340.24		1,645,322.98	2,361,617.35	443,308.25	

4.5 በባለሥልጣን ሳይፈቀድ የተፈጸመ ክፍያ፤

የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ	ብር	1,248,612.21
የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ	"	163,097.78
የፌዴራልና የአርብቶአደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር	"	3,070,723.27
የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን	"	3,052,171.30
የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት	"	12,266,194.89

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር	"	3,121,328.32
የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	"	267,460.00
ጠ/ድምር	ብር	26,334,898.94

ሂሳቡ ለመ/ቤቱ አገልግሎት መዋሉ ሥልጣን ባለው ኃላፊ ፊርማ መረጋገጥ እንደሚገባና ለመረጋገጡ ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.6 **የወጪ ሂሰብን ማዘጋጀት ፤ማረጋገጥና መፍቀድን በተመለከተ**

የወጪ ቫውቸሮቹን የማዘጋጀት፤ የማረጋገጥና እና የመፍቀድ /የማጽደቅ/

ስራ በአንድ ሰዉ የተከናወነ

የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	ብር	87,020.00
የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን	"	143,717.61
ጠ/ድምር	ብር	230,737.61

ክፍያ ከመከናወኑ በፊት ወጪዉን የማዘጋጀት፤ የማረጋገጥና እና የማጽደቅ ስራ በአንድ ሰዉ እንዳይፈጸም ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባና የተጠቀሰውም ሂሳብ ለመ/ቤቱ አገልግሎት መዋሉ ሥልጣን ባለው ኃላፊ ፊርማ መረጋገጥ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.7 **ከበጀት ዓመቱ ውጪ የተፈጸመ ክፍያ**

- **የደረጃዎች ኤጀንሲ** ብር 327,750.00

መ/ቤቶቹ የሚፈጽማቸው ክፍያዎች ለመ/ቤቱ አገልግሎት ስለመሆኑ በሚመለከተው ኃላፊ ሊፀድቅ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.8 **የውል ዋጋ እና የማስረከቢያ ቀን ባለመጠቀሱ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ፡፡**

- **የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢነተርፕራይዞች ኤጀንሲ** 2,131,525.00

በውል ውስጥ የገንዘብ መጠን እና ማስረከቢያ ጊዜ እና ሌሎች በመመሪያው ውስጥ የተጠቀሱት ጉዳዮች ተካተው ውሉ ሊስተካከል እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.9 በብልጫ የተከፈለ፤

የፌዴራልና የአርብቶአደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር	ብር	216,436.00
ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በብልጫ ተከፍሎ	"	64,330. 00
የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ	"	8,785,781.61
ሀገር መከላከያ ሚኒስቴር /መሠረተ ልማት ዘርፍ/	"	2,925,029.88
ጠ/ድምር	ብር	11,991,576.49

ከዚህ ውስጥ ከፍተኛው በኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ከውል በላይ ለውጭ አገር ስልጠና እና ከውል ውጭ ለሲስተም ዝርጋታ ፕሮጀክቶች ማስፈጸሚያ የተከፈለ ሲሆን፤የተጠቀሰው ሂሳብ በስምምነት (በድርደር) ካልሆነም ወደ ሕግ ማቅረብ ተመላሽ መደረግ እንዳለበትና ወደፊቱም ከውል በላይ ክፍያ እንዳይፈጸም ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርታችን ገልጸናል፡፡

4.10 የንብረት ገቢ ደረሰኝ ያልቀረበለት ወጪ ሂሳብ፤

የፌዴራልና የአርብቶአደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር	ብር	63,070.00
ፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት	"	6,433,032.76
የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	"	429,411.54
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በዋናው መ/ቤትና በሚሲዮኖች	"	97,064.38
ጠ/ድምር	ብር	7,022,578.68

የወጪ ሂሳብ ከመመዝገቡ በፊት በበቂ ማስረጃ የተደገፉ መሆኑ ቁጥጥር ሊደረግ እና የተገዙት ዕቃዎች በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ሳያስደርጉ ወጪ ማድረግ መመሪያን ያልተከተለ ከመሆኑም በላይ ለዘረፋ ስለሚያጋልጥ ገቢ ሊሆኑ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.9 <u>የንብረት ገቢ ደረሰኝ ላይ የዕቃው ብዛትና የአንዱ ዋጋ ሳይመዘገብ የተገኘ</u>

- ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በዋናው መ/ቤትና በሚሲዮኖች ብር 152,565.56

4.10 የሂሣብ መደቡን ሣይጠብቅ ተመዝግበው የተገኙ፤

የኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሪዲቴሽን ጽ/ቤት	ብር	363,699.45
የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ	"	15,010.88
የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	"	3,919,224.90
የፌዴራልና የአርብቶአደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር	"	908,998.91
በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት	"	699,260.60
የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ጽ.ቤት	"	22,224.90
የቀድሞው ጥቃቅንና አነስተኛ ኤጀንሲ	"	587,143.90
የፌዴራል ስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን	"	51,112.50
የኢትዮ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን	"	52,891.75
የበጎ አድራጎት ድረጅቶችና ማህበራት	"	32,292.00
ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር	"	1,081,194.34
ጠ/ድምር	ብር	7,733,055.13

የመንግስት የሂሳብ አወቃቀር ስርዓትን ተከትሎ በተገቢው የሂሣብ መደብ ሂሳቦች እንዲመዘገቡ ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ እና ለተጠቀሱት ሂሳቦች ማስተካከያ ሊሠራ እንደሚገባና የሚያዘጋጇቸው የሂሳብ ሪፖርቶች የአጠቃላይ የሂሳብ እንቅስቃሴ በትክክል ሊያሳዩ የሚችሉ መሆን እንዳለባቸው በላክነው ሪፖርት አሳስበናል፡፡

4.11 በተሰብሳቢ መያዝ ሲገባው በወጪ የተመዘገበ ቅድሚያ ክፍያ

የፌዴራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ኤጀንሲ	ብር	636,170.77
የሥነ ምግባርና ጸረ ሙስና ኮምሽን	"	489,711.98
ጠ/ድምር	ብር	1,125,882.75

4.12 ሌሎች ከግንባታዎች ጋር የተያየዙ ችግሮች

የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር

- በመሠረተ ልማት ዘርፍ በ2008 በጀት ዓመት ለኮንስትራክሽን ሥራ ከተፈጸመ ክፍያ ተቀናሽ የተደረገ የመያዣ ሂሳብ ብር 18,214,829.95፤ ከ2008 በጀት ዓመት በፊት ብር 57,192,037.63 በድምሩ ብር 75,406,867.51 በሂሳብ መደብ 5061 ያልተመዘገበ እና ሪፖርት ያልተደረገ እንዲሁም ሂሳቡም በየበጀት ዓመቱ በወጪ ሳይመዘገብ ተገኝቷል፡፡

- ለመከላከያ ኮንስትራክሽን ኢንተርፕራይዝ ለተለያዩ የግንባታ ሥራዎች የመያዣ 2.5% (ሪቴንሽን) በሚል በድምሩ ብር 19,658,266.84 የመያዣ ሂሳብ የምዝገባ ማስረጃ ሳይርኖረው ለተቋራጩ ተመላሽ ተደርጎ ተገኝቷል፡፡
- የሁለት ፕሮጀክቶች ማለት ሽሬ ሆስፒታል ግንባታ እና ሽሬ ሆስፒታል ሳይት ወርክ በውል መሠረት ሳይጠናቀቅ የቀረበት የጉዳት ካሳ ከጠቅላላ ዋጋ1/1000 በድምሩ ብር 1,112,302.24 ሲሆን እንዲሁም በ6 ፕሮጀክቶች ጃንሜዳ ስታፍ ኮሌጅ የውስጥ ለውስጥ መንገድ፤ ደ/ዘይት ሪፈራልሆስፒታልግንባታ፤መቀሌ ኮሚናል ግንባታ ስራ፤ባህርዳር አፓርትመንት መንገድ ስራ፤ጃንሜዳ ሰላም ማስከበር ማእከል ግንባታ፤መቀሌ አፓርትመንት የውስጥ ለውስጥ መንገድ ሥራ በውሉ መሠረት የጉዳት ካሣ የጠቅላላ ውሉ 10% በድምሩ ብር 43,712,905.38 ሲሆን በዐጠቃላይ ከ8 ፕሮጀክቶች በድምሩ ብር 44,825,207.62 ለመሠረተ ልማት ግንባታ ዘርፍ (ለውል ሰጪ) የጉዳት ካሳ ሳይከፈል ተገኝቷል፡፡ ዘርፉ ግንባታቸው በውሉ መሠረት ያልተጠናቀቁትን ከላይ የተጠቀሰውን የጉዳት ካሣ ገቢ ሊያደርግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

<u>የኢትየጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን</u>

በክፍያ ምስክር ወረቀቶች መሠረት ያልተቀነሰ ቅድሚያ ክፍያ	ብር	1,687,872.35
የሪቴንሽን ያልተቀነሰ	"	<u>366,928.77</u>
ጠ/ድምር	ብር	<u>2,054,801.12</u>

ከተቋራጩ ተቀናሽ መደረግ የነበረበት ተመላሽ እንዲደረግና ለግንባታ ሥራ ከሚፈጸሙ ክፍያዎች ተቀናሽ የሚደረጉ ተከፋይ ሂሳቦች የግንባታ ሥራው ሲጠናቀቅ ተመላሽ መደረግ የሚገባው ሂሳብ በአግባቡ ተመላሽ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ሊመዘገብና ሪፖርት ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡እንዲሁም የግንባታ ዘርፉ ተመላሽ የሚደረጉ የመያዣ ሂሳቦችን በትክክል መዝግቦ በመያዝ ወደ ሚመለከተው ክፍል ገቢ በማድረግ እንዲመለስ ጥያቄ ሲቀርብ ተመዝግቦ በተያዘው የመያዣ ሂሳብ መሠረት ተመላሽ ሊደረግ አእንደሚገባ አሳስበናል፡፡

4.13 **<u>በወጪ ሂሳብ ዙሪያ የታዩ የአሠራር ድክመቶች</u>**

<u>በዋናው መ/ቤት</u>

- በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 573250 ብር 8,433.25 በጀት ስለመኖሩ የሚያረጋግጠው ሰራተኛ በቂ በጀት እንደሌለው /ኔጌቲቭ ባላንስ/ ቢገልጽም ክፍያው ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

- በባንክ ወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 573098 ብር 100,000.00 ለመጽህፍ ግዥ የዋለ ሲሆን ክፍያው ሲፈቀድ የበጀት ክፍሉ በጀት እንደተፈቀደ ያረጋገጠው በ6313 የሂሳብ መደብ ሲሆን በወጪ ማስመስከሪያ ላይ የተመዘገበው 6313 ቢሆንም በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ (TR) ላይ በ6213 ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

<u>በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የኒውዮርክ ኤምባሲ</u>

- ለመስተንግዶ ክፍያ ብር 47,925 ለወ/ሮ ወሰንየለሽ ፋንታሁን የተከፈለ ሲሆን ለምግብ ዝግጅት ውል ያልተገባና ምንያህል እንደተጠቀሙ በምን ያህል ብር እያንዳንዱ አገልግሎት እንደተገኘ የማይገልጽ በመሆኑ የክፍያውን ትክክለኛነት ማጣራት አልተቻለም፡፡

- ለዲያስፖራ በዓል ቪዲዮ ቀረጻ ውል ሳይገባ ብር 17,040.00 ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

- በቫውቸር ቁጥር 006109 በድምሩ ብር 10,650.00 የመ/ቤቱ ሰራተኛ የሆኑት ወ/ሮ ፍሬህይወት ሃ/ገብርኤል እረፍት በመውጣታቸው ለቢሮ ጽዳት አገልግሎት ለወ/ሮ ሃገሬ ተግይበለ ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን በሰዓት ምን ያህል እንደተከፈላቸው ውል ባለመገባቱ የክፍያውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

4.16 **<u>ለኦዲት ያልቀረቡ ሰነዶች</u>**

- **የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን** …….. ብር 1,540,212.14፤

ሠነዱ ተጠይቆ ሊቀርብ ባለመቻሉ የወጪውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

<u>የፌዴራል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙሰና ኮሚሽን</u>

ከብር 14,014,461.71 ውስጥ ከ1ዓመት በታች ብር 3,784,775.10፤ ከ1 ዓመት አስከ 5 ዓመት ብር 9,855,688.61፤ ከ5 ዓመት በላይ አስከ 10 ዓመት አስከ 15 ዓመት ብር 374,000.00 ተከሳሾች ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ ለመንግስት ገቢ የሆነ ወይም ለተከሳሾቹ ተመላሽ እንደተደረገ ከፋይናንስም ሆነ ከሚመለከተው የተመዘገበ ሀብት ምርመራ ጥናት እና ኤግዚቢት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ማስረጃ ለማግኘት አልተቻለም፡፡ መረጃ የማይቀርብበት ሂሣብን በተመለከተ ከሚመለከተው የመንግስት አካል ጋር በመነጋገር ማስፈቀድ እንዳለባቸውና ይህ ካልሆነ የወጪ ሂሣቡ ለመ/ቤቱ አገልግሎት መዋሉን ለማረጋገጥ ማስረጃዎቹ ቀርበው አዲት የሚደረጉበት ሁኔታ ሊመቻች እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

4.17 <u>የሂሳብ የማስተካከያውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ</u>

በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን

<u>በአስተዳር ልማት ዘርፉ</u>

- በሰኔ 30 ቀን 2008 በተለያዩ ጆርናል ቫውቸሮች 51 የሂሳብ ማስተካከያ በዴቢትና ክሬዲት በክሬዴት የተሠራለትን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ በማጣቀሻ ቁጥር ሳይደገፍ /ሳይጠቀስ/ እና የመጀመሪያው ምዝገባ መሠረት የሆኑት የሂሳብ ሰነዶች ለማግኘት ባለመቻሉ የሂሳብ የማስተካከያውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ ..... ብር 412,632.982.08

<u>የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት</u>

- ሂሳብ ማስተካከያ ሲደረግ የየትኛው ሂሳብ ለመሆኑ ለማረጋገጥ ያልተቻለ ብር 1,633,486.22
- በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በ2007 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርት በሂሳብ መደብ 5052 /የዋስትና መያዣ/ በሂሳብ ሪፖርት የተያዘውና በባንክ ባለው መካከል በልዩነት የታየው ብር 4,911,997.97 በ2007 ዓም እና ከዚያ በፊት የነበረ ቢሆንም በ2008 በጀት ዓመት ማስረጃ ሳይቀረብ ሂሰብ ተሰተካክሎ ተገኝቷል፡፡

<u>የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን</u>

- ብር 2,525,378.93 በሂሳብ መደብ 4251 ዴቢትና በ4103 በክሬዲት የተመዘገበው በሂሳብ ምዝገባ ማዘጋ በአድቫንስ ተይዞ የነበረውን ክፍያ ለማስተካከል በሚል ቅድሚያ ክፍያው ለምን ሥራ እንደዋለ የሚገልጽ ማስረጃ ሳይቀርብ ባለጥቅሙ ግንዘቡን ስለመቀበሉ የሰጠው የግንዘብ መቀበያ ደረሰኝ ባንክ ወደ ባለጥቅሙ የባንክ ሂሳብ ገቢ እንዲደረግ የጻፈው ደብዳቤ ለኦዲት ተጠይቆ ማስረጃዎቹ ባለመቅረባቸው ሰኔ 30 ቀን 2008 የተደረገውን ማስተካከያ የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- የመጀመሪያ ምዝገ ሠነዶች ባለመቅረባቸው በዴቢት ብር 2,148,396.00 በክሬዲት ብር 2,434,721.77 ማስተካከያ የተሠራለትን ሂሳብ ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

<u>የኒውደልሂ ኤምባሲ</u>

- በኒውደልሂ ኤምባሲ በሂሳብ ማስተካከያ ምዝገባ ቁጥር 509515 ብር 45,160.69 በሂሳብ መደብ 4274 ሌሎች ተሰብሳቢ ሂሳቦች ክሬዲት እንዲሁም 5002 ልዩ ልዩ ተከፋዮች ዴቢት ተደርጎ የተመዘገበ ፤
- በሂሳብ ማስተካከያ ምዝገባ ቁጥር 509518 በሂሳብ መደብ 5002 ልዩ ልዩ ተከፋዮች ዴቢት እንዲሁም 5054 ሌሎች መያዣዎች ክሬዲት ብር 3,580,920.00 የተመዘገበ እና በሂሳብ ማስተካከያ ምዝገባ ቁጥር 509925 በሂሳብ መደብ 4010 ዝውውር ዴቢት እንዲሁም 4102-03 ባንክ እና 4203 ቅድመ ክፍያዎች ክሬዲት ብር 36,950.45 የተመዘገበ፤
- በሂሳብ ምዝገባ ማዘጋ ቁጥር 509549 ፣509548 ፣509547 ፣509546 ፣ 509545፣509544እና509540በድምሩ ብር 5,423,085.21 የተመዘገበ፤

<u>በዋናው መ/ቤት</u>

- በሂሳብ ምዝገባ ማዘጋ ቁጥር 910692 በሂሳብ መደብ 6217 ብር 3,717.40 ፣በሂሳብ መደብ 6231 ብር 246,340.31፣ በሂሳብ መደብ 6233 ብር 7,470.50፣በሂሳብ መደብ 6243 ብር 29,128.70፣በሂሳብ መደብ 6252 ብር 33,315.00 እና በሂሳብ መደብ

6256 ብር 4,048,716.81 በድምሩ ብር 4,368,666.72 ክሬዲት እና በሂሳብ መደብ 6412 ዴቢት ብር 4,368,666.72 የተመዘገበ ፤

- በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 910693 ላይ በሂሳብ መደብ 6412 ብር 2,685,662.04 በዴቢትና በክሬዲት የተመዘገበ እንዲሁም በሂሳብ መደብ 6231 ዴቢት ብር 220,834.49 እና በሂሳብ መደብ 6233 ክሬዲት ብር 220,834.49 የተመዘገበ፤
- በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 910696 ብር 1,692.33 በሂሳብ መደብ 4017 ዴቢት የሂሳብ መደብ 1489 ክሬዲት የተመዘገበውን ሂሳብ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የመጀመሪያው ምዝገባ ባለመቅረቡ (ባለመጠቀሱ) የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አልተቻለም፡፡
- በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 910697 ብር 331,591.06 በሂሳብ መደብ 6256 ዴቢት እና በሂሳብ መደብ 1489 ክሬዲት የተመዘገበ፤
- በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 910698 ብር 1,131.60 በሂሳብ መደብ 6256 ዴቢት በሂሳብ መደብ 6412 ክሬዲት የተመዘገበ፤
- በዋናው መ/ቤት በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 608437፣608249 እና በ 919749 የሂሳብ ምዝገባ ማዘዣዎች በድምሩ በዴቢት ብር 5,803,559.89 እንዲሁም በክሬዲት ብር 5,803,559.89 ተመዝግቦ የተገኘ ሲሆን ፤የሂሳብ ማስተካከያው ተገቢ የሆነ ማጣቀሻ ቁጥርና ለማስተካከያው ምዝገባ መነሻ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

የሂሳብ ማስተካከያ ሲደረግ የየትኛው ሂሳብ ለመሆኑ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ሊገለጽና የወጪ ሂሳቡ ማስተካከያ ትክክለኛነት በመረጃ ሊደገፍ እንደሚገባ ማስተካከያ የተሰራለትም የወጪ ሂሳብ ማስረጃው እንዲቀርብ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

5. <u>የተከፋይ ሂሳብ</u>

<u>ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ፤</u>

የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ብር	ብር	10,268.57
የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	"	94,337.76
የጠቅላይ አቃቤ ህግ	"	<u>41,400.00</u>
ጠ/ድምር	ብር	<u>146,006.33</u>

የተከፋይ ሂሳቡ ለሚመለከተው አካል ክትትል ተደርጎ ክፍያው እንዲፈጸም በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

5.1 **<u>ተከፋይ ሂሳብ ዙሪያ የታዩ የአሠራር ድክመቶች</u>**

<u>በተከፋይ ሂሳብ የተመዘገበና ዝርዝር ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ</u>

የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ	ብር	264,212.10
የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ዝርዝር ማስረጃዎች ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ተከፋይ ሂሳብ	ብር	159,561,189.14
የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ከተከፋይ ሂሳብ ውስጥ የሂሳቡ መነሻ ሰነድ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻ	"	14,472.57
ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ማስረጃ ያልቀረበለት የተከፋይ ሂሳብ	"	13,776,319.04
ጠ/ድምር	ብር	173,616,192.85

ማስረጃ ያላቸውን ተከፋይ ሂሳቦች ማስረጃቸውን በማጣራት ለሚመለከተው አካል መክፈል፣ ማስረጃ የሌላቸውን ሂሳቦች ለይቶ ማውጣት እና ለሚመለከተው አካል በማቅረብ አስፈላጊው እርምጃ እዲወሰድ ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

5.2 **<u>በተከፋይ ሂሳብ ላይ የታዩ የሂሳብ አያያዝ ችግሮች</u>**

- **የታላቁ ህዳሴ ግበባታ ማስተባበሪያ ጸቤት**

ባንክ ገቢ ሆኖ የተገኘ እስኪጣራ በሚል በተከፋይ የተያዘ ብር 456,716.25

- **የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት** ብር 313,148.43በ5061 ተይዞ የሚታየው የተከፋይ ሂሳብ ስራው ያለቀና የተያዘውንም የህንጻ ስራ መያዣ ከግ/ኢ/ት/ሚር ጠይቀው አምጥተው የከፈሉ መሆኑን፣ በ2005 ጀምሮ ምዝገባው መያዝ ከሚገባው በላይ በስህተት የተያዘና ግ/ኢ/ል/ትሚ /ር እንደሚገኝ፣
- **የፌዴራል ጥቃቅንና ኢንተርፕራይዞች ኤጀንሲ**

የተከፋይ ሂሳብ ተቀፅላ ሌጀሮች ያልተከፈተለት ብር 25,432.99

- **በጎ አደራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ**
  - ገቢ እንዲሆን የታዘዘበት ደብዳቤና የባንክ ገቢ ደረሰኝ (አድቫይስ) ያልቀረበለት ተከፋይ ሂሳብ ..... ብር 12,912,189.15

- ከማን ገቢ እንደሆነ ማወቅ ባለመቻሉ የሂሳቡን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ያልተቻለ ብር 1,452,398.18 በወቅቱ ለባለመብቱ ሳይከፈል ተገኝቷል፡፡

- **በኢትዮጵያ ብሔራዊ አክሪዲቴሽን ጽ/ቤት**

የተከፋይ ሂብ መደብ ሰይጠብቅ የተመዘገበ ብር 12,228.72

የፌዴራልና አርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር የተከፋይ ሂሳቡ ብር 10,601.93 በሐምሌ ወር 2007 ዓ.ም እና በነሐሴ ወር 2007 ዓ.ም ቢከፈልም ሂሳቡ አሁንም በተከፋይ ሂሳብ መደብ 5002 ክሬዲት እንዲሁም የባንክ ሂሳብ 4103 በዴቢት ተመዝግቦ የሚታይ መሆኑ ፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የግንባታ የመያዣ ሂሳብ የግንባታው ስራ አልቆ ርክክብ ከተደረገ በኃላ ለአንድ ዓመት ተይዞ የሚቆይ በመሆኑ ለሦስት ዓመት መቆየቱ አግባብ ሆኖ አልተገኘም፡፡የአመዘጋገብ ሰህተት ነው ቢባልም ሰህተቱ ምን ላይ እንደሆነ አልተገለጸም ፡፡ ስለዚህ አስፈላጊው እርምጃ ሊወሰድ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

6. <u>የበጀት አጠቃቀም</u>

6.1 <u>ሥራ ለይ ያልዋለ በጀት</u>

በ2008 በጀት ዓመት የተመደበው በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲገናዘብ ከ10% በላይ ያለውን ብቻ በመውሰድ ያልተሠራበት በጀት ተገኝቷል፡፡

6.2 <u>መደበኛ በጀት</u>

<u>ያልተሠራበት በጀት(መደበኛ)</u>

ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት	ብር	5,800,474.27
ንግድ ሚኒስቴር	"	13,659,359.39
የኢትጵያ ዜና አገልግሎት	"	12,932,537.41
ወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ	"	9,103,289.60
የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት	"	703,195.45
የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት	"	3,159,754.25
የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር	"	6,386,551.85
የፌዴራል ጠቅላይ አቃቤ ሕግ	"	1,062,528.58
የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ	"	142,012,434.17
የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ	"	12,123,606.14
የፌዴራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ	"	4,457,948.80

የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን	"	8,446,280.88
የቀድሞው ጥቃቅንና አነስተኛ ኤጀንሲ	"	16,567,675.12
በጎ አደራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ	"	5,282,994.59
የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት		1,857,918.04
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር	"	170,960,837.22
ጠ/ድምር	ብር	414,517,385.76

ካፒታል በጀት ያልተሠራበት

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት	ብር	28,990,218.00
የንግድ ሚኒስቴር	"	12,095,395.93
የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት	"	18,511,770.58
የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር	"	50,816,881.55
ጠ/ድምር	ብር	110,414,266.06

ከበጀት በላይ የወጣ መደበኛ በጀት

የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም	ብር	1,108,228.49
የንግድ ሚኒስቴር	"	299,790.65
የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ለግንባታ ከተፈቀደው	"	674,217.77
በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት	"	40,108.43
ጠ/ድምር	ብር	2,122,345.34

ያልተሠራበት የካፒታል በጀትን በተመለከተ ከፍተኛው የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ሲሆን ዘመኑ የተጠናቀቀው የግንባታ ፈቃድ ለመውሰድ በተከሰተው የአሠራር ችግር ሲሆን፣ ይህንንም ችግር ለመፍታት የአዲስ አበባ ምክትል ከንቲባ ድረስ በመቅረብ እንዲፈታ የተደረገ ቢሆንም ጊዜ በመፍጀቱ ተግባራዊ ሳይሆን የበጀት ዘመኑ በመጠናቀቁ መሆኑንና ገልጸዋል፡፡እንዲሁም ከበጀት በላይ የወጣውን በተመለከተ ንግድ ሚኒስቴርም ከበጀት በላይ የተቀመጠውን አስተያየትለወደፊቱ በትምህርትነት እንደሚወሰድና አቅጣጫ እንደሚያስቀምጥ ገልጿል፡፡ በመሆኑም አገሪቱ ያላትን ውስን በጀት በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ ማዋል ይችል ዘንድ በበቂ ዕቅድ ላይ የተመሰረተ በጀት አዘጋጅቶ በማስፈቀድ የተፈቀደለትን በጀት በአግባቡ ሥራ ላይ ማዋል እንደሚገባና የበጀት እጥረት ሲያጋጥም የበጀቱ ዝውውር በመጠየቅ ክፍያ

መፈፀም እንዳለበትና ለወደፊቱ በበጀት ጥያቄና አጠቃቀም ላይ ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ አሳስበናል፡፡

7. <u>በፌዴራል መንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት ያልተያዙ ሂሳቦች</u>

<u>የበጎ አድራጎት ድረጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ</u>

- ከተለመደው የባንክ ሂሳብ ሚዛን የተለየ ክሬዲት ሚዛን (Abnormal Balance) ሪፖርት የተደረገና ወደ ሚቀጥለው በጀት ዓመት(ሐምሌ 1 ቀን 2008) የዞረ ብር 213,121.01 ተገኝቷል ፡፡
- በባንክ ሂሳብ መደብ 4103 በተቀጽላ ሌጀሮች ብር 5,066,844.14 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን በክሬዲትና ብር 5,253,324.17 ዴቢት ሆኖ ሳለ በጀኔራል ሌጀር ተጣርቶ ማስተካከያ ሳይደረግ በዴቢት የተመዘገበ፣ ብር186,480.09 ተገኝቷል ፡፡
- በሳጥን ሂሳብ መደብ 4101 በተቀጽላ ሌጀር (002) ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን ብር 12,373.91 ክሬዲትና ብር 89,867.02 ዴቢት ሆኖ ሳለ በጀኔራል ሌጀር ተጣርቶ ማስተካከያ ሳይደረግ በዴቢት የተመዘገበ ብር 77,011.61 ተገኝቷል ፡፡
- በተሰብሳቢ ሂሳብ በተቀጽላ ሌጀር ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን ክሬዲት ሆኖ ሳለ በጀኔራል ሌጀር ተጣርቶ ማስተካከያ ሳይደረግ በዴቢት(opening balance) ብር 26,440.48 ተገኝቷል ፡፡

<u>በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን /በወንጀል መከላከል ዘርፍ/</u>

- በሂሳብ ሚዛን (Trial Balance) 5601/ የተጣራ ሀብት ከመደበኛ ሚዛን ውጭ በዴቢት ሪፖርት የተደረገ ብር 7,986,573.30 ተገኝቷል፡፡

<u>በፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር</u>

- የሳጥንና የተጣራ ሀብት ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በሰኔ 30 /2007 መጨረሻ የሳጥን ከወጪ ቀሪ ብር 85,991.85 ዴቢት ሲሆን የ2008 በጀት ዓመት የሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ መነሻ ሆኖ የተወሰደው ብር 172,363.05 ዴቢት ሆኖ ተገኝቷል፡፡በዚህም ምክንያት መነሻ ሚዛኑ በብር 86,371.20 በልጦ ተገኝቷል፡፡ እንዲሁም የተጣራ ሀብት በ2007 በጀት ዓመት መጨረሻ ብር 1,044,908.27 ክሬዲት ሲሆን በ2008 በጀት ዓመት መጀመሪያ ወይም ሐምሌ 1ቀን 2007 መነሻ

ሆኖ የተመዘገበው ብር 379,876.31 ክሬዲት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የተጣራ ሀብት መነሻ በብር 665,031.96 አንሶ ተገኝቷል፡፡

<u>ኢንቨስትመንት ኮምሽን</u>

የወጪ ሂሳብ አዲት ሲደረግ በዴቢት የተመዘገበው ሂሳብ መጀመሪያ ምዝገባ የተካሄደበት አጣቃሽ ቁጥሮች ወይም ሪፈረንስ ባለመጠቀሱ እና የመጀመሪያ ምዝገባ ባለመቅረቡ 18 ምዝገባዎች በድምሩ በዴቢት ብር 2,148,396.00 በክሬዲት ብር 2,434,721.77 ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

<u>ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር</u>
<u>በዋናው መ/ቤት</u>

- በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣ ቁጥር 608952 የበጀት ማስተካከያ በሚል በቀን 30/08/2008 በሂሳብ መደብ 6412 ዴቢት 50,000,000.00 እንዲሁም 6256 በሂሳብ መደብ ክሬዲት ብር 50,000,000.00 የተመዘገበው ሲሆን በምዝገባው ላይ በጀት ስለመፈቀዱ እንዲሁም የሂሳቡን ምዝገባ በሚያጸድቀው ሰው ያልፈረመ መሆኑ፤በተጨማሪም ምዝገባው ወደ ሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ /TR/ ሲመዘገብ በሂሳብ ምዝገባ ማዘዣው ላይ ያልተመዘገበ 6412 ዴቢት እንዲሁም 6256 ክሬዲት ብር 25,000,000.00 በተጨማሪነት ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- በዋናው መ/ቤት በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች ላይ ያለው የወጪ የሂሳብ መደብ በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ተመሳሳይ ባልሆነ የሂሳብ መደቦች ብር 244,817.70 ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

<u>በኒውዮርክ ኤምባሲ</u>

- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት በሂሳብ መደብ 1101/ስራ ግብር/ የተመለከተው ብር 173,723.71 በተጠቃለለው ሪፖርት በሂሳብ መደብ 1501/የተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ/ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

<u>በብራስልስ ኤምባሲ</u>

- በሂሳብ መደብ 6121 የወጪ ሂሳብ በሚሲዮኑ ሪፖርት የተመለከተው ብር 16,467,453.43 ሲሆን በማጠቃለያው ሪፖርት ላይ 16,467,828.30 በመሆኑም ብር 374.74 ልዩነት በመብለጥ ሪፖርት ተደጎ ተገኝቷል፡፡

- ለአዲት የቀረበው የዋናው መ/ቤት የሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ እና የሂሳብ ሪፖርቱ ተመሳሳይ መሆኑን እንዲሁም በሂሳብ ሪፖርቱ ላይ የቀረቡት የሂሳብ መደቦች በትክክለኛ የሂሳብ ሚዛናቸው/Normal balance/ ሪፖርት መደረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ፤በዋናው መ/ቤት በሂሳብ መደብ 6256 ባልተለመደ የሂሳብ ሚዛን/ Ubnormal balance/ ክሬዲት ብር 833,708.28 ሪፖርት ተደርጎ ተገኝቷል፡፡

ለሂሳቡ ተገቢውን ማጣራት በማድረግ የሂሳብ ማስተካከያ ሊዘጋጅለት እንደሚገባና ለወደፊቱም የሚዞሩ ቋሚ ሂሳቦች ወደ ሚቀጥለው በጀት ዓመት በትክክል ማተላለፋቸው ሊረጋገጥ እንደሚገባና የሂሳብ ማስተካከያ ሲሰራ የመጀመሪያው ምዝገባ ቫውቸር ቁጥሮች ሊጠቀሱ እና ምክንያቱ በጄቪው ላይ ሊገለጽ እንደሚገባ፤ ለተጠቀሱት የሂሳብ ማስተካከያዎች ማስረጃዎቹ ቀርበው በውስጥ ኦዲት ትክክለኛነታቸው እንዲጣራ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

5 <u>የዕቃና ንብረት አስተዳደር</u>

5.1 <u>የቋሚና አላቂ ዕቃ ቆጠራ ከመዝገብ ወጪ ቀሪ(ክእስቶክ ካርድ) ያልተገናዘበ ሆኖ የተገኘ፤</u>

- የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት
- የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን
- የኢትጵያ የደረጃዎ ኤጀንሲ
- የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር

በፌዴራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሠረት ቆጠራ ከመዝገብ ወጪ ቀሪ ጋር ተገናዝቦ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ሊቀርብ መቅረብ እንዳለበት፤ ለቋሚ ዕቃዎች ተከታታይ መለያ ቁጥር ለሁሉም ሊሠጣቸው እንደሚገባ አሰስበናል፡፡

5.2 <u>ለእያንዳንዱ ቋሚ ንብረት የራሱ የሆነ መለያ ቁጥር ያልተሰጠዉ ፤</u>

- የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት
- የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮምሽን
- የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ
- የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር

በፌዴራል መንግሥት የንብረት አያያዝና አጠባበቅ መመሪያ መሠረት ቋሚ ንብረቶች የመለያ ቁጥር ተሰጥቷቸውና ተመዝግበው መያዛቸው ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

<u>ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ ያልተካሄደባቸው መ/ቤቶች</u>

- **የቀድሞው ጥቃቅንና አነስተኛ ኤጀንሲ**

- አላቂ ዕቃዎች በበጀት መዝጊያ ፈሰስ እንዳይደረግ ያልተቆጠረ ..... ብር 639,405.38 ፈሰስ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡

ሐምሌ 1 ቀን ወደ ግምጃ ቤት ቢመለሱም በተደረገው የአላቂ ዕቃዎችና የጽህፈት መሳሪያዎች ቆጠራ ውስጥ አልተካተቱም፡፡ የተሰጠው ምክንያት በጀቱ አነስተኛ በመሆኑ ለቀጣይ በጀት ዓመት ለመጠቀም ታስቦ መደረጉን መገለጹ ግልፅነትን የሚያመላክት ቢሆንም የበጀት እጥረት ሲኖር ተጨማሪ በጀት ማስፈቀድ የተሸለ አማራጭ በመሆኑ በህጉ መሰረት እንዲሰራ አሳስበናል፡፡

5.3 **<u>ሌሎች የንብረት አያያዝ ድክመቶች</u>**

- በንግድ ሚኒስቴር የመ/ቤቱ ሠራተኞች የነበሩ በሞ/22 ወጪ ያደረጉት በድምሩ 11 ላፕቶፖች ተመላሽ ሳያደርጉ መ/ቤቱን የለቀቁ መሆኑ ታውቋል::

- በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ኤጀንሲ መጋዘን ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ እቃዎች ተከማችተው መገኘታቸው፤

ከሚመለከታቸው ግለሰቦች ላፕ ቶፖቹ ተመላሽ እንዲደረጉ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባና የንብረት አጠባበቁም በንብረት አስተዳደር መመሪያ መሠረት መከናውኑ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር ሊደረግ እንደሚገባ አሳስበናል፡፡

<u>የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር</u>

- በናሙና የተመረጡ ዕቃዎችን የስቶክ ካርድ ሚዛንና የቢን ካርድ ሚዛን እንዲሁም በአካል በመቁጠር በምዝገባ የሚታይና በአካል ያለው ሚዛን ልዩነት የሚያሳይ መሆኑ በአዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

- ብዛታቸው አስራ ሁለት(12) የሆኑ የጎማ ቁጥር 700/6 እና 12/20 ሰባት(7) ጎማዎች በ2008 በጀት ዓመት ቆጠራ ላይ፣ ቢን ካርድና እስቶክ ካርድ ላይ ሳይመዘገብ በንብረት ክፍል ውስጥ ተገኝቷል።

- የተለያዩ የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች እና ጎማዎች ከዕርዳታ ድርጅት የተገኙ በሞዴ-19 ሴሪ ቁጥር 38251-38262፣779341 እና 779334 ገቢ የተደረጉ ቢሆንም በቢን ካርድ እና እስቶክ ካርድ ላይ ሳይካተት /ሳይመዘገብ/ ተገኝተዋል።

- ከZIT በዕርዳታ የተገኙ ሌዘር ጄት ፕሪንተር እና ሁለት ሊኖቮን ላፕቶፕ ኮምፒዩተር ዋጋ ሳይሰጣቸው ለተገልጋዮች ተሰጥቶ ተገኝቷል።

<u>የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር</u>

- በመ/ቤቱ ግምጃ ቤት ውስጥ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ 81 የተለያዩ የመኪና ጎማዎች ፣ 23 ዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተሮች፣ 10 ላፕቶፕ ኮምፒዩተሮች ፣ 7 ፕሪንተሮች፣ 9 ዩ.ፒ.ኤስ፣ 21 ማይክሮፎኖች፣ 2 ፎቶ ኮፒ ማሽኖች፣ 110 የቶነሮች ቀፎ፣ ስፒከሮች፣ 14 የመኪና ባትሪዎች ፣ 1 ሞተር ሳይክል፣ 2 የውሃ ማጣሪያ ፣ 100 የተለያዩ መጋረጃዎች፣ 208 የተለያዩ ወንበሮች፣ 106 የተለያዩ ጠረጴዛዎች፣ 3 የተለያዩ የላፕቶፕ ቦርሳዎች፣ 2ት በካሬ የሚለኩ የወለል ምንጣፎች፣ 27 ስቴፕለር መምቻዎች፣ 22 ፓንቸሮች፣ 16 የሽንት ቤት መቀመጫዎች እና 8 የእጅ መታጠቢያዎች፣ 10 የወረቀት ትሪ፣ 49 የተለያዩ ባለገመድ እና ገመድ አልባ ስልኮች እና 1 በኤሌክትሪክ የሚሰራ ካልኩሌተር ማሽኖች ተገኝተዋል።

<u>የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ</u>

- ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ በርካታ ቁጥር ያላቸው የተለያዩ ኮምፒውተሮች፣ ላፕቶፕ ፣ሲስተም-ዩኒቶች ፣ ዩፒኤስ ፣ ኪ-ቦርድ ፣ ስካነር፣ ፕሪንተር ፣ የፋክስ ማሽን ፣ የፎቶኮፒ ማሽን መጽሀፍቶች እና ጋዜጦች፣ቶነሮች፣የፎቶ ኮፒ ቀለሞች፣ካርቦኖች፣የዴስክ ቶፕ ኮምፒዩተር ጨረር መከላከያዎች፣26 የሚሆኑ የሴት ጫማዎች ፣የእንጨት ውጤቶች አስፈላጊው እርምጃ ሳይወሰድባቸው ተገኝተዋል።

- በ2008 በጀት ዓመት በብር 59,925.80 የተገዛ የተሽከርካሪዎች ፍተሻ አገልግሎት መስጫ መሳሪያ/Portable digital under Vehicle Inspection/ ምንም አይነት አገልግሎት ሳይሰጥ ወደ ንብረት ክፍል ተመላሽ ሆኖ ተገኝቷል።

- ከ3 ዓመት በላይ ምንም ዓይነት እንቅስቃሴ የሌላቸው የተለያዩ የተሸከርካሪዎች መለዋወጫ ዕቃዎች /Spare Parts/ መጋዘን ውስጥ ተገኝተዋል።

<u>የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም</u>

- በተቋሙ ግምጃ ቤት ውስጥ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ የኮምፒውተር እቃዎች ፣ ፕሪንተር ፣ ፋክሶች ፣ የፎቶ ኮፒ እቃዎች ፣ አሮጌ የመኪና መለዋወጫ እቃዎች እና ተመላሽ የመኪና ጎማዎች ተከማችተው ተገኝተዋል።

<u>የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት</u>

- የቋሚ፣ የአላቂ እንዲሁም ያገለገሉ ንብረቶች ለቁጥጥር አመቺ ባልሆነ መልኩ በአንድ ግምጃ ቤት ተቀምጠው መገኘታቸው።
- ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ የጎማ የውስጥ ላስቲክ፣ የመኪና መለዋወጫዎች፣ የመኪና ባትሪዎች ተገኝተዋል።
- ከተሸከርካሪዎች ጋር የመጡ የተለያዩ የተሸከርካሪዎች መለዋወጫ ዕቃዎች /Spare Parts/ በመጋዘን ውስጥ ያለአገልግሎት መገኘታቸው ታውቋል።
- ነዳጅን ለመቆጣጠር እያንዳንዱ ተሽከርካሪ በሊትር ስንት ኪ.ሜ እንደሚጓዝ በተጨባጭ በመረጃ የተደገፈ ማስረጃ አለመገኘቱ፤

<u>በኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት</u>

- የተለያዩ ላፕቶፕ ኮምፒውተሮች፤ዴል ኮምፒውተሮች፤ጎማዎች፤ፕሪንተሮች በቆርቆሮ መጋዘን ውስጥ ለንብረቱ ደህንነት አመቺ ባልሆነና ለዐሐይና ዝናብ በተጋለጠበት ሁኔታ ተከማችተው ተገኝተዋል።

<u>የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ</u>

- ያለአገልግሎት በርካታ ቁጥር ያላቸው እቃዎች በንብረት ክፍል ተገኝተዋል። አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በመመሪያው መሰረት መወገድ እንደሚኖርባቸውና ንብረቶቹ ለበለጠ ብክነትና ጥፋት ከመዳረጋቸው በፊት ለንብረቶቹ ቋሚ የሆነ መጋዘን ሊዘጋጅላቸው እንደሚገባ በሪፖርታችን ገልጸናል።

<u>በነዳጅና የነዳጅ ኩፖን አጠቃቀም ላይ የሚታዩ ችግሮች</u>

የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር

- የመ/ቤቱ የነዳጅ አጠቃቀም ኦዲት ሲደረግ 2 የሚኒስቴር መ/ቤቱ ተሽከርካሪ መኪኖች በተመሳሳይ ቀን በአቢሲኒያ ካርድ እና በኩፖን ነዳጅ የቀዱ መሆኑ ታውቋል።

- የነዳጅ ኩፖን ለተጠቃሚዎች ሲሰጥ በሥራ ክፍሉ ኃላፊ ሳይረጋገጥ ወጪ የሚደረግ መሆኑ ታውቋል፡፡

የንብረት አስተዳደሩ መንግሥት ባወጣው የንብረት አያያዝና አጠባበቅ መመሪያ መሠረት እንዲስተካከል እና እንዲፈፀም የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ተገቢ የሆነ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ እንደሚኖርበት በሪፖርት ገልጸናል፡፡

5.4 <u>የተሸከርካሪዎች አያያዝና አጠቃቀም</u>

<u>የሰሌዳ ቁጥር የሌላቸው ተሸከርካሪዎች</u>

- የኢትዮጳያ ሰብዓዊ መብት ኮምሽን ተሸከርካሪዎች 3 ተሸከርካሪዎች የሰሌዳ ቁጥር 4-22342፣ 4-09989 እና 4-22553 የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር ወይም ሊቤሬ የሌላቸው ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- በወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ የባለቤትነት መታወቂያ ሰሌዳያልቀረበላቸ ቁጥር 4-16190 እና ሰሌዳ ቁጥር 4-22464 ተሸከርካሪዎች ተገኝተዋል፡፡
- በንግድ ሚኒስቴር ለ5 ተሸከርካሪዎች የሰሌዳ ቁጥር V.8 4-22428፤ ኒሳን ፒካፕ 4-22538፤ ፕራዶ 4-22429፤ ሚትስ ቡሺ ፒካፕ 4-20409፤ ቶዮታ ፒካፕ 4-22430 የባለቤትነት መታወቂያ (ሊብሬ) ያልቀረበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- የፌዴራልና የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴርየባለቤትነት መታወቂያ (ሊብሬ) የሌላቸው 21 ተሸከርካሪዎች ተገኝተዋል፡፡

የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩትኮድ 4- 21041 የመስክ /ቶዮታ ፒካፕ/ 4-21286እና 4-21085 አውቶሞቢል /ሊፋን 530/የተሸከርካሪዎች ሊብሬ ያልቀረበለት ተገኝቷል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው ተሸከርካሪዎችን (ሊብሬ) በተመለከተ ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር የባለቤትነት መታወቂያው እንዲወጣለት ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>በብልሽት ምክንያቶች የቆሙና በወቅቱ ያልተጠገኑ ተሸከርካሪዎች</u>

- የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር 27 የሚሆኑ የአስተዳደሩ ተሸከርካሪዎች በከባድ ብልሽት ምክንያት በአስተዳደሩ ጋራዥ ግቢ ውስጥ ያለአገልግሎት ለረጅም ግዜ ቆመው ተገኝተዋል፡፡

- የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የተቋሙ 2 ተሽከርካሪ መኪናዎች በከባድ ብልሽት ምክንያት ከሰባት ወር እሰከ ዘጠኝ ወር ድረስ ያለአገልግሎት ቆመው ተገኝተዋል፡፡

በብልሽት የቆሙት ተሽከርካሪዎች በመመሪያው መሰረት እንዲወገዱ ወይም ለሚመለከው አካል ርክክብ እንዲደረግ አስፈላጊው ክትትል ሊደረግ እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

<u>የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን</u>

- በሞተሩ አካል ላይ የሰፈረው ቁጥርና በሊብሬው ላይ ተመዝግቦ የተገኘው የተለያየ መሆኑ፤

<u>በበጎ አደራጎት ድርጅቶችና ማህበራት</u>

- በሞተሩ አካል ላይ የሰፈረው ቁጥርና በሊብሬው ላይ ተመዝግቦ የተገኘው የሞተር ቁጥር እንዲሁም በሻንሲው ላይ ያለው ቁጥርና በሊብሬው ላይ ከሰፈረው ጋር ተለያይቶ የተገኘ መሆኑ፤

በሊብሬውና በተሽከርካሪው ሞተሩና ሻንሲው ላይ ያለው ቁጥር ከሚመለከተው አካል ጋር በመነጋገር ተገቢውን ማስተካከያ ሊደረግበት እንደሚገባ በሪፖርታችን አሳስበናል፡፡

8. **<u>የውስጥ ቁጥጥርን በተመለከተ</u>**

<u>ልዩ ልዩ</u>

- የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎ የወጪ ሰነዶች ላይ በጀት መኖሩ እየተረጋገጠ በሚመለከተው ኃላፊ የማይፈረምበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- የንግድ ሚኒስቴር መ/ቤቱ አራት የእለት ገንዘብ ሰበሳቢዎች ዋስትና ያልያሲያዙ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- የክፍያ ሰነዶች (ቫውቸሮች)ላይ በጀት ስለመኖሩ በሚመለከተው ኃላፊ ሳይፈረም ተገኝቷል፡፡

<u>በኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ</u>

- የፋይናንስና አቅርቦት አገልግሎት ኃላፊ ከተፈቀላቸው ገደብ ውጪ ወጪዎች ተፈቅዶ ተገኝቷል፡፡
- የጥገና አገልግሎት ግዥ ሲከናወን ጥገናው በተጠየቀው መሠረት ስለመከናወኑ የማይረጋገጥ ኖኖ ተገኝቷል፡፡

- የክፍያ ሰነዶች (ቫውቸሮች) ላይ በጀት ስለመኖሩ በሚመለከተው ሠራተኛ ወይም ኃላፊ ሳይፈረም ተገኝቷል፡፡

<u>የኢትዮጲያ ዜና አገልግሎት</u>

- የወጪ ሰነዶች ላይ በጀት መኖሩ እየተረጋገጠ በሚመለከተው ኃላፊ የማይፈረምበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- በኢሚግሬሽንና ዜግነት ጉዳይ ዋና መምሪያ አዲስ አበባ ቦሌ ቅርንጫፍ በውጭ ምንዛሪ ገቢ ሲሰበሰብ በገቢ ደረሰኝ መሂ/2 ሲሆን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚገዛበትንና የሚሸጥበት የዕለቱ የውጭ ምንዛሪ ተመን ሳይቀመጥ በቪዛ(Stiker) ላይ በእጅ የተፃፈ የገንዘቡን ልክ የሚገልፅ (USD, EUR, CAD, ACD, GBP...) በማለት በጀርባው ላይ በእስክሪብቶ በእጅ ጽሑፍ ገቢ ከሚሆን በስተቀር የዕለቱ የምንዛሬ ተመን በባንክ ደረሰኙ ላይ በባንኩ የማይገለጽ በመሆኑ የገቢውን ትክክለኛነት ማረጋጥ አልተቻለም፡፡

<u>ጠቅላይ ፍ/ቤት</u>

- ብር 6,617,605.19 በጀት ስለመኖሩ በሚመለከተው ሠራተኛ ኃላፊ ሳይረጋገጥ ተገኝቷል፡፡

<u>ባለፉት ዓመታት አዲት ሪፖርት መሠረት እርምጃ ያልተወሰደ</u>

<u>የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት</u>

- ጽ/ቤቱ ከፓተንት ጥበቃና ቴክኖሎጂ ሽግግር እና ከንግድ ምልክት ኢንዱስትራያዊ ንድፍ ጥበቃና ልማት የአገልግሎት ክፍያ የሰበሰበዉ በሕግ በተተመነዉ የአሜሪካን ገንዘብ /USD/ሲሆን፣ የአገልግሎቱን ገንዘብ ሲሰበስብ ግን በብር በመሆኑ የቀኑ የባንክ የምንዛሪ ዋጋ መረጃ ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ</u>

- ኤጀንሲዉ ዉል ገብቶ ለሚሰራቸዉ ፕሮጀክቶች ስራዉን ካጠናቀቀ በኋላ ወይም በተወሰነ ጊዜ ለእያንዳንዱ ፕሮጀክት የገቢና የወጪ ማጠቃለያ የማያዘጋጅና ለሚመለከተዉ አካል ሪፖርት የማያቀርብ መሆኑ ታዉቋል፡፡

<u>የፌዴራል ጠቅላይ ዐቃቤ ህግ</u>

- በመ/ቤቱ ከሚገኙት ተሽከርካሪዎች ውስጥ የሰሌዳ ቁጥር 4- 0908 እና 4-0913 ሞተር ሳይክሎች ኢንሹይስና የመጡበት መ/ቤት ወይም ወደ መ/ቤቱ የመጡበት ሁኔታ በአጠቃላይ የግል ማዕደራቸው ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡

<u>የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ</u>

- በ2007 በጀት ዓመት የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ ሞዴል/64 ቆጠራ በማድረግ በቆጠራ ዕለት ከሚገኘው ከመዝገብ ከወጪ ቀሪ ጋር ተመዛዝኖ በወቅቱ ለሚመለከተው ኃላፊ ሪፖርት እንዲደረግ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል፡፡ በ2007 በጀት ዓመት እርምጃ እንዲወሰዱ በመ/ቤታችን አስተያየት ተሰጥቶአል፡፡ ይሁን እንጂ እስከ አሁን የተወሰደ እርምጃ አለመኖሩ መታወቁ፣

ኢንፎሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ ለሥራ አመራር ሪፖርት በላከው ምላሽኤጀንሲው ውል ገብቶ የሚሰራቸው ፕሮጀክቶች በአብዛኛው በተያዘላቸው በጀት የሚጠናቀቁ መሆኑን ከተያዘው በጀት ከተረፈ ከዚህ በፊት ለገ/አ/ ል/ሚ/ር አስፈቅደው እንደተጠቀሙ ለወደፊትም ሕጉ በሚፈቅደው መሰረት በጠቅላይ ሚኒስቴር በማስፈቀድ የሚጠቀሙ መሆኑ ገልጿል፡፡ በመሆኑም፡የኤጀንሲው በበጀት የሚተዳደር የመንግሥት መ/ቤት በመሆኑ አገልግሎት ሰጥቶ ሚያገኘውን ገቢ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል በትክክል ፈሰስ መሆኑንና ሂሳቡን ለመቆጣጠር እንዲቻል የወጪ ሂሳብ ማጠቃለያ በተወሰነ ጊዜ ወይም ፕሮጀክቱ መጨረሻ ፈሰስ ማድረግ እንዳለበት አሳስበናል፡፡

<u>የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን</u>

- የአስተዳደርና ልማት ዘርፍ ማስረጃ ተጠይቆ ሊቀርብ ያልቻለ ብር 574,305.88 መኖሩን በመጥቀስ ማስረጃዎቹ እንዲቀርቡ በተሰጠው አስተያየት መሠረት ለአዲት አለመቅረቡ፤-፡

<u>በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት</u>

- ለፍ/ቤቶቹ ዳኞችና ሠራተኞች የተከፈለው የቤት አበል በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ከ29 ዳኞች እና ሰራተኞች ብር 327,810.00 ፤ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ከ80 ዳኞች እና ሰራተኞች ብር 875,551.50 እና ከፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከ122 ዳኞች እና ሰራተኞች ብር 1,129,441.20 በድምሩ ብር 2,332,802.70

ያልተሰበሰበ የገቢ ግብር መኖሩ ተገልጸ እንዲሰበሰብ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡

- በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 2007 በጀት ዓመት የሂሳብ ሪፖርት በሂሳብ መደብ 5052 /የዋስትና መያዣ/ የተመዘገበ ብር 80,421,210.67፤-በባንክ ሂሳብ ቁጥር 1000002275418 /የማስያዣ ገንዘብ ማጠራቀሚያ/ የሚታይ የገንዘብ መጠን ብር 70,524,601.63 ፤ በሲፒኦ ገቢ የሆነውን ባንክ ያልሰበሰበው ብር 3,295,440.98 ፤-የዋስትና ገንዘብ ተመላሽ ብር 1,689,170.09 በድምሩ ብር 75,509,212.70 ፤-በመያዣ ሂሳብ መደብ /5052/ በሂሳብ ሪፖርት የተያዘና በባንክ ባለው በልዩነት የሚታየው ብር 4,911,997.97 በ2007 ዓም እና ከዚያ በፊት የነበረ ቢሆንም በ2008 በጀት ዓመት ማስረጃ ሳይቀረብ የሂሰብ ሪፖርቱ ተሰተካክሎ ተገኝቷል፡፡
- በ2005 ኦዲት በተሰጠው አስተያየት ማስረጃ ያልቀረበለት ብር 31,755.00 ወጪው ለፍርድ ቤቱ አገልግሎት መዋሉንና ትክክለኛነቱን ለማረጋገጥ ማስረጃ እነዲቀርብ አስተያየት በ2007 በጀት ዓመት ኦዲት የተሰጠበት ቢሆንም ማስረጃ ሳይቀርብ ተገኝቷል፡፡
- ለፕሬዝዳንቱ ጽ/ቤት አገልግሎት የሚውል ወንበር፤ ለሰበር ዳኞች ጠረጴዛ ግዥ የንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞዴል 19) ደጋፊ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 88,250.00 በወጪ የተመዝገበው በሞ/19 ሳይቆረጥለት ተገኝቷል፡፡
- በ4274 ያልተሰበሰበ ሂሳብ ብር 21,125.67 ማስረጃ ሳይቀርብ ከሪፖርት ወጥቶ ተገኝቷል፡፡
- የፎቶ ኮፒ ማሽን መለዋወጫ ዕቃዎች ባለመመዝገባቸው እንዲመዘገቡ አስተያየት ቢሰጥም ሳይመዘገቡ ተገኝቷል ፡፡
- በፍ/ቤቱ ስር የሚገኙ አራት ተሽከርካሪ መኪናዎች የባለቤትነት ደብተር (ሊብሬ) የሌላቸው መሆኑ ታውቋል፡፡
- በ2007 በጀት ዓመት ኦዲት በተሰብሳቢ ከተያዘው ብር1,547,895.37 ውስጥ በሂሳብ መደብ 4210 ብር 1,526,309.64 ውስጥ በተደረገው ማጣራት ብር 1,212,912.36 በስህተት 4009 መመዝገብ የነበረበት መሆኑን በማረጋገጣቸው ለገ/ኢ/ል/ሚ እንዲጻፍላቸው ለጠቅላይ ፍ/ቤት በደብዳቤ መጠየቃቸውን ፤ ብር 313,309.60 ባንክ ገቢ በመደረጉ ከብሄራዊ ባንክ ባር ተነጋግረው ምላሽ እንደሚሰጡ ፤ የገለጹ ቢሆንም ውሰኔ ሳያገኝ ከሪፖርት ተሰርዞ መገኘቱ ፡፡

- ሐምሌ 1/2006 በጥሬ ገንዘብ የተቆጠረው ሂሳብ ብር 763,330.23 ሲሆን በሂሳብ ሪፖርት በብር 40,000.00 አንሶ ብር 723,330.23 ሪፖርት መደረጉን በመግለጽ ምክንያቱ ተጣርቶ ርምጃ እነዲወሰድ አስተያየት የተሰጠ ቢሆንም ምንም እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል፡፡

<u>በቀድሞው ፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጅንሲ</u>

- የሰልጣኞች ማስረጃነት ለኦዲት ባለመቅረቡ ለውሎ አበል እና ለትራንስፖርት ወጪ የሆነ በድምሩ ብር 1,779,105.92 አገናዝቦ ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ አለመቻሉ፡፡
- ኤጀንሲው ብር 286,120.80 በባንክ ሂሳብ ለባለጥቅሙ ያስተላለፈ ቢሆንም ሂሳቡ በባንክ ወጪ ሳይመዘገብ የተገኘ መሆኑ፤
- እቃውን በሙሉ ማቅረብ ባለመቻሉ ብር 178,825.50 ተመላሽ ተደርጎ የገቢ ደረሰኝ የተቆረጠለት ቢሆንም በባንክ ሌጀር ላይ ሳይመዘገብ የተገኘ መሆኑ፤

<u>የታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤት</u>

- ለህዳሴ ግድብ ግንባታ ገቢ ማስገኛ SMS /8100 A/ የአጭር መልእክት ጨዋታ የሚሰበሰበውን ገንዘብ በኢትዮጲያ ንግድ ባንክ በተከፈተው ሂሳብ ቁጥር 10000009848960 ብር 417,153.57 ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡
- ለህዳሴ ግድብ ግንባታ ገቢ ማስገኛ SMS /8100 A/ የአጭር መልእክት ጨዋታ የተሰበሰበው ገንዘብ በኢትዮቴሌኮምና በፋና ብሮድ ካስት በልዩነት የሚታይ ብር -1,453,461.00 እልባት ሳይደረግለት ተገኝቷል፡፡
- በ2007 በጀት ዓመት ኦዲት የማሻሻያ ሀሳብ የተሰጠ ቢሆንም ገንዘቡ ሙሉ ለሙሉ ገቢ ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡ በኢትዮቴሌኮምና በፋና ብሮድ ካስት በልዩነት የሚታይ ብር 1,453,461.00 እልባት በአሁኑ ኦዲትም ተግባራዊ ሳይደረግ ተገኝቷል፡

<u>የበጎ አድራጎት ድርጅት ማህበራት ኤጀንሲ</u>

- ብር 18,628,379.47 በ2008 በጀት ዓመት ውስጥም እልባት ሳያገኝና ሳይወራረድ ተገኝቷል፡፡

<u>ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር</u>

<u>የወጪ ሂሳብ</u>

- የኢፌዲሪ ኤምባሲ ፕሪቶሪያ ለስልክ ራውተር አገልግሎት የተከፈለው ወጪ ብር 2,508.62 ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ሂሳብ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

- የኢፌዲሪ ኤምባሲ ፕሪቶሪያ ለአምባሳደር መኖሪያ ቤት የኤሌክትሪክ ጥገና አገልግሎት የተከፈለ ብር 5,720.00 ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪ የጥገና ጥያቄ ቀርቦ በሚመለከተው ኃላፊ የተፈቀደበት ማስረጃ አልቀረበም፤
- በኢፌዲሪ ኤምባሲ ፕሪቶሪያ ለተከበረው የብሄር ብሄረሰቦች ቀን 250 ሰው የምግብ አቅርቦት ለሰጡበት በሚል ለትሪስት ሪስቶራንት የተከፈለው ብር 35,200.00 አጥጋቢ ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ሂሳብ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪ አገልግሎቱን ለማግኘት በሚመለከተው ሰራተኛ ወይም ሀላፊ ሁኔታው ተገልጾ የጸደቀ ማስታወሻ አልቀረበም አገልግሎት የሰጠው ድርጅት /ሆቴል/ እንዴት እንደተመረጠ ማስረጃ የለም፡፡
- በኢፌዲሪ ኤምባሲ ብራስልስ የሚሲዮኑ መሪ መኖሪያ ቤት ሳተላይት ዲሽ ለማሰተካከለ የጉልበት ክፍያና የማቴሪያል ግዥ ተፈፀመዋል ነገር ግን የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ብር 19,460.00 በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- በኢፌዲሪ ኤምባሲ ብራስልስ ለሚሲዮኑ የሰነድ ማስቀመጫ ብረት ቁም ሳጥን ግዥ መፈፀሙ ይታወቃል ነገር ግን ክፍያ ሲፈፀም ብር 4,172.00 ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ ሂሳብ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- በኢፌዲሪ ኤምባሲ ቤጂንግ ከዋናው መ/ቤት ለኤምባሲው ከበጀት ላይ በሚቀነስ የሂሳብ ሰነድ ግዢ በብር 2115.54 ተገዝቶ ለሚሲዮኑ የተላከ እና በተሰብሳቢ ተይዞ የነበረ ሲሆን ሚሲዮኑ በወጪና በበጀት ምዝገባ ያከናወነ ሲሆን ዋናው መ/ቤት በተሰብሳቢ ከመዘገበ በኋላ ከተሰብሳቢነት ሲያወጣ ምዝገባ የተከናወነበት ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ፡፡
- በኢፌዲሪ ኤምባሲ ዋሽንግተን በቫውቸር ቁጥር 069181 ለውሃ አገለግሎት ክፍያ ብር 16,169.24 ምዘገባ የተከናወነው ሲሆን ነገር ግን ማሰረጃ የቀረበው በብር 5,265.80 በመሆኑ ልዩነት ብር 10,903.44 ያለማሰረጃ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
- የወጪ ሂሳቦች ትክክለኛነት ኦዲት ሲደረግ የወንድ ሙሉ ልብስ ሱፍ ነክ ታክስን ጨምሮ ብር 1800*118 =ብር 212400 እና የሴት ሙሉ ልብስ ሱፍ ነክ ታክስን ጨምሮ የአንዱ ዋጋ ብር 1600*76 =ብር 121600 በድምሩ ብር 334000 ያለጨረታ በቀጥታ ዘካሪያስ ታደሰ ልብስ ስፌት /ቲሞኒየር / ግዢ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም የግዢ መጠየቂያ አልቀረበም ፣ ክፍያው ቫትን ጨምሮ በድምሩ ብር

334000 መሆን ሲገባው ብር 348398.55 በመከፈሉ ብር 14,398.55 በብልጫ ክፍያ ተፈጽሞ ተገኝቷል፡፡

- በናሙና ተመርጠው ለአዲት ስራ ከተጠየቀው ሰነዶች ውስጥ በሮም ኢምባሲ የጥቅምት ወር 2007 ሂሳብ ሰነድ ቁጥር 16929 ለአዲት ስራ አልቀረበም፡፡

ባለፉት አዲቶች በተሰጠው አስተያየት መሠረት እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ አሳስበናል፡፡

የ2008/2009 በጀት ዓመት ሂሳብ

አዲት የተደረጉ መ/ቤቶች ዝርዝር

ተራ ቁጥር	አዲት የተደረገው መ/ቤት	መ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ለኦዲት የቀረበበት ቀን	በአዲት የተሸፈነ የተስተካከለ በጀት		
			መደበኛ	ካፒታል	ድምር
1	የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር	24/4/09	9,500,000,000.00		9,500,000,000.00
2	ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት	3/5/2009	847,197,015.03	122,119,510.00	969,316,525.03
3	የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኤጀንሲ	10/1/09	23,020,030.00		23,020,030.00
4	ንግድ ሚኒስቴር	2/3/09	81,486,204.00	2,488,963.07	83,975,167.07
5	የወሳኝ ኩነት ምዝገባ ኤጀንሲ	23/01/09	64,444,905.14		64,444,905.14
6	የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮምሽን	2/02/09	48,087,100.00		48,087,100.00
7	የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት	26/3/09	41,726,560.00	29,486,100.00	71,212,660.00
8	የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር	መስከረም 30/2009	1,768,465,225.29	136,828,870.00	1,905,294,095.29
9	የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር	ጥቅምት 24/2009	442,545,890.00	800,000,000.00	1,242,545,890.00
10	የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት ኤጀንሲ	ኅዳር 8/2009	422,020,010.00	400,000,000.00	822,020,010.00
11	የሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ኤጀንሲ	ነሐሴ 19/2008	90,240,620.00	0.00	90,240,620.00

12	የፌዴራል አርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር	መስከረም 30/2009	46,211,614.00	0.00	46,211,614.00
13	የጠቅላይ ዐቃቤ ህግ	ነሐሴ 5/2009	96,951,830.00	131,239,000.00	228,190,830.00
14	የመንግስት የልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር	ጳጉሜ 2/2008	28,443,010.00	0.00	28,443,010.00
15	የፌዴራል የከተማ መሬትና መሬት ነክ ንብረት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ	ነሐሴ 24/2008	15,994,590.00	0.00	15,994,590.00
16	የኢትዮጵያ አክሪዲቴሽን ጽ/ቤት	ጥቅምት 14/2009	10,059,610.00	0.00	10,059,610.00
17	የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም	ጥቅምት 21/2009	40,195,870.00	0.00	40,195,870.00
18	የኢትዮጵያ አዕምሯዊ ንብረት ጽ/ቤት	ሐምሌ 21/2008	14,689,640.00	0.00	14,689,640.00
19	የኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓቶች ልማት ኢንስቲቲዩት	ጥቅምት 9/2009	30,533,970.00	0.00	30,533,970.00
20	የፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን	13/03/2009	1,971,541,364.72	99,269,240.72	2,070,810,605.72
21	የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት	24/05/2009	44,046,231.00	-	44,046,231.00
22	የፌደራል የሥነ ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን	23/02/2009	58,856,436.72	--	58,856,436.72

23	የፌደራል ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ኤጀንሲ	05/01/2009	60,724,360.00	-	60,724,360.00
24	የፌደራል በጎ አደራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ	02/03/2009	35,308,130.00	-	35,308,130.00
25	የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አማሪ ጉባኤ ጽ/ቤት	ነሀሴ 20/ 2009	9,721,300.00	-	9,721,300.00
26	የኢትየጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን	ታህሳስ 13 /2009	32,662,136.00	8,983,789.77	41,645,925.77
27	የታላቁ ሕዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ አስተባባሪ ብሔራዊ ምክር ቤት ጽ/ቤት	ታህሳስ 21/2009	9,721,300.00	-	9,721,300.00
28	ጠቅላይ ፍ/ቤት 9.1 የፌዴራል ከ/ ፍ/ቤት 9.2 የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት	23/02/2009	211,103,065.24	31,976,700.00	243,079,765.24
29	የንግድ ውድድርና የሸማቾች ጥበቃ ባለስልጣን	11/12/2007	27,394,260.00	-	27,394,260.00